

ሥርዓት



የመሳፍንት መርቁ

ደስማዕከ ወርቁ



ዳር ተጋዳላይ

ልቦለድ

፪፻፲፯ ዓ.ም
አዲስ አበባ

All Rights Reserved to Yismake worku.
ያለፈቃዶ ወዘሠረቆ በስልጣነ ኪ.ን ወጥበብ ውገዘ ለይኩን። © ይስማዕከ ወርቁ-ሄኖክ

DERTOGADA

A Novel by Yismake Worku

የመጀመሪያ ዕትም ሚያዝያ ሄኖክ ዓ.ም

ሁለተኛ ዕትም ሰኔ ሄኖክ ዓ.ም

ሦስተኛ ዕትም ሐምሌ ሄኖክ ዓ.ም

አራተኛ ዕትም ነሐሴ ሄኖክ ዓ.ም

አምስተኛ ዕትም ጥቅምት ሄኖኽ ዓ.ም

ስድስተኛ ዕትም ህዳር ሄኖኽ ዓ.ም

ሰባተኛ ዕትም ታህሣስ ሄኖኽ ዓ.ም

ስምንተኛ ዕትም ታህሣስ ሄኖኽ ዓ.ም

ዘጠነኛ ዕትም ሚያዝያ ሄኖኽ ዓ.ም

ዋና አከፋፋይ ፡- አይናለም መጻፍት ቤት

አድራሻ፡-ክብሔራዊ ቴአትር ቤት ጀርባ

☎ 011 550 58 44/011 550 58 45

የሽፋንና የውስጥ ዲዛይን፡-ይስማዕከ ወርቁ
ኮምፒዩተር ትየባ፡- መላኩ ኃ/ሚካኤል

E-mail: ramatohara@gmail.com

መግለጫ

በዚህ በተራቀቀና በህዋ ቅርምት (space exploration) ዘመን በአማርኛ ተዕፎ ለመነበብ በቂ ብቃት ያለው ፊር ቀጻጅ ልቦለድ እነሆላችሁ።

ሀ) ቁንጭው እስከነ ታሪክ አወቃቀሩ እንከን አይወጣለትም፣ ከዚያም ጋር ከማንም ሌላ ፀሐፊ የሚለየው ይስማዕከ የራሱ «እንትን» አለው (style)::

ለ)ብዙ ሳይንስ ፊክሽን አንብቤም በሲኒማ አይቼም አውቃለሁ፣ ይሄ የምታነቡት ፀሐፊውንና እንዲዕፍ ቀስቀሰው ያስቀጠሉትን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ስናነበው፣ ከማንኛቸውም ይስተካከላል።

ሐ) ትረካውን ከምዕራፍ ወደ ምዕራፍ ስንከተለው ልብ አንጠልጥል ነው፣ አንድ ነጠላ ታሪክ ይዞ ችክ አይልብንም፣ የብዙ ውስብስብ ታሪኮች ጭማቂ ሆኖ አንድ ገፅ ስንገለብጥ አዲስ ነገር እናገኛለን፣ በድርጊት የተሞላ ነው (ፍጥነቱ)።

መ) ሳይንስ፣ ስለላ፣ ሮማንቲክ፣ ታሪካዊ ልቦለድም ጭምር ነው....ከዚህ አንፃር፣ ትስስርሻቸው እስካሁን ያልታዩንን የተለያዩ ክስተቶች አቀራኝቶ አቅርቦልናል። ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን ያስተሳሰረ ተሻጋሪ ልቦለድ ነው።

ሠ) ይሄ የመጨረሻው ኑጥብማ....ከሚያውጠነጥናቸው ሀሳቦች አንዱም ብቻ እቻት። ለቁሳዊ ሀብትና ለአዕምሮአዊ ሀብት ስለሚደረግ ትንቅንቅ። ደሞ ሀገር ወዳድነት... ማን ለራሱ ሲል ምን ተከፍሎት ማንን ወይስ ምንን ይሸጣል? ማንስ ለሀገሩ «እስከመጨረሻዋ ደም ጠብታ» ይፋለማል? ወዘተ... የተቀረውን አንባቢ ከወዘተ ጋር ቢወያይበት ይመረጣል።

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

ምስጋና

የሁሉም ነገር አባቴ ዓለሙ ቢያድጌ ጌታሁን ...ያንተን ታላቅ አባትነት መመስከሪያ ቃል ካላቸው ገና ከዘመናዊው ትምህርት ጋር በደንብ ሳልተዋወቅ ጀምሮ የገዛህልኝ መጻሕፍት ይመስክሩልኝ። እነሆ የልጅ ቡራኬ።

ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር (አቦይ) የዚህ መጽሐፍ ረቂቅ በኔ ቢረቀቅም ባንተ ደምቋል። በየትኛውም ዘመን ውስጥ ከየትኛውም ትውልድ ጋር መኖር የመቻልህ ምስጢር ይህ አንዱ ፈርጁ ነው። አዲስ ዘመን፣ አዲስ ትውልድና አዲስ እሳቤ አንተን አያስፈሩም። ያለፈኝን ዘመን ባንተ ኖሬያለሁና እነሆ ስብሐት ለአብ!

ጋሼ የሻው ተሰማ (ደራሲና ሀያሲ) በሌለ ቅንፍ ውስጥ የኮተቤው ወጌሻ....በጥበብ እጅ ሲታሽ የማይጠገን የስነፅሁፍ ውልቃት፣ የማይጠግግ ወለምታ እንደሌለ አይቻለሁና እነሆ ብዕሬን ለምስጋና አነሳለሁ። ደራሲና ገጣሚ በፅውቀቱ ስዩም፣ ዶ/ር ዮፍታሄ ስዩም፣ ደራሲና ገጣሚ እንዳለጌታ ከበደ፣ ደራሲና ገጣሚ ዘላለም ጌታቸው፣ ዶ/ር ከፈለኝ፣ አሜሪካዊው ደራሲ ዳንኤል ጆንስን ሁላችሁንም ከጥበብ ማዕድ አይለይብኝ።

ገጣሚ በለው ዝየሁ በቅንፍ ውስጥ የኔ ገማልያል... እነሆ የተዋረስነው ጋኔን ስሙ ሥነ ጽሁፍ ነውና በጠበልም በመገረፍም በስቅላትም አይለቅም። ብንሞትም አብሮን አይሞትም። እንግዳ ወርቅ ሀብቴ በቅንፍ ውስጥ የኔ ቤተ መጻህፍት... ያነበብከውን ሁሉ ለማዳመጥ መቃብራችን እስኪቆፈር ያቆየናል። ታድለን!

ፀጋ አንዳርጌ....ለዛ ሁሉ ልፋት ምስጋና በቂ ነው ወይ? ከሆነ እነሆ እስከ መጪረሻው ጊዜ የሚያቆይ ምርቃት ጀባ ብያለሁ። መላኩ ኃ/ሚካኤል፣ እመቤት እንዳለ፣ ብሩክ ተስፋዬ፣ ቃልኪዳን ጌታቸው፣ ትዕግስት ሰለሞን፣ ፋሲካ ጌታቸው፣ ናርዶስ ፀጋዬ፣ መ/ር አላዛር ጌታቸው፣ አቶ ደረጀ ዋለ፣ ጌትነት ዳናና ድልዓለም አዩ መርቄያለሁና...አሜን በሉ።

መግለጫ

ከላይኛው ደራሲ ዘንድ የተላከ ታላቅ መልእክ በመንፈቀ ሌሊት በሬን በርግዶ ገብቶ ከእንቅልፌ አባነነኝ። ራሴን ጎዝጉዤ በራሴ ላይ ተኝቼ ነበር። ከወርቃማ ክንፉ ላይ አንድ ላባ ነቅሱ ብዕር ቀርፆ ሰጠኝ። በታላቅ ሰሌዳ ላይም «ማሒር ሻላል ሐሽ ባዝ» ብለህ ጻፍ አለኝ። ከነገረኝ ቃል አንዳች ባጎድል ከሀይወት መፅሐፍ ላይ እንደሚሰርዘኝም አስጠነቀቀኝ።

በሰጠኝ ብዕር ከላቤ ወዝ ቀለም እየጠቀስኩ ስከትብ የነገረኝን ቃል የሚናገሩ ገፀ ባህርያት (አምሳለ ሰብዓት) ከዘመኔ ጨለፍኩ። የፈጠርኳቸው ጥቂት አምሳለ ሰብዓት በዘመኔ ከማውቃቸውና የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ጋር በሥጋ በነፍስ ተዛመዱ። በ'ርግጥ እግዜር የፈጠራቸው ገፀ ባህርያት የተሠሩት ከሞቃ ሲሆን እኔ መፍጠርን ከፈጠረኝ ተምሬ የፈጠርኳቸው አምሳለ

ሰብዓት ግን የተጨለፉት ከሰው ላይ ነው። ከ'ኔና ከመሰሎቼ ግዘፍ ነስተው፣ ከሰው ሥጋ ሥጋን፣ ከሰው ምኞት ምኞትን፣ ከሰው ህልም ህልምን..... ወስደው ፍፁም ሰው ፍፁም እነሱን ሆነው ተፈጠሩ።

ሆኖም እኔ በፈጠርኳቸውና የላይኛው ደራሲ በፈጠራቸው አምሳለ ሰብዓት መካከል አንድ ልዩነት አለ። የላይኛው ደራሲ የፈጠራቸውን ገፀ ባህርያት ይገድላቸዋል። እኔ ግን አልገድልም፤ አላድንምም። ከሞቱም 'ራሳቸው ይሞታሉ እንጂ፤ ከዳኑም ራሳቸው ይድናሉ እንጂ። እኔም ከእነሱ ያልተሻልኩ ነኝና። ለመሞታቸውም ለመትረፋቸውም ተጠያቂ አለመሆኔን ስነግራቸው ፈነጠዙ። እንዲህም አልኳቸው። «እኔ ብዕር እንጂ ሰይፍ የለኝም። አልጠብቃችሁም። ለጉስቁልናችሁ....ለመደወያችሁ ሁሉ ማንም ተጠያቂ አይሆንም። ራሳችሁን አድኑ። ሁላችንም የራሳችን በሽተኞችና የራሳችን ዶክተሮች ነን። እኔ ራሴ የራሴ ታማሚ የራሴ አስታማሚ የራሴ ዶክተር የሆንኩ የላይኛው ደራሲ የፈጠረኝ አስተኔ ገፀ ባህርይ ነኝ። ሁላችንም የላይኛው ደራሲ የፈጠረን ገፀ ባህርያት ነን። አዎ፤ በእርግጥ ...እኔ ፈጣሪያችሁ ነኝ። ስለናንተ ሐጢአት ግን በመስቀል ላይ አልቸነከርም።..... ስለእናንተም ከእናንተ በላይ አላውቅም።...እኔ ከላይኛው ደራሲ የምለይበት አንድ ሌላ ነገር... ብትሞቱብኝ በእኔ ዘንድ የማወርሳችሁ ገሀነምና መንግሥተ ሰማያት አለመኖሩ ነው። ገሀነሙም መንግሥተ ሰማያቱም ያለው ከእናንተ ውስጥ ነው። በምድር ላይ ኃጥዕና ጻድቅ እኩይና ሰናይ ገፀ ባህርይ የለም። ከእናንተ በተቃራኒ የቆመ ኃይል እኩይ ሲላችሁ እናንተ ደግሞ መልሳችሁ እኩይ ትሉታላችሁ። ሁሉም ለራሱ ሰናይ ገፀ ባህሪ ነውና። ሰናይ እኩ ስል አላዳላም። ደረስኪችሁ እንጂ አልደርስባችሁም» ብዬ ስነግራቸው ሁላቸውም ተደሰቱ። የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህሪያትም ጋር ተቀላቀሉ። ከአምሳለ ሰቦቹና

የላይኛው ደራሲ ከፈጠራቸው ገፀ ባህርያት ከህይወታቸው እየጨለፍኩ ይህን መጽሀፍ ጽፌ ስጨርስ ከተኛሁበት የቀሰቀሰኝ መልአክ ቀሪውን የህይወታቸውን ምስጢር እንዳልናገርባቸው ፍም በመሰለ ነበልባላዊ ሰይፉ ከንፈሮቼን አተማቸው። አስቀጥሎም ‹‹ዕቀብ ቃለ ተነብዮቱ ለዝንቱ መጽሐፍ እስመ በፅሐ ዘመኑ›› ብሎ በጥንታዊዉ የግዕዝ ቋንቋ ተናግሮኝ ከንፉን እያማታ ወደ መጣበት ተመለሰ። ‹‹ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል ጠብቀው›› ማለቱ ነው። የላይኛው ደራሲ ‹‹የፈጠርኩትን ላባ የት አባህ ጥለኸው መጣህ!?›› ብሎ እንዳይቆጣው የፈራ ይመስል ከወርቃማ ከንፉ ላይ ነቅሎ የሰጠኝን ላባም መልሶ ከንፉ ላይ ተክሎት ነበር የበረረው።

ይስማዕከ አዶኒ

ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ

ለሳይንቲስት ኢንጂነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ

ቅድመ ታሪክ

አሜሪካ፡- በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1989 ዓ.ም። በአሜሪካ አየር ኃይል ቢሮ ውስጥ የተቀመጠውን ጥቁር መዝገብ የከፍሉ ዋና አዛዥ ሲያገላብጡት ከቆዩ በኋላ ሰፊው ጠረጴዛ ላይ በብስጭት ወረወሩት። የአሜሪካ አየር ኃይል አባል የነበረው ጌራ ከተልዕኮው እስከዛሬ አልተመለሰም። ባለከንፉ ፓይለት በመባል ይወደስ የነበረው ጌራ ከተሰወረ ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካ አየር ኃይል አባላትና የጦር መኮንኖች ስሙን ሳያነሱት ውለው አያውቁም። ይህ ኢትዮ - አሜሪካዊ ወጣት ፓይለት ከመሰወሩ በፊት በአሜሪካ የህዋ ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ስሙ ከገነነው እውቁ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ጋር በተደጋጋሚ አብሮ ታይቷል ይባላል። ከመሰወሩ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት ኢንጂነር ሻጊዝን መርምሮት ነበር። እሱ ግን ስለጉዳዩ እንደማያውቅ ተናግሮ ድርቅ አለ። በአነስተኛዋ የጦር አውሮፕላን ወደ አፍሪካ እንደበረረ የሚጠረጠረው ጌራ ግን እስከ አሁን ሊገኝ አልቻለም።

ይህ ከሆነ ከሁለት አመት በኋላ እውቁ የሚሳዬል ባለሙያ ኢትዮ-አሜሪካዊዉ ሳይንቲስት ኮሎኔል ፍስሐ ስለረጅም ርቀት ቲወንጫፊ ሚሳዬል የጀመረውን ቀመር በጅምሩ ጠረጴዛው ላይ ትቶ ተሰወረ። "ኢትዮጵያ" በሚል ቅጽል ስም የሚጠሩት የሥራ ባልደረቦቹ ደርቀው ቀሩ። ስለ ኢትዮጵያ በስሜታዊነት ሲናገር ይቀልዱበት ነበር። አንዳንዴም «....አንተ ሰው!..... ወይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነህ! ወይም መንግሥቱ ኃይለማርያምን ውጠኸዋል!...." እያሉ ሲቀልዱበት ስቆ ዝም ይል ነበር። ይህ ኢትዮ-አሜሪካዊ የሚሳዬል ሳይንቲስት ከሚንቅላቱ በቀር ይዞት የጠፋው ቤሳ ቤስቲን የለም አተባለ ቢወራም ሀብቱን ግን ከመሰወሩ በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንዳሸሸ የአሜሪካ የመረጃ ሰዎች ደርሰውበታል ይባላል። ይህ ሰው በጠፋ በሶስተኛው ቀን የናሳው ሻጊዝ እጅጉ ከአንተ ጋር አብሮ ታይቷል በሚል ተመርምሮ ነበር። እሱ ግን "...አሁንስ ከኢትዮጵያ ያመጣችሁት ዶሮ ካለ እሱም ቢጠፋባችሁ እኔ ዘንድ እንዳትመጡ ሰጋሁ" ሲል ተሳለቀ።

እስራኤል፡- መጋቢት 1990 ዓ.ም። በቱልአቪቭ አቅራቢያ ምድር ውስጥ በተገነባው ሀቡዕ የምርምር ጣቢያ ውስጥ በሥራ ከተጠመዱት ሳይንቲስቶች መሀል ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች ሳይታሰብ የውሃ ሽታ ሆኑ። እነዚህን ሳይንቲስቶች ለመያዝ የእስራኤል ኮማንዶዎች ያልመነቀሩት ጉዋዳ ጎድጉዋዳ የለም ነበር። ነገር ግን እስከ አሁን ሊያገኙዋቸው አልቻሉም።

ሰሜን ኮሪያ፡- መስከረም 1991 ዓ.ም። የኮሪያ ዘማች ከነበሩትና ኮሪያ ከቀሩት ኢትዮጵያዊ አባቱ እና ከአንዲት ኮሪያዊት የተወለደው ኢትዮ-ኮሪያዊው ሳይንቲስት በሮቦቶች ከሚታገዘው ሀቡዕ

የኒውክለር ማብላያ ጣቢያ መሰወሩ በምስጢር እንዲያዝ ተደረገ። ፍለጋው እስከ አሁን ቀጥሎ ነበር.... የበላው ጅብ ሊጮህ አልቻለም እንጂ።

ህንድ፡- ነሐሴ 1992 ዓ.ም። አውቁ የኮምፒዩተር ሳይንስ ሊቅ ግርማቸው ዘለቀ የሂማሊያ ተራራዎችን ለመጎብኘት እንደሄደ እስከዛሬ አልተመለሰም። በሄሊኮፕተር የታገዘው የህንድ ፖሊሶች ሀሰሳ መና ሆኖ ቀረ። በሂማሊያ ተራራዎች መሃል ቀልጦ የቀረው ግርማቸው ለህንድ አስፈላጊ ሰው ነበር ይባላል።

ሩሲያ፡- ጥቅምት1994 ዓ.ም። ወደ ቀድሞዋ ሶቭዬት ህብረት ለትምህርት ከተላኩት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ከመሔዱ በፊት "አሞራው" በሚል ቅጽል ስም ይጠራ ነበር። ባለብሩህ አዕምሮ ከመሆኑም በላይ ራሺያ ያየችበት ልዩ ተሰጥኦው በቀላሉ እንዳትሰቀው ግድ አላት። ነገር ግን የራዳር ቴክኖሎጂ ሳይንቲስቱ "አሞራው" ከሩሲያ እጅ ከወጣ ከአራት አመት በኋላ አንድ የሩሲያ ጋዜጣ የመጥፋቱን ዜና አተመው።

ቻይና፡- ታህሣሥ 1995 ዓ.ም ኢንጂነር ሻጊዝ በምስጢር ወደቻይና በሮ ነበር። ባልታወቀ ምክንያት ድርድሩ አልሰመረም። እውቁ የናሳው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ለቻይና የሀዋ ምርምር ተቅዋም እንዲሠራ ቻይና ያቀረበችለትን ረብጣ ገንዘብ ረግጦ ሆንግ ኮንግን በለቀቀ ማግስት በቻይና የሀዋ ምርምር ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ የነበረው ኢንጂነር ኢዩኤል አጥናፉ መሰወሩ ከቻይና የደህንነት ሰዎች ጆሮ ደረሰ።..... አንዲት ድምጽ አልባ አውሮፕላን ከቤቱ ጀርባ በድቅድቅ ጨለማ ስታርፍ ኢዩኤል ያለውን ሀብት በሙሉ በባንክ ወደ ኢትዮጵያ ለአንድ መነኩሴ አዛውሮ መመለሱ ነበር። መነኩሴው ይውለው ገንዘቡ እንደደረሳቸው ከነገሩት ከአርባ ደቂቃ በኋላ ከቤቱ ጀርባ ባረፈችው ድምጽ አልባ አውሮፕላን ቻይናን ለቆ ወጣ። ሆንግ ኮንግ በቻይና ኮማንዶዎች ብትታመስም ኢትዮጵያዊዉ የቻይና የሀዋ ሳይንቲስቶች ባልደረባ የትም ሊገኝ አልቻለም። የቻይና የደህንነት ሰዎች የኢዩኤልን መሰወር ከኢንጂነር ሻጊዝ ወደ ቻይና መጥቶ መመለስ ጋር ቢያያዙትም እስካሁን ግን የተረጋገጠ ነገር አልተገኘም።

ኩባ፡- ጥር 1995 ዓ.ም። ፊደል ካስትሮ አንድ መርዶ ተነገራቸው። መርዶውን እንደሰሙ ወዲያው ላልተወሰነ ጊዜ ከኩባ ማንም እንዳይወጣ አዘዙ። የኩባ ኬላዎች በሙሉ ተዘጉ። የኩባ አውሮፕላኖችም ላልተወሰነ ጊዜ ከበረራ ታገዱ። በዛች ቀን ያልተፈተሸ ነገር ቢኖር የፊደል ካስትሮ ኪስ ብቻ ነውም ተብሎ ተቀልዷል። ተራ የህዝብ ማመላሻዎችና የቤት መኪናዎች በየመንገዱ በሰልፍ ተፈተሹ። ከሰማይ ጠቅስ ፎቆች እስከ ደሳሳ ጎጆዎች ተመነቀሩ። ኩባ ደብቃ ያኖረችው ኢትዮጵያዊ የሜድካል ላቦራቶሪ ሳይንቲስት ግን የትም ሊገኝ አልቻለም። የትም!

አመክንዮ

ኢትዮጵያ፡- 1961 ዓመተ ምህረት። ጀምበር በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ልትጠልቅ አቅላልታ ነበር። አንድ የተበሳጨ መነኩሴ በብስጭት የምንኩስና ቆቡን ከራሱ ላይ መነጨቀው። ከራሱ ላይ የመነጨቀውን የምንኩስና ቀይ አስኬማ ከአዲስ አበባ እምብርት አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ግርጌ ወርውሮ ሲጥሰው በዛ የሚያልፉ መንገደኞች በትንግርት እየተመለከቱት ነበር።

ከአራዳው ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በታች ወደሚገኙት መሸታ ቤቶች እየተገላመጠ ወርዶ አማርጦ ገባ። ሲጠጣ ቢያመሽም ሽንቱ ከመምጣቱ በቀር ፍንክች አላለም ነበር። አሁንም ብቻውን እየተበሳጨ ከማንም ጋር ታንቲራ ሳይገጥም የጠጣበትን ሸኽሬታ ከፍሎ ሲወጣ በምናምንቴ የተወጠቀችውን ከረጢቱን በጉያው አጥብቆ ይዞ ነበር። "ወይኔ ዲዲሞስ!" ይላል በየደቂቃው። "ከአሁን ወዲህ ማንም አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ! ማንም! .....እኔ አያሌው በላይሁን ነኝ። አያሌው በላይሁን! .....አያሌው በላይሁን ነኝ!.... አያሌው ጀግናው! .....ጀግናው አያሌው እንደ ዝንጆሮ ጭሮ ያደገው! ....ማንም ከአሁን በኋላ አባ ዲዲሞስ ብሎ እንዳይጠራኝ!..ማንሽም አባ እንዳትይኝ! አባሽን ፈልጊ!....." አያለ ወደ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ተመለሰ። ሽንቱ ፊኛውን እንደ ንፋፊት እንደ ወጠረው ነበር።

ከአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን በረጅሙ እያንፎለፎለ "አንተ ድንጋይ! አሸናብሃለሁ!..." ሲል ባካባቢው የሚያልፉት ሰዎች መንገዳቸውን ገተው መሳቅ ዠመሩ።

"አንተ ድንጋይ! ..... አሸናብሃለሁ። ....ይኸው እኔ ግን አለሁ ..... እንቁልልጭ! አንተ ግን ድንጋይ ሆነሃል .....ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ተው ብየህ አልነበረም?..... አንተ ድንጋይ!..... ክፉ ቀንን ማለፊያ ጥበብ አልነገርኩህም ነበር?.... አንተ ድንጋይ!..... ሆን ብለህ ነው!..... ሆን ብለህ !....ክፉ ቀንን በጥበብ ከማለፍ በላይ ጥበብ የለም! ...አንት ድንጋይ! ....ይህንም ነግሬህ ነበር። ይህቺ ደም መላስ የለመደች ሀገር የምትለወጥ መስሎሃል! .....ቴዎድሮስን በላች! አልተለወጠችም።.....ገብርዬን በላች! አልተለወጠችም። ....ምኒልክ ደከመላት!..አልተለወጠችም።..... ፋሲልን...በላች! አልተለወጠችም። አሉላን በላች! አልተለወጠችም! አንተንም በላች አልተለወጠችም!..... የበላይን ደም ጠጣች! ይኸው አልጠረቃችም። ስንት ጀግኖች ሞቱላት.....አልተለወጠችም። አልነገርኩህም?! .....ጴጥሮስ! አልነገርኩህም?! ....አትሰማም። ወይኔ ዲዲሞስ! ወይኔ አያሌው በላይህ! ...አንተ ብትኖር ኖሮ ይሄኔ አቡነ ዲዲሞስ እባል ነበር። የዚህች ሀገር ዕጣፋንታ በእጃችን ይወድቅ ነበር። እንለውጣት ነበር። ግን ሞትክ! ተው እያልኩህ ሞትክ! ጽጽስና ሳትሾመኝ ሞትክ።

ይኸው እኒህኛው ጳጳስ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አበምኔት እንኳ ያድርጉኝ ብላቸው ከለከሉኝ። አባ ዝገንበሩን ሾሙት። አንተ ብትኖር ግን ወንበዴዎች ጳጳስ ሆነው አይሾሙም ነበር። እኔና አንተ የምናውቀው የዚህች ሀገር ውድ ምስጢር በወንበዴዎች እጅ አይገባም ነበር። አፈር ብላ!....አፈርስ በልተሃል አንተ ድንጋይ! እሸናብሃለሁ። አንተ ድንጋይ ስልጣን ፈልጌ እንዳይመስልህ! አበምኔትነት ስልጣን አለመሆኑን ታውቃለህ። ጵጵስናም ተራ ነገር መሆኑን አታጣውም። ለምን ስልጣኑን ላትሰጠኝ ሞትክ? ለግሌ እንዳልሆነ እያወክ! ለዚህች ሀገር ታላቅ ሥራ ልንሠራ ተስማምተን ከዳኸኝ አንተ ድንጋይ። እሸናብሃለሁ። ...አንት ድንጋይ! ጓደኞችህ ተመችታቸው በማርቼዲስ ሲንሸራሸሩ ይኸው አንተ ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ድንጋይ! እሸናብሃለሁ..." እያለ ሲለፈልፍ አንድ ወጣት "ድንጋይ አይደለም! ....ድንጋይ አይደለም!..." እያለ በደም ፍላት ዘሎ ግብግብ ገጠመው።

"ድንጋይ ነው!" ሐውልቱ ላይ ሲሸናበት የነበረውን ዕቃውን አራግፎ ወደ ሱሪው ሰገሰገው። "ድንጋይ ነው!"

"ድንጋይ አይደለም!" እድሜው በግምት ወደ ሃያ አምስት አመት የሚጠጋው ወጣት ተንተባተባ። ወጣቱን ያውቀዋል። በዛ ወቅት አለ የሚባል ገጣሚ መሆኑን ያውቃል። ይህን ወጣት እዛው አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ስብሰባ ሲገባ በጊዜ አይቶት ነበር። ወጣቱ ከስብሰባው ሲወጣ ጠብቆ ሐውልቱ ላይ ሽንቱን መሸናቱ..... ከወጣቱ ጋር ግብግብ መግጠሙ ሁሉ ወጥመዱን በትክክል ማጥመዱንና ወጥመዱም በጊዜ መያዙን እያረጋገጠለት ነበር። አንገት ላንገት ተናነቁ። በቡጢ ሊቃመሱ ያ ወጣት በትክክል ፀጋዬ ገብረ መድህን መሆኑን እያጤነ ነበር። ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች ገላገሏቸው።

ወጣቱ ገጣሚ እየተበሳጨ ቤቱ ሲገባ በቅርብ ርቀት ሰውዬው እየተከተለው ነበር። ፀጋዬ ሌሊቱን አልተኛም፣ ሲፅፍ አደረ። ‹‹ጴጥሮስ ያችን ሰዓት›› የተሰኘውን ቴአትር በዛች ሌሊት ፅፎ እንዳገባደደ በደረቀው ሌሊት የሚፅፍበት ቤት በር ተንኳኳ። በሩ እደተከፈተ ሰውዬ ዘው ብሎ ወደ ውስጥ ገባ። ያኔ ፀጋዬ እየተንቀጠቀጠ ነበር። በሁዋላ ግን ሊያጠቃው እንዳልመጣ ተገነዘበ።

እንዲያውም በዛች ሌሊት የፃፈውን የቴአትር ረቂቅ አንስቶ ወረቀቶቹን እያተረማመሰ "እኮራብሃለሁ። ገና....ገና....ዓለም ሳታስበው ታከብርሃለች። ብዕርህን ወደ ሰገባው እዳትመልሰው። አየህ...ይህች አገር ህዝብ አላት ሰው ግን የላትም። እንጨት ብቻውን

ቆሞ ቤት አይሠራም። ማገር ያስፈልገዋል። ህዝብም ብቻውን ሀገር አይሆንም። አንድነቱን የሚጠብቁ ካስማዎች ያስፈልጉታል። የዚህች ሀገር አንድነት ካስማዎች እነ ቴዎድሮስ እነ ምኒልክ..... አሁን የሉም። አንተ እነሱን መሆን አትችልም። ራዕያቸውን ብትጋራ ግን እነሱን ትተካቸዋለህ። እነሱን ለመተካት ደግሞ ግዴታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆን አይጠበቅብህም።" ንግግሩን አቁሞ ቅንድቡን ዓይኑ አፋፍ ድረስ አንጠለጠለና የፀጋዬን ዓይነ ውሀ ጠልቆ መረመረው። ፀጋዬ ምንም መልስ አልሰጠውም። ባግራሞት እየተመለከተ ዝም አለው።

በምናምንቴ ነገሮች ከተወጠቀችው ከረጢቱ ውስጥ አንድ ሰፊ ብራና መዝረጠና ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው። የነተበው ጥንታዊው የብራና ገፅ ላይ በቀይ ቀለም የተቀረፀ ካርታ ይታያል። ፅሑፉ በጥንታዊው የግዕዝ ቋንቋ የተፃፈ ነው። የወለል ምንጣፍ በሚያክለው የብራና ገፅ ላይ በጥቁር ቀለም ይሄ የሚል ቁጥር ከላይኛው ህዳግ ላይ ይታያል።

"ማልልኝ!" አለው የፀጋዬን። "በኢትዮጵያ አምላክ ማልልኝ!" አለው እንደገና መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀይ ቀለም የኢትዮጵያ ካርታ የሳለበትን ገፅ እያወጣ። ፀጋዬ እጁን እመፅሐፉ ላይ ሳያቅማማ አሳረፈ።

"ቴአትሩን ፅፈህ ጨርሰኸዋል?" አለው ስልቻው ውስጥ እጁን ልኮ ሌላ ነገር እየበረበረ።

"በግርድፉ....." ፀጋዬ መለሰለት።

"ጥሩ። ይህ ደግሞ ለቴአትሩ መዝጊያ የገጠምከው ግጥም ነው!" ፀጋዬ ለጴጥሮስ ያችን ሰዓት ቴአትር መዝጊያ የፃፈውንና «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» የሚል ርዕስ የሰጠውን ግጥም አንስቶ ሰውየው ድምፁን ዘለግ አርጎ አነበበው። ድምፁ እንደ ሐምሌ ነጎድጓድ አስገምጋሚ ነው። "ገጣሚ በሆነ!" አለ ፀጋዬ በልቡ አነባበቡ ደስ ብሎት።

ግጥሙን አንብቦ እንደጨረሰ "ግሩም ነው! .....ይበል ነው! ....ጨብጠኝ!" አለ ሰውየው። በደስታ ሰክሮ ሊጨብጠው መዳፉ አንበሳ የሚሰባብር ያህል ጠነከረበት። ጨብጦ ሲነቀንቀው እጁን ለመንቀል የሚታገል መሰለው። አጥብቆ ቢመታው ኖሮ በአንድ ስንዘራ ህቅ እንደ ሚያደርገው አመነ ፀጋዬ። ከዛም ሁሉም ነገር ገባው።

"ነገር ፈልጎኝ ነው ለካ።"

"መልካም! አሁን ነገሩ ተለወጠ ማለት ነው።አንድ ሥራ ላዝህ ነበር። ከባድ ሥራ። አሁን ግን በቀላሉ ሥራውን እንዲህ

እናድርገው....." አለ በሌላ አጭር ብራና ላይ የሰፈረ የቃላት ዝርዝር እያወጣ፡፡ "እነዚህን ቃላት እዚህ ግጥም ውስጥ በታትነህ ትደባልቃቸዋለህ፡፡ አዘበራርቀህ ዝራቸው፡፡ ለግጥምህ ጉልበት ከመሆናቸውም በላይ እኔም ከእንግዴህ ይህን ከረጢት ይዤ አልንከራተትም፡፡....በላ!...ዝራቸው!"

ፀጋዬ የተሰጡትን ቃላት በዓፈው ግጥም ውስጥ በታትኖ ዘራቸው፡፡ ቃላቱ 48 ናቸው፡፡ ሰውየው ባድናቆት እንደገና ጨበጠውና 48ቱ ቃላት የተዘሩበትን ግጥም እየተመለከተ በሌላ ወረቀት ላይ አንድ ጉጥ ያለው መስቀል መሳል ጀመረ፡፡ በመስቀሉ ላይም አያሌ ቁጥሮችንና አንዳንድ ከባባድ ቃላትን ከቀረፀበት በኋላ ሰቆቃወ ኤጥሮስ የሚለውን ምስጢራዊ ግጥም በብራና ወረቀት ላይ ከከረጢቱ ባወጣው መቃ-ብዕርና ቀለም ቀዳው፡፡ በብራናው ላይ ገልብጦ ከጨረሰ በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደገና አነበበው፡፡ በሚያስገመግም ድምፅ፡፡ .....

ሰቆቃወ ኤጥሮስ

አየ+ ምነው እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ምነው ቀኝሽን ረሳሻት?
እስከመቼ ድረስ እንዲህ+ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን+ ሰቀቀንዋን+ጣሯን ይበቃል ሳትያት?
አላንቺ እኮ ማንም የላት....
አውሮጳ እንደሁ ትናጋዋን+ በፋሽስታዊ ነቀርሳ
ታርሳ+ተምሳ+ በስብሳ
ሂትለራዊ አባጭ ጫንቃዋን+ እንደ ኮረብታ ተጭኗት
ቀና ብላ እውነት እንዳታይ+ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት
ነፍሷን ድጦ ያስበረክካት
ሥልጡን ብኩን መፃጉዕ ናት፤....
እና+ ፈርቼ እንዳልባክን+ ሊርቀኝ የኃይልሽ ውጋጋን
አንቺ ካጠገቤ አትራቂ+ በርታ በደኝ እመ ብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት+ እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን፡፡
አዎን+ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ+
እማማ ኢትዮጵያን መንፈሴ+ተፈትሖ እንዳይከዳት ሠጋሁ..
አዋጅ+ የምሥራች ብዬ+የትብት ምግቤን ገድፌ
ከናቴ ማህፀን አልፌ
በኢትዮጵያ ማህፀን አርፌ+
ከአፈርዋ አጥንቴን ቀፍፌ
ደሜን ከደሟ አጠንፍፌ
ከወዟ ወዜን ቀፍፌ
በሕፃን እግሬ ድኼባት+በሕልም አከናፌ ከንፌ
አረኝነቴን በሰብሟ+ በምድሯ ላብ አላልፌ

ከጫጩትና ከጥጃ+ከግልገል ጋር ተቃቅፌ፣
በጋው የአረኖ አደባባይ+ ከረምት እንደወንዙ ፍሳሽ
በገጠር የደመና ዳስ+ በገደል ሸለቆ አዳራሽ
ከቆቅና ከሚዳቋ+ ከሸጣራ ጠረን ስተሻሽ
በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ+ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ
ከፍልፈል ጋር ሩጫ ሰንጥም+ ከቀበሮ ድብብቆሽ
ከናዳ ጫፍ ሳር አጨዳ+ለግት ሳሜ ትንሽ ግጦሽ
ለጥጃዬ የሌት ግርዶሽ
ለጥማድ በሬዎች ራት+ ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ
ለግልገሌ ካውሬ ከለል
እማሳው ሥር ጎጆ መትከል
ለፀሐይ የሾላ ጠለል+ ለዝናብ የገሳ ጠለል
ውሉ የንብ ቀፎ ማለስ+ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ
ግጦሽ ሣር ሲለመልም+ ሲለማሩ ሰደድ ሜዳ
አዝመራው ጣል ከንበር ሲል+ ከብቱ ለሆራ ሲነዳ
ፈረስ ግልቢያ ስሸመጥጥ+ ከወፎች ዜማ ስቀዳ
ልቤ በንፋስ ተንሳፎ+ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ...
ያቺን ነው ኢትዮጵያ የምሳት
እመ ብርሃን እረሳሻት?
ያችን የልጅነት ምሥራች? የሕፃንነት ብሥራት
የሣቅ የፍንደቃ ዘመን+ የምኞት የተስፋ ብፅአት
ያቺን የልጅነት እናት?
አዛኟ እንዴት ብለሽ+ ጥርሶችሽን ትነክሽባት?
ሰሜን በሰምሽ ሰይሜ+ባገልግሎትሽ ስዋትት
ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት+ ከደጓ ቤት እመዕሕፍት
ካንቺ ተቀራኝታ ዕድሌ+ ካንቺ ተቀራኝታ ነፍሴ
ከቀፈፋ ደጀ ሰላም+ ከቤተ ልሔም ቅዳሴ
አኮ+ ቀፎ+ ዳባ ለብሶ
ቅኔ ዘርፎ ግሥ ገሥ
መቅደስ አጥኖ+ማኅሌት ቆሞ
በልብሰ ተክህኖ አጊጦ+ በብር አክሊል ተሸልሞ
እመ ብርሃን ያንቺ ጽሳት+ ነፍሴ ላይ በሳት ታትሞ
የመናኒው ያባ ተድሳ+ ረደ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ
ሕይወቴ አምነትሽን ጸንሶ
ሥጋ ፈቃዴ ተድሶ
ለሕንፃሽ መዲና ቆሞ+ ለክብርሽ ደባብ ምሰሶ!
ሰሜን በሰምሽ ሰይሜ+ ሆነሽኝ የእምነቴ ፋናስ
ለዋዜማሽ ግሽን ማርያም+ ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ
ስሮጥ+ በወንበሩ አኖርሺኝ+ በእንበሳው በቅዱስ ማርቆስ
ታዲያን ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወድቅ+ ከምትሰጪኝ ለፍርሃት ጦስ
ምነው በረኝነት ዕድሜ+ ዓይኔን በንጣጣት የሎስ
የጋኔል ጥንብ አንሳ ከንፈሩ+ ወርዶ በጨለማ በርናስ፡፡
ባክሽ እመብርሃን ይብቃሽ+ ባክሽ ምስለ ፍቁር ወልዳ

ጽናት ስጪኝ እንድካፈል+ የእናቴን የኢትዮጵያን ፍዳ
ከነክሳት መርዝ እንድቀምስ+ ከነደደችበት እቶን
የሷን ሞት እኔ እንድሞታት+ ገላዋ ገላዬ እንዲሆን።...
አምን+ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ።...
ሕፃን ሆኜ የእርግብ ጫጩት+ አንዳንዴ ራብ ሲያዳክማት
ችጋር ከጎጆዋ ገፍቶ+ እዛፍ ግርጌ ሲጥላት
እናቷ በርራ ደርሳላት
በእክናፏ ሙቀት ታቅፋት
እፍ እያለች ግንባሯ ላይ+ ሕይወት ስትተነፍስባት
ወዲያው ነፍስ ትዘራለች
ሽር-ብር-ትር እያለች።
ባክሽ አንቺም አትራቂብኝ
እመ ብርሃን እናቴ+ ትንፋሽሽን እፍ በይብኝ
ዕናትሽን እፍ በይብኝ+
ወይም ይቺን የሞት ጽዋ+ ጥላዋ ነፍሴን ካፈናት
እንዳልጠጣት አሳልፊያት
መራራ ክንፏን ገንጥለሽ+ቀጠሮ+ቃልዋን ግደፊያት፤...
አለዚያም ዕናትሽን ስጪኝ+ ልጠጣው ኪዳነ-ውሉን
የኔ ፍቃድ እምነትሽ ነው+ ያንቺ ፍቃድ ብቻ ይሁን።
እንደ ጳውሎስ እንድፀና+በፍርሀት እንዳልታሰር
በውስጤ ከሚታገለኝ+በሥጋ አውሬ እንዳልታወር
ለዕየለቱ ሞት እንዳልሰንፍ
የኪዳኔ ቃል እንዳይነጥፍ
ቃልሽ በሕሊናዬ ዲብ +ኃይልሽ በህዋሴ ይረፍ።
ፍርሀት ቢያረብብኝም +አንቺ ካለሽ አልሰጋም
ኩርትም ብዬ እችልበት +እሸሸግበት አይጠፋም
የግማደ መስቀሌን ጉጥ + እታገስበት አላጣም
አለዚያማ ብቻዬን ነኝ+ኢትዮጵያም አላንቺ የላት
አንቺ አዕኝኝ እንድጸናላት።
አስርጪብኝ የእምነት ቀንጃ+ለሥጋቱ አጣማጅ አቻ
ለጭንቀቱ-መቀነቻ።.....
አምን+ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ
እምፀናበት ልብ አጣሁ.....
ፕሀሂኔ ቀበና (ፀጋዬ ገብረ መድህን)

"ግሩም ነው! አሳት የላሰ ግጥም! አሳት የላስክ ልጅ!" የፀጋዬን ግንባር ግጥም አድርጎ ሳመው። "ማስጠንቀቂያ!" አለው ከዚያ። "ከዚህ ግጥም ላይ አንድም ቃል አንድም ነጥብ እዳይለወጥ! ይህ ምስጢር ነው። ከዚህ ግጥም ውስጥ አንድ ቃል ብታወጣ ከሀገርህ ጋር ያለህ ወዳጅነት ይጎድፋል። ለመሆኑ.....ታሳትመዋለህ?"

"እንደ አምላክ ፈቃድ....."

"እንግዲያውስ እንደነገርኩህ! አንድም ቃል እንዳይለወጥ! አንድ ቀን ይህ ግጥም....." ትኩር ብሎ አይቶት በብራና ላይ የፃፈውን የሰቆቃወ ጴጥሮስን ቅጂ ከረጢቱ ውስጥ ቋጥሮ ሲወጣ ነግቶ ወፎች እየዘመሩ ነበር።ፀጋዬ አፉን ከፍቶ ቀረ። እየሮጠ ተከትሎ "ስምህ ማነው? ዳግመኛ ላገኝህ እፈልጋለሁ...." ሲል ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ጠየቀው። ሰውየው እርምጃውን ገቶ ወደኋላ ዞረ። "የፈለከውን ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ። እኔና አንተ ከእሁን በኋላ የምንገናኘው የግጥም መጽሀፍህ ሲታተም ብቻ ነው። ደህና ሁን!" እርምጃውን ቀጠለ። ፀጋዬም በዓይኑ ሸኘው።

ይህ ከሆነ ከአምስት አመት በኋላ በ1966 ዓ.ም የፀጋዬ ገብረ መድህን አሳት ወይ አበባ የሚባለው የግጥም መጽሀፍ ታተመ። ‹‹አሳት ወይ አበባ›› ለህትመት ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በገባበት ዕለት ከሰአት በኋላ ማተሚያ ቤቱ ውስጥ አንድ መነኩሴ ታይተው ነበር። መነኩሴው ካሜራ ከፍል የገቡት ሰቆቃወ ጴጥሮስ የሚለው ግጥም በዛ ጥራዝ ውስጥ መካተቱንና ቃሉም አለመለወጡን አረጋግጠው ለመውጣት ቢሆንም ወደ ማተሚያ ቤቱ ሲገቡ ግን ለህትመት የተዘጋጀ «አክሳፎስ» የሚል ርዕስ ያለው መጽሀፍ ይዘው ስለዚሁ መጽሀፍ የህትመት ጉዳይ ለመነጋገር በሚል ሰበብ ነበር። «አክሳፎስ» የሚባል መጽሀፍ ግን አስካሁን ድረስ ታትሞ ለንባብ አልበቃም።

ይህ ከሆነ ከብዙ አመታት በኋላ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን በራሱ ድምፅ አንብቦ «አብረን ዝም እንበል» በሚል ረዕስ ባሳተመው የግጥም ሲዲ ካሴት መግቢያ ላይ ሰቆቃወ ጴጥሮስን የፃፈበትን ምክንያት እንዲህ ብሎ ሲያብራራ ተደመጠ።

"ሰቆቃወ ጴጥሮስ የጴጥሮስ ያችን ሰዓት መዝጊያ የታሪካዊ ጀግናው የመጨረሻ ቃል ነው። ‹የመጨረሻውን ቃል ለጀግናው ተውለት።›› ይላሉ፣ ጥንታውያን የታሪካዊ ቴአትር ፀሐፍት.... እነ ኢኩራን ኤፍራት...እነ ዩሩፒድዩስ።....እቡነ ጴጥሮስ ሌሊቱን በግራዚያንና በባንዶቹ.. በባንዶች አሽከሮች አኮርባሽነት በገነተ ልዑል ጉድጓድ ቤት ውስጥ ሲገረፍ... ሲመሪመር ኢትዮጵያን ከድተህ በሞሶሎኒ እመን' ተብሎ ሲተለተል አድሮ በማግስቱ ጠዋት በአደባባይ በጥይት ተደበደበ። በግራዚያኒ ትዕዛዝ የጥይት እሩምታ ተኩሰው የጠቀጠቁት ጣሊያን ያሰለጠናቸው የሰሜን ባንዳዎች ወንድሞቻችን ናቸው። ጴጥሮስ እንኪንስ ህዝቡ ምድራቱ ጭምር ለፋሽስት እንዳትገዛ አውግዞ ሞተ። ..... በልጅነቴ ከአምቦ ከተማ ለመጀመሪያው ጊዜ በ15 ዓመቴ ከቡር ዘበኛ ካዴት ልገባ ጠፍቼ ስመጣ አዲስ አበባ እምብርት መዳረሻ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት

ክትሬንታኒትሮ መርጀ.....አባቱ ሰለአቡነ ጴጥሮስ የእረኝነት እድሜና የጀግንነት ጀብድ ህይወት በከፍተኛ አድናቆት ያጫውቱኝ የነበረው ትዝ ብሎኝ ሐውልቱ ሥር ቆሜ ቀረሁ። .....ይህ በሆነ ከአሥር ዓመት በኋላ አለቃችን የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ክቡር ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ማስታወቂያ ሚኒስትር እባው አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ስብሰባ ጠርተውን ቢሮአቸው አምሽተን ስንወጣ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ አንድ ሞቅ ....እ.... ያለው የተበሳጨ ጀብራሬ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን እየሸና 'አንተ ድንጋይ! ነይሮችህ ተመችታቸው በማርቼዲስ ሲንሸራሸሩ ይዝው አንተ ድንጋይ ሆነህ ቀረህ። ....ድንጋይ! አሸናብሃለሁ!.... ሲል በልጅነት ደም ፍላት ዘልዬ ከጀብራሬው ጋር ግብግብ ገጠምኩ። ‹ድንጋይ ነው››.....“ድንጋይ አይደለም!”....በሚል በቡጢም ተቃመስን። ከስብሰባው የተቡተኑ ሰዎች ገላገሉንና እየተበሳጨሁ ቤቴ ገባሁ። ሌሊቱን አልተኛሁም። ‹ጴጥሮስ ህያው ነው› ለማለት፣ ‹ጴጥሮስ ድንጋይ አይደለም› ለማለት ይመስለኛል፤ ጴጥሮስ ያችን ሰአትን ስጭር አደርክ። እንዳልኩት ይህ ስነግጥም የታሪክዊ ጀግናው የመጨረሻ ቃል ነው....” ይህ የራሱ የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የምስክርነት ቃል ነው። ይህን ንግግርም ብዙ ኢትዮጵያውያን አዳምጠዋል። ሎሬቱን ...መጽሀፉን ያነበቡም ያላነበቡም ያደንቁታል። ነገር ግን ስለ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን እንጂ በዚህ ንግግሩ ውስጥ ‹ጀብራሬ› ተብሎ ስለተጠቀሰው ኃያል ሰው የሚያውቅ ማንም የለም። በሎሬቱ ንግግር ውስጥ ግን አንድ ነገር መገንዘብ ይቻላል። “ሞቅ.....ያለው የተበሳጨ ጀብራሬ” የሚል የሚያሻማና ብዙ ጥያቄ የማቀሰቀስ ገለፃ አለ። ሞቅ ያለው! ደግሞ የተበሳጨ! ደሞ ጀብራሬ! ደሞ በቡጢ የሚያቀምስ! ደሞ ግብግብ ተጋጥሞ የማይወድቅ! ደሞ በንግግሩ ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው ስለ አቡነ ጴጥሮስ ብዙ የሚያውቅ የሚመስል! ደሞ በራስ በመተማመን የተሞላና "ድንጋይ!" ብሎ የሚሳደብ! ደሞ ስንት ቦታ ባደውን ተቀምጦ ሀውልት ላይ የሚሸና!

ሆኖም ቆብ ጣዩ መነኩሴ ዳዲሞስ ጀብራሬው ባይናር ኖሮ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን ባልሸና! አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ላይ ሽንቱን ባይሸና ጴጥሮስ ያችን ሰአትን የመሰለ ቱአትር ባልተሣፈ.....ሰቆቃው ጴጥሮስም ባልተገጠመ። አንድም ቃል ሳያጨመርበት አንድም ቃል ሳይቀነስበት የታተመውና በጣፋጭነቱ ላለፉት ብዙ ኢመታት ሲከመከም የኖረው ሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም ባለ 105 ስንኝ ነው። ቃላቱም 497 ናቸው። ሎሬቱን ጨምሮ...48ቱ ቃላት ያጨቁትን ምስጢር ለመፍታት የቻለ ግን አስካሁን አልተገኘም።

፩

ካሊፎርኒያ፥ አሜሪካ
፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅጉ ራሱን ስቶ ከተኛበት የማያንዘገገ ክፍል ውስጥ ከሰመመኑ ከነቃ ከሰዓታት በኋላ አንድ ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቅ ጠይም ዶክተር ቆሞ በጭንቀት እየተመለከተው ነበር።

"እንኳን በሰላም ነቃህ፣ ኢንጂነር ሻጊዝ" አለ ዶክተሩ ፈገግ ብሎ።

"ከነቃሁ እኮ ቆይቻለሁ.....ሆኖም ስለፈገግታህ አመሰግናለሁ" አለው ኢንጂነር ሻጊዝ ዓይኖቹን ገርበብ እንዳደረገ።

"እኔም አመሰግናለሁ ኢንጂነር ሻጊዝ። በእርግጥ ግራ ተጋብቼ ስለነበር ያከምኩትን ገመምተኛ ከሰመመኑ ሲነቃ መቀበል በሚባኝ ብሩህ ፊት ስላልተቀበልክ ይቅርታህን አለምናለሁ። ብሽተኞችን የሚፈውሳቸው ከዶክተሩ የህክምና ርዳታ ይልቅ ብሩህ ፊቱና ፈገግታው ነው› ብዬ አምናለሁ። የደመቀ ፈገግታና የፈካ ፊት የሚያፈውሰው በሽታ የለም" አለ ጠይሙ ዶክተር። ፊቱ በብዙ ጥያቄዎች መሀል እንዳለ ያሳብቃል። ግራ መጋባት ይታይበታል።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በምስጢር ወደ አሜሪካ ከተላከ ረዥም ጊዜ የሆነው የኢትዮጵያ ደህንነት አባል በመጨረሻ ሁሉ ነገር እንደ ጨለመበት ተረዳ። ቤቱ ተከቢል። እጅህን ስጥ ሲባል «እንኪንስ እኔን አንዲት ዘለላ ፀጉሬን አታገኟትም» ሲል በስልክ ተሳልቋል። ድምፃቸው ይሰማዋል። ዳናቸው ወደበሩ እየቀረበ ሲመጣ ሽጉጡን በራሱ ጭንቅላት ላይ ደቀነው። «አቀድማችኋለሁ.....በሱ ጭንቅላት ላይ ምላጭ አልሰብም...»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"የወንዜን ሰው ትመስላለህ" አለው ኢንጂነር ሻጊዝ። "ከሐበሻ ምድር የመጣህ ሳትሆን አትቀርም።"

"አልተሳሳትክም" አለ ጠይሙ ዶክተር ብዙ ወረቀቶችን እያተረማመሰ። "ዶ/ር ሚራኸር እባላለሁ። ወደ አሜሪካ ከመጣሁ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል። አዚህ ሆስፒታል ውስጥ ከተቀጠርክ ግን ጥቂት ጊዜዬ ነው። .....በዚህ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ስላንተ የህክምና ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ለማወቅ ችያለሁ" የኢንጂነሩን የህክምና ሁኔታ የሚገልፁ መረጃዎች የያዙት ብዙ ወረቀቶች እያገላበጠ ሰማያዊው ወንበር ላይ ተቀመጠ። በጠይም ፊቱ ላይ ያንጎበበውን የጥያቄ ደመና የሚያዘንብበት ጊዜ መድረሱን አምኗል።

"ኢንጂነር ሻጊዝ... ከአሁን በፊት ብዙ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ማድረግህን ያወኩት በቅርቡ ባገኘሁት ምስጢራዊ ሰነድ ላይ

ነው" አለ ሚራዥ ግንባሩን በመዳፉ አሻሸ። "ከ1969 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በደረሰብህ የልብ ህመም ምክንያት ብዙ ጊዜ የልብ ቀዶ ጥገና ተደርጎልሃል። ከዛም ወዲህ በየሁለት ወሩ ቀዶ ጥገና ይደረግልሃል። በየሁለት ሳምንቱም በሃኪም የመታየት ግዴታ አለብህ። ያሰቅቃል!" ዶ/ር ሚራዥ በማያውቀው ስሜት ራሱን ነቀነቀ።

"ለመሆኑ አንተ ማነህ?" ሲል ዶክተሩን በጥሞና እየተመለከተ ጠየቀው ሻጊዝ። "እንዴት እንድታክመኝ ፈቀዱልህ?"

"አዎ.....አክሜህ አላውቅም። የህክምናህን ጉዳይ ግን ብዙ ጊዜ አክታተል ነበር። ይህን ጊዜም ስናፍቅ ነበር። ያገኘኋቸውን መረጃዎች ላካፍልህ ስጠብቅ ነበር። ይሽኖውን ቀዶ ጥገና ብቻዬን አይደለም ያደረኩልህ። ከሌሎች ዶክተሮች ጋር በመሆን ነው። ቀዶ ጥገናውን በበላይነት እንዲመራ የተወከለው ሐኪም ዶ/ር ሉስ ካን ባልታወቀ ጉዳይ ወደ ሌላ ሆስፒታል በመዛወሩና ተረኛም ስለነበርኩ ተክቼው እንድሠራ ተደርጓል። በእርግጥ እስካሁን እኔን አታውቀኝም። አሁን ተዋውቀናል። የህገርህ ሰው በመሆኔ ብቻም ሳይሆን የሙያ ግዴታዬና ህሊናዬ የሚጠይቀኝ በመሆኑ ነው የጤንነትህን ጉዳይ በጥብቅ መከታተል የጀመርኩት" በረጅሙ ተንፍሶ ንግግሩን ቀጠለ።.....።"አንተ እኔን ባታውቀኝ አይገርምም። የሚገርመው እኔ አንተን ባላውቅህ ነው። በእርግጥ ኢትዮጵያውያን ስላንተ ማወቅ ጀመሩት በቅርቡ ነው።.... በቅርቡ። ስላንተ በጣም የሚታወቀው በሰለጠነው ዓለም አካባቢ ነው። ስላንተ ብዙም ባይሆን በጥቂቱ ለማወቅ ችያለሁ። ከመገናኛ ብዙሃንና ከሰዎች አንደበት ብዙ ሰምቻለሁ። በህዋ ምርምር ዓለማችን ካፈራቻቸው እውቅ ሳይንቲስቶች መሃል ግዙፍ ስም ያለህ ሳይንቲስት መሆንህን አውቃለሁ። በዚህ አጋጣሚ እንደምኮራብህ ልነግርህ እወዳለሁ። ልኮራብህም ይገባል። ኢትዮጵያም ልትኮራብህ ይገባል። በህዋ ምርምር አንቱ የተባለ አንድ ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ማግኘት ቀላል አይደለም። ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነህ። ኢትዮጵያ አንዳንተ ያለ ሰው ለማፍራትና ለማሰልጠን ብዙ ቢሊዮን ዶላር ማፍሰስ ባስፈለጋት ነበር። ብቻህን ታግለህ እዚህ ደረጃ መድረስህ ለብዙ የህገርህ ልጆች አርአያነቱ ላቅ ያለ ነው። ከዳፕሎማ ተነስተህ የአለማችን ታላቅ የህዋ ሳይንቲስት መሆንህ ለህገርህ ሰዎች ታላቅ መነሳሳትን ይፈጥራል። ኢትዮጵያውያን አትንኩኝ ባዮች ብቻ ሳይሆኑ እድሉን ካገኙ መሰልጠንና መበልፀግ የሚችል አዕምሮ ያላቸው እንደሆኑ ለዓለም ታላቅ ምስክር ሆነህል።"

"ለመሆኑ ሰነዱ በእጅህ ይገኛል?" ኢንጂነር ሻጊዝ ቦመደመም ጠየቀው። እሱ አቅቶት የተወውን ነገር ይህ ሰው እንዴት ሊደርስበት እንደቻለ ተደንቆ።

"ሙሉ አይደለም" አለ ዶ/ር ሚራዥ ትንሽ ትክዝ ብሎ።

"በእጅህ ስላለው....." ኢንጂነር ሻጊዝ ሰውነቱ ላይ በተተካከሉት የህክምና መሣሪያዎች እንደተተበተበ ሳይነቃነቅ ጥቃቅን አይኖቹን ብቻ እያንቀዋለለ የዶክተሩን መልስ መጠባበቅ ጀመረ።

ዶክተር ሚራዥ የተረጋጋ መንፈስ አይታይበትም። ብዙ ጊዜም በር በሩን ይመለከታል። "ብቻ ግን አንድ ነገር አለ" ሚራዥ ቅጭም ብሎ በእጁ የያዛቸውን ወረቀቶች አርገፈገፋቸው።

"አዎ አውቃለሁ፤ አሁን ማወቅ የምፈልገው የደረስክበት ምስጢር ካለ ያንን ነው" ሻጊዝ በጥያቄ መልክ የግንባሩን ቆዳ ሸበሸበው።

"ነገሩ በቀላሉ የሚገባና ግልፅ የሆነ ነገር አይደለም። ሰነዱ ላይ ያለው ሪፖርት በትክክል የልብህን በሽታ ምንነት አይገልፅም። ብቻ የመጀመሪያው የልብ ቀዶ ጥገናህ ላይ የሆነ ጉዳይ ሳይኖር አይቀርም። ያሁኑ የልብ ቀዶ ጥገናህ ሲደረግ ያየሁትና..... የተደረገው ሌላ ሪፖርቱ የሚለው ሌላ። አሁንም ቢሆን የተፃፈው ሪፖርት ከበሽታህ ጋር የማይገናኝ ነው። የ.ማ.ይ.ገና.ኝ!» ተቁነጠነጠ።

«የሆስፒታሉን ዳይሬክተር ለማናገር ጉብቼ ነበር። ያገኘሁት ምላሽ ምን እንደሚል ታውቃለህ? ‹አያገባህም አርፈህ ሥራህን ሥራ› ነበር ያሉኝ። እንዲያውም ይህን ክትትሌን ካላቆምኩ በሰዓታት ውስጥ ከሆስፒታሉ እንደሚያሰናብቱኝ በጥብቅ አስጠነቅቀውኛል። እኔ ደግሞ እንደዚህ አይነት ነገሮችን መጋፈጥ ደስ ይለኛል። ይህን ጉዳይ አንተ ቸል ብትለው እንኳ መጋፈጤን አላቆምም። አሜሪካ እንደምትፈልግህና እንደምታስፈልጋትም አውቃለሁ። ግን በዚህ መልኩ መሆን የለበትም። ነፃነትህንና ሰብአዊ መብትህን ከዚህም በላይ በህይወት የመኖር መብትህን መጋፋት ታላቅ ወንጀል ነው። የተደረገልህ ቀዶ ጥገና የተለየና በየትኛውም ከአሜሪካ ውጭ ያለ ሀገር ሊሰጥ የማይችል ነው..." ዶ/ር ሚራዥ ለማስረዳት ግራ ተጋብቷል።

"እሱንማ..... አውቃለሁ።.....ከአሜሪካ ውጭ መታከም ስለማልችል አይደል እንዴ የዚህች ሀገር አስረኛ ሆኜ የተረሁት?! እሱንማ አውቃለሁ» አለ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ። "ይልቅ የተለየ የደረስክበት ምስጢር ካለ ንገረኝ። እርዳታህን እሻለሁ። የፊለክውን ያህል ለመክፈልም ዝግጁ ነኝ" አለ ሻጊዝ በተማፅኖ።

«እኔንም ይህ ጉዳይ ይመለከተኛል። አንተኮ ለሀገርህ ብቸኛ ሰው ነህ። አንተን ብረዳ ረድቻት የማላውቃትን ሀገሬን መርዳት ቻልኩ ማለት ነበር። ግን እንዴት አድርጌ? በጣም በጥብቅ የተያዘ ምስጢር ይመስለኛል። ብቻ እግዚአብሔር ከረዳኝ ባደርግልህ ደስታውን አልችለውም ነበር።" ዶ/ር ሚራዥ አፍንጫው ላይ የተሰካውን ነፃ መነፅሩን አንስቶ ከነፃ ጋዋኑ

ኪስ ባወጣው መሐረቡ የአይኑን ሥር እየጠራረገ ተነስቶ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠውን ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ቁልፎች መነካካት ጀመረ።

ኢንጂነር ሻጊዝ ግንባሩን ወደላይ እንደሸበሸበ ዶ/ር ሚራዥን በጥያቄ ይከታተለዋል። ከዕውቅናውና ከስኬቱ ጀርባ ውጣ ውረድ የበዛበት የህይወቱ ጉዞ ከአዕምሮው ተሰነቀረ።

ጠፈርን ገዝተዋል ከሚባሉት እውቅ የህዋ ሳይንቲስቶች አንዱ የሆነው ኢንጂነር ሻጊዝ ለአሜሪካ የህዋ ምርምር ተቋም ናሳ ያበረከተው ግኝት ገና በ43 አመቱ በአሜሪካ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅናን አስገኝቶለታል።

በናሳ ውስጥ የመንኮራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር ሆኖ ፈረቃ ላይ በመውጣት ሁለተኛ ሰው ከሆነው የአፖሎ ጠፈርተኛ ቡዝ አልድሪን ጋር በመሆን ሁለት የህዋ መንኮራኩሮችን ዲዛይን አድርጓል። የጁፒተር፣ የሳተርን በተለይም በቀጣይ ለአሜሪካና ለዓለማችን ሀያላን ሀገራት ማረፊያነት ተስፋ የተጣለባት ፕላኔት ማርስን ውስጣዊና ውጫዊ አካል የሚያጠናውን ልዩ የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ በመሆን ለጠፈር ምርምር ያደረገው አስተዋፅኦ ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል። በዚህ ወቅት የመሬትን ውስጣዊና ውጫዊ ሀብት ከመመርመሩም ባሻገር ስለ ሳተላይቶችና ራዳሮችም የጠለቀ እውቀት ካላቸው ሳይንቲስቶች ግንባር ቀደሙ ሳይንቲስት ነው።

ይህ ሰው ወደ አሜሪካ ካገባ ጊዜ ጀምሮ በሠራው አስደናቂ ሥራ ምክንያት ከአንድ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እጅ በጣም ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙትን ሽልማት ተቀዳጅቷል። በተራቀቁ ላቦራቶሪዎችና በአሜሪካ ምስጢራዊ የቴክኖሎጂ ተቋማት ውስጥ በያዛቸው ጥብቅ የቴክኖሎጂ ምስጢሮች ምክንያት አንድም ቀን አንዲትም ደቂቃ ከጥበቃና ከክትትል ውጪ ሆኖ አያውቅም። እንዲያውም ወደ ኢትዮጵያ ከመጣበት ጊዜ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያ የገባው የሲ.አይ.ኤ ቡድን ለደህንነቱ ሥጋት የሆኑ ነገሮችን ካጠናና ካስወገደ በኋላ ነበር አሜሪካ የፈቀደችለት። ኢትዮጵያ በመጣበት ጊዜ ይደረግለት የነበረው ጥበቃም አንድ አሜሪካዊ ባለስልጣን ከሚደረግለት ጥበቃ በላይ ነበር ይባላል። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይቀርም ለተፈቀደለት ጊዜ ብቻ የሚያቆይ ምስጢራዊ ህዝምና እንደተሰጠው እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው። ፊጥኖ የተመለሰበትም ምክንያት ይህ ነበር። በግልፅ ከተቀጠሩለት እስከ አፍንጫቸው ከታጠቁ አጃቢዎቹ በተጨማሪ በዙሪያው የሚያንጎራብቡ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች በዓይነ ቁራኛ ይጠባበቁታል። ወደሚንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ እየተንቀሳቀሱ በጥብቅ ይጠብቁታል። ጠፈርን የገዛ የአሜሪካ

የጠፈር ምርምር ሳይንቲስት መሆኑ ብቻም ሳይሆን የቋጠረው የአሜሪካ የቴክኖሎጂ ምስጢር የበለጠ ጥበቃውን አክሮታል።

ቻይና፣ ጃፓን፣ ኢራን፣ ህንድ፣ ፓኪስታን፣ ሰሜንኮርያ፣ አስራኤልና ሩሲያ ይህንን ሳይንቲስት በእጃቸው ለማስገባት ጥያቄያቸውን በምስጢር ሲያቀርቡለት ረብጣ ገንዘብም በመቋጠር ነበር። አስራኤልም ከነዚህ ሀገራት ጋር ያረገውን ግንኙነት ስታነፈንፍ ከኖረች በኋላ ጥያቄዋን አለመቀበሉን ስትረዳ ከእሷ በቀር ወደ የትኛውም ሌላ ሀገር እንዳይሄድ በተለይም በአረብ ሀገራት እጅ እንዳይገባ በስለላ ድርጅቷ ሞሳድ በኩል ጥብቅ ክትትል ለማድረግ ከሲ.አይ.ኤ ጋር ተቀላቅላለች። ከአሜሪካ መንጋጋ ፈልቅቀው ለመውሰድ የሚኳትኑትን ሀገራት አሻፈረኝ ቢላቸውም ክትትላቸውን ግን አላቋረጡም። በነዚህ ሀገራት ክትትል ምክንያትም ሞሳድና ሲ.አይ.ኤ የበለጠ ጥበቃቸውን እንዲያጠናክሩ አድርጓቸዋል። ይህንን ሳይንቲስት ሁሉም የዓለም ሀገራት ይፈልጉታል...ከኢትዮጵያ በቀር።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ቤቱ ከተከበበ ሶስተኛ ቀኑ ነው። ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ እንደ ደቀነው በሩ በኃይል ተንኳኳ። «ገዳዮቼ እያንኳኩ ነው» ሲል ለራሱ ተናገረ። የኢንጂነሩ የቅርብ ሰው ለመሆን በመቻሉ ጉዳዩን እሱ ይዞት ቢቆይም ከባለፈው ስብሰባ ወዲህ ግን ሌላ ሁለት ደህንነቶች እንዲከታተሉት ተቀይረው መጥተዋል። የኢንጂነሩን መወገድ በሚቃወሙና በሚደግፉ ጎራዎች በተከፈለው በዛ ስብሰባ ላይ ያንፀባረቀው ሀሳብ ጉባኤውን ለሁለት ከገመሰው ወዲህ እሱ ራሱም ታዳኝ ሆኗል። ዋሽንግተን ነው ሲሉት ዴንቨር እየታየ እስካሁን ያጋበሳቸውን መረጃዎችና ሰነዶች ጠራርጎ ይዞ ሲሸሽ ከርሞ ከሶስት ቀናት በፊት ነው ካሊፎርኒያ ውስጥ አሁን ባለበት ሁኔታ የተያዘው። ሲገቡ በርና መስኮቱን መሰባበር ሲጀምሩ ሽጉጡን ወደ ሽንጡ መልሶ በፍጥነት ሰነዶቹን ጠራርጎ በእሳት አያያዛቸው። ቤቱ በወረቀቶቹ ቃጠሎ ጢስ እንደታፈነ በድምፅና በምስል የተቀዱ መረጃዎችን እየሰባበረ ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው። ባንዲት ብጣቂ ወረቀት ላይ አንድ ቃል ካሰፈረ በሁዋላ መልሶ ሽጉጡን ጭንቅላቱ ላይ ደቀነው።.....

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሻጊዝ ገና በልጅነቱ ነበር የተለያዩ ማሽኖችን የመፍታትና የመገጣጠም ፍቅር ያደረበት። ኢትዮጵያ ውስጥ ቦንጋ ከቀሩት ጣሊያኖች የኢሌክትሪክ ሱቅ ጀምሮ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በወቅቱ በሩሲያውያን በሚተዳደረው የባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ዘርፍ የእርሻ ቴክኖሎጂን አጠና። ከባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ተቋም በማዕረግ የተመረቀም ሲሆን ውጤቱም በተቋሙ ታሪክ ሁለተኛው ከፍተኛ ውጤት ነው።

በኋላ ደግሞ በኢትዮጵያ የአውቶሞቲቭ ሰርቪስና ሴልስ ኩባንያ የቴክኒካል ዋና አማካሪ ማናጀር በመሆን ለሁለት አመታት ሠርቷል። በ1964 ዓ.ም በጃፓን አቨርሲስ ማህበር ባገኘው ነፃ የትምህርት ዕድል ወደ ጃፓን አመራ። በጃፓን ሂሮሺማ ዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪና አቶሞቲቭ ኢንጂነሪግን አጠና። በኦሳካ ዩኒቨርስቲም የጃፓኖችን የቴክኖሎጂ ምስጢር ለመረዳት ሲል ጃፓንኛ ቋንቋ ለመማር አሳቅማማም። ከጃፓን ወደ አሜሪካ ሲያመራ በጠፈር ምርምር የመሳተፍ ህልሙን እውን ለማድረግ በመቋመጥ ነበር።

አሜሪካም ከጃፓን የመጣውን ባለ ብሩህ አዕምሮ የቴክኖሎጂ ሰው እጁን ስማ ተቀበለችው። ወደ አሜሪካ ከገባ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የኤሮስፔስ ኩባንያዎች ሲሰራ ቆይቶ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ (NASA) ተቀጠረ።

በናሳ ቆይታው የመንኩራኩር ሲስተም ዲዛይን ኢንጂነር በመሆን መንኩራኩሮችን ዲዛይን ማድረግ፣ መሥራትና መገጣጠም፣ መሞከርና ማምጠቅ...ተግባሩ ሆነ። በዚህ ወቅት ዝናው እየናኘ አውሮፓ ደረሰ። ለአውሮፓ ስፔስ ኤጀንሲም በርካታ ተግባራትን አከናውኗል።

በስፔስ ሲስተም ከፍል የበረራ ዳይናሚክ ሲሙሌተር እና 'ኔክስት ጀነሬሽን' ተብሎ የሚጠራው 'ግሎባል ፖዚሽን ሳተላይት ሲስተም' የፈጠራ ባለቤት ሳይንቲስት ከመሆኑም ባሻገር 'ስታር ዋርስ' ተብሎ የሚጠራውን የመከላከያ ሲስተም ቴክኖሎጂ ለማጎልበት የሳይንቲስቶችና የኢንጂነሮች ቡድን መሪ በመሆን ሠርቷል።

ከእስራኤል አሜሪካዊት ባለቤቱ ሶስት ልጆች ቢወልድም ትዳሩ የሠመረ አልነበረም። የልጆቹን የአሳዳጊነት መብት ለማግኘት በፍርድ ቤት ለመከራከር ሕግ ማጥናቱ ብዙዎችን አስገርሟል። ብዙዎች ‹ለያንዳንዱ ችግሩ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የሚማር ብቸኛው ሰው ሻጊዝ እጅጉ ነው› ይላሉ። በጠፈር ሲስተምና በኤሮኖቲካል ምህንድስና በከፍተኛ ውጤት በዶክትሬት ዲግሪ ከመመረቁም በተጨማሪ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽንም የማስተርስ ዲግሪ አለው።

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ በ1969 ዓ.ም በአሜሪካ የጠፈር ምርምር ማዕከል ናሳ ውስጥ ከተቀጠረ በኋላ በአሜሪካ የቴክኖሎጂ ማህበረሰብ ውስጥ ስሙ የገነነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው። ግን ብዙም ሳይቆይ የልብ በሽተኛ ሆነ። ከዚያም በየሁለት ወሩ የልብ ቀዶ ጥገና ማድረጉን ቀጠለ። ከዚህ ቀዶ ጥገና በስተጀርባ ያለውን ምስጢር እሱም ቢሆን በውል አያውቀውም።

በልቡ ህመም ምክንያት ከተወሰነ የአየር ክልል በላይ መውጣትና መብረር ባለመቻሉ የተነሳ እንጂ ጨረቃ ላይ በማረፍ የመጀመሪያው ጥቁር መሆን ይችል እንደነበር ሁልጊዜም ይናገራል።

ፊቱን ወደ አፍሪካ ማዞሩና በተለይም የሀገሩን ማዕድንና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት የተማሩ ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ በሳይንሳዊ ጥበብና በተራቀቀ ቴክኖሎጂ አማካኝነት አውጥቶ ሀገሩን ከድህነት አዘቅት ቶሎ መንጥቆ ለማውጣት በተነሳባት በዚህ ወቅት ክትትሉ ከቀን ወደቀን እየጠነከረበት መጥቷል። ብዙዎች እንደሚሉት ወደዚች ደሀ ሀገሩ ቢሄድ በሌሎች ሀገራት እጅ ላለመውደቁ አሜሪካ ማረጋገጫ የላትም። እስራኤልም ቢሆን ይህ ሳይንቲስት በአረብ ሀገራትና ፀረ እስራኤልና አሜሪካ አቋም ባላቸው ሀገራት እጅ እንዳይገባ ክትትሏን አጠናክራለች። ይህ ሰው የዓለማችንን ራዳሮች ሳተላይቶችና የመገናኛ አውታሮች በፈለገው ጊዜ መዝጋት የሚችል አእምሮያለው ሰው ነው።

በፕላኔታችን ሰማይ ላይ የተበተኑት ጥቁር ሳጥን ወይም በምህፃረ ቃል ‹‹ሳሞስ›› በሚል ምስጢራዊ ስም የሚጠሩት ፀረ-ሚሳዬል መመልከቻ ሳተላይት ስልቶችና ሌሎች በየዘጠና ደቂቃው መሬትን እየዞሩ ሃምሳ ሺህ ወታደሮች በዓመት ውስጥ ከሚሰበስቡት መረጃ እጥፍ የሚበልጥ ጉዳይ የሚሰበስቡትን ሳተላይቶች ቢዘጋቸው የሚከተለውን መገመት ቀላል ነው። ከዚህም በላይ በብሩህ አእምሮው የሰበሰበውን ምስጢር በምንም መልኩ ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ቢሰጥ አሜሪካም ሆነች እስራኤል እንኳን ቦንብ የጫነ አውሮፕላን ማንም ተራ ወንበዴ አሽመድምዶ የሚያፈራርሳቸው ተራ መንደሮች እንደሚሆኑ ያውቁታል። የአሜሪካን የቴክኖሎጂ ምስጢር እንደውሃ የጠጣው ይህ ሳይንቲስት ጠላቶቻቸው ምድርን የሚንጡ ተምዘግዛጊ ሚሳዬሎች ባለቤት በሆኑበት በዚህ ወቅት በጠላቶቻቸው እጅ ቢገባ የሚከፍሉትን ዋጋ ያውቁታል። በመሆኑም ይህንን ሳይንቲስት ከጥበቃው ባሻገር ከአሜሪካ የማያስወጣው ቢወጣ እንኳ ከሁለት ወር በኋላ እያጣደፈ የሚያመጣው የልቡ ጉዳይ ነው። .....

ዶ/ር ሚራኻር የኮምፒውተሩን ቁልፎች ሲነካካ ከቀየ በኋላ ተመልሶ ወንበሩን ኢንጂነር ሻጊዝ ወደተኛበት አልጋ አስጠግቶ ተቀመጠ። ኢንጂነር ሻጊዝም አንዳች መላ ያገኘ መስሎት አይኖቹን በልጥጦ አፍ አፉን ተመለከተው።

“ግዴለህም። ለዚህ ጉዳይ ጊዜ ስጠኝ። በየጊዜው የደረስኩበትን ሁኔታ ሪፖርት አደርግልሃለሁ። ጊዜና ጥብቅ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ይህንን ምስጢር እስከምንጨ ማወቅ ይገባናል” አሉ ዶ/ር ሚራኻር አንድ ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ።

"ግን ቶሎ መሆን አለበት። የልቤ ጉዳይ ከተስተካከለ ...." አዕምሮው ወደ አፍሪካ ገሠገሠ..... ወደ ኢትዮጵያ።

"ሌላ ጥያቄ የሆነብኝ ነገር....." አለ ዶ/ር ሚራኹር አሁንም ጣቱን ከንፈሩ ላይ ጣል አድርጎ እያሰላሰለ ብድግ ብሎ። "ጀርባህ ላይ ያለውን ንቅሣት ልብ ብለኸው ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀው። ‹‹ዴርቶጋዳ›› የሚለውን የጀርባው ንቅሣቱን ፅሁፍ ከጀርባው ዞሮ እየተመለከተ።

"ንቅሣት?"

"አዎ..." አለው ሚራኹር። ‹‹ዴርቶጋዳ.....ስለ ሚለው ንቅሳትህ።››

"በወጣትነቴ ነው የተነቀሥኩት" አለ ኢንጂነር ሻጊዝ የወጣትነቱን ዘመን እያስታወሰ።

"ማነው የነቀሰህ?"

"ማን ነበሩ? አዎ። አለቃ አያሌው ናቸው! አለቃ አያሌው።"

"አለቃ አያሌው ማን ናቸው?" አለ ሚራኹር በጉጉት።

"አያሌውን የማውቃቸው በልጅነቴ ቦንጋ እያለሁ ነው። ቦንጋ የከፋ ጠቅላይ ግዛት ከተማ ናት...ኢትዮጵያ ውስጥ" ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ አያሌውን በደንብ ለማስታወስ እየጣረ።

"በልጅነቴ አለቃ አያሌው ወደዚያች ከተማ ሲመጡ አስታውሳለሁ። በጣም ጎበዝ ተረትና ታሪክ አዋቂ ነበሩ። እኔ እንዲያውም አባቴ ካስተማሩኝ ተረት በላይ የነገሩኝ አለቃ አያሌው ናቸው። በተለይ በጣሊያን ጊዜ ስለነበረው የኢትዮጵያ ሁኔታ አጠጠርጥረው የሚያውቁ ሰው ናቸው። እርሳቸው እንደነገሩኝ ከሆነ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተደባልቀው የውስጥ አርበኛ ሆነው ተዋግተው ነበር። ጣሊያን ሲባረር የንጉሡን መምጣት ተከትሎ ወደ ቦንጋ ከተማ መጡ። ቦንጋ የመጡበትን ምክንያት ማንም በውል የሚያውቅ የለም። ብቻ ቦንጋ ከቀሩ የጣሊያን ቤተሰቦች ጋር የሚኖር አንድ ዲዎላ የሚባል ልጃቸውን ለመጠየቅ ከባህር ዳር ከተማ ተነስተው እንደመጡ ነግረውኛል። ጣሊያኖችን ሲያዩ ይደበቁ ነበር። ከልጃቸው ጋር ስለ ማይስማሙ ከእኔ ጋር ነበር ብዙ ጊዜ የሚያሳልፉት። ታሪክ ማውራት ይወዳሉ። ስለማዳምጣቸውም ይወዱኝ ነበር። በተለይ ከጣሊያኖች ጋር ስለምቀራረብና በኤልክትሪክ ሱቃቸው ውስጥ እውል ስለነበር የልጃቸውን ሁኔታ እየተከታተልኩ እናግራቸውም ነበር። አባቴም በኢጣሊያ-ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት በፀረ ፋሽሽት ዘመቻ ጀብዱ የሠራ ወታደር ስለነበር ስለጦር ሜዳ ውሎው ይተርክልኝ ነበር። እሳቸውም የአባቴን አይነት ታሪክ ነበር የሚነግሩኝ። በጣም የተማሩ ሰው እንደነበሩ ተረድቻለሁ። የቤተክህነት ትምህርት በጣም ያውቁ ነበር። እንዲያውም የቤተ ክህነት ትምህርት እንድማር ይገፋፉኝም ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ

እንዳነብና ከአያንዳንዱ ስራዬ በፊት እግዚአብሔርን እንዳስቀድም ብሩን የከፈቱልኝ እርሳቸው ናቸው። ከጣሊያኖችም ጋር ብዙ ሞያ እንደቀሰሙ ነግረውኛል።" ኢንጂነር ሻጊዝ ለኒህ ሰው ልዩ ፍቅር ነበረው።

"እና ለምን ነበር ንቅሳቱን የነቀሱህ?"

"በህይወትህ ውስጥ ሊጠቅምህ የሚችል ከባድ ነገር ነው ብለው ነበር የነቀሱኝ። ለልጃቸው ማድረግ የፈለጉትን ነገር ከልጃቸው ጋር ስለማይስማሙ ለእኔ አደረጉልኝ። በወቅቱም ተማሪ ስለነበርኩ እንዲያውም ትምህርትን የሚገልፅ መድሃኒት መስሎኝ ነበር።"

"ትርጉሙን አልነገሩህም?"

"ትርጉሙ..." አለቃ አያሌው ትውስ አሉት .. ተናግረው የማይደክማቸው ሰው ነበሩ። ትርጉሙን ነግረውት ነበር። ግን ትኩረቱ ትርጉሙ ላይ አልነበረም። መድኃኒትነቱ ላይ እንጂ። የትምህርት መድኃኒት መስሎት ነበር.....ዘኪያገድፍ። የማስታወስ ብቃትን የሚጨምር መድኃኒት።

"....‹ዴርቶጋዳ› ማለት ምን ማለት ነው?" ብሎ ሊጠይቃቸው ፈገግ ብለው "እንዲያ ነው ልጅ። እንዲያ ነው። ሚጠየቅ ያደርጋል ሊቅ። ጎበዝ ልጅ! ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቃለህ?" ብለው መልሰው ጠየቁት። "ጉንዳኖች ውሃ ሲሻገሩ አይተህ ታውቅ ከሆነ በውሃው ላይ ተያይዘው ተያይዘው ይቆማሉ። ጉንዳኖች ተያይዘው በወንዝ ላይ በሚሠሩት መንገድ ሌሎች ብዙ ጉንዳኖች ይሻገራሉ። ተያይዘው ይሻገራሉ። ተደጋግፈው አስፈሪውን ወንዝ ይሻገሩታል። ባይያያዙና ባይደጋገፉ ግን አይቻላቸውም። አንዲት ጠብታ ዝናብ ለአንድ ጉንዳን ውቅያኖስ ብትሆንም ብዙ ጉንዳኖች አንድ ላይ ከተያያዙ ግን ውቅያኖስ መሻገር ይችላሉ። በመሆኑም ዴርቶጋዳ ማለት....." እስከዚህ የነገሩትን ነግሮት ሌላውን ግን ሊነግረው አልፈለገም። ይህን አሰ ብቻ ሊያውቀው የሚፈልገው ጉዳይ ነው።

"ትርጉሙን ሲነግሩኝ በትክክል አላዳመጥኳቸውም መሰለኝ። ትኩረቴ..... አዩህ..... የመሰለኝ የትምህርት መድሃኒት ነበር። ብዙ ነገር የማወቅ ጉጉት ስለነበረኝ መማር ነበር የዛ ወቅት ታላቁ ፍላጎቴ። ለረጅም አመታትም አእምሮዬ ንቅሳቱን በመድኃኒትነት ተቀብሎት ነበር። ልዩ ኃይል አእምሮዬ ውስጥ እንደሚሰራ በማመኔ በራስ መተማመኔን ከፍ አድርጎልኛል። ሁሉን ነገር ማድረግ እችላለሁ ለማለት አዳፊር ነበር። በውስጤ አንድ አጋዥ ኃይል አለ ብዬ በማመኔም በትምህርቱ አለም የተሳካልኝ ሰው እንድሆን አድርጎልኛል። ከባህር ዳር ፓሊቴክኒክ ኮሌጅ ከዲፕሎማ ተነስቼ ያለ ማጋነን ለሳተርን.....ለመሬት ... ለማርስና

ለጁፒተር ፕላኔቶች ምርምር የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ ለመሆን ችያለሁ። ታላቅ የዳበረ ሥነ ልቦናም ነበረኝ።"

"አሁንም በዚህ ኃይል ታምናለህ?" ዶ/ር ሚራዥ ተገረመ።

"ማመንም አለማመንም አልችልም አሁን። በዚህ ጉዳይ ያደረኩት ሳይንሳዊ ጥናት የለም። በደፈናው ይዤ ነገር ውሸት ነው ማለት ደግሞ ኢሳይንሳዊ ነው። ያረጋገጥኩት ነገር እስከ አሁን የለም። ሥነ - ልቦናዊ ተፅዕኖው ግን ቀላል አልነበረም።" ኢንጂነር ሻጊዝ አለቃ አያሌው ከጀርባው የነቀሱትን ንቅሳት በመስታወት ካልሆነ በቀር ዞሮ ማየት ስለማይቻል ከ1960ዎቹ ወዲህ ብዙም ትኩረት ሰጥቶት አያውቅም። ረስቶታል ማለት ግን አይቻልም።

'ድግምት አሰርቶ ነው ጎበዝ ተማሪ የሆነው' ላለመባል ብዙ ጊዜ ጀርባውን ለማንም አያሳይም ነበር። እርሱ ግን ‹እኔ በተፈጥሮዬም ጎበዝ ነኝ። ይህ ንቅሳት በርግጥ ልዩ ኃይል ሊያጎናፅፈኝ ይችላል። ሰይጣናዊ ግን ሊሆን አይችልም። ሰይጣን እንዴት እውቀትን ሊገልፅልኝ ይችላል? ሰይጣን የሰውን ልጅ ትንሣኤና ስልጣኔ የሚደግፍ ከሆነ ሰይጣንነቱ ምን ላይ ነው? አእምሮን ብሩህ አድርጎ የሰዎችን የማስታወስ ችሎታ የሚያበለፅግ ሰይጣን ካለ እሱ እንዴት ጠላቴ ሊሆን ይችላል? ይልቅስ ጥበብ የእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ጥበቡን ጥበብን ለሚፈልጉት ያድላል። አለቃ አያሌው ደግሞ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሰው ናቸው። እሳቸው የበይጣን ወዳጅ ከሆኑማ እኛ ሰይጣኖች ነን ማለት ነው። ሰው መጠበብ ሲያቅተው ጥበበኞችን ያጥላላል። ክፉ ስምም ይቀባል። ጠንቋይ ይላል። የኛ ሀገር ጥበበኞች ጠንቋይ እየተባሉ ቢወገዙ የፈረንሳይ ብልጣ ብልጦች የኛን ሀገር የጥበብ መሣሕፍት ወስደው በላቦራቶሪ ፈትሸው ዶ/ር ይባላሉ። ሰው መደንቆር ሲጀምር ጆሮውን ትርፍ ጎላ ይላል። ቢሆንም ሰው በራሱ ምስሪ ነው። እግዚአብሔር እኔን ለድንቁርና አልፈጠረኝም። አለቃ አያሌው በንቅሳት አእምሮ የሚከፍቱውን መድኃኒት ባይነቅሱኝም እኔ ብሩህ አእምሮ የተሰጠኝ ሰው ነኝ። አለቃ አያሌው ይህን ያደረጉልኝ ስለሚወዱኝ ነው። ሰው መደንቆር ሲጀምር ወሬኛና ሁሉንም ነገር ተቺ ይሆናል። ወሪያም ሁሉ!" ይላል ስለንቅሳቱ ሲያስብ። መልሶ ደሞ " ምን ይሆን?" ይላል።

ዶ/ር ሚራዥ ከኢንጂነር ሻጊዝ ጀርባ ላይ ያለውን ንቅሳት ያየው ቀዶ ጥገናውን በሚደረግለት ወቅት ነበር። በጊዜው ልዩ ስሜት ተሰምቶታል። ንቅሳቱን ሲያይ። ረጅም ሰአታት የወሰደው የኢንጂነሩ የልብ ቀዶ ጥገና ከመጀመሩ ከአንድ ደቂቃ በፊት ለምርምራ የቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ ላይ ሲያገላብጠው ነበር ከጀርባው ላይ ካለው ንቅሳት ጋር የተፋጠጠው። ቀዶ ጥገናው ካለቀ በኋላም ስለንቅሳቱ ሲያስብ ነበር። ኢንጂነሩ ከሰመመኑ ሙሉ በሙሉ ነቅቶ እስኪያናግረው ትዕግስቱ ቢያልቅም መጠበቅ ግን ግዴታው ሆኖ

ነበር። አሁን ከኢንጂነሩ ጋር ስለዚህ ጉዳይ መነጋገር ከመጀመሩ በጥቂት ቆይታ ውስጥ መግባባታቸው ስለ ንቅሳቱ ለሚጠይቀው ማንኛውም ጥያቄ መልስ እንደሚሰጠው ተሰፋ አድርጓል። ከኢንጂነሩ ጀርባ ላይ ያለው "ዴርቶጋዳ" የሚለው የቆየ ንቅሳት ደብዘዝ ቢልም በደንብ ይለያል። ከጀርባው በኩል ትንሽ ገልበጥ አድርጎ ንቅሳቱን በደምብ ተመለከተው።

"ዴርቶጋዳ" ከሚለው የንቅሳቱ ጽሁፍ መሀል ያለው ‹ቶ› ፊደል በባለ ጉጥ መስቀል ቅርፅ የተሠራ ነው። በ‹ቶ› ፊደል የአናት ቀለበት ውስጥ በቀጭኑ የተባፉ ቁጥሮች ይታያሉ። 54_4 9_5 10_6 29_{23} 77_5 30_{456} 52_7 33_2 ⁇ ⁇ ⁇ 97_5 ከሚለው ትንሽና ትልቅ ሆኖ ከተባፊው ቁጥር ቀጥሎ ' "ኦርያ ኢትዮጵያ" የሚል በቀጭኑ የተቀረፀ ቃል አለ። ከዚሁ ቀለበት ውስጥም 98_{123} 9_6 10_{67} 40_{567} 88_{123456} የሚል ቁጥር ይታያል። ከባለ ጉጡ መስቀል መስቀልያ ላይ "ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ" የሚል ቃል የተቀረፀበት ሲሆን በክንፍና በክንፉ መጨረሻ የአበባ ዕምቡጥ ከሚመስሉት የመስቀሉ ጫፎች ላይ "ቀጠሮ ቃል" እና "መራራ ክንፍ" የሚሉና ግራ የሚያጋቡ ቃላት ሰፍረዋል። ከታች ከመስቀሉ ግርጌ ደግሞ ቁልፍ ይመስላል። ሞልህቅ ከሚመስለው ጫፍ ሥር ደሞ "ዴርቶጋዳ" ይላል።

‹‹የእነዚህን ቃላት ትርጉም አላውቅም ነው የምትለኝ ታዲያ ኢንጂነር ሻጊዝ?›› ሚራዥ ተደምሟል፡

"የጥንት ወፍ ጠባቂዎች፣ እረኞች ሰብላቸውን የሚያወድም ግሪሳ አዝመራቸው ላይ ሲያርፍ በወንጭፍ ድንጋይ ከመወርወራቸው በፊት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ‹ኦርያ!› ይሉታል። ድምፃቸውን ሰምቶ ያልተነሳውን ተባይ ይወነጭፉበታል። በድንጋይም ክንፉን ይሰብሩታል። ስለሆነም ኦርያ ኢትዮጵያ ማለት 'የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ' የሚል የማስጠንቀቂያ ቃል ነው። ‹ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ› የሚለው ደግሞ **‹ምርኮ ፈጠነ ብዝበዛ ቸኮለ!›** ማለት ነው። ኦርያ! ...ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ..... የኢትዮጵያ ተባዮች ተነሱ.... ምርኮ ፈጥኗል...ብዝበዛ ቸኩሏል። ማለት ነው።...ይህ ለምን እኔ ጀርባ ላይ ተነቀሰ? መልሴ አላውቅም ነው። ግን ለምን ይህን ያህል ትኩረት ሰጠኸው? ከዚህ የበለጠ በንቅሣት የሚዥጎረጎሩ ሰዎች በሞሉበት አሜርካ ውስጥ ተቀምጠህ የእኔ የደበዘዘ ቅንሣት እንዴት ይህን ያህል ሳበህ?" ሲል መልሶ ጠየቀው ሻጊዝ።

"የገረመኝ ይዜ አይደል!" አለ ዶ/ር ሚራዥ። "ካንተ ጀርባ ላይ ያለው ንቅሣት በተመሳሳይ መልኩ እኔ ጀርባ ላይም አለ። ተመልከት!" ነጭ ጋወኑን እና ሸሚዙን አውልቆ ጀርባውን አዞረለት። ሻጊዝ በመገረም የሚራዥን ተመሣሣይ ንቅሣት ከጀርባው ላይ አነበበው። "ዴርቶጋዳ...ኦርያ ኢትዮጵያ...ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ።"

"እንዴት ተመሳሳይ ነገር ሊኖረን ቻለ?"

"ከአሁን ቀደም እንተዋወቅ ነበር?" አለ ኢንጂነር ሻጊዝ።

"በፍፁም ከአሁን ቀደም የጋራ ምስጢር እስኪኖረን ድረስ ልንተዋወቅ አንችልም። በፍፁም። በተለያዩ አለማት የኖርን ሰዎች ነን። እኔ ቅድም እንደነገርኩህ የማውቅህ ባነበብኩትና በሰማሁት ነው። በአካል ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁህ ከቀናት በፊት ይህን ቀዶ ጥገና ሳደርግልህ ነው። ከዚህ በተረፈ ግን እኔና አንተን ሊያገናኝን የሚችል አንዳችም መንገድ አልነበረም። አንዳችም መስመር!"

"የት ነው ተወልደህ ያደከው?"

"የተወለድኩበትን አላውቅም። ያደኩት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ጣና ሐይቅ ውስጥ በሚገኝ አንድ ደሴት ላይ።"

"ጣና ሐይቅ ውስጥ ..... የትኛው ደሴት ላይ?"

"ክብራን ደሴት ላይ። ከባህር ዳር ከተማ በጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀው ጣና ሐይቅ ውስጥ ከሚገኙት እንጦንስና ክብራን በመባል በሚታወቁት መንታ ደሴቶች ላይ ነው ያደኩት። እስክጎረምስ የሴቶች ገዳም በሆነው በእንጦንስ ደሴት...ከጎረመስኩ በኋላ ደግሞ የወንዶች ገዳም በሆነው በክብራን ደሴት ላይ ነው ያደኩት አንተ ደግሞ ከፋ!.....ምን አገናኘንን?" አለ ዶ/ር ሚራኾር።

ወዲያው በሩ በኃይል ተበርግዶ ሶስት ሰዎች ወደ ክፍሉ ተንደርድረው ገቡ። ሁለቱ ነጭ ጋወን የለበሱ ዶክተሮች ሲሆኑ የእንደኛው ማንነት ግን አይታወቅም።

"ዳይሬክተሩ በአስቸኳይ ይፈልጉሃል ዶ/ር ሚራኾር?" አለው አንደኛው ዶክተር። "ባስቸኳይ!" ከዚህ ቀደም አይቶት የማያውቀው ሰውዬ ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጣቸውንና የኢንጂነር ሻጊዝን የህክምና መረጃ የያዙትን ወረቀቶች ላፕቶፕ ኮምፒውተሩንም አንስቶ ሊወጣ ሲል ሚራኾር ጎትቶ ወለሉ ላይ ዘረገፈው። ሰውዬው በፍጥነት ተነስቶ ፈገግ አለ በደረቁ። "ቀዩ መስመር ውስጥ ከገባህ ቆይተሀል።" ሽጉጡን መኾርጦ ከሚራኾር ጭንቅላት ላይ አነጣጠረበት። "ቀጥል!.....ዲቃላ!"

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በሩን በርግደው ተከታትለው ሲገቡ ጭንቅላቱ ላይ የደቀነውን ሽጉጥ ምላጭ ሳበው። ከተቀመጠበት ወንበር ጀርባ ያለው ነጭ ግድግዳ በደመ- ፍጥጣቂ ተጨማለቀ። በጢስ በታፈነው ላሉን ውስጥ እየተጨናበሱና እያሳሉ አይተው ራሱን ባጠፋው ደህንነት በድን ላይ በብሽቀት ጥይት አርከፈከፉበት። አንደኛው ደህንነት ያገኘውን እቃ እየጠለዘ ሲበሳጭ አንደኛው ደግሞ የሰነዱን አመድ ዘግኖ በብሽቀት ሳቀ። በመጨረሻ ከጻፈው አንድ ቃል በስተቀር አንዳችም መረጃ አላስቀረም።.....ሁለቱም ብጣቂው ፅሁፍ ላይ አፈጠጡ።.....«ዶርቶጋዳ?.....ምን!?».....ተያዩ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሚራኾር የህክምና ክፍሉን ለቆ ወጥቶ ወደ ዳይሬክተሩ ቢሮ ከመሄዱ

በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ኢንጂነር ሻጊዝን ፍዝዝ ብሎ ተመለከተው። ሻጊዝም ሚራኾን በዓይኑ አነጋገረው። በቀዶ ህክምናው ክፍል ውስጥ የተተከሉት ስውር ካሜራዎች የሚቀርፁትን ምስልና ድምፅ ኮምፒውተራቸው ላይ የሚከታተሉት የሆስፒታሉ ዳይሬክተር ዶ/ር ሚራኾርና ኢንጂነር ሻጊዝ የተነጋገሩአቸውን የአማርኛ ቃላት ወደ እንግሊዘኛ የሚተረጉመውን ማሽን የዘጉት ዶ/ር ሚራኾር ወደ ቢሮአቸው ሲገባ ብቻ ነበር። ምንም ቃል ሳይተነፍሱ አንድ ገፅ ወረቀት ጠረጴዛው ላይ አንስተው ለዶ/ር ሚራኾር ሰጡት። ከሥራ መባረሩን የሚገልፅ። "ለምን?" አለ ዶ/ር ሚራኾር። ምንም ምላሽ አልሰጡትም ዳይሬክተሩ። "ውጣልኝ አሁን ሥራ ላይ ነኝ።"

፪

ቴልአቪቭ : እስራኤል

"በውድ ዋጋ ነው አይደል የተገረዝሽው?" አላት አይናቹን አጥበ እየተጠጋት። ሊለምናት ቢኖርም ፍንክች ብላለት አታውቅም።

"አትጠጋኝ" አለችው ውስጧ እያረረ።

"በእውነት ያንቺን ያህል እግዚአብሔርን ብለምነው ሶስት መቶ ሚስቶች ሰጥቶ ሰማኒያ አቁባቶች ይመርቀኝ ነበር" አሁንም እየተጠጋት።

"አትጠጋኝ" አለችው አሁንም ወደኋላ እያፈገፈገች። ቋጥኝ የሚያክል ራሱን እንደ ክር የቀጠነ አንገቱ እስኪቀነጠስ በአሉታ ወዘወዘው። የበለጠ ዓይኑን እያጠበበ ተጠጋት። ቤቷ ውስጥ ባይሆን ኖሮ የያዘችውን የብርጭቆ ውሃ ላዩ ላይ ከልሳበት ባስወጣችው ነበር። ደግሞም አብረው የሚያከናውኑት አንድ የጋራ ጉዳይ አላቸው ።

"ደጋግሜ እንደነገርኩህ አጉል ጊዜህን ባታባክን ይሻላል" ንዴቷን ከውሃው ጋር እየዋጠች ዝም አለችው።

ደረቷ ላይ ተጠጋግተው ከተወጠሩትና ቀጥ ቀጥ ብለው እንደ አምባ ተራራ የቆሙ ጡቶቿ ላይ አይኖቹን ተክሎ በምላሱ ከንፈሩን አረጠበ። በጧት በመምጣቱና የሚቋምጥለት አካሏን በውስጥ ልብስ በማየቱ በጧቱ የቀሰቀሰውን መልአክ አመሰገነው። ተራራ የሚያክል ራሱን እንደ ክር በቀጠነ አንገቱ ላይ አንጠልጥሎ ያቀረቀረ መሰለና ገላዋን ወደ ላይ በደፈረሰ ጥቃቅን ዓይኖቹ እንደ ሽንኩርት መላጥ ጀመረ። እንደ ወርቅ የሚያንፀባርቁ የአግር ጥፍሮቿን ቃኝቶ ሽቅብ ቃተተ። የውስጥ ገላዋን በሚያሳይ ነጭ ስስ የሌሊት ልብሷ ውስጥ የቆመለትን ማራኪ ገላዋን በዓይኖቹ ሽቅብ ሲጠባ ፊት ለፊት ገጥመው የሴትነት መለያዋን የሸፈኑ ጭኖቿ ጠሩት። ‹መሀላችን ግባ ዘግተን የያዝነው ልዩ ዕቃ በመካከላችን አለ› አሉት። ከጎን ሰፋ ያለው ዳሌዋ ከቀጭን ወገቧ ሥር ውሏል። የተቀነበበ እምብርቷን አልፎ ደረቷ አልበቃቸው እንዳለ ተጠጋግተው የተከፈሉ ትላልቅ ጡቶቿ ከአድማስ ጥግ እንደሚታዩ ተራሮች አልታሰፍ አሉት። ከመቃ አንገቷ ላይ የማይለየውንና በትልቅ ሀብል ያሰረችውን በ‹ቶ› ቅርፅ የተሠራ ባለጉጥ ግማደ መስቀል ላይ ሲደርስም ይጥገበኝ ብላ

የቆመች ይመስል ስታየው ቆይታ ፈገግ አለች። የጎመራ የወይን ፍሬ የሚመስሉ ከንፍሮቿ መሀል ችምችም ያሉ ነጫጭ ገዳይ ጥርሶቿን እንደምንም ሲያልፍ የወሲብን ቆሌ የሚጠሩ አይኖቿ ጋር ተጋጭቶ ቆመ። አይታት የማያውቅ አዲስ ፍጡር አዲስ መስላ ታየችው። ቡዝዝ....ፍዝዝ አንዳለ በማያውቀው ኃይል ተገፍትሮ ከንፈሯ ላይ ሲያሳርፍ የላከው ከንፈሩ በፍጥነት ፊቷን ስታዞር ጆሮ ግንዷ ላይ አረፈ። ወዲያው በአይበሉባዋ የሚያቃጥል ጥፊ ስታሳርፍበት ወደኋላ ተንገዳግዶ ቆመ።

የማይታገላት አደገኛ ሴት ሆነችበት እንጂ ከጭኖችዋ መሀል ገብቶ ለዓመታት የቋመጠለትን ሲሳይ በግዳጅም ቢሆን ሊቋደስ ልቡ ቆርጦ ነበር። ግን ብዙዎችን ያንበረከከችና የሞሳድ ባልደረቦቿ ‹‹አቦ ሽማኔዋ›› እያሉ የሚያመካሹአት ሲጓራ ናት።

ለእስራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ በአባልነት የመለመላትም የህክምና ምርመራዋን የሰራውም ራሱ ነው። ከሁሉም በፊት ያጠመደው ውበቷ። እሱም ውበቷንና እሷን ማጥመድ ጀመረ። ዛሬ ደግሞ ለጋራ የሚያጠምዱት ወጥመድ አላቸው። የእስራኤልን አንድ ወጥመድ በጋራ አጥምደው አሸክላቸው ውስጥ የሚገባውን ታዳኝ አንቀው ለእስራኤል መስጠት አለባቸው። ይህ ተልእኮ የወደቀው በነዚህ ሁለት አይሁዶች ጫንቃ ላይ ነው።

ሲጓራ አናንያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየችው ‹‹ዘመቻ ሙሴ›› በተሰኘው እስራኤል የኢትዮጵያ ፈላሻዎችን በሱዳን በኩል አስኮብልላ ወደ እስራኤል በወሰደችበት ጊዜ ነው።

ዶ/ር አናንያ ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሮ የሞሳድ የህክምና ክፍል አባልና ተመራማሪ ሆኖ ሲሰራ አንድም ቀን ስለፍቅሩና ስለግል ህይወቱ መደላደል አስቦ አያውቅም። የፅዮናዊነት መዝሙር ሲያዜም አደገ። አይሁድነት በደሙ ውስጥ ሲዘዋወር ኖረ። የዘወትር ንግግሩ ማሳረጊያ "እስራኤል ለዘለአለም ትኑር!" ሆነ። ሲጓራን ካያት ጊዜ ጀምሮ የግሉ እንደምትሆን እርግጠኛ ሆኖ ኑሮ ነበር። በተለይ በዚህ ወቅት ፍላጎቱ ንሮበታል። አማላይ ገላዋ አቅበዝብዞታል።

ጥፊውን ወደ ውስጡ ውጦ በቀጭን አንገቱ ቋጥኝ የሚያክል ራሱን ከግራ ወደቀኝ ቀጫጭ አድርጎ በተለሳለሰ መንፈስ ልመናውን እንደገና ሊጀምር ሲል"አናንያ! እኔና አንተ የተወከልነው ለሀገራዊ ተልእኮ ብቻ ነው። ደግሞ ብቻዬንም ቢሆን እንደምወጣው ታውቃለህ። እመነኝ ....የከፈልኩትን ያህል መስዋዕትነት ከፍዬ ኢንጂነር ሻጊዝን አንቂ ለእስራኤል አስረክባታለሁ። እንዲያውም አንተ የመጀመሪያውንና ተገቢውን ሥራ ሰርተህ ጨርሰሃል። የቀረውን ለእኔ ተወው" እያለለችው ነው። ዶ/ር አናንያ ግን በዚህ ኦፕሬሽን ምክንያት ከእሷ ጋር አብሮ በመሳተፉ ግንኙነታቸውን

ተጠቅሞ የግሉ ሊያረጋት ወስኗል። ደሞም ሲበዛ አልከኛ ነው። እስከመጨረሻው ታግሷት ክንዱ ውስጥ ሊያስገባት ቆርጧል።

ጎትታ ወደ አንዲት ጠባብ ክፍል ይዛው ገባች። በካርታዎችና በፎቶዎች ከተሞላችው ክፍል ውስጥ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን አንደኛውን ትልቅ ፎቶ ጠቆመችው። እንደ ልጃገረድ ጡት የተቀሰሩ ሁለት መንታ ደሴቶች በሐይቁ ላይ ይታያሉ።

"እነዚህ ደሴቶች በኢትዮጵያ የጣና ሐይቅ ላይ የሚገኙ ክብራንና እንጦንስ የሚባሉ ደሴቶች ናቸው። እኔ የሴቶች ገዳም በሆነችው በእንጦንስ ደሴት እሱ ደግሞ የወንዶች ገዳም በሆነው በክብራን ነው ያደግነው" አለች ከሁለቱ መንታ ደሴቶች ፎቶ ላይ ዓይኖችዋን ተክላ። ከማትፈልገው ትዝታ ውስጥ ሊዘፍቃት አዕምሮዋ ወደኋላ በፍጥነት ፈጠነባት። "እሱ ነው የልጅነት ፍቅሬ። መቼም ቢሆን የማልረሳው። ሞቼ እንደገና ብፈጠር እንኳ አብሮኝ የሚፈጠረው። ሚ.... ራ! ሚራኾር"

አእምሮዋ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ወደ ኋላ ሸመጠጠባት። ልጓም አልባ ፈረስ ሆኖ ወደ ደሴቶቹ ጋለበባት። የትዝታዋ ፈረስ ከቱልአቪቭ ተነስቶ እየሰገረ ቀይ ባህርን አቋርጦ ከመካከለኛው የኢትዮጵያ መልአክ ምድር መሃል ከታላቁ የጣና ሐይቅ እምብርት ውስጥ ከሁለቱ ደሴቶች መሀል ወስዶ ዘፈቃት።

በጣና ሐይቅ ላይ አርባ ያህል ደሴቶች አሉ። በሃያ ያህሉ ደሴቶች በውድ ቅርሶች የታጨቁ ገዳማትና አድባራት ሲገኙም በሃያዎቹ ግን ከአሞራዎች በቀር ማንም አይኖርባቸውም። ሲጻራ በትዝታ አውታር ተስባ በመካከላቸው የሰጠመችባቸው ክብራንና እንጦንስ ከባህር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በማራኪ ተፈጥሮአዊ ደን የተሸፈኑት ኮረብታማዎቹ መንትያ ደሴቶች መካከል ያለው ርቀት በጣም አጭር ከመሆኑም በላይ በመካከላቸው ያለው መስተጋብር የጠበቀ ነው። ለሴቶች ገዳም ሥርዓተ ቅዳሴ ለማድረስ መነኮሳት የሚመጡት ከወንዶች ገዳም ነው። ሴቶች ግን ለምንም አገልግሎት ወደ ወንዶች ገዳም አይሄዱም። ውንዝ ነው። "ለሴቶች ማለፍ፡ የተከለከለ ነው" የሚል በጥቁር ቀለም የተፃፈ ማስጠንቀቂያ ገና ከደሴቱ መግቢያ ላይ አለ።

ሲጻራ ግን ወደዚህ የወንዶች ገዳም ደሴት የምትገባበት ጉዳይ ነበራት። አካሏ ቢከለከልም ልቧ ወደ ወንዶች ገዳም ገብታ ፍቅሯን ከደሴቱ መቧጠጥዋ አልቀረም። ደሴቱን በፍቅር ዓይኗ ማየት የጀመረችውም ሚራኾን ካፈቀረች ጊዜ ወዲህ ነበር። «ለምን ግን እንድገባ አይፈቅዱልኝም? እዚሁ አደደል በንፅህና ያደኩት? ለምን እኔንም እንደ ሌላው ሴት ይከለክሉኛል?.....የማልፈልገውን ግን አይከለክሉኝም! ....ወይ ልቤ ሞኙ ለምንድነው ግን የከለከሉትን አጥብቆ የሚፈልግ? ባይከለክሉኝ ይሻል ነበር አለዚያ የሚከለክሉኝ

የበለጠ እንድፈልገው ያደርጉኛል። እኔ እምፈልገው ሁሉ ያለው ደግሞ ከተከለከልኩት ነገሮች ውስጥ ነው.....» ትል ነበር ዘወትር ለብቻዋ ስትሆን።

ሲጻራ ወደ ሴቶች ገዳም የገባችው ገና በሶስት አመቷ ነበር። ወደዚች ደሴት አምጥተው ለሴት መናንያኑ ያስረከቧት ከመንትያዎቹ ደሴቶች በጣም ርቆ በሚገኘውና ዳጋ አስጢፋኖስ በሚባለው የወንዶች ገዳም ውስጥ የሚኖሩት አባ ፊንሐስ ነበሩ። አባ ፊንሐስ ለሴት መናንያኑ ሲያስረክቧት ተጥላ አገኘኋት ብለው ቢሆንም ወላጅ አባቷ ናቸው የሚባል ጭምጭምታም ይሰማ ነበር። ነበር። በድሜ ከፍ እያለች እውነትም ስትመጣ አባ ፊንሐስን እጅመሰለች መጣች።

ሲጻራ ወደሴቶች ገዳም በገባችበት ወቅት በሴት መናንያኑ እንክብካቤ የሚያድግ በሁለት አመት የሚበልጣት ወንድ ህፃን ነበር። የገዳሙ ማህበር ተሰባስበው «አብረው ይደጉ። አብረው መዋላቸው ለሁለቱም ሥነ-ልቦና ይጠቅማል። በዚያውም ግብረ ሕፃናትን ይለማመዱ" ተብሎ በመወሰኑ አብረው ማደግ ጀመሩ።

ህፃኑ ሚራኾርም ከየት እንደመጣ አይታወቅም። አባ ዝገንበሩ የሚባሉ መነኩሴ እመንገደ ተጥሎ አገኘሁት ብለው ነበር ወደ ሴቶች ገዳም ያመጡት። "እኛም ከየት እንደመጣን አናውቅም። ከየትም ይምጣ ከየት ዋናው የሰው ልጅ መሆኑ ነው። አንዱ እግዚአብሔር ፈጥሮታል። በዝሙትም ይወለድ በጋብቻ ወንጀለኞች ወልደው የጣሉት እንጂ ተጥሎ የተገኘው ልጅ አይደለም። በቤቱ ውስጥ ያድግ ዘንድ አምላክ ሲጠራው እኛ ወደየት እንጥለዋለን?" ብለው ነበር የሴቶች ገዳም አመምኔት አማሆይ ወለተ ኪሮስ አቅፈው ያሳደጉት።

ሚራኾን አማሆይ ወለተ ኪሮስ ፀሎት ሲያደርሱም ሆነ ሲሰግዱ አቅፈውት ነው። መሬትላይ ያስቀመጡት እንደሆነ ወይባ የሚባለውን የምነና ልብሳቸውን ጨምድዶ እንደጠጣ እየተንጠላጠለ አላያቸው ላይ ይወጣል። ቦኋላ አባ ፊንሐስ ሲጻራን ይዘው የመጡ ጊዜ እሷን እንደጉድ ትክ ብሎ እየተመለከተና እየነካካ አብሯት መጫወት ሲጀምር አማሆይ ወለተ ኪሮስን ረሳቸው። ሲጻራም ዝምተኛው ሚራኾን እንደ አሻንጉሊት እየነካካች ከሱ ጋር በመጫወት አብረው በትንሿ ደሴት ላይ ድክድክ እያሉ አደጉ።

ሚራኾርና ሲጻራ ባንድ ላይ ፊደል ቆጥረው የዘወትር ፀሎትን፣ ውዳሴ ማርያምንና ዜማን....በሴሊት፣ ወንጌላትንና መዝሙረ ዳዊትን፣ ከመፅሐፍ ቅዱስም ብሉያትንና ሐዲሳትን እየተማሩ ወደላቀ ደረጃ ተሸጋገሩ። ቀን ቀን እየመጡ ዋርካው ሥር ከማያስተምሩአቸው አባ ዝገንበሩ ከሚባሉትና ሚራኾርን ካመጡት መነኩሴ ቅኔም ቆጠሩ።

ሚራኾ ከህነት ተሰጥቶት ቤተ መቅደስ ገብቶ መቀደስ ጀመረ። ሲጻራ ግን ሲያምራት ቀረ። ሲጻራ በንዴት ብትቃጠልም ብቻዋን ከማጉረምረም አልፋ ለማንም አልተናገረችም። «ለፍቼ ለፍቼ ... በሌሊት እንቅልፌን እያቋረጥኩ ተምሬ እንዲህ ጉድ ይሰሩኝ?....ቆይ...እመብርሃን ድንግል ማርያም ሴት አይደለች? በቤተ መቅደስ ውስጥ አይደለም ያደገችው? .....ወይ ፈጣሪዬ ይቅር በለኝ! ...እኔ ደካማዋ ጌታ ኢየሱስን ከወለደችው ከእመብርሃን ጋር ራሴን ስላስተካከልኩ ይቅር በለኝ! ላያስገቡኝ ዝም ብዬ ነው የምወሸክት። ፈጣሪዬ ....ግን እኮ በመቅደሱ ውስጥ ላገለግልህ በመፈለጌ ነው። ምን ሐጢአት አለው እስኪ? እሃ.....ለካ አመቤታችን በቤተ መቅደስ የቆየችው አሥራ አምስት አመት እስኪሞላት ነው። እኔም ለካ አስራ አምስት አመት ሞላኝ። ይቅር በለኝ አምላኬ አስራ አምስት ሞልቶኝ ቤተ መቅደስ ለመግባት በመመኘቴ። ውይ! ይቅርታ» ደረቷ ላይ ያጎጠጎጡ ጡቶቿን ስታያቸው ታላቅ ሀጢአት እንደሰራች ጉብጥ ትላለች አፍራ..... ልትደብቅ። በለበሰችው ወይባ አቡጀዲ ሽፍንፍን አድርጋ ምኞቷን ሁሉ ዋጠችው ።

ጡቶቿ ከደረቷ የበለጠ አፈንግጠው ስላጋለጧት አፈረችባቸው። አሸቻቸው እንደሎሚ ሎክሎክው የሚጠፋ መስሏት። የውስጣቸው እንቁር እያመማትም ፈተገቻቸው። እንደ ቡግንጅ ፈርጠው ወይም እንደ ጀሮ ደግፍ ሚሙተው ከደረቷ እንዲጠፉ ተሳለች። ነገር ግን የበለጠ እያሞጠሞጡ እያጎጠጎጡ ቅል ቅል አከሉባት። ውበቱ እንዲጠፋ አፈር በሚመስል ቀለም ተነክሮ በተቀለመ መነኮሳቱ ሁሉ በሚለብሱት ልብስ በመሸፈኑ የዳሌዋ መሞናደል ከአሷ በቀር ማንንም አላሳሰበም። ግን ይሞቃታል። የማታውቀው ስሜት ይወሰውሳታል። ሰውነቷ ሲሞቃት በፀሎትና በስግደት ለመቅጣት ከተፈጥሮ ጋር ውጊያትጀምራለች። ግን አላሸነፈችም። እየፆመች እየራባትም ዳሌዋ ወደኋላ ጡቷ ወደፊት ይጎትታታል። ልቧም ሚራኾን ሲያይ ከበሮውን መደለቅ ጀምሯል።

በዚህ ወቅት በሁለቱም ገዳማት ማህበራት አንድ ትዕዛዝ ወጣ። "ልጆቹ ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ስለደረሱ አብረው እንዳይውሉ" የሚል። ሚራኾ ወደ ወንዶች ገዳም ወደ ክብራን ተወሰደ። የህፃንነቷን ጊዜ ናፈቀች። ከሚራኾ ጋር መዋል ቀርቶ አብራ ቆማ እንኳ ማውራት አትችልም። የአድሜዋ እኩያ ካለእሱ ማንም የለም። ዘወር ስትል የምታየው የጨረጨሱ አሮጊቶችን ቀና ስትል የጠራ ሰማይን ስታቀረቅር የጣና ሐይቅን ነው። ከዚህም ካለፈ በጥቋቁር ፍራ የጠመመውን የጣና ዳር የደቅማ ዛፎች። ወይም የማይናገሩና የማያዩ ዓይናማ አለቶችን።

በተለይ ስለ ሚራኾ የምትሰማው ፍቅሯን የበለጠ አጋጋመው። በአሮጊቶች አፍ ብዙ ይወራለታል። ከሁሉም አማሆይ ወለተ ኪሮስ ድሮም ስለሚወዱት ከአፋቸው አይለዩትም።

ከሚራኾ ጋር መገናኘት ያልቻለችባቸው ጊዜያት ረዘመ። የማይመሹ ቀኖች፣ የማይነጉ ሌሊቶች አሰቃዩአት። ተረኛ ሆኖ ለአገልግሎት ወደ ሴቶች ገዳም መጥቶ ሲቀድስና ኪዳን ሲያደርስ ብቻ ነበር በቅርብ ርቀት የምታየው። አብረው እንዳያወሩም ክህነቱን እንዳታስፈርሰው ሲባል ‹እንዳታሰናክይው› ተብላለች። ከሐሜትና ከሰይጣን ፈተናም ለመራቅ ጭምር ሲሉ ቢገናኙ እንኳ ሰላም አይባባሉም። "ሁሁ! ለምን አሰናክለዋለሁ! .....ግን ምኑ መንፈስ ነው ወደሱ የሚጎትተኝ? ለምንድነው ሰውነቴ የሚፈትነኝ? ለምንድነው ነፍሴ እሱን የምትጠማው? ርኩስ መንፈስ ይሆን እንዲህ የሚያደርገኝ! አዎ ዲያብሎስ እየተፈታተነኝ ነው። ሳጥናኤል አሸክላውን እያጠመደብኝ ነው። መቼስ ሰይጣን ጓዙን ጠቅሎ ገዳም ውስጥ አይደል የሰፈረው? በዓለም ማንን ሊፈትን? በዓለማማ ሁሉስ በሐጢአት የወደቀ አይደል! ማንን ይፈትናል? ሁሉስ ሳይፈተን የወደቀ አይደል! እዚህ ነው እንጂ ገዳም ውስጥ ሰይጣን ጦርነት ያሰበት። መቼስ መልካም በሌለበት ክፉ የለ! .....ቢኖርስ መኖሩ በምን ይታወቃል? ሰይጣንስ መንፈስ ቅዱስ ባለበት ከሌለ መኖሩ በምን ይረጋገጣል። በርኩስ መንፈስና በቅዱስ መንፈስ መካከል ብዋከብስ እኔ ማነኝ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ የተፈተነው በቆርንቶስ ተራራ ገዳም አርባ ቀን ሲፀልይ በሄደበት ወቅት አይደል? ኢየሱስን ደፍሮ የፈተነ ሰይጣን እኔንማ ምን ጭንቁ! ይልቅስ ንቆ በተወኝ። የጋለ ገላ የሞቀ ሰውነት ይገፍ እንደኋት እቋቋመዋለሁ?..... አልችልም።እግዚአብሔር ሆይ እንዳላሰናክለው ከፊለግህ አገልጋይህን ጠብቅ። እንኳን ሰይጣን መልአክ የሚቀናበትን ልጅህን ያዝልኝ። እኔ ግን ተሸንፌአለሁ። እወደዋለሁ። ወድጀን ነው? ጥለህብኝ እንጂ!" ወዲያው ደሞ መጎልዬ መጎልይ ዘሰሎሞን የሚለውን የመዕሐፍ ቅዱስ ክፍል ትገልጣለች። "በአፉ መሳምን ይሳመኝ" ይላታል። "ፍቅርህ ከወይን ጠጅ ይልቅ መልካም ነው" የልቧን ይነግራታል።

"እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ! እኔ ጥቁር ነኝ፣ ነገር ግን ውብ ነኝ። እንደ ቄሳር ድንኳኖች እንደ ሰሎሞንም መጋረጃዎች።..... ነፍሴ የወደደችህ አንተ ንገረኝ፣ ወዴት ታሰማራለህ፣ በቀትርስ ጊዜ ወዴት ትመስጋለህ?" ይህን ስታነብ ሚራኾ መልሶ "ዘዶቅማው ጥላ ሥር በጣና ዳር ዓይናማ አለቶች ጠባብቅ እመስጋለሁ" ያላት ይመስላታል።

"ከጥላው ቢታች እጅግ ወድጄ ተቀመጥኩ፣ ፍሬውም ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው። ..... ውዴ የእኔ ነው፣ እኔም የእሱ ነኝ፣..... ውዴ ሆይ ቀኑ እስኪነፍስ ጥላውም እስኪሸሽ ድረስ

ተመለስ፤.....በቅመም ተራራ ላይ ሚዳቋውን ወይም የዋለው እምቦሳ ምሰል፡፡..... ሌሊት በምንጣፌ ላይ ነፍሴ የወደደችውን ፈለግሁት፤ፈለግሁት አላገኘሁም፡፡....." የሰሎሞን መዕሐፍ ባይኖር ኖሮ መዕሐፍ ቅዱስን አትገልጠውም ነበር፡፡

እነዚህን ጣፋጭ የፍቅር መዝሙሮች ስታነብ ሰውነቷ ይግላል፡፡ ልቧ ነጋሪቱን ይወግራል፡፡ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል፡፡ በጭኖቿ መካከል ቅዝቃዜ ይሰማታል፤ ታማትብና ራዕዩ ዮሐንስ የሚለውን የመዕሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ መዕሐፍ ታነባለች፡፡ ማብረጃዋ እሱ ነው፡፡ ራዕዩ ዮሐንስ.....ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት የፃፈው አስፈሪ መዕሐፍ ለደሴቷ ጉብል የግለቷ መቀዝቀዣ ነው፡፡ እሱ ነው የሚያበርድላት፡፡ ....የመጨረሻው ሰዓት፡፡ ....ዘንዶው፡፡.... አውሬው፡፡ "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፤ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም የነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር..." *ይህ ነው የሚያሰክንላት፡፡* የመጨረሻው ሰዓት፡፡ የአስፈሪው ጊዜ ትንቢት፡፡ ወይም ደግሞ አንቀፀ ንሥሐ የሚባለውን የንስሐ መዕሐፍ አውጥታ ታነባለች፡፡ በንስሐ አለንጋ ራሷን ትገርፋለች፡፡ ወይም ‹‹መንገደ ሰማይ›› የሚባለውን አንዲት ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ ስለምታደርገው አስፈሪ ጉዞ ታነባለች፡፡ መላእክተ ፅልመትና መላእክተ ብርሃን ነፍሷን ሲቃሙ፡፡ መላእክተ ፅልመት ሰይፋቸውን መዘው ከአጋንንቱ ጋር ሲፋለሙ ይታያታል፡፡ ትሰናከናለች፡፡ ውዳሴ ማርያም ትደግማለች፡፡ እያማተበች ትነሳለች፡፡

መልሳ ደሞ ስለ ሚራኾር ማሰላሰል ትጀምራለች፡፡ ወደሴቶች ገዳም የሚመጣው በተራ ነው፡፡ ሰሞነኛ ሲሆን ብቻ ወር ሲገባ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሳምንታት ሰሞነኛ አገልጋይ ነው፡፡ ቀሪዎቹን ሁለት ሳምንታት ደግሞ በናፍቆት እየተወቀጠች ታሳልፋቸዋለች፡፡ «እዚህኛው ደሴት ሆነሽ እዛኛው ደሴት ድረስ ተጣሪ፡ሁለት ሳምንታት ሳታይው መቆየት ለአንቺ አይቻልሽም» የሚል ሹክሹክታ ይሰማታል፡፡ ትላልቅ አይናቹን ሙዝዝ ብላ ማየት ያምራታል፡፡

አንድ ቀን ሌሊት መተኛት አቃታት፡፡ እንቅልፍ በዓይኗ አልዞር አለ፡፡ በጨለማው ድባብ ውስጥ እየተደናበረች ከደሴቷ ወደብ ወርዳ አለቱ ላይ ቁጭ አለች፡፡ የጣና ሐይቅ ማዕበል ከአለቱ ጋር ሲጋጭ በሚፈጥረው ፍንጣቂ በውሃ ስትበሰብስ እንኳ አልታወቃትም፡፡ ቆይቶም ሰማዩ በመብረቅ እየታረሰ በጉርምርምታ የታጀበ የዝናብ ዶፍ እዛ የተንጣለለ ሐይቅ ላይ ሲወርድ ከተቀመጠችበት አለት አልተነሳችም፡፡ ወደ ወንዶች ገዳም አሻግራ ማዶ ማዶ እያየየች ሌሊቱን እዛው አድራ ጠዋት የኪዳኑ ደወል እስኪደወል አለቱ ላይ ተቀምጣ አነጋች፡፡

በቀጣዩ ሌሊት በስዕለ ቅዱሳን ከተዋበች ጎጆዋ ከገባች በኋላ የመቅረዙን የዘይት ክር ለኮሰችው፡፡ ልታነብ የዘረጋችው መፅሐፍ አፉን እንደከፈተ ነበር፡፡ ራቁቷን ነጭ አቡጀዲ ከላይ የናረ ሐምራዊ ግምጃ ከሥር ከተነጠፈባት መደቧ ላይ ተኝታ መቅረዙ ላይ አፈጠጠች፡፡ ስቅስቅ ብላ ማልቀሷን ነጩ አንሶላ ላይ የነጠበው የፅንባዋ ጠብታ ነገራት፡፡ ልትፅፍለት ወሰነች የሆነውን ሁሉ፡፡ ፅሁፍ እንድትለማመድበት የመቃ ብዕርና ከተቆሉ አዝርዕትና የተቀመመ ጥቁር ቀለም ነበራት፡፡ ወረቀት ግን መፃህፍት ቤቱ ውስጥ ነበር፡፡ ‹ዛሬ መፃፍ አለብኝ....በቅጠልም ላይ ቢሆን ጭንቄን ተገላግዬ ጠዋት ከኪዳን መልስ እጠብቀዋለሁ ከዛም ሰጥቼው ሹልክ....› ወዲያው አንድ ብልሐት ተከሰተላት፡፡ ከነጩ አቡጀዴ ላይ ቀዳ መፅሐፏ ላይ አስደገፈችና በመቃ-ብዕሯ ከጥቁሩ ቀለም እየነከረች ፃፈችለት፡፡

ጠዋት....የኪዳኑ ፀሎት ረዘመባት፡፡ ትልቁ ደወል ተደውሎ የኪዳኑ ፀሎት እንደተጠናቀቀ በምሥራቁ በር ቆማ ጠበቀችው፡፡ በምስራቁ በር ሴት መቆም ይቅርና ማለፍ አይፈቀድላትም.....እሷ ግን አማራጭ አልነበራትም፡፡ የምሥራቁ በር ተከፍቶ ሚራኾር ነጭ አቡጀዲ ትዕምርተ መስቀል ተላብሶ ብቅ ሲል ወኔዋ ተነነ፡፡ በቆመችበት ተብረከረከች፡፡ ወደወንዶች ገዳም ለመሄድ በቀጭኗ መንገድ ደሴቷን መውረድ ሲጀምር ደንግዛ ቆማ በዓይኑዋ ብቻ ተከተለችው፡፡

ከራሷ ጋር ታግላ የልብ ልብ ከገዛች በኋላ ደሴቷን በሩጫ ወረደችና ከወደቡ ወደ ጀልባዋ ሊገባ ሲል ደረሰችበት፡፡ አብረውት ሁለት ተረኛ ኪዳን አድራሽ መነኩሳትም ነበሩ፡፡ "ሚ...ሚራኾር....?" ጥርሷን ነክሳ ጠራችው፡፡ ከጀልባዋ ወርዶ ወደ እሷ መጣ፡፡ የተጠቀለለ ነጭ አቡጀዲ ጨርቅ በፍጥነት ሰጠችውና "ለማንም አታሳይ!" ብላው እየተንቀጠቀጠች ወደ ጎጆዋ ተመለሰች፡፡ ሚራኾር ከጀልባዋ ወርዶ የክብራንን የወንዶች ገዳም መሬት ከረገጠ በኋላ የደሴቱን ኮረብታ በሩጫ ወጥቶ ትልቁ የዶቅማ ባፍ ሥር ቁጭ ብሎ ነጩን ቅዳጅ አቡጀዲ ጨርቅ ገለጠው፡፡

«ሚራኾር በጣም ተጨንቄ ነበር፡፡ ራሴን ለመግዛት ሞክሬ ነበር፡፡ ከማላውቀው ወጥመድ ውስጥ መግባቴን ከአንተ ውጪ ለሌላ ለማንም ብናገር ንስሐ ግቢ ከተሃለት በቀር ሁነኛ መፍትሔ እንደማይሰጡኝ አውቃለሁ፡፡ የሰይጣን ፈተና ነው ብዬ ለብዙ ቀናት ሰውነቴን በፆም ቀጣሁት፡፡ የሚሰጠኝን መቁነን በድብቅ ለወፎች እየበተንኩ ሳልበላ ለብዙ ቀናት ቆየሁ፡፡ መልክአ ኢየሱስን፣ ድርሳናትን፣ መስጦመ ኢያንንትን፣ ገድለ አቡነ ዘዮሐንስን ሁሉ እየደገምኩ በሱባኤ ለብዙ ሳምንታት

አሳለለፍኩ፡፡ እመ ምኔታችን እማሆይ ወለተ ኪሮስ ስትበጠበጥ አይተው በሽንቁሩ ግንድ ለሰረውኝ ስፀልይ ሰነበትኩ፡፡ ልድን ግን አልቻልኩም፡፡ ፈተናዬ የሀሊና ዕረፍት ነሰቶኛል፡፡ ከእግዚአብሔር ቤት ለሰወጥተው ሊጋንንት በደስታ ሊሰቁብኝ በጀርዬ ይሰማኛል፡፡...ሚራዥ እባክህ ድረስልኝ፡፡ ደግሞ እውነቱን ሳልደብቅ ልንገርህ፡፡ በየደቂቃው አንተን ማጡት ያሰኘኛል፡፡ለምንድን ነው?..... ሚራዥ..... ሰይጣናት ጥለው ሲዘባበቱብኝ ማየት ትፈልጋለህ? .....እንግዲያውስ ዛሬ ማታ በታንኳም ቢሆን መጥተህ ችግሬን ካልፈታህልኝ የመጨረሻ ለማራጩ ራሴን ወደዚህ ሐይቅ ወርውሬ ለሰይጣናቱና ለአጋሮቻቸው እጀን መስጠት ነው፡፡ መቼም ከዚህ በላይ ስቃይ አይኖር! ዛሬ ማታ ከደሴቱ ወደብ ትልቁ አለት ላይ አጠብቅሀለሁ፡፡ አንብበህ ስትጨርስ አጥበህ ጣለው ካለቀቀልህ አቃጥለው፡፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡ »

ሚራዥ ደብዳቤውን አንብቦ ሲጨርስ ተነስቶ በደስታ ዘለለ፡፡ በእሱ ውስጥ መከራ ሲያሳየው የኖረው ስሜት በእሷም ውስጥ በመኖሩ ሐሴት አደረገ፡፡ «ሲጳ... እኔ አንቺ ያለሽበትን ደሴት አሻግሬ እያየሁ ትልቁ ዛፍ ላይ ወጥቼ እንደምውል ማን በነገረሽ?..... ይምሽ እንጂ በዋናም ቢሆን አልቀርም፡፡» ሳይታወቀው እየለፈለፈ ነበር፡፡

ቀኑ አልመሸለት አለ፡፡ እንደ ሁልጊዜው መኃልዬ መኃልይ ዘሰሎሞንን ደግሞ ደጋግሞ አነበበው፡፡ «አስተማሰልኩኪ አንተ ሃቤዬ ጥቀ አዳም መላትሕኪ ከመ ማዕነቅ ወክሣድኪ ከመ አርማስቆስ፡፡ አምላለ ወርቅ ይግበሩ ለኪ ኮሰኮሰ ዘብሩር .» አሱዋ ደግሞ ከማዶ «ውዴ ሆይ ቀኑ እስኪነፍስ ጥላውም እስኪሸሽ ድረስ ተመለስ» ብላ የመለሰችለት መሰለው፡፡

«የለም ቀኑ አልመሸልኝም፡፡ ከማይመሽ ቀን የማይነጋ ሌሊት ይሻላል» አለ እየተንጠራራ፡፡ «ኩለንታኪ ሰናይት አንተ ሃቤዬ፡፡ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ፡፡ ንዒ እምሊባኖስ መርዓት ንዒ እምሊባኖስ፡፡» የሚሉ የሰሎሞንን መኃልያት ሊመላለስ ለእብደት ሊዳርጉት እንደሚችሉ ፈርቶ ተነስቶ ለጉብኝት ከመጡት ፈረንጆች ጋር ወደ ዕቃ ቤት አመራ፡፡ ከምንጊዜውም በበለጠ በዛ መዚየም የሚገኙትን ቅርሳቅርሶች በመሉ ከሰፊ ማብራሪያ ጋር ሲሰጥ ዋለ፡፡ በአስተርጓሚ፡፡

"ቤተ ክርስቲያኑ የተሰራው በተጠረቡ ቀይ ድንጋዮች ነው፡፡ እነዚህ በመቅደሱ ዙሪያ የምታዩአቸው ከጥርብ ከድንጋይ የተሰሩ አስራ ሁለት አምዶች ናቸው፡፡..... ከመቅደሱ ግድግዳ ጋር ተያይዞ የተሰራው ሕንፃ የገዳሙ መስራች የአቡነ ዘዮሐንስ መቃብር ነው፡፡..... ይህ ቤተክርስቲያን እንደምታዩት በደሴቱ አናት ላይ ነው የተሠራው፡፡.... ይህ የድንጋይ ደወል ነው፡፡..... በዚህ ዕቃ ቤት

ውስጥ ከአስደናቂ ቅርሶች አንዱ ይህቺ በወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በራሱ እጅ የተሳለችው የቅድስት ማርያም ስዕል ናት፡፡ .....ይህ ከብረት የተሰራው የአቡነ ዘዮሐንስ የፀሎት ልብስ ነው፡፡....ወደዚህ ገዳም መግባት የሚችሉት ወንዶች ብቻ መሆናቸው ለየት ያደርገዋል፡፡ በዳጋና በአንዳንድ የጣና ገዳማት ሴቶች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፡፡ .....እዚህ ቀጥሎ ካለው ደሴት ደግሞ ሴቶች ብቻ የሚኖሩበት ገዳም አለ» እያለ ያልጠየቁትን ሁሉ ሲለፈልፍ ትዝ አለችው፡፡ ሲጳራ፡፡ ሳይሰናበታቸው ወጥቶ ሄደ፡፡ ሌላ ሰው ተጠርቶ አስጎበኛቸው፡፡

ሲጳራ በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ አለቱ ላይ ቁጭ ብላ ሚራዥን ስትጠብቅ መንፈቀ ሌሊት አለፈ፡፡ አላስችል አላት፡፡ ልብሷን አወላልቃ ወደ ጣና ተወረወረች፡፡ ወደ ወንዶች ደሴት መዋኘት ጀመረች፡፡ እየመጣም ከሆነ እዛው ሐይቁ ውስጥ አገኘዋለሁ፡፡ሲያጋጥማት የሚችለው ዓዞና ጉማሬ አላስጨነቃትም፡፡ በህፃንነቷ ስትዋኝ አትደክምም ነበር፡፡ አሁን ግን በፍርሃት የሚርድ ሰውነቷ አልንሳፈፍ አላት፡፡

የሚዋኝ ሰው እየቀረባት መጣ፡፡ "ሲጳራ!" አላት የለሆሳስ ድምፅ፡፡ የምታውቀው ድምፅ፡፡ ራሷን ብቅ አድርጋ "ወዬ" አለችው፡፡

"ምነው?" አላት በድንጋጤ፡፡

"ቆየህብኛ::"

"እሺ ተመለሽ ወደመጣሽበት ዋኚ"

"ደክሞኛል፡፡ አልቻልኩም፡፡"

"አይዞሽ፡፡"

"እያቃተኝ ነው ሚራዥ" እያቃተኝ ነው ስትል ይበልጥ አቃታት፡፡ ተጠግቶ ደገፍ አደረጋት፡፡ ሰውነቷ ይፋጃል፡፡ ሰውነቱን ነዘረው፡፡ ትንፋሿ ለመጠጠው፡፡

"አይዞሽ እየደረስን ነው፡፡" የልብ ምቱ ሲፈጥንበት ታወቀው፡፡ ውሃው ውስጥ ሆኖም አቃጠለችው፡፡ እሷንም እያቃጠላት ነው፡፡ ከሐይቁ ዳር ሲደርሱ አለቱ ላይ የጣለችውን ልብሷን ለበሰች፡፡

ሚራዥ በዋና ሲመጣ ራሱ ላይ የደገለለውን ልብሱን ፈትቶ ለብሶ ሁለቱም አለቱ ላይ ተቀምጠው በፀጥታ ተዋጡ፡፡ አብረው ሲያድጉ ከአፍ እየተቀማመሙ ይጫወቱት የነበረው ሁሉ ዛሬ ውሃ በላው፡፡ የሁለቱም አንደበት ተሳሰረ፡፡

«ሚራዥ..... በጣም በረደኝ!...» አለችው ጥርሶቿን እያፋጨች፡፡

"ምን ይሻላል?"

"ለምን ወደኔ ጎጆ አንሄድም?" ስትፈራ ስትቸር ጠየቀችው፡፡

"እንዴ! .....እሱማ ከባድ ነገር ነው፡፡"

"እንዴት?"

"ሰ.... ሰው ቢያየንስ?"

"እና ምን ተሻለን?"

"እሺ ከገዳመ· ውጭ ካለው ቆርቆሮ....." ድፍረታ ገረማት።

"እመቃብር ቤቱ ዘንድ?"

"አዎ። ለብርዱ እዛ....."

"እሺ። እንሂድ" ሚራዥ አደገኛውን ነገር እያደረገ መሆኑ ቢሰማውም አላቅማማም።

እመቃብር ቤቱ ውስጥ ገብተው ከውስጥ ቀረቀሩት። የመቃብር ቤቱ ወለል አፈር እስከቁርጭምጥሚታቸው ዋጣቸው። ከምንም አልጣፉት። ሚራዥ ከግድግዳው ላይ የተሰካውን ደረቅ ሣር አውርዶ ጎዝጎዘውና ተቀመጡ። ዝምታ።

«...እማሆይ ወሰተ ኪሮስ እየተሻላቸው ነው?» አላት ዝምታቸውን ለመስበር ያህል።

«የለም እየባሰባቸው ነው።ሐኪም ቤት ሊወሰዱ ሲለመኑ ‹የሚያድንም የሚገድልም እግዚአብሔር ብቻ ነው› ብለው እምቢ አሉ።እርጅናውም እየተጋፋቸው ነው።»

"ምን ነበር ያስጨነቀሽ?" አምጦ ጠየቃት።

"እኔ እንጃ!" የምትለው ጠፋባት።

"እንዴት?" ገብቶታል። ግን.....

"ብቻ አንተን ....." መናገር አልቻለችም። ‹ምን አይነት ገመና ነው? ለምን ይጠይቀኛል? ዝም ብሎ እንደ እኔ.....› በውስጧ ተብሰለሰለች።

"ሚራ... በቃ...የሆነ ነገር አሰኝቶህ ያውቃል አይደል?" አለችው የግዷን።

"አዎ.....አንዳንድ ነገሮች ያሰኙኛል። አንዳንዶችን ላገኛቸው ስችል ሌሎች ደግሞ የማላገኛቸው ናቸው።"

"እኔን ደግሞ የሚያሰኝኝ .....የሚያሰኝኝ ... በቃ.....አንተ አሰኝተኸኛል። አሰኝተኸኝ።" ተገላገለችው።

"ማለት....."

"አሰኝቸኛ በቃ ውሀ!" ሌላ ጥያቄ እንዳይጠይቃት ፀለየች።

"እኔንም አሰኝተሸኛል።..... ማለቴ..." አንገቷ ውስጥ ተሸጎጠ።ትንፋሿና ትንፋሹ በፍጥነት ተዋሃዱ። የማያውቁት መግነጢሳዊ ኃይል አዋሃዳቸው። ከንፈር ለከንፈር ሲያያዙ ምን እያደረጉ እንደሆነአላወቁም።..... ብቻ ሁለቱም ከሰሎሞን የመዝሙር መፅሐፍ ውስጥ ያነበቡአቸው በዕዝነ ህሊናዎቻቸው ተደመጡአቸው።.....ሳይታወቃቸው የንጋቱ ደወል በሁለቱም ደሴቶች ላይ ተሰማ። ሁለቱም የንጋቱን ደወል በልባቸው ሳይረግሙት አልቀሩም።

የመቃብር ቤቱን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት በትልቅ ሰንሰለት የታሰረ በ ‹ቆ› ቅርፅ የተሰራ ግማደ መስቀል ከአንገቱ አውልቆ አሰረላት።

"አመሰግናለሁ ..... መስቀሉ በጣም ያምራል ....መስቀሉን ላይ አንተ ከእኔ ጋር እንደሆንክ እያሰብክ....." መስቀሉን ሞብጥ አድርጋ። "..... መቼ ነው ተመልሰህ የምትመጣ?" አለችው። ተመልሰው የሚገናኙበት ጊዜ እንደ አድማስ ጥግ ርቋት።

"ተነግ ወዲያ ማታ እዚሁ መቃብር ቤት ውስጥ እንገናኛለን"

"እስከ ነገ ወዲያ!.... ሩቅ ነው። ግን እጠብቅሃለሁ።.... እንዳትቀር እሺ?"

"..... አልቀርም። ይልቅስ አንቺ እንዳትቀሪ" ወደ ወደቡ በፍጥነው ውስጥ ለውስጥ እየጣሰ ወረደ። ከወዲያኛው ማዶ የወንዶች ደሴት እየሞገ እስኪደርስ ሐይቁ ዳር አሰቱ ላይ ተቀምጣ በዓይኗ ሸኘችው። እዛኛው ማዶ ወደብ ሲደርስ እጁን አውለበለበላት።እሷም ከተቀመጠችበት አለት ተስፈንጥራ ተነስታ ሁለት እጆችዋን አወናጨፈቻቸው።

ከሶስት ቀናት በኋላ እንደገና መቃብር ቤቱ ውስጥ ተገናኙ።..... ከሴሊቱ አጋማሽ ላይ ላይ እሪታ ከሴቶች ገዳም ተሰማ። መቃብር ቤቱ ውስጥ ባሉበት በድንጋጤ ድርቅ አሉ። የሴት መበለቶች ድምፅና ኡኡታ እየበዛ እሪታው እየበረከተ መጣ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አካፋና ዶማ የያዙ መቃብር ቆፋሪዎች ወደ መቃብር ቤቱ ከንፈራቸውን እየመጠጡ መጡ። ሲጓራ በፍርሃት የሚራዥን ክንድ አጥብቃ ያዘችው። "ከውጭ ነው የምንቆፍረው ከውስጥ?" ሲል አንዱ ወደ መጡበት ድምፁን ከፍ አርጎ ጠየቀ።

"ወይኔ ሰው ሞቶ የመቃብር ጉድጓድ ሊቆፍሩ ነው እንዲ?" በጆሮው አንሾካሾከች። ክው አለ።

"የታመመ ሰው አለ እንዲ ?"

"እማሆይ ወሰተኪሮስ ሞቱ "ሳለት ነው። ሌላ የታመመ የለም።"

"የኛ መፈረሻ ይሄ ነው?.... ወይኔ እግዚአብሔር ተጋለጥን። ሃናለ....."

"ምን ዓይነት ፈተና ነው....." አፏ መረረት።

"እሺ, ወጥተን....."

"እንዲ በር ላይ እኮ ናቸው!"

"ቆይ እንዴት መጡ?"

"በታንኳ መጥተው ይሆናላ!"

"ምን ሰራሁ እመብርሃን! ውይ..."

መልሱን ይዘ የመጣው ሰውዬ "ከውስጥ ይቆፈር ብለዋል" አለ እየተነፋነፈ።

"ከውስጥ ከሆነማ መብራት ይዘህ ና እንጂ! ጴሮስ እማሆይ ወለተ ኪሮስን ያክል እናት ሜዳ ላይ ይቀበራሉ?" በሩን እያንቋቋ ከፈተው።

".....ሰው አለ እንዴ?" አለ እስክ ዓይናቸው አስግጎ። የተቀመጡበት መሬት ተከፍቶ ቢጨጣቸው በወደዱ።

"እንቱ አባ ፊንሐስ ?! እረ ሰው ነው! .....እስኪ ጢፉን አምጡት!" አለ ወደፊታቸው ይበልጥ አይኑን እያፈጠጠ። የጢፉ ብርሃን ከሁለቱ ዓለም ሰዎች ላይ መጥፎ ዐዳሉን ጣለ። ለሁለቱም ያ የጢፍ ብርሃን ከጨለማ የባሰ ርጉም ነበር።

"ኧረ የእስራኤል አምላክ ምኑን አሳየኸኝ!?" አባ ፊንሐስ ፊታቸውን አዞሩ። ከዳጋ እስጢፋኖስ የመጡት የእማሆይ ወለተ ኪሮስ ቤጠና መታመም ሰምተው ቢሆንም ከሲጳራ ጋር የሚነጋገሩበት ጉዳይም ነበራቸው።

"ኧረ ጉ.....ድ! ኧረ!... ኧረ !.....ሰአሊ ለነ ቅድስት!..... የግሸኗ እመቤት! .....ፍጡነ ረድኤት! " ሁለተኛው ቆፋሪ መነኩሴ አባ ማቴዎስ ራሳቸው አፍረው ዓይኖቻቸውን በእጆቻቸው ጋረዱ።

"ሚራኻ.... ምነዋ የኔ ልጅ.... ውዳሴ ማርያም መድገም ተውከ እንዴ? ምነዋ ሰይጣንን በፀሎት ብትዋጋው!? " አባ ፊንሐስ ያልጠበቁት ዱብ እዳ ነበር የገጠማቸው።

"ምነዋ ልጄቼ ..... ጉድ! ጉድ!.... ጉድ ነው።" አባ ፊንሐስ ከአንድ ቀን በፊት ከዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መጥተው ለሲጳራ መንፈሳዊ ብርታት የሚሰጥ ያሉትን ቀኖና እና ስግደት ሰጥተዋት ተመልሰው ነበር። ወደሴቶች ገዳም የመጡት የሴቶች ገዳም እመምኔት የሆኑት እማሆይ ወለተ ኪሮስ መድከማቸውን ምክንያት በማድረግ ቢሆንም ከሲጳራ የሚፈልጉት አንድ ታላቅ ጉዳይ ነበራቸው። ሲጳራን እየዘሩ የሴቶች ገዳም ውስጥ ሲፈልጉም ነበር።

ሚራኻ አፋ ተሳሰረ። ሲጳራ እንዳትደነግጥ ሲል የራሱን መሸማቀቅ ወደ ውስጡ አመቀው። "አይዞሽ....." እጇን ይዟት ከመቃብር ቤቱ ወጡ።

እሱም ተጨንቋል። ነገር ግን ምንም ያልተሰማው መስሎ እየዕናና ይዟት ወደ ወደቡ ወረደ። ከወደቡ የተጠጋ ታንኳና ጀልባ ሲያይ ወደታንኳው እየመራ

"ተከተይኝ" አላት። "አብረን እንሄዳለን።"

"ወዴት መሄድ እንችላለን?"

"ወደየትም ይሁን። ብቻ ከዚህ መውጣት አለብን። ከአሁን በኋላ ተእነዚህ ገዳማት ውስጥ መኖር ለእኔና ለአንቺ የማይቻል ነገር ነው።.... እንኳን በአንድ ቤት ውስጥ ጨለማ ለብሰን አግኝተውን ቆመን እንዳናወራ መከልከላችንን መዘንጋት የለብሽም።"

"ተረድቼሃለሁ ሚራ..... ግን ..... ወዴት ብለን እንሄዳለን?" ከመንታወቹ ገዳማውያን ደሴቶች ውጭ የሚያውቁት ዓለም እንደሌለ ታውቃለች ሲጳራ።

"ጉዞውን እንጀምረዋለን.... መድረሻችንን አካሄዳችን ይወስነዋል። አትፍሪ። ወደየትም ይሁን ብቻ እግራችን ወደሚወስደን ቦታ እንሂድ...."

«እሺ ታንኩ ጋር ልሁን እንጂ ብቻ የትም ይሁን እንሂድ»

ከታንኳው ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እጇን ጥብቅ አድርጎ ይዟት ቆመ። በከፊል ደመና የተሸፈነችው ጨረቃ በምትረጨው ቀዝቃዛ ብርሃን ደረቷ ላይ ያሰረባት ግማደ መስቀል ሲፈልቅ የውስጧ የፍቅር ነፀብራቅ ልቡ ላይም ፈለቀ። ያሰረባትን መስቀል ጥብቅ አድርጋ ይዛ "መቼም አልጥለውም እሺ.....ስለታህን እድሜየን በሙሉ ይገርው እኖራለሁ።..... ትናንት አባ ፊንሐስ ያሰርክልኝን መስቀል «ስሜኝ » ብለው ለምነውኝ ነበር። እምቢ አልኳቸዋ" ከዓይኖቿ ውስጥ የወጣ የማትቆጣጠረው ኃይል አስፈንጥሮ ደረቱ ላይ አላጠቃት። ተብሰክስካ ከንፈሮቹን ጎረሰችው። እሱም ተንገብግቦ ጎረሳት።

ወዲያው ከኋላዋ እጅዋን ለቀም አድርጎ አንድ ሰው ሲጨብጣት በድንጋጤ ጮኸች። አባ ፊንሐስ ናቸው። ምንም ሳይናገሩ በፍጥነት ሞተሩን አስነስቶ ከሚያንራው ጀልባ ውስጥ ጎትተው ከተታት። ጀልባውን የሚነዱት መነኩሴ አባ ማቴዎስ ናቸው። የሞተሩ ድምፅ ይበልጥ ጨመረና ኃይቁን በሐይል ቀዝፎ ይዟት ጉዞ ሲጀምር ሲጳራ እሪታዋን አቀለጠችው።

በተለይም ጀልባው አሷን ብቻ ይዞ ባህሩን እየሰነጠቀ ሲሄድ አኡታዋን አቀለጠችው። አባ ፊንሐስና ጀልባውን የሚነዱት መነኩሴ አባ ማቴዎስ አንደም ቃል ሳይተነፍሱ ዝም አሏት። በዋና ወደ ሚራኻ ልትሄድ ወደ ሐይቁ ተወረወረች። አባ ፊንሐስ እጆቿን ይዘው እንደ ገና መልሰው ጀልባው ላይ ጭነው ይዘዋት ከነፉ። የሚራኻ ደምፅ ከሩቅ ይሰማታል ሲጠራት የህልም ጥሪ ሆነባት። ድምፁ እየራቃት ሄደ። የሞተሩ ድምፅና የጣና ማዕበል ድምፁን ዋጡባት። ሁለቱን መንትያ ደሴቶች ወደኋላ እያየቻቸው እንደህልም አለም እየራቁት ከእይታዋ ውጭ ሆኑ።

ሚራዥ ዘሎ ሐይቁ ውስጥ ገብቶ በዋና ጀልባውን መከተል ጀመረ። በጀልባውና በእሱ መካከል ያለው ርቀት የአድማስ ዳርቻ ያህል ሲርቀው ሆዱን ባር ባር ብሎት ዕንባ ባነቀው ድምፅ ለመጨረሻ ጊዜ ተጣራ። "ሲጳራ...ሲጳ.....ሲ.....ሲ.....ሲ....." ተስፋ የከዳው የሰለለ ድምፁ ለእሱም አልሰማው አለ። የእሷም ድምፅ እየሰለለ እየመነመነ በጣና ማዕበል ተዋጠ። ውሃውን ጨብጦ ወደ ሄደችበት በትኖ እየተነፋረቀ በሁለቱ ደሴቶች መካከል ፈዞ ቀረ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

በኋላ አራት መነኮሳት ሚራዥን ይዘውት ወደ ገዳሙ ጀልባ ከተቱትና ወደ ነበረበት ክብራን የወንዶች ገዳም አሻገሩት። ሁሉም በሀዘን ተውጠዋል። እማሆይ ወለተ ኪሮስ በመሞታቸው ብቻም ሳይሆን በሚራዥ መውደቅ ምክንያት። በሚራዥና በሲጳራ መካከል ስለተፈጠረው ነገር ብዙዎች መነኮሳት የሰሙት ሚራዥ ወደነበረበት ወደ ክብራን የወንዶች ገዳም ከተመለሰ በኋላ ነበር። ከእማሆይ ወለተ ኪሮስ ሥጋዊ ሞት በላይ አሳዛኝ የሆነው የሚራዥ የቁም ሞት ነበር። መነኮሳቱ ለሰንት ነገር ይደርሳል ያሉት ብላቴና የቤተክርስቲያን አገልጋይ በሰይጣን ወጥመድ ገብቶባቸዋልና አዘኑ።

በተለይ የክብራን ገዳም አበምኔት የሚሉት ጠፍቶባቸው ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ "መታሰር አለብህ። ሰይጣንን ልትዋጋው ይገባል" ብለው መነኩሴ ሲተላለፍ እንደሚደረገው ሁለት ቀዳዳዎች ባሉት ግዙፍ ግንድ ሁለት እግሮቹን በቀዳዳዎቹ ውስጥ አሾልከው በእግረ መቅ አሰሩት። የእግረሙቁን ቁልፍ ማህደራቸው ውስጥ ከተው እየተበሳጨ ሳያናግሩት ባዶው ቤት ውስጥ ጥለውት ሄዱ።

ከሰዓታት ቆይታ በኋላ መለፍለፍ ጀመረ። "ፍቱኝ! ..አትለዩኝ!..... ሰይጣን አይደለም....." ማንም የሚመልስለት የለም።

ሁሉም መነኮሳት በደንጋዩ ደወል ተሰብተው ከተሰበሰቡ በኋላ እንዲፀልዩለት አበምኔቱ አሳስበው አሰናበቱአቸው። በክብራን ገዳም ውስጥ ሁለት የድንጋይ ደወሎች አሉ። ትልቁ የድንጋይ ደወል መነኮሳቱን መሰብሰቢያ ሲሆን ትንሹ ደግሞ ስብሰባውን መበተኛ ነው። በመሆኑም በትልቁ የድንጋይ ደወል የተሰበሰቡት መነኮሳት በትንሹ የድንጋይ ደወል ድምፅ ሲበተኑ ጀምረው ሁሉም ለሚራዥ ፀሎት ማድረስ ጀመሩ።

"እናንተ ሽማግሌዎች! የማታውቁትን ለምን ታደርጋላችሁ? ፍቅርንና ሰይጣንን ለይታችሁ ማወቅ ለምን ተሳናችሁ?.... ፍቱኝ! ...አላበዛችሁትም? .....ጥላኝ ሄደች!.... ፍቱኝ.....አፍነው ወሰዷት። ላስጥላት ፍቱኝ። ስለራሳችሁ ፀልዩ። እኔ ጤነኛ ነኝ። ጤና ያጣችሁ እናንተ ናችሁ።....." ሚራዥን የሚያዳምጥ ጆሮ ግን አልነበረም።

አርባ ቀን ሙሉ ታስሮ ሲለፈልፍ ከረመ። አልተሻለውም። መለፍለፉ ሲታገስለት የተመለሰ መስሏቸው በፊቱት ማግስት በአሮጌ ታንኳ እየቀዘፈ ሁለቱን መንታ ደሴቶችና ገዳማት ጥሏቸው ሸሸ።

ባህርዳር ከተማ ሲደርስ ሁሉም ነገር ተደነጋገረው። የማያውቀው ዓለም።.... መኪና። .....ግርግር። .....ሱሪ ያጠለቁና ዳሌያቸውን የሚወዘውዙ ሴቶች። ጭናቸውንና እምብርታቸውን የሚያሳዩ ልብሶች የለበሱ ልጃገረዶች። ስንቷን ሴት እያየ ሲጳራ መሆን አለመሆንዋን መለየት ይቻላል? አፍጥጦ ሲያያቸው "እህ! ይህ ደሞ ምኑ ባሳገር ነው ከእብዶች ሆስፒታል የተለቀቀ መሆን አለበት። ምን እንደ ቡዳ አፍጦ ያያል? ..." እያሉ ገላምጠውት ይሄዳሉ። እሱ ግን ሲጳራን ከዚህ ሁሉ ሴት መሀል እንደማያጣት እርግጠኛ ነበር። አቅጣጫ እንደሳተ የተገለጠለት ቆይቶ ነው።

በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰላሰለ ከባህር ዳር ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በረንዳ ላይ እየተኛ ሲዋትት ሰነበተ።

አንድ ቀን ከተኛበት በረንዳ አንድ ሰው ሊቀሰቅሰው ተሰማው። ቀና ሲል ሞተሩን ያላጠፋ የጭነት መኪና ቆሞ ሽራው ውስጥ ሰዎች እየገቡ ተመለከተ። ሁለት ኮማንዶዎች ወርደው ክንድና ክንዱን ይዘው መኪናው ውስጥ ጫኑት። ከብዙ ጉዞ በኋላ ለውትድርና ከታፈሱት ሰዎች ጋር አንድ በረሀ ውስጥ አብሮ ተራገፈ። "ግራ ቀኝ፣...ቀኝ ግራ፣.....ወደኋላ ዙር! ....ወደፊት! ...እናት ሀገር" ምናምን። ጊዜው ወታደራዊዉ የደርግ መንግስት የሞት ሽረት ትግል በሰሜን አካባቢ የሚያደርግበት ወቅት በመሆኑ የዚህ ጦርነት ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ያገኘውና የሰሜኑን ጦር የተቀላቀለው ከአድካሚ ስልጠና በኋላ ነበር።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

እነ ሲጳራ ሲነጋጋ ጎርጎራ ወደብ ደረሱ። ጀልባዋን እዛው ትተው ወደ ሰሜኑ አቅጣጫ ረጅም የእግር ጉዞ ካደረጉ በኋላ አንድ ቀጥቃጮችና አንጥረኞች ከበዙበት መንደር ደረሱ። ማንም አይነጋገርም። ዝም ብሎ መጓዝ። ከዚህ መንደርም ብዙ ሰዎች ጓዛቸውን እየጠቀለሉ ተከተሏቸው።

ከቀናት ጉዞ በኋላ የጎንደርን ኩሙማ ወደጎን ትተው ወደ ሰሜን ተራራ ተጓዙ። ተጓገሮችም እየበረከቱ መጡ። ከሚያገኙት መንደር ሁሉ የሚጨመር ተጓዥ አለ።

"ቆይ.... ወደየት እየተጓዝን ነው?" አለች ሲጳራ አንድ ትልቅ ዋርካ ሥር ለአረፍት እንደተቀመጡ።

"ወደ ተቀደሰችዋ ምድር" አሉ አባ ፊንሐስ የሰሜንን ተራራ አንጋጠው እያዩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያናግሯት ነው።

"ማን ናት የተቀደሰችዋ ምድር?" እሷም በላዩ ላይ ባዘቶ የመሰሰ ጉም የሸፈነውን የራስ ጻሽንን ተራራ አሻቅባ እያየች አባፊንሐስን መልሳ ጠየቀቻቸው።

"የተቀደሰችዋ ምድርማ እግዚያብሔር ለአባቶቻችን ቃል ኪዳን የገባላቸው እስራኤል ናት- ኢየሩሳሌም"አሏት። ስለ ኢየሩሳሌም ታውቃለች። በመፅሐፍ ቅዱስ።

አባ ማቴዎስ ፈንጠር ብሎ ከሚገኘው ጉብታ ላይ አርባጣ አፈር እየቆፈሩ ከማህደራቸው ሲከቱ ሌሎች ከሩቅ ይሰሳቁባቸዋል።

አባ ፊንሐስ.....ቀጠሉ...እየተልጎመጎሙ...እተቁነጠነጡ..."አየሽ ልጄ ሲጻራ.... አንቺ የማታውቂው ብዙ ነገር አለ። በመጀመሪያ ...አባትሽ እኔ መሆኔን ልነግርሽ እወዳለሁ።"

ካቀረቀረችበት ቀና አለች ግራ ተጋብታ። "ምን?!" ቅንድቧን በጥያቄ መልክ ሸብሸባ።

"አዎ ልጄ። ወደ ሴቶች ገዳም ያስገባሁሽ ወድጄ አይደለም። ደኽየሁ። እናትሽንም ሞት ነጠቀኝ። አዝዬሽ በልመና ላሳድግሽ ተንከራተትኩ" የለበሱትን ወይባ አቡጀዴ ሰብስበው ግራ እጃቸውን ገልጠው አሳዩአት። ክንዳቸው በጥይት ተቦትርፎ በተሰበሰበ ግንድ መስሏል። "እዬውልሽ ልጄ። እኔ አባ ዝጉበሩና አባ ዲዲሞስ አንድ የጋራ ጉዳይ ስላለን..... ተይው ይህን ሌላ ቀን ነው የምነግርሽ። ጣና ሐይቅ ላይ በጣሊያን ጊዜ የመርከብ..... ለካ ሌላ ቀን እነግርሻለሁ ብያለሁ። አሁን አይደለም።»

ሚራዥ ካሰረላት በ"ቶ" ቅርፅ ከተሰራው ባለ ጉጥ መስቀል ላይ አይናቸውን አልነቀሉም። ለምን ይህን ያህል ገዜ አፍጥጠው እንደሚያዩት ግን አልገባትም። ባለፈው እንድትሰጣቸው ጠይቀዋት እምቢ ብላቸው ነበር።

«እየውልሽ ልጄ...» አገጫቸውን አሹለው ወደ ሰሜን ተራራው ሲያዩ እሷም ተራራዎችን ተመለከተቻቸው። "ከምታይው ተራራ ግርጌ ነበር እኔና እናትሽ በአንጥረኝነትና ብረት በመቀጥቀጥ ስንተዳደር የነበር። ማረሻ ሽጠን የምናገኘው ገቢ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ሆኖም ተስፋ ያስቆረጠኝ የምወዳት እናትሽ አንቺንና እኔን ጥላ ስትሞትብኝ ነበር። እዚህ አስቸጋሪ ቦታ ላይ አንቺን ማሳደግ ተሳነኝ። ቤተ አስራኤላዊና የአይሁድ እምነት ተከታይ ብሆንም ቀን እስኪወጣ ብዬ እምነቴን በልቤ እንደያዝኩ አንቺን ላሳድግ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ገባሁ። አንቺን በእንጦንስ ደሴት ለሴቶች ገዳም ሰጥቼ እኔ ደሞ በዳጋ እስጢፋኖስ የወንዶች ገዳም ውስጥ መኖር ጀመርኩ። አሁን ግን ዘመዶቻችን ሊወስዱን መጡ።"

ከተጓጉቾች መሃል በአህያ ላይ ተጭኖ የሚጓዘውንና ፊቱን በጥቁር የዋልካ ጭቃ ቀብቶ ከሐበሻ ጥቁር አይሁዶች ጋር የተመሳሰለውን ፈረንጅ እያሳዩአት።

ፊቱን በዋልካ ጭቃ የተለቀለቀው ፈረንጅ ፎቶ ያነሳል፣ ቪዲዮ ይቀርፃል፣ አባ ፊንሐስንም ቃለ መጠይቅ እድርጎ ቃላቸውን በቴፕ ሲቀርፅና ፎቶም ሲያነሳቸው አይታ ነበር። እሱዋንም ትኩር ብሎ ይመለከታታል። ዓይኑዋን ካልሰበረች ዓይኑን አይሰብርም። ከሁዋላ ስትቀር ወደሁዋላ ይዞራል። ከፊት ስታልፍ እየገሰገሰ ይደርስባታል።

"...ይሄ ነው ዘመዳችን?.... .ነጪ ሰውዩ? .....እንዴት ሆኖ?" ግራ ገባት። "እነማን ናቸው ዘመዶቻችን?" ራሱን ተሳቅቶ ፊቱን የዋልካ ጭቃ ተለቅልቆ ከሸማግሌዎች ጋር ቆሞ የሚነጋገረውን ወዘ ልውጥ እያየች።

"እስራኤላውያን ናቸው ወገኖቻችን። ከዚህ የመከራ ኑሮ ሊያላቅቁን መጥተዋል። አንገታችን ደፍተን፣ አፈር ለብሰን ነበር። አሁን ግን ደረሱልን። እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል ወደገባላቸው ማርና ወተት ወደምታፈሰው ከነአን ሊወስዱን መጡ" ልቧን አማለው ሚራዥራን ሊያስረሷት መስሏቸው ነበር። የእሷ ልብ ግን ከሚራዥ ጋር እንደተቆራኘ ነበር።

"እና ምነ ሚራዥ አብሮን ቢሄድ? ለምን ጥላችሁብኝ መጣችሁ? አባ... እሱን እኮ አሁን እያሰቃዩት ነው የሚሆነ! ክህነቱን ሃፈረሰ ይመስላቸዋል እኮ!..... ግን ምንም አላደረግንም አባ.... እባክዎ ሂደን እናምጣው?" ዓይናቸው ላይ እየተቁለጨለጨች ተማፀነቻቸው።

"ይሄማ የማይሆን ነገር ነው። እየውልሽ ልጄ የማታውቂው ይህንን ነው። እኛ ቤተ እስራኤላውያን ነን። የእግዚያብሔር ህዝቦች ። በእግዚያብሔር የተመረጠውን ዘር ከሌላ ዘር እንደባልቅም።"

"እንዴ! ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን አግብቶ የለ? እኔስ ለምን....." አቋረጣት።

"እነዚህ የሚወስዱን ሰዎች ሁሉን ነገር አጥንተው ጨርሰዋል። እስራኤላዊ ያልሆነን ማንንም አይወስዱም" አሉ ወደ ጠጉረ ልውጡ ሰውዩ እያማተሩ።

"እኔ ግን እሱን ትቼ ንቅንቅ አልልም" አለች ወደ መጣችበት አቅጣጫ ፊቷን አዙራ። አልመለሱላትም። የእረፍት ሰዓት ሰላበቃ ሁሉም ጓዙን እየጠቀለለ ተነሳ። በቀኝ እጃቸው እጇን ይዘው እየጎተቱ ከሚጥመለመለው ተጓዥ ጋር ተደባልቁ።

ከትከሻቸው ጹላ ቅል ቃንቁራቸውን ሰካክተው ያንጠለጠሉ፣ ማረሻ ማጭድ፣ ጉራዴ፣ ሰይፍ፣ ጦር፣ አንካሴ፣ መቆፈሪያ፣ መጥረቢያ፣ አካፋ፣ ዶማ እና ሌሎችም ዝክንትሉችን አንጠልጥለው ይጓዛሉ። ከወዘ ልውጡ ሰውዩ ጋር በአብራይስጥ ቋንቋ ከሚነጋገሩት ሽማግሌዎች ጋር ህፃናት፣ ጓዝ የተጫኑና በድርቁ

የሚቀምሱት አጥተው በአጥንታቸው የሚሄዱ አህዮች ይጋፋሉ። ይጓዛሉ።

ከጎንደርና አካባቢዋ፣ ከወለቃ፣ ከሩፋኤል፣ ከሲልቀት፣ ከጎርጎራ፣ ከጭልጋ፣ ከቋራ፣ ከጃናራ፣ ከእንከኮሽሺሊት፣ ከአርማጭሆ፣ ከብልባሆ፣ ከጠዳ፣ ከደንቀዝ እየመጡ ጉዞውን ተቀላቀሉ። ከወገራ አውራጃ ዳግሞ ከዳባት፣ ከሰላምጌ፣ ከጉራሬ፣ ከዋርዋ፣ ከብራ ኢየሱስ፣ ከአምባ ጊዮርጊስ፣ ከደርጋጅ፣ ከጫርቢጣ እየመጡ ተደባለቁ። ሲደባለቁ የሚያወጡት አንድ ቃል ብቻ ነው። «ሻሎም።»

ከጎጃም ደግሞ ከባህር ዳር፣ ከቡሬ፣ ከደብረማርቆስ፣ ከዲማ፣ ከይስማላ ሳዮርጊስ፣ ከአዲት፣ ከዱር ቤቴ፣ ከቁንዝላ፣ ከግብግቢት ቀድመው ደርሰዋል። ከበጌ ምድርም ከወረታ፣ ከሐሙሲት፣ ከፎገራ፣ ከደብረታቦር፣ ከአፈረዋናት፣ ከእስቴ፣ ከፋርጣ፣ ከውዴ፣ ከኩርያ ማርያም፣ ከመነጉዘር፣ ከአሞራ ገደል የመጡትም ከኋላ ደረሱባቸው። ከደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ከምእራብ ኢትዮጵያ፣ ከምስራቅ ኢትዮጵያም መጥተዋል።

ወቅቱ ኢትዮጵያ በእርስ በእርስ ጦርነት የምትታመስበት በመሆኑ ሁሉም ባተሌ ነበር። በሽምቅ ተዋጊዎች ጦር በአራቱም አቅጣጫ የሚንቦጀቦጀው የደርግ መንግስት በጦርነት በመማገዱና የሚይዝ የሚጨብጠውን በማጣቱ ቤተ እስራኤላውያኑን ወደ እስራኤል ለማጓጓዝ «ዘመቻ ሙሴ» ለተሰኘው የእስራኤል ኦፕሬሽን ተፈፃሚነት አመቺ ወቅት ነበር። በሱዳን በኩል ሰርገው ለገቡትና ለዓመታት ለሰለጠኑት የእስራኤል ሰላዮችም ወርቃማ ጊዜ ነበር።

ቤተ እስራኤላዊያኑ በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜን ምዕራብ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተበታትነው ሲኖሩ ለሁለት ምዕት አመታት ያህል ወደ እስራኤል ለመመለስ ምኞት የነበራቸው ቢሆንም ይሁዲ መሆናቸው የተረጋገጠው ከረጅም ጥናት በሁዋላ "ፈላሻዎች በማያጠራጥር ሁኔታ የዳን ነገዶች ናቸው" ተብሎ በመታወጁና ይህም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዛሬው ደቡባዊ የአረቢያ ልሳነ ምድር ይኖሩ እንደነበር ተረጋግጧል በመባሉ ነው።

የእስራኤሉ የስለላ ድርጅት ሞሳድ ፈላሻዎችን ከኢትዮጵያ በምስጢር ለማስኮበለል የተሳካለት ወቅትም ኢትዮጵያ በጦርነት ውዥንብር ውስጥ በገባችበት ወቅት ነበር። ፈላሻዎችን የማጓጓዙ ተግባር በቀጠለበት በዚህ ወቅትም የወቅቱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስተር ሺሞን ፔሬዝ "ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከኢትዮጵያ በደህና ወደ ሀገራቸው እስኪመለሱ ድረስ ዕረፍት አይኖረንም" ያሉት የረሃብተኛ ፈላሻዎች ሁኔታ በተባባሰበት በነፋሻማው የፀደይ ወቅት ነበር።

ጉዞው ቀጥሏል ። ጥምልምሉ። በጎላ ጉዞው ከቀን ወደ ሌሊት ተዛወረ። በእውራ ጎዳናዎች የሚነጉደውን ረጅም ተጓዥ በመቆራረጥ በየጥሻው በድብቅ ማስጓዝ ነበር አዋጭ ሆኖ የተገኘው።

ሲጓራ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገችውን ረጅም ጉዞ መቋቋም አልቻለችም። ጭብጥ ከምታህል ድንክየ ደሴት ነው ያደገችው። ልቧን እስኪደክማት እንኳ ሮጣ አታውቅም። በጣና ሐይቅ ላይ ግን ልቧን እስኪደክማት ዋኝታ ታውቃለች። አሁን ደሞ የባሰ ልቧ ወደኋላ በፍቅር ገመድ እየተጎተተ ነው። በአካል ተገዳ ብትጓዝም በመንፈሷ ከሚራዥ ጋር ቀርታለች። እግሮቿ ደም በደም ሆነዋል። የጭኗ ጠባብቅ ተገሽላልጧል። ከንፈሮቿ ተቆራርሰዋል። ውበታ ጠውልጓል። ከአያሌ ቀናት ጉዞ በኋላ የደባርቅን ኩተማ አለፉ። ከጎንደር ኩተማ ቦኋላ ከመቶ ሀላሣ ሁለት ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘዋል። ወደተራራው አንጋጣ አስገራሚውን ትርኢት ጨለፈችው።

የሾሉ ተራሮች.... የምድር ቀንዶች መስለው ቆመዋል። ተፈጥሮ በአለቶች ላይ ያነፀቻቸው እነዚህ ተራሮች ቆመው እንደጅረት የሚፈሰውን ትውልድ ይታዘባሉ። በተራሮች ጫፍ ላይ አስገራሚው ትርዒት ይታያል....ቲያትር። የሚደባደቡ ዝንጆሮዎች። የሚባዝኑ ወፎች። የሚያላዝኑ ቀበሮዎች። ከረጃጅም አለቶች ላይ ፈልቀው በአለቶች ላይ በቀጭኑ ብትን ብለው ለሚወርዱት ፏፏቴዎች ከሁሉም ተራራዎች በላይ ሰማዩን እየቡዋጠጠ የተኮፈሰው ራስ ዳሽን ተራራ ይቀኝላቸዋል።

ሲጓራ ራስዳሽንን ወደላይ አንጋጣ አይታ ጫፉ ላይ እግዚአብሔር የተቀመጠበት መሰላት። በራስ ዳሽን አናት ላይ የሚጥመለመለው ዳመናና ጉም የጠመጠመ የቅኔ መርጌታ አስመስሎታል። መርጌታ ራስዳሽን ወደ ሰማይ ተጠግቶ ለእግዚአብሔር በጆሮው ይቀኝልታል። መወድሱን ያወርድለታል። እግዚአብሔርም ለመርጌታ ራስ ዳሽን የደመና ጥምጣም የደመና ኩታ ይሸልመዋል። ከተራሮች ሁሉ መርጦ ራስ ዳሽንን እድሜ ስላደለው የበረዶ ሽበት ጣል ጣል አድርጎበታል-ከደመና ጥምጣሙ ሥር። ራስ ዳሽንን ያዩ ጤና ያጣ ካልሆነ በቀር ተራራ ነው አይልም። ግዑዝ የድንጋዮችና የአለቶች ጥርቅም አይመስለውም። ነገር ያረገዘ ህያው አካል ይመስላል እንጂ። የሰሜን ተራሮች ከስሩ ጉባዔ ቃና እየተቀኙ በያሬድ ዜማ ያሸበሸቡለታል። ራስ ዳሽን ከላይ ተከፍሶ ያዳምጣቸዋል።

በዘጠኝ ሺህ ጫማ ከፍታ ቁመቱ ልክ ቆሞ ሰማዩን ይጠባል - ራስ ዳሽን። ይንን ተራራ ቤተ እስራኤላውያን መ·ጭ·ጭ ያሉበት ምክንያት ግልፅ ነው። በንጉስ ሀብታህ ዘመን ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በ2300 ዓመተ ዓለም አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ

እንደገቡ የሚነገርላቸው ቤተእስራኤውያን የአገሩን ውበትና አቀማመጡን አይተው በጣም ስለተደሰቱ ታማኝና ታዛዥ ዜጎች ሆነው በዚህ ተራራ ላይ ለመኖር። ንጉሡን ጠይቀው በመጀመሪያ ቢያቅማማም ብርዳማና ተራራማ ከሆነው ክፍል መሬት እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት በራስ ዳሽንና በቅርቡ ከሚገኙት ተራራማ ሥፍራዎች መሬት ተሰጣቸውና መኖር ጀመሩ። አንዳንዶቹ በቀዝቃዛው አየር ምክንያት ቢሞቱም የቀሩት ግን ተራራውን ተጣብቀው ብርዱን ተቋቁመው ኖሩ።

ተራራውንም በልዩ ልዩ ሥም ይጠሩት ነበር። ሰሜን፣ አሜርጋ፣ አምባራስ፣ አቤር እያሉ። አቤር ማለት አምላካዊ በር ማለት ነው። ተራራውን ለስግደትም ይጠቀሙበት ስለበር ነው። በዘመነ አሪት በየዓመቱ ምዕመናኑ ተራራ ላይ ወጥተው መፀለይ ልማዳቸው ሥለ ነበር።

የሰሜን ተራራ ለቤተ እስራኤላውያን ብዙ ጠቀሜታ የነበረው ሥፍራ ነበር። ተራራው ላይ ወጥቶ በዙሪያው ያለውን ምድር ቁልጭ አድርጎ በአራቱም ማዕዘን ያሉትን ቦታዎች ያሳያል። ታላቅ ከፍታ ያለውና ለውጊያም አመቺ በመሆኑ ይህንን ተራራ መመኘታቸው ለምን እንደነበር መገመት ቀላል ነው። ብዙ ጦርነቶችን ድል አድርገውበታል። የጠላት ኃይል ሲያይልባቸው ከዋሻዎቹ ውስጥ ገብተው እየተደበቁ ያመልጡ ነበር። በኋላም ራሳቸውን ያደራጁና ከዋሻው ወጥተው አለት ደንጊያ እያንከባለሉ ጠላቶቻቸውን ያጠቁ ነበር።

"የኩሽ ልጅ ሬመስ፣ዩዳ እና ሳቢላ የተባሉ ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩት" ይላሉ ወግ ነጋሪ የቤተ እስራኤላውያን ሽማግሌዎች። "ዩዳ በኢትዮጵያ ያለነው ቤተ እስራኤላውያን አባት ነው" ይላሉ ደክሚቸው ጥላ ሥር ሲያርፉ። ሲጓራም ታዳምጣለች። ከየትም ይምጡ ከዬት ግድ የላትም። አንድ ልቧ ወደኋላ ቀርታል። ሌላኛው ልቧ በሰሜን ተራሮች አናት ላይ ተመስጎ የራስ ዳሽንን የተፈጥሮ ትርዒት አብሮ ይተውናል።

ከተራሮች ወረድ ብለው ከተበታተኑት መንደሮች ደረሱ። የከብት በረቶችና የእርሻ ማሳዎች በኮሳላ ጎጆዎች ዙሪያ ይታያሉ ። መንደሩ ውስጥ ከየሳር ቤቶች አናት ላይ የዳዊት ኮከብ ምስል ተሰቅሎ ተመልከታ ግራ ተጋባች።

ከነዚህ የፈላሻ መንደሮች የኅበጡ አሮጊቶች፣ በረሃብ የጠወለጉ ህፃናትና ሽማግሌዎች እየወጡ "ሻሎም" እያሉ ተጥመልምለው የመጣውን ነገደ ፈላሻ ዝዙን እየተቀበሉ እግሩን እያጠቡ ተቀበሉት። ተጓገዙ የደረሰው ከመሸ ነበር። በወናፍ የከሰሉን እሳት ግልጥጥ የሚያደጉት አንጥሮኞችና ቀጥቃጮች የጀመሩትን

ማረሻና ጎራዴ ሠርተው ለመጨረስ ፍም የመሰለውን ብረት በመዶሻ በህብረት ይቀጠቅጣሉ። በጉዞ ወቅት ሽጠው ለመጠቀም።

አባ ፊንሐስ የሲጓራን እጅ እየጎተቱ የዳዊት ኮከብ ምልክት ካላበት ምኩራብ ውስጥ ይዘዋት ገቡ። ቆባቸውን አውልቀው ከምኩራቡ በር ላይ ካለው የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ሲጨምሩት በድንጋጤ ደነዘዘች። አንገቷ ላይ ዓይናቸውን አሳርፈው ማተቧንና ያሰረችውን ባለጉጥ መስቀል ሊያወልቁ እጃቸውን ሲሰዱ ማተቧንና ሚራዥ የሠጣትን መስቀል ጨምድዳ "እንዴ! እረ በስመ አብ ይበሉ! .....ማተቤን?" አለች ክው ብላ።

"ከአሁን በኋላ አያስፈልግሽም።"

"እንዴት ነው የማያስፈልገኝ? መስቀሉን ደግሞ ይልቀቁት ሚራዥ የሰጠኝ ነው። .....ይልቀቁት። እርስዎ ሰጥተውኛል? ...."

"እዚህ ቦታ ላይ አያስፈልግም አልኩሽ። ከአሁን በኋላ አያስፈልግሽም። ከ..ሁን በኋላ የአባቶቻችን አምላክ ታመልኪያለሽ።"

"ሊያሰልሙኝ ነው?"

"አይደለም ልጂ። የእስራኤልን አምላክ አዶናይን እንድታመልኪ ነው። ከአሁን በኋላ አይሁድ ነሽ። የዳዊት ዘር! የነአብርሃምን የነያዕቆብን አምላክ ታመልኪያለሽ።"

"እኔም እኮ የማመልከው አሱን ነው። ሰይፍ በአንገቴ ቢያልፍ ተዋህዶ እምነቴን አልከድም። ማተቤን አልፈታም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን አልክድም። እርስዎ አላሳደጉኝም። ኢየሱስ አባቴ ማርያም እናቴ ሆነው ነው ያሳደጉኝ።" እንባዋ መጣ።

"ባላሳድግሽም ወልጀሻለሁ። አባትሽ እኮ ነኝ ልጂ። እንዴት ልጄን እንድትሳሳት እመክርሻለሁ?" አሏት ቆባቸው የኖረበትን ነጭ ሽበታቸው ዳር ዳር የሠረበትን መላጣቸውን እያሸ።

ማተቧን ጥብቅ አርጋ ይዛ ሲከራከሩ። አይሁዶች የሚደፏትን ትንሽ ብጣቂ ቆብ እናታቸው ላይ ጣል ያደረጉ .ሽማግሌ የአይሁድ ካህን የምሽቱን ጸሎት በአብራይስጥ ቋንቋ ማሰማት ሲጀምሩ ሁሉም መድረኩ ላይ ወደ ቆሙት ካህን አማተሩ። ፀጥታ ሰፍኖ የእሳቸው ድምጽ ብቻ ማስገምገም ጀመረ።

የምሽቱ ፀሎት ዘወትር ማታ ማታ ሀሌይ በምትጠልቅበት ሰዓት የሚያደርሱት ፀሎት ነው። ሽማግሌው ካህን በሚርገበገብ ድምፃቸው ጸሎቱን ጀመሩ። "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አስራኤል፣ አምላክ ያዕቆብ፣ አምላክ ሙሴ ወዓሮን፣ አምላክ ዳዊት መሰሎሞን። በሠርክ ወበነግህ በኩሉ ጊዜ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘነብረ ግቢየ መመንክረ በህቲቱ ቅዱስ። ወይምላዕ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር ኩሎ ዓለመ። ይትባረክ ወይትቀደስ ስመ ስብሐቲሁ። ቅዱስ ;ንያል ወቡሩክ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም አለም።

አሜን" እስከዚህ ያለው ፀሎት ግዕዝ ስለሚመስል ገባት። "እምላካችን የተባረከ ነው። የአብርሃም አምላክ፣ የዳዊትና የሰሎሞን አምላክ። ለአምክ ምስጋና ይሁን ዘወትር፣ ጠዋትም ማታም። ታላላቅና አስደናቂ ነገሮችን ሰርታል። ብቻውን። ቅዱስ እሱ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ታላቅነት መላውን ዓለም ይሞላዋል። ታላቅ ስሙ የተባረከና የተቀደሰ ነው። እርሱ ቅዱስ ነው። ታላቅ ነው። ለዘለአለሙ የተባረከ ነው።" ማለት መሆኑ ገባት።

ቀጥለው የፀለዩት ግን አልፎ አልፎ ጣል ጣል ካሉት የግዕዝ ቃላት በቀር አልሰማት አለ። "ሄርዝጋ ዲርሚጋ ሰሁንቱጋ ወሬዛ በኃይሉ ወወሬዛ በምኩናኑ እደረሽ ወሴጋ ይዝምዝ። ሰሐር ሰሀአርስጋ ንጉሥ በላዕለ ኩሉ ለሊከ ነጋሢ ድርሚሊ ነገሣ ሰናር የደራ አዶናይ ምዜናን። አዶናይ ዘሃሎ ወይሄሉ ገርግሻው አዶናይ። ዲርማ ግርግሻው ይትአየን መልአከ እግዚአብሔር አውዶመ ለአለ ይፈርህወ። እንኩቶን ከሸንጋው አዲሪጋው ናሁ መልአከየ የሐውር ቅዳሜየ እግዚኦ በሰማይ ሳህልከ እግዚኦ ዋው ይምጻእ ምህረትክ። እግዚኦ ሳማይሊ ሰማውሶ ኪሳሁሊ አነደገሊገመሰ ....." ሽማግሌው ካህን ትንፋሽ አጥሯቸው የሚወድቁ መሰሳት። አሳቸው ያለማቋረጥ በተንተገተጉ እሷን ደከማት።

ግራ ስትጋባ ያዩአት አባታ አባ ፊንሐስ በሹክሹክታ እየተረጎሙላት ነው። "የነበረውና ያለው አዶናይ፣ ታላቁ አዶናይ። ለሚፈሩት መጠኒየቸው ነው። እንደዚህም ይላል ፡ አዩት መልአኬ ከፊታችሁ ሆኖ ይመራችኋል።" ጌታ ሆይ፣ ፍቅር የተመላው ደግነትህ በሰማያ ይገኛል። አምላክ ሆይ ምህረትህ ይወርድልን ዘንድ እንማፀንሃለን። የነበር'ኸውና ያለ'ኸው አዶናይ፣ የአብርሃም አባት፣ የይስሃቅ አባት፣ የያዕቆብ አባት፣ የእራኤል አባት፣ አባታችን፣ እምነታችን በአንተ ላይ ነው። የነበር'ኸውና ያለ'ኸው አዶናይ፣ መላእክትህ ቀን ቀን አያርፉም፣ ሌሊት ሌሊት አይተኙም።.....የእግዚአብሔር ስም ምስጢራዊ ነው፣ ቃሉም የተቀደሰ ነው፣ የእሱ ቃል ለነፍስ የደስታ ምንጭ ነው፣ ለሥጋም መድኃኒት ነው። አምላክ እንዲህ ይላል፣ ልጄ የበኩር ልጄ እስራኤል፣ ልጄ እሱ ነው። ....በእርግጥም እስራኤልን የፈጠር'ኸው ለክብር ነው። ጥሬ ሥጋ አይበላም፣ የፍየል ደምም አይጠጣም....." ካህኑ አይደክመውም። አባ ፊንሐስም ከጀርዋ ጥግ በረጅም ጢማቸው ከተደፈነው አፋቸው ውስጥ ትርጉሙን ያፈልቁላታል። ፀሎቱን በቃላቸው ስለሚያውቁት የሰውየውን ድምፅ አያዳምጡም። አፍንጫቸውን የተያዙ ይመስል እየተነፋነፉ ነው የሚተረጉሙላት። እሷ ግን የምኩራቡን ውስጥ እየቃኘች ነው። ወዲያው ፀሎቱ አብቅቶ ሽማግሌው ንግግር አደረጉ። "የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን። በዜተ አስራኤላውያን ዘንድ ቅዱስ

ከሆኑት ተራሮች የመጣችሁ ከዳሽን ቅዱስ ተራራ፣ ከምድራሮ ቅዱስ ተራራ፣ ከጃኒ ፈንቃራ ቅዱስ ተራራ የመጣችሁ የእስራኤል ቅዱሳን አባቶች እንኳን ደህና መጣችሁ። ሻሎም" አሉ ሁለት እጃቸውን ከፍ አድርገው። ሁሉም ባንድ ላይ "ሻሎም።" አሉ እጆቻቸውን እንደ ካህኑ ከፍ አድርገው።

በየዓመቱ የቤተ እስራኤላውያን ካህናት ከሚፀልዩባቸው ቅዱሳን ተራራዎች የመጡት ሽማግሌዎች በተለይ የተቀደሰችዋን ምድር ከነአንን በአይናቸው ሊያዩ ጊዜው በመቅረቡ ተደስተዋል። በየአመቱ ቅዱሳን ተራራዎች ላይ እየወጡ ይፀልዩ ነበር። በጭልጋ አውራጃ ከሚገኘው ዳሽን ተራራ ላይ፣ በደንቢያ አውራጃ ከሚገኘው ምድራሮ ተራራ ላይ፣ በጎንደር አውራጃ ከሚገኘው ጃኒፈንቃራ ተራሮች ላይ እየወጡ የመታን ዘመዶቻቸውን ስም እየጠሩ ‹‹አሚያን›› ይቀነጥሩላቸዋል። ‹‹አሚያን›› ማለት በልብሳቸው ጫፍ የሚቋጥሩት ትንሽ ጥሬ ጨፍ ነው። እሚያኑን ቆንጥረው አለት ላይ ይበትኑታል። ይህን ሲያደርጉ የመታኑ ነፍሳት ዕረፍት ያገኛሉ ብለው ያምናሉ። ስለዚህም ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የሚቀነጥሩት እሚያን ጨፍ ይዘዋል።

ሲጻራ የምኩራቡን ውስጣዊ ዝባዝንኬ በዓይኗ ትዳስሳለች። ምኩራቡ ከእስራኤል በመጡ ትርኪ ምርኪ ቁሳቁሶች ተሞልቶአል። ከቴልአቪቭ የመጣው ‹‹ቶራ›› የተባለው የአብራውያን ቅዱስ መፅሐፍ ከጥግ ካለው ሰፊ አትሮንስ ላይ ተቀምጧል። የዳዊት ኮከብ ምስል የተቀረፀባቸው ሸክላዎችና የጌጥ አቃዎች ዙሪያውን ተሸኮትኩተዋል ።

የፀሎቱ ጊዜ አብቅቶ ሁሉም ያለውን ተቃምሶ አጥንት ሰብሮ የሚገባው የዳሽን ብርድ እያንዘፈዘፈው ግማሹ ከውጭ ቦታ ያገኘውም ቤት ውስጥ በየወለሉ ላይና በየመደቡ ተከራምቶ ተኛ።

ሲጻራ ከአባ ፊንሐስና አብረዋቸው ጀልባውን ሲነዱ ከነበሩት ከአባ ማቴዎስ መሃል ተኛች። እንቅልፍ ሲጥላቸው አንዳታመልጥ አንድ እጇ በገመድ ከግንድ ጋር ታስራ። እኩለ ሌሊት አካባቢ ከጭኖቿ መሃል ቅዝቃዜ ተሰማት። "የፈጣሪ ያለህ!" አለች። የወር አበባዋ ነው። ትንሽ ገድቦ የሚያስቀርላት የውስጥ ሱሪ አንኳ አልለበሰችም። በርግጥ የውስጥ ሱሪ ለብሳ አታውቅም። የለበሰችው ከላይ እስከታች የተንቦረሰሰ የወይባ አቡጀዲ ቀሚስ ነው። ወገቡዋ ላይ ብቻ ሰፊቀበቶ የሚመስል ቅናት የሚባለውን የገዳማውያኑን መታጠቂያ ታጥቃለች። እማሆይ ወለተ ኪሮስ የወር አበባዋ ሲመጣ የምትጠቀመውን ዘይ አስተምረዋት ነበር። ነገር ግን ጉዝጉዝዋ ውስጥ የደም ጨርቅ ስላልያዘች ዘይውን ለመጠቀም አልቻለችም። የነበራት ብቸኛ አማራጭ ማልቀስ ነው። ማነፋረቅ።

ጠዋት በሰሜን ተራሮች ጫፍ ፀሐይ እግሯን ስትሰድ ሳትረግማት አልቀረችም። ቀሚሷ በደም ተዘፍዝፏል። የተኛችበት ምድር ተከፍቶ ቢውጣት መርጣ ነበር።

አባፊንሐስ ተነስተው ልጃቸው ላይ ሲያማትሩ በድንጋጤ ታቅፈው አነሷትና እጇን ፈትተው በቅርብ ወደሚገኘው ወንዝ ይዘዋት ወረዱ። ወንዙ ውስጥ እስከልብሷ ገብታ ልብሷን ላይዋ ላይ አጥባ ብትወጣም ከጥቂት ቆይታ በኋላ መልሶ ተጨማለቀ።

ማታ የምሽት ፀሎቱን የመሩት ሽማግሌ የአይሁድ ካህን እየተጣደፉ መጡና በቁጣ "እንዴት የአባቶቻችንን ሥርዓት ትጥሳላችሁ? እንዴትስ ሰባት ቀን ሳይሞላት የመንፃት ሥርዓት ታደርጋላችሁ። እናንተ ቤተ እስራኤላውያን ነን አላላችሁም? ከሆናችሁ እንዴት የመርገም ጎጆ ያለበትን አትጠይቁንም....." ሊገባት አልቻለም።

"በይ ተነሺ!....."

ወደ አንዲት ከመንደሩ ርቃ ወዳለች ደሳሳ ጎጆ ቤት ይዘዋት ሄዱና "ግቢ! ከሰባት ቀን በኋላ የመንፃት ሥርዓት ይደረግልሻል" ብለዋት ጎጆዋን ከውጭ ዘግተውባት ወደመጡበት መንደር ተመለሱ።

አባ ፊንሐስም ከጎጆዋ በር ላይ ተቀምጠው አቀርቅረው ከቆዩ በኋላ ወደ ወንዙ ወርደው በመታጠብ የመንፃት ሥርዓት አደረጉ። መርገሚ የመጣባትን ሴት ስለነኩ።

እምነቱን እጅግ አጥባቂ የሆነው ቤተ እስራኤላዊ አይሁድ ገበያ ወጥቶ ሲመለስ እንኳ ከቤቱ ከመግባቱ በፊት ወንዝ ወርዶ ታጥቦ መንፃት አለበት። የቤተ እስራኤላውያን ወገን የሆነ ሰው ከክርስቲያኖች ወይም ከሙስሊሞች ጋር እህል አብሮ ቢቀምስ ወይም አብሮ ከጠጣ በድርጊቱ ተፀፅቶ ንስሐ ገብቶ ለተወሰነ ጊዜ የመንፃት ሥርዓት ካልፈፀመ በስተቀር ወደ ቤተ እስራኤላውያን የስግደት ቦታ እንዳይገባ ይከላከላል። የመንፃቱን ሥርዓት የሚፈፅም ሰው ጥሬ ሽንብራ እየቀረጠመ ለሰባት ቀናት መፆም አለበት። የፆመ ጊዜ ሲያበቃ የንሥሐ ፀሎት ከዳዊት መዝሙር ተደግሞ ፀጉሩን ተላጭቶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት።

አባ ፊንሐስም ከማህደራቸው የዳዊትን የመዝሙር መፅሐፍ አውጥተው «ተሰለለኒ እግዚኦ» የሚለውን ደግመው ከወንዙ ውሃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ካሉ በኋላ የመነፃት ሥርዓቱን ፈፅመው ወጡ።

ሲጓራ አንዲት ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ቤተ እስራኤላዊት ልጃገረድ የወር አበባዋ በሚታያት ጊዜ እንደምታደርገው ለሰባት ቀናት ከመርገሚ ጎጆ ከሰነበተች በኋላ ወደ ወንዝ ወርዳ ሰባት ጊዜ ወንዙ ውስጥ ጠልማ ወጣች። በዚህ አላበቃችም። የፀሐይ

መጥለቂያ ሰዓት ደርሶ ጭልምልም እስከሚል እዚያው መዋል ነበረባት።

በዚህ ጥብቅ ሥርዓት ውስጥ እንዴት መኖር እንደምትችል ግራ ገብቷታል። ለሁሉም ነገር የመንፃት ሥርዓት አይቀሬ ነው። ከቤተ እስራኤላውያኑ አንዱ ገበያ ወጥቶ የቤተ እስራኤላውያን ወገን ካልሆኑ ሰዎች ጋር ሲገበያይ ቢነካካ ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት ወንዝ ወርዶ በውሃ ታጥቦ መንፃት አለበት። በገበያው ውስጥ የተጠቀመባቸውን ቁሳቁሶች፤አቁማዳ፣መጫኛ፣ አጎዛ፣ ጀንዲ፣ ቁርበት እንኳ ማጠብ አለበት።

ሲጓራ ወንድ ልጅም ብትሆን ኖሮ የመንፃቱ ሥርዓት አይቀርላትም ነበር። ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሴሊት በህልሙ ከብልቱ ነባዘር ቢፈስበት ማለዳ ሲነሳ የተኛበትን ምንጣፍና የለበሰውን ልብስ ጠቅልሎ ወንዝ ወርዶ ማጠብ አለበት። ይህ በሚደርስበት ጊዜ በቋራኛ ቋንቋ "ሰርክ ተነካ" ይባላል። ሰውነቱንም ወንዝ ውስጥ በመጥለም ማንፃት አለበት። እድሜው ሃያ አመት ሲሞላም ሚስት ማግባት ግዴታው ነው። ከሚስቱ ጋር ሴሊት ግብረ ሥረ ግንኙነት ከፈፀሙም በበነጋታው ከሚስቱ ጋር ወንዝ ወርደው ሁለቱም ተጣጥበው መንፃት አለባቸው። የኢትዮጵያ ቤተ እስራኤላውያን ይህን ሥርዓታቸውን ከቅድመ አሪት ጀምረው ጠብቀው የኖሩበትን ምድር ለቀው ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ በአውራ ጣታቸው ከቆሙ ሰነበቱ። እስራኤል ሀገር ውስጥ ካላቸው የምኩራብ ቁጥር በላይ ምኩራቦች የሰሩባትን ምድር ኢትዮጵያን ለቀው ለመሄድ ከመላው ኢትዮጵያ ተጠራርተው ነቅለው ወጥተዋል።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከቀናት በኋላ ጉዞው ተጀመረ.....ወደ ሱዳን። ተጓዦቹ ንዛቸውን በአህያና በትከሻቸው ጭነዋል። በማዳበሪያና በአቁማዳ፣ በስልቻና በሸክላ ራሳቸው ላይ አቁረው የበረሃውን ጉዞ ተያያዙት።

ሱዳን በረሃ ከመድረሳቸው ብዙዎች ህፃናትና አዛውንቶች የበረሃ ሲሳይ ሆኑ። በረሃብና በውሃ ጥም እየተሰቃዩ አለቁ። አንዳንዶች ደግሞ ያሳደገን መራት ይብላን ብለው ወደ ነበሩበት ተመለሱ።

በእባብና በጊንጥ እየተነደፉ በሱዳን በረሃ ውስጥ የወደቁትም ብዙ ናቸው። ሲጓራ በዚህ ጉዞ ያየችውን ስቃይ ገሃነም ውስጥ ብትገባ እንኳ የምታገኘው አልመሰላትም። ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ ለመድረስ ከሁለት ወራት በላይ አስቸጋሪና አድካሚ የእግር ጉዞ አደረገች።

ከሱዳን የስደተኞች መጠለያ ለመድረስ ሁለት ማይልስ ርቀት ሲቀራቸው ደግሞ አባ ፊንሐስ በእባብ ተነድፈው ወደቁ። የእባቡ መርዝ በሰውነታቸው ለመሰራጨት አፍታ አልፈጀበትም። አባ ማቴዎስ የፅባቡን መርዝ የሚያረክስ መድሃኒት የሚቀመሙባቸው እፅዋቶችን ፍለጋ ቢንከራተቱም ዝቅ ሲሉ አሸዋ ቀና ሲሉ የሚያቃጥል ሰማይ በሚታይበት የሱዳን በረሀ ውስጥ ሊያገኙ አልቻሉም።

አባ ፊንሐስ በጣረ ሞት እየተንዘፈዘፉ ሲጓራ ያሰረችውን ባለጉጥ መስቀል ጨምድደው ይዘው «ል....ጀ አ....አሁን ወደሁዋላ እንዳትመለሽ ከጊዜ በሁዋላ ግን በዚህ መስቀል.....» ያሉት ሳይገባት ሁሉ ነገር ተጠናቀቀ። ሲጓራ ስቅስቅ ብላ እንድታለቅስ ያደረጋት አባትነታቸው ሳይሆን ከስደተኞች ጣቢያ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው በመሞታቸው ነበር። ግን አንድ የተናገሯት ቃል በጆሮዋ ደጋግሞ አቃጨለባት። "ወደኋላ እንዳትመለሽ!!.....ወደኋላ እንዳትመለሽ....."

"አዎን! ከእንግዴህማ ልመለስ ብልስ በየት ብየ እመለሳለሁ? በቃ ይሄበሀይወቴ ሊያጋጥመኝ የታቀደ ነገር ነው።" አለች በልቧ። "ወደ ኋላ አልመለስም።"

እለቱ ዕለተ ሰንበት በመሆኑ አባ ፊንሐስ አልተቀበሩም። በአይሁዳውያን ሥርዓት መሠረት በዕለተ ሰንበት፣ በቅዳሜ ቀን የሞተ ሰው አይቀበርም። የተቀበሩት በነጋታው ከሱዳን የስደተኞች ካምፕ አቅራቢያ ባለ አሸዋማ ቦታነው። እንደ ትክክለኛው የአይሁድ ሥርዓት ከሆነ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ጥቁር አይሁድ ሥርዓት የአባፊንሐስ የመቃብር ጉድጓድ አራት ማዕዘን ተደርጎ በአምስት ሜትር ጥልቀት መቆፈር ነበረበት። የአስከሬኑ አራስና አግር በሚያርፍበት ወገን "መርገብ" የሚባለው ጠፍጣፋ ድንጋይም መጣል ነበረበት። ጉድጓዱ ተቆፍሮ ሲያልቅና "መርገቡ" ከሥፍራው ሲደረግ ከበላይም ከበታችም ባዶ ይሆናል። መርገቡ በሁለት በኩል በጫፍና በጫፉ ብቻ ጉድጋዱ መካከል ተይዞ ይንጠለጠላል። ይህ የሚደረገው በድንኑን የያዘው ሬሳ ሳጥንም ሆነ ሌላ መጠቅለያ መሬቱን ነክቶ እንዳያረክሳት ነው። አስከሬኑ ወደ መጨረሻ ማረፊያው ከመግባቱ በፊትም ካህናቱ መቃብሩን እያጠኑ ይሸው ‹‹ቤትህ፤ ከእንግዴህ ከዚህ መመለስ የለም›› ብለው መሰናበት ነበረባቸው። በሶስተኛውም ቀን ጠጉሯ፣ ቀንዶቿና ጥፍሮቿ ባካሏ ሁሉ ትክክል የሆነች እንከን የሌላት ቀይ ጊደር ታርዳ ደምዋና የተቆራረጠ አካሏ በወይራ ወይም በግራር ፍልጥ በሚነድ እሳት ተቃጥሎ አመዱን በአዲስ ሸክላ አታ ካህናቱ መከፋፈል ነበረባቸው። አመዱም በውሃ ተበጥብጦ ሬሳ በነካውና በቀረበው ሰው ላይ ሁሉ መረጨት ነበረበት። የጊደራቱ

አመድ እርኩስ ነገር የነካ ሰውን ያነፃል ተብሎ ስለሚታመን። ለአባ ፊንሐስ ግን ከዚህ ሁሉ ሥርዓት አንዱም አልተፈፀመም።

ሲጓራ በዚህ የሱዳን ስደተኞች ካምፕ ከአባ ማቴዎስ ጋር እየተዘዋወረች አሰቃቂውን ጉስቁልና ተመልክታለች። በረሃብ የሞገጉት ህፃናትና አዛውንቶች አጥንታቸው ይቆጠራል። የተቦተራረፈ ጋቢ የለበሱ በሽተኞች ሞት ሞት ከሚሸቱት ከቀይ መስቀል ድንኳኖች ውስጥ እየሞቱ ይወጣሉ። ነጫጭ ጋወን የለበሱት ነጫጭ ዶክተሮች በሽተኛ የሚወጉበት መርፌ በመልአከ ሞት የተሞላ ይመስል የሚያክሙት ሁሉ እጃቸው ላይ ይሞታል።

ጠኔ ካነጠፋቸው ስደተኞች መሃል አንዲት ጠና ያለች ሴት ከኢትዮጵያ ቋጥራ ያመጣቺውን አርባጫ አፈር ስትበላ ስለታየች ሌሎችም ለመከፈል ከበቧት። ሌላኛው ሽማግሌ ደግሞ ለእሚያን የቋጠሩትን ጤፍ ሊቅሙ ታዩ።

ቀድሞም ምንም ስንቅ ያልያዙት አባ ማቴዎስና ሲጓራ ለመጨረሻ ጊዜ ያገኟትን ቁራሽ የበቆሎ ቂጣ ተገላገሉባት።

"አባ እርስዎ ይብሏት አትበቃንም። "

"ልጄ አንቺ ብያት አትበቃንም።"

"አይሆንም አባ እርስዎ ይጉረሷት።"

"ልጄ እባክሽ አንቺ ብይልኝ እኔማ ባይሆን እችለዋለሁ። ብበላውም ጥፍር አንጂ ሰውነት አይሆነኝም።"

ሲገላገሉ አንድ በልቶ የማያውቅ የሚመስል አጥንቱ የገጠጠ ሰው ቁራሿን ቂጣ አንስቶ ከአፉ አደረጋት።

«እርፍ!» አለች ሲጓራ «ግልግል!»

አባ ማቴዎስ ወደ አንዲት የማሽላ ገንፎ ወደ ምታገነፋ ሴት ሲጓራን ይዘው ሄደው "እባክዎ ልጀ ረሃቡን አልቻለችውም" አሏት።

"ታዲያ እኔ ዩኒሴፍ ነኝ? ለራሴ ልጀ ደሜን እየጠባ እያዩኝ። ይበሉ ወደመጡበት። ቀልደኛ ኖት?"

"ምን ተሻለኝ ልጀ?!" ተሸማቀቁ። ዙሪያ ገባውን ሲያማትሩ ቂጣዋን ከሰለቀጣት ሞጋጋ ሰውዬ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ። መልስልኝ አልለው ነገር! አሉ በሆዳቸው።

"ልጀ ቆይ እስከ ነገ የሚበላ እንፈልጋለን። ብናጣ ብናጣ ተነገ ወዲያ እናጣዎ።" ተስፋ እየሰጧት ነበር። እሷ ግን ለደቂቃ የሞትቆይም አልመሰላትም። ከረሃቡ ውሃ ጥሙ ባሰባት።

ትዋኝበት የነበረው የጣና ሐይቅ ትዝ አላት። እየሳቀች የምትንቦራጨቅበት ቀዝቃዛ ውሃ። በሃሳብ ሃይቁ ውስጥ መዋኘት ጀመረች። በሁለቱ መነታ ደሴቶች መሃል ስትዋኝ ታያት። ቀጥሎ ደግሞ ሚራዥን አየችው። እየዋኘ መጥቶ በጨለማው ውስጥ አለቱ ላይ ተቀምጠው ጨረቃዋን እያዩ ስለፍቅር ሲዘምሩ። መቃብር ቤቱ

ውስጥ ገብተው ፍቅርን ሲጎራረሱ። መቃብር ቆፋሪዎች መጥተው ሲያስወጧቸው። አባ ፊንሐስ ከሚራሹ ለይተው ጀልባዋ ውስጥ ሲከቷት.....ወይኔ! ብላ ከሐሳቧ አለም ነቃች። ብዙ ደቂቃዎችን በሐሳቧ በመቆየቷ ረዛብና ጥሟን ረስታው ነበር።

አባ ማቴዎስ ፈገግ አሉ። ከማህደራቸው የከተቱት አርባጫ አፈር ትዝ ሲላቸው። አርባጫውን አፈር ከማህደራቸው ዘግነው እንደትበላ ለመኑዋት። «እባክሽ ልጄ ባይሆንለነፍስሽ መያዣ ይሆናል።»

ወዲያው ህፃን ልጇ የሞተባት ሴት ኡኡታዋን ስታቀልጠው ወደ ሴቷ ዞረች። ገንፎ የከለከለቻት ሴት ነበረች። ለልጇ ገንፎውን በስሱ ሳታበላው ሞተ። ጦሙን በባዶ አንጀቱ ፈጅሙን የመንገደ ሰማይ ጉዞ ያለሥንቅ ተያያዘው። ብዙም ሳይቆይ ከድንኳኖቹ ራቅ አድርገው አሸዋውን ቁፍር ቁፍር አርገው ቀበሩላት።

ሴትዮዋ ልጅዋን ቀብራ ስትመለስ ገንፎዋ ተበልቶ ጠበቃት። "ማነው ገንፎየን የበላብኝ?!" አንባረቀች በሌለ አንጀቷ። እየተመናቀረች መጥታ ሲጓራ ላይ አፈጠጠችባት። ካንገትዋ ሥር የተገታተረው ጅማትዋ ከሩቅ ይቆጠራል።

"አንቺ ነሽ?!" አለቻት። "አሁን ልጠፍጥፍሽ?"

"አረ እኔ አይደለሁም! ማርያምን!" እመቤቴ ቅንጥስ ታርገኝ!" አለች ሲጓራ ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ። አፍዋ በሙሉ ጭቃ ሆኖአል። የምታላምጠው አርባጫ አፈር በከንፈርዋ ጻርጻር ተዝረክርኮአል።

"እሽሽሽ....." አሉ አባ ማቴዎስ የሲጓራን አፍ አፍነው።

"ማርያምን አትጥሪ። አይሁድ ካልሆንሽ አይወስዱሽም"

"አይውሰዱኝ! አላበዙትም? ደግሞ እመቤቴን ማለት አልችልም? አሷን ጠልተው ማንን ሊወዱ ነው?"

"እየውልሽ.... ለእነሱ እኮ ኢየሱስ ገና አልተወለደም። እግዚአብሔር አንድ አምላክ አንጂ አንድም ሦስትም ነው ብለው በስላሴ አያምኑም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከማርያም የተወለደ የእግዚያብሔር ልጅ ነው የሚለውን አይቀበሉም። ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ተሰቅሎ፣ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ፣ከሞት በተነሳ በዓርባኛው ቀን ወደ ሰማይ አረገ የሚለውን ትምህርት አይቀበሉትም፣አያምኑበትም። መሲሑ ገና ከእስራኤል ወገን እንደሚወለድ ነው የሚያምኑት። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና አይወልድም፣አይወለድም፣አይሞትም፣ይገድላል እንጂ።ብለው በፅናት ያምናሉ" አሷት አባ ማቴዎስ ሰው እንዳያሰማቸው በለሆሳስ።

"ለእኔ ግን ኢየሱስ ተወልዶአል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳም ንዶታል። ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን መካከል ተነስቶ በአርባኛው ቀን አርጓል።..... አላዩም?!

.....ይህ ሲሆን በስፍራው ያልነበረነው እኛ ስናምን ለምን እነሱ ያዩት አላመኑም?" ጥያቄዋ አይጣል ነው ድሮም።

"...‹ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው › ተብሎ ተፅፏል ልጅ። ራሱ ኢየሱስም ‹ነቢይ በሀገሩ አይከበርም› ብሏል።"

"እሱማ ልክ ልካቸውን ነግሯቸው ነበር።"

"በቃ ዝም በይ። እሱ ራሱ ያልመሰላቸውን!" ደንቋቸው ፈገግ አሉ። "በቃ ልጄ ዝም በይ። ባካባቢያችን ያሉት ከሰሙን ያቃጥሩብናል። እዚህ በረሃ ውስጥ ጥለውን ከሄዱ ደግሞ መድረሻ የለንም ሀገራችንንም ጥለናት መጥተናል። ተይ! ‹ጅብ እስኪይዝ ያነክስ› ብለዋል አበው። ብቻ ኢየሩሳሌም እግባ እንጂ በሰሌሆም ወንዝ አቅራቢያ ከሚገኘው ንጉሥ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ከተናዘዘላት የርስት ቦታ ላይ ካለው ዴር ሡልጣን ገዳማችን ገብተን እንቀመጣለን። እስከዚያ ግን የልብሽን በልብሽ ያዥው"

አባ ማቴዎስ ምንም እንኩዋ እስራኤላዊ ባይሆኑም ኢየሱስ የተመላለሰባቸውን ቦታዎች ሁሉ ተሳልመው ዴር ሱልጣን ገዳም የመግባት ህልማቸውን እውን ለማድረግ ጉዋጉተዋል። ለዚህም ሲሉ የምንኩስና ቆባቸውን ከራሳቸው አውርደው ልባቸውላይ ደፍተውታል።

ገንፎዋ የተበላባት ሴት የልጇን ሞት ረስታ ረሃቧን ልታስታግስ ከጠረጠረችው ጋር ሀሉ ስትሟገት ሲጓራና አባ ማቴዎስ እየተመለከቱ ምሽቱ እየገፋ ሄደ።

በድንገት በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ ሽራ የለበሱ የጭነት መኪናዎች ሙብራታቸውን እያንበገበገ መጥተው ሲቆሙ የታጠቁ ከማንዶዎች ከመኪናዎች ወርደው በፍጥነት አካባቢውን ተቆጣጠሩት። በየድንኳኑና በውጭ አሸዋ ላይ የፈሰሱት ፈላሻዎች እየተጋፉ፣ እየተዋከቡ ወደ መኪናዎች ተጫኑ። ፈላሻ ያልሆኑትም ስማቸውን ‹ሙሴ፣ያዕቆብ፣ይስሐቅ› እያሉ እየተመዘገቡ ተጫኑ። አሸዋው ላይ እንቅልፍ እንደ ስጦ ያሰጣቸውም ዓይኖቻቸውን እየሞገሞቁ ተነስተው ሰልፉ ውስጥ ተቀላቀሉ።

ሞላድ ለዘመቻ ሙሴ ያዘጋጃቸው እነዚህ መኪናዎች በአንድ ጊዜ መቶ ሰው ብቻ መጫን የሚችሉ ቢሆንም መኪናው ላይ የሚወጡት ግን ከእጥፍ በላይ ነበሩ። በምግብ እጥረትና በበሽታ ሲሰቃዩ በመኖራቸው እንኳንስ በመኪና በሰይጣናት ፈረሶች ላይ ተፈናጠውም ቢሆን ከዚህ ምድራዊ ገሃነም ማምለጥ ይፈልጋሉ።

ፈላሻዎቹ በተዘጋጀላቸው አውሮፕላን ወደ ቴልአቪቭ ለመብረር ገና በበረሃው ውስጥ በሞላድ ወደተዘጋጀው አውሮፕላን ማረፊያ ለመድረስ የስድስት ሰዓት የመኪና ጉዞ ማድረግ አለባቸው።

ሲጓራ ሰልፉ ውስጥ ያለውን ግፊ አልፋ መኪናው ውስጥ ልትገባ ስትል አባ ማቴዎስ ስለጠፉባት ተመልሳ ፍለጋ ስትጀምር

ኢትዮጵያ ውስጥ ራሱን ተላጭቶና ለመመሳሰል ፊቱን የዋልካ ጭቃ ተቀብቶ የነበረው ነጭ ሰውዬ እጇን ይዞ እየጎተተ መኪናው ላይ አስወጥቷት ‹‹ይመታል፤የራስህን ተጓዝ፤ይመታል፤›› ብሏት ሄደ። መኪናው ውስጥ አፏን ከፍታ ቀረች። አማርኛውን አወላግዶ በመናገሩ ሳይሆን በአባ ማቴዎስ መጥፋት።

አውሮፕላኑ ማረፊያ እስኪደርሱ ተፋፍነው ከቆሙት ሰዎች መሃል ብዙዎቹ ለዘለአለሙ አንቀላፉ። መውደቂያ ቦታ ስለሌለ በቁማቸው ሞተው ከመኪናው እስኪራገፉ በቁም ሸክም ሆነው ቆዩ። ከመኪናው ከወረዱ በኋላ በረዘው ውስጥ ታጉረው ቆሙ። ሲጸራ በውኸንብሩና በግርግሩ መሃል እየተዘዋወረች አባ ማቴዎስን ብትፈልግም ልታገኛቸው አልቻለችም።

አስፈሪው አውሮፕላን እያስገመገመ ሲያርፍ የበረሃውን አሸዋ በሙሉ ዓይኗ ውስጥ የከተተው ይመስል ማየት አቃታት።

በነፋሱ ተገፍትራ ከወደቀችበት ስትነሳ ብዙ ፈላሻዎች አይተውት በማያውቁት አውሮፕላን ተደናግጠው ወደ በረሃው እየተሯሯጡ ተበታተኑ። እሷ ግን ገዛነም ቢመጣም ላትንቀሳቀስ ወስናለች። አውሮፕላኑ ውስጥ ቀድማ የገባች እሷ ነበረች።

ከዚያ በረሃ ተነስቶ ቴልአቪቭ እስኪደርስ አውሮፕላኑ ውስጥም ብዙዎች ላይመለሱ ሲያሸልቡ አይታለች። አሁን ሞትን ለምዳዋለች። ፍርሃቷ ሁሉ ተሟጦ አልቋል።

ቴልአቪቭ ሲደርሱ ቤተ እስራኤላውያኑ እየወደቁ እየተነሱ አስፋልቱን ሲስሙ ቆማ እያየች ነበር። "የተቀደሰው ምድር ይሄ ነው በቃ? ወይ ቅዱስ እግዚአብሔር!" ብቻዋን አግተሙተመች። አባቷን አጣች። አሁን ደግሞ ከአባ ማቴዎስ ተነጣጠለች። ደርቃ ቀረች። «ያለ እኔ ማንም ለእኔ የለኝም በቃ። እግዚያብሔርም ፊቱን አዙሮብኛል። ያዙርብኝ እንጂ! ገዳሜንና ፍቅሬን ጥዬ የመጣሁ ከሃዲ አይደለሁ! ግን እኮ እግዚያብሔር ባይተወኝ ኖሮ እኔ ጥያቸው ላለመምጣት ታግዬ ነበር እግዚያብሔር ሊረዳኝ ስላልፈለገ ነው በቃ። እራሴን ማዳን አለብኝ። ለንሰሐ ሞት እንድበቃ። ባልበቃስ! ምናባቱ ከዚህ በላይ ገዛነም አለ?» በውስጧ ስትብላላ አንዲት አሮጊት ከጥጓ ተገለናልፋ ወደቀች። ሌላ ህፃንም ልንቁስቁስ ብሎ ተከተላት። ሞት በረከተ። አባ ማቴዎስን ብትፈልግም ልታገኛቸው አልቻለችም። «ሞቱ? ምናለ ቁጣዋን ቢበሏት ኑር! እኔና! ....እኔ አፈር ልብላ! ....እኔ ነኝ ስግደደር ያስወሰድክባቸው!...ለኔ ብቻ አበሉኝ እንጂ አርባጫውን አፈር ቢቀምሱ ኖሮ እንደኔ ነፍሳቸውን ያቆዩአት ነበር።..... አሁን በየት ብየ ነው የምሄደው? ዬር ሱልጣን የሚባለው ገዳምስ በየት በኩል ይሆን?» እያለች ስታውጠነጥን ኢትዮጵያ ውስጥ ፊቱን በዋልካ ጭቃ ተለቅልቆ

ያየችው ፈረንጅ መጥቶ "አንቱ? ና! ተከተለኝ! ማቴዎስ ሞቷል!" ሲላት ድርቅ ብላ ቀረች።

"ሞቱ?" አለች። "እኔ አፈር ልብላ።"

ክንዷን ይዟት መኪና ውስጥ አስገባትና ተፈተለከ። «አናንያ እባላለሁ።» አላት እዩከነፈ። አልመለሰችለትም። እየዞረ ያያታል።

ከአንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ሲያስገባት ስፍር ቁጥር የሌለው ፈላሻ ስሙን እየተመዘገበ ነበር። ስሟን አናንያ አስመዝግቧት በአዳራሹ ውስጥ ሰፊ ንግግር ከተደረገ በኋላ ሁሉም ሰው ትልቅ የመታጠቢያ ቦታ ሄዶ ታጥቦ የፈላሻዎቹ ልብስ ተሰብስቦ ሲቃጠል የእሷም ገዳም ውስጥ ለብሳው ያደገችው ወይባ ቀሚስና መደረቢያው ተቃጠለባት። በምትኩ ሰውነት የሚያጣብቅ ሱሪና ከላይ ደግሞ ሹራብ ተሰጣትና በግዷ ለበሰች። «ቻው ቻው ኢትዮጵያ..... ሻሎም ቴልአቪቭ... ሻሎም -ኢዝራኤሊያ! ..... ሻሎም - ኢየሩሳሌም-ሰላም አሌኩም።» .....

ከወራት በኋላ በአንድ ከቴልአቪቭ አቅራቢያ በሚገኝ አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ራሷን አገኘችው።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከአመታት በኋላ ደግሞ ሁሉም እስራኤላዊ ተማሪ እንደሚያደርገው ለወታደራዊ ግዳጅ ወታደራዊ ሥልጠና ለለጠነች። አብራይስጥ ቋንቋ አቀላጥፋ መናገር ከመቻሏም በላይ በወታደራዊ ቅልጥፍናዋ ትደነቃለች። ዕዮናዊነት በደሟ ውስጥ መቀላቀል ጀምሮ "እስራኤል ለዘለአለም ትኑር!" ማለትም ከጀመረች አመታት አልፈዋል።

እስራኤል ባደረገቻቸው በስለላ የተቀመሩ ጦርነቶች ላይ ተሳትፋ የፈፀመችው ጀግንነት ሲታወሳት ለእሷም ይደንቃታል። በዚህ ወቅት ነበር አናንያ ለሞሳድ የመለመላት። ሞሳድ ማንን መመልመል እንዳለበት ያውቃል። እሷ እንደሆነች የምትጨነቅለት ቤተሰብ የላትም። አባቷም ሱዳን ውስጥ የጊንጥና የእባብ ሲሳይ ሆነው ሲወድቁ አይታለች አደገኛው አናንያ - አጥማጁ ሞሳድ። ማንን ብላ ከግዳጇ ወደኋላ ትላለች? ለማን ብላ በጥቅም ትደለላለች?

አጥማጁ አናንያ አጥማጇን አቦ ሸማኔ በማጥመዱ በኩል እንደተሳካለት ሁሌም ይናገራል። የፍቅር አዙሪቱ ውስጥ ለመክተት ሲል ደሞ አሁንም ድረስ ከጥጓ ነው።

ሲጸራ በትዝታ ተሰባ ያደገችበትን የታሪኳን ደም ስትጠባ ለሰአታት መቆየቷን ያወቀችው ዶ/ር አናንያ "እና ከዚያ ወዲህ አግኝተሽው አታውቂም?" ብሎ ቢጥያቄ አሁን ወዳለችበት ዓለም ሲመልሳት ነበር።

"ማንን?" አለች ለለአታት ስትመለከተው ከነበረው የመንታ ደሴቶች ፎቶ ላይ ዓይኗን ነቅላ።

"ሚራዥን"

"በጭራሽ! ወደ ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ሄጀ ፈልጌዋለሁ። ወዳደግንበት ገዳም በድብቅ ተመላልሼም አጠያይቄ ነበር። ነገር ግን ላገኘው አልቻልኩም። በንስሐ እንዲመለስ ለአርባ ቀናት ታስሮ ከቆዩ በኋላ ሲፈታ ከገዳሙ ወጥቶ እንዳመለጠ ሰምቻለሁ። የት እንደ ደረሰ እግዚያብሔር ይወቀው።"

"እና ከዚህ በላይ መፈለግ አለብሽ?"

"መጨረሻ እስከሚባለው እፈልገዋለሁ።"

"ይሄማ ቂልነት ነው። መች ሲጻራ ይሄ እብደት ነው። ይሄኔ እሱ በህይወት ላይኖርም ይችላል። ካለም ይሄኔ ከአንዷ ጋር ትዳር ይዞ ሊሆን ይችላል። ወንዶች እንደሽንኩርት የሚላላጥ ልብ ነው ያላቸው። ይልቅ አሁን የፍለጋሽ መጨረሻ ደርሷል። አሁን እኔ ከጥግሽ አለሁልሽ" እንደገና እየተሟዘዘባት ነው። መልሶ አበሽቃት።

"ሞዛዛ! አታውቅበትም ደግሞ።"

"ባውቅበት እሺ ትይኝ ነበር?"

"ብሽቅ! ሁለተኛ ይህን ጥያቄ እንዳታነሳብኝ። ወደማልፈልገው ትዝታ ውስጥ ከተሸኘ አዘናግተሽኛል ደሞ" ሰአቷን ተመለከተች። በሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ውስጥ ለስብሰባ የተጠሩበት ሰዓት እየደረሰ ነው። በሻጊዝ ጉዳይ።

"በል እንፍጠን" መኪናዋ ውስጥ ተከታትለው ገቡ። መኪናዋን ኮለኮለቻት።

፫

ሉሳንጀለስ ፡ አሜሪካ

ዶ/ር ሚራዥ በሉሳንጀለስ ከተማ ደቡብዊ ምዕራብ ጫፍ ከ101ኛ ጐዳና ገባ ብሎ በሚገኝ ጥንታዊ አፓርታማ ውስጥ መኖር ከጀመረ ሶስት ዓመት ከመንፈቅ አልፎታል። ብዙም ግርግር አይበዛበትም። አፓርታማው ጥንታዊ ቢሆንም የመዋኛ ገንዳውና የመኪና ማቆሚያው በቅርቡ በመታደሱ የዘመናዊነት ይዘት ተላብሷል። በዚህ አፓርታማ የሚኖሩት ሰዎች አብዛኞቹቹ እድሜ ጠገቦች ናቸው።

የዶ/ር ሚራዥ መኖሪያ ቤት በዚህ አፓርታማ ስምንተኛፎቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን በጥቃ የሰፈነበትም ነው። ከሥራ ተመልሶ አንዳንዴ መስኮቱን ሲከፍተው ከፓስፊክ ውቅያኖስ በሚነሳው የነፋስ ሽውታ ከሚውለበለበው ነጭ የመስኮት መጋረጃ ውጭ ሌላ የሚታይ እንቅስቃሴ የለም። በቤቱም ውስጥ በብዛት ሲገባ የሚታየው ዶ/ር ሚራዥ ብቻ ነው።

ቤቱ ውስጥ ከመሠረታዊ ቁሳቁሶች ውጭ የቅንጦት እቃዎች የሉም። መኝታ ቤቱ ውስጥ ዘመናዊ አልጋ ቢኖርም እሱ ግን የሚተኛው መሬት ላይ በተነጠፈ ፍራሽ ነው። ኩሽና ውስጥ አንድ ትልቅ ብረት ድስት፣ ሌላ አነስተኛ ብረት ድስት፣ መጥበሻ፣ መክተፊያ፣ ቢላዋዎች፣ ሴንኪሉና ሌሎች ትንሽ ቅራቅንቦ እቃዎች በጥቂቱ አሉ። ሳሎኑ ውስጥ ቴሌቭዥን፣ ኮምፒውተሮች፣ ሶፋና ወንበሮች ሲኖሩ በዚህ ሳሎን ብዙውን ቦታ የያዙት የመፃሕፍት መደርደሪያዎች ናቸው።

እነዚህ ትላልቅ የመፃሕፍት መደርደሪያዎች አንዳንዶቹ ግድግዳውን ተደግፈው ሲቆሙ ሌሎቹ ደግሞ መሃል ላይ በመፃሕፍት ጠቅ ብለው ሞልተዋል። ቤቱም ቤተ መፃሕፍት እንጂ መኖሪያ ቤት አይመስልም። መፃህፍቱ በየፈርጃቸው የተከፋፈሉ ናቸው። የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የህክምና፣ የሳይንስ፣ ... ወዘተርፈ ተብለው በየሼልፉ አናት ላይ ተዕፎባቸዋል። የሐይማኖት መፃሕፍትም እንደዛው። የአርቶዶክስ ተዋህዶ፣ የእስልምና፣ የካቶሊክ፣ የጌሮቴስታንት፣ የቡድሐዘምና የሌሎች ሃይማኖቶች መፃሕፍትም ለየብቻ ተደርድረዋል። በሌላ መደርደሪያ ደግሞ የጥናትና የምርምር ጥራቶች ታጭቀዋል። የተለያዩ ዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያሳትሟቸው ጆርናሎች፣ መፅሔቶችና ጋዜጦችም በየፈርጃቸው የተካተቱበት መደርደሪያ አለ።

መሃል ለመሃል ሳሎኑ ውስጥ የተጋደመው ረጅም ጠረጴዛ ላይ የተከመሩ ወረቀቶች በኮምፒውተሮች መሀል አሉ። ከሳሎኑ በአንድ ጥግ የተነጠፈ ፍራሽ ሲኖር በራስጌ በኩል የማይጠፋው ጊታርም አለ። ዶ/ር ሚራዥ በንባብና በሊሎች ነገሮች ተወጣጥሮ

ከቆየ በኋላ ራሱን የሚያዝናናው በዚህ ጊታር ነው። አንዳንዴ ጊታሩን ሲጫዎት ምንም አይነት የከንፈር እንቅስቃሴ አያሳይም። ኦይኑን ጨፍኖ ለረጅም ሰዓታት በጊታሩ ድምፅ ተመስጠ ይቆያል። በጋስፊቅ ውቅያኖስ ዳርቻ በተለይ ጀንበር ልትጠልቅ አቅራቢያ ጊታሩን ሲጫወት በጥልቅ ይመሰጣል። በተመስጠው ውስጥ ግን የጊታሩን ድምፅ ይረሳና የሚያስበውን የሃሳብ ጅረት ተከትሎ ይነጠቃል። ሥራዎቹን የሠራቸውም በዚህ ሥልት ነው በጊታሩ የሙዚቃ ቃና ተመስጠ ውስጥ ሆኖ።

ዶ/ር ሚራኾ ቁመቱ መካከለኛ ነው። ተክለ ሰውነቱ ጠንካራ ወታደር ያስመስለዋል። አረማመዱና አቋቋሙም የወታደር ቅጥ ነው። ጥርት ያለ አይኖቹ ለጠይም ፊቱ ድምቀት አልብሰውታል። ዓይኖቹም የሚያስፈሩ ሳይሆን የሚባሩ አይነት ናቸው። ብዙ ጊዜ ፈገግ አይልም እንጂ ጥርሶቹ ክርችም ብለው ተጠጋግተው በጉራማይሌ ድዱ ላይ የበቀሉና የሚያማምሩ መሆናቸው ከስንት አንዴ ሲስቅ ይታያል። የሚስቅም ሰዎች እንባቸውን እያንገዋለሉ በሚስቁበት ነገር ሳይሆን አንድም ሰው በማይስቅበት ነገር ነው። አንዳንዴ ሳቅ እንደ ውሃ በወረፋ የሚቀዳ ይመስል ሁሉም ሰው ስቆ ከጨረሰ በኋላ ይስቃል። ሰዎች ስቀው ሲጨርሱ ሲስቅ ሰዎችን ባሳቃቸው ነገር ሳይሆን ሰዎች በመሳቃቸው የሚስቅ ይመስላል።

ሚራኾ ዝምታው ውቅያኖስ ነው። ነገር ሲጀምርም እንደ ጅረት። ብዙዎቹ የሚወዱት ብዙ ስለሚያዳምጣቸው ነው። ዝም ብሎ አዳምጦ የሱን ሃሳብ ጣል የሚያደርግ ሳይታሰብ ነው። ብዙ ጊዜ ሲያወራ የሚታየውም በእድሜ ገፋ ካሉ ሰዎች ጋር ነው። ምናልባትም በገዳሙ ውስጥ ሲያይ ያደገው ሽማግሌዎችን ስለሆነ ይሆናል። የልጅነት ህልሙም እንደ ዳጋ እስጢፋኖሱ መነኩሴ እንደ አባ ዝምበሩ ትልቅ ጢም እንዲኖረው ነበር። አሁንም ቢሆን በጆሮ ግንዱ ብዙል ቀጠን ብሎ ወርዶ አገጩ ሲደርስ ሰፋ ብሎ ችምችም ያለ ጥቁር ጢም አለው።

አንዳንድ የሥራ ባልደረባዎቹም ችምችም ያለ ረጅም ጥቁር ጢሙን በማጣቀስ አሸባሪው ይሉታል። ከጢሙ ይልቅ ዝምታው ያሸብራል። ጢሙ በአጠቃላይ ውብ ፊቱን ክብብ አድርጉ የሚጠብቅ አጥር ይመስላል። ፀጉሩ ሳብ በመሆኑ ቢጐፍርም አያስጠላበትም።

ዶ/ር ሚራኾ ድምፁ ወፈር ያለና በውስጡ ብዙ ደስ የሚል ቅላፄ ያለው ነው። የገዳሙ ዲያቆን እያለ ብዙዎች ሲዘምርና ሲቀድስ ይመሰጡ ነበር። አሁን ግን በእረፍት ሰዓቱ ከአንድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ባጠናው የጊታር መሳሪያ ድምፅ እንጂ የሱ ድምፅ አይሰማም። ሲነጋገር ግን የሚያስገመግም የነጐድጓድ ድምፅ ያለው ሰው ነው።

በቤቱ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በግንኙነቱ ላይ ብዙ ለውጥ አምጥተዋል።ሲያነብአይመርጥም።የሚያምንበትንም የማያምንበትንም

ያነባል። በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ሆኖ ብዙ የማይመሸ ቀኖችንና የማይነጉ ሌቶችን አሳልፏል። ከእነዚህ መጻሕፍቱ በቀር ሌላ ዘመድ የለውም። የሚያገኘው ገቢ በብዛት መጽሐፍ ለመግዛ ይውላል። ዘመዶቹን አያውቅም። እናት፣ አባት፣ አጐት፣ አክስት፣ የሚባሉ ነገሮች በአእምሮው መጥተው አያውቁም። ትዝ የሚሉት የባና ሐይቅ ደሴቶችና የዛፎች ጥላ ብቻ ናቸው።

ከዚህም ጋር በየቀኑ ትዝ ሳትለው የማታልፈው ግን ሲጓራ ናት። በሁለቱ ደሴቶች መካከል ያሳለፉት የፍቅር ጊዜ ትዝ ይለዋል። ከትዝታው ለመላቀቅም መጻሕፍቱ አይነተኛ አማራጮቹ ናቸው። ከሰዎች ጋር ተቀላቅሎ ብዙ መጫወት አይችልም። ያደገበት የገዳም ህይወት በሰዎች መካከል ገዳማዊ አድርጎታል። ሥራውን ግን በአግባቡ ይሠራል። በጥንቃቄ። በእሱ ስህተት ሰው እንዲጎዳ አይፈልግም። ለበሽተኞችና ጤና ላጡ ሰዎች እጅጉን ያዝናል። ይጠነቀቅላቸዋልም። «ዶክተሮች የእግዚአብሔር እጆች ናቸው። እግዚአብሔር ለበሽተኞች ፈውስን የሚሰጣቸው ዶክተሮችን ተጠቅሞ ነው» ብሎ ያምናል።

አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤቱ መጥታ ዝምታውን የምትሰብርለት ማሮዳ ናት። ማሮዳ እሱ ቤት ስትመጣ መቶ ሰው የሚያወራ ነው የሚመስለው። መፃሕፍቱን በሚመለከት «ቤትህ እኮ የደራሲ ቤት ነው የሚመስለው» ስትለው

«እኔ የሚታየውንና የሚጨበጠውን አካል ቀድጄ ስሰፋ መፃህፍት ደግሞ የማይታየውን አካሌን ቀድደው ይሰፉልኛል። ሐኪሞች በሽተኞችን ብቻ ሲያክሙ ደራሲያን ደግሞ ሐኪሞችንና በሽተኞችን ያክማሉ። ደራሲያን እንደ መላእክት ናቸው። መላእክት የሰውን ወደ እግዚአብሔር የእግዚአበሔርን ወደ ሰው ሲያደርሱ ደራሲያን ደግሞ የሕዝቡን ወደ መንግሥት የመንግሥትን ወደ ሕዝብ ያደርሳሉ። እውነተኞች ደራሲያን የሕዝብን ወደ መንግሥት አድርሰው መንግሥት ካልሰማ የመላእክትን ተግባር በማገዝ የሕዝብን ወደ እግዚአብሔርም ያደርሳሉ። እውነተኞቹ ደራሲያን በህዝብና በመንግሥት፣ በመንግሥትና በመንግሥት፣ በህዝብና በህዝብም መካከል የሚኖሩ የማይሰበሩ ድልድዮች ናቸው። እውነተኞቹ መልእክቱን በወቅቱ ሲያደርሱ ሐሰተኞቹ ደራሲያን ደግሞ የነበረው ሥርዓት ካለፈ በኋላ ከምናምን ዓመት በፊት የሣፍኩት ያኔ ፈርቼ ያላሳተምኩት ብለው ህዝብን ያቆስላሉ። አንድ ሥርዓት ካለፈ በኋላ ተራ ሰውም ቢሆን ያንን ሥርዓት ቢሳደብ አይታሰርም።ስላለፈው ስርዓት አስቀያሚነት በወቅቱ አስቀያሚነቱን መዋጋት ፈርቶ ካለፈ በኋላ ህዝቡን የሚሸነግል ደራሲ እሱ ከሐሜተኞቹና ጅብ ካለፈ ከሚጮሁት ውሾች ተራ ይመደባል። ያለፈውን ስርዓት የሚከስ ደራሲ የሞተ ውሻን ከሚደበድብ ሰው አይሻልም። የነበረበትን ሥርዓት እንዲሻሻል የሕዝብን ጩኸት ያሳስተጋባ ደራሲ ሥርዓቱ ካለፈ በኋላ ቢንተባተግ እሱ የሞተ ውሻን ከሚደበድብ ቂል በምን ይሻላል? የህዝብን ብሶት ወደ መንግሥት

የማያደርሱ ደራሲያን የመንግሥትና የህዝብ ጠላቶች ናቸው። መንግሥትንም ህዝብንም ያሳስታሉና። መታተም ባለበት ዘመን ያልታተመ ድርሰትና ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ አንድ ናቸው..» እያለ ይመልስላታል።

ሜሮዳ ይህን ነገሩን ስታይ «በእውነት ደራሲ ብትሆን ሳይሻል አይቀርም»! ትለዋለች።

እሱም «ደራሲ ልሁን ተብሎ አይኮንም። ግን ያደክብት ቦታ ለድርሰት ሥራ አመቺ ነበር። ገዳሙ ውስጥ ያነበብኳቸው ገድላትና ተአምራት ከሃይማኖታዊ ገፅታቸው ጀርባ የረቀቁ የሥነ ፅሑፍ ሥራዎችም ናቸው። እነዚህ ..... የኢትዮጵያ ገድላትና ተዓምራት የፈጠራ ሥራዎች ከሆኑ የዓለቸቸው ሰዎች የኖቤል ተሸላሚዎች መሆን ይገባቸዋል። በልብወለዳዊ ዓይን ቂየናቸው እነዚህን መጽሐፍት የዓለቸቸው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶች የኖቤል የሥነ ፅሁፍ ሽልማትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን መጠራረግ ይገባቸዋል» ይላታል።

ሚራዥ ታፍሶ የሰሜኑን ጦር ከተቀላቀለ በሁዋላ በሁለት አውደ ውጊያዎች ተሳትፏል። በሰሜኑ ጦርነት ወደ ሰንጠቅ ብርጌድ በመጨረሻ ከተቀላቀሉት ጓዶች ውስጥ አንድ ጥሩ ሥነ ምግባር የተላበሰ ወታደር ጓደኛ በማግኘቱ በህይወቱ ላይ ብዙ ለውጥ ያመጣለት እሱ ነው። ወታደሩ አስገራሚ ሆኖ አገኘው። ይህን ወታደር በማሰልጠኛ ጣቢያ ውስጥም አይቶት ነበር። እንዲያውም አንድ የተናገረው ቃል ትዝ ሲለው ይኖራል። በጀርባቸው አሸዋ ተሸክመው ጫንጫን እየተነፈሱ ወታደራዊ ሥልጠና በሚሰለጥኑበት ወቅት «በሥልጠናው ብዙም አትማረርበት። የሰላም ጊዜ ልምምድ ለክፉ ቀን ያገለግላል። ብትችል ህገርህን ከገንጣዮች ትታደግበታለህ። ባትችል ራስህን ታስመልጥበታለህ»ነበር ያለው። ይህ ወታደር ከጀርባው ከተሸከመው ወታደራዊ ትጥቅ በተጨማሪ አንድ ሻንጣ ሙሉ መጻሕፍትም ተሸክሞ ይዋጋ ነበር። ጦርነቱ ጋብ ሲል መፅሐፉን ከሻንጣው አውጥቶ ማንበቡ ይጀምራል። የክፍል ጓደኞቹ «ሌኒን» ብለው ሲጠሩት «እኔ ሌኒን አይደለሁም! እኔ ራሴ ነኝ ዶ/ር ዣንጊዳ!» ይላቸዋል።

«እየቀለድክ ነው?» አለው ሚራዥ አንድ ቀን። «ዶክተር ነህ በርግጥ?»

«አዎን» አለው ዣንጊዳ። «በህክምና ተመርቄ ከቤተሰቦቼ ጋር በደስታ የምርቃት በአሌን ስናከብር የቀበሌ ሽሞች አፈሱኝ»

«ስንት ጦር ቁስለኛ ሆኖ የሚያክመው አጥቶ ወየው እናቴ እያለ ሲሞት ዶ/ሩን ነው ተራ ወታደር ያደረጉህ?»

«የሚያደርጉትን አያውቁምና አትፍረድባቸው።»

«ወይ ጉድ!» ብሎ ዝም አለ ሚራዥ።

በዚህ ጦር ሠራዊት ውስጥ ዶ/ር ዣንጊዳን በማግኘቱ ከመፅናናቱም በላይ በድብቅ መጽሐፍ እያዋሰው ማንበብ ጀመረ።

የልብ ወለድ፣ የፍልስፍና፣ የታሪክ ፣ የሥነ ልቦና መጻህፍትን ከዶ/ር ዣንጊዳ እየተዋሰ አነበበ። መጻህፍቱን ሽፋንና ርዕሶቻቸውን ገንጥለው ያቃጥሏቸው ነበር። ምክንያቱም ከሌኒንዝም- ማርክሲዝም ፍልስፍና ውጪ ሌላ ሀሳብ የያዙ መፃሕፍትን ሲያነቡ ቢያዙ «የኢምፔሪያሊዝም አቀንቃኞችና የሲ.አይ.ኤ ሰርጎ ገቦች» ተብለው የሚደርስባቸውን እደጋ በመፍራት ነው።

መፅሐፍቱን ይገነጥሉና በሌላ ካርቶን ከለበጿቸው በኋላ አዲስ ርዕስ ይሰጧቸዋል። «የወዝ አደሮች ትግል»፣ «ማርክሲዝም»፣ «ሌኒንዝም»፣ ወይም «የሠራተኛው መደብ ትግልና የበዝባዦች ውድቀት» ብለው ይሰይሙታል።

ሚራዥ ለዶ/ር ዣንጊዳ የህይወቱን ታሪክ አጫውቶታል። በጦር ሰፈራቸው ውስጥም በአንድ ክፍል ውስጥ ከሌሎች ስድስት ወታደሮች ጋር ስምንት ሆነው ሲኖሩ በጣም ተቀራርበው የሚያወሩት ሚራዥና ዶ/ር ዣንጊዳ ነበሩ።

ሚራዥ በገዳም ውስጥ ያደገ መሆኑን ከነገረው ጊዜ ጀምሮ ዶ/ር ዣንጊዳ «ገዳማዊው» ብሎ ነው የሚጠራው።

«ገዳማዊው!» ይለዋል። ዶ/ር ዣንጊዳ።

«ወዬ!»

«ውዳሴ ማርያም አስተምረኝ። እኔ ደግሞ እንግሊዘኛ አስተምርሃለሁ።»

«ምን ገዶኝ» ይላል ሚራዥ። «ግን ምን ያደርግልሃል ውዳሴ ማርያም? ክላሽንኮቭና ውዳሴ ማርያም አይጣጣሙም።»

ዣንጊዳ...የሚራዥን የትምህርት አቀባበል ሲያይ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ቢገባ ባጭር ጊዜ ውስጥ ታላቅ ሰው እንደሚሆን ነግሮት ከወታደራዊ ካምፑ ካመለጡ ትምህርት ቤት እንደ ሚያስገባው ቃል ገብቶለታል። መውጫ ቀዳዳ አጥተው ነው እንጂ ውስጥ ውስጡን ሁለቱም ከወታደራዊ ካምፑ ለመጥፋት ካቀዱ ሰንብተዋል።

በጦር ሰፈሩ ስምንት ሆነው በሚኖሩባት መጠለያ ውስጥ የተንጠለጠለው ፋኖስ ድቅድቁን ጨለማ ወደ ውጭ በሚጋፋበት አንድ ምሽት እንደቀድሞው ሚራዥና ዣንጊዳ አፍ ላፍ ገጥመው ያወራሉ። ሌሎቹ ወጥ ቤቱዋን በጋራ ስለመወሰብ እቅድ ይነድፋሉ። ከዚህ ቀደምም የአንድ ገበሬ ሚስት በመድፈራቸው ከባድ ቅጣት ከተቀጡ ሳምንት አልሆናቸውም።

ሚራዥና ዣንጊዳ በአንድ መፅሐፍ ይዘት ዙሪያ እየተነጋገሩ ቢሆንም ጆሮአቸው ግን ስለወሲብ ከሚያወሩት ወታደሮች የሚመጣውን ድምፅ እየተቀበለ ነበር። በዚህ ቅጽበት ከስድስቱ አንደኛው ወታደር ከውጭ እየተንደረደረ አንዲት ሴት ተሸክሞ ገባ። አጁ በአረንጓዴ ቅዳጅ ልብስ ተለጉሟል። ታልጐመጉማለች። ምን እንደምትል ግን አትሰማም። ሰውነቷ

ደልደል ያለና ለወሲብም የምትጋብዝ አይነት ናት። ስድሰቱ ወታደሮች ሊፈራረቁባት ካቀዱ ቆይተዋል። ወጥ ቤቷ ሜሮዳን።

«እኔ እጀምርና ሌሎቻችሁ ትቀጥላላችሁ። ....አንተ ከኔ ትቀጥላለህ.... ከዛ አንተ ... አንተ ... አንተ ... አንተ ... ሌላም የሚፈልግ ካለ መቀጠል ይችላል። ግን ሁላችሁም ሃምሳ ሃምሳ ብር ለመያዛችሁ እርግጠኛ መሆን አለባችሁ። አለቀ በቃ።» ብሎ እየተጣደፈ ሱሪውን ዝቅ አድርጉ ላይዋ ላይ ተከመረባት። ሊሎቹ መጀመሪያ ባይሆኑ እንኳ ሁለተኛ ባለተራ ለመሆን እየተጉሻሸሙ ነው። ባለፈው እንዲሁ አንድ መንደር ውስጥ የያዙአትን የአንድ ገበሬ ሚስት ሲፈራረቁባት ገና ሶስተኛው ሰው ላይ ነበር በድን የሆነችው። ይህችም ሳትዝለፈለፍ በትኩሱ ለማግኘት እየተገፋፉ ነው።

ሚራዥና ጐንጊዳ የሚያዩትን ትርኢት ማመን አቅቷቸዋል። ሚራዥ በተለይ ይህ አይነት ትዕይንት የመጀመሪያው ነው። ስለ ወሲብና ዝሙት አንብቦ ቢያውቅ እንጂ በገሃድ አይቶ አያውቅም። ልቡ በድንጋጤ እየመታ እያለ «ገዳማዊው ሃምሳ ብር ከሌለህ ላበድርህ እችላለሁ» አለው ላይዋ ላይ ተከምሮ የሚጋልባት ወታደር።

«አፈር ብላ! ልቀቃት አሁን»

«እሪ እባክህ!»

«ልቀቃት ብዬሀለሁ ጀርባህን በጥይት ሳልበሳው።» ክላሽንኮቩን አቀባብሎ ቆመ ሚራዥ።

«አይ የመነኩሴ ነገር! ወይ ዲያውቆን መሆን! ይልቅ ና! ዛሬ አይነጥህን ግለጥ። ሌላ ጊዜ የምታፈርስበትን ዕድል ላታገኝ ትችላለህ። ስላልቀመስክ ምንም ላይመስልህ ይችላል። ግን ይህን በመሰለ መልካም ሜዳ ላይ ምላጭ መላብ ገሃነም ነው የሚከትህ።»

«ገሃነም ግባ!» አለ ሚራዥ ጠመንጃውን ለጐንጊዳ ሰጥቶ ክናዱን እየሰበሰበ።

«አትለቃትም።» አንገቱን ይዞ ከላይዋ አንስቶ አፍንጫውን በቦክስ ነረተው።

«ሌሎቻችሁ እንቃነቃለሁ ብትሉ ይህን ጥይት ነው የማርከፈክፍባችሁ» አለ ጐንጊዳ ሚራዥ ያቀበለውን ክላሽንኮቭ ከኋላቸው ወድሮ። «ሙሾች»

ሴቷ ላይ ተከምሮባት የነበረው ወታደር ፈርጣማ ስለነበር ሚራዥን መንጋጭላውን በቦክስ ሲነርተው ራሱን አዙሮት ተንገዳግዶ ቆመ። ሚራዥም መልሶ በደምፍላት አገሬን ሲያጣምመው ወታደሩ በቁሙ ተዘረረ።

ሴቷ እየተንከባለለች ወደ ጐንጊዳ ተጠጋች። ሚራዥ ወታደሩ እንደወደቀ በከስክስ ጫማ ጭንቅላቱን ከመሬቱ ጋር አጣብቆ ደፈጠጠው።

ሴቷ አዲስ የወጥ ቤት ሠራተኛ መሆኗን ያወቁት ወዲያው ነው። ጐንጊዳ ጠመንጃውን እንደ ወደረ ሻንጣውንና ጓዛቸውን እንዲይዝ ለሚራዥ ነግሮት ጓዛቸውን
ጠቅልለው ከሴቷ ጋር ክፍሉን ለቀው ወጡ።

ጥይት ተኩሰው ራሳቸው ርምጃ መውሰድ አይችሉም። ያላቸው አማራጭ ክፍሉን ለቀው መውጣት ነበር።

«እኔ.....» አለ ጐንጊዳ ዝወጡ በኋላ። «ከዚህ ሠራዊት ጋር ከእንግዲህ አንዲትም ጥይት በጠላት ላይ አልተኩስም።..... ሚራዥ ማምለጥ አለብን።»

«እምን። እኔም ይህን እያሰብኩ ነበር።» አለ ሚራዥ። ሴቷ እየተንቀጠቀጠች ነበር የቆሙችው።

«ግን እንዴት ማምለጥ እንችላለን?» አለ ሚራዥ

«ዋርድያዎችን አውቃቸዋለሁ። እኔ ሄጄ እነሱን ሳዋራቸው አንተ ተከትለኸኝ ትመጣለህ። የሚቀጥለውን ደግሞ የሚያመቻችልን ይሄ ነው» ብሎ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጥ ሰጠው።

«ከኔ ጀርባ ትሆንና ሁሉንም በቅልጥፍና ትመታቸዋለህ።»

«የት አገኘኸው?» አለ ሚራዥ ማፈኛ የተገጠመለትን ድምፁ ሳይሰማ የሚተኩሰውን ሽጉጥ እያገላበጠ።

«ውጊያ ውስጥ ከወደቀ ጄነራል ላይ የወሰድኩት ነው።» አሉው ጐንጊዳ።

«ግን ቀልጣፋ መሆን አለብህ አለበለዚያ ጭቃ ነው ሚያደርጉን።»

«እንዴ ጠብቁኝ።» ብላ እየፈጠነች ወደ ወጥ ቤት ሄደች። ወጥ ቤቷ ሜሮዳ።

«የምናመልጥበትን ጊዜ ለምን አናዘገየውም?» ሲል ሚራዥ ጠየቀው።

«ሽህ ጊዜ ብንዘጋጅ ከዚህ የተሻለ መንገድ የለም። ቢኖርም ከዚህ ሠራዊት ጉን ቆሟ ከእንግዲህ አልዋጋም። ልንገርህ ሚራዥ፣ ይሄ ሠራዊት አያሸንፍም። በውስጡ ብዙ ባለጌዎች አሉበት። ጠሩን አሰልፈው የሚያስጨርሱ ቅጥረኞች ተሰግስገውበታል። አሁን እነዚህ ደፋሪዎች ቅጥረኞች ላለመሆናቸው ምንም ማረጋገጫ የለንም። የገበሬ ሚስቶችና ልጃገረዶች እየተደፈሩ ነው። ጨዋዎችና የዋሆች እናቶቻችን እየተደፈሩ ነው። ወታደር እየተፈራረቀባቸው ደም የሚሸኑ ሴቶች ሥፍር ቁጥር የላቸውም። ብዙ የተከበሩ ባለትዳሮችና ሴቶች አንገታቸውን ደፍተዋል። የነዚህን ሚስት ሳትቀር ቄሱ መስቀሉን ይዞ እየዝዘተና እየተማፀነ ተደፍራለች። ሴት ተማሪዎችና የገበሬ ልጆች ያለ እድሜያቸው ልጅ አዝለዋል። ከፊሎቹ የማያውቁትን ወታደር ልጅ አርግዘዋል። ይህ ሁሉ የሆነው በጥቂት ቅጥረኞችና በባለጌዎች ነው። ይህ ሁሉ ርግማንና እንባ የሚፈስበት ሠራዊት እንደማሸነፍ ነመዓሁ መገመት አይፈግትም። የገበሬ ልጅና ተማሪ ታፍሶ ያለበቂ ሥልጠና እና ስንቅ ወደ ጦር

ግንባር እየተማገደ እንዴት ነው ድል የሚገኘው? በዚህ ሠራዊት ውስጥ እናት ሀገራቸውን ከገንጣዮች ለመታደግ የሚፋለሙት እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ሀገሪቷም እነዚህን ጀግኖች በየጦር ግንባሩ እያጣች ነው። ጀግኖችና ሀቀኛ ልጆቿ ደማቸውን እያፈሰሱላት አድርባዮችና ቅጥረኞች የሚሾሙባት ናት ይህች አገር።» እንባው አንቆት ፀጥ አለ ጐንጊዳ።

«አዎ። ልክነህ ጐንጊዳ የሀገራችንን ጥፋት ቆመን ከምናይ እግራችን እንደመራን ብንሄድ ይሻላል።»

«ሚራዥ.... እግራችን አይመራንም ሞንቅላታችን እንጂ። ሞንቅላት ነው እግርን የሚያዘው። ችግራችንም መምራት የሚገባው ስለማይመራን ነው።»

«ልክ ነህ ጐንጊዳ። ስለተሳሳትኩ ይቅር በለኝ።»

«የሚጋነን አይደለም። ከሁለም በላይ ስህተትን አምኖ ማሻሻል ይበልጣል። ያልተሳሳተ አይማርም» አለ ጐንጊዳ።

«ሚራዥ ያልኩህን እንዳትረሳ በፍጥነት ዋርድያዎችን መቆጣጠር አለብን።»

«እኔ ነኝ የምቆጣጠራቸው» አለች ወጥ ቤቷ ሻንጣዋን አዝላ። ከመጣች ቆይታለች። ቆማ እያዳመጠቻቸው ነበር። «ባለ ውለታዬ ናችሁ። እናንተን መርዳት አለብኝ። እንኩ ሻንጣዬን ያዙልኝ። የባትሪ ምልክት ሳሳያችሁ ብቻ ትመጣላችሁ። ርቧቸው ስለነበር ምግብ እንዳመጣላቸው ተማፅነውኛል። ግን ቢያንስ አርባ ደቂቃ መታገስ አለባችሁ። ቃኘዎች እንዳይዟችሁ ጓዙን ደብቁትና ሽንት ቤት የምትሄዱ ምሰሉ። ሁሉን ነገር ለእኔ ተውት።»

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት መዳረሻ ላይ የባትሪውን ምልክት አዩ። ጓዛቸውን ተሸክመው ወደ በሩ ሲሄዱ ዋርድያዎች ወዳድቀዋል።

«ፍጠኑ።» አለች ወጥ ቤቷ። «ሌላ አደጋ ውስጥ ሳንገባ ማምለጥ አለብን። ጥያቄ አልቀበልም» ሻንጣዋን ከሚራዥ እጅ ተቀብላ ወደ ጫካው ተመሰገች። እነሱም ተከተሏት።

ጐህ ሲቀድ ተሰነይን በርቀት አልፈው ከሰዳን ጠረፍ ሊደርሱ የስድስት ሰዓታት የእግር ጉዞ ይቀራቸው ነበር።... አስቸጋሪው ጉዞ ከዚህ በኋላ እንደሆነ ነገረቻቸው። ከኋላቸው የሚከተሉ ፈላጊዎች ሊኖሩ ከመቻላቸውም በላይ በአካባቢው ከነበረው የጦርነት ውጥረት አንፃር በሌላ ጦር እጅ የመውደቃቸው አደጋ በዛው ልክ እንደሆነም ጭምር። ....ከአንድ አለታማ ሸለቆ ውስጥ ሲደርሱ ፀሐይ እግሯን ሰደደች። ሸለቆው ውስጥ ተደበቁ።

«ሜሮዳ እባላለሁ።»

«ጐንጊዳ እባላለሁ አሰ ደግሞ ገዳማዊው ሚራዥ ነው።» ሁላቸውም የፈካ ገፅታ ታየባቸው።

«አሁን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።» አለች

«ጥያቄ አንድ።» አለ ጐንጊዳ።

«ዋርድያዎቹን እንዴት ገደልሻቸው?»

«ምግቡ ተመርዞ ነበር። ተመለሰ?»

«በትክክል ተመልሶልኛል።»

«የሚቀጥለውን የጥያቄ እድል ለገዳማዊው ልስጥ። ስሙን ማን ነበር ያልከኝ?»

«ሚራዥ»

«ሚራዥ... ያንተ ጥያቄስ?» አለች ወደ ሚራዥ ዞራ። መልስ አልሰጣትም። ወደ ምሥራቅ ዞሮ ከንፈሩን ብቻ እያንቀሳቀሰ ነበር።

«የጠዋቱን ፀሎት እያደረሰ ነው። ሁል ጊዜም እነደዚህ ነው» አለ ጐንጊዳ።

«እሺ. እንተ ሁለተኛውን ጥያቄ ጠይቂኝ።»

«ስለሚቀጥለው ጉዞ መነጋገር እንችላለን?» አላት ጐንጊዳ።

«በደንብ።» ሻንጣዋ ውስጥ የተጣጠፈ ካርታ አውጥታ ነፃ ቀጠናዎችንና የጦር ሠራዊት የሠፈረባቸውን አካባቢዎች አሳየቻቸው።

«ይህ አካባቢ የህወሐት ይዞታ ነው።» ጐንጊዳ በግርምት እየተመለከታት ነው።

«ይህኛው ደግሞ የሻዕቢያ።» ፍጥነቷና ንግግሯ የወጥ ቤት አይመስልም።

«ወጥ ቤቷ.. ይቅርታ.. ሜ..ሮዳ.. ሜሮዳ ስለእንቺ ማንነት ማወቅ እንችላለን?» ሚራዥ ፀሎቱን ጨርሶ ካርታው ላይ አፍጥጦ ነበር። አሁን ግን እሷ ላይ አፈጠጠ።

«ወጥ ቤቷ ሜሮዳ ነኝ!» ፈገግ አለች።

«አትቀልጂ ንገሪን።» ጐንጊዳ ደግሞ ጠየቃት።

«እሱን ለሌላ ጊዜ እንተወው። አሁን በአላማ አንድ ሆነናል። ስለዚህ አብረን የጀመርነውን ጉዞ መጀመሪያ እንጨርስ ሌላው አያመልጠንም።»

«ተስማምተናል ወጥ ቤት። ስለካርታው ትንታኔሽን ቀጥይ» ሚራዥ በሚያስገመግም ድምፁ አግተመተመ።

«እዚህ ካምኘ ላይ ሶስት ብርጌድ ሠራዊት አለ። እዛኛው ላይ ደግሞ ሁለት ብርጌድ።» ካርታው የሰሜን ኢትዮጵያን የወታደራዊ ቁልፍ ቦታዎችና የጦር ስፍሮችን የያዘና በመረጃ የተሞላ ነው። የወታደር ብዛት፣ የመሳሪያ አይነት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዛት፣ ወታደራዊ ብቃት፣ የመልክአ ምድር ድጋፍ በካርታው ግርጌ በቁጥርና በኮድ ምልክቶች ታሞዳል።

«ከዚህች ሴት ጀርባ አንድ ትልቅ ኃይል አለ።» ሲል አሰበ ጐንጊዳ። ግንም ይኑር ማን ብቻ እኔንና ሚራዥን ከዚህ ጥልፍልፍ አሳት ታውጣን።»

«አሁን.....» አለች ሜሮዳ። «ልብሶቻችሁን አውልቁ።» ሁለቱም «ምን?» አሉ ወደሷ በአንድ ላይ አፍጠው። ሻንጣዋን ፈትታ ሶስት የተለያዩ የሴት አሮጌ ቀሚሶችና የተቀዳደዱ ነጠላዎች አወጣች።

«ለዛሬ ሴት መሆን አትፈልጉም?» አለች እንዲለብሱት እየጋበዘቻቸው::

«እንሆናለን እንጂ::» አለ ጐርጊዳ በሞተ ድምፅ:: ሚራዥ ቀሚሱን ሲለብስ ሳቁ አፈነው::

«እኔ ግን ሰው ቢያገኝኝ የምስቅ ይመስለኛል::ለመሆኑ ጢም ያለው ሴት አለ?» አለ ሚራዥ ሳቁ እየመጣ::

«ሞልቶ::»

«ሙት በይኝ እስቲ::»

«ግዴለህም ጢምህን እኔ ድራሹን አጠፋልህና በነዚህ ቀለሞች ሳስማምርህ ቁርጥ ጣል የገጠር ሴት ነው የምትመስለው:: ግንባርህን ሽብሽበው::»

«ሽብሽቤ ልጓዝ?»

«ሽበሽብሽው በዚህ ቀለም ከቀባሁት በኋላ ስትለቀው ቀለሙ በሚፈጥረው ሽንተረር የተሸበሸበ ይመስላል:: ከዚያም አሮጊት ትመስላለህ::» አለችና ሜሮዳ እንደነገረችው አደረገችለት::

ፊቱን በሰጠችው መስተዋት እያየ ከተገረመ በኋላ ሻንጣውን ማዳበሪያ ውስጥ ከተተችለትና ወገቡ ላይ ጭና በነጠላ አስነገተችው:: ምርኩዝ አስይዛው ጐንበስ ብሎ መሄድ አለማመዳችው:: አጭር የሴት ጥላም ያዘ:: ጐርጊዳን ደግሞ በራሱ አቁርሮ እንዲሸከም አደረገች:: በወገቧ ሻንጣዋን ጠቅልላ ተሸክማ እሷ ከፊት፣ ሚራዥ ከመሃል፣ ጐርጊዳ ደግሞ ከኋላ ሆነው ጉዟቸውን ቀጠሉ:: በጦርነቱ የተፈናቀሉ ሴቶች ነው የሚመስሉት::

ገላጣ ቦታዎች ላይ ወሬ እየሰለቁ አስቸጋሪ ቦታዎችን ደግሞ ድምጥማጣቸውን እያጠፉ ብዙ ርቀት ከተጓዙ በኋላ የሚንደቀደቅ ድምጽ ሲሰሙ ሁላቸውም በድንጋጤ ወደኋላቸው ዞሩ::

አረንጓዴ ሬንጀር ቀለም ያለው ሄሊኮፍተር ደርሶባቸዋል:: ከሄሊኮፍተሩ በር ላይ መትረየስ ወድሮ የመገናኛ ሬድዮ ጆሮው ላይ የሰካው ተኳሽ በሬዲዮው እየወሸከተ ቁልቁል አንዳች ነገር ያስላል:: ዓይኑ ቁጥቋጠውና ቋጥኙ ላይ ሁሉ ይቃብዛል::

ሄሊኮፍተሩ ዝቅ ብሎ እየበረረ ይንደቀደቃል:: በሬድዮ የሚለፈልፈውና መትረየስ የወደረው ወታደር ጥቁር መነፅሩን አውልቆ በጦር ሜዳ መነፅር ሲመለከት ሶስት ቡትቶ የለበሱ ሴቶች ሙልብ አሉለት መነፅሩ ውስጥ:: መትረየሱን አስተካክሎ በፍጥነት አነጣጠረባቸው::

«ምን ይሻላል?» አለ ሚራዥ

«እኔ እንጃ!!» አለ ጐርጊዳ ተስፋ በቆረጠ ድምጽ::

«የመሮጥ አዝማሚያ እንዳታሳዩ::» አለች ሜሮዳ::

«እንዴ ለምን ሮጠን ቋጥኙ ውስጥ አንገባም?»

«እንዳትሮጡ ብያለሁ:: ዝም ብላችሁ በተረጋጋ ሁኔታ ተራመዱ»

«እየቀረቡን እኮ ነው::»

«ብንሮጥም አናመልጣቸውም:: እሳት የሚተፋ መትረየስ እኮ ነው ያነጣጠሩብን::»

አካባቢውን ያነዋወጠ ፍንዳታ ሲሰሙ በድንጋጤ ደንዝዘው ወደ ኋላቸው ዞሩ:: ሄሊኮፍተሩ በእሳት እየጋየ ወደታች ተምዘገዘገ::

«አሁን በፍጥነት መሮጥ አለብን:: እንሩጥ::» አለች ሜሮዳ:: ሚራዥ ሴት መሆኑን ረስቶ ጐባጣውን አቃንቶ ይፈተለክ ገቦመር:: ጐርጊዳም ቀሚሱን እስከጭኑ ከፍ ከፍ አርጎ ከኋላ ተከተላቸው::

ሄልኮፍተሩ እየጋየ ሲወድቅ ፓይለቱ በፓራሹት ወደ ላይ ተመንጥቆ ወጥቶ ከአንድ አነስተኛ ኮረብታ ላይ ሲያርፍ አዩት::

«ራሱ በራሱ ነው የነደደው?» ሚራዥ ከኋላዋ እየሮጠ ጠየቃት::

«አይደለም:: በጠላት አየር መቃወሚያ ተመትቶ ነው» አለች ሜሮዳ:: «ይህንም እጠብቅ ነበር:: ቀጠናቸውን አልፈው በጠላት ክልል ውስጥ ገብተው ነበርና::» እየተፈተለኩ አንድ ሸለቆ ውስጥ ገብተው ተደበቁ:: ጀንበር እስክትጠልቅ በሸለቆው መካከል ባገኙት ዋሻ ውስጥ አምሽተው ወደሱዳን የሚገቡበትን እቅድ መንደፍ ጀመሩ::

«እናንተ ሴቶች» አለች ሜሮዳ በፀጥታ አዘቅት ውስጥ የገቡት ጓደኞቿን:: «ሴትነቱ አይበቃችሁም?»

«እኔ ግን ተመችቶኛል:: ቀሚሱ ያማረብኝ አይመስላችሁም?» አለ ሚራዥ መቀነቱን እየፈታ::

«እራትስ ብንቀማምስ ምን ይመስላችኋል?» ብላ ከሻንጣዋ ውስጥ በፌስታል የቋጠረችውን ምግብ ፈትታ አቀረበች:: ሚራዥና ጐርጊዳ ተያዩ:: ሙሉ በሙሉ አላመኗትም:: የሚከተሏትም በጥንቃቄ ነበር::

«ገብቶኛል:: የዋርድያዎች አጣ ፈንታ እንዳይደርሳችሁ ፈርታችሁ ነው አይደል? እመኑኝ እኔ እናንተን የማጠቃበት ምክንያት የለኝም» ብላ ጥቅልል አርጋ በወንድ አጐራረስ ቀድማ ቀመሰችላቸው:: «በእውነት እናንተ ባለሙሊታዬ ናችሁ:: እነዚያ ሁሉ ወታደሮች ቢፈራረቁብኝ ኖሮ እስከአሁን ደም ሽንቼ ልሞት እችል ነበር:: እናንተ ታደጋችሁኝ እንጃ ::»

አካባቢው ሙሉ በሙሉ በፈልማ ከተዋጠ በኋላ ለቀጣዩ ጉዞ መዘገጃጀት ጀመሩ:: ቀሚሶቻቸውን በጀለቢያ ቀየረችላቸው:: ሙስሊም የአረብ ሴቶች የሚለብሱትን ዓይነርግብም ከለበሱ በኋላ የሱዳን ዜጐች ለመምሰል የሚያስችላቸውን ገፅታ እስኪላበሱ ድረስ ራሳቸውን አስተካከሉ::

«እነዚህ ዘዴዎች የሞነርኳቸውና ውጤታማም ስለሆኑ አትስጉ» ብላ የሱዳን መታወቂያዎችን አውጥታ ስትሰጣቸው

ባግራሞት ተመለከቷት። ሁለቱም መታወቂያዎች በሴት ስሞች የተዘጋጁ ናቸው።

«ቆይ» አለ ጐንጊዳ «አንቺ ማን ነሽ?» ሚራዥ ተጨምሮ።

«ወጥ ቤቷ ሜሮዳ።»

«አትቀልጂ።»

«የምንነጋገርበት ጊዜ አሁን እንዳልሆነ አልነገርኳችሁም?»

ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ ውስጥ እየወደቁ እየተነሱ ለአራት ሰዓታት ያክል ተጉዘው ከጠረፍ ጠባቂዎች ሊደርሱ አራት መቶ ሜትር ያህል ሲቀራቸው

«ቁሙ!» አለቻቸው። «እየደረስን ነው።» ከሻንጣዋ ውስጥ ያወጣችውን የተሰባበረ ሬዲዮ የሚመስል ነገር ገጣጥማ መነጋገር ጀመረች በእንግሊዘኛ ቋንቋ። ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ሬድዮው ወደ እሷ ደወለ።

«ዋ አር አን ዘ ዌይ ...ሺሺሺ ... ዋ ... ሺሺ አር ..ሺሺ ... አን ...ሱዳኒዝ ...ቦደር ናው። ሺሺ ... ካም ...ሺሺ ...አሉን ...ሺሺ ፈርስት ኘሊስ ...466። ዩ ካን ካም ቱ ዘ ቦርደር ናው።» ሜሮዳ እዚሁ እንዲጠብቋት ነገረቻቸውና ወደ ጠረፍ ጠባቂዎች ገሰገሰች።

አካባቢው ፀጥ ረጭ ብሏል። መብራቷን ለቃ ሞተሯን ያጠፋችውን ላንድ ክሩዘር መኪና ክላሽንኮቭ የታጠቁ ታጣቂዎች ከበዋታል። መኪናዋ ውስጥ ከኋላ ተቀምጦ የነበረው ነጭ ሰውየ ወርዶ ከጠባቂዎች አለቃ ጋር ለብቻ ከተነጋገረ በኋላ ወደ ሜሮዳ ተመልሶ «ጓዝሽንና ሰዎችሽን ይዘሽ መምጣት ትችያለሽ አሁን» አላት።

ሜሮዳ በፍጥነት ወደነ ሚራዥ ከመጣች በኋላ ይዛቸው ሄደችና መኪናዋ ውስጥ ገቡ። መኪናዋ ፊቷን መልሳ ወደ መጣችበት ሽመጠጠች።

ሜሮዳ የሲ.አይ.ኤ ሰላይ መሆንዋን ያወቁት ሱዳን ካርቱም ከተማ ውስጥ በተከራዩችላቸው አነስተኛ ቤት ለሳምንታት ከቆዩ በኋላ ነበር።

በሞቃታማዋ ካርቱም ከተማ ውስጥ ለወራት ከቆዩ በኋላ በሜሮዳ እገዛ አሜሪካን ሀገር ገብተው ሁለቱም የሉሳንጀለስ ከተማ ነዋሪዎች ሆኑ።

ጐንጊዳ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ትምህርት ማስረጃውን አገኘ። ሚራዥም በሉሳንጀለስ ከተማ ደቡባዊ ምዕራብ ዳርቻ በአትክልተኝነት ተቀጥሮ ከቆየ በኋላ ጐንጊዳ በህክምና ሙያው ስለተቀጠረ በእርሱ እርዳታ ትምህርት ቤት ገባ።

ትምህርቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቁ ምክንያት የሆነው ቀድሞ የተማረው የገዳሙ ውስጥ የአብነት ትምህርት ሲሆን ከዓመታት በኋላ ለተመረቀበት የህክምና ሙያ መንስኤ የሆነውም በውትድርናው ወራት ያየው የቁስለኞች ሥቃይ ነው።

ዶ/ር ሚራዥ አሉ ከተባሉ ሰርጂኖች ተራ ለመመደብ ጊዜ አልፈጀበትም። ከዶ/ር ጐንጊዳ ጋር ግንኙነታቸው እስከአሁን አልተቋረጠም። ዶ/ር ጐንጊዳ ወደ ሚሠራበት በቴክሳስ ግዛት ውስጥ ወደ ሚገኘው አውስቲን የህክምና ማዕከል ብቅ እያለም ይጠ ይቀዋል።

ሜሮዳ አልፋ አልፋ እየመጣች ትጠይቀዋለች። በዚህ አጋርታማ ስምንተኛ ፎቅ ላይ የሚንሳፈፈውን የዝምታ መንፈስ የምትሰብረው ሜሮዳ ናት። ሰሞኑን ግን ጥፍት ብላለች።

ዶ/ር ሚራዥ ልብሱን አውልቆ በቁም መስታወቱ ውስጥ ከተገተረው ምስሉ ላይ አንባቱን የኋሊት ጠምዝዞ የጀርባውን ንቅሳት ሲመለከት ብዙ ቆይቶአል። «ዴርቶጋዳ» ምንድን ነው?» ይላል ለብቻውን። «ለምንስ እኔ ላይና ኢንጂነር ሻጊዝ ጀርባ ላይ የተሳለው ንቅሳት አንድ አይነት ሆነ..... አይቲንክ..... ዋ ሃቭ ሳምቲንግ ኢን ኮመን!.....አንድ የጋራ ምስጢር ከጀርባችን ሳይናገር አይቀርም»

ስለንቅሳቱ ሲያስብ ከቆየ በኋላ መልሶ ደግሞ ስለ ኢንጂነር ሻጊዝ የልብ ህመም ማሰብ ጀመረ።

«እነዚህን ሁለት ምስጢሮች መፍታት አለብኝ።» ብሎ ብቻውን እየተነጋገረ እያለ ስልኩ ተንጫረረ።

«ሃሎ?»

«ጤና ይስጥልኝ ዶ/ር ሚራዥ።»

«ጤና ይስጥልኝ ኢንጂነር ሻጊዝ» አለ ሚራዥ ሲጠብቀው በመደመሉ ተደስቶ።

«በ10ኛ መንገድ ቁልቁል እየነዳሁ ነው። ከነገርኩህ ቦታ እጠብቅሃለሁ።»

«መጣሁ ኢንጂነር። መጣሁ....» ፈጥኖ ስልኩን ዘግቶ መለባበስ ጀመረ። ሚራዥ ሁሌም እንደሚያዘወትረው ሰማያዊ ጅንስ ሰሪና ነጭ ቲሸረት ከለበሰ በኋላ ፎቁን በአሳንሰር ወረደ። ሰማያዊ ኘራዶዋን መኪና አስነስቶ ወደ 10ኛ አውራ ጐዳና አሳብሮ ገባ።

፩

ሎሳንጀለስ ፡ ሳንታሞኒካ መናፈሻ

ጀምበሯ በፓስፊክ ውቅያኖስ ሰማይ ጠርዝ ላይ ፍም መስላለች። የፀሐይዋ ወርቃማ እግሮች የውቅያኖሱን ውሃ የቀለጠ ወርቅ አስመስለውታል። ዝፍዙ ላይ የሚዋልል የወርቅ ውሃ ይመስላል። የውቅያኖሱ ወርቃማ ማዕበል ግድግዳ መስሎ ይመጣና ከባህሩ ዳርቻ ላይ ሲደርስ አሸዋው ላይ ዕርቃናቸውን ከሚንከባለሉት ልጃገረዶች ጀርባ ላይ ብትን ብሎ ይመለሳል።

ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ዳርቻ ያለችው ሳንታ ሞኒካ መናፈሻ በልጃገረዶችና በከበሌዎች ሳቅ ደምቃለች። ዓይንን ቆንጥጠ ቀልብን አሟጠ የሚይዘው የሴቶች ዕርቃን ገላ ላይ ዓይናቸውን የሚያንከባልሉ ጎረምሶች ጨዋታቸውን አድርተውታል።

ዶ/ር ሚራዥና ኢንጂነር ሻጊዝ እርቃናቸውን በአሸዋው ላይ በሚፈነድቁ ሴቶችና ጥንዶች የተሞላውን የባህር ዳርቻ ትርኢት የዘነጉት ይመስላሉ። አእምሮአቸው በአንድ የጋራ ጉዳያቸው ላይ ተወጥሯል። አብሯቸው አንድ ነጭ ሰውየ ተቀምጧል። ሰውየው ከወየበ ጥርሰና መፃጉዕ ከመሰለ ገፆታው ጋር ቅጥነቱ ተዳምሮ መቃብር ፈንቅሉ የተነሳ አስክሬን ይመስላል። ላለፉት አሥራ ሰባት አመታት በተሰማራበት የንቅሳት ሙያ የታወቀና ትርፋማ የሆነ ሰው ነው። ሲናገር ፈጣን ነው።

ወዲያው አንዲት ነጭ ካዲላክ መኪና በፍጥነት መጥታ እንደቆመች አራት ጥቁዋቁር የለበሱ ሰዎች ወደ መናፈሻው ገብተው ተቀመጡ። አንደኛው ዓይኖቹን ሚራዥና ሻጊዝ ላይ ተክሎ ክንዱ ላይ እንደ ሰአት ባሰረው መነጋገሪያ በፍጥነት ያንሾካሹካል።

የራሺያ ዘይቤ ባለው እንግሊዝኛ «ታቃሳችሁ?» አለ የንቅሳት ባለሙያው። «አሜሪካ የንቅሳት ዲዛይን ማዕከል ነች። በተለይም በ1891 ዓ.ም በኤሌክትሪክ ኃይል ለሚሠራ የመጀመሪያው የንቅሳት መሳሪያ የባለቤትነት መብት ከተሰጠ ወዲህ» ጉሮሮውን ቆሎ ቆሎ ይጠራርጋል። ጉሮሮውን ጠራርጉ ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ። «ብዙ የአሜሪካ የህንድ ጐሳዎች በተለይ ሰውነታቸውንና ፊታቸውን ይነቀሳሉ። ጥቂት የካሊፎርኒያ ጐሳዎችም በተለያዩ ቀለማት ቆዳቸውን ይነቀሳሉ። በኒውዝላንድ የአሪ ጐሳዎች በአጥንት ስባሪ ፊታቸው ላይ የተጠ ማዘዘ ዲዛይን ያለው ንቅሳት ይነቀሳሉ። በጃፓን የአየኑ ጐሳዎች፣ በናይጀሪያ የኢቦ ጐሳዎች፣ የአረቦና ፒግ ሀንዶችና የማላያ ሲኖዬ

ጐሳ አባላት በእሾህ ወይም በመርፌ መሰል መሳሪያዎች ይነቀሳሉ» ሁለቱም በንቃት ንግግሩን እያዳመጡት ነው።

«ታውቃላችሁ?» አለ ሲጋራውን ምጐ። «ንቅሳት ከክርስቶስ ልደት በፊት በተቀበሩ የግብፃውያን ያልፈራረሱ ሬሳዎች ላይም ተገኝቷል። የጥንታዊት ግሪክና የሮም ደራሲያን ግሪካውያን፣ ፈረንሳውያን፣ ጀርመናውያንና እንግሊዛውያን ንቅሳት ይጠቀሙ እንደነበር ፅፈዋል።»

«ለምን ጥቅም ነበር የሚነቀሱት?» አለ ሚራዥ ለረጅም ጊዜ ካዳመጠው በኋላ። ለሻጊዝ ግን ንቅሳቱ ብዙም ግድ የሰጠው አይመስልም። የዶ/ር ሚራዥን ስሜት በጥልቀት የሚመረምር ይመስላል።

«እኛጋ የሚነቀሱት ብዙሃቹ የፍቅረኞቻቸውንና የሚወዱትን ሰው ስም አንዳንዶች ደግሞ የተወለዱበትን ዓመተ ምህረትም ይነቀሳሉ። እኛ የማናውቃቸው ዲዛይኖችንም ይነቀሳሉ።» ሲጋራው እጁ ላይ ሲያልቅ ሌላ ሲጋራ አቀጣጠለ።

«ሌላ በንቅሳት ዙሪያ የምታውቀው ምስጢር ይኖራል?» አለ ዶ/ር ሚራዥ። ሁል ጊዜም ምስጢር የሆኑ ነገሮች ቀልቡን ይገዙታል። 'በግልፅ ከማገኘው አልማዝ ይልቅ የተደበቀ ትርኪ ምርኪ ነገር ይመስጠኛል' ይላል ዘወትር።

«ሌላ?» ሲጋራውን እንደ እናት ጡት ምጥምጥ አድርጎ ጠ ብቶ። «ሮማውያን ወንጀለኞችንና ባሮችን እንዲነቀሱ ያደርጉ ነበር።» ሁለቱም ተያዩ። ሚራዥና ሻጊዝ። «ወንጀለኞችና ባሮች ይነቀሱ ነበር? ወንጀለኞች ልንሆን አንችልም። ባሪያ ፍንገላም ቆሟል። ምናልባት ግን ከባሪያ ፍንገላ ያመለጥን ቢሆንስ? በጃንሆይ ጊዜ የባሪያ ፍንገላ?» አለ ዶ/ር ሚራዥ በውስጡ።

ሰውየው ንግግሩን ቀጠለ። «በእርግጥ አንዳራድ ሰዎች እኔ የማላውቃቸውን ምስጠራዊ ነገሮችን እንድነቅስላቸው ዲዛይን ሰርተው ይመጣሉ»

ዶ/ር ሚራዥ ቲሸርቱን ዝቅ አድርጐ የጀርባውን ንቅሳት ለነሬጬ ሰውየ አሳየውና ወደ ቦታው መለሰው። «ይህን ዓይነት ንቅሳት አይተህ ታውቃለህ?» አለው።

«እስቲ እስቲ መልስህ አሳየኝ?» ሰውየው እንደቱርክ ዶሮ የተመለጠ የመሰለውን አንገቱን አስጐ ንቅሳቱን ለረጅም ጊዜ ተመለከተው። «ዴርቶጋዳ» የሚያውቀው ፊደል። በ'ቶ' ፊደል ላይ የተቀረፁትን ውስብስብ ቁጥሮች እየተመለከተ «ይቅርታ ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም»አለ። «ግን ተራ ነገር አይመስለኝም። በንቅሳቱ ላይ ያሉት ቁጥሮች ምናልባት በዘፈቀደ የተቀመጠ አይመስለኝም። በ'ቶ' ፊደል ላይ ያሉት ቁጥሮች ምናልባት አንድን ምስጢራዊ ነገር የሚያመለክቱ ይመስለኛል። ምናልባት ንቅሳቱን የነቀሳችሁን ሰው ብታናግሩት የተሻለ ሳይሆን አይቀርም»

«የነቀሰን ሰውማ በህይወት የለም» አለ ሻጊዝ።

የሁለቱንም ተመሳሳይ የጀርባ ላይ ንቅሳት ካየ በኋላ አንገቱን እየነቀነቀ «አንድ የጋራ የሆነ ምስጢራዊ ነገር ሳይኖራችሁ አይቀርም።» ብሎ የጨረሰውን የሲጋራ ቁራጭ በጫማው መሬት ላይ ደፈጠጠው።

ሰውየው ኢንጂነር ሻጊዝን በአትኩሮት ይመለከተዋል ከዚህ በኋላ ከኢንጂነሩ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው መፈለጉን ዓይኖቹና አኳኋኑ ያሳብቃሉ። ኢንጂነር ሻጊዝ በንቅሳቱ ላይ እንደሚራዥ ትኩረት ቢሰጥ የበለጠ ቅርርበሹን ማስፋት ይችል ነበር። ኢንጂነሩ ግን ለንቅሳቱ ደንታ የሌለው ይመስላል።

የንቅሳት ባለሙያውን ካሰናበቱት በኋላ ብቻቸውን ተቀምጠው ለየግላቸው ጥቂት አሰላሰሉ። «በነገራችን ላይ እኔ ድሮ ገዳሙ ውስጥ እያለሁ ስለኢትዮጵያውያን ንቅሳቶች አንድ መነኩሴ አጫውተውኝ ነበር።» አለ ሚራዥ ፀጥታውን ለመስበር።

«ምን ሲሉ አጫወቱህ?» አለ ሻጊዝ ከሃሳቡ ባንኖ።

«የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስቲያኖች የክርስትና ስማቸው እንዳይጠፋባቸው ሰውነታቸው ላይ ይነቀሱት ነበር። በድንገት በማይታወቁበት ቦታ ቢሞቱ ክርስቲያኖች መሆናቸው ታውቆ በፀሎተ ፍትሐት እንዲቀበሩ።» አለ ሚራዥ መነኩሴው ያጫወቱትን ለማስታወስ እያማጠ።

«አዎ።ሌላው የነገሩኝ ነገር .....ኢትዮጵያውያን ስሞቻቸውን በየዘመኑ ለዋውጠዋል። ለምሳሌ በዘመነ አሪት ስሞቻቸው ለየግላቸው ልዩ ልዩ ነበር። ማለትም አንዱ በአንዱ ስም አይጠራም ነበር። ለምሳሌ 'አብርሃም' 'አብርሃም' ነው። በዚህ በኛ ዘመን ግን ብዙ አብርሃም የሚባሉ ሰዎችን እናውቃለን። እኔ አንድ ሰው 'አብርሃም' ተብሎ ሲጠራ ትዝ የሚለኝ የመፅሐፍ ቅዱሱ አብርሃም ነው። ዋናው ቁም ነገራችን ግን ስለንቅሳቱ ነው።»

«እሺ ንቅሳቱን በተመለከተ ሌላ ምን ነበር የነገሩህ?»

«ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሲጠመቁ ደግሞ የክርስትና ስም ወጣላቸው። ለምሳሌ ገብረ ኢየሱስ፣ ወለተ ማርያም እየተባሉ ይጠሩ ጀመር። በኋላ ደግሞ የሐይማኖት ግፊት ሲነሳ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስቲያኖች በስማቸው እየታደኑ ይገደሉ ጀመር። በዚህ የተነሳ የክርስትና ስማቸውን በንቅሳት ሰውነታቸው ላይ በመደበቅ አበበ፣ ከበደ፣ ወዘተረፈ እየተባሉ መጠራት ጀመሩ። አሁን ያለንበት ትውልድ መጠሪያ ስሙን ያገኘውም ከዚህ ሂደት በኋላ ነው። ስለዚህ ንቅሳት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ትርጉም ያለው ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በነፃነት እምነታቸውን ማራመድ ባልቻሉበት ወቅት የክርስትና ስማቸውን በንቅሳት የሚደብቁበትን ያህል ሌሎች ምስጢሮችንም በንቅሳት ማስቀመጥ እንደሚችሉ መገመት ቀላል ነው።» ሚራዥ ነገሮችን ሁሉ ከእርሱ ንቅሳት ጋር

ለማገናኘት ቢጥርም ስለነሱ ንቅሳት ጠብ የሚል ነገር ሊያገኝ አልቻለም።

«ስለመሃለኛው ፊደል ስለ 'ቶ' የምታውቀው ነገር ይኖራል? ምናልባት ፊደል በፊደል ማየቱ ሳይሻል አይቀርም።» አለ ሻጊዝ እንደንስር ጠልቀው የሚያዩ ዓይኖቹን ወደ ሚራዥ ቀስሮ።

ስለ 'ቶ' ፊደል አንድ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ማንበቤን አስታውሳለሁ።» አለ ሚራዥ ጥንታዊውን መጽሐፍ እያስታወሰ። «እንደ መጽሐፉ 'ቶ' ፊደል ሰውንና ክርስቶስን ይወክላል። በአጭሩ 'ቶ' ፊደል የህይወት ምልክት ነው። በመካከለኛው ጥንታዊት ኢትዮጵያ በካራን የፀሐይ አምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ የምሥራቁ ግድግዳ ከአልማዝና ከዕንቁ፣ ከእምራልድና ከወርቅ እንዲሁም በተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች ያሸበረቀ እንደ ነበር ተጽፏል። ከዚህ በታች ደግሞ የሁለት ሴት አናብስት ቅርፅ አለ። ከላያቸው መሃሉ የህይወት ምልክት የሆነ 'ቶ' ፊደል ያለበት ፀሐይ ተስሏል። መጽሐፉ 'ቶ' ፊደል የመጀመሪያው ሰውንና ክርስቶስን የሚወክለው የህይወት ምልክት መሆኑን ያስረዳል»

«በነገራችን ላይ ላንድ የቴክኖሎጂ ስብሰባ ባንድ ወቀት ግብፅ ሄጄ ነበር። አንዳንድ ጥንታዊ መካናትን ስጐብኝ ይህን ፊደል ያየሁት ይመስለኛል» አለ ኢንጂነር ሻጊዝ ጉብኝቱን እያስታወሰ።

«አዎ። ልታየው ትችላለህ። ምክንያቱም ዛሬ ታሪክ ከመገልበጡ በፊት ግብፅ የኢትዮጵያ ልጅ ነበረች። እንዲያውም ግብፃውያን በአንድ ዘመን ኢትዮጵውያንን ያመልኩ ነበር። የጥንት ግብፃውያን ኬሜቶች የአባይ ወንዝ ምንጭ ከጨረቃ ተራሮች ሥር እንደሆነና ኢትዮጵያም የአማልክት ምድር እንደሆነች ያምኑ ነበር። የፒራሚድ አሠራርን፣ የቤተመቅደስ አሠራርን፣ ስነ ፈለክንና ሌሎች ጥበባትን ከኢትዮጵያውያን አማልክቶቻቸውና ከግብፅ በስተደቡብ ከሚኖሩ ህዝቦች እንደተማሩ በሂሮግለፊክስ ስዕላዊ ጽሑፎችና በታሪክ ፀሐፊዎችም ከትበውታል። በእርግጥም አንተ እንዳየኸው በግድግዳ ስዕሎቻቸው ላይ አማልክቱ በእጆቻቸው የሚይዙት ልዩ የህይወት ምልክት የሆነው 'ቶ' ፊደል ምንጭ ከጨረቃ ተራሮች ሥር ካለችው የአማልክቱ ምድር ኢትዮጵያ ነች።»

«እንዳልከው ይህ ምልክት ከኢትዮጵያ ፊደሎች አንዱ ነው። ከክርስቶስ ልደት በኋላም ከመስቀል አይነቶች እንደ አንዱ ሆኖ መወሰዱን እኔም አውቃለሁ። በተለይም በወሌና በበጀምድር የሚገኙ ሴቶች ይህንን ምልክት በግንባራቸው ላይ ይነቀሱታል» ኢንጂነር ሻጊዝም የሚያውቀውን አከለበት።

«ያም ሆነ ይህ በእኛ ንቅሳት ላይ ያለው 'ቶ' ግን በሌሎች ነገሮች ዑደላ ነው። ቁልፍ ነገር ይመስለኛል» አለ ሚራዥ የፊደሉ ቅርጽ ወደ ቁልፍነት ማዘንበሉን እያየ።

«ምናልባት ያንድ ምስጢራዊ ነገር ቁልፍ ይመስለኛል።»

«ሌሎች ፊደላትስ?»

«በጥቅሉ ዲርቶጋዳ የሚለው ቃል ስለዚህ ምስጢራዊ ነገር ብዙ መረጃዎችን የያዘ ይመስለኛል»

ይህንንና ሌሎች መሠረታዊ ነገሮችን ሲጨዋወቱ ከቆዩ ዘኋላ ስለ ኢንጂነር ሻጊዝ የጤንነት ጉዳይ መነጋገር ቀጠሉ።

«ጤንነትህ እንዴት ነው አሁን እየተመለሰ ነው?» አለ ዶ/ር ሚራኽ በረጅሙ ተንፍሶ።

«እያገገምኩ ነው። ግን ያው ከሁለት ወር በኋላ መልሼ መቀደዴ የማይቀር ጉዳይ ነው። የልቤ ጉዳይ ዘላቂ መፍትሔ እስካላገኘ ድረስ ስቀደድ ስሰፋ መኖር እጣ ፈንታዬ ነው።»

«ኢንጂነር» አለ ሚራኽ በትካዜ። «በዚህ ወቅት ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ማከናወን እፈልጋለሁ።»

«ምን ምን ነገሮችን?» ሲል አንጂነር ሻጊዝ ጠየቀው።

«አንደኛ የአንተን የልብ ችግር መፍታት እፈልጋለሁ። የዚያችን ደሀ ሀገር ችግር ለመፍታት በተነሳህበት ወቅት የገጠመህ አሰቸጋሪ ጉዳይ የግልህ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቷን እንወዳለን የሚሉትንም ይመለከታል። ለአሜሪካ የሠራኽውን ሩቡን ያህል እንኳ ያች ደሀ ሀገር ትፈልጋለች። ሀገሪቷን የረቂቅ ቴክኖሎጂ ባለቤት ማድረግ የሚቻለው እንዳንተ ያሉ የቴክኖሎጂ ሰዎች ተባብረው ከተነሱላት ነው። እስራኤልን መልሰው በ1948 የገነቧት ሰዎች ጥቂት ሀገራቸውንና ህዝባቸውን የሚወዱ ጽዮናውያን ናቸው። ለውጥ ለማምጣት ብዛት ብቻ ሳይሆን ቁርጠኛ አቋም ያላቸው ጥቂት ሰዎች በቂ ናቸው። አንተ ደግሞ ቁርጠኛ አቋም ካላቸው ሰዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ ነህ። ወንጌልን ለአለም ይሰብኩ ዘንድ ኢየሱስ የመረጣቸው ደቀ መዛሙርት አሥራ ሁለት ብቻ ናቸው። ኢትዮጵያን መልሶ ለመገንባትም ግዴታ ሚሊዮኖች አያስፈልጉም። ጥቂት ቁርጠኞች በቂ ናቸው። ጥቂት ቁርጠኞች ሚሊዮኖችን ከኋላቸው ያሰልፋሉ። ስለዚህ አንተን ማዳን አንዱ ጉዳዬ ነው። ሁለተኛው ዋና ጉዳይ ደግሞ የንቅሳታችን ምስጢር ማፈላለግ ነው።» በልቡ የያዘው ግን ሌላ ልዩ ጉዳይ አለው። ሲጻራን መፈለግ። ግን ወዴት ብሎ እንደሚፈልጋት ግራግብት ብሎታል። ሞኝ ያስመስለኛል ብሎ ባያተወው ኑሮ ማስታወቂያ ለማስነገርም አስቦ ነበር። «በዓለም ላይ ከ6 ቢሊዮን በላይ ህዝብ ነው ያለው። ሴቶችም ከግማሽ በላይ ይሆናሉ። ከዚህ መሃል ሲጻራን እንዴት ልታገኛት ትችላለህ?» ብሎት ነበር አንድ ቀን ባርንጊጻ። እሱ ግን ልቡ ቀርጦለት ረስቶአት አያውቅም።

«ለማንኛውም ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ። ራስህን በጥንቃቄ ያዘው። በማስተዋል ሁሉንም እናደርገዋለን።» አለ ሻጊዝ። «...ማስተዋል ይጋርድሃል ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ይላል ቅዱሱ መፅሐፍ።»

እየተነጋገሩ ወደ መኪኖቻቸው ሲገቡ ጥቋቁር መነፅር አድርገው ተቀምጠው የነበሩት ሰዎችም ወደ መኪኖቻቸው ገብተው ተከተሏቸው።

ዶ/ር ሚራኽ ከኢንጂነር ሻጊዝ ተለይቶ ወደ ቤቱ ሲጓዝ አራቱን ሰዎች የያዘችው ነጭዋ ካዲላክ መኪና እየተከተለችው ነበር። በ101ኛው አውራ ጉዳና ተገንጥሎ ወደ አፓርታማው በሚወስደው መንገድ ሲታጠፍም ነጭዋ ካዲላክም አብራው ታጠፈች። መኪናውን ለማሳለፍ ፍጥነቱን ሲቀንስ ካዲላኩም ፍጥነቱን ቀንሶ ከኋላው ተከተለው። መኪናው ውስጥ ያሉትን ሰዎች በጉን መስታወቱ ለማየት ቢጥርም ሊለያቸው አልቻለም።

ወደቤቱ እንደገባ በመስኮቱ በኩል ቁልቁል ካዲላክዋን እየተመለከተ እያለ ከአፓርታማው መኪና ማቆሚያ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ። መኪናው ውስጥ ቦንብ ተጠምዶ እንደነበር ሲያውቅ በድንጋጤ ተንቀጠቀጠ። ወዲያው አካባቢው በፖሊስ መኪና ድምጽ ተዋጠ።

ካዲላክዋ ከአካባቢው ከተሰወረች ከደቂቃዎች በኋላ ፖሊሶች ሚራኽን በጥያቄ ያጣድፉት ጀመር።

«ስለተፈጠረው ነገር የምታውቀው ነገር አለ?»

«በፍፁም የማውቀው ነገር የለም።»

«ግባ።»

«ዮት ነው የምገባው?»

«ቃልህን መስጠት አለብህ።»

«የምን ቃል ነው ምሰጣችሁ?»

«ሁሉንም ነገር በኋላ እንነጋገራለን። ቃልህን ልትሰጥ ይገባል።»

ሰማያዊና ቀይ ቀይ ጨረር የሚተፋት የፖሊስ መኪናዎች ሚራኽን ይዘው ተወነጨፉ።

፫

ዶክተር ሚራኾር ለፖሊስ ቃሉን ሰጥቶ ከተመለሰ በኋላ ከወዳጁት እንደተሳከ የማያውቀውን ደብዳቤ ኢንቨሎፑን ከመቅደዱ በፊት ለዶክተር ግርንጊዳ ስልክ ደወለ። ከሥራም ስለተፈናቀለ ወደ አስቲን ሄዶ ከዶክተር ግርንጊዳ ጋር ለመሥራት አሰቧል።

«ሃሎ» አለ ሚራኾር።

«ጤና ይስጥልኝ! አስቲን የህክምና ማዕከል?»

«አም ጤና ይስጥልኝ። ምን እንርዳዎ?» የሴት ድምፅ መለሰለት።

«ዶ/ር ግርንጊዳን ነበር እሳክም?» ሲል ጠየቀ ሚራኾር።

«ተሳስተዋል ጌታዬ።» አለች ሴቷ ከወዲያኛው ጫፍ

«ይህ ቴክሳስ ውስጥ ያለው አስቲን የህክምና ማዕከል አይደለም?»

«ነው ጌታዬ። ግን ዶክተር ግርንጊዳ ወደ ሥራ ከገቡ ሁለት ወር አልፏቸዋል» አለች ሴትየዋ። «ይሀን አገር የሰማውን ጉዳይ አሳወቁም እስከአሁን? ዜና አያዳምጡም ማለት ነው።» ቀጥላ የተናገረችውን ማመን አቃተው። በድንጋጤ ደንገዘ የስልኩን እጀታ በቀስታ ዘጋው።

«የፈጣሪ ያለህ!» አለ ሚራኾር ከው ብሎ።

ከሁለት ወር በፊት የተላለፈ ዜና ይዳገምለት ይመስል ጠረጴዛው ላይ የርቀት መቆጣጠሪያውን አንስቶ ቴሌቪዥኑን ከፈተው። እየተላለፈ የነበረው የጡት ማስያዣ ማስታወቂያ ነበር። ጡት ማስያዣውን የምታስተዋውቀው ሴት ግርንጊዳን የዋጠችበት ይመስል አፍጦ ቴሌቪዥኑ ውስጥ ተመለከታት። ዕርቃንዋን ቆማ የጡት ማስያዣውን ከክብ ጠቆሟ ላይ አውልቃ አንሶላ ውስጥ ወደሚጠብቃት ወንድ ስትሄድ ወንዱ ደግሞ ከአንሶላው ውስጥ ወጣ ብሎ አልጋው ላይ የጣለችውን ጡት ማስያዣ ባዶ ደረቱ ላይ ለብሶ እየሳቀ ወደ አንሶላው ውስጥ ይዟት እስኪጠልቅ ማስታወቂያውን ቆሞ በመመልከቱ በራሱ ተገረመ።

የላከ አድራሻ የሌለውን ደብዳቤ ኢንቨሎፕ ቀዶ ውስጥ ያለውን መልእክት ሊያነብ ሰፍ ብሎ ሲመለከት ከባዶ ወረቀት ጋር ተፋጠጠ። «ባዶ ወረቀት?» ሲል ብቻውን ጮኸ። «ማነው ሊያሳብደኝ የሚሳሳር!» ጠረጴዛውን በቡጢ ነርቶ ከጥጉ ያለውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ። ተደርድረው ቤቱን የሞሉት መሳሕፍቱ ያናግሩት ይመስል ዓይኑን አንቀዋለለባቸው።

በሰማው አንድ አስደንጋጭ ዜና ዓይኖቹን ከመጻሀፍቱ መደርደሪያ ላይ ነቅሎ ከቴሪቪዥኑ ስክሪን ላይ ወረወራቸው።

ቅብጥብጧ ሴት ጋዜጠኛ ጡቶቿን በነፊል አጋልቦ በሚያሳይ ጥቁር ልብስ ከታጀለው ደረቷ በላይ ያለውን አጭር አንገቷን ሰበር ሰካ እያደረገች የምታነበንበውን ዜና ማመን አልቻለም።

«በትናንትናው ምሽት እውቁ የንቅሳት ባለሙያ ሚስተር ጆንስ መኪናው ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ ህይወቱ አለፈ። ሚስተር ጆንስ ላለፉት አስራ ሰባት አመታት በንቅሳት ሞያ ተሰማርቶ የኖረ ትርፋማ ሰው ሲሆን ትናንት አመሻሹ ላይ በሌሳንጀለስ ከተማ ዳርቻ በምትገኘው ሳንታ ሞኒካ መናፈሻ ከሁለት ሰዎች ጋር ሲገናኝ አምሽቶ ወደ ሥራ ቦታው ሲመለስ መኪና ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ ህይወቱ ማለፉን ፖሊስ ገልጿል። አብረውት ከነበሩት ሰዎች በአንደኛው ዶክተር ሚራኾር በሚባል ሰው መኪና ውስጥም የተጠመደ ፈንጂ ፈንድቶ ቃጠሎ እንዳስነሳ ሲገለፅ ዶክተሩ ከመኪናው ከወጣ በኋላ ቦንቡ በመፈንዳቱ ህይወት ሊተርፍ ችሏል። ቦንቡን ያጠመዱትን ሰዎች ይዞ ለፍርድ እንደሚያቀርብ ፖሊስ የገለፀ ሲሆን ህብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግም አያይዞ ገልጿል።»

ዜናው እንዳበቃ ላቡ በግንባሩ ጭርር ሲል በመዳፉ ሞዥቀ አገፈጩን በእጁ አስደግፎ በድንጋጤ ተዋጠ።

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?» ራሱን ጠየቀ። «ማነው እያጠመደኝ ያለው? ለምን የንቅሳት ባለሙያውስ ተገደለ? እኔንስ ማነው ቦንቡን ያጠመደው?» ድምፁ ከጣራ በላይ እስኪሰማ ድረስ ብቻውን እየጮኸ ነበር።

«እጅህ የማትችለውን ጉዳይ እየነካካ እንደሆነ አሳወቅህም? ሚስተር ሚራኾር!» ሲል ከኋላው የሚናገር ድምጽ ሰምቶ ሲዞር ጥቁር ጭምብል ለብሶ ሽጉጥ ካነጣጠረበት ሰው ጋር ተፋጠጠ። ትንፋሹን ዋጥ አድርጉ «ምን?» አለ ዶክተር ሚራኾር።

«አም። ጉረኛ ነህ። ጤና ይጣህ ዶ/ተር!» ጣቱን ወደ ምላጩ ላከው።

«ምን እንደምትል አልገባኝም። የያዝከውን ነገር መለስ አድርገውና ብንነጋገር የተሻለ ነው» አለ ዶ/ር ሚራኾር ጭንብሉ ውስጥ ያለውን ገጻይ ሊያረጋጋ።

«በሽተኛ ሰው መሆንህ አየገባኝ ነው። በሽተኞች በሽተኞችን ለማዳን ሲነሱ ማየት ትልቁ የአለማችን አስቂኝ ቀልድ ነው።»

«እየውልህ ...ለምን አንግባባም።»

«እንዳትንቀሳቀስ። ባለህበት።»

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?»

«እንደዚህ። ይሄው እጅህን በእጅህ ልትቆርጥ የቀረህ የእኔ ጣት ምላጩን እስኪስብ መጠበቅ ብቻ ነው። ግን ይህ ቂልነትህ

በገሃነም ውስጥም የሚያኖርህ አይመስለኝም። በገሃነም ውስጥ ያሉት እንዳንተ ያሉት ቂሎች አይደሉም።»

«እየውልህ ....»

«ዝም በል! ለመሆኑ ኢንጂነሩ ያስፈለጋችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠምዳችሁ ልታርሱት ነው? የምንረዳችሁ ገንዘብ ለአህያ መግዣ አይበቃችሁም? አርፋችሁ በአህያችሁ አታርሱም? መልካም ጉዞ ሐኪምና ታካሚ ወደ ሌለበት ገሃነም በሹተኛው ዶክተር...» ብሎ የሸጉጡን ምላጭ ሊስብ ሲል በአፍጢሙ ተደፋ። የድምፅ ማፈኛ በተገጠመለት ሽጉጥ ጭንብል ያጠለቀውን ገዳይ መትታ የጣለችው ሜሮዳን ከኋላ ቆማ ሲያያት ከሰማይ የወረደች መልአክ መሰለችው። ገዳዩ በግንባሩ ወለሉ ላይ እንደተደፋ ከጀርባው በልቡ ትክክል ደገመችው።

በድኑን ተራምዳ ሚራዥን አቀፈችውና «ቶሎ መውጣት አለብን» አለችው። «የምትፈልገውን ጓዝ ቶሎ ቶሎ እንጫን።»

«መኪናዬ እኮ ተቃጥሏል። አልሰማሽም?» አላት ሚራዥ ከደረቱ ተጠግታ እንዳቀፈችው።

«እሱን አውቃለሁ» አለችው። «የጭነት መኪና ይዤ መጥቻለሁ።»

«ይህ እንደሚሆን ታውቂ ነበር እንዴ?» አላት የሲ.አይ.ኤ ኤጀንት መሆንዋን የዘነጋው ይመስል።

«እንዴት አላውቅም?» አለችው አስገርሟት።

«እነማን ናቸው እነዚህ ሰዎች?»

«ሲ.አይ.ኤዎች።»

«ቆይ እንዴት?»

«ከዛ ሰውዬ ጋር በጀመርከው ጉዳይ ነዋ!»

«ከማን ጋር?»

«ሁለት ነገር ልንገርህ። አንደኛው ... የኢንጂነር ሻጊዝን የልብ ቀዶጥገና ምስጢር ማነፍነፍ ጀመርክ። ሁለተኛው ከሆስፒታሉ ብትባረርም ከኢንጂነሩ ጋር ብዙ ጊዜ አብረህ ታየህ። ስለዚህም ሊያስቆሙህ ፈለጉ። እንድትወገድ ተወሰነ።»

«የንቅሳቱ ባለሙያ ግድያስ በምን ምክንያት ነው?»

«ከሩሲያ ደህንነቶች ጋር ግንኙነት ነበረው። ወደናንተ ከመምጣቱ በፊት ከራሺያዎች ጋር በአንድ ነገር ላይ እንደተደራደረ ሲ.አይ.ኤ ደርሰበታል።»

«ምንድን ነው የተደራደረው?»

«የራሺያ የቴክኖሎጂ ሰላዮች የንቅሳት ባለሙያው ከሻጊዝ ጋር ግንኙነት እንዳለው ካወቁ በኋላ ኢንጂነሩን ጠልፈው ወደራሺያ ለመውሰድ እንዲረዳቸው ጠቀም ያለ ገንዘብ ሰጥተውታል። የንቅሳቱ ባለሙያ ደግሞ በትውልድ ሩሲያዊ ነው። ስለዚህ እንዲወገድ

ተወሰነበት። በነገራችን ላይ እንድትወገዱ የተወሰነባችሁ ሁለታችሁ ብቻ አይደላችሁም።»

«ደግሞ ሌላም አለ?»

«ሌሎችም አሉ። ህንዶች፣ ፓኪስታኖች፣ ጃፓኖች፣ እስራኤሎች፣ ቻይናዎች፣ ኢራኖች... እሱን ለመውሰድ እያንዣበቡ ነው። የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎችም እየተከታተሉት ነው።»

«የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች?»

«አዎ። የአትዮጵያ የደህንነት ሰዎች።»

«ለምንድን ነው የሚፈልጉት እነሱ ደሞ?»

«ሊያስወግዱት ይፈልጋሉ።»

«የፈጣሪ ያለህ! ... ለምን?»

«ሰውየው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እጁን አስገብቷል።»

«እና ቢያስገባስ ሀገሩ አይደለች እንዴ?» አለ ሚራዥ ደንግጦ። «ደግሞ እኮ አባብለው ሊይዙት የሚገባ ሰው ነው። ምንም አይነት የፖለቲካ አመለካከት ይኑረው ሀገሪቷ ተቀብላ እውቀቱን መጠቀም አለባት። አመለካከቱ የግሉ ነው። የዚህን ሰው የቴክኖሎጂ እውቀት ለማግኘት የአለማችን ሀገራት የማያድኑት ከእሱ ፍቅር ይዟቸው ነው እንዴ ድሮስ? እንዴት ሀገሩ በሯን ትዘጋበታለች? እንዴት የሀገሩ ልጆች ለመግደል ያድኑታል?» ገነፈለ።

«አልገባህም በቃ» አለችው ሜሮዳ። ደረቅ ፈገግታዋን እያሳየችው።

«የጀመረው የፖለቲካ ትግል ሰላማዊ ትግል አይደለም። ጠርነት አውጇል። ይህን ነው እያልኩህ ያለሁት።»

«አይምሰልሽ። ሰውየውን ቀርቤ አይቸዋለሁ።» አለ ሚራዥ ድምፁን ለዘብ አድርጉ።... «የጦረኝነት ስሜት ውስጡ የለም።»

«ውስጡ ባይኖርም በጥጉ ያሉ ሰዎች የገፋፉት ይመስለኛል።»

«ቢሆንም..... መወገደ የለበትም። ሀገሪቱ የመንኩራኩር ማምጠቂያ ጣቢያና የረቀቀ የቴክኖሎጂ ማዕከል ባይኖራትም በሳተላይትና በዘመናዊ ራዳር ያለው እውቀቱን ልትጠቀምበት ይገባታል። እስኪ አስቢው ይህ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ መቶ ሰው ቢያሰለጥን እንኳ ራሱን አባዝቶ አገሪቷን በቴክኖሎጂ ማበልፀግ አይችልም? በዛ ላይ ገንዘብ ያለው ሰው ነው። የረቀቁ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ወደሀገሩ እንዲያስገባ መጐትጐት ሲገባ ማለደድ?»

«አሁንም ያልገባህ ነገር አለ።»

«ሳይገባኝ ይቅር አልኩሽኮ።»

«ያም ሆነ ይህ አሜሪካ ትፈልገዋለች። ከህዋ ምርምሯ ጀርባ ሌላ ሀገራዊ ምስጢር ይዟል። የረዥም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳኤሎቿን፣የራዳሮቿ፣የሳተላይቶቿ፣ የቴክኖሎጂ ምርምር ጣቢያዎቿ ሌሎችም ወታደራዊና ሳይንሳዊ ምስጢሮቿ በእጁ እንደመሆናቸው

መጠን ትጠብቀዋለች። ዓይን የሚያዙና ሞልፊቶች ሁሌም በዙሪያው ያንጥባባሉ። ከኢትዮጵያም ሆነ ከማንም ሀገር ሰው፣ ገዳዩም ሆነ ወዳጁ ጋር ከተገናኘ እንደሁኔታው ያገኘው ሰው አስጊ ከሆነ ይወገዳል። አንተ ግን አመለጥክ። በነቡ ከመኪናህ ከወጣህ በኋላ ለምን እንደፈነዳ ታውቃለህ፡ ...ከንተ መኪና ውስጥ የተጠመደው በንብ መቆጣጠሪያ በእጄ ገባ። በነፈዜ ካዲላክ ከሚከታተሉህ ሰዎች ጀርባ መኪናዋ ውስጥ ሆኜ እየተከታተልኩህ ነበር። ከመኪናህ ወጥተህ ስምንተኛ ሮቅ ላይ ሳይህ አፈነዳሁት።» ይህን በማድረጓ ምናልባት ከሲአይኤ የሚጠብቃት አደጋ እንዳለ ብታውቅም ሲሞት ዝም ማለት አልቻለችም፣ ትወደዋለች።

«ወጥ ቤት ሚሮዳ መቼም አንቺ እኮ አስገራሚ ሰው ነሽ» አላት። «ከሠር ካምፑ አትዮጵያ ውስጥ ጀምሮ ህይወቴን እየታደግሽልኝ ነው።» ይህን እየተነጋገሩ እቃውን እየሸከፉ ነበር።

«ከሁሉም በላይ» አለ ሚራኻ። «መዛሕፍቶቼን ጥዬ ወደ የትም ንቅንቅ አልልም።»

«የተወሰኑትን ብቻ ምረጥና እንሂድ ይልቅ ሁሉን ማግበስበስ አያስፈልግህም።»

«በፍፁም አላደርገውም። የምመርጠው መጽሐፍ የለም። ሁሉም መጻሕፍት ባለሙለታዎቼ ናቸው። መጻሕፍቶቼ ስንት ረጃጅም ቀኖችንና ጀግጃጋ ሌሊቶችን አሳጥረውልኛል መሰለሽ!»

«ሌላ መርሳት የሌለብህ ነገር አለ፣» አለችው ንዙን ሁሉ ጠቅልለው መኪና ማቆሚያው ውስጥ ከቆመችው መኪና ውስጥ ከጫኑ በኋላ።

«አዎ። ጊታሬን ረስቼዋለሁ። ጊታሮቼን!»

«ጊታሮቼን፡» ስትል ጠየቀችው። «ደሞ ስንት ሆኑ፡ »

«ባለፈው ቀን አንድ ኢትዮጵያዊ ሽማግሌ ሰውዬ ሌላ ጊታር ሰጠኝከ። አልነገርኩሽም ለካ። ሰውየው ሁል ጊዜ በፓስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ ጊታር ስጫወት እየመጣ ይመለከተኝ ነበር። ባለፈው ከአንድ ሳምንት በፊት የጊታር ስጦታ አበረከተልኝ። ምንድን ነበር ያለኝ፡» ሲል ራሱን ጠየቀ።

«ምን አለህ፡» አለችው ዕቃውን መኪናው ላይ እያመጅቸች።

«አዎ። እንዲህ ነው ያለኝ። እስከ ህይወትህ ፍፃሜ ጊታሩን አትጣልብኝ አደራ። ጊታሩን አትጣለው። ለሌላ ሰውም አትስጥ። በህይወቴ ሁሉ እንደዚህ ያለ ስጦታ ለማግኘም ሰጥቼ አላውቅም። በዚህ የጊታር ዜማ አንድ ቀን ወደ ጥልቁ ምስጢር ትገባበታለህ አለኝ።»

«ሰውየውን ታውቀዋለህ እንዴ፡»

«እረ አላውቀውም። ግን ...ጊታሩን ሲሰጠኝ «ስፈልግህ ነበር! በመጨረሻም አገኘሁህ» ብሎኝ ነበር። ለምንድን ነበር የምትፈልገኝ፣ ብለው ይህን ጊታር ልሰጥህ ብሎኝ ከፊቴ ተሰወረ።

«ሰብድ መሆን አለበት። ወይም የጊታር አፍቃሪ ራስታ ወይም ደሞ ሾጥ ያደረገው መሆን አለበት» አለችው።

«እኔጃ። ሰውየው ሽማግሌ ነገር ነው። ቢሆንም ጊታሩን አልጥልበትም። ላምላው።»

የረሳውን ጊታር ይዞ ተመለሰ።

፭

ኒውዮርክ ፡ አሜሪካ

በኒውዮርክ ከተማ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት አደባባይ ማዶ ገባ ብሎ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቷ ከደረሱ ቆይተዋል። የዶክተር ሚራዥን እቃዎች በቤቷ ውስጥ ቦታ ቦታ ሲሰጡ አድረው ውለዋል። መጻህፍቱም ከወለሉ እስከጣሪው በደረሱ መደርደሪያዎች ታጭቀዋል። ቤቷ ፀጥታ የሰፈነበትና ደበቅ ያለ መሆኑ ለሚራዥ ሰላም ሰጥቶታል። ገዳማዊው ሚራዥ ፀጥታ ነፍሱ ነው። ዝምታም ሰላሙ። አሁን ሥራውን ከጨረሱ በኋላ ሚራዥ ገላውን ለመለቃለቅ ገብቷል።

የሜሮዳ ቤት ብዙም የሴት ቤት አይመስልም። በትርኪ ምርኪ የሴት ዕቃዎች የተሞላ አይደለም። ደብዘዝ ያሉት አምፕሎች ከወርቃማ ውብ ሶፋዎች ላይ ሲንፀባረቁ ዓይንን ይስባሉ። ፍንትው ያለ ደማቅ ብርሃን አይመቻትም። እንዲያውም ጨለማ ነፍሷ ነው። ሁሌም ከብርሃን ስትሸሽ ነው የኖረችው። የሥራዋ ልብሱ ጨለማ ነው። ውስብስቡ ሲ.አይ.ኤ ጨለማን አስለምዷታል። ጨለማ ለብሳ በጨለማ ዳብሳ በጨለማ ጉርሳ ትኖራለች።

ሲ.አይ.ኤ ሳይመለምላት በፊትም ሥራዋ ዘላለም ጨለማ ሊሆን ነበር። ሴተኛ አዳሪነት። ጨለማ አዳሪነት። ያ ብኩን የጨለማ ህይወቷ ወደ ሌላ የጨለማ ህይወት ከተታት።

በአዲስ አበባ ከተማ ሰዋራ ሥፍራዎች ጨለማ ለብሳ ገላዋን ስትሸጥ ነበር እናትዋ ከብዙ ዓመታት በፊት። ይህን ህይወት የጀመረችበትን ቅፅበት መቼም ረስታው አታውቅም። እናቷ ሴተኛ አዳሪ ስለነበሩ አባቷን አታውቅም። ባላውቀው ይሻላል ትላለች። እናቷ አረጁ። ፊታቸውን ማዲያት ወረሳቸው። ከማዲያቱ በተጨማሪ ቆዳቸው ተሸበሸበ። ምንም አይነት መቀባባት የማይገድበው እርጅና ተጫናቸው። ደምበኞቻቸውን በሙሉ አጡ።

ሜሮዳ የእናትዋን አስከፊና ጭምዛዛ ህይወት በልጅነቷ ጨለጠችው። ከእናቷ አንድ ቀን ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ወደ ባህርዳር ከተማ ይዘዋት ሲሄዱ በባህርዳር ሥራ ሞልቷል የሚባል ወሬ ሰምተው ነበር። ያኔ ሜሮዳ የአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተፈትና ወድቃ ነበር። በመውደቋ የበለጠ ህይወቷ ጉመዘዘ። ውድቀቷ ወደ ሌላ ውድቀት ወረወራት። ከአዲስ አበባ ባህርዳር ከተማ እስኪደርሱ ድረስ እናቷ ምንም አላናገሯትም። ወደየት እንደሚሄዱም አላወቀችም ነበር። ከእናቷ ጋር ተጣልተው ነበርና። እናቷ ብዙም ስነ ምግባራቸው የሚያስቀና አልነበረም። የበለጠ ባሰባቸው። ብስጭት ሲሉ ኢ ስነ ምግባራዊ ቃላትንም ይናገሯታል።

«እኔ ገላዬን ሸጬ እስከ አሁን ድረስ ያስተማርኩሽ እንድትወድቂ ነበር?» አሏት ባህርዳር ከደረሱ ከጥቂት ቀናት በኋላ። ሥራ ሞልቷል የተባለው ወሬ ወሬ ብቻ ሆኖ ነበር ያገኙት። ባልታወቁበት ቦታ ሄደው በአዲስ መልክ ሥራ ለመጀመር ነበር። ያቀዱት ግን አልተሳካም። በወታደር ተጨናንቃለች.....እንዲያውም የባህር ዳር ሴት በሙሉ ቢሸረሙጥ እንኩዋ ለወታደሩ አይበቃውም ሲባል ጊዜ እስኪደርሱ የቸኮሉላት ባህር ዳርን አንድም ወታደር አላገኙባትም። ተስፋቸው ጫጭቶ ሞትን እስከ መናፈቅ ራሳቸውን ከህይወት መዝገብ ላይ ለመፋቅ እስከመመኘት ደረሱ።

«እኔ ሌላ ምን አወርስሻለሁ የማውቀውም የተማርኩትም ሽርሙጥና ነው። ግቢበታ! በቃ። ከአሁን በኋላ ከእኔ በምን ትሻያለሽ? የተማረ ከወደቀ ካልተማረ በምን ይሻላል? እኔም አንቺም ሌላ ምንም የለንም፡ ከሴት ብልታችን በስተቀር። ስለዚህ ትንሿ ብልትሽን አዘጋጂት። የኔዋን ጨርሰናታል፤በቃት። ባይበቃትም ከአሁን በኋላ የሚነካት የለም። ጨርጭሳለች፤ ገጥማለች። ሸጠን በላናት። ተሸጣ አንችን አስተማረች። አሁን አድገሻል፤ በቃኝ። እኔም ተስፋ ቆርጫለሁ። ደላላው የመጀመሪያ ደንበኛሽ ፈረንጅ እንደሆነ ነግሮኛል።» ይህን ሲነግሯት የሜሮዳ እንባ በጉንጯ እየፈሰሰ ነበር የውድቀት እንባ። የተስፋ መቁረጥ እንባ። የፍርሃት እንባ።

«በደንብ አስተናግጂው። ሁኚልኝ እንደሚልሽ ሁኚለት.....»እናትዋ ይህን ተስፋ አስቆራጭ ንግግር የሚነግሯት ከአባይ ወንዝ ድልድይ ላይ ቆመው የውሃውን አወራረድ ቁልቁል እየተመለከቱ ነበር።

«ያው! ደላላው መጣ ሂጂ።ፈረንጁን ጥሩ ዋጋ እንዲከፍልሽ ጠይቂው። እኔ ግን አላስቸግርሽም። ኑሬም አያምርብኝ። ራስሽን አኑሪ። እንደኔ እስከትጨረጭሽ።» እናቷ አልመስላት አሉ። ስለሚናገሩት የማያስቡ መሆናቸውን ታውቃለች። «ብልት... ምናምን» ሲሉ ይሰቀጥጣታል። ምናልባት የሥራው ጠባይ ይሆናል ብላ ታስብ ነበር። ሲማቱም ጨካኝ ናቸው። እናት አይመስሏትም። በራ የምትጠፋበት ብታገኝ ትሄድ ነበር።

«ሌላ የማወርስሽ ምን አለኝ? ተምረሽ ትለውጭኛለሽ ብዬ ነበር። ስትወድቂ ተስፋዬም አብሮ ወደቀ። ለእኔ አትጨነቂ። ራስሽን አኑሪ።» ብለው ከድልድዩ ላይ ወደታች አዩና ራሳቸውን ወደ አባይ ወረወሩት። «እማዬ!» ብላ ሜሮዳም ልትወረወር ስትል ደላላው እጇን ይዞ አስቀራት። አባይ ከሚያግተለትለው ማንድና ግፋፎ ጋር ይዟቸው ጥርግ አለ። አባይ ከመሙላቱ የተነሳ ፈረሰኛውን እያሰገረ ነበር። ድፍርስርሱ አባይን ቁልቁል ከድልድዩ ቆማ እያየች ራሷን ልትወረውር በትታገልም ደላላው ጉትዩ ታክሲ ውስጥ ዱሎ ይዟት ከነፈ።

በዛው ምሽት እንባዋ ሳይደርቅ ደላላው ለፈረንጁ ሸጣት። ሴትነቷን ሸጠው። ፈረንጁ ብዙ ዶላሮችን መዥረጥ አድርጉ ለደላላው ሲሰጠው ደላላው መልሶ «ድንግል እኮ ናት ጌታዬ!» አለው። «እሱንማ ነግረኸኛል።» አለ ፈረንጁ ቀልጠፍ ባለ እንግሊዝኛ።

«ስለዚህ ዋጋዋም ያስጨምራል» አለ ደላላው በሞተ እንግሊዝኛ። ፈረንጁ ሌላ የዶላር ኖቶች ሲጨምርለት ተቀብሎ ደላላው እየተንበጀበጀ ጠፋ። ፈረንጁን ከዚህም በፊት ደጋግማ አይታው ታውቃለች። በተከራዩበት ሰፈር ይመጣ ነበር። ከሴታቸው ፊት ለፊት ካለ ጠላ ቤት ተቀምጦ ብዙ ጊዜ ክፍት የሚሆነውን የነ ሜሮዳን ደሳሳ ቤት እያጮለቀ ይመለከት ነበር። ሜሮዳን በጣም ሲያያት አንገትዋን ትሰብርም ነበር። በዚህ በጁ በወደቀችበት ወቅት ካሁን አሁን ምን ያደርገኝ ይሆን እያለች ስትርድ እርሱ ግን ምንም አይነት የወሲብ ጥቃት ሳያደርስባት ላንድ ወር ያህል ካቆያት በሁዋላ ወደ ኬኒያ ወሰዳት። ናይሮቢ በሚገኘው ልዩ የሲ.አይ.ኤ ማሰልጠኛ ጣቢያ ውስጥ ራሷን አገኘችው። መሠረታዊ የስለላ ሥልጠናዎችን ወሰደች። የመሣሪያ አጠቃቀም፣ የምስጢር አያያዝ፣ ... የመረጃ አሰባሰብ፣ አለባበስ፣ የማስመሰያ ሥራ አሠራርንና ሌሎችን ብዙ አድካሚ ሥልጠናዎች ከወሰደች በኋላ መልሶ ወደ ኢትዮጵያ አስገባት።

ከዚያም በሰሜኑ ጦር ውስጥ ወጥ ሰሪ ሆና ተቀጠረች። እናቷን እድሜ ልኳን በድህነት ስታማቅቃትና ገላዋን ስታሸጣት ከኖረችው ሀገር በተቃራኒ ቆመች። ሀገሯን በሰፈረችላት ቁና ተሰፈረቻት። ወታደራዊ ምስጢሮችን በሚስብ ጥም ከተለከፉ ወታደራዊ ባለስልጣናቷ እጅ እየነጠቀች ለሲ.አይ.ኤ ስትሰጥ አንዳችም ደንታ የላትም ነበር። ወጥ ቤቷ ሜሮዳ ወጡን ስታማስል የወታደራዊ ባለስልጣናቷን ምስጢሮችም ለሲ.አይ.ኤ እያማሰለች ነበር።

ማንንም የሚያንበረክክ ገላዋ እንኪንስ የወሲብ ትማት ያቃጠለውን የበረሃ ባለስልጣን ሁሉን ነገር ትቶ ዓለምን ንቆ የወጣን መናኝም ያማልላል። ውበቷንና ቅብጥብጥ ገላዋን የሚያልፍ የለም። «ቂስንና ወታደርን ከወሲብ በቀር ሌላ ወጥመድ አይዛቸውም» ስትል ታስባለች። ማጥመጃዋ ገላዋ ነው።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አጥማጇ ሜሮዳ ጨለማ ልብሷ ነው። ቤቷም ጨለመለም ያለ ነው። ከኒውዮርክ ከተማ ውጪ በብዙ የአሜርካ ከተሞች ኑራለች። ሎስአንጀለስ፣ ቨርጂኒያ በሲ.አይ.ኤ ዋና መሥሪያ ቤት አቅራቢያ፣ ፊላደልፊያ፣ አክላሃማ፣ ዋሽንግተን....።

ዶክተር ሚራዥ ህይወቱን በሙሉ ተርከሳታል። ሲጻራን ቢረሳላት ደስታዋ ነበር። ግን አልሆነላትም። አማላይ ገላዋን መመልከት አልቻለም። ለብዙ አመታት የእሷ እንዲሆን

ለምናዋለች። እሱ ግን «እምቢ» አላት። «እምቢ» ሲላት ደግሞ የባሰ እየወደደችው መጣች። እምቢታው የተፈቃሪነት ዋጋውን እናረባት። እምቢታ የፍቅር ዋጋ ጭማሪ መሆኑ ገባት። ውስጧ ግን ተሰፋ ቆርጦ አያውቅም።

«ዛሬ ይለይለታል» ብላ ሻወር ቤቱን በርግዳ ትስገባ መለመላዋን ነበረች። እሱም መለመላውን እየታጠበ እያለ ተንደርድራ ስትገባ ሀፍረተ ሥጋውን በሁለት እጁ ደብቆ «አንቺ! ምን ነካሽ?» አላት በሩን ዘግታ ዕርቃኗን እየሳቀች ስትጠጋው ደንግጦ። እውነተኛ ፈገግታዋ የወሲብን ቆሌ ይጠራል። ያ የዘወትር ደረቅ ፈገግታዋ የት እንደደረሰ ሊገባው አልቻለም። ችርችም ካሉት ጥርሰጅ መሃከል ፍንጭድ ልዩ የደስታ በር መስለ ታየው። ገላዋ ለፍቅርም ለምርኮም ለበቀልም የተሳለ መሆኑን አወቀ። ፀጉሯ በአጭሩ እንደወንድ የተቆረጠና እንደኑግ ልጥልጥ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ውብ ነው። አጭሩ ላዛ ፀጉሯ ቅንብብ ካለው የራስ ቅሏ ጋር ውበት አላብሷታል። አይኖችዋ እንደዛሬ የወሲብን አድባር ሲጣሩ አይታቸው አያውቅም። ጡቶቿን ወደፊት አስጠግታ ፍትወቱን አማለለችው። ልቡ እስኪፈርጥ ዳንኪራ እየረገጠ ነው። ጫን ጫን መተንፈስ ጀመረ። ትንፋሹ ትጉልል እያለ ከአፉ ሲወጣ ሲጋራ እንደሳበ ሰው ጭሱ ፊቷን እየገረፈው ነው። የእሷንም የውስጧን ቃጠሎ የሚያሳብቀው ትንፋሽዋ እየተንቦለቦለ ከንፈሩን ገረፈው። ሻወር ቤቱ በሞቀ ትንፋሻቸው የፍል ውሃ ክፍል መሰለ። የሚጋረፍ ትንፋሽ። የሚለመጥጥ ጉም። ቅርድድ እንኮይ ከንፈር። አፏን ከፍታ አፉን ዘጋችው። ከንፈሩን ገመጠችው። መናገር አይችልም አሁን። ሌላ ቋንቋ። ምላሱን በምላሷ ቀለፈችው። ሁለቱ እጆቹም አንገቱን ዞረው የፍቅር አዙሪት አዞሩበት። ከግድግዳው ጋር አላጠቀችው። ሁሉም ነገር ከአምሮው ጠፋበት። ጡቶቿ ደረቱን ወጉት። ቀጭኑ ወገቧ ታጥፎ ሽንጡ ውስጥ ገብቷል። ጭኖቿ ፎከከ ብለው ተከፋፍተው አንድ ጭኑን መሃል አስገቡት። ቀንዱ ተቀስሮ ዳሌዋን የጐንዮሽ መውጋት ጀመረ።

«ትገ ይልሃል ወታደሮች ሊረባረቡብኝ ሲሉ ያስጣልከኝ፣» ዓይኑ ውስጥ ዓይኗን ተከላ።

«እናነ ያስጣልኩሽ የእኔን ፍትወት ለማርካት አይደለም።»

«ማደ.ለሀም አርካብኝ። የኔ ቆንጆ ነፍሴ እየቃተተችልህ ነው። ጭሮቼ መካከል የተነሳውን ቃጠሎ እንድታጠፋልኝ እፈልጋለሁ።»

«አልችልም። ገመናት ነው።»

«አይደለም። የኔ ቆንጆ ሲሆን አይችልም።»

«ሜሮዳ ወዳልሆነ ነገር ውስጥ እየከተትሽኝ ነው።»

«አይደለም ሚራ። ወደሆነ ነገር ነው። ወደ ፍቅር።» አለችው። እየተነፈሰች። እየተነፈሰ። እየቃተቱ። «እየጐዳሽኝ ነው ሚራዥ። እያቆሰልከኝ ነው። እያቃጠልከኝ። ብትገለኝ ይሻላል።»

«ፍቅር ሁሌም እንድ ነው:: ያለ ፍቅር ወሲብ ደግሞ...»

«ታዲያ እኔን አታፈቅረኝም? እኔ ይሄን ያህል እያፈቀርኩህ»

«እኔም ይህን ያህል የማፈቅራት አለቻ::»

«የለችም:: ሲጻራ የምትባል መንፈስ በእውኑ ዓለም ውስጥ የለችም:: የህልም አለምህ ውስጥ ነው እየዳከርክ ያለኸው:: ሲጻራ ቅዠት ናት::»

«ፍቅር ታዲያ እንዲህ በቀላሉ የሚፋቅ ነገር ነው? ...ብፍቀው እንኳ ስንጥቅጣቂው አይጠፋም:: ብጂጥጠው ይጂጥጠኛል:: ደግሞ እሷን መፋቅ አልችልም::.....»

«አህ!! .....ውጣልኝ በቃ!» አንባረቀችበት:: ቁርጧን አውቃ:: የሻወር ቤቱን በር ከውስጥ ወርውራ ዘጋችው:: ጣቶቿን ወደ ብልቷ አንሸራተተቻቸው:: .....

ከውጭ ፈጣን ትንፋሿ ይሰማዋል::

ከደቂቃዎች በኋላ ስታቃስት ሰማች:: ከዛም ውሃው «ሺ» ሲል ተሰማው:: እንደተንፈሰች አወቀ:: እንደቀዘቀዘች::

ወጥታ መኝታ ቤቷ ውስጥ አልጋዋ ላይ «ጂ» ብላ ተኛች:: «ጨካኝ!» ብላ:: «ደረቅ መነኩሴ!»

በዛው እንቅልፍ ወሰዳት::

፯

በነጋታው ጠዋት ካደረበት ሶፋ ላይ ተነስቶ ቁርስ ሠራ:: ሚሮዳ አንሶላዋ ስጥ ነበረች:: እስካሁን አልነቃችም:: መንቃት አትፈልግም ይሆናል:: ሚራዥ ወደ አልጋዋ ሄዶ ከአልጋው ጫፍ ተቀመጠና ፍዝዝ ብሎ አያት:: አንሶላ ውስጥ እስከ ውበቷ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ሰጥማለች:: ክብ ራሷና አጭር ጥቁር ወጉሯ ከአንሶላው ውጭ ናቸው:: ከናፍሯ ተንሽ ሸልቀቅ ብሎው ፍንጭቷን ያሳያሉ:: ከኋላዋ ዳሌዋ አንሶላውን ከፍ አድርጐ የተራራ ሰንሰለት አስመስሎታል:: ወገቧ ተሰብሮ አልጋው ውስጥ የገባ ይመስል ከተከመረው ዳሌዋ ውስጥ ገብቷል::የተኛች አትመስልም ታዲያ፡ ፎቶ ለመነሳት የተስተካከለች እንጂ:: ሚራዥ ባዲሱ ጊታሩ ለስለስ ያለ ዜማ እየተጫወተ አነቃት:: ዓይኗን በዝግታ ከፍታ አየችው:: ከሙሉ ነጭ ሱፍ ልብሱና ከጊታሩ ጋር በአምላክ ፊተ ምስጋና የሚያቀርብ መልአክ መስሎ ታያት:: ፊገግ ሲል ነጫጭ ጥርሶቹ ከለበሰው ጥርት ያለ ነጭልብስ ጋር ተመሳሰሉባት::

በጊታሩ የሚጫወተው ዜማ የፍቅር ዜማ መሆኑን ታውቃለች:: የምኒልክ ወሰናቸው መዚቃ::

«..... ፍቅር አያረጅም
ሙዚዲድ አያረጅም
ውበት ቢጠወልግ ሰውነት ቢጃጅም ...»

ደሞ አበሸቃት:: ይህ ዜማ ለእሷ አይደለም:: ለሲጻራ ነው:: «አያረጅም መስሎሀል!» አለችው:: «ብሸቅ:: ለዚህ ነው የቀሰቀስከኝ? ለሲጻራ የምታንቆረቁረውን ዜማ ልታሰማኝ?» ነጫጭ ጥርሶቹን ሸልቅቅ አድርጐ ሙዚቃውን ቀጠለ:: ፍቅር ምላሹ ንፉግ ነው:: ዝም ብሎ ፍቅር ነው ብላ ታምናለች:: ራስዋን ነቅንቃ ዝም አለችው::

«...ፍቅር አያረጅም
ሙዚዲድ አያረጅም
ውበት ቢጠወልግ ሰውነት ቢጃጅም .....»

«የኛ ሺክስፒር ደሞ ስለፍቅር ልታስተምረኝም ታስባለህ»

«ሺክስፒር ሲጻራን ያውቃታል» አላት:: «ፍቅርን እኔ ባየሁበት መነፅር ሺክስፒር አላየበትም:: ለንግሊዞች ጉረኞች ስለሆኑ አካብደውት እንጂ ከእሱ በኋላ የተነሱ ደራሲያን ስለማያላብድ ፍቅር ፅፈዋል:: ጉረኞች ቢሆኑም ግን እንግሊዞችን አደንቃቸዋለሁ:: የራሳቸውን ሰዎች ያሞካሻቸዋል:: እያጨበጨቡ ሰዎቻቸውን ያጀግኗቸዋል:: እንግሊዝ ታላቅ የምትሆነው በፖለቲከኛ ብቻ ሳይሆን በታላላቅ ሰዎቿ መሆኑን ስለሚያውቁ ለወጣቶች ሁሉ ገና

ምንም ላልሠሩት እጃቸው እስኪደማ ያጨበጭቡላቸዋል።ያ ካልሆነማ እንግሊዝ ያለነ ሼክስፒር ምንድን ናት፣ እኛ ደግሞ በተቃራኒው የኛ የሆኑትን ሰዎች እናሳድዳቸዋለን። ኢትዮጵያውያን ያድናቆት ችጋራሞች ነን። ሰዎቻችንን በሐሜትና በስድብ እናሸማቅቃቸዋለን። ወጣቶችን መቀበል ...አይሆንልንም። አዲስ ነገርን መቀበል አንሻም። አዲስ አሳቤና ሳይንስ ጠላታችን ይመስለናል። ለዚህም ኢትዮጵያውያን እስከ አሁን ከቅድመ አሪት ጀምረው በሚፈጩበት በድንጋይ ወፍጮ እየፈጩ ነው። ኢትዮጵያውያን ስለሚያቁት እንጂ ስለማያውቁት እንዲወራ አይፈልጉም። አንቺም እንደነሱ አትሁኝብኝ። ሲጻራን እንደምወዳት እንደማፈቅራት እነግርሽ ዘንድ ሼክስፒር መሆን አይጠበቅብኝም።»

«...ፍትር አያረጅም
መውደድ አያረጅም
ውበት ቢጠወልግ ሰውነት ቢጃጅም ...»

«ቆይ! ባትኖርስ፣» አለችው «ሞታ ቢሆንስ፣ እንዲህ ሆነህ ልትሞት ነው፣ »

«ይልቅ ተነሺ ተጣጠቢ ...ቁርስ ደርሷል።»

«ባሌ ብትሆን እንዴት ያምርብህ ነበር አንት መነኩሴ።» ካልጋዋ እመር ብላ ተነስታ ከጀርባው ወጣችበት። እስከሳሉኑ አልወረደችም። አዝሏት ጊታሩን እየመታ እስከ ባኞ ቤት ወሰዳት። ከጀርው ሥር ስማው ወረደች።

«ቁርስህ ይጣፍጣል መነኩሴው።»

«ገዳማዊ ነኞ! መንፈሴ ሰፎበት ከሆነስ፣» አላት ቁርሳቸውን እየበሉ እያለ። «ስለ ጎንጊዳ መሰወር ታውቂ ነበር፣»

«እም።»

«ለምን አልነገርሽኝም፣»

«የትና ለምን እንደተሰወረ አላውቅማ። ስለማላውቀው ነገር ማውራት ስለሚያስጠላኝ።»

«ማን ማን የሰወረው ይመስልሻል፣»

«ግምትም ያስጠላኞል። የሲ.አይ.ኤ እጅ እንደሌለበት ግን ሙሉ በሙሉ እግርጠኛ ነኝ።»

«ሌሎች የስለላ ድርጅቶችስ፣»

«ጎንጊዳን ታውቀው የለ፣»

«ለምን እንዲህ አልሽ፣»

«እሱ የራሱን ህይወት ገዛ ብሎ የሚኖር ሰው ነው። በምንም አይነት ነገር ውስጥ እጁን አያስገባም። ስለዚህ ማንኛውም የስለላ ድርጅት ከጎንጊዳ ጋር የሚያገናኘው ነገር አይኖርም።»

«እና የት ደረሰ ልበል፣»

«እኔ ምን አውቄ። ምናልባት ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ከሆነስ፣ ዜናው የሚለው 'የደረሰበት ጠፋ' ነው። ደግሞ.....በየትኛውም

የአሜሪካ አውሮፕላን አልተጓዘም። ምናልባት ከንፍ አውጥቶ ይሆናል እንግዲህ።»

«አትቀልጂ።»

«ከመነኩሴ ጋር የዋለ ሌላ ምን ይመኛል፣ እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት ስድስት ክንፍ አብቅሎ ለመብረር ከመመኘት ሌላ። መጭ። ቀልዴን አይደለም። ካንተ ጋር መዋል ሌላ ምን ትርፍ አለው፣ ዕድቅንና መንግስተ ሰማያትን ከመመኘት ሌላ ...ያም ሆነ ይህ ዶ/ር ጎርጊዳ ራስ ምታቴ አይደለም። አንተ ነህ ራስ ምታት የሆንከብኝ። እውነትም ሚራኛ! የማትጨበጥ ሞገድ።» ጠም ያልበቀለበት ጉንጩን መርጣ ስማው ልትታጠብ ሄደች። እሱም የበለጠበትን ሳህን አንስቶ ተከትሏት ሄደና ታጥበው ሶፋ ላይ ተቀመጡ።

ሜሮዳ ላኘቶኝ ከምጊሙተሯን ሞኗ ላይ አድርጋ ቁልፎቹን እየነካካች እያለ ዶ/ር ሚራኛ ባለፈው የደረሰውን ፖስታ አያገላበጠ ማየት ጀመረ።

ፖስታው ላይ የተመታው ማህተም ከባህርዳር ፖስታ ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ መምጣቱን ከመመልከቱ ውጪ የላኪ አድራሻ የለበትም።

«ደሞ የደረሰኝ ፖስታ አስገርሞኛል።» አላት።

«ምኑ ነው ያስገረመህ፣» አለችው ወደሱ ተንጅታ እየተጠጋች።

«ውስጡ ምን እንዳለ ታውቂያለሽ፣»

«ደብዳቤ ነዋ።»

«አይደለም። ባዶ ወረቀት። ይኸውልሽማ አይው።»

የደብዳቤውን ፖስታ ተቀብላ እውስጡ ያለውን ባዶ ልሙጥ ወረቀት ለረጅም ጊዜ ዓይኖቿን ተክለችበት። ያላንዳች ነገር የተላከ ባዶ ወረቀት አልመሰላትም። እንደ ሲ.አይ.ኤ ወኪልነቷ እንደዚህ ያሉ ምስጢራዊ ነገሮችን መጐርጐር አንዱ ሥራዋ ነው። መጐርጐር ጀመረች። ባዶውን ወረቀት። «እናያለን።» ብላ ወደ ጓዳ ሄደችና ከብ ሞልፋ የሚመስል መሰታወት ይዛ ተመለሰች።

በክቡ ሞልፋ መሰል አጉሊ መስታወት ባዶውን ወረቀት ስታየው በሐምራዊ ቀለም የተሣፈ ነገር አስተዋለች።

«ሚራኛ» አለች ዕሑፉን እያነበበች። «ና ተመልከት።» ሚራኛም በመስታወቱ ዕሑፉን ተመለከተው። «እንዳንድ ምስጢራዊ ነገሮች እንደዚህ እንደሚሄፉ አታውቅም በሥውር የብዕር ቀለም፣» አለችው። እሷም አብራ ከቡ መስታወት ላይ አፍጣ።

ዕሑፉ «የጊታሩን የድምፅ ሳጥን ክፈተው» ይላል።

ሽማግሌው ሰውዬ የሰጡትን ጊታር አምጥቶ የድምፅ ሳጥኑን ተመለከተው። ላዩ ላይ ተካፋች ነገር እንዳለው ተመለከተ። በጊታሩ የድምፅ ሳጥን ላይ ቁልፍ የሚመስሉት ነገሮች ለጊታሩ ውበት ሶተተከለ ጌጦች ነበር የመሰለት። ነገር ግን ቁልፎቹ በላያቸው

ቁጥር እንደተቀረፀባቸው ተመለከተ:: የትኛውንም ቁልፍ ቢጫን ሊከፈትለት አልቻለም:: ለረጅም ጊዜ ተያዩ:: እንደገና ባዶውን ደብዳቤ በክቡ እጁ መስታወት አሰሱት:: በጀርባው በኩል ፮፪፫ የሚሉ ቁጥሮች በሐምራዊው ሥውር ቀለም ተፅፈው አገኙ:: ሚራኽ እነዚህ ቁጥሮች የተቀረፀባቸውን ቁልፎች ተጫናቸው:: ድስት....አራት....ሦስት....ስምንት....:: ቁልፎቹን ሲጫናቸው የጊታሩ የድምፅ ሳጥን ተንሸራትቶ ተከፈተ::

ውስጡ በአልሙኒየም መሰል አብረቅራቂ ቀላል ንጣፍ የተለበጠ ነው:: ከአብረቅራቂው ልባጥ በታችኛው ክፍል የተጠቀለለ የብራና ወረቀት ተያይዟል:: ስቦ አወጣውና ጥቅሉን ተረተረው:: ከውስጡ ሌላ ብጣቂ ወረቀት ወደቀ:: አንስቶ አነበበው:: *'ጥብቅ ምስጢር ይላል ከላይ:: ዝቅ ብሎ ደግሞ ጥቂት የአማርኛ ቃላት ሰፍረዋል::*

«ጥቅሉን ተጠቀመው:: ሀገርህ ትፈልግሀለች:: ኢትዮጵያ እንደገባህ ከባህርዳር ከተማ አባይ ድልድይ ማዶ በገብርኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ መካነ መቃብር የአባ ሲርጋጋን መቃብር ፈልገህ ካገኘህ በኋላ ቆፍረው:: ቀጣዩ መልእክት መቃብሩ ውስጥ ተቀምጠልሃል:: ይህንን መቃብር ስትከፍት ማንም እንዳያይህ ተጠንቀቅ» ይላል ብጣቂው ፅሑፍ::

ፈጥኖ የብራና ጥቅሉን ተረተረው:: የቆየና የነተበ የብራና ፅሑፍ ነው:: በቁም ፅሁፍ በጥንቃቄ የብራናው ወረቀት ላይ የሰፈረውን ነገር ሊያይ ግራ ተጋባ:: ይህ ሁሉ ጥንቃቄ የተደረገለትና በጥቅል ብራና የተፃፈው አንድ የሚያውቀው ነገር ነው:: እንዲያውም ይህ ጽሁፍ የተወሰደው በህይወት ዘመኑ ከሰበሰባቸው መጻሕፍት ከአንዱ ውስጥ ነው:: ከኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ከሉሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ግጥሞች ውስጥ ኢትዮጵያዊነት ውስጡ እንደ ነበልባል የሚጋረፍበት ግጥም ውስጥ ምን ምስጢር ቢኖር ነው በዚህ በጊታር የድምፅ ሳጥን ውስጥ በተራቀቀ ምስጢር የተላከለት? በጉጉት «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» የሚለውንና በጊታሩ ውስጥ በምስጢር ከማያውቀው ቦታ የተላከለትን ግጥም ደጋግሞ አነበበው::

ከግጥሙ ሥር እድሜ ልኩን ምስጢር ሆኖበት የኖረውና በ'ቶ' ቅርፅ የተሠራው ባለጉጥ መስቀል ተሰሏል:: በባለጉጡ መስቀል ላይም ግራ ሲያጋቡት የኖሩት ቃላትና ቁጥሮች ተቀርፀውበታል:: 54_{2} 9_{5} 10_{6} 29_{23} 77_{5} 30_{456} 52_{7} 33_{2} ፬፬፬ 97_{5} .. አርያ ኢትዮጵያ 98_{123} 9_{6} 10_{67} 40_{567} 88_{123456} ...፬፬፬...መራራ ክንፍ....ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ....ቀጠሮ ቃል.... ፬፬፬.... ዴርቶጋዳ::

«የፈጣሪ ያለህ!» አለ ሚራኽ:: «ምን ይመስልሻል ሜሮዳ?»

ፅሑፉን አንብቦ እንደጨረሰ ሜሮዳን አያት እሷም ጨርሳ እያየችው ነበር:: ለረጅም ደቂቃ ቢሰሳብ ተውጠው ከተያዩ በኋላ «ይህንን ነገር የላኩት በጣም የሚያውቁህ ሰዎች መሆን አለባቸው::»

አለችው:: «ለምን መሰለህ? የላኩልህን ጊታር አስብ:: ጊታር እንደምትወድ ያውቃሉ ማለት ነው:: ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚያጠምዱህ በምትወደው ነገር ውስጥ ነው:: እንደገና ግጥም እንደምትወድ ስለሚያውቁ በዚህ ግጥም ሊያጠምዱህ ፈለጉ:: ስለዚህ ይህን ነገር የሚያደርጉት ሰዎች እጅግ በቅርብ አንተነትህን ጠ ልቀው የሚያውቁ ሰዎች ስለመሆናቸው አልጠራጠርም:: እነማን ይመስሉሃል?»

«በአለም ላይ የማውቃቸው ሰዎች እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው:: በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች:: ስማቸውን ልጥራልሽ ለምሳሌ..»

«እስኪ በል ...»

«አንደኛ ሲጻራ ...»

አቋረጠችው:: «ብሽቅ! ብሽቅ ነገር ነህ:: ከሲጻራ በላይ እኔ አሳውቅህም አንተን? እሷን የምታውቃት መቼ ነው? ስንት ዘመን ተቆጥሯል ከዛ ወዲህ? አንተን ስትተድስ እንጂ ጊታር ስትመታ ታውቅሃለች? አንተን ቅኔ ማህሌት ውስጥ ስትቀኝ እንጂ ዘመናዊ የአማርኛ ግጥም ስታነበንብ ታውቅሃለች? ዝም ብለህ ...ኤጭ!» ተነስታ ሄደች:: «ካንተ አፍ ሁለተኛ ሲጻራ የሚል ቃል ሲወጣ መስማት እንደማልፈልግ ነግሬሀ ነበር:: ዘጊ! አዘማም መንፈስ ናት እሷ! እርግጠኛ ነኝ ፍቅር የሚለካ የሚሰፈር ቢሆን ከእሷ በላይ እኔ እንደማፈቅርህ ይረጋገጥ ነበር:: አዘማ ናት! አንተንም አዘማም አድርጋሃለች::» እያግተመተመች ወደ መኝታ ክፍሏ ስትሔድ ተከተላት::

«አየሽ ሜሮዳ ...እኔ የምፈልጋትን ያህል እየፈለገችኝ እንደሆነ አልጠራጠርም:: ትወደኛለች:: እኔም እወዳታለሁ:: ታፍና ተወሰደች:: ሰዎች ለያዩን:: አቅጣጫችንና የህይወት መስመሮቻችን ተለያዩ:: በቃ እስቲ ምንድን ነው ሐጢአቷ? እኔስ ፍቅሬን ስፈልጋት ብኖር የተሳሳትኩት የት ላይ ነው? ምናልባት ያች ሴት አንቺ ብትሆኝ ኖሮም ስፈልግሽ እኖር ነበር::» አሳዘነችው:: ግን ደግሞ ልቡ ወደ ሲጻራ ይጠመዝዘዋል::

«አየህ ...በልጅነትህ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ካሉት ተራሮች ላይ ከወደቀው አድማስ በቀር የሚታይህ አድማስ የለም ነበር:: ከጣና ሐይቅ በላይም ሐይቅ ያለ አይመስልህም ነበር:: ግን እንደዛ ሆኖ አሳገኘኸውም በህይወትህ የበለጠ አድማስና የበለጠ ሀይቅም አይተህል:: በታስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ ጊታር ስትጫወትም ነበር:: ሁሌም በተራመድክ ቁጥር አድማስህ ይሰፋል:: ከሚታዩህ ተራራዎች ላይ ስትቆም ሌሎች ብዙ ተራሮች ይታዩሀል:: የጋረዱህን ተራሮች በቆምክባቸው ቁጥር የበለጡ ተራሮችን ታያለህ:: ሲጻራ መጀመሪያ የጋረደችህ ተራራ ነች:: አሁን ቆመህባት ልታልፍ ይገባል:: ከአድማስህ መስፋት ካልፈለግህ ቢተር ሌላኛዋ አድማስህ እኔ ነኝ:: አሁን እኔን ተመልከተኝ ቢቃ:: ምናልባት ልትወደኝም እኮ ትችላለህ:: ግን አላስገድድህም:: እኔ ግን እሺ ብትለኝም እምቢ

ብትለኝም እወድሃለሁ::» ዓይኖቿ እንባ አንቆረዘዙ:: ማነፍረቅ አልፈለገችም:: ሀሳቧን ወደ ሌላ ለመመለስ «ጥንጊዳ ነክቶት የሚያውቅ ዕቃ አለህ?» አለችው:: ቀልቧን ወደ መጀመሪያው ነገር ለመመለስ እየታገለች::

«አዎ» አላት:: «እንዲያውም ከወራት በፊት ደጋግሞ ሲያነበው የነበረውንና 'እሳት ወይ አበባ' የሚለውን የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህንን መፅሐፍ ላምጣልሽ::»

እሳት ወይ አበባ የሚለው መፅሐፍ ውስጥ ጨረር በሚተፋ ብዕር መስል መሳሪያ ገፆቹን ስትመረምር ከቆየች በኋላ 'ሰቆቃወ ጴጥሮስ' የሚለው ግጥም ከተፃፈባቸው ገፆች ላይ የጥንጊዳን አሻራዎች አገኘቻቸው:: የተላከውን ባዶ ደብዳቤም በዛው መሳሪያ አሰለችው:: ተመሳሳዩን የጥንጊዳን አሻራ አየችና «በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጥንጊዳም አለበት::» አለችው::

«ምንድን ነው እየሆነ ያለው?» ራሱንም እሷንም ጠየቀ::

«እኔ ምን አውቄ::» አለች ሜሮዳ:: «ብቻ ግን አንድ ምስጢራዊ ነገር እንዳለ እገምታለሁ::»

«ምን አይነት ምስጢር?» አለ ሚራዥ:: «በአፋጣኝ ኢንጂነር ሻጊዝን ማግኘት አለብኝ::» ጊታሩን መልሶ እንዳገኘው እየገባጠመ:: ቁልፎቹን መልሶ በተሰጡት ቁጥሮች ሲጫናቸው የጊታሩ የድምፅ ሳጥን ተንሸራቶ ተዘጋ:: «ሻጊዝን ማግኘት አለብኝ:: ቢያንስ አንድ ጊዜ ሳላገኘው ወደ ኢትዮጵያ አልሄድም::» አለ የጊታሩን ክሮች በጣቱ እየነካካ::

«ጊታር ልትጫወትለት ነው?» አለችው:: «ሞኝ መነኩሴ ነህ ሚራዥ:: ቀሽም ነገር ነህ::»

«እንዴት?»

«እሱን አልፋ፡ ውሾች እንደሚከተሉት አታውቅም? መሞት ትፈልጋለህ? እንደገና ከሲ.አይ.ኤ ጋር መጋፈጥ ትፈልጋለህ?»

«እንደምንም ማግኘት አለብኝ::» ብሎ ተንቀሳቃሽ ስልኩን አንስቶ የኢንጂነር ሻጊዝን የስልክ ቁጥሮች ሲጫን ከእጁ ላይ መነጨቀችው:: «ስልክህ መጠለፉን እንኳ አታውቅም» አለችው:: «የምታሳዝን ፍጡር::»

እጁን ይዛው ወደ መኝታ ቤት ወሰደችውና በሌላ ስልክ እንዲደውልለት ሰጠችው:: ደውሎ ኒውዮርክ ከተባበሩት መንግስታት ህንፃ አቅራቢያ በሚገኝ ባንድ ረጅም ህንፃ ላይ እንዲገናኙ ቀጠረው:: ኢንጂነር ሻጊዝም ሊያገኘው እንደሚፈልግ በጥድፊያ ነበር የነገረው::

፲

ኒውዮርክ÷አሜሪካ

ከራሱ በላይ ከደፋው ጥቁር ሞላላ ባርኔጣና ከነጭ ሱቶ ጋር ያነገተው ጊታር ተጻምሮ ምርጥ የሮክ ሙዚቃ አቀንቃኝ አስመስሎታል:: ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር ወደ ተቀጣጠሩበት ሰማይ ጠ ቀስ ህንፃ በአሳንሰሩ ወጥቶ ሲደርስ ሳይንቲስቱን ቀድሞት ነበር::

ከአስራ ሁለተኛው ፎቅ ላይ ሆኖ ቁልቁል ሲመለከት የጥቁሯ አውቶሞቢል በሮች በሁለቱም በኩል ተከፍተው ግምብ ግምብ የሚያካክሉ ጋርዶች ሲወጡ አየ:: አካባቢውን ተገላምጠው ከቃኙ በኋላ ሌላ ቀጠን ያለ ሰው ወጥቶ የፊተኛውን በር ከፈተ:: ሙሉ ጥቁር ሱፍ የለበሰ ሰው ወጥቶ የተጣመመ ከረቫቱን እያስተካከለ ወደ ፎቁ ሽቅብ አንጋጠ ተመለከተ:: በጥቁር መደብ ላይ ስላሽ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መስመሮች ያረፈበት ከረቫቱን አይቶት ያውቃል ሚራዥ:: ከላይ ሆኖ ቁልቁል ሲመለከተው መሃል አናቱ ላይ የሀብታም አውድማ የሚያህል በራው ክብ ራሱ ላይ ታየው:: ከግንባሩም በኩል በሁለት አቅጣጫ የሸሸው በራው መሀል ላይ ሾጠጥ ብሎ የገባውን ስስ ፀጉሩን የባህር ወሽመጥ አስመስሎታል:: በጆሮዎቹና በማጅራቱ በኩል የቀረው ጥቁር ፀጉሩ በራውን ከቦ ጋሜ የተከረከመች ልጃገረድ እንጂ የ55 ዓመት ጉልማሳ አያስመስለውም::

ዶ/ር ሚራዥ ቁልቁል የሚመለከተው ሰው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ መሆኑን ለማወቅ አፍታ አልፈጀበትም:: ጋርዶቹ አውቶሞቢሏ ውስጥ ተመልሰው ከገቡ በኋላ በዝግታ ተራምዶ ወደ ህንፃው ገባ:: ከአይኑ እስኪጠፋ ተከተለውና ጊታሩን አውልቆ ወንበር ይዞ ተቀመጠ::

ኢንጂነር ሻጊዝና ዶክተር ሚራዥ ተገናኝተው መነጋገር ከመጀመራቸው አራት መኪናዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተከታትለው መጥተው ከሰማይ ጠቀሱ ህንፃ ስር ባለው መኪና ማቆሚያ ቆሙ:: ከውስጣቸው የወጣ ሰው ግን አልነበረም::

ሚራዥን ስትከታተለው የነበረችው ነጭዋ ካዲላክ መኪና ከሁሉም ቀድማ ነበር የደረሰችው:: ነጫጭን ካዲላክ ሲያይ በድጋሚ ከሲ.አይ.ኤ ጋር መጋፈጡን አረጋግጦ ምን ማድረግ እንዳለበት በውስጡ እያውጠነጠነ ነበር ሚራዥ::

ሁሉቱ ዕውቅ የሞላድ አባሎች ሲጓራና ዶክተር አናንያ፣ከጥቁሩ ቢ.ኤም.ደብልዩ መኪና ውስጥ ተቀምጠው ሰማይ ጠቀሱን ህንጻ በዓይነ ቁራኛ እየተከታተሉት ነው:: የናሳውን ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝን እያንዳንዱዋን እንቅስቃሴ በስውር እየተከታተሉ ለበላዮቻቸው ሪፖርት ሲያቀርቡ ቆይተዋል:: ሞላድ

የኢንጂነሩን ጉዳይ ብቻ በሚመለከተው ልዩ ስብሰባው ላይ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ኦፐሬሽኑን የሚመሩት ሲጳራና ዶ/ር አናንያ በተገኘ ማንኛውም ክፍተት ኢንጂነሩን በስውር አፍነው ይዘውት ወደ እስራኤል ለመብረር ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል። ከሁዋላቸው ማንኛውንም ጥሪ የሚጠባበቁ የሞሳድ ኮማንዶዎች በተጠንቀቅ ላይ ናቸው። ታዲያ ኢንጂነሩን አፍነው ወደ እስራኤል ሲወስዱ ሰው ቀርቶ ሰማይና ምድርም ማወቅ እንደሌለባቸው ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል። ከኢትዮጵያ በቀር ሁሉም የአለማችን ሀገራት ዓይናቸውን የጣሉበት ይህን ታላቅ ሳይንቲስት አፍኖ መውሰድ ግመል ስርቆ አጎንብሶ የመሄድ ያህል ከባድ እንደሆነ ግን አላጡትም።

ሲጳራና ዶ/ር አናንያ ክፍተቱን ከመጠበቅ በተጓዳኝ ሳይንቲስቱ በድብቅ የሚያደርጋቸውን ምስጢራዊ ድርድሮች በመከታተልም ሪፖርት ያቀርባሉ። እስከ አሁን ከተለያዩ የሰለጠኑ ሀገራት ዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በድብቅ መግዛቱን ደርሰውበታል። በተለያዩ ሀገራት የህክምና፣ የምህንድስና እና ወታደራዊ መሳሪያዎችን ሳይቀር መግዛቱን እንደ ደረሱበት ሲጳራና ዶ/ር አናንያ ለሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ሪፖርት አድርገዋል። እስደናቂው ነገር ግን እስከአሁን የገዛቸውን የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች የት እንዳደረሳቸው አለመታወቁ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ሀገራት ከተሰወሩት ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶች ጋር ግንኙነት እንዳለውም አረጋግጠዋል። እስካሁን ያልታወቀ ነገር ቢኖር ሳይንቲስቶቹን የት እንዳደረሳቸው አለመታወቁ ነው።

ሲጳራና አናንያ ሳይንቲስቱ የሚያደርጋቸውን ድርድሮች ከማነፍነፍ በተጓዳኝ እንደ አደገኛነቱና እንደ አስፈላጊነቱ ከእርሱ ጋር ድርድር በሚያደርጉት ላይ እርምጃ እንዲወስዱም ታዘዋል። በተለይ ፀረ እስራኤል አቋም ካላቸው ሀገሮች ጋር ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ምስጢር እንዳያቀብል ከእርሱ ጋር ድርድር ያደረጉ ሰዎች በስውር ይወገዳሉ። ሲጳራና አናንያ ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር የተቀመጠው ባለጊታር ማንነት እስካሁን አልተገለጠላቸውም። የዚህን ሰው ማንነት ለመለየት ከፍቁ እስኪወርዱ መጠበቅ ትክክለኛው አማራጭ መሆኑን ሲጳራ አምናበታለች።

በነገጬ ካዲላክ መኪና ውስጥ ሲ.አይ.ኤዎች፣ በጥቁሩ ቢ.ኤም ደብልዩ መኪና ውስጥ ሞሳዶች እንዳሉ ሁሉ በቀይዋ ፊያት መኪና ውስጥም የሩሲያ ሰላዮች ተቀምጠው ወደፎቁ አንጋጠዋል። ኬጂቢ የራሺያና የህልውናዋ ዋልታ በነበረበት ዘመን ራሺያ ከአሜሪካ ጋር የምታደርገውን የቴክኖሎጂ እሽቅድምድም ከፊት ሆኖ ራሺያን ለመምራት ውስብስብ የስለላ መዋቅሩን በመላው አለም ሲዘረጋ የአሜሪካን የህዋ ምርምር ተቋም የናሳን ምስጢሮች ለመመንተፍና የአሜሪካን ሁለገብ የቴክኖሎጂ ደረጃ ለማጥናት

አደገኛ ሰላዮችን በገፍ አሜሪካ ውስጥ ካሰማራ ዘመናት ተቆጥረዋል። በደቡብ ካሊፎርኒያ በሚገኘው የአየር ኃይል ተቋም ወደ አየር የሚወነጨፈው የአሜሪካ «ሳሞስ» ሳተላይት በውስጡ ባረገዛቸው ረቂቅ መሳሪያዎች እየታገዘ የራዳሮችን፣ የሬዲዮችን፣ የመገናኛ አውታሮችን፣.....የኢራን፣ የቻይናና የሶቭየት ሳይንቲስቶች የሚያከናውኗቸውን የኒውክለርና የጠፈር ምርምሮችን እንደሚያነፈንፍ እንኳ ሩሲያ አለም ያወቀው ነው። በ1970 ዓ.ም ብቻ የአሜሪካ የስለላ ሳተላይቶች በሶቭየት ህብረት ላይ አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ቀናት ኡደት ማድረጋቸውን ሩሲያውያኖች ያውቃሉ። ሶቭየቶችም በበኩላቸው ሶስት ጊዜ እጥፍ የሆኑ ሰላይ ሳተላይቶች በአሜርካ ላይ ብቻ ኡደት እንዲያደርጉ ወንጭፈዋል። በየቀኑ የአሜርካን የህዝብ ቁጥር ሳይቀር ቆጥረው የሚያስረክቡ የረቀቁ ሳተላይቶች በአሜሪካ ላይ ኡደት ሲያደርጉ ሲውሉ የሶቭየት እግረኛ ሰላዮች ደግሞ በድብቅ ገብተው የአሜሪካን የቴክኖሎጂ ምስጢሮች ይቃርማሉ። የሬድዮ መልእክቶች ተጠልፈው ይደመጣሉ፣ በሐይማኖት፣ በንግድ በልዩ ልዩ የሽፋን ሥራዎች የሰረጉ ሰላዮች የሚንቁት መረጃ አይኖርም። እንኳንስ ከናሳው ሳይንቲስት ከሻጊዝ ይቅርና ከአንድ የናሳ የፅዳት ሠራተኛ የሚያገኙት መረጃ ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው። ለዚህም ሲባል ኬጂቢ ጠፈርን የገዙ ከሚባሉት እውቅ ሳይንቲስቶች ግንባር ቀደም በሚባለው በኢንጂነር ሻጊዝ ዙሪያ አደገኛ ሰላዮቹ እንዲያንጎበቡ ትዕዛዝ ካስተላለፈ ቆይቷል። ምክንያታቸውም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የጦርነት ሥልቶችና ጦርነቶች የሚደረጉት በኤሌክትሮኒክስና በመረጃ መሳሪያ በሚቀነባበሩ ዘዴዎች ነው። መሳሪያዎችን ከመግዛት ይልቅ መሥራቱ የበለጠ ፍቱን መድሃኒት ነው። ተሠርተው የሚገዙት መሳሪያዎች፣ የሠሪዎችንና የሻጮቹን አሻጥሮችንም አብረው ስለ ሚያስታቅፉ። ሆኖም በአሜሪካና በሩሲያ መካከል የሚደረገው የቴክኖሎጂ ፉክክር የህልውና ጉዳይ እንጂ የጉራ ብቻ አይደለም። የሩሲያን ራዳር ሊዘጋ የሚችል ጥበብ አሜሪካውያን በፈለሰፉ ማግስት ሩሲያውንም የበለጠ ተራምደው ራዳሮቻቸውን ሊያጭበረብርና ሊዘጋ የሚችለው መሳሪያ ተቃዋሚ የሆነ ጥበብ ፍፈለሰፉት በዚህ የረቀቀ የኑለላ መዋቅራቸው ነው። በሳይንስና በሳይንቲስቶች ላይ በማንገርበብ። በሩሲያ አዳኖች ከሚታደኑ የአለማችን የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሊቃውንት ውስጥ አንዱና የጊዜው ሰው ደግሞ ኢንጂነር ሻጊዝ ነው። ሆኖም በቀይዋ ፊያት መኪና ውስጥ ተቀምጠው ወደ ሰማይ ጠቀሱ ህንፃ የሚያንጋጥጡት የሩሲያ የቀድሞው ኬጂቢ ርዝራዦች ህንፃው ላይ ካንድ ጊታር ከያዘ ሰው ጋር የሚነጋገረውን ሳይንቲስት ለማጥመድ ነው።

ከቀይዋ ፊያት ጀርባ ከቆመችው ሰማያዊ አውቶሞቢል ውስጥ ደግሞ የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች ስለዚህ የሀገራቸው ልጅ

እያወሩ ነው። ስለ ሐበሻው ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ። እያወሩ ያሉት ግን ሰውየውን ወደሀገራቸው መስደው የቴክኖሎጂ እውቀቱን በዝብዘው ሀገራቸውን የረቀቀ የቴክኖሎጂ ባለቤት ስለማድረግ አይደለም። ግንባሩን በጥይት ወንፊት ስለ ማድረግ እንጂ። በዚህ ሰው ሳይ ግድያ መፈፀማቸው በግልፅ ቢታወቅ ሀገር ውስጥ የሚቀሰቀሰውን ቁጣና አመፅ በመፍራት ሰውየውን የማስወገዱ ሁኔታ ማንም ሳያውቅ መሆን እንዳለበት ወስነዋል። በመሆኑም ይህ ጉዳይ በጥቂት ሰዎች እጅ እንጂ በአንዳንድ ሀገር ወዳድ ባለስልጣናት እጅ እንኳ አልገባም። ይህ ሰው እንኳንስ ጭንቅላቱና ሊቅነቱ አስከሬኑ እንኳ ኢትዮጵያን አይረግጣትም ሲሉም ዝተዋል። ይህ ግዳጅ የተሰጣቸው ታማኝ የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች ስለዚህ ሳይንቲስት እያወሩ ሽቅብ አንጋጠው ከሰማይ ጠቀሱ ሀንፃ ባስራ ሁለተኛው ፎቅ ላይ ዓይናቸውን ተክለዋል። ቀደሞ ሲከታተሉው የነበረው ደህንነት ሰነዱን ሁሉ አቃጥሎ ራሱን ካጠፋ ወዲህ እነዚህ ሁለት ደህንነቶች ስራቸውን እንደገና አሀዱ ብለው ለመጀመር ተገደዋል።

«ይህ ሰው ከአርበኞች ግንባር ጋር ከሚተባበር ለአባት አርበኞች ምርኩዝ መግዣ ቢልክላቸው ይበጀው ነበር» አለ አንደኛው ፈገግ ብሎ።

«እስኪ እናያለን ቦንጋን ሲረግጣት?» አለ ሁለተኛው። ሲጋራውን እያቀጣጠለ።

ዶ/ር ሚራኾር ከተቀመጡበት ሀንፃ ሥር መኪና ማቆሚያው ውስጥ ከቆመት መኪናዎች ውስጥ የወጣ ሰው ባለመኖሩ ተገርሟል። መኪናዎቹ ሰው አልባ ተሽከርካሪዎች መሰሉት። መስታወቶቻቸው ወደ ውስጥ ስለማያሳይ ውስጥ ያሉትን ማየት አልቻለም። ነጪን ካዲላክ ግን አውቋታል። ሲአይኤዎች ተቀምጠው እንደሚከታተሏቸው ማወቁን ለኢንጂነር ሻጊዝ ነግሮታል። አንጂነር ሻጊዝም «እኔ ለምጃቸዋለሁ።.....ሁሌም ይከተሉኛል።» ሲለው ሜሮዳ የነገረችው ትዝ አለው። «እሱን ብዙ ውሾች ይከተሉታል።»

ኢንጂነር ሻጊዝ በእሱ ምክንያት ከሥራ በመፈናቀሉ ሲአይኤዎችም ባደረጉበት የግድያ ሙከራ ማዘኑን ገልያለታል ለዶክተር ሚራኾር። የንቅሳት ባለሙያው ከዜጂቢዎች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ሜሮዳ የነገረችውን ሲነግረው ሻጊዝ ብዙም አልተደነቀም። ብዙ የሚከታተሉት ሰዎች እንዳሉ ነገረው። የሚመጡበት ሁኔታና መንገድ ግን ሁል ጊዜም ይለዋወጥበታል።

ዶ/ር ሚራኾር በጊታሩ የድምፅ ሳጥን ውስጥ ያገኘውን «ዴርቶጋዳ» ስለሚለው ንቅሳታቸው ፍንጭ ማግኘቱን በደፈናው ሲነግረው ፍንጩን እንዴት እንዳገኘ አልጠየቀውም ኢንጂነር ሻጊዝ። ሻጊዝ በንቅሳቱ ምስጢር ላይ ምንም አይነት ጥያቄ ባለማንሳቱ ሚራኾር ግራ ተጋብቷል። ምናልባት ምስጢሩን ደርሰበት

ይሆን? ሲል አሰቦ «ስለ ዴርቶጋዳ የደረስክበት ነጥብ አለ ወይ?» ብሎ ሊጠይቀው ሲቃጣ ከተቀመጠበት ፎቅ ወዲያ ማዶ ስለሚታየው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህንፃ አሻግሮ እየተመለከተ ሌላ ወሬ ቀጠለ።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አደባባይ በአንድ ግንብ ላይ «ሰይፋቸውን ማረሻ፣ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ፣ ህዝብም በህዝብ ላይ ሰይፍ አያነሳም፣ ሰልፍም ከእንግዲህ ወዲህ አይማሩም» በሚል ስለተፃፈ ጥቅስ ኢንጂነር ሻጊዝ ወሬ መዘ ማውራት ጀመሩ።

«ይህ ጥቅስ ደስ አይልም?» አለ ሻጊዝ በግንቡ ላይ የተቀረፀውን ጥቅስ ለሚራኾር ከነገረው በኋላ።

«እጅግ ደስ ይላል እንጂ!» አለው ሚራኾርም።

«ከጥቅሱ በታች በ1975 ኢሳይያስ የሚለው ስም እንዲቀረፅ ሳይደረግ በፊት ለአስርት አመታት ያህል የጥቅሱ ምንጭ ሳይገለፅ ቆይቷል» አለ ሻጊዝ። «የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓላማ ዓለም አቀፍ ሰላም ማስፈን እንደሆነ ለመስበክ ጥቅሱን ያመነጨበት በ1945 ድርጅቱን የመሰረቱት ሰዎች ናቸው ይባላል። ግን ጥቅሱና ድርጅቱ አይጣጣሙም።»

«እንዴት?» አለ ሚራኾር እሱም አሻግሮ ወደተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህንፃ እየተመለከተ።

«እስኪ ይግረምህ። ማነው ሰይፉን ማረሻ ለማድረግ የሚቀጠቅጥ? ዓለም በጥይት ቋንቋ ብቻ መግባባት በሚችሉ ፖለቲከኞች ተሞልታ ማረሻቸውን ሰይፍ ለማድረግ በሚቀጠቅጡበት ወቅት ማንን ለማቄል ነው ሰይፋችሁን ማረሻ አድርጉ ብለው የሚሰብኩት? አየህ....ብዙዎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን እንደ በጌ አድራጊ የኃይማኖት ድርጅት ይቆጥሩታል። ግን የጥቂቶች ክንድ ነው። እንዲያውም የመንግስታት አምባገነንነት መሰረቱና አርአያቸው ይኸው ድርጅት ነው። የአምስት አገራት የበላይነት ብቻ የሚንፀባረቅበት ድርጅት። ዋነኛ ሽሪኮቹ ደግሞ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ናቸው። ወደኛ ነገር ስንመለስ.....ወንድም ሚራኾር ብዙ ነገሮች ያሳስቡኛል» አለው በደቃቃ የንስር ዓይኖቹ እየተመለከተው።

«ምን አይነት ነገሮች?» አለው ሚራኾር ለመስማት እየተመቻቸ።

«በጥቂቱ ልንገርህ። የሚከነክነኝን። አንተ ስለእኔ የምታውቀው አለህ። በመገናኛ ብዙሃን ወይም በስሚ ስሚ። ስለ እኔ ማወቅህና አለማወቅህ አያሳስበኝም። እኔ አንተን በማወቄ ግን እኮራለሁ። ምክንያቱም ውስጥህ ቅንነትክን አይቻለሁ። ከዚህ የበለጠ ነገር የለም።» ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ ለመሳብ። «በሲስተም ኢንጂነርነትና በፈጠራ ሳይንቲስትነት በሠራሁባቸው ዓመታት ከሌሎች ሳይንቲስቶች ጋር በመተባበር ለመሬታችንና ለሌሎች

ኘላኔቶችም የምርምር ሳይንስ የሚያገለግሉ መንኮራኩሮችንና ሮኬቶችን ለመፍጠር ችያለሁ። ግን ምን ዋጋ አለው!» ኢንጂነር ሻጊዝ የዶ/ር ሚራኹን ዓይኖች ጠልቆ ተመለከታቸው።

«እንዴት ዋጋ የለውም? አለው እንጂ። ይህ እኮ ለብዙዎች ኩራት የሚሆን ተግባር ነው በተለይም ለጥቁር ህዝቦች» አለው ዶ/ር ሚራኹር።

«ዋጋ እንደሌለው የተረዳሁበትን ምክንያት ልነግርህ ነው። ላለፉት በርካታ ዓመታት ስታር ዋርስ ለሚባለው የመከላከያ ሲስተም ቴክኖሎጂ ለማጉልበት የሳይንቲስቶችና ኢንጂነሮች ቡድን መሪ በመሆን አገለገልኩ። ይህም ከንቱ መሆኑን አወኩ፡ የልዕለ ሀያላኑን ሀገራት መንኮራኩሮች ወደ ህዋ ሳስወነጭፍ ኖርኩ። የሰሜን አሜሪካ የህዋ አስተዳደርና የአውሮጳ የህዋ ማዕከል የሳይንቲስቶች ቡድን መሪ ሆኜ በህዋ ውስጥ ለሚደረግ ተልዕኮ መጠቀሚያ መንኮራኩርና ምድርን እየዞሩ ደህ ሀገራትን ለብዝበዛ የሚያመቻቹ ሳተላይቶችን እንዲመጥቁ አደረኩ። በጠፈር መንኮራኩር የምድርን ሀብት በተለይም የአፍሪካ አህጉርን የመሬት ውስጥ ሀብት አይቼ በሶስተኛው አለም በረሀብና በሰቆቃ የሚሰቃዩ ህፃናትንና አዛውንቶችን ሳስብ ውስጤ ይሰበራል። ከዚህ በላይ ከንቱነት አለ? እኔ የኘላኔቶችን ውስጣዊና ውጫዊ አካል በዩኒቨርስ ውስጥ ለማጥናት ስኪትን ወገኖቼ ግን በረሃብ አለንጋ ይገረፋሉ።» ዓይኖቹ እንባ አቀረሩ።

«እና ከንቱነቱ ምንድን ነው?» አለ ሚራኹ «ማወቁ መልካም አይደለም እንዴ?»

«ባላወኩት ወዲያ! አየህ ሃያላን ሀገራት መሬትን ወደ ገሃነምነት እየለወጧት ነው። ድሮ በቅኝ ግዛት የአፍሪካን የምድር ሀብት ሞጨለፉና ከበሩ። አሁንም ቀሪውን ለመቀራመት የማይሠሩት ደባ እንደሌለ አውቄያለሁ። መሬት ወደ ገሃነምነት ብትለወጥ ቀዳሚ ተጠቂዎቹ አሁንም የሶስተኛው አለም ደሃዎች ናቸው። የኃይል ሚዛኑ በዚህ ከቀጠለ የመሬት ህልውና የሚያከትምበት ጊዜ በየደቂቃው እየፈጠነ እየቀረበ ነው። በፈጠሩት ገሃነማዊ መሳቱት የምድራችን ውሃ ፈልቶና ተኖ ውቅያኖሶች ላይ አውሎ ነፋስ የሚነሳበትን ጊዜ ለማወቅ አቡሻህር ገልጦ ጠጠር መጣል አያስፈልግም።»

«አልገባኝም ኢንጂነር። እያልከኝ የለኸው ታዲያ ዛፍ እንትከል ነው?»

«የምነግርህ ለምን የመሬትን ሀብት ከመጠን በላይ መቀራመት እንደፈለጉ ነው። መሬትን ተቀራምተዋታል። አሁን እየተቀራመቱ ያሉት ደግሞ ዩኒቨርስን ነው። ለዚህም ነው መንኮራኩሮቻቸውን በየጊዜው የሚያመጥቁት። ሌላ ምቹ የሰው ልጅ መኖሪያ ካገኙ ዜጐቻቸውን ወደዚያ በመንኩራኩር ያጓጉዛሉ።»

ሚራኹ ከት ብሎ ሳቀ።

«እየቀለድኩ አይደለም። አሜሪካውያን ወይም ቻይናውያን ወይንም ሩሲያውያን አልያም ኮርያውያን አለበለዚያም ጃፖናውያን ቀድመው በህዋ ውስጥ በሚገኘው አዲስ ገነት ውስጥ ይሰፍራሉ። በተለይም ለእስራኤላውያን አስፈላጊ ነው። በዚህ የጠበባቸውን ያህል በዚያ ሰፋ አድርገው ለመያዝ። ከጨከኑም ሁሉንም ይዘው በኋላ የሚመጣውን መንኮራኩር በተምዘግዛጊ ሚሳዬል አመድ ሊያደርጉት ይችላሉ። ከዚያም ደህ ሃገራት መሬት ላይ እየዳሁ ገሃነሙ ውስጥ ተጠራርገው ይገባሉ። አፍሪካ ወደ ገሃነም ሀያላኑ ወደ ሌላ ኘላኔት። ወደ ሌላ ገነት። ይህ ከመሆኑ በፊት የመንኮራኩሮች ግንባታና የኃይል አቅርቦት ሩጫና ፉክክሩ በልዕለ ሃያላኑ ሃገራት እየተጧጧፈ ነው። የኃይል አቅርቦቱን ለማሟላት የመሬትንና የጨረቃን ህብት በመንኮራኩር በማሰስና በመቃረም ተግባር ላይ ናቸው። ነገሩን አጭር ለማድረግ ያህል ለምሳሌ የኢትዮጵያን የምድር ሃብት ብናይ እንኳንስ ለኢትዮጵያውያን ለአፍሪካ ህዝቦችም የሚበቃ ነው። የምነግርህ ያየሁትን ነው። ሚራኹ። ዩራኒየሙ፣ ኘላቲኒየሙ፣ የከሰል ድንጋዩ፣ መዳቡ፣ ወርቁ፣ ብሩ፣ የነዳጅ ድፍድፉና አልማዙ ሁሉ ያላት ባለፀጋ ሀገር ናት። የብዙ ሃገራት አይን አርፎባት የኖረው ለሌላ ለምንም አይደለም። ኢጣሊያን አስወጥታ እንግሊዝ፣ እንግሊዝን ገዝግዛ አሜሪካ፣ ምናልባት አሁን ደግሞ የአሜሪካን ቦታ ለመያዝ ደፋ ቀና የምትለው ቻይናም....እነዚህ ሁሉ የሚሻኩባት ምድር ኢትዮጵያ ያንቀላፋችበት ወቅት ላይ ነን። በአሁኑ ወቅት.....ኢትዮጵያ ለብዝበዛ ተንጋላ የተኛች ሀገር ናት። ይህን ሁሉ ሀብቷን ደብቀው ህዝቧን በእርዳታ ሸባ እያደረጉ ለድህነትና ለጭቆና እየተከፈለን ሳንኖር እየኖርን ያለንበት ወቅት ላይ ነን።» ኢንጂነር ሻጊዝ የሚራኹን ትኩረት ያገኘበትን ቅፅበት ላለማቋረጥ ቀጠለ። «ኢትዮጵያን ለመመንተፍ በኢንቨስተር ስምና በተለያዩ የረድኤት ድርጅቶች የተሰገሰጉ ወንበዴዎች ህዝቡን በስብሰባና በፎረም ቁጭ አድርገው እያንጫፈፁ እነሱ ሥራቸውን ከመሰኛ ባለሥልጣኖቻችን ጋር በሽርክና ይሠራሉ። ምናልባት የኢትዮጵያን ጉዳይ ዕለት በዕለት የምትከታተል ከሆነ...»

«አዎ በመጠኑ እከታተላለሁ።» አለው ዶ/ር ሚራኹ።

«የኢትዮጵያ መሪዎች በየቀኑ ብድር ይፈራረማሉ። ባለስልጣናቱ የብድር ሥምምነት ሳይፈራረሙ የሚውሉበት ቀን የለም። ኢትዮጵያ መቼውው ትውልድ ከፍሎ የማይጨርሰው ብድር ተበድራለች። እያንዳንዱ ወጣት እያንዳንዱ ታዳጊ የሚወርሰው ሌላ ነገር የለም። ቀጣዩ ትውልድ የሚወርሰው የትየለሌ ዕዳ ብቻ ነው። የገንዘብ ዕዳ፡ የሞራል ዕዳ፡ የደም ዕዳ። ገና የምንከፍለው ብዙ ነገር አለ። ኢትዮጵያውያን ነዳጃቸው ላይ ቆመው እየለመኑ ነው። ኢትዮጵያውያን ዩራኒየማቸው ላይ ቆመው ኃይል አጥሯቸዋል፡ በጨለማ እየኖሩ ነው። የኢትዮጵያ ጥቂቁር አልማዞች ጥቁር አልማዛቸው ላይ ቆመው እየተመፀወቱ ነው። ...ይህን ሁሉ የዘበዘብኩብህ ወድጀ አይደለም። ወንድሜ ሚራኹ?.....እኔና አንተስ

እስከመቼ ዝም እንላለን?» አለው ይበልጥ ወደፊቱ ተጠግቶ በጥያቄ ዓይን:: «ስለዚህ ጉዳይ እስከመቼ ድረስ ዳር እንቆማለን?»

«እስከመቼም!» አለ ሚራዥ ውስጡ ተቃጥሎ:: «እኔ በበኩሌ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ ማንኛውንም ተግባር ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ:: ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? የችግሩ ሰንሰለት ተቆርጦ የማያልቅ ነው:: የሰው ኃይልና በቂ ገንዘብ ይፈልጋል::»

«በቂ ገንዘብ ብቻ አይደለም የሚፈልገው:: ብዙ ህዝብም አይደለም የሚፈልገው:: ልብ ለልብ ከተገናኘንና አብረን ከሰራን እንኳንስ አንዲት ሀገር አለምን መለወጥ የሚያስችል እውቀትና አቅም አለን:: አለማችን የተለወጠችው እጅግ በጣም በጥቂት ሰዎች ነው:: አሥር በማይሞሉ:: አሜሪካን በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዋዜማ የአቶሚክ ኢነርጂ ባለቤት ያደረጓት ሳይንቲስቶችን አስብ:: ኤንሪኮ ፈርሚን፣ ሊዎ ስዚላርድን፣ አልበርት አንስታይንን፣ ሩተርፎርድን፣ ቦንን.....:: የእነዚህ ሳይንቲስቶች ባንድ የታሪክ አጋጣሚ መገናኘት ነው አሜሪካን ልዕለ ሀያል ሀገር ያደረጋት:: አሜሪካ አዕምሮን እንዴት ማጠብ እንዳለባት ታውቅበታለች:: ገና ምድሯን ሳትረግጥ አሜሪካዊ የሆንህ ያህል እንዲሰማህ የሚያደርጉ ታላላቅ ሰዎች ያሉባት ሀገር ናት:: እኛ ሀገር ደግሞ ባደክበት ቀየ ባደክበት ምድር ወዘ ልውጥ እየተባልክ ትኖራለህ:: ለሀገርህ ባዳ ሆነህ አያገባህም እየተባልክ አፍህን ጠመንጃ ሽብቦት ብታውቅ እንኩዋ እንዳላወክ ሆነህ ትሞታለህ:: እነዚህ አሜሪካን ልዕለ ሀያል ሀገር ያደረጉዋት ሳይንቲስቶች ሁሉ አሜሪካውያን ናቸው? አይደሉም:: አምባገነን መሪዎቻቸው ያሳደዷቸው የሌሎች ሀገራት ዜጐች ናቸው:: የኛና የሌሎች ኢትዮጵያውያን ምሁራን እጣ ፋንታም ከዚህ የተለየ አይደለም:: ኢትዮጵያ የተማረ ሰው አጥታ አይደለም የተማረ ስለማትወድ እንጂ:: ግን ...» አለው ኢንጂነር ሻጊዝ:: «አንድ ነገር ያስፈልጋል:: ለለውጥ ራስን መስጠት:: አሁንም..... ኢትዮጵያ አንድ አብዮት ያስፈልጋታል:: ልጆቿን የማይበላ አብዮት! ራሱን የማይውጥ አብዮት! ሳይንቲፊክ ሪቮሉሽን:: በሳይንስና ቴክኖሎጂ የታገዘ አብዮት:: አየህ ሚራዥ..... ለውጥን የሚጠላ ኢትዮጵያዊ የለም:: ለውጡ ሆዳቸውን ከሚያጐልባቸው ጥቂቶች በቀር:: ችግሩ ግን የለውጡ አካል ለመሆን የሚፈልግ የለም:: በሌሎች ሞትና ደም ለመጠርቃትና ኑሯቸውን ለማደላደል የሚመኙ ብዙ ናቸው::»

«እኔ በበኩሌ» አለ ዶ/ር ሚራዥ:: «በሰቆቃ ውስጥ ያሉት ወገኖቼን ችግር መቅረፍ የምችልበት አቅም ያለኝ ሰው ከሆንኩ ይሽሙ እንደፈለገህ አድርገኝ:: ግን እንዴት ለውጡን ማምጣት እንችላለን?..... ኢትዮጵያ እያስፈለግሃት አትፈልግህም:: ኢትዮጵያ እንደ ሴተኛ አዳሪ ሴት ተኳኩላ በር ላይ የምትጠብቃቸው የሩቆችን ነው:: ገመናዋን ጉዷን የሚያውቁላትን አታስጠጋም::

ባይኗ ገርፋ ታባርራቸዋለች:: በሰይጣ ትጠርጋቸዋለች:: የተማሩት ይሰደዳሉ:: የሚማሩት ወጣቶችና ታዳጊዎች ከእስር ቤት በማይተናነሱ ትምህርት ቤት ተብየዎች ታጉረው የነቀዘ ቲምሪ እንዲሸመድዱ አእምሯቸው ነፃነትን እንዳያስብ ተደርገው ይውላሉ:: ከዚህ ሰንሰለት ለማምለጥ የሚጥሩ ሲገኙ በጠላትነት ይፈረጃሉ:: ታዲያ እኔና አንተ በምን አይነት መልኩ ይህን ያህል ችግር መቅረፍ እንችላለን?» ሲል ሚራዥ መልሶ ጠየቀው::

«እንግዲያውስ የያዝከው መንገድ ወደዚያ የሚያደርስህ ነው!» አለው ኢንጂነር ሻጊዝ::

«የትኛው የያዝኩት መንገድ?» ሲል ጠየቀው ሚራዥ

«ወደ ተጠራህበት ያለማቅማማት ተጓዝ:: ወደ ኢትዮጵያ ሂድ:: አታቅማማ:: በአቅማማህ ቁጥር መንገድክን ትስታለህ:: እስከ አሁን የተጨዋወትነው ሀገራዊ ጥያቄ የሚፈታው በያዝከው ጎዳና ነው:: በድጋሚ የምነግርህ በአቅማማህና ባወላወልክ ቁጥር ተመራጩ ሰው አትሆንም:: ቅድም ያልከው:: ዩራኒየሙ፣ የሰብል ድንጋዩ፣ መዳቡ፣ ወርቁ፣ ኘላቲኒየሙ፣ የነዳጅ ድፍድፍ ገደሎችም ከአንተ አይበልጡም:: ኢትዮጵያ እየጠራችህ ነው:: እነዛኞቹን ርሳቸው:: ዝም ብለህ የራስህን ጉዞ ተጓዝ::» ሲለው ዶ/ር ሚራዥ የማያውቀው የተወሳሰበ ነገር ውስጥ እግሩን ማስገባቱን ተረዳ:: ግን 'ለምን አይነግረኝም ሁሉን ነገር?' ሲል አሰበ::

ሚራዥ ግራ ተጋብቶ ለደቂቃዎች ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ «ወዴት ነው የምጓዘው?» ሲል ሻጊዝን ጠየቀው::

«ይህን ምስጢር እንዳቀብልህ አልተፈቀደልኝም:: አንድ ምክር ግን ልለግስህ እችላለሁ:: ከሁሉም በላይ ምስጢር ጠባቂነትህን ማረጋገጥ አለብህ:: ቅንጣት የምታህል ስህተት ወደገሃነም እንደምትወረውርህ አስብ:: ላስፈራራህ አይደለም:: አንድ ነገር ግን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ:: ጉዞ ጀምረህ መመለስ እንደማትችል:: ካልፈለግህ አሁን ንገረኝና አሁኑኑ ማቆም ትችላለህ:: አርፈህ የግልህን ህይወት መኖር ትችላለህ::»

ዶ/ር ሚራዥ ለረዥም ጊዜ በብዥታ ውስጥ ከቆየ በኋላ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረሰ:: «የመጣው ይምጣ:: አላቅማማም:: አላፈገፍግም» ሲል ነገረው:: «ግን የአንተን የልብ ችግር መፍታት እፈልግ ነበር::»

«የልቤን ችግር ለመፍታት የቻልከውን አድርገሃል:: ከአቅምህ በላይ ነው አሁን:: ሲለኝ ብለህ ከሥራ ተፈናቅለሃል:: በህይወትህ ላይ አደጋ እንዲንጎበብ አድርገሃል:: ከዚህ በላይ ልታደርግልኝ የምትችለው ነገር የለም:: ብንችል አንድ ቀን ሀገራችን ውስጥ እንፈታዋለን:: አለበለዚያ ስለ እኔ ለረጅም ጊዜ መኖር አትፅኢነቅ:: እኔ እልፍ ለመኖር ምኞት የለኝም:: ኢትዮጵያ ውስጥ በየቀኑ በረሃብ ስለሚያልቁ ህፃናት ተጨነቅ:: እኔ ብሞት ኢትዮጵያ ሰው አታጣም:: በየዘመኑ አንዳንድ ሰዎችን አጥታ

አታውቅም:: ደጋጉቹ በክፉዎቹ ብዛት እየተዋጡ እንጂ:: አትጨነቅልኝ:: ይልቅ እኔም አንተም ሞት ሳይቀድመን ወገኖቻችንን ከሞት የምንታደግበት ወቅት ላይ መሆናችንን አስብ:: ኢትዮጵያውያን አንገታቸውን የደፉበት ወቅት ላይ ነን:: በሃፍረት ተሸማቀዋል:: አቀርቅረዋል:: ሴቶች ለአረብ ነጋዴዎች እየተሸጡ ነው:: ወጣቶች በጠረፋማ አካባቢዎች ከሀገር ሲወጡ በጋንጃቸው እየታረዱ ነው:: ኢትዮጵያ ተስፋ በቆረጡ ወጣቶች ተሞልታለች:: ራዕይ ያጡ ህዝቦች ጎተራ ሆናለች:: ራዕይ የሌለው ህዝብ ደግሞ ይጠፋል:: የተስፋው መስኩት መከፈት አለበት:: ኢትዮጵያን ሌላ ሰው መጥቶ አይለውጥልህም:: አንተን ለመለወጥ ሌላ ሰው አይመጣም:: ይህን ሀቅ እወቅ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ሺ ብትን የሚሉ ቻይናዎችና አረቦች ሁሉ ለእንተ ብልፅግና ግድ የላቸውም:: ሀገርህን ከቅጥረኞችና ከወሮበሎች የምትታደግበት ጊዜ አሁን ነው::» ሻጊዝ የሚራዥን እጅ ያዘውና የዓይኖቹን ውስጥ ተመለከተ::

«አንድ ጥያቄ እንድጠይቅህ ፍቀድልኝ?» አለው ሚራዥ::

«ጠይቀኝ እስከተፈቀድልኝ እነግርሃለሁ::» አለው ሻጊዝ::

«ወደ ጦር ሜዳ እየላካችሁኝ ነው?»

ሻጊዝ ከት ብሎ ሳቀ:: «የደርግ ወታደር እንደነበርክ አውቃለሁ:: ገዳማዊ እንደ ነበርክም እንዲሁ:: ታዲያ ወታደርና መናኝ ሞት ይፈራል?»

«አይፈራም ይሆናል:: ግን ጦርነት አልወድም:: እናም ከአሁን በኋላ በማንም ሰው ላይ ቃታ አልስብም::»

«እኛም ሰይፍህን እንድታነሳ አንፈልግም:: ስለዚህ ኦየሄድክ ያለኸው ወደ ጦርነት እንዳልሆነ እወቅ::»

«ታዲያ ወዴት ነው?»

«እሱን ምስጢር እንድነግርህ አልተፈቀደልኝም:: ብዬሃለሁ አይደለም? ሁለት አማራጮች አለህ አሁን:: ጉዞውን አሁኑኑ በእኔ ፊት ማቆም አንድ፣ ሳታቅማማ በጊታርህ ዜማ ዘና እያልክ መጓዝ ሁለት:: ከዚህ በተረፈ በማስተዋል መጓዝ:: በጥበብ መጓዝ:: አለቀ::»

«አምንሃለሁ ኢንጂነር::»

«እኛም በረጅም ጊዜ ጥናት ታማኝነትህን ማረጋገጥ ጀምረናል:: አንተም አሁን አረጋግጥልን:: ባለማቅማማት::»

«አላቅማማም:: ግን ዴርቶጋዳ ምንድን ነው?»

«ባላቅማማህ ቁጥር ወደ ዴርቶጋዳ የምትደርስበት መንገድ ቀና ይሆናል:: ዝም ብለህ ወደፊት ተጓዝ:: አሁን የሚመሩህ አሉ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ በተራህ የምትመራቸው አሉ:: መጀመሪያ ጥሩ ተመሪ ሁንና ከዚያ ጥሩ መሪ ትሆናለህ::»

ኢንጂነር ሻጊዝና ዶ/ር ሚራዥ ይህን ሲነጋገሩ በነበሩበት ቅፅበት አንዲት ወፍራም ሴትዮ ወደ ህንፃው አሳንሰር ገባች:: ማንም ትኩረት አላደረገባትም:: መኪናዎቹ ውስጥ ያሉት ሰዎች የቆርቆሮ ቢራ እየጠጡ ሽቅብ አንጋጠው እየተመለከቱ ነው::

ወደ ህንፃው የገባችው አሮጊት ሴትዮ እጅግ ወፍራም በመሆንዋ እግሯን ከወገቧ ወገቧን ከአንገቷ ለይቶ ማወቅ አይቻልም:: ክብ ጉጆ ቤት ትመስላለች:: ከጀርባዋ ረጅም ሻንጣ አንግታለች::

ሚራዥ ሴትዮዋ ወደ ውስጥ ከገባች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በተንቀሳቃሽ ስልኩ መልእክት እንደደረሰው ሻጊዝን ተሰናብቶት ተነስቶ ወደ ህንፃው ሽንት ቤት ገሰገሰ::

ወዲያው ከጥቁሩ ቢ.ኤም.ደብልዩ መኪና ውስጥ ተቀምጠው የነበሩት ሲጳራና ዶ/ር አናንያ ከመኪናዋ ወጥተው ወደ ህንፃው አሳንሰር በፍጥነት ገቡ::

ከቀይዋ ፊያት ውስጥ ያሉት የኬጂቢ ወኪሎች ከነጭዋ ካዲላክ ውስጥ የነበሩት የሲ.አይ.ኤ ሰዎችም ተከታትለው ወጥተው ወደ ህንፃው ገቡ:: ሰዓቱ መድረሱን ተገንዝበዋል:: ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር ያንን ያህል ሰዓት ተቀምጦ ሲያወራ የነበረው ባለጊታር የሚያዝበት::

የሞሳድ ኤጀንቶች ሲጳራና አናንያም ይህን ያህል ጊዜ ከኢንጂነሩ ጋር ተቀምጦ የቆየውን ባለጊታር ማንነት ለማወቅ ብቻም ሳይሆን አንገቱን ለመበጠስ ሽጉጣቸውን አቀባብለው እየጠበቁት ነው::

ኢንጂነር ሻጊዝ በቁጥር አስራ ሁለቱ በር በኩል በሚገኘው አሳንሰር ፎቁን ወርዶ ወደ መኪና ማቆሚያው ሲደርስ ጋርዶቹ ከመኪናው ወጥተው አካባቢውን ተቆጣጠሩትና ከለላ ሰጥተው ወደ መኪናው አስገቡት::

ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ጉጆ ቤት የምታህለው ወፍራም ሴትዮ ሻንጣዋን ከጀርባዋ እንዳዘለች ሌላ ክብ ከሆነች ወፍራም ሴት አስከትላ ወጣች:: ሁለቱ ወፍራም ሴቶች ተከታትለው ከሩቅ ወደቆመችው የቤት መኪና እንደገቡ መኪናዋ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሀንፃን ወደቀኝ ትታ ከነፈች::

የኢንጂነር ሻጊዝ ተንቀሳቃሽ ስልክ ጠራ:: «ኢንጂነር ሻጊዝ ከህንፃው ወጥቼ ሄጃለሁ:: ደህና ነኝ አሁን:: ስለእኔ ደህንነት አታስብ:: ስለአንተ ደህንነት እንጂ:: አሁን ተንቀሳቀስ ካለህበት:. መልካም ጊዜ:: ቻው::» ስልኩ ተዘጋ:: የዶ/ር ሚራዥ ድምፅ ነበር::

«የኔ አንበሳ» አላት ሚራዥ ሜሮዳን:: «አደንቅሻለሁ::» ኢንጂነር ሻጊዝ ዶ/ር ሚራዥ ምን አይነት ዘዴ ተጠቅሞ ከህንፃው ወጥቶ እንዳመለጠ ባያውቅም ደህና በመውጣቱ ተደሰተ::

የኢንጂነር ሻጊዝ መኪና ከአካባቢው እስከምትሰወር ወደ ህንፃው የገቡት የሞሳድ፣ የሲ.አይ.ኤና የኬጂቢ ሰዎች አልተመለሱም ነበር:: ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር የነበረው ባለጊታር የውሃ ሽታ በመሆኑ በንዴት ጠፈው ተመለሱ::

ሲጓራና አናንያ ሽጉጣቸውን መልሰው ወደ ሽንጣቸው እየሸጎጡ ወደ መኪናቸው ሲገቡ ሲጓራ በንዴት ጦፋ አናንያን ገላመጠችው::

«አንተ ነህ!» አለችው:: «እዛው አብረው እንደተቀመጡ ሄደን ፊቱን ብናየው ኑሮ ቢያንስ ፈልገን ለመያዝ ያመቸን ነበር:: ከዚህ ርቀት ቁጭ ብለን ይህን ያህል ሰዓት ስንቆይ ከነጭ ሱፉና ከጊታሩ ውጭ ያየነው ነገር የለም:: አደገኛ ሰው ለመሆኑ ደግሞ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገንም:: እንዴት ሊያመልጠን ቻለ? ሺት! ትከፍላለህ:: ስለዚህ እንዝላልነትህ ዋጋ ትከፍላለህ:: እኛን መልሶ ሊያሳድደን የሚችል ሰው ለመሆኑ ፕርፕር የለኝም» ብላ አናንያ ላይ አንባረቀችበትና የመኪናዋን መሪ በንዴት በቡጢ ነርታ አበረረቻት:: ዶ/ር አናንያ እጉረምርሞ ፀጥ አለ:: ለ'አቦ ሸማኔዋ' መልስ መስጠት እንደሌለበት ያውቃል:: በሱ ድምዳሜ እሷ ሁሌም ትክክል ናት::

ሜሮዳ ከቤቷ ከደረሰች በኋላ መኪናዋን አቁማ ክቧን ሴትዮ ወደ ሳሎን ይዛት ገባች:: ሴትዮዋ ሻንጣዋን አውርዳ ጊታሯን ከሻንጣዋ አወጣች:: የለበሰችውን ዝክንትል ስታወልቅ መቅጠን ጀመረች:: ከወፍራሟ ሲትዮ ውስጥም ዶ/ር ሚራዥ ወጣ:: እሷም ክብ ያስመሰላትን መአት ልብስ በየተራ አወለቀችው::

«ወፍራም ሴት መሆን እንዴት ነበር?» አለችው ሜሮዳ እየተፍለቀለቀች:: ደረቅ ፈገግታዋ ከሚራዥ ጋር ስትሆን ብዙም አይታይም:: ሚራዥ ደረቅ ፈገግታዋ ሌላ ምስጢር ሊኖረው እንደሚችል መጠርጠር ጀምሮአል:: ከልቧ ሲሆን ከገዳይ ፈገግታዋ በኋላ በፍንጭታ የሚፈልቀው ሳቋ ህይወትን ያደምቃል::

«ሴት መሆን እንዴት ደስ ይላል በናትሽ! በተለይ ይህችን ወፍራም ሴትዮ የማህል ብሆን ኑሮ ሞት ገድሎ የሚጨርሰኝ አይመስለኝም ነበር::»

«የቤት ኪራዩን አትችለውማ! ወፍራሞች ከቀጭኖች እጥፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ የሚያዝዝ ህግ እየተረቀቀ ነው አሉ:: ወንድሜ.....አርፈህ ቅጠን::»

«ይህችን የምታክል ሴት ቴአትር ቤት ብትገባ አሁን የአንድ ሰው ትኬት ቆርጣ ልትገባ? እኔ ግን ትኬት ቆራጩን ብሆን የስድስት ሰው ነበር የምቆርጥላት:: ለማንኛውም አሪፍ ቲያትረኛ ነሽ»

«አንተም አሪፍ አርቲስት ሳይወጣህ አይቀርም:: አም አሁን ደግሞ የኛን ቲያትር.....:: ካንተ ጋር ሮሚዮና ዠልዬትን ሆነን እንድንጫወት እፈልጋለሁ.....»ይዛው ሶፋው ላይ ወደቀችና ከንፈሩን ነከሰችው:: አልከለከላትም::

፱

ሲሲሊ.....ሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ

ስልኩን በቀስታ ከዘጉት በሁዋላ በእርካታ ፈገግ አሉ:: ጣና ሐይቅ ውስጥ በምትገኝ አንዲት ብጣቂ ደሴት ላይ የኢንቨስትመንት ስምምነት ለመፈራረም ጫፍ መድረሳቸውን ያበሰራቸው ስልክ ነበር:: የተቀዳላቸውን ወይን ተጎንጭተው ጉንጫቸው ውስጥ እያንቀዋለሉት ብርጭቆው ላይ ቡዝዝ ብለው ጥቂት ካሰላሰሉ በሁዋላ ከፍስሐቸው ጋር ተጉመጥምጠው ዋጡት:: «ከረጃም እልህ አስጨራሽ ጊዜ በሁዋላ!» አሉ ቃላቱን ጠበቅ አድርገው:: «ያ ኃያል ምስጢር የግሌ ሊሆን ነው! ግን.....ምን አይነቶቹ ቀሽሞች ናቸው? እንዴት እስካሁን አልደረሱበትም? በርግጥም ከኔ በቀር ወደዛ ምስጢር የሚደርስበት የለም! .....ማንም ጭቃ ራስ!.....ጭንቅላት! ይጠይቃላ! ...ጭንቅላት!» በጠቀሞሚ ጣታቸው ጭንቅላታቸውን ጠቆም ጠቆም እያደረጉ ተነስተው ከተንጎራደዱ በሁዋላ «ቪቫ ሞርሞርዲና! ቪቫ ቡስኪ!» ብለው መልሰው ተቀመጡ:: ፈርጣማው ጥቁሩ የግል ጠባቂያቸው ዲዎላ በሁኔታቸው ፈገግ ሲል ባዶ ቀይ ድዱን አይተውት «ቪቫ ዲዎላ! ቪቫ ባሪያው!» አሉት እሱንም:: «ቀን ሊወጣልህ ነው አንተ ባሪያ! የሞት ሽረት ትግል ካላደረግህ ግን ባርነትህ ይቀጥላል::»

«መሆንዲሶቹን እዛው ሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ አስወግጃቸዋለሁ» አላቸው:: «የሠሩትን ጠላቂ ኤክስካቫተር ዶዘር አንደ ፈለግሁት ማድረግን ካለማመዱኝ በሁዋላ::»

«የማውቀውንና ያስፈፀምኩትን ነገር መልሰህ አትንገረኝ አንተ ባሪያ! እንዳንተ ደደብ እንዳልመስልህ:: ይህ የሁሉም ነገር መጀመሪያ ነው:: ና ይልቅ ወይን ጠጣ:.....ለዚህ ጣፋጭ ስኬታችን ብርጭቆአችንን ከፍ እናድርግ::»

ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ የዘጠና አራት አመት ዕድሜ ባለፀጋ ቢሆኑም በምድር ላይ ዘጠና አራት ቀናት የቆዩ ያህል አይሰማቸውም:: የመኖር ፍላጐታቸውና ሀብት ሆሚጋበስ ህልማቸው ገና እንደጐመራ ነው:: ምንም እንኳ ዘመዶቻቸው እርስ በእርስ ተጫርሰው ቢያልቁም እሳቸው ግን የባለዳንና የካፖዲካቺ ሰዎች ሀብታም ናቸው::

በሲሲሊ የሚዲትራኒያን ባህር ዳርቻ ከሰው መዳረሻ ርቆ በተሠራና ከፍተኛ ጥበቃ በሚደረግለት መኖሪያ ቤታቸው ሁስተ ከአርባ በላይ ሰዎች አሏቸው:: ከነዚህ ሰዎች መካከል አሥራ ስምንቱ የግል ጠባቂዎቻቸው ሲሆኑ ሃያ ሁለት ያህሉ ደግሞ እቁባቶቻቸውና ሚስቶቻቸው ናቸው::

በአለም ዙሪያ በተበተኑ ወኪሎቻቸው አማካኝነት በሞኖፖሊ የያዙት በኮሎምቢያና በጃማይካ ውስጥ ያሉት ሰፊ የእፅ ማሳዎች ማሌዥያ ውስጥ የተተከለው ግዙፍ የዘይት መጭመቂያ ፋብሪካ፣ ጣሊያን ውስጥ ያሉት ሶስት የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ያለው እውቁ የአልማዝ ማዕድን አውጪ ኩባንያ እንዲሁም በዲሞክራቲክ ኮንጐ ውስጥ ከሁለት ዓመታት በፊት የከፈቱት የማዕድን ማውጫ ጣቢያዎች ባለቤት የሆኑ የጣሊያን የማይታዩት ቱጃር ናቸው—ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ።

ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከአድዋ ድል አርባ ዓመት በኋላ እንደገና በ1928 ዓ.ም ስትወር ከቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ገና ወጣት ነበሩ። የኢጣልያ ጦር በአትዮጵያ ለአምስት አመታት ሲቆይ የሞርሞርዲኖ ቤተሰብ በባህር ዳር ከተማ ምሥራቃዊ ጫፍ በጣና ሐይቅ ዳርቻ በአንድ ዘመናዊ ቤት ውስጥ ይኖር ነበር። ይኸው ቤተሰብ የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባሮ ሲወጣ ኢትዮጵያን የሙጥኝ ብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ቀረ። ጣሊያናዊው ቤተሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀረበትን ምስጢር ማንም የሚያውቅ አልነበረም። በኋላ ምንጩ ባልታወቀ ግጭት ቤተሰቡ ለሁለት ተከፈለ። የሞርሞርዲኖ አያቶች ከባህርዳር ከተማ ሸሽተው በከፋ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ወደ ምትገኘው ቦንጋ ከተማ ሲጓዙ ግማሹ እዛው ቀረ። በዚህ ወቅት የቤተሰቡ ብዛት ከኢጣሊያ በመጡት አጐቶቻቸው ተበራክቶ ነበር። በኋላ ደግሞ እርስ በእርስ መገዳደል ተጀመረ። በዚህ ወቅት ሞርሞርዲኖ ወደ ቦንጋ ከሄደው ቤተሰብ ጋር አብረው ተጉዘው ስለነበር የጠቡን መንስኤ ሊያውቁት አልቻሉም። የሞርሞርዲኖ አባት ጣሊያናዊው ቡስኪ ወደ ኢጣልያ ብቻቸውን ሸሽተው ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ተመልሰው ሲመጡ ቤተሰቡ በመገዳደል ተመናምኖ ነበር። የቀሩትም በቦንጋ ከተማ የኤሌክትሮኒክስ መሸጫ ሱቅ ከፍተው የሚኖሩ ጥቂት አቅመ ቢስ ጣሊያናውያንና በባህርዳር ከተማ የቀሩ ተጣሪ አዛውንቶች ብቻ ነበሩ። ቡስኪ ከጣሊያን እንደተመለሱ ሁሉንም ነገር ተቆጣጠሩትና ቤተሰቡ ይፋጅበት የነበረውን ምስጢር የግላቸው አደረጉት።

በ1940 ዓ.ም በቡስኪ የረጅም ጊዜ እቅድ መነሻ ይሆኑ ዘንድ ሶስት ባለሞተር የአንጪት ጀልባዎች በጣና ሐይቅ ላይ ታዩ። በዚህም በቡስኪ የንግድ ኢምፓየር ውስጥ ብቻ የሚንቀሳቀስ የባህር ላይ ትራንስፖርት በጣና ሐይቅ ላይ ተጀመረ። ቡስኪ ይህንን የሚያደርጉበትን ምክንያት ማንም አያውቅም ቤተሰብም ቢሆን። ዘግየት ብሎ ደግሞ የባህርዳርንና አካባቢውን ህዝቦች ያስደመመ አንድ ነገር ተከሰተ። ጣሊያናዊው ቡስኪ ጣና ሐይቅ ውስጥ የኢጣልያ ጦር ያሰጠማቸውን ሶስት ጀልባዎች አወጡ።

የኢጣልያ ጦር በጦርነቱ ወቅት ነሰሜን ወደ መሃል አገር በሚያደርገው ግስጋሴ የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎችን በተለይም ጎጃምንና ጎንደርን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ያመቸው

ዘንድ መቀመጫውን ጉንደር፤ የማዘዣ ጣቢያውን ደግሞ ጉርጉራ ላይ በማድረግ በጣና ሐይቅ ላይ ስንቅና ትጥቅ ለማጓጓዝ በርካታ የሞተር ጀልባዎችና መርከቦችን በባህሩ ላይ አሰማርቶ እንደነበር ቡስኪ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር።

በመሆኑም የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባሮ ሲወጣ ለወታደራዊ አገልግሎት ሲጠቀምባቸው የነበሩትን መርከቦችና ጀልባዎች በጣና ሐይቅ ውስጥ አስጥሟቸው መውጣቱንና ጥቂቶች የሰጠሙበትን ቦታ ጠንቅቀው የሚያውቁት ቡስኪ ጉርጉራ ወደብ አጠገብ በሚገኘውና ከፍተኛ ጥልቀት ባለው የጣና ሐይቅ ክፍል በአንጋራ ተክለሃይማኖት ደሴት አቅራቢያ የሰጠሙትን ሶስት ጀልባዎች አወጧቸው። በነዚህ ከሐይቁ ሰጥመው በወጡ ሳንጆርጅ፣ ሳንታማርያ እና ሳኒኮላ በተባሉ ሶስት መርከቦች «ናቢጋ ጣና» በሚል ስም የይስሙላ ማህበር ያቋቋሙት ጣሊያናዊው ሰው ቡስኪ የቀለጠ የባህር ላይ ትራንስፖርት ድርጅት ሲጀምሩ የጠየቃቸው ኢትዮጵያዊ የለም ነበር። በእረግጥ ጣሊያናዊው ቡስኪ ይህን ያደረጉት በሐይቁ ላይ በከፈቱት የትራንስፖርት ድርጅት ለመክበር አልነበረም። የአካባቢውን ህዝብ የትራንስፖርት አማራጭ እንዲኖረው በማሰብም አልነበረም። እንዲያውም ይህ የሥራቸው ጅምር ነበር። ሌላ የሚፈልጉት ታላቅ ምስጢር እንዳላቸው እርሳቸው ብቻ ነበር የሚያውቁት። «ናቢጋ ጣና» እንቅስቃሴውን በማጠናከር የጥገናና የስምሪት ማዕከሉን ጉርጉራ ላይ በማድረግ ከጉርጉራ ባህርዳር የቀጥታ ጉዞ ማካሄድ ጀምሮ ቀስበቀስ ስምሪቱን ወደ ምዕራብ ጣና ዳርቻ ቁንዝላና ደንገል በር አካባቢዎች በማስፋፋት እስከ 1950ዎቹ ድረስ ለንጉሳውያን ቤተሰቦች ጠቀም ያለ ጉርሻ በመስጠት ሲባዝን ቢኖርም የቡስኪ ልብ አልደረሰም ነበር። በግላቸው ብቻቸውን የሚያምኑትና የሚፈልጉት ታላቅ ምስጢር የውሃ ሽታ ሆነባቸው።

ይባስ ብሎ በዚህ ሁኔታ እስከ 1967 ዓ.ም የዘለቀው የናቢጋ ጣና ኩባንያ ንጉሳዊው አገዛዝ አክትሞ የደርግ መንግስት ሲተካ መስከረም 16 ቀን 1967 ዓ.ም በመንግሥት ተወርሶ «ናቢጋ ጣና» በወታደራዊው መንግስት ቁጥጥር ስር ዋለ። የቡስኪ ተስፋም ሰለለ። ጣና ሐይቅ ያረገዘው የቡስኪ ሃያል ምስጢርም ተዳፍኖ ቀረ። የወታደራዊው መንግሥት ከፍተኛ ቁጥጥር አላሰናዝራቸው ሲል ቡስኪ የጣናውን ምስጢር ለሞርሞርዲኖ አሸጋገሩ። ሞርሞርዲኖ ቡስኪም የጣናውን ምስጢር እንዳረገዙ በአስገድዶ መድፈር ተከሰው እስራት ተበየነባቸው። በኋላም ከኢትዮጵያ ተባረሩ። ተጫርሶ በውርደትና በሽንፈት ጣሊያን የገባው የቤተሰቡ ቅሪት በሲሲሊም ጥሩ ነገር አልገጠመውም። ሞርሞርዲኖ ከዚህ ቤተሰብ ሙሉ በሙሉ ከሚፈጠገጥ የተለየ አማራጭ አልነበራቸውም። ከሲሲሊ ማፍያዎች ጋር ተቀላቀሉ። ሲሲሊ በዚህ ወቅት የማፍያዎች የዕርስ በእርስ ግጭት የሚያምሳት እረፍት አልባ ምድር ሆና ነበር የጠበቀቻቸው። መገዳደልና በቀል የዘወትር የሲሲሊ ተራ ትርኢት ነበር።

ከማፍያዎች ጋር ሲቀላቀሉ የራሳቸውን ቡድን የመመስረትና ዶን የመሆን ህልም ሰንቀው ነበር። ሲሲሊ ውስጥ ለማፍያዎች የሚሰጠውንና ዶን የሚለውን የክብር ስም ለማግኘት ቀላል ባይሆንም እርሳቸው ግን በብልጠት ቀላል አደረጉት። ቀስ በቀስ ሲሲሊ ሞርሞርዲኖ የሚለውን ስም መስማት ጀመረች። አስፈሪው ሞርሞርዲኖ የሲሲሊን ማፍያዎች አቻ ለመሆን የተጠቀሙትን ዘዴ እስከዛሬ ማንኛውም ማፍያ የተጠቀመው አልነበረም። የማፍያዎች አለቃ ሆነው ዶን የሚለውን የክብር ስም ሲጐናፀፉ ጠንካራ የማፍያ ቤተሰብ መሥርተው ነበር። በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ግን አንድም ዘመዳቸው አልነበረም፡ ከአርባ በላይ ሰዎች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ አንድ ታማኝና አደገኛ ጥቁር ሰው መኖሩንም፡ መላ ሲሲሊ ያውቃል። አትዮጵያዊው ዲዎላ የሞርሞርዲኖ ቀኝ እጅ የሆነበትን ምስጢር ግን እሱ ብቻ ነው የሚያውቀው።

ዶን ሞርሞርዲኖ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ቀርቶ ከነበረው ቤተሰብ ውስጥ የተረፉ ብቸኛው ሰው ናቸው። ሲሲሊያውያን የሲሲሊ ራስ ይሏቸዋል። ፓሌርሞም ከመንግሥት ባለስልጣናት ይልቅ ለሞርሞርዲኖ ሰጥ ለበጥ ትላለች። ሲሲሊ ውስጥ ትክክለኛ ገዢዎች ማፍያዎች ናቸው። በማፍያዎች ጥበቃ ውስጥ ያልታቀፈ ማንኛውም ቤተሰብ በአንድ ሌሊት ላለመጥፋቱ ዋስትና የለውም። በማፍያዎች ጥበቃ ውስጥ ሆኖ ለነርሱ የማይገብር ቤተሰብ ይጠፋል።

በዚህ ከፍተኛ ጥበቃ በሚደረግለት የቤታቸው ግቢ ውስጥ ዝር የሚል የለም። የዛሬውን ደስታ በፈንጠዝያ ለማጀብ ከምድር በታች በተሰራው ሌላኛው የቤታቸው ክፍል ውስጥ በእሳት መሞቂያው አቅራቢያ ወይን እየተቀዳ በእቁባቶቻቸውና በሚስቶቻቸው የተከበቡት ዶን ሞርሞርዲኖ ሴቶቹ በሚዘምሩት ለእርሳቸው መወድስ ሲባል በተደረሰው መዝሙራቸው እየተደሰቱ፣ የጥንታዊነትና የታላቅነት ስሜት እየተሰማቸው ነው። ሴቶቹ በቆየ ዘየ ሚዘምሩት የውዳሴ መዝሙርና በወይኑ መጠጥ ስሜታቸው በደስታ ንሯል። ሳቁና የወይኑ ጹቅጹቅታ አስፈንድቋቸዋል።

«....ጌታ ሞርሞርዲኖ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ የሲሲሊው አድባር
አይሞት አያረጅም ፀሐይ ቢጠወልግ ጨረቃ ቢሰበር .....»

ሰምተው አይጠረቁም ይህን መዝሙር። መዝሙሩን ሲሰሙ ወንድነታቸው ይነቃቃል። ሁሉም ነገር ወደንረት ያመራል። ቀንዳቸው ይሾላል። በወይኑ ሞቅታና ዕርቃናቸውን በዙሪያቸው በሚያሻሿቸው የወሲብ እመቤቶች በሚመሰሉ ሴቶች እቶናዊ ገላ በእርካታና በንረት ይሰቃሉ። ምድር ቤቱን የሳቅ ማምረቻ ያስመስሉታል። በወይኑ ጹቅጹቅታና የእሳቱ ነበልባል በፈጠረው ግለት ከእቁባቶቻቸው መሃል ደስ ያለቻቸውን መርጠው ይወስባሉ። ሌሎች ሲያሻሿቸው ከፊሉቹ መዝሙሩን ይቀጥላሉ። የጀመሯት

ካልጣመቻቸው ሌላኛይቱን ጐትተው ጭኗ ሥስጥ ይገባሉ። እሷም ካልጣመቻቸው ሌላይቱን ከኋላ ማጥቃት ይጀምራሉ።

የዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ እድሜ እየገፋ በመጣ ቁጥር የእቁባቶቻቸውና የጠባቂዎቻቸው ህብታቸውን የመቀራመት ሽኩቻም በዛው ልክ እየናረ መጣ። እሳቸው ግን ፀጉራቸውና ቆዳቸው እንጂ ልባቸው ገና አላረጀም። ቅንጣት ታህል ዝንጋኤ አይነካካቸውም። እንዲያውም እያረጁ በመጡ ቁጥር የማስታወስ ብቃታቸው እየበለፀገ መጣ። በአንድ ወቅት ፈረንሳይ ውስጥ ሾርባ ቀርቦላቸው ከተመገቡ በኋላ ሲከፍሉ አስተናጋጁ አምስት ሱ አጥቶ ያልመለሰላቸውን ሁሉ ሳይቀር እስከ ቀኑ እስከ ሰዓቱ ድረስ ያስታውሱታል።

ጠባቂዎቻቸው በኒህ አዛውንት እድሜ ዘልዛላነት መማረር ጀምረዋል። የአዛውንቱን ሞት እየተጠባበቁ እርስ በእርሳቸው አሥራ ስምንቱም ሊጫረሱ ሴራ እየተጠማጠሙ ነው።

ከአስራ ስምንቱ ጠባቂዎች ውስጥ ብቸኛው ጥቁር የሆነው ዲዎላ አያሌው የሴራው ቅድሚያ ተጠቂ ሆኗል። በእርግጥ የቀድሞ ስሙ ሽብሩ አያሌው ነበር። ቀጥሎ ስሙን ፊላ ብሎ ራሱ በመሰየሙ ፊላ አያሌው እየተባለ ይጠራ ነበር። ከኢትዮጵያ ወደ ጣሊያን ከመሄዱ በፊት በሁለት የኢትዮጵያ ከተሞች ኑሯል። አንዱ ባህርዳር ከተማ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቦንጋ ከተማ ውስጥ ነበር። በባህር ዳር ፊላ አያሌው ይባል የነበረውን ወደ ቦንጋ ሲሄድ ደግሞ ሞርሞርዲኖ ባወጡለት ስም ዲዎላ አያሌው ተብሎ ይጠራ ነበር። ቦንጋ ውስጥ ይኖር የነበረው ከኢትዮ ጣሊያን ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ከቀረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ጋር ነበር። ይህ ቤተሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀረበትን ምክንያት በውል ባያውቅም በምኞት ምክንያት እንዳልሆነ ግን ያውቅ ነበር። የዚህ ቤተሰብ አባላት በከፊል ወደ ጣሊያን ሲሄዱ አብሮ ወደ ጣሊያን ተጓዘ። የመርሞርዲኖ ቡኪስ ታማኝ ጠባቂ ሆኖ መኖር ከጀመረ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። የሞርሞርዲኖ ጠባቂዎች ህብታቸውን ለመቀራመት እርስ በእርስ ሲጠላለፉ እሱን ቀድመው ለመጣል እንደተባበሩበት ገብቶታል። ክፋታቸውንና ሴራቸውን ቀድሞ ይነቃባቸዋል። ይህ ወቅት ግን እጅግ ያመረረበት ወቅት ነው። ያመረረበት ምክንያትም ከጉልበት በቀር ብዙም እውቀት ለለሌለው ነው። እድሜ ልኩን ዶን መርሞርዲኖን ሲያገለግል የኖረው በጉልበቱ ብቻ ነው። ታማኝ ጠባቂያቸው ያደረጉት ደደብ በመሆኑና ባለመማሩ መሆኑን በአለቀ ሰዓት ደርሰበታል። «እርስዎን ለመግደል ሲዘጋጅ ደርሰንበታል» በማለት ሌሎች ጠባቂዎች ስላሴሩበት ጨለማ ክፍል ውስጥ ሲደበደብ ሰንብቶ የወጣው በቅርቡ ነው። ከዚህ ሰፊትም ብዙ ጊዜ በዚህ ጨለማ ቤት ውስጥ ተደብድቧል። በንዴት ዓይኑ የቀላበት ምክንያት የሌሎች ጠባቂዎቻቸውን ውንጀላ እንደ እውነት ተተብለው የዱላ ውርጅብኝ ባስወረዱበት ዶን ሞርሞርዲኖ የጭካኔ በትር ምክንያት ነው።

ዲዎላ መልከ ጥፉ ነው። መልከ ጥፉነቱንም ይወደዋል። ጥቁረቱ የጀበና ያህል ከመሆኑም በላይ ፊቱ በጩቤ በተሸነታተሩ መስመሮች የተሞላ ነው። አንድ ዓይኑም በድብድብ ምክንያት ፈርሟል። የፊት ጥርሶቹም በድብድብ ወላልቀው ከዓመት አንዴ ሲስቅ የሚታይ ቀይ ድዱ ብቻ ነው። በረጅም ቁመቱ ልክ የለበሰው ግዙፍ ሥጋ ጠንካራና የማይበገር ሰው አስመስሎታል። አመድ የሚያደርጉ ከንዶቹን የቀመሱ ብዙዎች የመኖራቸውን ያህል በተንኮል የጉመዘዙ ፅዋዎችን የጋቱትም አያሌ ናቸው። መልከጥፉው ዲዎላ 'ሁሉም የራሱ ቆንጆ ነው።' ብሎ ሲያምንም 'ሁሉም የራሱ አምባገነን ነው' ይላል። ስለዚህም ከሌሎች የወረሰውን ጭካኔ በራሱ ላይም ይፈፅማል። ሲናደድ ደረቱን በጩቤ ይሸነታትረዋል። የሚያውቃቸው ክፉ ሰዎች በበለጡ ክፉዎች ሲተኩ አይቷል። ክፉዎቹ ሲወድቁም ክፋታቸው ወደ ውስጡ የገባበት ይመስል ክፉ ሰው አድርጎታል። ዲዎላ በጠላቶቹ ፊት ብልጣብልጥ ሆኖ ለመታየት አይሞክርም። ይልቁንም ቂላቂል ለመምሰል የማያደርገው ጥረት የለም። ስለ ማንኛውም ነገር ያለውን ፍላጎት በግልጽ አያንፀባርቅም። ፍላጎቱ በሙሉ ለማንም ግልጽ ሆኖ አያውቅም። በቀሉም ቀጥተኛ አይደለም። ሰዎች ሲበቀሉት የሚበቀላቸው በተበቀሉት መንገድ አይደለም። ቢደበድቡት ወዲያው መልሶ አይደባደብም። ዘግይቶ የበለጠ ይበቀላቸዋል።

ከዚህ በፊት ጨለማ ክፍል ውስጥ በዶን ሞርሞርዲኖ የመግደል ሴራ ተጠርጥሮ ሲደበደብ በነበረበት ወቅት የግራ እጁን ትንሽ ጣት በጉጠት ቆረጡበት። በኋላ ግን የሀሰት ውንጀላ መሆኑን ስለደረሱበት በምርመራውም ወቅት በውሸት መመርመሪያ መሳሪያቸው ስላረጋገጡ ፈቱት። ከተፈታ በኋላም ዶን ሞርሞርዲኖ የበቀል ስሜት ፊቱ ላይ አላነበቡበትም። ላንብብ ቢሉም በውሸት መመርመሪያውና አእምሮ ላይ በሚገጠመው ረቂቅ መሳሪያ ገጥመው ካልመረመሩት በስተቀር ፊቱ ላይ የሚያነቡት ነገር አይኖርም። የዲዎላ ፊት ሁል ጊዜም ያው ነው። ስርዝ ድልዝ የበዛበት ጽሁፍ፣ ከሚመስል ፊቱ ላይ ምንም ነገር ማንበብ አዳጋች ነው። ሞርሞርዲኖ ራታቸውን በሚመገቡበት ወቅት ከሚመገቡት የሥጋ ሾርባ ውስጥ ቆራጣ የሰው ጣት አግኝበት። የበሉት ሁሉ ግልብጥ ብሎ ወጣ። ሲያስታውኩም የሆድ ዕቃቸው በሞላ በአፋቸው የተዘረገፈ ነበር የመሰላቸው። አንጀታቸው እስኪወጣ አንቋረሩ። ይህ ሲሆን ዲዎላ በሩ ላይ ቆሞ ከሌሎች ጋርዶች ጋር ሆኖ ይመለከት ነበር። ከዚህ በላይ በቀል እንደሌለ ተረዳ። ዶን ሞርሞርዲኖ ውጫዊ አካሉን ሲያስደበድቡት እሱ ደግሞ ውስጣዊ አካላቸውን ቀጠቀጣቸው። በትንሽ ጣቱ ሆዳቸውን አሳሰለው። ረካ። ሞርሞርዲኖ ጋርዶቻቸውን በሙሉ አስጠርተው ይህን አሰቃቂ ሁኔታ ማን እንዳደረገባቸው ጠየቁ። ጋርዶቻቸው በሙሉ «አላደረግንም» ሲሉ ሽምጥጠው ካዱ። ዲዎላም አላደረኩም ብሎ ድርቅ አለ። በኋላ ጣቱ

የጥቁር ሰው ጣት መሆኑ ተደረሰበት። ሞርሞርዲኖ ወጣቸው ውስጥ ያገኙት ጣት የጥቁር ሰው ጣት ሆኖ በመገኘቱም ለሁለተኛ ጊዜ ከመጀመሪያው የባሰ አስታወኩ። የሌሎች ነጭ ጋርዶች ጣቶች ተቆጥረው ሙሉ ሆነው ተገኙ። ጣቱ የዲዎላ ባሪያው መሆኑ የተደረሰበት ትንሽ ጣቱ በእስር ቤት እያለ ምስጢር እንዲያወጣ በጉጠት መጉንደሹ ከተረጋገጠ በኋላ ነበር።

ዲዎላም ጣቱን ካደ። «የኔ አይደለም» ሲል። ብሽቅ አደረጋቸው። «አንተ አረመኔ ባሪያ ጣትህን ትክዳለህ?» አሉ ሞርሞርዲኖ መልሰው በፍልጥ እያስደበደቡት። «እዎ እክዳለሁ።» አለ ዲዎላ። «ገና ሁሉንም ጣቶቼንና እኔንም ጭምር እክዳለሁ። ለርስዎ ጌትነትና ለቆየ ወዳጅነታችን ስል።» ይህን ሲል ቁጣቸው ሙሽሽ ብሎ ጠፋ። ለጌትነታቸው ሲል ጣቱን የሚያበላቸው ሌላ ማን አለ፣ በንዴት ሳቅ ተንፈቅፍቀው ማሩት።

ዲዎላም አስከትሎ ይህንን ተናገረ። «ከዳክዬ ሥጋ የእኔ ሥጋ አይሻልም፣ ዳክዬዎች ትል ይበላሉ። በውሃ ውስጥ የሚዝለገለጉ ሙታኖችን ከሚበሉ ዳክዬዎች ሥጋ የሰው ሥጋ አይሻልም፣ ሰው ቅዱስ ነገሮችን ይበላል። ስለዚህም ቅዱስ ነው። በቅድስና ደግሞ የሮም ጳጳሳትን የሚስተካከል የለም። አይደለም ጌታ ሞርሞርዲኖ?»

«ዝጋ! አንት ዝጋታም ባሪያ።» አሉ ሞርሞርዲኖ። የሮም ጳጳሳትን ስለሚጠሉ ቅዱስ ስላላቸው ተናደው። ዲዎላ ግን ንግግሩን ቀጠለ። «ስለዚህ» አለ ዲዎላ።.....«ብፁአንና ቅዱሳን የሆኑትን የሮም ጳጳሳትን መብላት እንጀምራለን።» አጨበጨቡለት ዶን ሞርሞርዲኖ። ጳጳሳቱን ስለሸነቆጠላቸው።

«ያንተን ጥቁር ጣት ግን አንበላም» አሉት። «አንተ ባሪያ የተናገረከው በቂ ነው።»

«ግዴለምትም ጌታ ሞርሞርዲኖ ቆዳየ ጥቁር ቢሆን ውስጤ ቀይ ነው። አጥንቴ ደግሞ ነጭ።» ራሱን ወደሳቸው ማቀራረቡ ነበር።

ዲዎላ መከፋቱንና በቀሉን የሚገልፅበት መንገዱ ብዙ ነው። ጉምዛዛና ቅጠል የበዛበት ሻይ ይወዳል። ይህን እየጠጣ ንብ መጥታ ብርጭቆው ጠርዝ ላይ ብታርፍ በማንኪያ ገፍቶ የፈላው ሻይ ውስጥ ይከታትና ልትወጣ ስትዳክጥ ማየትና በማንኪያ እዛው ሲያማስላት ያስደስተዋል። ደስ ሲለው ደግሞ ቀይ ድዱን እንደ ደመራ ፍም ግልጠጥ አድርጉ በዝግታ ይስቃል።

ደሞ አንድ ቀን ደግሞ በዶን ሞርሞርዲኖ ግቢ ውስጥ ካለት ርግቦች አንዷን ይዞ ክንፍዋን በመቀስ ቆረጠባት። ክንፏን ሲቆርጥ ያዩት ሌሎች ነጭ ጋርዶች ወደ ሞርሞርዲኖ እያዳፉ አቀረቡት።

«አንተ ባሪያ ምናባክ ቆርጠህ ነው ክንፏን የቆረጥክባት?» አሉት።

«ምናጠፋሁ ታዲያ ጌታ ሞርሞርዲኖ?» አለ ዲዎላ::

«ምናጠፋሁ ይለኛል ደግሞ ይህ ብስብስ ባሪያ! በለው! አሉ::» አንዱን አንቆ የመጣውን ጋርድ::

«እኮ ምን አጠፋሁ?»

«እንዴት ክንጁን ትቆርጥባታለህ?»

«ስላስቸገራት እኮ ነው ጌታ ሞርሞርዲኖ::» አለ ዲዎላ::

«ይህች እርግብ በዚህ ግቢ ውስጥ ስትኖር አንድም ቀን ስትበር አይቻት አላውቅም:: እዚሁ ትውላለች:: ምግቧን እንሰጣታለን:: እዚሁ ታድራለች:: ታዲያ..... እርግቧ ክንጁን ካልበረረችበት ከትርፍ ገላ በምን ይሻላል?» ሞርሞርዲኖ ከጆሮ ግንዳቸው አካባቢ ለብቻው በቅሎ የተንጠለጠለ ትርፍ ገላ ስላላቸው እሱን በአሽሙር ሲነካቸው ጭምር ነበር::

«እርግቧ ክንጁን ካልተጠቀመችበት ቆርጠን ለእባብ ብንቀያለው አይሻልም? ሁል ጊዜ በሆዱ እየተሳበ ከሚማቅቅ?» ስለ እባብ በልጅነቱ የሰማውን አፈ ታሪክ ጨለፈላቸው:: «እየውልዎት ጌታ ሞርሞርዲኖ እባብ እንደ ጊደር አራት እግር ነበረው አሉ:: ታዲያ ለአዳምና ለሔዋን በለስን አሳያቸው:: አዳምና ሔዋን እውቀት የሚገልፀውን ዛፍ በሉ:: እነሱ በበሉ እባብ ተረገመ:: ያውም እኮ እውቀት የሚገልፀውን ዛፍ በማሳየቱ ነው:: በእርግማኑ ምክንያትም አራት እግሮቹ ሆዱ ውስጥ ገብተው በደረቱ መሳብ ጀመረ:: የሮም ጳጳሳት እንደሚሰብኩት የአዳምንና የሔዋንን እርግማን ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሲሸርላቸው ለእባብ ግን እስከ አሁን የተሰቀለለት ክርስቶስ የለም:: የነሱ እርግማን ሲሻር እባብ ግን እስከ አሁን አራት እግሮቹን አጥቶ በደረቱ እየተሳበ ይኖራል:: ጌታ ሞርሞርዲኖ! እርስዎ ፍትሐዊ ነዎት:: አይደለም እንዴ ጌታ መርሞርዲኖ?»

«ነኝ» አሉት:: አውቆ ሲጃጃል እየገረማቸው ሁሉም ያዳምጡታል:: ይህን ብቃቱን ባይነግሩትም እጅግ ያደንቁለታል::

«እኮ! እኔም እርሱን አውቃለሁ:: እርግጠኛ ነኝ እርስዎ ክርስቶስን ቢሆኑ ለእባቡም ይሰቀሉለት ነበር:: ቢያንስ አራት እግሩን ይመልሱለት ነበር:: እስኪ ይታየዎት ጌታ ሞርሞርዲኖ! እንዴት ፈጥሮ በደረቱ እያስዓዘ ያሰቃየዋል?! እሺ ከቀጣም መቅጣት ያለበት የመጀመሪያውን ተንኮለኛ እባብ መሆን በተገባ:: በለሱ ድረስ ወስዶ እንዲበሉ የጋበዛቸውን እባብ እስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቢቀጣው ባልከፋ:: እኔም ያለጥፋቴ እየተቀጣሁ ነውና:: ግን አንድ እባብ በበደለ እንዴት የእባብ ዘር በሙሉ ባልሰራው በደል ይቀጣል እንዴት ምድረ እባብ እስከዛሬ መከራውን ያያል?»

«መናገር የፈለከውን ቅልብጭ አድርገህ ተናገር አንት መሽሎ ባሪያ:: ይልቅስ መዘላበድ የዘርህ ነው:: ምን ዙሪያ ጥምጥም

ያስኬድሃል?» አሉት ሞርሞርዲኖ:: አውቀው መነካካታቸው ነው ብዙ እንዲለፈልፍ::

«ይህ እኮ ነው ችግሩ ጌታ ሞርሞርዲኖ! አያት በበደለ ልጅን መቅጣት:: አዎ! አባቴ ዙሪያ ጥምጥም ይጓዝ ነበር:: የሱም አባት ዙሪያ ጥምጥም ሊጓዝ ይችል ይሆናል:: እኔን ግን በእነሱ ዙሪያ ጠምጥመው አይስደቡኝ:: እኔ የርስዎ ቅን አገልጋይ ነኝ:: ነገሬም ቅልብጭ ያለ ነው:: የተናገርኩትም ስለ ፍትሐዊነት ነው:: እርግቧ ክንጁን ካልበረረችበት ተቆርጦ በደረቱ አፈር ድሚ ለሚግጠው እባብ ይሰጠው:: ምናባቷ! ወይም ከጳጳሳት አንዱ ስለእባቦች ኃጢአት ይሰቀልና እባቦች እግሮቻቸው ይመለሱላቸው:: አበቃሁ::»

«አጨብጭቡለት!»አሉ ሞርሞርዲኖ ጳጳሳቱን ስለለከፈላቸው ተደሰተው:: ዲዎላ ምን መናገር እንዳለበት ያውቃል::

ዲዎላ የኒህ ሰው ሁነኛ ጠባቂ ነው:: ሐብታቸውን ለመቀራመት ሲሳፈጡ እርሱ ግን ይህ ፍላጐት እስከ አሁን በግልፅ አልተንፀባረቀበትም:: ከሁለት ዓመታት ጀምሮ የሚወስደው ሥልጠና ውስብስብ ሆኖበታል:: ከወሰዳቸው ስልጠናዎች አንዱ የምንኩስና ስልጠና ሲሆን የሚሄድበትን ግዳጅ ለመወጣት የምንኩስናውን ሥልጠና በደንብ ተከታትሏል:: ከግዳጅ በኋላ ስለሚያገኘው ከአገልጋይነት ወደ ጌትነት ስለሚያደርሰው ታላቅ ምስጢርም እያሰላሰለ ነው:: ሁሉን ነገር የግሉ የሚያደርግበትን መንገድም እየቀየሰ ነው:: ይህን ለማሳካትም ብዙ እውቀት ባይኖረውም ድብቅ ብልጠትና ጉልበት አለው:: አጋር ባይኖረውም ብቻውን በምድርና በሰማይ መካከል የቆመ ጠንካራ ምሰሶ አድርጐ ራሱን ይቆጥራል:: ሙሉ ቢጫ የምንኩስና ልብስ ተሰፍቶለታል:: የመነኩሴ ቆብም ተዘጋጅቶለታል:: በዶን ሞርሞርዲኖ የግል አውሮኘላን ወደ ኢትዮጵያ ተጉዞ ባህርዳር ከተማ የሚደርስበት ቀን ተወስኗል:: ከዚያም የሚሄድበትን ከእርሱና ከሞርሞርዲኖ በቀር ማንም አያውቅም::

፲

ባህርዳር፡ኢትዮጵያ

ሰማዩ የደመና በርናሱን ደርቧል። ጥልማሞት መስሉ በጥቁሩ ደመና ቀኑን አጨልሞታል። ሰማይና ምድሩ በጭጋግና በጉም አውታር ተያይዟል።

የባህርዳር ከተማዋ ፀሐይ በጠቋቆረውና በጨላለመው ሰማይ ደን ውስጥ የደመና ቆቧን ደፍታ መንናለች። ሰማዩን ከሚያርሰው ብልጭታ በቀር የብርሃን ፍንጥቅታ አይታይም። ሰማዩ በመብረቅ ሲታረስ 'ጪርደድ' በሚለው ነጐድጓድ ምድሩ ይንቀጠቀጣል። ህይወት ይደነብራል። ድንብሸ ...ድንብሸብሸ...በሚለው አስፈሪ ጉርምርታ ተራራዎች ያቃስታሉ፤ አለቶች ይቃትታሉ። ብልጭ ድርግም! ከሚለው ሰማይ ማህፀን የተወለደው ጥቁር ደመና ይነፋረቃል። መብረቁ ሰማዩን 'ጪርደድ' 'ድርግምግም' 'ፍግምግም' ሲያደርገው ህይወት ያማትባል። ውሽንፍሩ የባህርዳርን ዘንባባዎች ያስጮሃቸዋል። በወጀቡ ዛፎች ይሰግዳሉ። አበባዎች ይረግፋሉ። ቅጠሎች ይቀነጠሳሉ። አሮጌው ሰማይ መቋጠር አቅቶት ያፈሳል።

አስራ ሶስተኛዋ ወር ጳጉሜ ከባተች ሶስተኛ ቀኗ ነው። የባህርዳርን ውበት ሶስተኛዋ የጳጉሜ ቀን አጨፍግጋታለች። የወራቶች ቅንጣቢ ጳግሜ ቅንጣቢዋን ከነሐሴ በተዋሰችው የአንድ ቀን የመብረቅ እሳት ትጠብሳለች።

በወጀብና በውሽንፍር በታጀበው ዶፍ ዝናብ ውስጥ ጥቁር ካፖርት በቁመቱ ልክ የለበሰ ባለጊታር ሰውዬ በባህር ዳር ከተማ አውራ ጐዳና ታየ። ጥቁር ባርኔጣውን ውሽንፍር እንዳይነጥቀው ከአንገቱ ጋር አያይዞ ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ወደ አባይ ማዶ በሚወስደው አውራ ጐዳና ሲጓዝ የለበሰውን ጥቁር ካፖርት ነፋሱ እያንሳፈፈው ነበር።

በዝናቡ ውስጥ እርቃናቸውን የሚፈነጩት ህፃናት የባለጊታሩን ትኩረት ሳቡት። ዶ/ር ሚራኾን። ህፃናቱ ዝናቡ ውስጥ እርቃናቸውን እየቦረቁ እየተሳሳቁ «ሩፋኤል...ሩፋኤል...ሩፋኤል ...ሩፋዬ.... ከሸንብራው ጐታ ስደደኝ ጌታዬ ...» ይላሉ።

ጳጉሜ ሦስት ቀን መሆኑን ያወቀው በህፃናቱ ዜማ ነበር። ጳግሜ ሦስት የቅዱስ ሩፋኤል በአል ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚከበር ያውቃል። በዚህ ቀን የኢትዮጵያ ሰማይ ዝናብ እንዲያወርድ ይፀለያል። ጳጉሜ ሦስት ቀን የሩፋኤል አለት የሚዘንብ ዝናብ ጠበል ነው ተብሎ ስለሚታመን። በዚህ ዕለት ህፃናት ልብሳቸውን አውልቀው ዝናቡ ውስጥ ይፈነጫሉ። የዓመቱ ፀሎት ሁሉ ተሰብስቦ ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ዕለት ነው ይላሉ። ልክ የፖስታ ቤት ሠራተኛ ደብዳቤዎችን ሰብስቦ ለተላከላቸው እንደሚያድል መልእክ

ሩፋኤልም እንዲሁ የዓመቱን ፀሎት ሰብስቦ ለእግዚአብሔር ያሳርጋል የሚባለውን ብሒል የህፃናቱ ቡራቃ አስታወሰው።

የዝናቡን ፀጥታ ተከትሎ ከመንገዱ ዳር ሙዚቃ ቤት የተከፈተ ሙዚቃ ከጆሮው ሲደርስ ርምጃውን ገታው። ዝናቡ ከቆመ በኋላ በባህርዳር የመንገድ ዳር ቦኮች ውስጥ ቁልቁል ከሚነዶለዶለው የጐርፍ ድምፅ ጋር የተከፈተው ሙዚቃ እየተስረቀረቀ ከጆሮው ሲደርስ ነሸጠው። የቦብ ማርሌ የነፃነት ዜማ። ልብን የሚሰርቀው የቦብ ማርሌ ሙዚቃ ጊታሩን አስመዝለጠው። ሙዚቃውን በጊታሩ መንገድ ላይ እየሄደ ሲያጅበው ህፃናቱም ዙሪያውን ከበው መጨፈር ጀመሩ። ጉልማሶችና ጉረምሶችም በባለጊታሩ ጊታርና በቦብ ሙዚቃ ተጐትተው አውራ ጐዳናውን ሞሉት። በቦብ ማርሌ የቤዛነት ዜማ ፈነጩ። ዶ/ር ሚራኾ ልዩ ደስታ ተሰማው። አብዮት የሚመራ መሰለው። ነፃነትን የሚያጭረው የቦብ ሙዚቃና አርነት የወጣ ከሚመስለው የጐርፍ አወራረድ ጋር የሁሉንም ልብ ሰረቀ።

Redemption Songs
Old ;pirates, Yes, they rob I;
Sold I to the merchant ships;
Minutes after they took I,
From the bottomless pit.
But my hand was made strong
By the hand of the Almighty
We forward in this generation
Triumphantly
Won't you help to sing
These songs of freedom?
'Cause all I ever have;
Redemoption songs:
Emancipate your selves from mental slavery;
None but ourselves can free our minds.
Have no fear atomic energy
'Cause none of them can stop the time.
How long shall they kill our prophets.
While was stand aside and look? Ooh!
Some say it's just a part of it.
We've got to fulfill the book.
Won't you help to sing
These songs of freedom?
'cause all I ever have.
Redemption songs .....

ለህፃናቱ ሰላምታ ሰጥቷቸው በጭብጨባ ከተሰናበቱት በኋላ በረጅሙ የአባይ ድልድይ ላይ ተሻግሮ ወደ አባይ ማዶ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ገሰገሰ።

አባይ ማዶ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሊደርስ ሲቃረብ የምሽቱን ፀሎት እየሰማ ከአንዲት የመንገድ ዳር ካፌ ተቀምጠ ቀጣይ እንቅስቃሴውን በሚመለከት ማሰላሰል ቀጠለ:: ወደ መቃብር ቦታው ለመግባትና ከአባ ሲርጋጋ መቀብር ውስጥ የተቀመጠለትን ቀጣይ ትዕዛዝ ለማግኘት ምዕመናኑ ከቤተ ክርስቲያኑ እስኪወጡ እየጠበቀ::

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ በፀጥታ ተውጦ ወደ ጆሮው የሚገቡ ድምፆችን አዳመጣቸው:: ከባህርዳር ወደ ጉንደር የሚጓዙ መኪናዎች ድምፅ፣ የጉጃም ዘፈ ያለው አማርኛ የሚናገሩ ሰዎች፣ የበጅምድር ዘፈ፣ የጎንደር ዘፈ፣...የሚናገሩ ሴቶችና ወንዶች ድምፅ:: ይህን ሲሰማ የጉጃምና የጉንደር ኩታ መጋጠሚያ ቦታ ላይ መሆኑን ተረዳ:: አባይ ማዶ::

ሌላ ድምጽ ደግሞ ከጆሮው ገባ:: በርቀት ካለ መስጂድ የሚደርስ አዛና:: «አላህ ወአክበር ...»

በመሃል ደግሞ የጎሮቴስታንት መዝሙር ከጆሮው ጥልቅ አለ::

«ሥራዬን የሠራህልኝ
መንገዴን ያቀናህልኝ
አማኑኤል ከፍ በልልኝ
የኔ ጌታ ከፍ በልልኝ ...» ከመዝሙሩ ጋር የብዙ ሰዎች ድምፅ አብሮ ይሰማዋል::

መዝሙሩ ጋብ ሲል ደግሞ የሰባኪው ድምፅ ተሰማው::

«...ሃሌ ሉያ!! ኢየሱስ ጌታ ነው!!»

«አሜን!!» የብዙ ሰዎች ድምፅ ተከተለው::

«ሻላላማንዶ .....»

«እሰይ የኔ ጌታ»

በመሃል ደግሞ ሌላ ድምጽ ተሰማው:: ሙዚቃ

«.... ላፍ አርጋት
ላፍ አርጋት.....» የይርዳው ጤናው ዘፈን::

ከዛ ደግሞ የለማኞች ፊጩኸት::

«ስለ አይነ ብርሃን ... ስለ ሙሉ አካል... ራቴን ...» ይህን ሁሉ አይኖቹን ገጥሞ አዳመጣቸው:: ደግሞ ሌላ ድምጽ ወደ ጆሮው መጣ:: ከአባይ ማዶ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የሚወጣ የምዕመናኑ የፀሎት መዝጊያ መዝሙር::

«እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረን»

ቄሱ ፀሎቱን ሲያሳርጉ ሰማ::

«አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ስጠን ...»

መንገዱን የሞሉት ነዳያንም ማላዘናቸውን ቀጠሉ::

«...ስለ ዓይነ ብርሃን ..»

«...ስለ እመቤቴ ....»

«...ስለ ቸሩ እግዜር ...»

«ጣል ጣል አርጉልኝ ወገን እምስትም አስርም!»

«ሰርቼ ማልበላ ...ራቴን እባካችሁ.....»

ሌላ ደግሞ የአካባቢውን መንገደኛ ትኩረት የሳበ ለየት ያለ ለማኝ በአካባቢው ተከሰተ::«ስለ መንግስቱ ኃይለ ማርያም» እያለ የሚመፀወት ለማኝ:: «ስለ መንግስቱ ኃይለ ማርያም.....» ለማኙ አንድ እግሩ ጭኑ ላይ የተቆረጠ ሲሆን ፊቱ ላይ የጀግና ስሜት የሚነበብበት አይነትና በመለመኑም የማያፍር ይመስላል:: የመንገደኛውን ትኩረት ከመሳቡም በላይ የሚጣልለት ገንዘብ መሬት ላይ ያነጠፈውን አዳፋ ልብስ እያለበሰው ነው::

«ስለ ጀግናው መንግስቱ ኃይለ ማርያም እያላችሁ ጣል ጣል አርጉልኝ ወገን! ስለ መንግስቱ ኃይለ ማርያም:: ስለ ጀግናው የእናት አገር ልጅ:: ወገን.....የዛሬ አስራ አምስት ዓመት ጦርነቱን በቁርጥ የተዋጋሁ ጀግና ነበርኩ:: ተመትቼ ወደኩ:: ለእናት ሀገር አካሌን በመገበሬ አልቆጭም ..... ተመፅዋች የሆንኩት አካሌን ለእናት ሀገር ሰጥቻት ነው:: በሚቀጥለው ምርጫ ደግሞ ድምጼን እሰጣታለሁ:: ወገን ጣል ጣል አርጉልኝ:: ስለ መንግስቱ ኃይለ ማርያም....» ከድሮ መፅሔት ላይ የገነጠለውን ባለቀለም የመንግስቱ ኃይለ ማርያምን ፎቶ ግራፍ ላብ ባጠቆረው ካርቱን ዙሪያውን ጠርዞ ደረቱ ላይ አንጠልጥሎታል::

ህዝቡ የመንግስቱ ኃይለ ማርያምን ፎቶ ለረጅም ሰዓት ቆሞ ያያል:: ላይጨልም:: ብርሃን ላይጠፋ ፎቶ ግራፉን እስከ ለማኙ ደረት ለማየት ይጋፋል:: «ስለ ጀግናው የእምዬ ኢትዮጵያ ልጅ ስለ መንግስቱ ኃይለ ማርያም እያላችሁ:: ወገን ጣል ጣል አርጉልኝ»

ሚራኾር ሻንጣውን እንደያዘ ግርግሩ መሃል ገብቶ አስደናቂውን ለማኝ ያያል:: ሚራኾር ከስንት ዘመን በኋላ የጦርነቱ ወቅት ትዝ አለው::

«ስለ ጠቅላይ ሚንስትሩ በለኝና መቶ ብር ልስጥህ» አለው አንድ ነገረኛ የሚመስል ሲጋራ የሚያጨስ ሰውየ ድምጹን ከፍ አርጎ ከህዝቡ መሃል እየተጋፋ ዘልቆ::

«ቂጥህን ጥረግበት» አለው ገላምጦ:: «በስመ· የምለምንበት ሌላ ሰው መች አጣሁ....» ሌጥ አሮጌ ስዕል እያወጣ:: «ስለ አጤ ቴዎድሮስ...ስላንድ ለናቱ...ስለ ሽህ ጠላቱ....ከአንግሊዝ በመድፍ ከሱዳን በጊንጥ ተዋግቶ ስለ ሰንደቃችን ራሱን ስለ ሰጠው ስላንድ ለናቱ...ስለ ሽህ ጠላቱ..... »

«ስለ ኢየሱስ በለኝና ሃምሳ ብር.....» አለው ሌላ ወጣት እየሳቀ::

«ያለ ሥራ መቆም ክልክል ነው» አለው ለማኙ።..... ሳቅ በረከተ። «ይኸው የኔ ኢየሱስ.....» ሲል የአጼ ቴዎድሮስን ስዕል ከፍ አርጎ አሳየው። ሌላ ረዥም ሳቅ።

«ስለ ጀግናው መንግስቱ ኃይለማርያም። አሁንም 'ኢትዮጵያ ትቅደም ሆዳም ይውደም' የምትሉ ጣል ጣል አድርጉልኝ ወገን»

ሚራዥ ተቀምጠላት ወደ ነበረው ካፌ ተመልሶ በለማኙ ዙሪያ የተሰበሰበውን ህዝብ እየተመለከተ ባካባቢው የሚወድቀውን ጨለማ ይጠባበቅ ጀመር።

አንድ ወጣት በለማኙ ዙሪያ ከተሰበሰበው ህዝብ መሃል ወጥቶ መጣና ሚራዥ ከተቀመጠበት ጥግ ተቀመጠ።

«አይገርምም?» አለ ለብቻው ወደ ትርምሱ እየተመለከተ አጭሩ ወጣት።

«ምኑ?» አለው ሚራዥ እሱን ያናገረው መስሎት።

«ለማኙ» አለ ወጣቱ ወደ ሚራዥ ዞሮ። ከዛም ወረቀትና ብዕር ከጃኬቱ ኪስ አውጥቶ መፃፍ ጀመረ።

«ግጥም ትወዳለህ?» አለ ዕፎ ሲጨርስ ወደ ሚራዥ ዙሮ።

«በጣም እንጂ! ግጥም ተመስጦን እስከ ሰባቱ ሰማያት የሚያመጥቅ የጥበብ ሰረገላ ነው» አለው ሚራዥ ወደ ፃፈው ወረቀት እየተመለከተ። «ገጣሚ ነህ እንዴ?»

«ነበርኩ።» አለ አጭሩ ወጣት።

«እንዴት ነበርኩ?» አለ ሚራዥ ተገርሞ።

«ነበርኩ። ግን ግጥሞቼን የሚያዳምጥልኝ አጣሁ። ሀገሬ ወጣቶችንና ልጆችን በቀላሉ አትቀበልም። ቅኔዬን ለማስደመጥ ሰባ ዓመት እሰኪሞላኝ እየጠበኩ ነው። ያኔ ብስብስ ግጥም ቢሆንም ያዳምጡኛል። ኢትዮጵያ ውስጥ ለመደመጥ ከፈለግህ መሸበት አለብህ። እዚህ አገር ከአስተሳሰብህ ይልቅ ሽበትህ ይከበራል። ሆኖም.....ሽበት የእርግና ምልክት እንጂ የብስለት መለኪያ አይደለም። ሽበት የጠወለገ ፀጉር ነው። ራስህ ላይ መታየት ያለበት አንጐልህ እንጂ ሽበትህ መሆን የለበትም። የሽበት የሽበትማ ድንጋዮችም ይሸብታሉ። ይህቺ ችጋራም ሀገር ችጋራም ያደረገችኝ ሳያንሳት ደግሞ እንዴት ባይሆን ግጥሜን አታዳምጠኝም?....»

«ሀገሪቷማ ችጋራም አይደለችም....» ሚራዥ አቋረጠው።

«ናት እንጂ። ሀገሪቷ የምልህ እኮ ህዝቦቿን ነው። ተራራዎቿና የሚፈሱ ወንዞቿማ ምን አርገውት? ህዝቦቿ እንጂ! ጆሯቸው ላይ የተኙ ህዝቦቿ እንጂ ችጋራሞች። ከኔ ግጥም ውስጥ እኮ ከችጋራቸው ነፃ የሚወጡበት ሀሳብ ሊኖር ይችላል። ከቅኔዬ ውስጥ እኮ ተፈልቅቆ የሚወጣ አንዳች መፍትሔ ይኖራል። ግን አያዳምጡኝም። ጆሯቸው ላይ ተኝተዋል። ግጥም ድሮ ቀረ ይሉኛል። አዲስ ፊት አዲስ ሰው ማየት አይፈልጉም። ሁል ጊዜ የአንድ ሰሙ ስም ያወድሳሉ። አንድ ሎሬትና ባለቅኔ አላቸው።

እሱም በጥረቱና በብርታቱ በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ በመግባቱ እንጂ እነሱ ስሙን አልሰጡትም። ዘለዓለም እሱን ግጥሙን ያልሰሙለት መጽሐፉን ያላነበቡለት ሁሉ በስሚ ስሚ ያወድሱታል። ሲወደስ ስለሰሙ ብቻ ያወድሳሉ። ያወድሱት እኔም አወድሰዋለሁ። ግን ሌላም ሰው መቀበል አለባቸው። እኔንም ሊቀበሉኝ ይገባል። ወጣቶቿን ካልተቀበላቸው የወደፊቷ ኢትዮጵያስ? ...»

«ማነው እሱ ...»

«እንድ ግጥሙን ልበልልህና እኔ ስሙን ሳልነግርህ ሰውየውን ታውቀዋለህ።»

«እስኪ እባክህ ግጥሙን በልልኝ።» ወጣቱ ደስ በሚል ቃና የሎሬቱን ግጥም ያነበንብለት ጀመር።

«ሰቆቃወ ጴጥሮስ»

ኣየ፣ ምነው እመብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት
ምነው ቀኝሽን ረሳሻት?
እስከ መቼ እንዲህ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን ሰቀቀንዋን፣ጣሯን ይበቃል ሳትያት? ...»

መቶ አምስት ስንኞች ያሉበትን ይህን ረጅም ግጥም እንደ ዥረት አፍሶለት ሲጨርስ ገጣሚው በአድናቆት ተመለከተው። አነባበቡ ማረከው። ከዚህ ጀርባ ግን ገጣሚው ሌላ ተልእኮ እንዳለው ተረዳ። ከዚህ ግጥም ጋር የተጣበቀ ምስጢር እንዳለ ያውቃል። ገጣሚው የበለጠ ጥርጣሬውን እናረበት። ያቃተው ግጥሙንና ከጀርባው በልጅነቱ የተነቀሰውን በ 'ቶ' ቅርጽ የተሠራውን ባለጉጥ መስቀል ማገናኘት ነው። ፍንጭ አጣ። በባለጉጡ መስቀል ላይ የተፃፉት ቁጥሮች ምናልባት በግጥሙ ውስጥ የተካተቱ ቃላት ብዛት መስለውት ቃላቱን ከሜሮዳ ጋር ቆጥረዋቸው ነበር። የቃላቱ ብዛት ግን 497 ሆነበት። እሱ ጀርባ ላይና በተመሳሳይ መልኩ ብራናው ላይ የተሳለው ባለጉጥ መስቀል ላይ ያሉት ቁጥሮች ግን የትየለሌ ናቸው። $54_{4}\ 9_{5}\ 10_{6}\ 29_{23}\ 52_{7}\ 33_{2}\ \ddot{0}\ddot{0}\ddot{0}\ 97_{8}\ 98_{123}\ 9_{6}\ 10_{67}\ 40_{567}\ 88_{123456}$። 'ታዲያ ይህን ያህል ቁጥር ምንድን ነው' ወይስ ልዩ የሒሳብ ቀመር ነው? እንዲህ አይነት የሒሳብ ቀመር ደግሞ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።' እያለ በውስጡ እየተብሰለሰለ ገጣሚውን በነዚህ ጥያቄዎች መሀል እየተመለከተው ሳለ «የግማደ መስቀሌን ጉጥ እታገስበት አላጣም!!» የሚለውን ስንኝ በአፅንኦት ደገመው..... ከጨረሰ በኋላ።

«ባለግጥሙን አወከው?» አለ ገጣሚው በመቀጠል።

«አዎን አወኩት»

«እየውልህ ሰውየው ባለቅኔ ብቻም ሳይሆን በግጥሞቹ ውስጥ የደበቃቸው ብዙ ምስጢሮች አሉ። ምስጢረኛ ባለቅኔ ነው።»

«እንዴት አይነት ምስጢር?» ሚራኽ ሰፍ ብሎ ጠየቀው።

«መፅሐፉን አንብበኸዋል?»

«አዎን አንብቤዋለሁ።»

«አሁን ያልኩህን ግጥምስ?»

«አንብቤዋለሁ።»

«እሺ 'የግማደ መስቀሌን ጉጥ እታገስበት አላጣም' ማለት ምን ማለት ነው?» አለ ገጣሚው ፈገግ እያለ።

«እኔም አልገባኝም» አለ ሚራኽ በመደናገር።

«እየውልህ ሰውየው በግጥሞቹ ውስጥ አንዳንድ ግራ የሚያጋቡ ስንኞችን ይከታል። የሥነ ፅሑፍ ሰዎችም ሳይገባቸው ዝም ብለው አጫፍረው ሲተረጉሟቸው ሰምቻለሁ። አሁን እስኪ 'የግማደ መስቀሌን ጉጥ ምንድን ነው?'» አለው እንደ ገና ወደ ሚራኽ የበለጠ ተጠግቶ። «ጉጥ ያለው ግማደ መስቀል! ... ጉጥ ያለው ግማደ መስቀል አይተህ ታውቃለህ?»

«ግን እኮ ግጥሙ ስለ አቡነ ጴጥሮስ ነው። ምናልባት እርሳቸው ...»

«ታዲያ አቡነ ጴጥሮስ ጉጥ ያለው መስቀል መታገሻ ጥግ አያጡም ማለት ምን ማለት ነው? በል ለማንኛውም መሽቶብኛል በጊዜ ልሂድ» ብሎ ገጣሚው ብድግ አለ።

«አንተ የፃፍከውን ግጥም ሳታነብልኝ?» አለው ሚራኽ። «ስለዚህ ጉዳይስ የምታውቀው ነገር አለ ...ማለቴ ስለ ሎሬቱ ግጥም..... ስለ ሰቆቃወ ጴጥሮስ.....» አብሮት ለመነሳት እየዳዳው።

«መንገደኛ ነኝ። አንተም መንገደኛ ትመስለኛለህ። ከተገናኘን ሌላ ጊዜ የእኔን ግጥም አነብልሃለሁ» ብሎት ከቁመቱ የማይተናነስ ጃኬቱን ዚኝ እየዘጋ ሄደ። ሚራኽ ገጣሚውን በዓይኑ እየሸኘው አፉን ከፍቶ ቀረ።

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን የቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ፀጥ ረጭ አለ። ከባድ ጨለማ መካነ መቃብሩ ላይ ወድቋል። ቀን ሲተራመስ የነበረው ህዝብ አሸልቧል።

ኢትዮጵያ ባንዲራዋን እውርዳ ሰንደቋ ላይ አንቀላፍታለች። ዝንቡም ሰውም ተኝቷል፡ ወፎችም መብረር አቁመዋል። ከብቶች በበረት አህዮች ቢጋጣ ታጉረዋል። ተራሮች ዝም ብለዋል። ወንዞች ግን ይፈላሉ። የጅቦች ተራ ነው። ጅቦች በየተራራው በየሸለቆው ይደነፋሉ። ህዝቦቿም ጥቁር አልማዛቸው ላይ ተኝተው ያልጠረቃ ሆዳቸውን እያከኩ ነው። «ኢትዮጵያውያን በመብራት የተፈጠሩ ይመስል ፀሐይ ስትጠልቅ አይናቸውም ጭራሮውን ይዘጋል» ብሎ ፈገግ አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ጀምበር ሲያዘቀዝቅ በይፋ ሰንደቅ አላማ ከተሰቀለበት ወርዶ እንቅልፍ ይለጠጣል። እንዲያውም የከተማ ሮንዶች ቱልቱላ እየነፉ ሰአት እላፊ መንገድ ላይ የሚያገኙትን ሰው ሁሉ ይደበድባሉ ሲባል የሰማው ትዝ ብሎት

ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ቀን ቀን እንጂ ሌሊት እንደሌለች ተረዳ።

ድቅድቁን ጨለማ በእጅ ባትሪው ብርሃን እያባረረ እንደ ኒውዮርክ ህንፃ የተደረደሩት የመቃብር ሐውልቶች ላይ የተፃፉትን ስሞች እያነበበ ሲዟዟር ሌሊቱን አጋመሰ። የመቃብራቱን ሐውልቶችና ጌጣጦች ሲያይ 'ኢትዮጵያውያን ከህይወት ይልቅ ለሞት ክብር አላቸው። ህይወትን ቅጠል ጉዝጉዘው ሲቀበሏት ሞትን ግን መቃብር አስጊጠው ይጠብቁታል። ከመኖሪያ ቤቶቻቸው ይልቅ የመቃብር ሐውልቶቻቸው ይልቃሉ። መኖሪያ ቤቶቻቸው ደሳሳ ጉጆዎች ሲሆኑ የመቃብር ሐውልቶቻቸው ግን በውድ ጠ ብቾችና ሽክላዎች ያጌጡ ናቸው። በህይወት ዘመናቸው አበባ ቀጥፎ የሰጣቸው ባይኖርም መቃብራቸው ላይ ግን የማይደርቁ አበቦች የኘላስቲክ አበቦች ለደረቁ በድኖቻቸው ይቀመጣሉ። ይህ እብደት ነው። ምናለ በህይወት ዘመናቸው እንደዚህ ቢያምርባቸው' እያለ ብቻውን እያጉረመረመ የመቃብር ሐውልቶችን ስም ሲያነብ ቆይቶ ከአንድ ሐውልት አልባ ልጥፍ መቃብር ላይ ሲደርስ ቆመ። የሚፈልገው መቃብር እንደ ሌሎቹ መቃብሮች ባለ ግርማ ሞገስ ይሆናል ብሎ ነበር። ከራስጌው ከሚታየው ጥቁር የብረት መስቀል በቀር መቃብር የሚያስመስለው ነገር የለም። መሬት ከተነጠፈው ስሚንቶ ላይ «አባ ሲርጋጋ ከ1886 –1996» የሚል ጽሁፍ ተቀርፆበታል። ፊራ ተባ እያለ ከጀርባው ያዘለውን ረጅም ሻንጣ አውርዶ ከውስጡ ዶማና አካፋ አወጣና መቆፈር ሲጀምር ዝናቡም መዝነብ ጀመረ። በአፉ የእጅ ባትሪውን ነክሶ መቃብሩን በስሚንቶው ዙሪያ ቆፍሮ ከጨረሰ በኋላ ጠፍጣፋውን ድንጋይ ሲያነሳው ከባዱ ገደል መቃብር ጋር ተፋጠጠ። መቃብሩ ውስጥ ምንም አስክሬን የለም።

«ምን አይነት ጉድ ነው?» አለ በብሽቀት መቆፈሪያውን ወርውሮ። «እንዴት ባዶ ምድር ያስቆፍሩኛል? ማነው ግን እንዲህ የሚጫወትብኝ? ቆይ ከእኔ ስቃይ የሚያገኙት ደስታ ምንድን ነው?» ጥቂት ከተነጫነጨ በኋላ የቆፈረውን ባዶ መቃብር አፈር በአካፋው ሲገፍ አንድ አነስተኛ ክብ ቀይ ድንጋይ በአካፋው ከተነሳው አፈር ጋር ወጣ። ቀዩን ክብ ድንጋይ አንስቶ እያገላበጠ ሲያየው ከቆየ በኋላ በልብሱ አፈሩን ሙልጭ አድርጉ ሲጠርገው ላዩ ላይ የተቀረፀ ፅሑፍ አነበበ። «ዴርቶጋዳ» ኪስ የሚመስለውን ቀይ ድንጋይ በባትሪ እያገላበጠ ካየው በኋላ ያገኘውን ጉጥ ነገር ሲጫነው ድንጋዩ ለሁለት ተገመሰ። ውስጡ ክፍት ነው። ድንጋይ አልነበረም። ከብረት የተሠራ ውስጠ ክፍት አሎሎ ነገር ነበር ለካ። በነተበ ብራና የተፃፈ አጭር ፅሁፍ ከውስጡ አገኘ።

«ሊያተርፍህ ሲፈልግ ሀልም ያሳይሃል» ይላል ፅሁፉ። ደጋግሞ አነበበው «ሊያተርፍህ ሲፈልግ ሀልም ያሳይሃል። ..... ሊያተርፍህ ሲፈል ..... ሊያተርፍህ..... »

«እሺ ይህን ለማስተማር ነው ይህን ሁሉ ፍዳ የሚያሳዩኝ? ይህ ታዲያ ምን ምስጢር አለው?» ብሎ በምሬት ቁራጩን ብራና ሲወረውረው በዝናቡ ውሽንፍር ተንሳፎ በጀርባው ተገለበጠና መሬት ላይ አረፈ። በጀርበው የሆነ ነገር አየ። ወደ ወደቀበት ጉንበስ ብሎ በጥቃቅን የተፃፈውን ነገር አነበበው። «ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ከሳላት የቅድስት ማርያም ስዕል ጀርባ ቀጣዩ መልእክት ተቀምጦልሃል» ይላል። ትንፋሹን ሰብስቦ በረጅሙ ተነፈሰ። «ወንጌላዊው ሉቃስ የሳላት የማርያም ስዕል የት ናት...?» ራሱን ጠየቀ። ያለችበትን ቦታ ለማስታወስ በትዝታ ወደኋላ ሸመጠጠ።

ያገኘውን መልዕክት እያምሰለሰለ ቀዩን ድንጋይ ወደ ሻንጣው አስገብቶ የቆፈረውን አፈር ወደ መቃብሩ መለሰው። መቃብሩን ሊዘጋ ጠፍጣፋውን ሀውልት ወደነበረበት ሲጐትት ኮሽታ ሰምቶ ወደ ኋላው ዞረ። እርፍ የማያክል ዱላ የያዘ ሰው «ማነህ?» አለ ዱላውን ሊያሳርፍበት እንደተንጠራራ። «አንተ ሰው በላ! እለቅህ መስሎሃል። አስክሬኑን በላኸው! አስክሬኑን ሳላስተፋህ አለቅህም።» ዱላውን ሲጥልበት ወደ ጉን ተሰፈንጥሮ አመለጠ። ዱላው መሬት ላይ አረፈ።

«ይኸው! እየው ጥሩንባዬን!» በአንገቱ ያነገተውን ጡሩንባ አሳየው። «ይህን ጥሩንባ ነፍቼ ህገር ይሰበሰባል። ከዚህ መቃብር ፈንቅለህ አስክሬን በመብላትህ ይፈርድብሃል። በላኸው! የአባ ሲርጋጋን አስክሬን በላኸው! እነፋለሁ! እነፋለሁ! ይህን ጉድ አገር ይስማ!»

«አልበላሁም!» አለ ሚራዥ። «አባ ሲርጋጋ መቃብሩ ውስጥ የሉም። እኔ አስከሬን...»

አቋረጠት «ዝም በል! በቀር በላሁ ልትል ነው? ይልቅስ ማንነትህን ንገረኝ። ይህን ጥሩንባ ነፍቼ አገር ጉድ ላይል?»

«ልጃቸው ነኝ።» አለ ሚራዥ ሌላ ውሸት እንደሌለው ሲረዳ። «የአባቴ መቃብር ላይ ሀውልት መሥራት አልችልም? አባቴን! እንዴት የአባቴን መቃብር? ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? ማነህ ከአባቴ መቃብር መጥተህ የምትደበድበኝ? ንፋ! እንዲያውም ጥሩንባውን ንፋ! ከሥራህ ነገ ጠዋት ትባረራለህ!» የሚራዥ አእምሮ በፍጥነት አሰበለት።

«አንተ የአባ ሲርጋጋ ልጅ ነህ?» በምፀት ሳቀ ሰውየው። «አዎ! እንደያውም ከፈለግህ ሻንጣዬ ውስጥ ከአባቴ ጋር የተነሳሁትን ፎቶ ላሳይህ እችላለሁ» ወደ ሻንጣው ተራምዶ ሻንጣውን ሙሉ በሙሉ በእጁ መያዙን ሲያረጋግጥ እግሬ አውጭኝ በጨለማው ውስጥ ሻንጣውን ነጥቆ ተፈተለከ። ብዙ ርቀት ከሮጠ በኋላ ወደ ኋላ ዞሮ ሲያይ የተከተለው ማንም አልነበረም።

፲፩

ከአሉሚኒየም ብረት ወደ ተሠራችው የሞተር ጀልባ ሲገባ ጣና ሆቴል ውስጥ ጥሉት የመጣው እንቅልፉ ተከትሉ እያዳፋው ነበር። ጉርብጥብጥ ጉዝጉዝ የተኛ ይመስል ከምቹው የጣና ሆቴል አልጋ ላይ ሲገላበጥ ነበር ያደረ። ሀሳብ ሲያገላብጠው።

ወንጌላዊው ሉቃስ ስሏታል የምትባለውን ቅድስት ማርያም ስዕል የት እንደሚያገኛት ቢያውቅም ከጀርባዋ ያለውን መልእክት እንዴት አድርጐ መውሰድ እንደሚችል ግራ ገብቶታል። ቢሆንም ወደዚያው እየሄደ ነው። በልጅነቱ ሲያስጐበኛት ነበር። አሁን ግን ሊጐበኛት እየሄደ ነው። ወደነበረበት እየተመለሰ። በልጅነቱ ወዳደገበት ገዳም። ወደ ወንዶች ገዳም። ወደ ክብራን።

ወጣቱ የጀልባዋ ካፒቴን አስጐብኚ ሊፈልግለት ቢሞክርም ዶ/ር ሚራዥ ግን አስጐብኚ እንደማይፈልግ ነግሮት ሁለቱ ብቻ ናቸው በትንሽዋ ጀልባ የጣናን ሐይቅ ሊሰነጥቁት በጠዋቱ ዘመናዊዋ ጀልባ ውስጥ የተቀመጡት። በምሥራቁ የጣና ሰማይ ጥግ ጀምበር እግሯን ስትሰድ ወጣቱ ካፒቴን ሞተሯን ገመዱን ስቦ ሲያስነሳው ጀልባዋ እያጓራች ጣናን መሰንጠቅ ጀመረች። ይህ ሲሆን ብጣና ሐይቅ ላይ በባህር ዳር ባህር ትራንዚት ወደብ የቆሙ አሮጌ የአሸዋና የህዝብ ጀልባዎች ሞተራቸውን እያሞቁ ነበር። ሚራዥ አሮጌዎቹ መርከቦች ላይ ዓይኑን ተክሎት ቀረ። ያው ናቸው፤ ከስንት ዘመን በኃላም አልተለወጡም።

ከባህር ዳር ተነስታ ጉርጉራ ለመድረስ ሁለት ቀን የጣናን ሐይቅ ስትዋኝ የምትሰነብተው የጣናነሽ ጀልባ ሞተሯን እያሞቀች ተመለከታት። መንፈሱ በትዝታ ቢዋጥም በነገሮች አለመለዋወጥ ውስጥ የታሪክ ዝግመትን ተመለከተ።

የጣናነሽ ጀልባ በጣና ሐይቅ ላይ ከሚጓጓዙት ጀልባዎች ሁሉ በመጠኗ ሰፊና ትልቅ ስትሆን ባለሁለት ሞተርም ናት። ይህች ጀልባ በስድስት መቶ ሊትር ነዳጅ አንድ ሺህ ኩንታል ጭና መጓዝ ትችላለች። ከባህር ዳር ተነስታ ዘጌ፣ ጉረር፣ ቁንዝባ፣ አሰፋደብር፣ ዳልጊ ደርሳ ጉርጉራ ትገባለች። ከዚያም በሄደችበት ዝክንትሏን ሰብስባ ትመለሳለች።

ፋሲለደስና ድል በትግል የሚባሉት ጀልባዎችም ቆመው ታዩት። ከሀንጋሪ ተገዝታ የመጣችው ዳህላክ የምትባለው ጀልባና ከሆላንድ የተገዛችው የካቲት የምትሰኘዋ ጀልባ በፀጥታ ቆመዋል። የኢጣልያ ጦር ከኢትዮጵያ ሲባረር በአንጋራ ደሴት አስጥሟቸው በጓላ ቡስኪ በተባለ ግሊየፍዊ ከሐይቁ የወጡት አፈር የፈጃቸውና የወየቡ የአሸዋ ጀልባዎችም ሊንቀሳቀሱ ሞተራቸውን እንደ ዕህል ወፍጮ እያንገራገጩ ነበር።

ሚራዥ ዓይኑን መርከቦቹ ላይ ነቅሎ ሐይቁ ላይ ወረወረው። የጣና ሐይቅ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሐይቆች መካከል በትልቅነት የሚስተካከለው የለም። ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ስኩየር ኪሎ ሜትር አጠቃላይ ስፋት ሲኖረው አቀማመጡም ከሰሜን እስከ ደቡብ ሰባ አምስት ኪሎ ሜትር ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ደግሞ ስድሳ ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው። የጣና ሐይቅ ከባህር ወለል በላይ በሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሜትር ወይም ስድስት ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ የተንጣለለ ምስጢራዊ ሐይቅ ነው። ከያዘው አራት ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ የውሃ ይዘት በላይ በብዙ ምስጢሮች የታመቀ ኃይቅ ነው። ጣና ሁሌም እርጥብ ነው። ዳር ደንበሩን ከዘጌ እስከ ጎርጎራ ከጎርጎራ እስከ ፎገራ የሸበቡትን ዓይናማ ድንጋዮች ታከው 'ርብ'ና 'ጉማራ'ን ጨምሮ ከሰላሳ የማያንሱ የጉንደርና የጉጃም ወንዞች ይገብሩለታል። ውሃ፣ ታሪክ፣ አፈር፣ አዕምሮ፣ እንጨት፣ ህይወት። ሆኖም ጣና በቃኝ አይልም። ሲጠግብ በምሥራቃዊ ዳርቻው መተንፈሻ አለው.....ዓባይ። ጣና በከረመቱ ማብቂያ መስከረም ሲጠባ ከሐይቁ በአባይ አበጋዝነት የሚወጣው ውሃ በሰከንድ አራት መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል ያማከላል። በታህሳስ በሰከንድ ወደ መቶ ሜትር ኪዩብ ያህል ያማከልና በግንቦት ደግሞ በሰከንድ አስር ሜትር ኪዩብ ደርሶ ሲቀበል ይከርማል። ሲያምጥ ይከርማል። መስከረም ላይ በግዮኑ መልአክ ተራዳኢነት ጭንቁን ይገላገላል። ያንቀላፋት ኢትዮጵያኑን እስከ እንቅልፋቸው ትቶ አባይ በእንቁላል ቅርፊት ሲቀዳባቸው ለሚንገበገቡለትና ነቅተው ለሚጠብቁት ግብዣውያን ይደርስላቸዋል።

የነሚራዥ ጀልባም ያህን አረንጓዴ ሐይቅ እየቀዘፈች ከባህር ዳር ከተማ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያህል ከተጓዘች በኋላ ከመንደሮቹ ደሴቶች መሀል ደረሰች። ሁለቱም ደሴቶች የሚገኙት ግራኪ በሆነ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ባለውና በደን በተሸፈነ ኮረብታማ ስፍራ ነው። ከጣና ደረት ላይ ያጐጠጐጡ ልጃገረድ ጡቶች ይመስላሉ። አሞራዎች ይጠቧቸዋል። ማዕበሉ ይጋጫቸዋል። የመናንያኑ ፀሎትና የወፎች ዝማሬ ያለመልማቸው ይመስል ቢጋ ከክረምት ደረቅ ነገር በነዚህ ደሴቶች ላይ አይታይም።

ጀልባዋ ከወንዶች ገዳም ወደብ ሥር መልህቋን ስትጥል ዶሪር ሚራዥ ወደ ሴቶች ገዳም ዙሮ አይኖቹን እንጠንስ ደሴት ላይ ወርውሯቸው ነበር። ሲጸራና ትዝታዋ ከቀዝቃዛው የጣና ሐይቅ አየር ጋር ዘልቀው ሰረሰሩት። ሲጸራና እሰ ፍቅርን የተቋደሰባቸው መንታ ደሴቶች መንታ ሕይወት ውስጥ ሲከቱት ተሰማው። ትዝታ ጥፍሩን አሹሎ ቁስሉን ያከከ መስሎ አቆሰለበት። መንፈሱና አካሉ ሁሉ ሲጸራን ተጣራ። «ምኑ አዙሪት መልሶ አመጣኝ?» ብሎ ፊቱን ቅጭም እንዳደረገ ካኘቴኑን ጀልባዋ ላይ ትቶት ብቻውን ወደኮረብታው ወጣ።

ከብራን ገብርኤል ደሴት ላይ ሲወጣ እንጦንስን አሻግሮ የሚያይበት የእሸ ዛፍ እስከ ግርማ ሞገሱ ተገትሯል። ይቀድስበት የነበረው ቤተ መቅደስ መጋረጃዎች እንኳ ያው ናቸው። የእጣኑና የማዕጠንቱ መአዛም አልተለወጠም። የሚያስጐበኙት መነኩሴ የተናገሩትን ታሪክ አንዱንም አልሰማቸውም። ያሳደገው ታሪክ ነው። አእምሮው እየተራወጠ ሁሉን ነገር ሲደቅንበት አይኖቹ በእንባ ተሞሉ። ድምፅ አውጥቶ ማልቀስ ነበር የቀረው። ለምን እንደሆነ ግን ሊገባው አልቻለም። ዘመናዊው አለም ውስጡ እየሚሚ ሲያልት እየተሰማው ነው። ሐኪምነቱም ሲተን። ራሱን ማዳን ራሱን ከትዝታው መፈወስ ተሳነው።

ቀልቡን ወደ መጣበት ጉዳይ ለመሰብሰብ ተሳነው። የሚያስጐበኙት መነኩሴ «ይህች ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የሳላት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ስዕል ናት።» ሲሉት ብቻ ነቃ።

«ይቅርታ አባቴ ስዕሏን ለመሰለም እፈልጋለሁ» ብሎ ወደ ስዕሏ ሲቀርብ ፈገግ አሉ መነኩሴው።

«ብዕአት አለብኝ። እመቤቴ በሰላም ወደ ሀገሬ ከመለሰችኝ ወንጌላዊው ሉቃስ በሳላት ስዕሏ ስር ፀሎተ ማርያም ለማድረስ ስዕለት አለብኝ። ፈቃድዎ ቢሆን አባቴ።» መነኩሴው ጢማቸውን በግራ እጃቸው ጐተት ጎተት እያደረጉ ለጥቂት ጊዜ ካዩት በኋላ በቀኝ እጃቸው በያዙት የእጅ መስቀላቸው ወደ ስዕሏ እንዲጠጋ ጋበዙት።

ተንበርክኮ ፀሎተ ማርያም እያደረሰ በቀኝ እጁ ከስዕሏ ጀርባ ይዳብስ ጀመር። ፀሎቱን ሲያደርስ ከልቡ አልነበረም ሀሊናው ከስዕሏ ጀርባ ስለተቀመጠለት መልዕክት መገኘት አለመገኘትና ምንነት እያወጣ እያወረደ ነው። መነኩሴው የማያዩ መስለው እየተከታተሉት ነው።

ከስዕሏም ጀርባ ሲዳብስ ቢቆይም ሊያገኝ የቻለው አንዳች ነገር አልነበረም። ሀሞቱ ፈሰሰ። ያስቀመጡለት መልዕክት የለም። ካጣው ደግሞ ሁሉንም ነገር ትቶ ህይወቱን ወደሰጠለት ተልዕኮ የመድረሻው መንገድ ፈጣለማ ዋጠው ማለት ነው። አንዱን መልእክት ሳይዝ ወደ ሚቀጥለው መጓዝ አይችልም። የሚቀጥለውን መንገድ ለመርገጥ ይህኛውን መመሪያ መጨበጥ አለበት። ግን አጣው። ፀሎቱን አጅርጦ ተነሳ። ወደኋላ ሊመለስ፣ 'ባቅማማህ ቁጥር መንገድክን ትስታለህ' ሲል ኢንጂነር ሻጊዝ የነገረው ታወሰው። ለይስሙላ በቻ መነኩሴው እንዳይታዘቡት ስዕሏን ስሞ ደንዝዞ ቆመ። እየተርበተበተ።

«ምንድን ነው እያደረክ ያለኸው?» አሉት መነኩሴው በቁጣ። «ውጣ ከዚህ አሁን!» የእቃ ቤቱን በር ይዘው ወደ ውጭ እንዲወጣ በዓይናቸው ገፉት። ድንጋጤ ወረረው።

«አባ .... ማለት ...እዚህ ...»

«እኮ ልትዘርፍ? ውጣልኝ አለበለዚያ ...» በአደጋ ጊዜ በምስጢር ተነፍቶ መነኮሳቱን የሚጣራውን ቱልቱላ አንስተው ወደ አፋቸው አስጠጉት::

«የለም:: አባ:: እንደዛ አይደለም ...ይቆዩ!» በዓይኑ ተማፀናቸው:: ቱልቱላውን ከአፋቸው መለሱት:: «በላ ተናገር!» አሉ አስፈሪ ግርማ ሞገስ ያላቸው መነኩሴ «ተናዘዝ! የመጣህበትን! ምን ልትሰርቅ እንደመጣህ ንገረኛ! ተናገር!» መልሰው ቱልቱላውን ወደ አፋቸው አስጠጉት::

«እየውልዎት አባ ...እኔ የመጣሁት ለስርቆት አይደለም::»

«ውጣልኝ አልኩህ! እሱን እዚህ አይደለም የምትነግረኝ! ውጭ እንነጋገራለን::»

«እርስዎ ዘንድ ...»

«ደሞ እኔ ዘንድ ምን አለህ? እኮ አብረን እንስረቅ ልትለኝ? እጅ ወደ ላይ!» ወፋፍራም መቁጠሪያዎች ያሉበት መቁጠሪያቸውን ከአንገታቸው አውልቀው:: ባለቁልፍ ሰንሰለት አምጥተው እጁን የኋሊት አስረውት የእቃ ቤቱን በር ከውጭ ዘግተውበት ሄዱ::
ከሃያ ደቂቃዎች በኋላ ተመልሰው እቃ ቤቱን ከፈቱት::

«ዶ/ር ሚራኾ?» አሉት መነኩሴው:: ወከክ አለ በድንጋጤ:: ያውቁታል::

«አ...አቤት?» አለ ሚራኾ ከድንዛዜው ባኖ::

«ይህን መልእክት ለአንተ እንድሰጥህ የተቀመጠልህ ነው:: ምን እንደምትፈልግ ገብቶኛል:: ከአባ ሲርጋጋ መቃብር ውስጥ ያወጣህውን አምጣው» ብለው ተቀበለውት አንድ በግምጃ የተጠ ቀለለ ነገር ሰጡት::

ሊፈታው ሲል «አዲስ ጉብኝዎች እየገቡ ነው ዶ/ር ሚራኾ:: ይዘኸው መሄድ ትችላለህ» አሉት ወደ በሩ እየተራመዱ:: ጥቅሉን ኪሱ ውስጥ ጨምሮ ተከትሏቸው ወጣ::

«አባቴ አንድ ጥያቄ ...»

አቋረጡት «እኔ የምመልስልህ ጥያቄ የለም:: መልእክቱን ሰጠሀህ:: በቃ የኔ ድርሻ እሱ ነበር:: ባይሆን መስቀሉን ተሳለም» ብለው መስቀላቸውን ካሳለሙት በኋላ አዲስ ወደ መጡት ጉብኝዎች ሄዱ::

ኮረብታውን ወርዶ ከደሴቱ ወደብ ሲደርስ ከአንድ ትልቅ ዛፍ ሥር ቆሞ በግምጃ የተጠቀለለውን ጥቅል ፈታው:: ከዛ ጥቅል ውስጥ ከወጣው ብጣሽ የብራና ወረቀት ላይ «ግዕበል እያላጋቸው ፈረሰኛ እየናጣቸው ሳያፈገፍጉ አቅማምተው ሳይበተኑ ተላቀው ጥቋቁር ጉንዳኖች እንኳ ወንዙን ሲሻገሩ እያቸው» የሚል መልዕክት ሰፍሮበታል:: የብራናውን ጀርባ ገልብጦ ሲያየው የቀጣይ ጉዞውን ትዕዛዝ አነበበ::

«በአሪቱ መሰዊያ ሥር ቀጣዩ መልእክት ተቀምጠልሃል» ይላል:: ብጣቂውን የብራና ወረቀት በግምጃው ጠቅልሎ ኪሱ ውስጥ ከሸጉጠው በኋላ በፍጥነት ወደ ወደቡ ወረደ::

ወደ ጀልባዋ ሲገባ የሐይቁ ነፋስ ፀጥ ብሎ ነበር:: ፀሐይዋ ከረር ብላለች:: ጀልባዋ ላይ ተኝቶ የነበረው ካኘቴን ዶ/ር ሚራኾ ወደ ጀልባዋ ሲገባ ባንኖ ተነስቶ የጀልባዋን ሞተር ከሐይቁ ላይ በሚንፀባረቀው ብርሃን የጠበበ ዓይኑን እያጨናበሰ አስነሳው::

ዶ/ር ሚራኾ ወደ ኋላ መመለስ አልፈለገም:: እረፍት የነሳውን ህቡዕ ነገር እስኪያገኘው እየተጣደፈ ነው:: ለባለጀልባው ጠቀም ያለ ገንዘብ ከጨመረለት በኋላ ወደ ጣና ቂርቆስ ሊወስደው ተስማማ:: ወጣቱ ካኘቴን የጀልባዋን አፍንጫ ወደ ጣና ቂርቆስ አዙሮ አከነፋት:: የአሪቱ መሰዊያ እዛ እንዳለ ያውቃል:: ጣና ቂርቆስ ውስጥ::

ብዙ ነገር እያውጠነጠነ ሳያስበው ጣና ቂርቆስ ደሴት ደረሰ:: ጀልባዋን ወደቡ ላይ ባለ ችካል ካሰሯት በኋላ ካኘቴኑን እዛው ጀልባዋን እንዲጠብቅ ነግሮት ሚራኾ ወደ ጣና ቂርቆስ ገዳም ገሰገሰ::

በምስጢራዊው የጣና ሐይቅ ላይ ከሚገኙ ምስጢራዊ ደሴቶች አንዱ የጣና ቂርቆስ ደሴት ነው:: በምስራቃዊው የጣና ሐይቅ ጫፍ ላይ የሚገኘው ይህ ህቡዕ ደሴት የብዙ ተመራማሪዎችን ቀልብ ስቦ የኖረ ነው:: የአትዮጵያ የትውፊትና የቅርስ ቅርጫት የሆነው ይህ ደሴት ለገዳምነት የታጨው ክርስቶስ ከመወለዱ በፊት በ፱፱፻፹፪ ዓመተ ዓለም ቀደም ብሎ ነው:: በዚህ ደሴት ላይ የሚገኙት የአሪት ዘመን መሰዊያ እና አሪታዊ ቁሳቁሶች ለአረጋዊነቱ ምስክር ናቸው:: የገዳሙ አንደኛው ጫፍ ከጣና ሐይቅ ጋር የተገናኘ ሲሆን ሌላው ጉኑ ሐይቁ ሲጐድል ከፎገራ ምድር ጋር በየብስ ይገናኛል:: ከገዳሙ በስተምስራቅ በኩል የቅድስት ክርስቶስ ሰምራ ገዳም ሲያዋስነው በምዕራብ በኩል ደግሞ በርቀት በጣና ሐይቅ ላይ የሚንሳፈፍ መሰበ ወርቅ የሚመስለው ታላቁ የዲጋ እስጢፋኖስ ደሴት ያዋስኑታል:: ጣና ቂርቆስ ደሴት በተለይም ምስራቃዊው ጉኑ በአስደናቂ የተፈጥሮ ምህንድስና የታነፀ ነው:: ከውሃው ውስጥ በምርጥ መሃንዲስ ተገንብቶ የወጣ እፁብ ድንቅ ኪነ ህንፃ የሚመስለው የድንጋዮችና የአለቶች ደርብ ዓይንን ያፈዛል::

ዶ/ር ሚራኾ በገዳሙ ምዕራባዊ ዕንፍ ከአለቱ ጋር የሚጋጨውን እና የሚፈናጠረውን የማዕበል ረቂቅ መዝሚቃና በገዳሙ ደን ውስጥ ሆነው የሚዘምሩትን አእዋፍ ጥዑመ ዜማ እያዳመጠ ቀጭኗን የእግር መንገድ ተከትሎ ወደ ኮረብታው ጫፍ ገሰገሰ::

ኮረብታው ላይ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን እንደደረሰ አንድ ኮሰስ ያሉ ሽማግሌ መነኩሴ የቤተክርስቲያኑን ቁልፍ በእጃቸው እያቅጨለጨሉ ከደኑ ውስጥ ብቅ አሉ:: በአክብሮት ሰገድ ብለው እጅ ከነሱት በኋላ «ለጉብኝት ነው?» አሉት::

«አዎን አባቴ::» አላቸው ሚራዥ:: የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር የጋለ ሰውነቱን ሰከን አድርጉታል:: ከረዣዥም ብሉይ ዛፎች ላይ እየተነሱ ወደ ጣና ሐይቅ እየተጫ.ጫ.ሁ ከሚምዘገዘጉ ባለረጃጅም ክንፍ አሞራዎች ድምፅና ከማዕበሉ ሞገድ በስተቀር የሚሰማ አንዳች ነገር የለም::

ዕድሜ የጠገቡትንና ረጃጅሞቹን የቤተ ክርስቲያኑን የእንጨት ሳንቃዎች እየከፈቱ በቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ የተሳሉትን ጥንታዊ ስዕሎች ካስጐበኙት በኋላ አራት ማዕዘን ቅርፅ ካለው ቤተክርስቲያን ተመልሰው በገቡበት በሮቹን እየዘጉ ወጡ::

መነኩሴው እንደተቀደደ ከበሮ በሚነፋነፍ ዝቅተኛ ድምፃቸው ስለገዳሙ እየተረኩለት ወደ እቃ ቤቱ ይዘውት ሄዱ:: «ይህን ቅዱስ ቦታ በመርገጥህ እግዚአብሔርን ልታመሰግነው ይገባል:: የእግዚአብሔር የክብሩ ዙፋን የሆነችው ታቦተ ፅዮን ያረፈችበት ቅዱስ ቦታ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ሕፃኑን ለመግደል ሄሮድስ ሲፈልገው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ግብፅ ይዛው ከተሰደደች በኋላ ከግብፅም ወደ ኢትዮጵያ ጉዞዋን ቀጥላ እዚህ ቅዱስ ቦታ መጥታ ስለ.መቆየቷ ድርሳነ ኡራኤል የተባለው ጥንታዊ መጽሐፍ ላይ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል:: በዚህ ገዳም ውስጥ ብቻ በሚገኘው ድርሳነ ማርያም በተባለ መጽሐፍ ውስጥ የጌታ ስደትና የእመቤታችን ቆይታ ሙሉ ታሪክ ተጽፎ ይገኛል:: ቅድስት ድንግል ማርያም የጌታችን እናት በዚህ ቦታ ሦስት ወር ከአስር ቀን ቆይታለች::»

መነኩሴው እቃ ቤቱን እየከፈቱም ትረካቸውን አላቋረጡም:: «እመቤታችን በዚህ ገዳም ላለች ይመራት የነበረው መልአክ ለዮሴፍ በህልም ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ሂድ ሲለው ዮሴፍ ወደሕጻኑ ቀርቦ «ፀአና በደመና - በደመና ጫናት» ብሎ ተማፅኖ በማቅረቡ ከዛ ወዲህ የገዳሙ ስም «ጣና ቂርቆስ» የሐይቁ ስም ደግሞ «ጣና» ተብሎ ቀረ:: ለዚህም የጽሑፍም የቁስም ማስረጃዎችን ማየት ትችላለህ::» ብለው ጥንታዊውን እቃ ቤት ከፍተው ወደውስጥ ጋበዙት:: መነኩሴው በጥንቃቄ እየተመለከቱት ነው:: ከእግር እስከራሱ እየመረመሩት::

በእቃ ቤቱ ውስጥ የመጀመሪያው ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሔኖክ፣ መፅሐፈ ሐዊ፣ የቅዱስ ያሬድ የእጅ መስቀል፣ ካባው፣ በራሱ እጅ የጻፈው ምልክት አልባው የድጓ መፅሐፍ፣ የወርቅና የብር እቃዎች፣ አንድ ሺህ አመት የሞላቸው ጥንታዊ ስዕሎች፣ እና ሌሎችን ለዓይን የሚታክቱ ቅርሶችን አስጎበኙት:: በዚህ ዕቃ ቤት ውስጥ ያሉት ቅርሶች ከመጨናነቃቸው የተነሳ ከአይጥ ለመከላከል ሲሉ ከጣሪያው ማገር ጋር መጻህፍቶችን በገመድ በአየር ላይ አንጠልጥለው ያሰሩትን ሲያይ ተገረመ:: አይጦቹ በማገሩ ላይ በመሔድ ገመዱን እየበጠሱ ቅርሶቹን እንደሚያወድሙባቸው ሲነግሩት እያዘነ ወጣ::

መነኩሴው ግራና ቀኙ በእሾህማ ቁጥቋጦዎች በተሞላ ቀጭን የአግር መንገድ እየመሩ ወሰዱት:: በጠባቡ መወጣጫ ደረጃ

ወጥተው በደሴቱ ላይ በሚገኝ ሜዳማ ቦታ አደረሱት:: በዚህም ታቦተ ጽዮንን ወደ ደሴቱ ይዘዋት የመጡት ካህናት የደም መስዋዕት ይሰዉበት የነበረውን መሰዊያ አሳዩት:: በአሪት ዘሌዋውያን ውስጥ ካነበበው ጋር የሚገጥም ነገር በማየቱ ከሶስት መቶ አመታት በላይ ታቦተ ጽዮን በዚህ እንደነበረች የሚያውቀውን ለማመን ተገደደ:: ቢሆንም የመጣበት ዓላማ ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ ሳይሆን የቀጣይ ጉዞውን ጠቋሚ መልእክት ለማግኘት መሆኑን አረሳም::

የተቀመጠለትን መልእክት በመሰዊያው ስር እየተሟሟረ ሲፈልግ መነኩሴው ትተውት ወደ ጫካው ገቡ:: ለብዙ ጎብኚዎች ግልጽ ሆነው የማይነገሩትን ድብቅ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ በልጅነቱ የሰማው ትዝ ብሉታል:: ለእርሱ ብቻ ይህ ነገር መደረጉ አንድ ነገር ከጀርባው እንዳለውም ገብቶታል:: በመሰዊያው ስር ያገኘውን አራት ማዕዘን ድንጋይ አንስቶ እያገላበጠ ካየው በኋላ እፍ እፍ ብሉ አፈሩን ሲያስለቅቀው በላዩ ላይ የተቀረጹ ጽሑፎች ብቅ ብቅ አሉ:: ድንጋዩ ከመሰዊያው ድንጋይ ለየት ያለና ቀይ ሲሆን ለእርሱ የተቀመጠለት መልእክትም ይህ ለመሆኑ አልተጠራጠረም:: በድንጋዩ ላይ ከተቀረጹት ፅሑፎች ጋር ስሙን ስላገኘው ለእርሱ የተቀመጠ ድንጋይ ለመሆኑ እርግጠኛ ሆነ:: በድንጋዩ ላይ ከተቀረጹት ፅሑፎች አንደኛው «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ይላል::

ጊታሩንና የጉዞ አቃፆቹን የያዘበትን ረጅም ሻንጣ ከጀርባው አውርዶ መፅሐፍ ቅዱስ ካወጣ በኋላ የኢሳያስን የትንቢት መጽሐፍ አውጥቶ ምእራፍ ስምንት ቁጥር አንድ ላይ ያለውን ጽሑፍ አነበበው:: «እግዚአብሔርም:- ታላቅ ሰሌዳ ወስደህ፣ ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ፣ ብለህ በሰው ፊደል ጻፍበት:: የታመኑትን ሰዎች ካህኑን ኦርዮንና የበራክዩን ልጅ ዘካርያስን ምስክሮች አድርግልኝ አለኝ» ይላል የኢሳያስ መፅሐፍ::

ኢንጂነር ሻጊዝ የነገረው ትርጉምም ትክክል እንደነበር አረጋገጠ:: እንደ ኢሳያስ «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» የሚለው ቃል ትርጉም «ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ» ማለት መሆኑን ቢያገናዝብም ይህ ቃል ለምን ለእሱ በመልእክትነት እንደተቀመጠለት ስላልገባው በተለያየ አቅጣጫ መተርጎም ጀመረ::

የተጠራበት ጉዳይ ሀገራዊ በመሆኑም ቃሉን ከሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር አገናዘበው:: «አዎ» አለ ሚራዥ ቀዩን ድንጋይ እንደያዘ:: «ምርኮ ፈጥኖአል:: ብዝበዛም ቸኩሉአል:: ሀገሪቱ በቅጥረኞችና በአድርባዮች እየተበዘበዘች ነው:: ሕዝቦቿ የበላይ ተመልካች ሆነዋል:: ተስፋ በቆረጠ ትውልድ ተሞልታለች:: ወጣቶቿ እንጀራ ፍለጋ በባዕዳን ሀገር ሲሰደዱ በጋንጃቸው እየታረዱ ነው:: ሴት ልጆቿ የአረብ ገረዶች እየሆኑ ነው:: ማምለጫ ያጡትም በጥቁር አልማዛቸው ላይ ተኝተው እየለመኑ ነው:: አዎ ጥቂቶች እየበዘበዙ ነው:: ብዙዎችም እየተበዘበዙ:: ኢትዮጵያን የተሰበረ መንፈስ ወሯታል:: ምርኮ ፈጥኗል:: ብዝበዛም ቸኩሏል::»

ቆሞ ሰጥ ያለውን የጣናን ሐይቅና አረንጓዴውን የፎገራን ምድር ሲያይ ከቆየ በኋላ «ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» ብሉ

ሳይታወቀው ሲጮህ ወደ ጫካው የገቡት መነኩሴ ቢጫ የምንኩስና ልብስ ይዘው ተመለሱና ሰጡት።

«ምን ላርገው?» አላቸው ደንገጥ ብሎ።

«ላንተ የተቀመጠው ሁለተኛ መልእክት ይህ ነው። ለብሰኸው ና ተብለሃል።» አሉት መነኩሴው በሚንቀጠቀጠው ድምጻቸው።

«ወደየት ነው የምሄደው?» አላቸው።

«እሱን እኔም አላውቅም። ስጥ የተባልኩት ልብሱን ብቻ ነው» ጥለውት ወደመጡበት ተመለሱ።

ወደጫካው ሲገቡ ሲሉም «ጫማህን መወርወርህን እንዳትረሳ» አሉት። ደንዝዞ ቢጫውን የምንኩስና ልብስ እንደያዘ ቆመ። ጫማውን አውልቆ ሻንጣው ውስጥ ከተተው። በኋላ በባዶ እግሩ መሬቱን ሊረግጥ ሲሞክር እግሩ ተንቀጠቀጠበት። ሣሩ ሳይቀር የሚበጣውን የለሰለሰ እግሩን ከሸካረው መሬት ጋር ለማለማመድ እንዴት እንደሚችል ግራ ገባው።

ቢጫውን የምንኩስና ልብስ ለብሶ ቀዩን የአመክሮ ቆብ ከደፋ በኋላ ቀጣይ ጉዞው ወደየት እንደሆነ ያምሰለሰል ጀመር።

በመሰዊያው ሥር ያገኘውን ቀዩን ድንጋይ በአፅንኦት ሲመረምረው ከቆየ በኋላ በጥቃቅን ጫር ጫር ተደርጎ የተቀረፀ ሌላ ጽሑፍ አገኘ። «ወነቦ ከመ ያንዝር» ይላል። እነዚህ ሰስት የግእዝ ቃላት አዲስ አልሆኑበትም። የሚሰጡት የተሳካ ትርጉም ግን ፍንትው ያለና ግልፅ አልሆነለትም። ቀዩን ድንጋይ እንደያዘ ሻንጣውን ከጀርባው ካዘለ በኋላ ኮረብታውን በቀጭኗ መንገድ ወርዶ ወደቡ ላይ ወደ ታሰረችው ጀልባ ተመለሰ።

ካፕቴኑ ጀልባዋ ውስጥ ወፍራም ጃኬቱን ፊቱ ላይ አድርጎ ተኝቶ ነበረ። ሚራዥ ሲገባ ጀልባዋ በፈጠረችው ውዝዋዜ ባኖ ተነሳ።

ሊሄድ ዘመናዊ የነበረው ሚራዥ ሲመለስ ለብሶት የመጣው የምንኩስና ልብስ ከጎፈረው ሪዙ ጋር ለዘመናት ጫካ ውስጥ የኖረ መናኝ አስመስሎታል። በእጁም ቀይ ድንጋይ ይዞ ያገላብጣል። ካፕቴኑ ፈገግ አለ። «ከመቼው መነኩስክ?».....አልመሰለለትም።

«ወነቦ ከመ ያንዝር» የሚለውን ፅሑፍ የሰማበትን ሁናቴ እያሰላለሰ በዝምታ ተዋጠ። በኋላ ጊታሩን አውጥቶ አውታሮቹን በጣቶቹ እየነካካ ማሰላሰሉን ቀጠለ። ካፕቴኑ በዝምታ ሚራዥን ይመለከታል።

አንዳች ትዝታ በጊታሩ ታና ውስጥ ብልጭ ብሎ ተመልሶ ጠፋበት። «ወነቦ ከመ ያንዝር» የሚለው ቃል የተፃፈበት ጎራዴ በአፅምሮው ውስጥ ተገለባብጦ ተመልሶ ጠፋ።

መልሶ ደግሞ በልጅነቱ ክብራን ገብርኤል የወንዶች ገዳም ውስጥ እያለ አባ ዮንበሩ የሚባሉት መነኩሴ ወስደው ያስገቡት ገዳም ትዝ አለው። በብዙ የነገሥታት ቅርሶች በተሞላው በዚያ ገዳም ውስጥ ካሉት ውድ ቅርሶች ውስጥ ኢትዮጵያን ለብዙ ዓመታት በንግሥና የመሯት ንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሕይወት ዘመናቸው ከእጃቸው ለይተውት የማያውቁት ጎራዴአቸው አንዱ

ነው። .....በዚህ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሰይፍ ላይም «ወነቦ ከመ ያንዝር» የሚል ጽሑፍ ተቀርጾበት እንዳየ ያስታውሳል።

«አገኘሁት!» ብሎ በደስታ ተፈናጥሮ ጀልባዋ ውስጥ ሲዘል ጀልባዋ ተንገዳገደች። «ቀጥታ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ንዳት» አለው ካፕቴኑን። «ወነቦ ከመ ያንዝር» የሚል ጽሑፍ የተቀረጸበትን የአፄ ዘርዓ ያዕቆብን ጎራዴ ያየው ከብዙ ዓመታት በፊት አባ ዮንበሩ ከክብራን የወንዶች ገዳም ወስደውት የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም በጎበኘ በት ወቅት መሆኑን በትክክል እንዳስታወሰው እርግጠኛ ነው።

ከጎርጎራ ወደ ባሕርዳር የሚነፍሰው ከባድ ነፋስ የጣናን ማዕበል አስነስቶ እንደፈረስ ያሰግረዋል። ጀልባዋ ለደሴቶች ትሰግድ ይመስል በማዕበሉ እየተዳፋችና እየተቃናች እየተናጠች ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም እየገሰገሰች ሳለ ጀንበር በጣና ሐይቅ ምዕራባዊ ፅንፍ እያቅላላች ነበር። ባለጅ ያጋለው ብረት የመሰለችውን የማታ ጀንበር ድርብርብ ጥቁር ደመና ከቧታል። በደመናው መሐል የምትታየው ፀሐይ የሰማይን መጋረጃ ገልጣ ጣናን አጮልቃ የምታይ መስላለች። ጨረሮቿን ሰዳ ታማስለው ይመስል ጣና ይገለባበጣል።

ባለረጃጅም ክንፍ ጥቋቁር አሞራዎች በጠቆረው የጣና ሰማይ ላይ የተሰለፉ የጦር አውሮፕላኖች መስለው ወደ ጎርጎራ ይምዘገዘጋሉ። በሰልፍ..... በሕገ አሞራ። መሪውን አሞራ ይከተሉታል።

«አየሃቸው?» አለ ሚራዥ በጣና ሰማይ ላይ የሚምዘገዘጉትን ክንፋም አሞራዎች አንጋጠ እየተመለከተ። «አሞራዎች መሪያቸውን ያምኑታል።»

«እየመራቸው አይደለም እኮ እንደኛ መሪ የራሱን ጉዞ እየተጓዘ ነው። ቀድሞ ለመብላት እየጓጓ።» አለ ካኘቴኑ።

«ለመሆኑ ወደየት እየሄዱ ነው?»

«ወደ ኤርትራ።» ካኘቴኑ ከት ብሎ ሳቀ። «ኢትዮጵያና ኤርትራ ያልከፋፈሏቸው አሞራዎችንና ወፎችን ነው። ኤርትራ ውስጥ የወደቀ ጥንብ ካለ የኢትዮጵያ ጥንባንላ አሞራ እንደሚግ ተወንጭፎ ላጥ የማድረግ አሞራዊ መብት አለው። ኢትዮጵያ ውስጥ ድርቅ ሲኖርም ከኤርትራ የተነሱ አሞራዎች መጥተው ከኢትዮጵያ አሞራዎች ጋር በፍቅር ይቃመሳሉ። ይህን ስታይ «እኔስ ባረግኝ» ትላለህ። በሁለቱ ሀገሮች ያሉ ህዝቦች እንዳይገናኙ ቦንብ ሲታጠርባቸው ወፎችና አሞሮች ብቻ እስከ አሁን አልተለያዩም። በእርግጥ ኤርትራ ለምትባል ሀገር ከዛም ከዚህም ያሉት ህዝቦች ዕውቅና የሰጡ አይመስለኝም። በእርግጥስ ድንበር የሌለው ምድር እንዴት ሀገር ሊባል ይችላል? እንዲያውም እርትራ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን እንኪንስ እኛ ግመላችን እንኪ ባንዲራችን ያውቃል። አረንጓዴ ቢጫ ቀዩን ነው የሚሉት አሉ። አንድ ቀን መልሰን እንደምንገናኝ ተስፋ አልቆርጥም። አውሮፓ አንድ ሊሆን በአንድ ገንዘብ መገበያየት በአንድ ቪዛ አገር ማቋረጥ ጀምሮ አንድ

ሰንደቅአላማ ሊያውለበልብ በሚጣጣርበት ወቀት እዚህ የእኛ መሰነጣጠቅ አሳዛኝ ነው። ሆኖም እነዚህ አሞራዎች በሁለቱ ሀገራት የድንበር ግጭት የወደቁ ወንድማማች ወታደሮችን ካንድ ማህፀን እንደ ወጡ ሁሉ ባንድ ሆድ ውስጥ መልሰው አገናኝተዋቸዋል። አሞሮቻችን የሁለቱ ሀገራት ጊዜያዊ አምባሳደሮች ናቸው። ወደፊት ሁለቱ መንግሥታት አሞራዎቻቸውንም ለመከፋፈል ከምድር እስከ ሰማይ መረብ ካልዘረጉ በቀር በረራቸውን አይተውም።»

«አሞራዎችን ቢያስተሪቸው መፍሰሳቸውን አያቆሙም። ከዚህ ወደዚያ ከዛም ወደዚህ።» አለ ሚራዥ ፈገግ ብሎ። ተጉዘው የማያልቁትን ጥቋቁር አሞራዎች ጐን ለጐን ደግሞ ነጫጮቹ ሳቢሳዎች ይበራሉ። «እነዚህ ደግሞ» አለ ካኘቴኑ። «እነዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ መንኩራኩሮች ናቸው። ኢትዮጵያ ወደ ህዋ የምታመጥቃቸው ሮኬቶች። ይኸው እስከዛሬ ታመጥቃለች። የኢትዮጵያ መንኩራኩሮች በየቀኑ ይወነጨፋሉ በየቀኑ ይመለሳሉ። ማርስ ደርሶ መልስ። አየህ ህዋን እንዲህ ቀድመን ተቆጣጥረነው ነበር። የአሜሪካውን የህዋ ምርምር ተቋም ታውቃለህ?» አለ ካኘቴኑ አሁንም እየሳቀ።

«አዎ ናሳን?»

«ናሳ ውስጥ የሚሠራውን ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስትስ?»

«ማነው እሱ?»

«ኢንጂነር ሻጊዝ ሲባል አልሰማህም እንዴ?»

«አንተም ታውቀዋለህ?»

«እንዴታ! ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የብዙ ኢትዮጵያውያን መነጋገሪያ ሆኗልኮ። መሆንም የሚገባው ሰው ነው። እንዴ! ኢትዮጵያ አህያ ጠምዳ በምታርስበት ወቅት ወደህዋ የሚመጥቁ መንኩራኩሮች ዲዛይነርና የሳይንቲስቶች መሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ መገኘትኮ የሚገርም ነገር ነው። አቦ እንዴት ያለ ጀግና ሰው ነው! ጭንቅላት ያለው ኢትዮጵያዊ ነው አቦ! ኮርቶ አኩራን። ምን ዋጋ አለው ታዲያ እኛ ያሉን መንኩራኩሮች እነዚህ ሳቢሳ አሞራዎች ናቸው። ...የኢትዮጵያ ነገር አንዱ ጥሬ አንዱ ብስል ነው። ኢትዮጵያን ጥሏት ሄደ። ኢትዮጵያ ሳይንቲስት ሻጊዝን እንዴት ልትጠቀምበት ትችላለች፣ ኢትዮጵያና ሳይንቲስቱ ተላለፉ። አንዳንድ ጊዜ ከአስተማሪው ተማሪው በልጦ ይገኛል። ድሆ ያደገባት አፈር የፈጨባት ምድር እስካሁን ስትድህ እሱ ቆሞ ሄደ። ከመሬትም አልፎ የማርስንና የጨረቃን ሽለቆዎች ማሰስ ጀመረ። እኛ ደግሞ እንደምታየን አለን። የዛሬ መቶ አመት ተመልሰህ ብትመጣም ያው ነን። እንደዚሁ ታገኘናለህ። ባናም እነዚያ የምታያቸው በፀደዩ አበባ የተንቆጠቆጡት የኢትዮጵያ ተራሮችም ያው ናቸው። ያብባሉ፤ይረግፋሉ። ህይወት ኢትዮጵያ ውስጥ ፈረቃ ነው። ሲዘንብ ታቆጠቁጣለህ፤ ሲደርቅ ትደርቃህ። በቃ ይህ ነው።»

ዶ/ር ሚራዥ ፍዝዝ ብሎ የካኘቴኑን ንግግር ሲያጸምጥ ቆይቶ ወሬውን ሲያቆም የራቀውን አቅርቦ የሚያሳየውን መነፅር አነሳና የዳጋ እስጢፋኖስን ደሴት በመነፅሩ ውስጥ ፈለገው። ጀልባዋ የኋሊት እንጂ ወደፊት የምትሄድ አልመስልህ አለው። ለመድረስ ቸኩሏል።

የማቅረቢያ መነፅሩን ማንገቻ በአንገቱ አጥልቆ ማዕበሉ ከሚያንገላታት ጀልባ ላይ እየተንገዳገደ ቆሞ ሲያስስ ከደቅ ደሴቶች አንዱና ዋነኛ የሆነው ዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ፊት ለፊት ገጭ አለ። አረንጓዴ ልቃቂት ይመስላል።

ያለመነፅር ለማየት ከርቀት ሲያማትር ጣና ሐይቅ ላይ የሚንሳፈፍ አረንጓዴ መሰበወርቅ የሚመስል ደሴት ታየው። ዳጋ። ቅዱሱ ደሴት። እየቆየ ደግሞ ጉድሮ የተከረከመ የእርኖ ራስ መሰለው.....ዳጋ።

ጀልባዋ በፈጠነች ቁጥር ደሴቱም እየፈጠነ ቀረበው። ጀልባዋን ማዕበሉ ሲያወዛውዛት ደሴቱም የሚወዛወዝ አረንጓዴ መሰበወርቅ መሰለው። ልትጠልቅ የተቃረበችው ጀንበር በደሴቱ አናት ላይ ከጥቋቁር ዳመናዎች ተፈልቅቀው ያመለጡ ቀያይ ወርቃማ ጨረሮቿን በትናበታለች። ተፈጥሮ በውበት ሸማዋ ተጠ ቅልላ ደሴቱ ላይ ወድቃለች።

ዳጋ ደሴት እየቀረበ መጣ። በስተምዕራብ የደሴቱ እናት ቀልል ያለ አረንጓዴ ኮረብታ ሲሆን በስተምስራቅ ደግሞ በዕፀዋት የተሸፈነ ሜዳ ነው። ከደቡብ እስከ ሰሜን አምስት ኪሎ ሜትር ያህል የሚረዝመው ዳጋ ደሴት ከላይ ሆኖ ሲያዩት ክንፉን ዘርግቶ ሐይቁ ላይ የወደቀ አረንጓዴ አሞራ ይመስላል። በወንጌል ዓይን ሲታይ ተሰምርተ መስቀል በአሪታዊ ዓይን ሲቃኝ የኖህ መርከብን የመሰለ ቅርፅ ያለው ደሴት ነው። ዳጋ በአረንጓዴ እፅዋት ባይጀቦን ኑሮ የጥፋት ውሃ እስከ ግማሽ ያጠለቀው የኖህን መርከብ ሊመስል የሚቀረው ኖህና ቤተሰቦቹ በውስጡ አለመኖራቸው ብቻ ነው።

ከሁለት ሰዓታት ጉዞ በኋላ በዳጋ ምዕራባዊ ጫፍ ባለው ጥንታዊ ወደብ የጀልባዋ ገመድ ከወደቡ ችካል ጋር ታሰረ። በደሴቱ ዳርቻ ከተረበረቡት ጥቋቁር ዓይናማ አለቶችና ድንጋዮች ጋር የሚጋጨው የጣና ማዕበል የታሰረችውን ጀልባ ከወደቡ ጋር ያጋጫታል። አረንጓዴ ጋቢ የተከናነበ ከሚመስለው ደሴት ውስጥ ቢጫ የምንኩስና ልብስ የለበሱ ሶስት መነኮሳት ወደ ወደቡ መጡ። የለበሱት ቢጫ የምንኩስና ልብስ ሚራዥ በጣና ቂርቆስ ገዳም ከተሰጠውና ከለበሰው ጋር ተመሳሳይ ነው።

ከሶስቱ አንደኛው እጅግ አዛውንት ናቸው። እንደ በረዶ የነጣው ጢማቸው ከቢጫው መጐናፀፊያቸው በላይ እስከ ደረታቸው ተንዠርግጓል። ጐበጥ ያሉ ጠይም መልክ ያላቸው ናቸው። ከሁለቱ መነኮሳት መሃል ቆመው ሚራዥን ለእፍታ ከተመለከቱት በኋላ ምንም ቃል ሳይተነፍሱ ወደ መጡበት ተመለሱ።

«በዓድቋ ተራዳኢነት እንኳን ደህና መጣችሁ::» አሉ አንደኛው መነኩሴ:: ሽማግሌው መነኩሴ ወደ ጫካው ከገቡ በኋላ:: «ምነዋ ከመሼ?» አሉ ሁለተኛው ጥቁር ጉርፊፌ ጢም ያላቸው መነኩሴ:: ከሪዛቸው ውስጥ ብልጭ ያለው ነጭ ፍንጭት ጥርሳቸው መልሶ ተከደነ::

«ማዕበሉ አስመሽቶብን ነው::» አለ ሚራዥ የመነኩሴውን ፊት እያነበበ::

ካኘቴኑ ወደ ሚራዥ ተጠግቶ «መሄዴ ነው::» አለ::

«በዚህ ጨለማ?» ሚራዥ ደንገጥ ብሎ::

«ነገ ወደዚህ ገዳም ለጉብኝት የሚመጡ ጣሊያናውያንን እንዳመጣ ድርጅቴ አዞኛል:: በፈለክኝ ሰዓት ብትደውልልኝ መጥቼ እወስድሃለሁ::» በጣቂ ወረቀት የተንቀሳቃሽ ስልኩን ቁጥር ፅፎ ሰጠው::

«እረ መሽቷል ተው?»

«ነገርኩህ እኮ ጣልያናውያኑን ይዤ በጧት ወደዚህ ገዳም እንድመጣ ታዝዣለሁ:: የሥራ ጉዳይ ነው:: ብትደውልልኝ በማንኛውም ጊዜ እመጣልሃለሁ::» ካኘቴኑ የጀልባዋን ሞተር አስነሰቶ ወደ ባህር ዳር ከነፈ::

ሚራዥ በሁለቱ መነኮሳት መሪነት ደሴቱ በር ሲደርስ ወደገዳሙ መግቢያ ከተተከለ ሰሌዳ ላይ «ዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም» የሚል ፅሁፍ አየ:: በጉን በኩል ደግሞ ሴቶች ወደ ገዳሙ እንዳይገቡና ማንም ሰው የጦር መሳሪያ ይዞ እንዳይገባ የሚከለክለውን ፅሁፍ አነበበ::

ጥቅጥቅ ባለው ደን ውስጥ እንደ ክር በቀጠኑቸው መንገድ እየመሩ ሲወስዱት ሚራዥ በሚያያቸው ሀገር በቀል ዛፎች ልምላሜ ተመስጦ ነበር:: ከሠያ ሰባት በላይ በሌላ የምድራችን ገላ ላይ ያልበቀሉ ሀገር በቀል ዛፎች በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት እንደሚገኙ ያነበበው ጥናታዊ ፅሁፍ ትውስ አለው:: ፀደዩን በፍካት ሊቀበሉ ከእንቡጣቸው የተሸለቀቁ አበቦች መአዛ ሲያውደው የተሸበሸበ መንፈሱ መዘረጋጋት ጀመረ:: ከገዳሙ መግቢያ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ የገዳሙ ተግባር ቤትና የዕህል ወፍጮ ቤት ይገኛል:: የሞተር ወፍጮውን ለዚህ ገዳም ያስተከለው የቀድሞው ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለ ማርያም መሆኑን ሲነግሩት ተገረመ:: ፕሬዝዳንቱ በመጨረሻው ሰዓት አካባቢ በዚህ ገዳም ውስጥ የተወሰኑ ቀናትን እንዳሳለፈና በገዳሙ ውስጥ ያለው የአንድነት መንፈስ አስደልቶት ብዙ ድጋፍ አድርጎ እንደ ነበር ጨምረው ነገሩት::

በዚህ ገዳም ውስጥ እስከ ሶስት መቶ የሚጠጉ መነኮሳት እንደሚኖሩ ቢገመትም ከአእዋፋቱ ዝማሬና ከጣና ሐይቅ የማዕበል ድንፋታ በቀር የሚሰማ ድምፅ የለም:: የደሴቱን ጥቋቁር አለቶች ከሚጋጨው የጣና ማዕበል ጋር የሚቀላቀለው የእንቁራሪቶችና የጉርጦች ድምፅ ቀስ ብሎ በሚነፍሰው ነፋስ እየተቀመረ በጆሮው

ሲንቆረቆር እውቅ የሙዚቃ አቀናባሪ የተጠበበበት ረቂቅ ሙዚቃ መሰለው:: የተኩፋተረ ፊቱ ሲፍታታ ተሰማው:: የተጨናነቀች ነፍሱ በእፎይታ ተነፈሰች:: ከየት እንደመጣ ባላወቀው ምክንያት አልባ ደስታ ነፍሱ ተንፈራገጠች:: ምናልባት በዚህ ደሴት ውስጥ ከጉመሩት የፀደይ መግቢያ አበቦች መአዛ የተቀመመ ደስታን የሚሰጥ ቅመም እንዳለ ጠረጠረ:: እንጂማ እሱን የማያፍነከንክ ደስታ ሌላ ከወዴት ይመጣል? «ላፊንግ ጋዝ ባፍንጫየ ገብቶ መሆን አለበት» አለ በሆዱ:: «ሳቅ ቀስቃሽ ንጥረ ነገር ሸቶኝ መሆን አለበት::»

ቀጭኗን መንገድ ተከትለው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ ሁለቱ መነኮሳት ወደ አንድ ሌላ መነኩሴ ቀርበው እጅ ነሱ:: ጥቂት ተነጋግረው ወደ ሚራዥ ተመለሱ:: «የገዳሙ መጋቢ በገዳሙ ውስጥ እንዲያድሩ ፈቅደዋል::» አሉ ጠይሙ ጢማም መነኩሴ:: ያለገዳሙ ኃላፊዎች ፈቃድ በገዳሙ ውስጥ ማደር እንደማይቻል ያውቃል:: ሰገድ ብሎ ለመልካም ፈቃዳቸው ምስጋና አቀረበ::

የምሽቱን ፀሎት ሊያደርሱ በየበአታቸው የገቡት መነኮሳት መውጣት ጀምረዋል:: ሁሉም እየመጡ ለሚራዥ ሰላምታ ሰጡት::

ሰላምታቸው ለየት ያለ ነው:: ገና ከሩቅ ሰላም ሊሉት ሲመጡ እስከ መሬት አጎንብሰው እየተንደረደሩ ይመጡና ከእሱ ሲደርሱ እጅ በመንሳት የበለጠ ከወገባቸው ሰግደው ትከሻውን ይስሙታል::

ከርቀት እስከመሬት አንገታቸውን ደፍተው እየተንደረደሩ ሲመጡ ለውጊያ የሚሽከረከሩ አውራ በጉችን ይመስላሉ:: የበለጠ እስከመሬት የተጐነበሰ የበለጠ ትህትናና አክብሮት መግለጡን ያመለክታል:: መነኮሳቱ ይህን የሰላምታ ዘይቤ ለዘመናት ይዘውት ኑረዋል:: በየቀኑ ከፀሎት በኋላ ሲገናኙ እርስ በእርሳቸው ይህንን አድካሚ ሊባል የሚችል ሰላምታ ሳይሰለቹ ይለዋወጣሉ:: ትህትናና ፍቅረ ቢፅ ዋናው አብሮ ለመኖር ያስተሳሰራቸው ሰንሰለት ነው:: ጮኽ መናገር፣ ጓደኛን ማንጓጠጥ፣ አለመታዘዝ፣ አብዝቶ መብላት፣ ያም መሻር የመሳሰሉት ጉዳዮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው::

ዶ/ር ሚራዥ ፍፁም የሆነውን የወንድማማችነት ድባብ ሲያይ የልጅነት ዘመኑ ውል ብሎ ታየው:: ክብራን:: የዳጋ ገዳምም እንደ ገዳም ክብራን የወንዶች ገዳም በመሆኑ የተቀራረበ ባህልና ትውፊት አለው:: እንዲያውም በጣና ሐይቅ ላይ ባሉ ደሴቶች ውስጥ ያሉ ገዳማት እርስ በእርስ እንደሚቀራረቡ ያውቃል:: ክብራን፣ ዳጋና ሐይቅ እስጢፋኖስ የበለጠ ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ገዳማት መሆናቸውንም ያውቃል::

በልጅነቱም አባ ገ/ጉበሩ ከክብራን ገዳም አምጥተው የዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳምን እንዳስጐበኙት ያስታውሳል:: በመሆኑም ባህሉንና ትውፊቱን ለመላመድ የሚያደርገው ጥረት አይኖርም:: ሰላምታቸውም አዲስ አልሆነበትም:: እሱም እንደነሱ እስከመሬት ለጥ ብሎ እጅ መንሳት አልተሳነውም:: ሁለቱ መነኮሳት ፈንጠር

ብሎ ብቻውን ወደተሰራው የእንግዳ ቤት ይዘውት ሄዱ። የእንግዳ ቤቱ ክብ የሳር ጉጆ ነው። መደቦቹ ላይ ከሰሌን በእጅ የተሠሩ ምንጣፎች ተነጥፈዋል፡ ከግድግዳው ላይ ያለው ቀንዲል ተለኩሷል። ጭል ጭል የሚለው የቀንዲሉ መብራት ወጋገን በደሳሳው ጉጆ ውስጥ ያለውን ጨለማ ወደ ውጭ ይገፋል። ከእንጨት ጥርብ የተሠራው የሳንቃ ንቃቃት በሚወጡት የቀንዲሉ ብርሃን ጨረሮች ፍንጣቂ ዙሪያ ትንሞች ይተራመሳሉ፤ ያላዝናሉ። በቀንዲሉ ብርሃን መፅሐፍ ከንፋቸው ላይ ዘርግተው ያነቡ ይመስል በብርሃኑ ጨረር ዙሪያ ይሽከረከራሉ። ያነበንባሉ። ትንሞቹ። ሚራዥ በሁለቱ መነኮሳት ታጅቦ ወደ ጉጆዋ ሲገባ ከተነጠፉት የሰሌን ምንጣፎች አንደኛው ላይ የተቀመጡት መነኩሴ ተነስተው ቆሙ።

«እርሳቸውም እንደ እርስዎ እንግዳ ናቸው» አሉ ጠይሙ ጢማም መነኩሴ። «አብራችሁ ተጨዋወቱ። መጋቢው መጥተው ይጐበኟችኋል።» ሁለቱ መነኮሳት የእንግዳ ቤቱን ሳንቃ የኋሊት ዘግተውት ሄዱ።

ሚራዥ እንደ እሱ እንግዳ የሆኑትን መነኩሴ እጅ ነስቶ ተቀመጠ። በግድግዳው ዙሪያ ማዶና ማዶ በተሰሩት መደቦች ላይ የተቀመጡት ሁለቱ እንግዶች ሳይነጋገሩ በዝምታ ተውጠው ቆዩ። እንግዳው መነኩሴ የለበሱትን ቢጫ የምንኩስና ቀሚስ በፈርጣማ አካላቸው ተወጣጥሮ እርጉዝ ሴት አስመስሏቸዋል። የደረቡት መጐናፀፊያ ተንሸራቶ መሬት እየላሰ ነው። ጥቁር ፀጉራቸው ላይ የደፉት ቆብ ራሳቸውን በከፊል ያሳያል። ጥቁር ፊታቸው ከፀጉራቸው ጋር ሊመሳሰል ምንም አልቀረውም። በጨቤ የተሸረካከተ መሆኑን የሚያሳብቀው ፊታቸው ዕድሜ ልካቸውን ሲደባደቡ የኖሩ አስመስሏቸዋል። የተሠበረ ቀንድ የሚመስለው ጉራዳ አፍንጫቸው በላልሏል። አገጫቸው ላይ የበቀለው ፀጉር ጥቁር ግንድ ላይ የሚርመሰመስ ጉንዳን ይመስላል።

ሚራዥ እንግዳውን ለረጅም ጊዜ እያጮለቀ ሲመለከታቸው ከእስር ቤት ያመለጠ አደገኛ ወንበዴ መስለው ተቀረቡበት። መነኩሴ ቀርቶ ምንኩስና የሚባል ነገር የሰሙ አይመስሉም። የምንኩስና ልብሳቸውን በሥርዓቱ ካለመልበሳቸውም በላይ ከሰውነታቸው ጋር ባልተዋሃደው ቀሚስና መጐናፀፊያ ዝርክርክ ብለዋል። ደሞ ጠብደል ናቸው። በየቀኑ በሬ እስከቀንዱ ሲውጡ የኖሩ እንጂ በያምና በስግደት ሲመጠመጡ የኖሩ አይመስሉም። የፊት ጥርሳቸውን በሙሉ ያጡ መሆናቸውን ያረጋገጠው አፋቸውን እስከጆሯቸው መልግደው ሲያዛጉ ነው። የተከፈተ አፋቸውን በመዳፋቸው እየከመከሙ «ስምህ ማነው?» አሉት። አንተ ብለው በመጥራታቸው የሚቀነስ ክብር ባይኖረውም ለስርዓተ ገዳም አዲስ መሆናቸውን ፍንጭ ሰጠው። ማን እንዳመነኮሳቸው እግዜር ይወቀው አሰ በሆዱ። ለነገሩማ አሱንስ ማን አመነኮሰው ልበስ የተባለውን ልብስ ምንኩስና ገላው ላይ ቢጭንም ነፍሱ እንዳልመነነሰች ግን ልቡ ያውቃል። አፉን መክርከም እንዳለበት አምኖ «ሚራዥ

እባላለሁ።» ብሎ ዝም አለ። መልሰው ደግሞ እርስዎ አሉት። ሬስተውት ነበር ለካ።

«አባ ሚራዥ ከወዴት መጥተው ነው?» ድምፃቸው ጆሮ የሚቆረቁር ለዛቢስ ነው። ጮክ ብለው በመናገራቸው ሰቀጠጠው። ጥያቄያቸው ደግሞ ትክክል አይደለም። በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ የቆዩ ቢሆኑ ኑሮ ከወዴት መባህ ብለው አይጠይቁም ነበር። በኢትዮጵያ ገዳማት የሚመጣ ማንኛውም መናኝ ሀገሩ፣ ዘሩ፣ ሐብቱ፣ ስልጣኑ፣ አይጠየቅም፡ እግዚአብሔር ፡ርቶት ከመጣ መጣ ነው በቃ። ከዚህ ውጪ የገዳሙን ስርዓት አክብሮ እስከኖረ ድረስ ራሱ ፈቅዶ ካልተናገረ በስተቀር «እስራኤላዊ ነህ፣ ኢትዮጵያዊ ነህ፣ ግብፃዊ ነህ፣ አማራ ነህ፣ ኦሮሞ ነህ፣ ትግሬ ነህ፣ ገለመሌ ነህ?» ተብሎ አይጠየቅም። ቢጠየቅም እንኳ መነኩሴ ትክክለኛ ማንነቱን አይናግርም። ማንነቱን ማጣራት ቢገባ እንኳ ማጣራትና መጠየቅ የሚገባው የገዳሙ ኃላፊ የሆነ መነኩሴ ነው። የገዳሙ አበምኔት ወይም መጋቢ ወይንም ሌላ ኃላፊ።

«ከዋልድባ ገዳም ነው የመጣሁት።» ሲል የምሽቱን ታሳቅ ውሽት ዋሸ ሚራዥ። «ዋልድባ ገዳም ወዴት ነው?» አሉ ጠብደሉ መነኩሴ።

«ዋልድባን የማያውቅ መነኩሴም አለ እንዴ?»

«ይኸው እኔ አለሁ።» ጥቁር ከንፈራቸውን ብልጥጥ ሲያደርጉት ጥርስ አልባው ቀይ ድዳቸው ከከሰል ጫፍ ላይ ያለ ፍም መሰለ።

«ዋልድባ ሲባል ሰምተው አያውቁም?»

«አረ ስቀልድ ነው..... ዋልድባን የማያውቅ መነኩሴ እንዴት ይኖራል?» በዚህ መሀል አባ ዲዎላ እባላለሁ ብለው ስማቸውን በስህተት ሲያስተዋዉቁት ለጥቂት መልሰው ዋጡት። አባ ዲዎላ ይህን ይበሉ እንጂ ከሲሲሊ ደሴት በዶን ሞርሞርዲኖ የግል አውሮንላን ከቀናት በፊት ኢትዮጵያ መግባታቸውን ልባቸው ያውቃል። ለመጠበት ልዩና ምስጢራዊ ተልእኮ የሚበጇቸውን ምርጥ ምርጥ ውሸቶችና የሀሰት ሽፋኖች ካልተጠቀሙ ከዚህ ገዳም ተባረው ተልእኳቸው ከንቱ እንዳይሆን ሰግተዋል።
ወዲያው መጋቢው ወደ እንግዳ ቤቱ ገቡ። ረዥም ሰላምታ ለሁለቱም ሰጥተው ተቀመጡ። ጥቂት አቀርቅረው ከቆዩ በኋላ «እዚህ ለመኖር ነው?» ሲሉ ሁለቱንም ጠየቁ። እንዳቀረቀሩ።

«አዎን እዚሁ ለመኖር ነው» አባ ዲዎላ ፈጠን ብለው መለሱ።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን።» አባ ሚራዥ አንገታቸውን ሰበር አድርገው ለስለስ ባለ ድምጽ።

«ያው ...መቼም በሌላ ገዳም የቆያችሁ ከሆናችሁ ታውቁታላችሁ ስለገዳም ሥርዓት እናንተን ማስተማር ድፍረት ይሆንብኛል። ውሃ ሽቅብ አይፈስም። በመዘውር ካልሆነ በቀር።»

መሬት ላይ ሰቃ የጠፋባቸው ይመስል ዓይኖቻቸውን ወለሉ ላይ ያንከባልሏቸዋል። «በመሆኑም ይህም ገዳም እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ገዳማት መጽሀፈ መነኮሳትን ተመርኩዞ ነው የሚስተዳደረው። ልዩው ነገር ግን በዚህ ደሴት ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ጦርነት ሲነሳ የተጋዙ ውድ ቅርሶች ስላሉ እነዚህን ሀገራዊ ቅርሶች ጠብቆ ለማቆየት የሞት ሽረት ትግል ይደረጋል። በመሆኑም እናንተም እንደኛው በፈቃደ እግዚአብሔር ወደዚህ ቅዱስ ሥፍራ ከመጣችሁ ዘንዳ ይህ ኃላፊነትም በላያችሁ ላይ ይወድቃል።» አሁንም እንዳቀረቀሩ።

«እረ ግዴለም። እኔ በበኩሌ ይህን ሀገራዊ ኃላፊነት በህይወቴ ውስጥ ለአንዴ እንኳ መሸከም እንዳለብኝ ይሰማኝ ነበር።» አሉ አባ ዲዎላ የቅርሱን ጥበቃ በተመለከተ።

«ሥርዓተ ገዳሙን በተመለከተ ግን ያው እንደ ሌሎቹ ገዳማት ነው። ለገዳም ህይወት መሠረታችንም የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በቅዱስ ቃሉ መሠረት። በአንድ ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ክርስቶስን «መጋባት አይጠቅምምን?» ብለው በጠየቁት ጊዜ እንዲህ የሚል ቃል አስተምሯቸው ነበር። «ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉም አይደለም። በእናታቸው ማህፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ። ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ። ስለመንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው።» ይህንንም ቃል በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ ቁጥር አስር ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን። እኛም በዚህ ገዳም ውስጥ ያለን መናንያን በዚህ ቃል ጥሪ የመጣን የክርስቶስ ጃንደረቦች ነን። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለው ሰዎች የሰለቡንም እንኖራለን። ብዙዎቻችን ግን ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳችንን የሰለብን ነን።» ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብለው ሁለቱንም በየተራ ተመልክተዋቸው መልሰው ንግግራቸውን ቀጠሉ።

«ብልቶቻችሁን የአመፃ የጦር እቃ አድርጋችሁ አታቅርቡ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን በተቻለን አቅም መስለብ ያለብን ከፉ ሀሳባችንን እንጂ አካላዊ ብልታችንን አይደለም። አንድ መነኩሴ ብልቱን ሰልቦ ቢመንን ከፉ ሀሳቦቹን ካልሰለበ ዋጋ የለውም» መጋቢው ቀና ብለው አባ ዲዎላን ተመለከቱ። አባ ዲዎላ በልባቸው ያለውን ሀሳብ ሁሉ ያወቁባቸው መስሏቸው ኩምሽሽ አሉ።

መጋቢው ቀጠሉ። «በዚህ ገዳም ውስጥ እንግዲህ ስለመንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች ወንድሞቻችሁ ይህን አለም ንቀው፣ መድሃኒታቸውን መስለው፣ ድምፀ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሰው፣ የእሾህ አክሊሉ ምላሌ የሆነውን ቆብ ደፍተው፣ ወገባቸውን በሰንሰለት ታጥቀው፣ ከዲያቢሉስ ጋር እየተዋጉ ያሉ ናቸው። ሆኖም «ሁሉን ትተህ ተከተለኝ» ያለውን ቃል በመያዝ እንጂ በዓለም ውስጥ የካበተ ሀብት የነበራቸው፣ ከብርና ዝና የነበራቸው ባዕለፀጋዎችም በዚህ ገዳም ውስጥ አሉ።

አመድ ነስንሰው ማቱ ለብሰው ለመፀለይ የመጡበት ምክንያት ይህንን የሚያልፈውን ዓለም ንቀው የማያልፈውን ዓለም ናፍቀው ነው።»

በዚህ መሀል ሁለት መነኮሳት የእግር ውሃ ይዘው መጡ። ሚራዥና ዲዎላ እኛው ራሳችን እንታጠባለን ብለው አሻፈረኝ ቢሉም ሁለቱ መነኮሳትን ተከትለው የመጡት ሌሎች ጠርቀም ያሉ መነኮሳት እኔ አጥብ እኔ አጥብ ብለው በመሻማት አጠቧቸው። ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ዝቅ ብሎ ያጠበውን አብነታዊ ቃል ለመፈፀም ሲሉ ሁሌም እንግዳ ሲመጣ እግር ለማጠብ ሽሚያ ነው። ከበረከቱ ለመካፈል ሲሉም የአባ ሚራዥን ሁለት እግሮች ሁለት መነኮሳት፣ የአባ ዲዎላን ገንደፊላ እግርም ሁለት መነኮሳት ተሻምተው አጠቧቸው። በተለይ አባ ዲዎላ በሰው እጅ ሲታጠቡ የመጀመሪያቸው ነበር። ምናልባት በሰው እጅ የታጠቡት ከእናታቸው ማህፀን አልል አሥር ተብለው ሲወለዱ ብቻ ሳይሆን አይቀርም። መነኮሳቱ ዝቅ ብለው ሲያጥቧቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የጌትነት ስሜት ተሰማቸው። በዶን ሞርሞርዲኖ ቦታ ተቀምጠው ሲሲሊን ሲያንቀጠቅጧት ታያቸው በሀሳባቸው። ባራያ የሆኑትን ያህል ጌታ ለመሆን ወደ ጌትነት የሚያወጣቸውን መሰላል ሲያቆሙ በሀሳብ ታያቸው። «ጌታ ለመሆን በአንድ ወቅት ባራያ ትሆናለህ።» በውስጣቸው አጉረመረሙ።

አባ ዲዎላ እጃቸውን ሲታጠቡ የግራ እጃቸው ጣቶች አራት መሆናቸውን አባ ሚራዥ ተመለከቱና ሰቀጠጣቸው። ትንሽ ጣታቸው የት ገባች?

አጥበው ታጥበው ከጨረሱ በኋላ መነኮሳቱ ሁሉ ቆሙ። ከመነኮሳቱ አንዳቸው «ፀሎት ይሰጠን።» አሉ። መጋቢው እግር በማጠብ የተሳተፉትን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲባረኩ ከመረቁ በኋላ አቡነ ዘበሰማያት ተደግሞ መነኮሳቱ የመጣውን ምግብ ለእንግዶቹ አቅርበው ወደ መጡበት ተመለሱ። በፀሎቱ ማዕድ ቡራኬ ምግቡ ከተባረከም በኋላ እንግዶቹ አባ ሚራዥና አባ ዲዎላ መመገብ ጀመሩ። የመጀመሪያውን ቁራሽ ከመጉረሳቸው በፊት «ይባርኩልኝ» አሉ አባ ሚራዥ ወደ መጋቢው እጅ ነስተው «ያስምርልዎት» አሉ መጋቢው። ስርዓቱን ባለመርሳታቸው ተደሰቱ።

አባ ዲዎላ ግን ይህን ሁሉ ስለማያውቁ ምግቡ ከመቅረቡ ለመቁረስ የቀደማቸው የለም ነበር። አባ ዲዎላ ምግቡን ሲያዩት ቀኟቸዋል። ዳቤ የሚባለውና ከዳጉሳ እህል የሚዘጋጀው ይህ ምግብ ከጉሮሮ የሚወርድ አይመስልም። «ቂጣ አይሉት እንጀራ ምን አይነት ጉድ ነው?» በምሬት ተቆራመዱ። እንዳይተውት እውነተኛ መነኩሴ ለመምሰል የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ መክሳሸቱ ነው። ዳቤ የማያውቅ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ከየት የመጣ ነው? ወገ በጠገበው ጥራር ላይ ያፈጠባቸውን ጥልግሞት የመሰለ ዳቤ ሲያዩ ተነስቶ የሚያንቃቸው መሰላቸው። ፋጋ በሚባለው የቅል ስባሪ የቀረበላቸው

ወጥ ከደራሽ የጐርፍ ውሃ ተቀድቶ የመጣ መሰላቸው። «ይህን እየተመገቡ ነው ዘለአለም የሚኖሩት? የማይታመን። መንግሥተ ሰማያት ሲያንሳቸው ነው። የሰው ልጅ ግን ለምን ራሱን ያሰቃያል? ቆይ ይሄ መንግስተ ሰማያት ግን ምንድን ነው? እንዴት ሰው የተሰጠውን አለም ንቆ ገና ያልተሰጠውንና የማያውቀውን አለም ያፈቅራል? ኧረ እኔስ ዓለሜን አልንቅም። ከፈለጋችሁ ለምን እንጠርጠስ አትገቡም። ማንም አውደልዳይ በዓለም አልሳካለት ሲል ሌላ አለም እስኪመጣ ይጠባበቃል። ኧረ እዛው! እኔ ዲዎላ ኢየሱስም ይምጣ ሞርሞርዲኖ ለእኔ ያው ናቸው። ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን አወርስሃለሁ ሲል ሞርሞርዲኖ ደግሞ ሲሲሊን እሰጥሃለሁ ይለኛል። ሁለቱም አንድ ናቸው። የሰውን ልጅ በጥቅም ለመደለል። በምን ሒሳብ ነው መንግስሥትህ ትምጣ ብዬ የምፀልይለት? በዚህኛው መንግሥት ምን ተጠቀምኩ መጀመሪያ! ኢየሱስና መንግስቱ እዛው በሰማይ ይቆዩልኝ። ሞርሞርዲኖን ጌታዬ ስል በኖርኩበት አፌ ደሞ ኢየሱስን ጌታዬ ልል? ጌታዬ ስል እንድኖር ከፈጠረኝ ተሳስቷል። እኔ የራሴን መንግሥተ ሰማያት አዘጋጃለሁ። መንግሥተ ዲዎላ ቀርባለችና ሁላችሁም ገደል ግቡ። አለም ከኔ በተቃራኒ ቆማ ነበር። አሁን ግን በኔ ቁጥጥር ስር የምትውልበት ጊዜ በየሰከንዱ እየቀረበ ነው። መንግሥተ ዲዎላ እየቀረበች ነው።» አባ ዲዎላ ይሄን እያሰላሰሉ ምግቡን ማቆማቸውን ዘንግተውት ነበር።

«ይቅመሱ እንጂ አባ?» መጋቢው በሀሳብ ባህር የሰጠሙትን አባ ዲዎላን አባነኗቸው። «እየበላሁ ነው። እየበላሁ ነው ...ታምሜ ነበር የከረምኩት። ትንሽ የምግብ ፍላጐቴ ቀንሷል። ቀስ እያልኩ እስተ እንግዲህ እበላለሁ። ለእሁኑ ግን በቃኝ።»

አባ ሚራኛ የተሰጣቸውን መቁነን ጨርሰው «ስብሐት ለአብ» ብለው አመስግነው ማዕዳቸውን ከፍ አደረጉ።

መጋቢው ማዕዱ ከፍ ካለ በኋላ ስርዓተ ገዳሙን የሚመለከተውን ንግግራቸውን ቀጠሉ። «.....ቅድም እንዳልኩት ምንኩስና በወንጌል የተገኘ ጥበብ ነው። የምነና አብነታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መነኩሳት በምድር ያሉ መላእክት ናቸው። ለስጋቸው አይኖሩም። መነኩሴ ማለት «ምሙት ዘተፈልጠ እምአለም» ማለት ነው። ቢሰድቡት የማይላደብ፣ ቢመቱት የማይማታ በልቡ ክፉ ነገርና ቂም በቀል የማያስብ ነው። ምሙት ዘተፈልጠ እምአለም....ከዓለም በሞት የተለየ። .....በዓለም ሆኖ የሚራብ እሱ መነኩሴ አይደለም ሰነፍ ነው። መነኩሴ የሚራብ ግን እያለው ነው። ዘመድ አዝማዱን አይናፍቅም። በአቱን ለቆ አይወጣም። ተቀምጦ አይፈርድም። የመነኩሴ ሰይፉ ዐለቱ ነው። ሰይፍ አያነሳም። አይቆጣም። በቁጡ ሰው መንፈስ ቅዱስ አያድርበትምና። ቁጡ ሰው የሰይጣን ደቀ መዝሙር ነው።» ቀና ብለው ሁለቱንም አዩአቸውና ቀጠሉ።

«ሰው ስጋዊ ወመንፈሳዊ ነው። ሰው ፈቃደ ስጋና ፈቃደ ነፍስ የሚዋጉበት የጦርነት አውድማ ነው። በመሆኑም ከወንድሞቻችሁ አንዳቸው በፈቃደ ስጋ ቢወድቁ መሰናከል አይገባም። ስጋዊ ወመንፈሳዊ መሆናቸውን ካወቃችሁ በቂ ነው። የነገሩትን ሳያስተውል ፈጥኖ የሚያምን ሰው ልበ ቀሊል ነው። በገዳሙ ውስጥ የምታዩት ደስ የማያሰኝ ነገር ካለ ለአበምኔቱ መንገር እንጂ ባያችሁት ነገር መሰናከል የለባችሁም። ወደ ገዳሙ ማህበር ከተቀላቀላችሁ ወዲህ በገዳሙ ውስጥ ካለ ወንድሞች ጋር አብራችሁ ችግሩንም ደስታውንም መካፈል፣ በፀሎት ጊዜ መገኘት፣ በተለይ በተለይ ደግሞ ወላኝ ነገር ፍቅረ ቢፅ ነው። እርስ በእርስ መዋደድ። የገዳሙ ማህበር ለገዳሙ ስራ ካልሳካችሁ በቀር ወደ ከተማ መውጣት በጥብቅ የተከለከለ ነው። አንዴ ንቃችሁት ወደ መጣችሁበት ዓለም መመለስ የለባችሁም።»

«ኧረ እኔስ የናኩት አለም የለኝም። አለም ንቃው የመጣ መነኩሴ ሁላ አለምን ንቄ መጣሁ ቢል አይደንቀኝም።» አባ ዲዎላ በውስጣቸው አፈዙ።

መጋቢው መነኩሴ «.....የገዳሙ አበምኔት አባ ዝንበሩ የተረፈውን ይነግሯችኋል። ነገ ጠዋት።» ብለው እጅ ነስተው ወጡ።

፲፪

አባ ሚራኾ ከደሴቱ ላይ ባለው ኮረብታ የገዳሙ ደወል ድምፅ ሲያስተጋባ ነቅተው እያናቸውን ሞኾቀው ሊቃኙ በእንግዳ ቤቱ ውስጥ ማንም የለም ነበር። አባ ዲዎላ የተኙበት መደብ ባዶ ነው። የንጋቷ ፀሐይ እግሮች በቤቱ ግድግዳ ንቃቃቶች ሰርገው ገብተዋል።

ከጀርባቸው የማይለየውን ረጅም ሻንጣ እንደ ልጅ አዝለው ወደ ወደቡ ወረዱ። አባ ዲዎላ በጣና ዳር በወደቀው አይናማ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው እየተጣጠቡ ነበር። አባ ሚራኾ ከአባ ዲዎላ ጥግ በሚገኝ ሌላ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው በማዕበል ግፊት ከድንጋዩ እየተጋጨ በሚመለሰው የጣና ሐይቅ ውሃ ያደረ ፊታቸውን አለቃለቁት።

አባ ዲዎላ ወደ ጫካው ሮጠው ገቡና ኪሳቸው ውስጥ የተንፈራፈረውን ተንቀሳቃሽ ስልክ እናግረው ከመመለሳቸው ሰባት ሰዎችን የጫነች ዘመናዊ ጀልባ እየተንደቀደቀች ከተፍ አለች። በውስጧ ግሊያናዊው የማፍያ አለቃ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ከአራት አጃቢዎችና ከአስተርጓሚዎች ጋር ጀልባዋ ላይ ተቀምጠዋል።

ጀልባዋ ወደ ወደቡ እንደተጠጋች አራቱ አጃቢዎች ከጀልባዋ ወጥተው አካባቢውን ተቆጣጠሩት። ዶን ሞርሞርዲኖ ሐበሻው አስጐብኚ ወጣት የሚለፈልፈውን አንድም ሳይሰሙ የገዳሙን በር ወደ ግራ ትተው ኮረብታው ላይ ወደታነፀው ቤተክርስቲያንና ሙዚየም የሚያደርሰውን ቀጭን መንገድ ተያያዙት።

ዲዎላና ሚራኾም ከጐብኚዎች ኋላ እየተከተሉ ወደ ኮረብታው ወጡ። ከኮረብታው ወገብ ላይ የፃድቃን ማረፊያ የምተባለው ቦታ ሲደርሱ ከፊት የሚመሯቸው መነኩሴ እረፍት እንዲያደርጉ ጋበዟቸው። የፃድቃን ማረፊያ ላይ ሳያርፍ ማንም ሰው ወደ ቤተክርስቲያኑ አይሄድም። ነፍ ላብ የሚያስልበው አቀበት የዶን ሞርሞርዲኖን ሳንባ ከደረታቸው ወትፎት ስለነበር ማረፉን አልጠሉትም። አባ ዲዎላም ፍየል ፍየል እየሸተቱ ነበር።

የፃድቃን ማረፊያ የዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳምን የመሠረቱት ፃድቁ አቡነ ሂሩተ አምላክ ወደ ደሴቱ ሲመጡ በጣና ሐይቅ ላይ እንደ ጀልባ አድርገው በላዩ ላይ ተቀምጠው እየቀዘፉ የመጡበት ተአምራዊ ድንጋይ የተቀመጠበት ቦታ ነው። ሐበሻው አስጐብኚ ወጣት ወደ ዶን ሞርሞርዲኖ ዞሮ «ይህ የምታዩት ጠፍጣፋ ጥቁር ድንጋይ ገዳሙን የመሠረቱት አቡነ ሂሩተ አምላክ በ1268 ዓመተ ምህረት በጣና ሐይቅ ላይ እየተንሳፈፉ የመጡበት የድንጋይ ታንኳ ነው።» አለ። ስሜት አልሰጣቸውም። ሊናገሩ ያሉትን ቃል መልሰው ዋጡት። «ይህ ሲሲሊ አይደለም።» አለ ውስጣቸው። ሲሲሊ ውስጥ የፈለጉትን የመናገር አቅም ብቻ ሳይሆን

የፈለጉትን ባለስልጣን የመፈንቀልም ስልጣን በእጃቸው ነው። ለዶን ሞርሞርዲኖ በምድር ላይ ሁሉንም ነገር የማድረግ ተአምር የተቀበረው ገንዘብ ውስጥ ነው። እንደእርሳቸው ድምዳሜ ስልጣን የገንዘብ ነው። መብት የገንዘብ ነው። ኃይልም ገንዘብ ነው። አቡነ ሂሩተ አምላክ ምናልባት በቅድስና ድንጋይ በውሃ ላይ ማንሳፈፍ ችለው ቢጋልቡ ግድ አይሰጣቸውም። ዶን ሞርሞርዲኖ ሲሲሊና ህዝቦቿን ሜዲትራንያን ባህር ላይ እድሜ ልካቸውን ሲጋልቡ ኑረዋል። «ቅድስና ድንጋይ ሲያስጋልብ ገንዘብ ደግሞ ህዝብ ያስጋልባል።» አሉ በውስጣቸው ሞርሞርዲኖ። ለዶን ሞርሞርዲኖ ታሳቁ የምድራችን ባለ ስልጣን ገንዘብ ነው። ቅድስና አይደለም። ለእሳቸው በጣና ሐይቅ ላይ የተንሳፈፈው ተአምራዊው የአባ ሂሩተ አምላክ ድንጋይ ቅንጣት ታህል ስሜት አልሰጣቸውም። እድሜ ልካቸውን ሲመኙት የኖሩትና ለአባታቸው ቡስኪ ከአቅም በላይ የሆነው ምስጢር ነው ስሜት ሊሰጣቸው የሚችል። የሩቁን አቅርቦ በሚያሳይ መነጽራቸው በደሴቱ ዳርቻ ደቡባዊ ምሥራቅ በኩል ያለውን ጣሊያን የሠራውን ወደብና በደሴቱ በኩል ለሚያልፉ መርከቦች ምልክት እንዲሆን የተከለውን የመብራት ማማ እየተመለከቱ ነበር ወደ ደሴቱ የሰሜኑ ወደብ የተጠጉት። ጣሊያናዊው ከበርቴ ሞርሞርዲኖ ቡስኪ በዳጋና በደቅ ደሴት መካከል በምትገኝ አነስተኛ ደሴት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ከከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ጋር ስምምነት የተፈራረሙት ከሁለት ቀናት በፊት ነው። ይህንን የኢንቨስትመንት ስምምነት ፊርማ የመፈራረማቸው ዜና እንዲህ ዓይነት ዜናዎች በየቀኑ ስለሚደመጡ ማንም ትኩረት አልሰጠውም እንጂ በሀገሪቷ ቴሌቭዥንና ሬድዮ ተሳልፏል። የጣና ሐይቅ አርጃኖዎች ፀሐይ መሞቂያ በሆነችውና የደሀ ሰው መዳፍ በምታህለው ብጣቂ ደሴት ላይ ለምን ዓይናቸውን እንደጣሉ ከእርሳቸውና ከአንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን በቀር ማንም አያውቅም። ግሩ ሲል የምስጢሩ ጫፍ የተያዘው በአባ ዲዎላ ነው። አባ ዲዎላ ወደ ዳጋ የመጡበት ጉዳይ በእርሳቸውና በዶን ሞርሞርዲኖ የተያዘ ከፍተኛ ምስጢር ነው። በርግጥ በብጣቂዋ ሰው አልባ ደሴት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ስምምነት ተፈራረሙ እንጂ ምን ኢንቨስት እንደሚያደርጉ በውል የሚታወቅ ነገር የለም። የተዘገበ ነገር ቢኖር አንድ ጣሊያናዊ ባለሃብት በአማራ ክልል ኢንቨስት ለማድረግ ስምምነት መፈራረማቸው ብቻ ነው። በእነሰተኛዋ ሰው አልባ ደሴት ላይ የሰፈሩት የሞርሞርዲኖ ሰዎችም በዛች ደሴት ላይ ምን እንደሚሰሩ አያውቁም። ለስንቅ ማመላለሻ ተብላ ከሲሲሊ ተጭና መጥታ የተገጣጠመችው ዘመናዊ ጀልባ ደሴቱን ልታህል ምንም አልቀራትም። በተተከለት ታሳላቅ አረንጓዴ ድንኳኖች ውስጥ የተቀመጡት የሞርሞርዲኖ ሰዎች እስከ አፍንጫቸው ታጥቀው ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ይህ ከሆነ በኋላ ነበር ዳጋ ገዳምን ሊጐበኙ የተንቀሳቀሱት። በእቅዱ መሠረት ጉብኝቱ ተጀምሯል።

ሞርሞርዲኖ በሰው አልባዋ ደሴት ላይ የሰፈሩበት ምስጢር ቁልፍ በዚህኛው ገዳም ውስጥ ደብዛው እሰኪገኝ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም። ካስፈለገም ደሴቱም ቢሆን ተንዶ ወደ ጣና ሐይቅ ይገባታል እንጂ የሚፈልጉት ነገር እስኪገኝ የማይሞከር ነገር አይኖርም። ለገዳሙ የለገሱት ገንዘብ ነገሮችን እንደሚያለሰልስ ተስፋ አድርገዋል። ከፃድቃን ማረፊያ ተነስተው የቤተ ክርስቲያኑን ጥንታዊ ስዕሎችና ንዋየ ቅድሳት ከጉበኙ በኋላ የሃገሪቷ ውድ ቅርሶች ወደ ተከማቹበት ወደ ገዳሙ ዕቃ ቤት ገብተው መጐብኘት ጀመሩ።

በዕቃ ቤቱ ውስጥ ረዥም ዘመናትን ያስቆጠሩ የብራና መፃሕፍት ታጭቀዋል። በሌላ ገዳማት ብዙም የማይገኙት መፅሐፈ ቀሌምንጦስ፣ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ ረቱዐ ሃይማኖት፣ ገድለ ሰማዕታት፣ ወንጌል ዘወርቅ በመባል የሚታወቀው በስዕል ያሸበረቀው ወንጌል፣ ባለሐረጉ መፅሐፈ አሪትና ግብረ ሕማም ጥቂቶቹ ናቸው። ለብዙ ሰዎች የማይታዩት እንደ መፅሐፈ ሐዊ፣ መፅሐፈ ፊላሎጐስ፣ መፅሐፈ በለረአም፣ መፅሐፈ አቡሻኽር፣ መፅሐፈ ጥበብ፣ መፅሐፈ ራፋኤል ዘአዶናይ ..... እና ሌሎችም በግዕዝ ቋንቋ የተፃፉ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የህክምና.....መፃሕፍት እንደሚገኙ ይጠረጠራል። ከንጉሥ አፄ ዳዊት የተበረከቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ ተሰንጥሮ የተሰራና በዝሆን ጥርስ ያጌጠ የእጅ መስቀል፣ የሚከፈትና የሚዘጋ የነሐስ መስቀል፣ የወርቅ ዘውዳቸውና የነሐስ ነጋሪታቸው ተደርድሯል። በንጉሥ አፄ ዘርአ ያዕቆብ የተበረከቱ የወርቅ መስቀል፣ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈበትና «ወነቦ ከመያንዘር» የሚል ዕሑፍ የተቀረፀበት በአልማዝ ፈርጥ ያጌጠ በሀይወት ዘመናቸው ከእጃቸው ተለይቶ የማያውቅ የእጃቸው ሰይፍ፣ የንግሥናቸው የወርቅ ዘውድና የነሐስ ነጋሪታቸው በአንድ በኩል ተገጥግጠዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከንጉሥ አፄ ፋሲለደስ የተበረከቱ ተገጣጣሚ የወርቅ ቅብ አልጋ፣ ባለ ሦስት እግር የዙፋን ወንበር፣ የወርቅ ዘውድና ካባቸውና ቀንደ መለከት ተሰድረዋል። ከዚህም በተጨማሪ የአራቱ ነገሥታት አፅም የአፄ ዳዊት፣ የአፄ ዘርአ ያዕቆብ፣ የአፄ ሱስንዮስና የአፄ ፋሲል አፅም ሳይፈራርስ በመስተዋት ሳጥን ውስጥ በክብር ተቀምጧል። ከዚህ ሌላ የአስር ነገስታትና የዘጠኝ ጳጳሳት አፅም በገዳሙ ውስጥ እንደሚገኝ የእቃ ቤቱ ጠባቂ በቃል ለጐብኚዎቹ ገለፀላቸው። የዕቃ ቤቱ ጠባቂ በዝግታና በሰለለ ድምፅ የሚናገሩትን ታሪክ ሐበሻው አስጐብኚ ደስ እንዳለው ወደ ጣሊያንኛ አየተረጐመ ለነ ሞርሞርዲኖ ይተርክላቸዋል። ከዚህ ሁሉ ቅርስ የሞርሞርዲኖን ትኩረት የሳበ አንዳች ነገር የለም። አባ ዲዎላ ግን በመስተዋት ሳጥን ውስጥ በክብር የተቀመጠውን የነገስታቱን አፅም ሲያዩ አባታቸው አለቃ አያሌው የነገሯቸው ምስጢር ትውስ አላቸው። ከነገሯቸው ሁሉ ያዳመጧቸውም በዳጋ እስጢፋኖስ ውስጥ ስለሚገኙት የነገሥታት አፅም የነገሯቸውን ታሪክ ነበረ። በተለይ

የንጉስ አፄ ዘርአ ያዕቆብን አፅም ወደ መስተዋቱ ሳጥን በጣም ተጠግተው በትኩረት ተመለከቱት። ሽው ወዳለ ትዝታ ሊገቡ ሲሉ ጉብኝቱ ተጠናቀቀ። ከእቃ ቤቱ ወጥተው የዕቃ ቤቱ በር ተዘጋ።

የአባ ሚራኾን ትኩረት የሳበው ደግሞ የአፄ ዘርአ ያዕቆብ የእጃቸው ሰይፍ ነበር። «ወነቦ ከመ ያንዘር» የሚል ዕሑፍ የተቀረፀበት። በትክክል መምጣት ወዳለባቸው ቦታ ለመምጣታቸው እርግጠኛ ሆነዋል። ጉብኝቱ ተጠናቀቀ። የእቃ ቤቱ ጠባቂ በሩን ጠርቅመው ዘግተው አባ ሚራኾን ጥለዋቸው ከእቃ ቤቱ ጥግ ወደታነፀችው የግል ቤታቸው ገቡ።

«ባሪያው! በል የነገርኩህን ሁሉ በልብህ አኑረው። ይህንን ተልዕኮ በብቃት ከፈፀምክ ጠንካራው ቀኝ እጄ ለመሆን ማንም የሚቀናቀንህ የለም።» አሉ ሞርሞርዲኖ እስከ አባ ዲዎላ ጆሮ ተጠግተው በሹክሹክታ። ቁልቁሉቱን እየወረዱ እያለ።

«እስከ አሁንስ ቀኝ እጅዎ አልነበረኩም እንዴ?»

«እስከ አሁንማ ባሪያዬ ነበርክ። ደነዝ! የምልህን ዝም ብለህ አዳምጠኝ። ጌታ የምትሆንበት ጊዜ እስከ አፍንጫህ ቀርቧል። ቁንጅና ድህነትን እንደሚሸፍን ገንዘብም ባርነትን ይጋርዳል። ብልፅግናህ ጥቁረትክን ይደብቀዋል። ያኔ የዓለማችን ኃያል ሰው ትሆናለህ። አለበለዚያ እንደ አሀያ ጆሮህን ጐትቼ የመጫን የማዘዝ መብቴ እንደተጠበቀ ይኖራል። ገንዘብ ከሌለህ ምን አቅም አለህ?.....የምታሸንፈውን መግዛትና መበዝበዝ የተፈጥሮ ህግ ነው። ሰይጣናዊ ህግ አይደለም። አሸናፊዎች ይኖራሉ። በዚህ ወቅት ለደህ እና ለህብታም እኩል ተፈጥሮ የሰጣቻቸውን ውሃ ሳይቀር ገንዘብ ደረጃውን አወራርዶታል። ውሃ ሁሉ እኩል አይደለም። ህብታም የተጣራና ከጀርም የፀዳ ውሃ ሲጠጣ ደህ ደግሞ እንደበሬ አጐንብሶ ከደፈረሰ ጅረት ለንጨጩን ነክሮ ይጠጣል። በዚህ እንኳ ያለው ልዩነት ይታይህ። ሁሌም ስለገንዘብ አስብ። ገንዘብ ካለህ መሪ ነህ። በቃ ገባህ?»

«አምን ገብቶኛል ጌታ ሞርሞርዲኖ።»

«ውሸትክን ነው አይገባህም። አንተ የሚገባህ ሰው አይደለህም በንቃትህ ላይ አውቀህ የተኛህ አህያ ነህ።»

«አይደለሁም ጌታ ሞርሞርዲኖ! በግዛቴ ውስጥ መጥተው አይባደቡ። ይህ ሲሲሊ አይደለም። ቆቤንና መጐናፀፊያዬን አያዩም እንዴ? ከንፍ አልባ መልአክ መስዬ ሳለ አህያ ይሉኛል?»

«ይቅርታዎትን አይንፈጉኝ ብፁዕነትዎ!» አሉ ዶን ሞርሞርዲኖ ደሴቱን የሚያናጋ ሳቅ ስቀው። «ይልቅ የአንዱ ክፍለ ሀገር ጳጳስ አድርገው እንዳይሾሙዎት ይጠንቀቁ።» አባ ዲዎላም የቋጠሩት ሳቅ ፈነዳ። ቀይ ድዳቸው ተሰጣ። የበርበሬ ጭቅጭቅ የመሰለች አንድ ዓይናቸውን አጥብበው ተንከተከቱ። ሞርሞርዲኖ የአባ ዲዎላን መቀመጫ ቸብ አድርገው ክንዳቸውን ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ቁልቁል ከረብታውን መውረድ ጀመሩ።

፲፫

አባ ዲዎላና አባ ሚራኾር በገዳሙ እንዲኖሩ የፈቀዱላቸው መጋቢው ነበሩ። አበምኔቱ አባ ገርንበሩ ከበአታቸው ወጥተው ለአባዲዎላና ለአባ ሚራኾር ፀሎተ ማርያም አድርሰው ለምን እንዳልተቀበሏቸው ግልፅ አልነበረም።

በመሆኑም ለአባ ዲዎላና ለአባ ሚራኾር በመጋቢው ሰብሳቢነት የገዳሙ መነኮሳት ፀሎት አድርሰው ከተቀበሏቸው ሰንበትበት ብለዋል። ለገዳማውያኑ እንደ ሚደረገውም ፀጥታ በዋጠው ጫካ ውስጥ ተፈናጥረው ከሚገኙት ጎጆ ቤቶች ለየግላቸው በአት ተሰጥቷቸዋል። ጐጆ ቤት። በዚህ ገዳም ውስጥ ከሰባት መቶ በላይ መነኮሳት እንደሚኖሩ ቢገመትም ደሴቱ አንድ ሰው እንኳ የሚኖርበት አይመስልም። ፀጥታ። መነኮሳቱ የሚገናኙት በህብረት ያሥራ ዘመቻ ወይም በህብረት ፀሎት ጊዜ ነው። ከዚህ በተረፈ ግን ካልተጠራ በቀር ማንም ወደ ማንም በአት ድርሽ አይልም። ቢመጣ እንኳ ወደ ቤት ከመግባቱ በፊት በሩቅ ሆኖ ያጨበጭባል። ሰው መጥቶ ካልተቀበለው በድፍረት ወደ ቤት አይገባም ወደ መጣበት ይመለሳል እንጂ። ይህም የሆነበት ምክንያት መነኮሳቱ ፀሎት ከጀመሩ ማንንም ስለማያናግሩ ነው። በተመስጠ ውስጥ ያለን መነኩሴ ማወክ በጥብቅ የተከለከለና ጠያፍ ነው። በገዳሙ ውስጥ ከሚታየው የጠበቀ አንድነት ጋር ግለሰባዊ ነፃነትም ይጠበቃል። ለእያንዳንዱ መናኒ በነፃነት የሚፀለይበት፣ የሚመሰጥበት፣ የሚያነብበት ቤት ለብቻው ይሰጠዋል። እንደ ስርዓቱ በቤቱ ውስጥ ሥጋዊ ሥራ ቢሠራ የሚያየውም የሚቀባውም አንድዬ ብቻ እንጂ ካልተናዘዘ በቀር ማንም መጥቶ አይከታተለውም።

የአባ ዲዎላና የአባ ሚራኾር ምነና በገዳሙ ትክክለኛ ሥርዓት መሠረት ቢሆን ኖሮ መጋቢው ይቀበሏቸዋል። ከዚያም ለሰባት ቀናት ያስተናግዷቸውና በሰባተኛው ቀን ለማህበሩ ካስተዋወቋቸው በኋላ እንደ ገዳሙ ሥርዓት አገልግሎታቸውን ይጀምራሉ።መጋቢው ይቀበልና በአበምኔቱ አማካኝነት ለማህበሩ ሃይማኖታቸውን በመሃላ ካረጋገጡ በኋላ ስማቸው ተመዝግቦ የአመክሮ ጊዜያቸውን ይጀምራሉ። ደንቡና ሥርዓቱ እንዲህ መሆኑን ቀድመው የተረዱት አባ ዲዎላና አባ ሚራኾር ግን ራሳቸውን አመነኩሰው ሥርዓተ ገዳምን የጠነቀቁ መስለው መጡ።

ዓለመ ምንኩስናን መርጠ ወደዚህ ገዳም የሚመጣ ማንኛውም ሰው እንደ ከዚህ ቀደሙ ቢሆን ኖሮ እንደደረሰ የምንኩስና ቆብ አይደፋለትም። ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ከማህበሩ በተመረጠ መምህራን ሥርዓተ ምንኩስናንና ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን እየወሰደ ይቆያል። ይህም የዕጩ መነኩሴ የአመክሮ ጊዜ ይባላል።

የእጩውን መነኩሴ የውሳኔ ዕናትና ቆራጥነቱን ለመፈተሽ መምህራኑ ልዩ ልዩ ከባድ ፈተናዎች ይሰጡታል።

በ1964ዓ.ም በሲኖዶስ በወጀቀው የገዳማት ሙተዳደሪያ ደንብ መሰረት ማንኛውም መነኩሴ የግል ገንዘብ /ቁሪት/ እንዳይኖረው መደንገጉ እሙን ነው። መናኝ ወደ ገዳሙ ከመምጣቱ በፊት ትዳርና ንብረት ያለው ከሆነ ከሦስት ሁለት እጅ የሚሆነውን ለቤተሰቦቹ ትቶ ከሦስት አንድ እጅ ለገዳሙ ገቢ ማድረግ አለበት።

አባ ዲዎላን ሞንቅ ያሳቸው ከዚህ ገዳም የሚያስባርሩ ሀጢኣትን አለማወቃቸው ነበር። በኋላ ግን አንድ አልፈው ወደ ኮረብታው የሚወጡ መነኩሴ ቤታቸው በር ላይ አስቁመው ጠየቁና ተረዱ። መነኩሴው የገለፁላቸውም በሲኖዶሱ አንቀፅ አሥራ አምስት ላይ ያለውን ድንጋጌ ነው።

አንቀፅ አስራ አምስት መሰረት አንድ መነኩሴ ከገዳሙ ስለማሰናበቱበት ሁኔታ ጠንቅቀው ተረድተዋል። አንድ መነኩሴ የገዳሙን ሕግና ትዕዛዝ በመተላለፍ ያለአባምኔቱ ፈቃድ ከቅዕረ ገዳሙ ወጥቶ ወደ ዓለማውያኑ ከተማ ወይም መንደር ቢወጣና ቢወርድ በመጀመሪያ ከማህበሩ ሁለት ሁነው ይመክሩታል። ባይሰማ ወደ አበምኔቱ አቅርበው ያስመክሩታል። አበምኔቱንም ባይሰማ ማህበሩ ፊት አቁመው ይመክሩታል። አሁንም ማህበሩን ባይሰማ ከማህበሩ ተለይቶ ቀኖና ይሰጠዋል። ቀኖናውን አልቀበልም ቢል ከገዳሙ ይባረራል። በማቴዎስ ወንጌል ቃል መሠረት።

መነኩሴው ለአባ ዲዎላ ያልገለፁላቸው አንድ ሌላ ነገር አለ። ቀኖናው ምን እንደሆነ አልገለፁላቸውም። አባ ዲዎላ የገመቱት ቀኖናው ስግደት ወይም ፀሎት ይሆናል ብለው ነው። ግን ሌላም አለ። ከገዳሙ መሃል ፈንጠር ብላ በተሠራችው ቤት ውስጥ ከአንድ ሁለት ቀዳዳ ካለው ሽንቁር ግንድ በቀር ማንም አይኖርም። የዚህ ግዙፍ ግንድ ሽንቁሮች የእግር ማስገቢያ ናቸው። ሲኖዶሱ በሚያዘው የማይመራ ወንበዴ መነኩሴ በግንዱ ሽንቁር ሁለት እግሮቹን እንዲያስገባ ከተደረገ በኋላ በእግረ ሙቅ ይቆለፍበታል። ተነስቼ ላምልጥ ቢል እንኳ ያንን ግዙፍ ግንድ በታሰሩ እግሮቹ ተሸክሞ መቆም እንኳ አይችልም። ለመተኛትም አይመችም። ቁጭ ብሎ ይመሻል፡ ይነጋል። ሰይጣን ባይኖርበት እንኳ ሞንቅ ሞንቅ ብሎት መለፍለፍ ይጀምራል። የተወሰነለትን ቅጣት ሳያፈፅም ማንም ያንን አስፈሪ ቤት የሚከፍት የለም። እግረ መቁንጮ የሚከፍትለት ማንም አይኖርም። ሊጐበኙት እንኳ የሚችሉት ሰአል በሚመስለው ቤት ውስጥ የሚረወጡት አደገኛ የጫካ ሽረራቶች ብቻ ናቸው። ምናልባት ይህ የቅጣት ዓይነት ለእንግዳ መነኩሴና ለአዲስ መናኝ በግልፅ ስለማይነገር ይሆናል መነኩሴው ለአባ ዲዎላ ያልነገሯቸው። ከዚህ ጋር አያይዘውም ሌሎች ሥርዓቶችን ነግረዋቸዋል። መነኩሴው ሲናገሩ «የኢትዮጵያ ገዳማት የሀገሪቷ ጥንታዊ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው» ብለው ነበር። በህዝብ አመራር እንደነ አፄ ቴዎድሮስ ያሉ መሪዎች የወጡት ከገዳማት መሆኑን

በማብራራት። የኢትዮጵያ ጥንታዊ ስነ ሀንፃ፣ ሥነ ፅሑፍ፣ የህክምና ጥበብ.....የፈለቀባቸው እነዚህ ጥንታውያን የኢትዮጵያ ገዳማት ከዩኒቨርሲቲ ጋር የሚመሳሰል የአንድነት አኗኗር ዘይቤ እንዳላቸው ነበር የነገሯቸው። የገዳሙ ደወል ሲደወል መነኮሳቱ ፀሎታቸውን አሳርገው የመቁነን እቃቸውን ይዘው ይወጣሉ። የፈለገ ግብር ቤቱ ውስጥ የፈለገ ወደ ግል በአቱ ወስዶ መመገብ ይችላል። በዋልድባ ከደረቀ የሙዝ ዱቄት የሚሠራ ቋርፍ የተባለ ምግብ፣ በደብረ ቢዘን ደግሞ እንጀራ በወጥ በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ግን ዳቤ የሚባለው ምግብ ይቀርባል። የሆነው ሆኖ የመቁነን ሥርዓቱም ሆነ ይዘቱ ቢለያይም በየትኛውም ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት የሚመገቡት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። በመቁነን ወቅትም እንደ ዜና አበው፣ መፅሐፈ ገነት የመሳሰሉት መፃሕፍት ይነበባሉ። በአበምኔቱ መሪነት ፀሎት ተደርጉ ማህበረ መነኮሳቱ ይመገባሉ። የመቁነን ሥርዓት ሲፈፀምም በአበምኔቱ መሪነት አቡነ ዘበሰማያት የተሰኘው ፀሎት በዜማ ይፀለያል። በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳትም በመቁነን አይበላለጡም ሁሉም እኩል መጠን ያለው ምግብ ይመገባሉ።

በኢትዮጵያ ሲኖዶስ አንቀጽ ፲፫ በተደነገገው መሠረት ለእያንዳንዱ መነኩሴ በየዓመቱ አንድ ጊዜ አንድ የሥራና አንድ የበአል ልብስ ይሰጠዋል። ዓመቱ ደርሶ ሌላ አዲስ ልብስ ሲቀበል አሮጌውን ያስረክባል። የብርድ ልብስና ምንጣፍ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ይታደላል። ሁሉም መነኮሳት የሚለብሱት አንድ አይነት ልብስ ነው። ወደ ቢጫ ያደላ ወይባ የሚባል ቀሚስና መጐናፀፊያ። የመነኮሰው ሥርአተ ምንኩስናውን ሲፈጽም ተባርኮ የተሰጠውን ቆብ ያጠልቃል። ያልመነኮሰው የአመክሮ ቆብ ይደፋል። የፀሐይ ቆብ። ጥቁር ራስም አለ። ቆብ ያልደፋ።

አባዲዎላ በሰነበቱባቸው ቀናት የሚፈልጉትን ለማግኘት ብዙ ውስብስብ ነገሮች እንዳሉ ተረድተዋል። በየጊዜው በፀሎት የመገኘት ግዴታ አለባቸው። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ «በእኩለ ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሳለሁ» ያለውን መሠረት አድርገው መነኮሳቱ በመንፈቀ ሌሊት ለፀሎት ሲነሱ ጣፋጭ እንቅልፋቸው እያዳፋቸው ወደ ፀሎት ቤት ይሄዳሉ። አባ ዲዎላ። ከዚያ ከሰዓታቱ ጋር መልክአ መልክዕና ተአምረ ማርያም ይነበባል። ከሰአታቱ በኋላ ደግሞ ሁለት የተመረጡ መነኮሳት ፀሎተ እጣን ያደርሳሉ፣ ከዚያም ፀለተ ኃይማኖት፣ መዝሙረ ዳዊትና ስንክሳር ይነበባል። ሊነጋጋ ሲል በእድሜ የበላይ በሆኑ ሽማግሌ መነኩሴ መሪነት የማህበሩ ፀሎት ለገዳሙ ስፋት፣ ለገዳሙ ያኑ ፍቅር፣ አንድነትና ከፈተና መጠበቅ ይፀለያል። ስለክርስትና መጠበቅና ስለ ሀገሪቷ ሰላምና አንድነት ምህላ ይቀርባል።

ከነጋቱ አሥራ ሁለት ሰአት ሲሆን መነኮሳቱ በየበአታቸው ሄደው የግል ፀሎታቸውን እንዲያደርሱ ይለቀቃሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን ለአባ ዲዎላ የሚገባቸው አንዳች ነገር የለም። አብዛኛው ፀሎትና ምህላ በጥንታዊው የግዕዝ ቋንቋ ነው የሚከናወነው። ስለዚህ አባ

ዲዎላ እግራቸው እንደቄጤማ እየተንቀጠቀጠ ዝም ብለው ቆመው ማደር እጣ ፈንታቸው ሆነ። ደግነቱ ያልተማሩና ፊደል ያልቆጠሩ እንደ እሳቸው እግራቸው እስኪቀጥን ቆመው የሚያድሩ ገበሬ መነኮሳትም አሉላቸው። በገዳሙ ውስጥ አለማወቅ አያስከስስም። እውቀትም የቅድስና ምልክት አይደለም። ለተማረ መነኩሴና ፊደል ላልቆጠረ መነኩሴ እኩል ክብር ይሰጣል። በዚህ ገዳም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የቅድስና መለኪያዎች ደግነት፣ ታዛዥነት፣ ንፅህ ልቡና፣ ቅንነት፣ ትጋትና ዕናት ናቸው። ሁሌም ከረፋዱ ሶስት ሰዓት ሲሆን በአስተባባሪዎች አማካኝነት እያንዳንዳቸው መነኮሳት እንደየችሎታቸው ለሥራ ይመማራሉ። ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን ኮረብታው ላይ ያለው ደዎል ያስተጋባል። ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ እስከ ሰባት ሰዓት የግል ፀሎት ያደርሱና ስምንት ሰዓት ሲሆን ሁለተኛው የማህበር ፀሎት ይደረጋል። በዚህ ጊዜ መነኮሳቱ በውሏቸው የሠሩት ሐጢአት ካለ ወደ አበምኔቱ እየቀረቡ ንስሐ ይገባሉ። ፀሎቱ ተጠናቆ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን የመቁነን ደዎል ይደወላል። ከመቁነኑ ፍፃሜ በኋላ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት መነኮሳቱ የግል ሥራቸውን በየበአታቸው በፀጥታ ይሠሩ ዘንድ ነፃ ጊዜ ይሰጣቸዋል። የሚያነቡት ያነባሉ፣ የሚታጠቡ ወደ ጣና ሐይቅ ወርደው ይታጠባሉ። አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ለሀብረት ፀሎት ደወል ይደወልና እንደገና ይሰበሰባሉ። ፀሎቱ ከተፈፀመ በኋላ ከመፅሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ክፍሎች ይነበባሉ። ስብሐተ እግዚአብሐር ይደረሳል።በመጨረሻም የዕለቱን ውሎ አስመልክቶ አበምኔቱ የተገደፈው እንዲስተካከል፣ የተጠናከረው እንዲበረታታ መመሪያ ይሰጡና መነኮሳቱ በየበአታቸው ይገባሉ። እንደገና ለሌሊቱ ፀሎት የደወሉ ድምጽ በደሴቱ አናት ላይ እስኪያንባርቅ።

ይህ ሥርዓት ለዘመናት ተጠብቆ እንዲኖር የሚሾመ መነኮሳት እጅግ የተመረመሩ የተፈተኑና በማህበረ መነኮሳቱ የታመነባቸው ናቸው። አስተዳደራዊ መዋቅሩም በአበምኔቱ፣ በመጋቢው፣ በገበዙ፣ በእቃ ቤት ጠባቂው፣ በፀሐፊው እና በሊቀ አርድዕቱ ላይ ይዘረጋል። የገዳሙ ንኅፈ የሆነው አበምኔት የአስተዳደራዊ መዋቅሩ ቁንጮ ነው። አበምኔቱ በትሩፋትና በአስተዳደራዊ ችሎታው የታመቀ መነኩሴና በማህበሩ ተመርጦ የሚሾም ነው። ግን.....በዚህ ገዳም ውስጥ.....ሽመት ለፈለገ ሽመት አይሰጥም። ለሽመት መታፈጊቱ የሚነገረው ሲሾም ብቻ ነው። አበምኔት ሆኖ የሚሾመው መነኩሴ የቁምስና ማዕረግ ያለው መነኩሴ መሆን አለበት። ማንኛውም መናኝ ለአባምኔቱ ምክርና ትዕዛዝ እንዲሁም መመሪያ መገዛት አለበት። አበምኔቱ በገዳሙ ለልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በንኅፈነት የሚሾሙ መነኮሳትን ከማህበሩ አስመርጠ ማሾም እንጂ በራሱ ፈቃድ ብቻውን ሽመት መስጠት አይችልም። በሲኖዶሱ መሠረት። የገዳሙ አበምኔት ከመመረጡ በፊት ምርጫው መቼ መሆን እንዳለበት ተወስኖ መነኮሳቱ በቢተክርስቲያን ውስጥ ይሰበሰቡና ይፀልያሉ።

በ1964 ዓ.ም በሲኖዶስ በፀደቀው የገዳማት መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ አራት መሰረት ምርጫው በድምፅ መስጫ ሳጥን በሚሰበሰብ ድምፅ ይካሄዳል። አበምኔቱ ከተመረጠ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ከማህበሩ ጋር ፀሎት ያደርሳል። ፀሎተ ቡራኬም ይደገማል። ከዚያ በተዘጋጀለት ቦታ ይቀመጥና መነኮሳቱ ተራ በተራ እጅ ይነሱታል። በዚህ ሁኔታ የተመረጠው አበምኔት ወደ ፓትሪያርኩ ይቀርብና ሹመቱ ይፀድቃል። አበምኔቱ ፈጣን ውሳኔ ይሰጣል። ለሚበላሹ ነገሮችና ለጠፉ ነገሮች ኃላፊነቱን ይወስዳል። በኃላፊነት የሚቀመጡ መነኮሳትን በገዳሙ ማህበር አስመርጠ ያሾማል።

ከአባምኔቱ ቀጥሎ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት መጋቢ ሆኖ የተመረጠ መነኩሴ ነው። የገዳሙ ገቢዎች በጊዜው እንዲሰበሰቡና ገቢ እንዲደረጉ ያደርጋል። አስቸኳይ መፍትሔ የሚያሻቸው የመወያያ ነጥቦች እየተቀበለ እንዲመከርባቸው ለአበምኔቱ ያቀርባል። በየወሩ መጨረሻ የገዳሙን አጠቃላይ የገቢ ሪፖርት ለአበምኔቱ ያቀርባል። ጉዋል መጋቢ የሚባል ምክትል መጋቢም አለው። ሲደክም ይረዳዋል። ገበዝ ሆኖ የሚመረጥም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተመደቡት መነኮሳት ሥራቸውን በትክክል እንዲሠሩ ይቆጣጠራል በጉደለም ይሞላል። የቤተክርስቲያኑን አልባሳት፣ ንዋየ ቅድሳትና መፃሕፍትም በደንብ ተጠብቀው እንዲቀመጡ ያደርጋል። የእቃ ቤት ጠባቂ ሆኖ የሚሾም መናኝ ግን እጅግ በጥብቅ ተመርምሮ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቱ ተመዝኖ ነው። በፍቅረ ንዋይና በቁሳዊ ፍላጐት የነደደ ሰው በዕቃ ቤት ውስጥ የሚቀመጡትን ቅርሶችና ውድ ሀገራዊ ሀብቶች ለመጠበቅ የሚችል ትክሻና ለሀገር ተቆርቋሪ የሆነ ሰፊ ልብ ያለው ሰው ተመርጦ ይሾማል። ፀሐፊ ሆኖ የሚመረጥ ደግሞ ወጭና ቀሪውን የገዳሙን ሀብት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። የገዳሙ ማህተምና የአበምኔቱ ፊርማ ላያርፍበት ማናቸውም ጉዳይ እንዳይሠራበት ተጠንቅቆ ይጠብቃል። ከመጋቢው በታች ተራ መናኝ ከሆነ አርድዕት በላይ ሆኖ ገዳሙን የሚያገለግለው ደግሞ ሊቀ አርድዕት ይባላል። ገዳማውያኑ ጉልበታቸውን አድክመው በላባቸውና በወዛቸው ለምግብ አቅርቦት እንዲሠሩ ያሰማራል።አትክልት ያስተክላል፣ ያስኮተኩታል፣ ያሳርማል፣ ያስቆፍራል። የማህበሩ ምግብ ከማለቁ አስቀድሞ ያዘጋጃል። ሊቀ አበው ሆኖ የሚመረጥ መናኝ ደግሞ በገዳሙ ውስጥ የታመሙ መነኮሳትን ይንከባከባል። ያረጁትን ይጠራል። ልብሳቸውን ያጥባል፣ ያሳጥባል። የዘጉትን መነኮሳት ይጐበኛል። በምድር ላይ ከሰው ልጅ ጋር ክፉም ሆነ በጐ ላለመናገር ወስነው እድሜ ልካቸውን በማንበብ፣ በመስገድ በመፀለይ በአታቸውን ዘግተው የሚኖሩ አበው መነኮሳትን በየዋሻው በየበአታቸው እየሄደ ይከታተላል። ያረፉት እንዲቀበሩ ያደርጋል። የዘጉ መነኮሳትን ስለማይነጋገሩ አስፈላጊ ነገሮችን የመመርመር ብቃት ያለውና አስተዋይ መሆን ይጠበቅበታል።

ከዚህ በተጨማሪም በገዳሙ ውስጥ ያሉ የህገሪቷ ምስጢራት እንዲጠበቁ እጅግ ከፍተኛ ወግ አጥባቂ የሆኑ ሽማግሌ መነኮሳት ከዚህ መዋቅር ጀርባ ቆመዋል። እያንዳንዷን እንቅስቃሴ አላዋቂ መስለው የሚከታተሉና በግልፅ የማይታዩ መነኮሳትም ተበጥሶ የማይዘለቀውን የመዋቅር ሰንሰለታዊ ገመድ ዘርግተዋል።

አባ ዲዮላ ይህን የጠበቀ ሰንሰለታዊ መዋቅር ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀባቸውም። በየአንዳንዷ እርምጃቸው መሰናክሎች ተቀምጠዋል። ወደዚህ ደሴት ሲገቡ በጫከው ውስጥ ድምፃቸውን አጥፍተው እንደጉንዳን የሚርመሰመሱት መነኮሳት ሞኞች መስለዋቸው ነበር። ብዙም ትኩረት ስላልሰጧቸውም የመጡበትን ከባድና ከባርነት ወደ ጌትነት የሚያደርሳቸውን ምስጢር ለመጨበጥ አፍታ እንደማያቆያቸው አምነው ነበር። ግን አንድም ውል ሳይጨብጡ ቀናቶች ነጐዱ። እጅግ ብዙ ኃይል የመሰብሰብ ያለው ረቂቅ የተንቀሳቃሽ ስልካቸው ባትሪም ሊያልቅ ነው።

የተንቀሳቃሽ ስልካቸው ባትሪ ከማለቁ በፊት ለዶን ሞርሞርዲኖ ለመደወል አሰቡ። ከረባዳው የደሴቷ ክፍል ሆነው ሲሞክሩ ተንቀሳቃሽ ስልካቸው አገልግሎት እንማያሰጥ ተረዱ። በደሴቱ ውስጥ የመረጃ መረብ ያለበትና የሌለበት ቦታ መኖሩን ያውቃሉ። በመሆኑም ወደ ኮረብታው በፍጥነት ወጡ። ነፍሱ ላብ እያላባቸው የተንቀሳቃሽ ስልካቸው ባትሪ ከማለቁ በፊት ኮረብታው ላይ ደርሰው ከትልቁ ዋርካ ላይ ወጡ።

በዋርካው ቅጠሎች ተሸፍነው ሙሉ በሙሉ ከመነኮሳቱ እይታ ውጪ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ወደ ዶን ሞርሞርዲኖ ደውለው በለሆሳስ መነጋገር ጀመሩ።

«አልቻልኩም» አሉ አባ ዲዮላ። «ልመለስ ነው።»

«እሺ ተመለስ። ግን አንድ ነገር ማወቅ አለብህ» ሞርሞርዲኖ በሚያስጠይፍና ንፁት በተሞላበት ድምጽ ከወዲያኛው ደሴት።

«ምን?» ዲዮላ ከወዲህኛው ደሴት።

«ለዘለአለም ባሪያዬ ሆነህ ትኖራለህ። እንደ አህያ እየቀጠቀጥኩ እንድገዛህ ፈቅደሀል።»

«አዎ ፈቅጃለሁ። እዚህም የስላሴ ባሪያ ነኝ። ከማላውቃቸው ሥላሴዎች ይልቅ የማውቅዎት እርስዎ ይሻሉኛል። እንደፈለጉ ያድርጉኝ።»

«አፈር ብላ!»

«ምን አሉ ጌታ ሞርሞርዲኖ» ስድቡን ሰምተዋል ግን.....

«ሃሞት የለሽ!»

«አይሰሙኝም ጌታ ሞርሞርዲኖ።»

«ዲያብሎስ!»

«ዲያብሎስ በሆንኩስ በተሻለኝ። የሰወሩትን አግኝው ነበር። እንዲያውም ዲያብሎስ መሆን አምሮኛል።»

«ኃይል እንጠቀም?» አሉ ጌታ ሞርሞርዲኖ።

«አንችልም!»

«እንዴት?»

«እዚህ ሁሉም ሞት የጠማው ነው። መነኩሴ አጥብቆ የሚፈልገው ነገር ቢኖር እረፍተ ሞቱን ነው። መነኩሴ የሚሆንም አስቀድሞ የሞተ ሰው ነው። እኛ ሳንገድላቸው አስቀድመው የሞቱ ናቸው። እንዲያውም በሰማዕትነት ለመሞት የሚሳል መነኩሴ ብዙ ነው። መነኮሳት ከዚህኛው አለም ይልቅ ለዛኛው አለም ጥልቅ ፍቅር አላቸው። ሞት ለመነኮሳት ወደ ዘለአለማዊነት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። ሞት በዚህ ደሴት ውስጥ ከዛፍ ጥላ አይበልጥም። ጌጥ ነው። ሞት ለነዚህ መነኮሳት ደስ የሚል ዕረፍት ነው። አይሰጡንም። ፍንክች ቢሉ አይሰጡንም። ለመስረቅ እንዳልሞክር ደሞ የሚሰረቀው ነገር የት እንደተቀመጠ አላውቅም። ለማሞኘትም አይመቹም።»

«አየውልህ ባሪያው! ፍቅር ያልፈታውን ገንዘብ ይፈታዋል። ገንዘብ ያልፈታውን ኃይል ይፈታዋል። በፍቅርና በገንዘብ አልሆን ካለን ኃይል ከመጠቀም ወደኋላ አንልም። ኃይል መጠቀም የመጨረሻው አማራጭ ነው።»

«ተሳስተዋል ጌታ ሞርሞርዲኖ። ኃይል ለመጠቀም አቅማችን አይፈቅድም።»

«እንዴት ነው የማንችለው? እኔ እኮ ሞርሞርዲኖ ነኝ! እንኒንስ አንድ ኋላ ቀር ደሴት እነ ሳልባቶሪ ጁሊያኖ፣ እነ አሞሪ አድሪኖ..... እነ....እነ... እነዛ ሁሉ ጀግኖች ነግሠው የኖሩባት ሲሲሊን ያንቀጠቀጥኩ ጀግና መሆኔን ረስተኸው ነው አንት ባሪያ! ይህን ደሴት ከፈለግሁ በግራ እጄ ገፍትሬ ጣና ሐይቅ ውስጥ ማስጠም አልችልም? ባሪያው! እስከ አሁን አላወከኝም ማለት ነው።»

«መለኮታዊ ጥበቃ የሚደረግለት ገዳም መሆኑንስ ልብ ብለውታል?»

«መለኮታዊ? ሃ! ሃ! ሃ!.....» ሞርሞርዲኖ በለበጣ እንደ እህል ወፍጮ ተንደቀደቀ። «አየህ ባሪያው..... መለኮት በእንደዚህ ዓይነት ትግሎች ውስጥ እጁን አያስገባም። በትግል ህግ መሠረት ያሸንፈ ይገባዋል። እናሸንፋለን-ይገባናል። መለኮት ፍትሐዊ ከሆነ በማንኛውም ትግል ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም። አንበሳ ጎሽ አደቅቆ ሲበላ መለኮት ጣልቃ አይገባም። ጅብም አህያን አራጉጦ አንጀቱን ሲመዘው መለኮት ጣልቃ አይገባም። የዓለም ዋነኛው ህግ በልቶ መበላት ነው። ያም ተባይ ያም ተባይ! መለኮት ለማን ሊያግዝ ይችላል? ሰውም እንስሳትን አርዶ ይበላል። እንዲያውስ ሐበሻ ጥሬ ስጋ እየዘለዘለ ሲበላ ዝም የሚል መለኮት ከሞርሞርዲኖ በተቀራኒ ይቆማል ብለህ ታስባለህ? እኔ ጥሬ ሥጋ አልበላም»

«ጠብሰው ይበሉ አይደል እንዴ ታዲያ!? ጠብሰውም በሉት ጥሬውን ያው ነው። ይልቅስ ትዝ አያስብሉኝ ጥብስ ሥጋ እየበላን ወይን የተጐነጨንበትን ወቅት። ያም ሆነ ይህ ገዳሙ በመለኮታዊ ጥበቃ ብቻ አይደለም የሚጠበቀው። የቀድሞ ወታደሮችና ጀነራሎች የነበሩ መነኮሳት መኖራቸውን ደርሼበታለሁ። ከዚህም ሌላ በዚህ ገዳም ውስጥ ብዙ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ፈላስፋዎች፣ኢንጂነሮችና ዶክተሮችም አሉ። እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ኢንጂነሮችና ዶክተሮች የላቁ ዶክተሮችና ኢንጂነሮች እዚህ ዳጋ ገዳም ውስጥ አሉ። እዚህ ምን እንደሚሠሩ አላውቅም። የዋዛ እንዳይመስሉዎት! እነዚህን ሰዎች መጋፈጥ የአድዋውን ድል መልሰው እንዲቀዳጁ እድል መስጠት ነው።»

ከት ብለው ሳቁ ሞርሞርዲኖ። «አድዋ?..... የአድዋ ድል? እኛ አፈገፈግን እንጂ አድዋ ላይ አልተሸነፍንም። ለአርባ አመታት በሠራነው ሥራ ተመልሰን መጥተን ድል አድርገናል። ኤርትራን የገነጠላችሁበት ምክንያት ምኒልክ ጦርነቱን ጨርሰው ጣሊያንን ከቀይ ባህር ስላላሻገሩት ነው? ምኒልክ ያልጨረሱት ጦርነት ካለ ይህ ከሳቸው የተሻለኩ ነኝ የሚለው ትውልድ ጦርነቱን መጨረስ አይገባውም ነበር? አቅም የለማ! ጣሊያን ኤርትራ ውስጥ ያቋቋመችው ፋብሪካዎችንና ካምፓኒዎችን የወረሱ ለቃቃሚዎች ባቋቋሟቸው ወንበዴዎች የተደረገው ግንጠላ አንዱ የኛ አሸናፊነት ማረጋገጫ ነው። አየህ ሐበሻን በሆዱ እንጂ በጦር በጎራዴ አታሸንፈውም። ከዚህ በላይ ሽንፈት አለ እንዴ? ተውማ ብዙ አታናግረኝ ....መቸም አፍንጫውን የተያዘ ለጊዜውም ቢሆን በአፉ መተንፈሱ አይቀርም። የኢትዮጵያ አፍንጫ ቀይ ባህር ነበር። አሁን እሱ አፍንጫዋ ተቆርጧል። ለዛም ነው አድዋ አድዋ እያላችሁ የምትነፋነፉት። አይገባህም እንጂ እያልኩህ ያለሁት ዓድዋ ላይ ድል አደረግን ማለት አትችሉም የተዋጋችሁለት መሬት አሁን የለምና። ዓድዋ አልከኝ..... አይ ባሪያው! ያም ሆነ ይህ የዓድዋ ድል አንተን አያካትትም። ሲሉ ሰምተሀል! አህያ! .....የእኔና ያንተ ራስ ምታትም ይህ አይደለም። የኤርትራና የኢትዮጵያ መሪዎች የሚቆምሩትን ቁማር እዛው ለእነሱ እንተወውና እኔና አንተ የራሳችንን ቁማር እንጫወት። አለም ቁማሩን የማያሸንፉትን አታስተናግድም። ለመሆኑ ገዳሙ ውስጥ መሣሪያ የታጠቁ አሉ?»

«...እ....እገምታለሁ» አለ ዲዎላ በተቆራረጠ ድምፅ።

«እገምታለሁ!?» በንዴት ጠፉ ሞርሞርዲኖ።

«እንዲያውም አረጋግጫለሁ።..... የማይሆን ነገር ነው ጌታ ሞርሞርዲኖ። አጉል ነው በረሃብ የምሰቃዬው። ከጉሮሮ የማይወርደውን ዳቤ የሚባል ቀፋፊ ምግብ መቋቋም አልቻልኩም። በዛ ላይ ሰገራው! ውይ..ውይ...ውይ! እዚህ ገዳም ውስጥ

ከመፀዳዳት መንታ መውለድ ይቀላል። መፀዳዳት አልቻልኩም። የፌስቱላ ሆስፒታል ውስጥ እንደሚያገኙኝ አይጠራጠሩ። በመከራ ኑሮ ነው ሥነላገል የሰነበትኩት። መንታ መውለድ ይቀላል። ጌታ ሞርሞርዲኖ እየሰሙኝ ነው? ድንጋይ እየበላሁ ነው ያለሁት ምግብ እንዳይመስልዎት። ምግብ አማረኝ። ውይ... ውይ ምግብ!.... ምግብ.....»

«ና!» አሉት ሞርሞርዲኖ በተሳላቂ ድምፅት። «ና! ዘለአለም የእኔን ፍርፋሪ ስትለቅም ትኖራለህ !ቀለማቸው ቀለምህ በመሆኑ መረጥኩህ እንጂ ስንት ጀግኖች እንዳሉኝ ታውቃለህ አንት ውሻ! ድሮስ ከባሪያ ምን ይጠበቃል? በዛ ላይ ከሐበሻ! ሐበሻ ምን አላማ አለው እንደውሻ ከመናከስ በቀር? እንደውሻ ይህችን አጥንት አገር ይዘው ከሚናከሱ ሐበሾች አንተስ በምን ትለያለህ? ውሻ አጥንቱን ሲነክበት ጥርሱን እንደሚያገጥ ሐበሾችም ይህችን የማትረባ ችጋራም አገር ይዘው ማቅራራት አመላቸው ነው። ታቅፈዋት ኖሩ እንደ አጥንት። ግን ጣሊያን በአምስት አመት ውስጥ ከሠራው በላይ ሶስት ሺህ ዘመን ተቀመጥንባት ለሚሏት ለዚህች አገር የሠሩላት የለም። ሆዳሞች ናቸው አቤህ... አንተም ሆዳም ነህ። እንደጀንያ ካልበላህ መቆም አትችልም። ሐበሻና ጀንያ ካልጠገበ አይቆምም። ሐበሻ ሀይወቱ ሆዱ ነው፤ ሞቱም በሆዱ ነው፤ መቃብሩም ሆዱ ነው። ና! የእኔን ፍርፋሪ ስትለቅም ኑር። አህያ!..... ሃ! ሃ! ሃ! ሃ!.....» ስልኩ ተቋረጠ። ስድቡ ሳያልቅ ባትሪው አልቆ።

፲፩

ካሊፎርኒያ፤ አሜሪካ
1997ዓ.ም

ዶ/ር አናንያ ዕርቃናቸውን ከሚውረገረጉት የሆቴሉ እንስት ዳንሰኞች የሚቅበጠበጥ ገላ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓይናቸውን ነቀሉ። ሲወስድሰት ያመሸው ጮርደን ከሴቶቹ አስማተኛ ገላ ጋር ተዳምሮ ፍትወቱን አንሮታል። ከጥጉ ተቀምጣ በሀሳብ የተዋጠችው ሲጳራን አይናቹን ቡዝዝ አርጐ ተመለከታት።

«ም...ን?» አለችው። ስትጐነጩው ያመሸችው አልኮል ፍንክች እንዳላደረጋት ተረዳ።

የሚንበቀበቀውን ሙዚቃ ተከትለው ከዳንሱ ወለል ላይ ተፋፍገው ከሚደነክሩት ዳንሰኞች መሃል የሲጳራን እጅ እየጎተተ ይዟት ገባ። አልተቃጠመችውም። አንዳንዴ ለቀቅ ታደርገዋለች።

ወደ ደረቱ ለማስጠጋትና ሙቀቷን ለመሞቅ የተፋፈገውና የተጨናነቀው የዳንስ ወለል ረድቶታል። ጡቶቿ ደረቱን ሲጐስሙት ልቡም እንደ ሙዚቃው መንደቅደቅ ጀመረ። ሙዚቃው ይንበቀበቃል። ምድረ ነጭና ጥቁር ውርጋጥ ተደባልቆ ይዘላል። በሠገነቱ ላይ ዕርቃናቸውን የሚተጣጠፉት ዳንሰኞች ቋሚ ብረቶችን በእግሮቻቸው ቆልፈው ይንሸራተቱባቸዋል። ህዝብ አዳም የቀረ አይመስልም።

አናንያ ትክክለኛ ቦታ መምረጡን ተገነዘበ።

ሲጳራን እንደ ሮማን ፍሬ ከተጠጋጋው ደናሽ መሀል ትኋት እየተሽለከለከ ተቀምጠውበት ወደነበረው ጠረጴዛ ተመለሰ። ከኪሱ ያወጣውን ከመጠጡ ቀለም ጋር የሚመሳሰል ባለ ቡኒ ቀላም ዱቄት ከሲጳራ ብርጭቆ ውስጥ ካለው ጮደል ያለ ወይን ውስጥ ሲቀላቅለው በቅፅበት ተቀየጠ። ከውብ ጭኖቿ መሃል የሚያድርበት ሴሊት መድረሱን አውቆ በኩራት ፈገግ አለ። ተመልሶ እጇን ይዟት ሲደንስ ቆይቶ መልሶ እዬጎተታት ወደ ጠረጴዛቸው ተመለሱ።

«ጠጪ እንጂ የኔ ቆንጆ» አላት የሱን ብርጭቆ እስከ አፍ ጢሙ በጮርደን እየሞላ። እሷ የመረጠችው የፈረንሳይ ወይን ቶሎ ሥራውን ስላልሠራ በሽቋል። ቢሆንም የጨመረው ዱቄት አዝለፍልፎ ክንዱ ላይ እንደሚጥላት እርግጠኛ ነው። ከዚያም ቀድሞ ወደ ያዘው ዘመናዊ አልጋ ይወስዳታል። ለአመታት ሲቋምጥለት የኖረውን ሴትነቷን ሊንፈላሰስበት ሊያደር በቁርጥ ወስኖአል።

«ወይን አልጠጣም በቃኝ» አለች ሲጳራ እጇን እንደተማረከ ወታደር ወደ ላይ አንስታ።

«ጠጪ እንጂ የኔ ቆንጆ....» አፉ እየተሳሰረ ነበር። ፊቱም ሪተቀቀለ ሳምባ መስሏል። «.. ....ባይሆን የጀመርሽውን ብርጭቆ ጨርሽው። ገዳችን እንዳይበላሽ። ነገ ሳይንቲስት ሻጊዝን አንቀን ወደ ቴልአቪቭ የምንወስድበት ቀን መሆኑን ረሳሽው የኔ ቆንጆ ገዳችን ይመር እንጂ። ችርስ በይኝ ይልቅ እንደ ገና» ብርጭቆውን አንስቶ ወደ ፊቷ አቀረበው።

ብርጭቆዋን አንስታ ከብርጭቆው ጋር አጋጭታለት ወደ ከንፈሯ በምትወስድበት ቅፅበት ጠረጴዛው ላይ ከነጠበች ርሚጥ ቡናማ ዱቄት ላይ አፈጠጠች።

«ሺት!ይህች አውሬ» አፍንጫው ላይ ላቡ ተንቆረዘዘ።

«ከዚህ መውጣት አለብን» አለች በፍጥነት እንደ ጥንቸል በርግጋ። «አደጋ ውስጥ ነን።»

«የምን አደጋ?»

«መጠጡ ተመርዟል።»

«ምን?»

«ይህን ሆቴል መልቀቅ አለብን አልኩህ በቃ።»

የመኪናዋን በር ከፍታ ገብታ በፍጥነት ሆቴሉን ስትለቅ አንዳች ነገር እያንዘፈዘፋት ነበር። አናንያ ከሁዋላ ወንበር ተቀምጧል።

ለጊዜው ከተከራየችበት አፓርታማ የመኪና ማቆሚያ መኪናዋን አቁማ ወደቤትዋ ይዛው ገባች። የንዬት ሲቃ እየተናነቃት ሽጉጧን ከሽንጧ መዠርጣ ከአናንያ አንገት ሥር ሽጉጠችው።

«አሁን ይህንን ሲባጉ አንገትህን በጥሼ ልጣለው?»

«ምን ነካሽ የኔ ቆንጆ....እ....» አለ ወደ ላይ እንዳንጋጠጠ እይናቹን ዘቅዝቆ።

«ያደረከውን ልትክድ ነው?»

«ምንድን ነው ያ...ያ..ያደረኩት? »

በብሽቀት ሳቅ ተንፈቀፈቀች። «ለምንድን ነው መጠጡን መመረዝ ያስፈለገህ?»

«አልመረዝኩትም ሲጳራ።»

«የምትበልጠኝ ይመስልሃል። ደደብ! ቢገባህ..... ደደብነትን ካለማወቅ የበለጠ ደደብነት የለም። ጭቃ ራስ! ሁሉንም ነገር ተከታትየዋለሁ። ልትክደኝ አትምክር። ተልከህ ምን እንደሆነ ብቻ ንገረኝ። ከጠላቴ ጋር ከዚህ በላይ መጓዝ አልፈልግም።»

«አልመረዝኩትም አልኩሽ። በእርግጥ.....» ቋጥኝ የሚያህል ራሱን በቀጭን አንገቱ ላይ ቀጫ አደረገው። «በ...በበ...በእርግጥ ዱቄቱን የጨመርኩት እኔ ነኝ። በማንም ተልኬ ሳይሆን እምቢታሽን

ለደቂቃዎች ለመስበር ነው። የላስኝ ፍቅርሽ ነው። በፍፁም አንችን ልጉዳሽ አልነበረም። ህይወትሽን የሚያቆም ነገርም አልነበረም። ትንሽ እንደ አንቅልፍ ሽልብ የሚያደርግ.....» ተልመጠመጠ።

መጠጡ አቅመ ቢስ እንዳደረገው ተገነዘበ። ቤቷ ውስጥ ከቋሚው ብረት ጋር በሰንሰለት ግጥም አድርጋ ስታሰረው አልተቃወማትም ነበር። ጥላው ወጣች። የመኪናዋ ሞተር ሲጮህ ተሰማው።

ከደቂቃዎች በኋላ ስትመለስ ብቻዋን አልነበረችም። አስከትላት ያመጣቻት ጭራቅ የምትመስል ነጭ ሴትዮ ወደታሰረበት ቋሚ ብረት ተጠጋች።

«እኔ ነው እንዴ ጅላጅሉ ሚስስ ሲጳራ?» ጥርሷ የሻንፖዬር ዓይነት መሆኑን ያየው ደረቅ ፈገግታ እስከ አይኑ ቀርባ ስታሳየው ነው። አልኮል ያጠነፈፈው ትንፋሽዋ ሲገርፈው ሆዱ ተገለባበጠ። «እኔም እንዳንተው የቀነዘረብኝ ጅላጅል ቢጤ ነኝ። አብረን ሌሊቱን እናቀነዝረዋለን።» ከቦርሳዋ መርፌ አውጥታ ሲሪንጁን የሞላውን ፈሳሽ በሙሉ ከደሙ ጋር ቀላቀለችው። ብዥ .....ብዥ....ብዥዥዥዥ.....ድንቅዝቅዝ.....ቅዝዝዝዝ...።....የታቹ ወደላይ ሲሆንበት ታየው። ቆይቶ ደግሞ የሚነዝር ስሜት አጥለቀለቀው። ወደብልቱ ሲንዶሎዶል.....። በዝብርቅርቅ ሰመመን ውስጥ ሆኖ ሲጳራን በአይኑ ተማፀናት። ሽጉጧን ይዛ ቆማለች።

«ወሲብ አይደል የፈለክው?» አለች ሲጳራ «እሱትልህ።»

«አም.... ብቃትክን ማዬት እፈልጋለሁ»አለች ጭራቅ የምትመስለዋ ሴትዮ ሱሪውንና ሙታንቲውን እኩል እያወለቀች።

«እንደዚህ!....አም።» ብልቱን እየሸቀሸቀች። «ትንሿ ብልትህ ወደ ዋሻዋ ተመልሳ እንዳትገባ ተዪ በላት።»

ሲጳራ ሁለት እጆቹ የታሰሩበትን ሰንሰለት ፈትታ አንድ እጁን ከቋሚው ብረት ጋር ጠርንፋ አሰረችና አንድ እጁን ነፃ አወጣችለት።

«አመሰግናለሁ ሚስስ ሲጳራ!» አለች ሴትዮዋ። «ለእሱ የማደርግለትን ለእኔም እንዲያደርግልኝ እፈልጋለሁ።»

«አም።» አለች ሴትዮዋ። «ሚጢጢየዋን ብልትህን በማቆም ስለተባበርከኝ አመሰግናለሁ። ካጠነከርካት ልትበቃኝ ትችላለች።»

አናንያ ሴትዮዋን ከኋላዋ ማጥቃት ጀመረ። በግዱ። ትለፈልፋለች። ድምጧ ያስጠላል። ሰቀጠጠው። ጨረሰ።

«ውይ!» አለች ሴትዮዋ። «ከምኔው? »

እንደገና ተጀመረ። መፈጠሩን እስኪጠላ። ሲጳራ ፊቷን አዙራ ቆማለች።

«ቅድም ቶሎ የጨረስክበትን ምክንያት ተረድቼልሃለው። አሁን ግን እኔ እስክጨርስ መቆየት አለብህ። አትጨማለቅ።»

«በቃኝ! የተረገምሽ!» አለ አናንያ በምሬት። «አልፈልግም!»

«እኔ እፈልጋለሁዋ!» አለች ሴትዮዋ በደረቁ አስጠሊታ ፈገግታዋ አግጥጣ። «ቡል ሺት!» እንግሊዝኛዋ የደቡብ አሜሪካውያን ቅላፄ ያለበትና ቀፋፊ ቃና ያለው ነው። «ኡኡ» ሲል ምንም አልቀረውም። እንደዚህ የተሰቃየበትን ቀን አያስታውስም። እንደገና መርፌውን አወጣች።.....ቆይታ ረጅም ምላሷን በከንፈሯዙሪያ እያሽከረከረች ቀረበችው። ጥርሷ መቶ ሰላሳ ሆነበት። ብዥዥዥታ። ብልቱን ቁልቁል ሲመለከተው ብዙ ሆኖ ታየው። አርባ.....ሃምሳ..... ከዛ ምን እንዳደረገ አያውቅም።

ጠዋት ዘግናኟ ሴትዮ ከወጣች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሲጻራ ሻንጣዋን ጠቅልላ ስትወጣ አናንያ ከቋሚው ብረት ጋር እንደ ታሰረ ከሰመመኑ ነቅቶ ነበር። ሲጻራን በበቀል ዓይን ተጉረጥርጦ ተመለከታት።

«ይህን ነበር አይደል የፈለከው?» አለችው ሲጻራ ሻንጣዋን እንደተሸከመች። «ከአሁን በኋላ ከኔ ጋር አብሮ የመስራት አጋጣሚ አይኖረንም። የሳይንቲስት ሻጊዝን ጉዳይ ለእኔ ተወው። በክንፋም አውሮኘላን ጭኜ ቴልአቪቭ ባላደርሰው ምን አለች በለኝ። አታውቀኝም ለካ።»

«አይደለም... ሲጻ....»

«ቻው!» ወጣች።

«ሲጻራ.... ሲጻራ.....ሲጻ....» የመኪናዋ ሞተር እስኪያንራራ ድረስ ስሟን እየጠራ ነበር። እንደታሰረ። ከእኩለ ቀን በኋላ በሁለት የእስራኤል ኮማንዶዎች ታጅቦ ወደ ቴሌአቪቭ በረረ። የሞሳድ የዲሲፕሊን ከሚቴ ሰብሳቢ ከሆኑት ወግ አጥባቂ አይሁዳዊ ጋር ሲነዛነዝ ከርሞ በከፍተኛ ማስጠንቀቂያ ታሰፈ። ዶ/ር አናንያ በሞሳድ ውስጥ ያለ እውቅ የቀዶ ህክምና ባለሙያ ባይሆን ኖሮ መሰናበቱ ባልቀረለትም ነበር።

ሲጻራ ያደረገችው በየደቂቃው ትዝ እያለው ሽንፈት አጥንቱን ዘልቆ ሰረሰረው። ረመረመው። ከዛ ጊዜ ጀምሮ በሲጻራ ላይ ጥርሱን ነከሰ። ደሙ በጥላቻ ሲለወስ ታወቀው።

ዶ/ር አናንያ ከሞሳድ ዋና መስሪያ ቤት በታች ባለው የምድር ውስጥ የህክምና ጣቢያ ስራውን ተመልሶ ሲጀምርም በጥላቻ ተሞልቶ ነበር። ሲጻራን የሚበቀልበትን ማንኛውንም ስልት መንደፍ ጀመረ። በቀል ውስጡን ሲያርመጠምጠውና አጥንቱን ሲግጠው ይሰማዋል።

፲፩

ጻጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣ ኢትዮጵያ

ራሳቸውን ያመነኮሱት አባ ዲዮላ በወጣትነት ዘመናቸው የሠሩት አንድ ስህተት በጻጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የሚኪትኑለትን ከባድ ምስጢር በቀላሉ እንዳያገኙ ሳንካ ሆኖባቸዋል። ስህተቱንም የፈፀሙት በአባታቸው በአለቃ አያሌው ወይም በአባ ዲዲሞስ ላይ ነበር።

የወጣትነት ዘመናቸው ውል ብሎ ሲታያቸው በአሁኑ አባ ዲዮላ ውስጥ የነበረው ወጣቱ ዲዮላ ተካሰተላቸው። ወጣቱ ዲዮላ ለምንም ነገር ደንታ የሌለው ነበር። የበለጠ ብልጥ ሆንኩ ሲል ራሱን የበለጠ ሞኝ ሆኖ ያገኘውም ነበር። ሰፍነግ ፈላሽ ነገሮችን መርጦ እንደሚመጥ ሁሉ ክፉ ነገሮችን መርጦ የሚመጥ አእምሮው ውስጡ በጥላቻና በበቀል እንዲሞላ አድርጉታል። ደስታ የሚሰጠው አንዳች ነገር የለም ነበር። ሁሉንም ያማርራል። ዲዮላን የማይከሰከሰው ነገር ምን ነበር? ምንም።

ምናልባት ከአባቱ ጋር አለማደጉ ለዚህ ጠባይ ሳይዳርገው አልቀረም ይባላል። አባቱ ከኢጣሊያና ከኢትዮጵያ ጦርነት በኋላ የት እንደደረሱ ለብዙ ጊዜ ሳይታወቅ ቆዩ። አልቃሻ እናቱም ሳያለቅሱ የዋሉበትና ያደሩበትን ጊዜ አያስታውስም። ቡቱለይ በቡቱለይ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት በየጦር ግንባሩና በየሰፈሩ የወዳደቁ የሰው ሥጋዎችንና እጅና እግሮቹን እየዘነጠሉ የሚያመጡ ውሾች ዘንጥለው የሚያመጡት እጅ የባለቤታቸው የአያሌው እጅ እየመሰላቸው እዬዬ ይሉ ነበር። ውሾችን አስጥለውም ክፋይ አካሉን ያዩና «ይሄማ የባለቤቱ እጅ አይደለም። የአያሌውን እጅ አውቀዋለሁ።» ጣቶቹንም አልረሳቸውም።» ብለው ሲያነፈርቁ ዲዮላ አንዳችም ዘለላ ዕንባ ጠብ አይለውም ነበር። ዝም። ዲዮላ በባህር ዳር ከተማ ዳርቻ ባለች ቆሻሻ ሰፈር ውስጥ ሲያድግ... ከሰፈሩ ልጆች ጋር ሲጣላ «የጋለሞታ ልጅ» የሚለውን ስድብ ሳይቀምስ ውሎ አያውቅም ነበር።

በአንድ ወቅት አባ ፊንሐስ የሚባሉ ሽማግሌ አንጥረኛ በዛች ቆሻሻ ሰፈር ውስጥ ታዩ። ከነዲዮላ ቤት ጥግ ባለ የቱንጣለስ ግቢ ውስጥ የሚኖሩትን ጣሊያናውያን ለምን እንደሚደበቁ ግን አይገባውም ነበር። ጣሊያናውያኑ ከኢትዮ-ጣሊያን የአምስት አመታት ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀሩ ቤተሰቦች ነበሩ።

አንጥረኛው አባ ፊንሐስ በተለይ ቡስኪ የተባለውን የጣሊያናውያኑን ቤተሰብ አለቃ ሲያዩ ይፈረጥጡ ነበር። አንዳንዴም ቡስኪ በአካባቢው ሲያልፍ ዘለው ከነዲምላ ቤት ይገባሉ። አንጥረኛው ፊንሐስ ከዲምላ እናት ጋርም ሲጨቃጨቁ ይሰማ ነበር።

«ባልሽ ግማደ መስቀሉን ይዞ የት እንደተሰወረ ካልነገርሽኝ በዚህ ጉጠት ነው አይንሽን የምመነግለው» ሲሉ ይሰማል።

«አላውቅም። በየቀኑ ሳለቅስ የምኖረው እኔስ ስላጣሁት አይደልም?» ይላሉ እናቱ።

«አውቀሽ ነው አንች ከሐዲ እንደባልሽ እየካድሽኝ ነው።» አጥረኛው ያንባርቃሉ።

እንዲህ ሲነዛነዙ ከኖሩ በኋላ አንድ ቀን ሴሊት ዲምላ እና እናቱ ወደ ተቀመጡባት ደሳሳ ጉጆ ዘው ብለው ገቡ።

«ባልሽ ያለበትን ትነግሪኛለሽ አትነግሪኝም?»

«ስንቱ አላውቅም ልበልም። አላውቅም!»

ቤቱን ዘግተው ዙሪያውን በእሳት እያያዙት። መስኮት አልባው ደሳሳ ጉጆ ዥው ብሎ በፍጥነት ነዶ ዲምላ ሰውነቱ ተጠባብሶ ሲወጣ እናቱ እዛው ነደው ቀሩ። ከአልጋው ጋር እንዳሰሯቸው ያወቀው በኋላ ነበር። ደማቸው ሲንጨቀጨቅ ሥጋቸው ሲንፈቀፈቅ አጥንታቸው እሳቱ ውስጥ ሲከሰከስ ቆሞ ከማየት ውጭ ሊፈይድ የቻለው ነገር አልነበረም ነበር ህፃኑ ዲምላ። ለመጀመሪያ ጊዜ ዕንባ ጠብ ያለው ያኔ ነበር። ቆሻሻዋ ሰፈር በመንፈቀ ሌሊት በእናቱ የሥጋ ሽታ ስትታጠን የወጡት መንደርተኞች የደረሱት ሁሉም ነገር ሲጠናቀቅ ነበር።

የእናቱ ኡኡታና ዋይታ በህፃኑ ዲምላ አእምሮ ውስጥ ታትሞ ቀረ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሰው የተባለን ሁሉ ጠላ። የእኔ የሚለው አንዳች ነገር የሌለው ዲምላ ከእናቱ ሞት ዐኋላ በዛ ቆሻሻ ባጥለቀለቀው ሰፈር ሲንከራተት ኖረ። ከባህር ዳር ከተማ ተጭነው መጥተው ከሚጣሉ ቆሻሻዎች ውስጥ በቆሻሻ ተጨማልቆ በቆሻሻ የተጨማለቁ የዳቦ ቁራሾችን ከውሾች ጋር ተሻምቷል።

አንድ ቀን ከተቃጠለው የእናቱ ቤት አቅራቢያ ካሉት ጣሊያውያን ቤተሰቦች ግቢ ውስጥ ዘው ብሎ ገባ። ለጣልያናውያኑ እየተሳሳከ ኑሮውን መግፋት ሲጀምር ቢያንስ ቢያንስ ከጣሊያውያኑ ውሾች በጥቂት ያነሰ ኑሮ መኖር ቻለ።

የጣሊያናዊው ቡስኪ ቤተሰብ ባልታወቀ ምክንያት ለሁለት ተከፍሎ ከፊሉ ወደ ከፋ ሲዔድ እሱም አብሮ ተጓዘ። በቦንጋ ከተማ ውስጥ ከሰፈረው የጣሊያን ቤተሰብ ጋር ተቆራኝቶ ከመኖር ውጭ ሌላ አማራጭ አልታየውም ነበር። በቦንጋ ከተማ የሰፈረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ውስጥ ዋነኛ ሰው የነበረው ጉልማሳው ሞርሞርዲኖ ቡስኪ ነበር። ሞርሞርዲኖ ቡስኪም ከውሻው ቀጥሎ

ይንከባከበው የነበረው ሰው ቢኖር ዲምላ አያሌውን ነበር። ዲምላ ከሞርሞርዲኖ ጋር ኮክቡ ከገጠመለት ጊዜ ጀምሮ የተሻለ ህይወት መምራት ቻለ። ሞርሞርዲኖን ላቡ ጠብ እስቲል ቢያገለግልም የተበዘበዘ መስሎ አይሰማውም ነበር።

በዚህ መሀል አባቱ አለቃ አያሌው ቦንጋ ደረሱ። ከየት እንደመጡ ማንም አላወቀም። ዲምላን «አባትህ ነኝ» ሲሉት አንዳች የጥላቻ ስሜት እንደምች ሽው አለው። የጋለሞታ ልጅ ሲባል የኖረው ትዝ አለው። በእሳት እንደቋንጣ የተጠበሱ እናቱ ታወሱት። የመንፈቀ ሌሊቱ የእሳት ነበልባል።

«የት ነበርክ?» አለ ዲምላ ተጉረጥርጦ። «ከደካማዋ እናቴ ጋር በችግር ስንጠበስ የት ነበርክ? በለቅሶና በዋይታ ኑሮአችን በዕንባችን ስናጥብ የት ነበርክ? እናቴ በቁም ስትለበለብ የት ነበርክ? እኔ ቁራሽ ዳቦ ከቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ስጉረጉር የት ነበርክ?»

«አየውልህ ልጄ እኔ.....» የአለቃ አያሌው አይኖች በዕንባ እየወረዙ።

አላስጨረሳቸውም። «አትንገረኝ! ምንም አይነት ይቅርታ ልቤ ላይ አይወድቅም ወደ መጣህበት ተመለስ። ያንን የሰቆቃ ጊዜ በየቀኑ እንድታስታውሰኝ አልፈቅድልህም።»

«ልጄ» አሉ አለቃ አያሌው። «ይቅርታ ልብ ላይ እንጂ መሬት ላይ አይወድቅም። በእርግጥ የመጣሁት ይቅርታን ልለምንህ አይደለም። የእኔ ውጣ ውረድ ስለማይገባህ ያንተን የሰቆቃ ጊዜ ሽረህ ይቅርታ እንደማታደርግልኝ አውቃለሁ። ሁሉንም የደረሰባችሁን ነገር ሰምቻለሁ። አሁን የመጣሁት ግን ልክስህ ነው። ልብ ካለህ ትጠቀምበታለህ።»

«ምንድን ነው እሱ?»

«አሁን አልነግርህም። ጥቂት ጊዜ ያስፈልገናል። ረጅም ነው ታሪኩ። እዚሁ እሰነብታለሁ።»

«አልፈልግም። ረጅም ነገር ያስጠላኛል። ከነገርከኝ ባጭሩ ነግረኸኝ ወደ መጣህበት ተመለስ።»

«አንዲህ ባጭሩ የሚነገር ነገር አይደለም ልጄ ጊዜ ያስፈልገዋል።»

አለቃ አያሌው በዛው በቦንጋ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቢቆዩም የዲምላን ትኩረት ሊያገኙ አልቻሉም። አያዳምጣቸውም፣ገና ሊያነጋግሩት ወዳሰቡት ሲዔዱ ይሸሻቸዋል፣ይደበቃቸዋል።

ከዲምላ ይልቅ ወደ ጣሊያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ መምጣት የሚያዘውትረው ወጣቱ ሻጊዝ እጅጉ ይቀርባቸው ነበር። ብዙም ነገር ይነግሩታል። የሻጊዝን አስተዋይነትና ብሩህ አእምሮ የተገነዘቡት አለቃ አያሌው ሰልጫቸው ሊያስተላልፉት የነበረውን ምስጢር ለሻጊዝ ሊያቀብሉት ወሰኑ። ምስጢሩን ከመዘርገፋቸው በፊት ግን

የምስጢሩን ቁልፍ ከጀርባው በንቅሳት አስቀመጡለት። ሙሉ በሙሉ እንዳልተረዳቸው ግን እርግጠኛ ነበሩ። አንድ ቀን ግን እንደሚደርስበት አልተጠራጠሩም።

አለቃ አያሌው ዲዎላን ቀስ በቀስ እየቀረቡ አንዳንድ ታሪኮችን ይነግሩታል። እሱ ግን አይገባውም። በአብዛኛው የሚነግሩት ስለ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ነበር። ባያዳምጣቸውም ዝም ብለው ይተርኩለታል።

«የኢትዮጵያ መሪዎች ከጥንት ጀምሮ ለሥልጣናቸው ሰፍሳፋዎች ናቸው» ይሉታል።

«እና እኔ ምን አገባኝ? ይንሰፍሰፉዋ! ድሮ ለሥልጣን ካልተንሰፈሰፉ ለምን ሊንሰፈሰፉ ነው?» ይበሳጫል ዲዎላ። አለቃ አያሌው እንደሁ አንዴ መተረክ ከጀመሩ ማቆሚያ የላቸውም።

«እናም አየውልህ ልጄ.....ለሥልጣናቸው ቀናኢ በመሆናቸውም ለሥልጣናቸው ህልውና ሲሉ የማያደርጉት ነገር የለም ነበር። በዓለም ላይ ታላላቅ በሆኑ አስማተኞችና ጥበበኞች ራሳቸውን ከግድያ ለመከላከል የሚያሰሩት ብዙ ድግምት ነበር። ለምሳሌ ስለ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ልንገርህ።»

«አትንገረኝ!»ይላል ዲዎላ። «ደክሞኛል። ስልችት ብለኸኛል።»

አለቃ አያሌው ግን ይቀጥላሉ። አባ ዲዲሞስ ትረካቸውን አያቆሙም።

«ንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኢትዮጵያን ለሰላሳ አራት በላይ አመታት ገዝቷል። መንበረ መንግሥቱም በሸዋ ነበር። በአክሱም ያሉ ጠላቶቹ ስለበዙ የደብረ ብርሃንን ከተማ ቆረቆረና በዚያ አንድ ትልቅ ቤተ መንግሥት አሠራ።»

«ኧረ በፈጠረህ አታድርቀኝ? ምንም የሚያገባኝ ነገር የለም ስለሱ!»

«አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በእርግጥ ጥበበኛ ሰው ነበር። ደራሲም ነበር። ብዙ መጻህፍትን ደርሷል። መጽሀፈ ብርሃንና መጽሀፈ ንግሥ የሚባሉ መጻህፍቱ የሚጠቀሱ ናቸው። በዘመኑ የነበሩትን ደራስያን በመደገፍ ስለመጻሕፍት ምርመራ ያለውን ዝንባሌና ችሎታ አሳይቷል።»

«ቅድም ስለ አስማት አሁን ስለድርሰት። ተው ተው ግን አታድርቀኝ? በምን ቀን መጣህብኝ ልበል!»

«አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለምን ከሕዝብ እይታ መደበቅ እንደሚያዘወትር ታውቃለህ?»

«ባላውቅ ይሻላል። ማወቅም አልፈልግም።»

«ከቤተ መንግሥቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድም ሆነ ሲመለስ ማንም ሰው አያየውም ነበር። ከቤተ መንግስቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወስደው መንገድ ግራናቀኙ በረዥም ግንብ የተከለለ

ስለነበር። "ጠላቶቼ ሥራይ ያደርጉብኛል" በማለት ከምሽት እስከ ንጋት ካህናት ቤተ መንግስቱን እየዞሩ እየፀለዩ እንዲያድሩ ያደርግ ነበር። ካህናቱም ቤተ መንግሥቱን እየዞሩ ጠበል እየረጩ፣ ክህደተ ሳይጣንና መዝሙረ ዳዊት እየደገሙ ያድሩ ነበር። ቦኋላ ላይ ግን ወጣ ወጣ ማለት ጀምሮ ነበር። ለምን ይመስልሃል?»

«ለምንም አይመስለኝም። ባትነግረኝ እመርጣለሁ።»

«አንድ ትልቅ ጥበብ አሰራ!... ማንኛውም የጦር መሣሪያ የዘርዓ ያዕቆብን ገላ መውጋት እንዳይችል የሚያደርግ ጥበብ በታላላቅ የአለማችን ጥበበኞች አሠራ።» ዲዎላ ጀሮውን አቆመ አዚህ ላይ።

«አርዌ በድላይ የተባለ የአዳል ባላባት ማመፁንና ግብር መክፈሉን ከዚህም በላይ ለጦርነት መሰናዳቱን ሰምቶ ሲዘምት የተከተሉት ጥቂት ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ከአረዌ በድላይ ሰፊር ትይዩ ከሆነ ቦታ ላይ ደርሶ የጠላትን ሀራዊት ብዛት አይቶ አልደነገጠም። ካስከተላቸው ጥቂት ወታደሮች መሀል ገሚሶቹ ነጋሪት እንዲጎስሙ ከፊሎቹ ጥሩንባ እንዲነፉ ሌሎች ደግሞ እንዲፎክሩና እንዲያቅራሩ ስለአደረገ ጦርነቱን ከመጀመሩ በፊት አሸነፈ። ጠላቶቹን አስበረገገ። ጦርነቱ የተጠናቀቀው ራሱ ዘርዓ ያዕቆብ አርዌ በድላይን እንገቱን ቀልቶ ከገደለው ቦኋላ ነበር። ዘርዓ ያዕቆብ ይህን ያህል ድፍረት ያገኘበት ምስጢር ቅድም በነገርኩህ ነገር ነው። ባሰራው ረቂቅ ጥበብ ምክንያት ማንኛውም የጦር መሣሪያ እንደማይመታው እርግጠኛ ነበር።..... አሁን የዘርዓ ያዕቆብ አዕም የተቀመጠው በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ነው።»

«ይህን ልትነግረኝ ነው ስንት ወንዝ ተሻግረህ የመጣኸው? ይህ ነው የምትነገረኝ ምስጢር?» ዲዎላ እርር ትክን አለ።

«ይህን ብቻ አይደለም። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የተቀመጠው የንጉስ ዘርዓ ያዕቆብ ዓዕም ሙሉ አይደለም። ከአፅመ መካከል ጥቂት አጥንቶች ተሰብረው ተወስደዋል፤ በውድ ዋጋም ተቸብችበዋል። ምክንያቱም የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አዕም የጦር መሣሪያ አያስመታም ተብሎ ስለሚታመን ነው። ከንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አዕም ትንሽየ ቅንጣቢ በአንገቱ አሥሮ የነበረው በላይ ዘለቀ ወራሪውን የጣሊያን ጦር በኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ቆሞ ሲዋጋ አንድም ጥይት ሊገድለው አልቻለም። እመነኝ። እኔ ለጥቂት ቀናት ከበላይ ዘለቀ ጉን ተሰልፌ ጣሊያንን ስዋጋ ይህን አይቻለሁ። በላይ ዘለቀ የንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን አዕም ሸራፊ በአንገቱ አሥሮ ነበር። ያለምንም ምሽግ ያለምንም ተገን ተራራ ላይ ቆሞ ዘመናዊ መሣሪያ እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የጣሊያንን ጦር መድረሻ ያሳጣበት ምክንያት ይህ ነው። በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘውን

የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብን አጥም ሄደህ ማየት ትችላለህ። አጥሙ ጎደሉ ነው። ቁጠርና ውሽታም በለኝ።»

«ባክህ! በላይ ዘለቀ ሲፈጠርም ጀግና ሆኖ ስለተፈጠረ ነው።»

«ጀግና አይደለም አላልኩህም እኮ። ጀግናማ ጀግኗ ነው። ይህን ማድረጉ እኮ ጀግነኑን የሚያጉላ እንጂ የሚያደበዝዝ አይደለም። ጥበበኛ መሆን በራሱ ጀግንነት ነው። ይህንን ጥበብ ለግል ጥቅሙና ለዝርፊያ አለመጠቀሙ ነው የበለጠ ጀግና የሚያደርገው። ጀግና ነው። አፅሙን ለምን እንዳሰረው ጠንቅቄ አውቃለሁ። የቅርብ ጓደኛውም ነበርኩ። እሱ ጫካ ውስጥ ጣሊያንን ሲዋጋ እኔ የጣሊያንን የጦርና የዕቃ መርከቦች በጣና ሐይቅ ላይ እነዳ ነበር። የጣሊያን መርከብ ካፒቴን ሆኜ የጣሊያንን ውስጠ ምስጢር ለአርበኞች የማቀብል የውስጥ አርበኛ ነበርኩ። ከበላይ ዘለቀ ጋርም የተገናኘነው በዚህ ወቅት ነበር። እንዲያውም የዘርዓ ያዕቆብን አፅም የሚያገኝበትን መንገድ ያመቻቸሁለት እኔ ነበርኩ።»

«እስቲ እንግዲያ ለእኔም ስጠኝና ያንን ፊንሐስ የሚባል አንጥረኛ እናቴን እንዳነደዳት ከአለበት ፈልጌ ላንድደው?» ዲምላ ድንገት ደሙ ሲፈላ ታወቀው።

«አስጨርሰኝ ይልቅ እሱን ለእኔ ተወው። እንዳልኩህ በላይ ዘለቀ ያንን ጥበብ ስለተጠቀመ ንጉሡ ከስደት ተመልሰው አለመግባባት ሲፈጠርም በንጉሡ ጦር በተከፈተበት ተኩስ አልወደቀም። ታስሮ የአስር ቤቱን ባለጠመንጃ ዘቦች ባዶ እጁን ገድሎ ሲወጣ ማንም በጥይት ሊያስቆመው አልቻለም። በመጨረሻ በስቅላት አንገቱ በገመድ ታንቆ ባደባባይ የተገደለበት ምስጢርም በጥይት መሞት ስለማይችል ነው።»

«ለእኔም ስጠኝ አልኩህ! አለበለዚያ አትዘብዝብኝ!»

«ላንተማ ልብ የለህም እንጂ ልብ ካለህ የምሰጥህ ከዚህ የበለጠውን ምስጢር ነበር። ግን ልብ የለህም። ልበ ቢስ!»

በሌላ ቀን አለቃ አያሌው ለዘመናት ደብቀውት የኖሩትን ምስጢር ሚፍሜሩን ነገሩት። ከ1933 ዓ.ም ጀምሮ ሲሰደዱለት የኖሩትን ምስጢር! በተለይ በ1961ዓ.ም ማንም እንዳያገኘው አደርገው የቆለፉትን ምስጢር ቁጢት ሲያስይዙት ዘሉ ተጠመጠመባቸው። «አባቴ የሆንከው ገና አሁን ነው። እስከ አሁን እጠላህ ነበር አሁን ግን! ...ግን ለማንም ከእኔ በቀር እንደማትናገር ቃል ግባልኝ!» ሲል ዲምላ ጮቤ ረገጠ።

ዲምላ አባቱ አለቃ አያሌው ወደ ጣልያኖች የኤሌክትሪክ ሱቅ መምጣት ከሚያዘወትረው ሻጊዝ እጅጉ ጋር አፍ ለአፍ ገጥመው የሚያወሩት ነገር አላስደሰተውም። እንዲያውም ምስጢሩን ለሻጊዝ ይነግሩብኛል ብሎ ከተጠራጠረ ሰንብቷል። አለቃ አያሌውና

ሻጊዝ እጅጉ አብረው በተቀመጡ ቁጥር መብገን ጀመረ። የውስጡ ቃጠሎ እየነደደ መጣ። ሻጊዝን አንቆ ለመጣል ተመኘ። ግን ሻጊዝን አንቆ ቢጥል አባቱ ለሌላ ሰው ምስጢሩን ላለማሳለፋቸው ዋስትና የለውም። ስለዚህ ዋናው አማራጭ የምስጢሩን ባለቤት ማጥፋት ሆኖ አገኘው። አባቱን ማስወገድ! .....ወሰነ። ይህ ታላቅ ምስጢር የግሉ ሆኖ የሚቀረው አባቱን ሲያስወግድ ብቻ እንደሆነ አመነ። አለበለዚያ ከአባቱ ጋር ቁጭ ብሎ ያወራውን ሁሉ ዕድሜ ልኩን ሲገድል መኖር አለበት። ስንቱን ገድሎ ይጨርሳል? አለቃ አያሌውን ለመግደል ሲወስን ያለማቅማማት ነበር።

በአንድ ምሽት አለቃ አያሌው ወደተኙበት ደሳሳ ጉጆ ሲገባ የሞርሞርዲኖን ሽጉጥ አቀባብሎ ነበር። በደሳሳዋ ጉጆ ውስጥ በኩራዝ መብራት የሚያነቡትን መፅሐፍ ሳያጥፉ ከጉጆዋ ወደ ገባው ልጃቸው ዞር አሉ አለቃ አያሌው። ፈገግ አሉ ።

«ልጄ መጣህልኝ!?» ልቡ ወደ አሳቸው እንደተመለሰ ተስፋ አድርገው። «ልጄ ያላንተ እኮ ማንም የለኝ! እስቲ ተቀመጥና አጫውተኝ እኔም የማጫውትህ ጉዳይ አለኝ።»

«ምን ታጫውተኛለህ ....ለእኔ የምታጫውተኝን ለሌላም ሄደህ ቱሽ ትላለህ።....አንተ ሆድ ውስጥ ምን ምስጢር ይቀመጥና!» ሽጉጡን መዥርጦ በግንባራቸው ላይ አነጣጠረባቸው። ዲምላ።

«ምነው ልጄ? ኧረ በስመአብ በል! ም....ምም.....ምን ነካህ ልጄ .... ም.....ም»

«በስማም? .....ሃ!ሃ!ሃ! ዳቦ ነህ አንተ በስማም ብዙ የምቆርስህ? ወይስ የፋሲካ በግ? ሰው በስማም ተብሎ አይታረድም የፋሲካ በግ እንጂ! ይህ ለፍላፊ ልሳንህ ካልተዘጋ ገና ብዙ ትሰፈልፋለህ።»

«ተው እንጂ ልጄ.....ተ....ተ.ተ.ተ.....ተተተ.....»

«ለኔ ያወረስከኝ አንዳች ነገር የለህም! ከዚህች ከነገርከኝ ነገር በቀር። እስኪ ምን ወረስኩ ከአንተ አባትነት? እ? ወይኔ ከርታታው ዲምላ! ከዚህች ከነገርከኝ ምስጢር በቀር ምን አወረስከኝ? እሷን ባይሆን የእኔ ማድረግ ያለብኝ አይመስልህም? እሷን ባይሆን....እሷን!..... ግን አፍህ ወንፊት ነው። አፍህ እንደወንፊት አይቋጥርም። እንደ ወንፊት የሚያፈስ አፍ ካለህ የተናገርከው ምስጢር መልሶ ያጠፋሃል። ሃ! ሃ! ሃ! ይቅርታህን አለምንም። ከአንተ የምፈልገውን አግኝቻለሁ። እንድትረግመኝም እንድትመርቀኝም አልፈልግም።» በሽጉጡ ውስጥ ተቀባብለው የነበሩትን ጥይቶች በሙሉ ጭንቅላታቸው ላይ አርከፈከፈባቸው። የሆነ ነገር ሊናገሩ አፋቸውን እንደከፈቱ ገልጠው ከሚያነቡት መጽሐፍ ገፅ መሀል በደም ተጨማልቀው ክንብል አሉ።

ዲዎላ ምስጢሩን ለሌላ እንዳይነግሩብኝ ብሎ አባቱን በገደለ ማግስት ተፀፀተ። መጠየቅ የሚገባውን ጥያቄ ጨርሶ ሳይጠይቃቸው ቸኩሎ ነበር እንደ ገደላቸው የገባው በኋላ ነው። የምስጢሩን ጫፍ ነገሩት እንጂ ሙሉ በሙሉ እንዳልነገሩት ቆይቶ የገባው። በንዴት ተቃጠለ።በይደር ሊነግሩት ያስቀመጡት ነገር ነበር። የተከፈተው መንገድ መልሶ ተዘጋበት። አባቱን በመግደል ወንጀል ተከሶም ወህኒ ተወረወረ።

በሞርሞርዲኖ ቡስኪ እገዛ ከአሰቃቂው እስር ቤት አምልጦ ከሞርሞርዲኖ ቡስኪ ቤተሰብ ጋር ወደ ጣሊያን ኮበለለ።ሲሲሊ እስከ ጥልፍልፏ ተቀበለችው። እስከ አሁን የኖረውም የሞርሞርዲኖን ትክሻ ሲጠብቅ ነው። ዕድሜ ልኩን።

ከዘመናት በኋላ አባቱ ሊነግሩት ጫፍ ያስያዙት ምስጢር ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኢትዮጵያ የቀረው የቡስኪ ቤተሰብ እርስ በእርሱ ሲገዳደል የኖረበት ምክንያት መሆኑ ገባው። ሞርሞርዲኖን ያህል የሲሲሊ ጌታ ለተራ ነገር ብለው ወደዚህች የዓለም ጭራ ወደሆነች ደሀ ሀገር እንደማይመጡም እርግጠኛ ነው።

በመሆኑም የዚህን ምስጢር ክር እንደገና ለመጨበጥ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የቀበሮ ባህታዊ ሆኖ ጓዳ ጉድጓዳውን እያነፈነፈ ይገኛል። ቀለሙ እንጂ ችሎታው እንዳላስመረጠውም ያውቃል። ዶን ሞርሞርዲኖ ከስንት ነፍሰ በላ ማፍያዎቻቸው መሀል የመረጡት የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ ለማረስ ነው። ባለ ጥቁር ቆዳው ዲዎላ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ ከኢትዮጵያውያን መነኮሳት ጋር በቀላሉ ተደባልቆ የሚፈልገውን ቋጠሮ ለመመንተፍ አማራጭ የሌለው ሰው ነው። አሁን ተልዕኮውን ለመፈፀም ራሱን አመንኩሶ በዳጋ ገዳም ውስጥ የበቃ መነኩሴ መስሏል። ነፍሰ በላው መነኩሴ አባ ዲዎላ በቢጫው የምንኩስና ልብስ ተከፍሰዋል።

አባ ዲዎላ አባታቸውን በማጥፋታቸው ሳይሆን አባታቸውን ሳያናዝዙና የምስጢሩን ቁልፍ በእጃቸው ሳያስገቡ በመግደላቸው ፀፀት እንደ ፍላፃ ልባቸው ላይ ተተክሎ አልነቀል ብሏቸዋል። በሌላ በኩል ምስጢሩን ቢያገኙት እንኳ ለዶን ሞርሞርዲኖ አሳልፈው ከመስጠት ባለፈ የእርሳቸው እንደማያደርጉት ተሰማቸው። ዓይን የማያዙሩት የሞርሞርዲኖ ጋርዶች ምስጢሩ እንደ ተገኘ እንደ ጉንዳን እንደ ሚወሯቸው ጥርጥር የላቸውም። ደሞም አንድ ነገር ተገለጠላቸው። አባታቸው የነገሯቸውን ያስታወሱት የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም አቃ ቤቱ ውስጥ በመስታዎት ሳጥን በክብር ተቀምጦ ያዩት ዕለት ነው። አባታቸው እንዳሉትም ከአፅሞቹ መሀል የተወሰነ ነገር እንደጐደለ በጣም ወደ መስታውቱ ሳጥን ተጠግተው አረጋግጠዋል። በመሆኑም ከዚህ አፅም ትንሽ ሰባሪ ለማግኘት ዕቅድ አወጡ። ግን እንዴት አድርገው? በገዳሙ ውስጥ ያሉትን የዋህ

መስለው ጠቢብ የሆኑ መነኮሳትን እንዴት መጋፈጥ ይችላሉ? እንደ ዓይን ብሌን ወደሚጠበቀው ዕቃ ቤትስ ማን ያስደርሳቸዋል? ከንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ትንሽ ስባሪ ቢያገኙማ የእሳቸው ህልም ብዙ ነበር።

ይህንን አፅም በአንገታቸው ካሰሩ የፈለገ ዓይነት ጥይት ቢተኮስባቸው ገላቸው ላይ እንደውሃ እየፈለሰ ሲወርድ በሀሳባቸው ታያቸው። የጥይት እርሳሶችን እንደዝንብ እንኳ ሳይቆጥሩአቸው ዝም ብለው ሥራቸውን ሲሰሩ።ወላ መትረዬስ ወላ ክላሽንኮቭ ወላ ዲሞትፊር ወላ ዲሽቃ ሚሳዬልም ቢሆን ቢተኮስባቸው ዝንባቸውን እንኳ ማስነሳት እንደማይችል እርግጠኛ ሆኑ። በጉልበታቸው ደግሞ ይተማመኑበታል። እንኳን መነኩሴ መልአክ አድቅቆ የሚጥል ክንድ ባለቤት መሆናቸውን መጐናፀፊያቸውን ሰብስበው ጡንቻውን ቁጥር አድርገው አዩት። የተከመረ ጡንቻቸውን ሳሙት። ይህ ከሆነ ለዘመናት የተቀበረውን ምስጢር ፈልፍሎ ለማግኘት ማንም እንደማያስቆማቸው አሰቡ።ይህንን ምስጢር እንዳገኙም ሞርሞርዲኖ ቡስኪን አፍንጫህን ላስ ይሉታል። ምክንያቱም የሞርሞርዲኖን ጋርዶች በሲሲሊ ተራራዎች ላይ ቆመው ዓይቀጡ ቅጣት እንደሚሰጧቸው በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም እርግጠኛ ናቸው። ከዛም በአልም ዙሪያ ያሉት የሞርሞርዲኖ ካምፓኒዎች ባለቤት ለመሆን ማንም ምንም አያግዳቸውም። በዚህ ገዳም ውስጥ የሚፈልጉት ምስጢር ብቸኛ ባለቤትም ይሆናሉ። ይህ ካልሆነ የሞርሞርዲኖ ዘላለማዊ ባሪያ ከመሆንና ከመበዝበዝ የሚታደጋቸው መኮማመኛ የላቸውም። በዛ ላይ ጉልበታቸው ከደከመ ተመልሶ ድህነት ሽምጥ እንደማይጋልባቸው በምን እርግጠኛ ይሆናሉ? አፅሙን የሚያገኙበትና ምስጢሩንም የሚፈልጉበትን መንገድ እያሰላሰሉ ወደ ዕቃቤቱ ተነስተው ገሰገሱ።

፲፮

የፀደዩ አበባዎች በኢትዮጵያ ተራራዎች ላይ ከስመዋል። የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት ዛፎች ግን በልምላሜ እንዳሸበረቁ ናቸው። 1997 ዓ.ም። እንደ ገና የክረምቱ ወራት መጣ። ሰኔም ብቶ ነበር። ወቅቱም በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፀሎት በዝቶበት ነበር። በሀገሪቷ ውስጥ የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ በተቀሰቀሰው ግርግር ሀገሪቷ ወደመጠፋፋት እንዳታመራ መነኮሳቱ ተንበርክከው እያለቀሱ ነበር።

በዚህ ገዳም ውስጥ ሬዲዮ ማዳመጥ ክልክል ቢሆንም አንድ መነኩሴ ግን አሻፈረኝ ብለው ባህር ዳር ከተማ በመሄድ ሪዲዮ ገዝተው መጡ። ትንሿን ሪድዮ ከበው የሚያመሹ መነኮሣትም ተበራክተው ነበር። በየቀኑ ጥሩ ዜና አይሰሙም ። መነኮሳቱ ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ መሆናቸው ከመቼውም ጊዜ በላይ የተሳበቀባቸውም በዚህ ጊዜ ነበር። የውጭ ሀገር ሬድዮዎች የሚያስተላልፉትን ዘገባ በእንግሊዝኛ እና በሌሎች ቋንቋዎች ያደምጡ ነበር። የጀርመን ድምፅ እና የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ዜናዎች የማይታለፉ ነበሩ። «ከ1997ቱ የኢትዮጵያ ምርጫ በኋላ በተፈጠረው አለመግባባት ይህን ያህል ሰዎች ሞቱ። ይህን ያህል ቆሰሉ።»

«አልቅሱ መነኮሳት... ወጣት አለቀ!» ይላል አንዱ።

«ወጣት እንደ አይጥ ኮርኒስ ውስጥ እያደረ ነው ፀልዩ!» ይላል ሌላኛው።

«አባ ይህ ነገር ተገቢ አይደለም። ዝም ይበሉ። ወይ ለምን ሄደው ምርጫ አልተወዳደሩም? ልጠድቅ መጥቼ ኩነኔ ሊያሰገቡኝ ነው እርስዎ ሰውዬ! ይተውኝ ሁለተኛ ፖለቲካ ሊያወሩኝ እንዳይመጡ። እሱን ራዲዎን ይዘውብኝ አይምጡ ብያለሁ እርስዎ ሰውየ....»

«መነኮሳት ለምን ድምጣቸውን እንዲሰጡ አልተደረገም?»

«መነኩሴ ምን ድምጥ አለው! ከውዳሴ ማርያም በቀር።»

«ድምጥዎትን ለማን ሰጡ አባ?»

«ለእግዜር» .....ሳቅ።

«እሪ መነኮሳት ተዉ ይህ ነገር ገደል እንዳይከታችሁ? ይህ ሬዲዮ በምን ቀን መጣ? ማነው ያመጣው ግን? ይዞልን ይሂድ ይህን ሬዲዮ! አለበለዚያ ወደ ጣና ሐይቅ ነው የምወረውረው!» አንድ

የተበሳጨ መነኩሴ። «ቦለቲከኛ መሆን የፈለገ መነኩሴ ሂዶ ምርጫ መወዳደር ይችላል። እዚህ የመጣነው ልንጠድቅ ነው። ወቼ ጉድ!...ወይ አመብርሃን! መነኩሴው ሁሉ ቦለቲከኛ ሆነልሽኩ።»

«ዛሬ ጠዋት ፀሎት ለላደረስኩም ማለት ይቀላል። የምርጫው ነገር መጥቶ ይሰነቀርብኛል። እባካችሁ ይህ ሬዲዮ ይሰበር.....» በሬዲዮው ላይ ግን ማንም ለመስበር የጨከነበት አልነበረም።

«አባ ገብረ እግዚዕ.... ያኔ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ቦንብ ጣይ አውሮፕላኖች ጣና ሐይቅን በክንፋቸው እዩሰነጠቁ ወደ ሰሜን ሲወነጨፉ ከዳጋ አናት ላይ ካለው ዋርካ ወጥተው "ገደሏቸው! ፈጇቸው!" ሲሉ የነበር... ኤርትራዊነታቸው አለቀቃቸውም እንዴ? ምነው እንግዲያ አሁን ዝም አሉ.... የኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባቸውም?»

«እሪ ዝም በል! እርሳቸው በኤርትራዊነት አያምኑም። የእርስ በእርሱ ጦርነት አሳስቧቸው ይሆናል እንጂ። ይኸው ኢትዮጵያን ሙጥኝ ብለው.. ኢትዮጵያ ናት ሀገሬ እያሉ አይደል እንዴ እዚህ የቀሩት!? እነ ዘርዓይ ደረስ የሞቱላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት ኤርትራ አይደለችም! እነ ራስ አሉላ ...አሉላ አባነጋ የምፅዋው የእሳት በር ....የኢትዮጵያው አጥር.... ሊጠብቃት የኖረችው ሀገር ኢትዮጵያ አይደለችም ወይ? ደቡብም ተወለድ ሰሜን ምስራቅም ተወለድ ምዕራብ ግድ የለኝም። ዘርህን እዚህ ገዳም ውስጥ የጠየቀህ ካለ ንገረኝ። ማንም ዘርህን አልጠየቀህም። ኤርትራ ውስጥ ብትወለድና እትብትህ እዛ ቢቀበር እትብትህን የበላው ምስጥ ግን ደቡብ ኢትዮጵያ ላለመገኘቱ እርግጠኛ አትሁን። ጋምቤላ ተወለድ። እትብትህን ጋምቤላ ውስጥ የበላው ምስጥ ግን አፋር ላለመድረሱ እርግጠኛ አትሁን። ለምን ከምስጡ ለመሸል አትሻም? ለምን ትጠባለህ?.....ሰፊ አገር እያለህ ለምን ጠባብ ክልል አገርህ እንዲሆን ትመኛለህ?...አህያ እንኳ ጋጣው ሲጠበው ይራገጣል። አትጥበብ። የማያላፋርህ ነገር ቢኖር በኢትዮጵያዊነትህ ማመንህ ብቻ ነው። በቃ።»

«ዘርንና ጐሣን ተመርኩዘው የሚመሠረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መምታት ነው... በቃ። የእገሌ ዘር ፓርቲ የዕገሌ ዘር ፓርቲ እያሉ ህዝቡን የከፋፈሉት እነሱ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ስድስት ሰዎች ብቻ ያሉት ብሔረሰብ አለ። እስኪ ይታዩዎት አባ? ከእነዚህ ስድስት ሰዎች ብቻ ካሉት ብሔረሰብ መሀል ኢትዮጵያን ለመምራት የሚችል አእምሮ ያለው ሰው ቢነሣና ቢመራት ምንድነው ችግሩ? ምንም። እኔ እቀበለዋለሁ። ኢትዮጵያን ለመምራት ዘር ሳይሆን ጭንቅላት መመረጥ አለበት! ....ጥሩ መሪ ሁልጊዜም ጥሩ ተከታይ አለው።»

«ልክ ብለዋል አባ!» አሉ አንዱ መነኩሴ ተቀብለው። «አዎ። ኢትዮጵያን ለመምራት ዘር ሳይሆን ሞኃንቅላት መመረጥ አለበት!። ኢትዮጵያ ቅን ህሊና ያለው መሪ ያስፈልጋታል። ምክንያቱም .....ህሊና ትንሹ እግዚአብሔር ነው።ቅን መሪ መንገዱ ሁሉ ይቃናለታል። ኢትዮጵያ እንደገና እንደ ቴዎድሮስ ያለ መሪ ያስፈልጋታል። ዳሩ...ኢትዮጵያ መሪዋን አታውቅም! ቴዎድሮስን መቅደላ ላይ ጥለውት የሸሹትንና እንግሊዝን እስተመቅደላ አፋፍ መርተው ያስመቱትን ይቅር ይበላቸው» ብዙ ብዙ ተባለ ከየመነኩሴው አፍ። አንድ ወግ አጥባቂ መነኩሴ መጤዋን መናኝ ሬዲዮ ተናደው ወደጣና ሲወረውሯት ያመጣት መነኩሴ እስተቆቡ ወደ ሐይቁ ተወርውሮ ገብቶ በዋና ሲፈልግ ውሎ አግቶ። ዳሩ የተነከሰ ባትሪ ድንጋይዋም በማለቁ ድብደባ በዝቶባት ነበር። ድምጠ ነፍናፋዋ ሬድዮ ሰጥማ ባትቀር ናሮ በቀጣዩ የምርጫ ዘመቻ አሸንፈው እንደ አጤ ቴዎድሮስ ከገዳም ወጥተው የኢትዮጵያን ህዝብ በቅንነት ለመምራት ያቆበቆቡ ብዙ መነኮሳት ነበሩ። በሰባዔም ተፈልጋ ያልተገኘችው ሬድዮ ብዙ መነኮሳትን አስከረፈች። የመነኮሳቱ ወሬም ወደ አባ ሚራኾር ዞረ።

«አባ ሚራኾር ግን ለምንድነው ሁልጊዜ በብራና ላይ የተፃፈ ግጥም ሲያነቡ የማያቸው?»

«ግጥም ስለሚወዱ ይሆናላ።»

«አይደለም። አይደለም። አንድ ግጥም ብቻ ዘወትር እንደውዳሴ ማርያም መደገም ግጥም መውደዳቸውን አያረጋግጥም።».....

አባ ሚራኾር የመንፈቀ ሌሊቱ ደወል ተደውሎም ከበአታቸው አልወጡም። ይህን ሌሊት በሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም ውስጥ ያለው ምስጢር ካልተገለፀላቸው እንዳይነጋ ያወዝቱት ይመስል ግጥሙ ላይ እንዳፈጠጡ እኩለ ሌሊት ሆነ። እስከ ዛሬ ድረስ በጊታሩ ውስጥ የተላከላቸውን በብራና ላይ የተፃፈውን ግጥም ብዙ ጊዜ ደግመው ደጋግመው እንበበውታል። ቃል በቃል ብለውት ብለውት አልፈለጥ ሲላቸው ፊደል በፊደል ማንበብ ጀምረዋል። ፊደሎቹ የደበቁትን ምስጢር ይናገሩ ይመስል በጎይናቸው ይማጠኗቸዋል። ዳጋ ገዳም ውስጥ ከደረሱ ጊዜ ጀምሮ ይህን የብራና ላይ ግጥም ሳያፈጠጡበት ውለው አያውቁም። አባ ሚራኾር የስነ ዕሑፍ ተመራማሪ በሆንኩ ኖሮ ሲሉም ተፀዕተው ነበር። ምስጢሩ ግን በሥነ ዕሑፍ ተመራማሪነት ብቻ የሚገኝ እንዳልሆነ ሳይገነዘቡት አልቀሩም። ሆኖም ከዚህ ግጥም ፊደሎች ጋር ጦርነት ገጥመዋል። ከብራናው ጀርባ ላይ ያገኙት ፍንጭ በመንፈቀ ሌሊት አስፈነጠዛቸው። «15₄» ይላል ፍንጩ። ቢቀይ ብዕር ደግሞ «ከ15ኛው ስንኝ አራተኛው ቃል ውስጥ» ተብሎ በቀጭኑ ተፅፏል።

ከሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም 15ኛውን ስንኝ ደግመው ደጋግመው አነበቡት። እንዲያውም ከአሥራ አራተኛው ስንኝ ጀምረው።

«....አንቺ ካጠገቤ አትራቂ፣ በርታ በይኝ እመብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን።»

የሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም 15ኛው ስንኝ በእርግጥም

«ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን»

የሚለው ስንኝ መሆኑን ከላይ ጀምረው ቆጥረው ደረሱበት። እዚህ ስንኝ ውስጥ ደግሞ አራተኛውን ቃል አፈጠጡበት። «እንዳልዘነጋት» ይላል ..... የአሥራ አምስተኛው ስንኝ አራተኛው ቃል። «እንዳልዘነጋት-----እንዳልዘነጋት----------እንዳልዘነጋት---------» አባ ሚራኾር ቃሉን ደጋገሙት።

ብራናው ላይ ከተፃፈው ሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም ዕሀፊት ውስጥ ለየት ባለ መልክ «እንዳልዘነጋት» ከሚለው ቃል ውስጥ የተፃፉት ፊደሎች "ዳ" እና "ጋ" ፊደሎች መሆናቸውን ደረሱበት ተንጋደውና ጐላ ብለው ነው የተፃፉት። ፊደሎቹን ገጣጠሙአቸው። "ዳጋ" የሚል ቃል ፈጠሩላቸው። «ሁሁ!» አሉ በደስታ ዘለው አባ ሚራኾር። «አገኘሁት! ፍንጩን አገኘሁት!!..... *ዳጋ*.....»

«ከዛ.....ከዛ.....እሺ.....*ዳጋ*.....ከዚያስ?» አባ ሚራኾር እየፈነጠዙ ጊታሩንና ሌሎች ዕቃዎቻቸውን ያስቀመጡበትን ረዥሙን ሻንጣቸውን ጐትተው ከውስጡ የጀርባቸውን ንቅሳት የሚያዩበትን መስታወት አወጡና ልብሳቸውን አውልቀው በቀንዲሉ መብራት የጀርባቸውን ንቅሳት ተመለከቱት። ብራናው ላይ በ"ቶ" ፊደል ቅርፅ ከተሳለው ባለጥ መስቀል ጋር ተመሣሣይ የሆነውንና ዴርቶጋዳ በሚለው ቃል መካከለኛው ቦታ ላይ የተቀመጠው ፊደል ወስጥ በረቂቅ የተፃፉትን ቁጥሮች አንድ በአንድ እየተመለከቱ ወረቀት ላይ አሰፈሯቸው።

«54_4 95 10_6 29_{23} 77_5 30_{456} 52_7 33_2 $\underline{000}$ 97_5.....» አባ ሚራኾር ባገኙት ፍንጭ መሠረት ጐላ ብለው የተፃፉት ቁጥሮች ስንኞችን አነስ ብለው ከሥራቸው የተፃፉት ቁጥሮች ደግሞ ቃላቶቹን እንደሚጠቁመ ደረሱበት። በቁጥር የተገለፀውን እያንዳንዱን ስንኝ በሌላ ወረቀት ገለበጡት።

«54_4.....54ኛው ስንኝ 4ኛው ቃል.....ምን ይላል? » ከሰቆቃወ ጴጥሮስ ግጥም ላይ ስንኝ ለቀማ ገበ። 54ኛው ስንኝ **«ከቀፈፋ ደጀ ሰላም፣ ከቤተልሔም ቅዳሴ፣»** ይላል። ከዚህ ስንኝ ውስጥ «*ከቤተልሔም*» የሚለውን ቃል ወስደው ለብቻው ዓፋት። ቅድም ካገኙት ቃል ጎን። «*ዳጋ ከቤተልሔም*.....» አነበቡት ከገጣጠሙት በኋላ። ሌሎችን ስንኞችም መልቀም ጀመሩ። «9_5.....9ኛው ስንኝ "ሂትለራዊ አባጭ ጫንቃዋን እንደ ኮረብታ ተጭኗት»....."*ኮረብታ*" የሚለውን ቃል ወሰዱትና ከሚደረድሩት

ቃል ጮን ዓፉት። «ዳጋ ከቤተ ልሔም ኮረብታ.....» ፈገግ አሉ። «እህ?» ሌላ ስንኝ ነቀሱ። 10ኛውን።

10_{6}.....10ኛው ስንኝ 6ኛው ቃል።

«ቀና ብላ እውነት እንዳታይ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት» ስድስተኛውን ቃል ወሰዱት።

"ቁልቁል" የሚለውን። ***«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል.....»*** ስደራው ቀጠለ። ካርታው ነፍስ እየዘራበት መጣ። ቀጠሉ። የነብሩን ጅራት ይዘው እንዴት ሊለቁ ይችላሉ?

29_{23}.....29ነኛው ስንኝ 2ኛውና 3ኛው ቃል። ***«በጋው የእረኛ አደባባይ፣ ከረምት እንደወንዙ ፍሳሽ»*** ሁለተኛውና ሶስተኛው ቃል«የእረኛ አደባባይ» ባንድ ላይ ነው። ከሚደረድሩት ቃላዊ ካርታ ጮን ዓፉት። ***«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ.....»*** ካርታው እየረዘመ መጣ።

77_{5}.....77ኛው ስንኝ 5ኛው ቃል። ***«ችጋር ከጮደዋ ገፍቶ አባፏ ግርጌ ሊጥላት»*** ከሚለው ስንኝ ውስጥ ***«ግርጌ»*** የሚለው 5ኛ ቃል ካርታው ጋር ሲፃፍ ***«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ.....»*** ይሆናል።

38_{456}....30ኛው ስንኝ 4ኛው፣5ኛውና 6ኛው ቃል። 38ኛውን ስንኝ አነበቡት። ***«በገጠር የደመና ዳስ፣ በገደል ሸለቆ አዳራሽ»*** ይላል። ከዚህ ስንኝ ውስጥ 4ኛው 5ኛውና 6ኛው ቃላት «በገደል፣ ሸለቆ፣ አዳራሽ» የሚሉት ናቸው። በዚህ መሰረት ካርታው «ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ.....»ሆኖ ተለጠጠ።

52_{7}...52ኛው ስንኝ 7ኛው ቃል። ***«ከዚማ ቤት እቅኔ ቤት ከድን ቤት እመግሕፍት»*** 7ኛው ቃል እዚህ ስንኝ ውስጥ «እመግሕፍት» የሚለው ነው። አባ ሚራኾ ተፍነከነኩ።

«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመግሕፍት.....» ካርታቸውን ሰድረው ወደሚቀጥለው ቁጥር ተመለከቱ።

33_{2}.....33ኛው ስንኝ። ***«ከፍልፈል ጋር ሩሜ ሰገጥም ከቀበሮ ድብብቆሽ»*** ይላል። ከዚህ ስንኝ ውስጥ 2ኛው ቃል «ጋር» የሚለው ነው። ካርታው ጋር አዋቀሩት።

«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመግሕፍት ጋር.....» እዚህ ላይ ግር አላቸው። 000 የሚሉት ቁጥሮች ትርጉም ምንድን ነው። ለጥቂት ደቂቃዎች እነዚህ ቁጥሮች ላይ አትኩረው ሲመለከቱ ቆይተው ምንም ፍንጭ ስላላገኙ ቁጥሮችን ወስደው ከካርታው ጮን ዓፏቸው።

«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመግሕፍት ጋር 000.....» ወደ ሚቀጥለው ቁጥር ተሻገሩ።

975..... 97ኛው ስንኝ ምን ይላል?.....***«ኩርትም ብዩ እችልበት፣ እሸሸግበት አይጠፋም።»*** እዚህ ስንኝ ውስጥ 5ኛው ቃል «አይጠፋም» የሚለውን ወስደው ከካርታው ጋር ደረደሩት።

«ዳጋ ከቤተልሔም ኮረብታ ቁልቁል የእረኛ አደባባይ ግርጌ በገደል ሸለቆ አዳራሽ እመግሕፍት ጋር 000 አይጠፋም።» ካርታው ክርችም ብሎ ሞላ። ...አባ ሚራኾ እመር ብለው ተነስተው ዘለሉ። እነዚህ የተጠቀሱት ቃላት ሁሉ የተቀመጡበትን የዳጋ አስጢፋኖስን ደሴት የሚገልፁ ቃላት ናቸው።.....እኒህ ሁሉ ቃላት «ሰቆቃወ ጴጥሮስ» ከሚለው የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ግጥም ውስጥ ተፈልቅቀው የወጡ ናቸው። ‹አስገራሚ ምስጢር፡ አስገራሚ ቅኔ፡ ዘይገርም ካርታ....› አባ ሚራኾ ተደነቁ። ‹ይህን ምስጢር ነበር ለካ ከጀርባየ ተሸክሜው የኖርኩት! ይህን ምስጢር ነበር ለካ ይህን ቅኔ ነበር ለካ ሳልፈታው የኖርኩት! አሁንም ግን ቅኔውን ሙሉ በሙሉ አልፈታሁትም። ጂራቱን ነው ገና የያዝኩት› ዳጋ የተቀመጡበት ደሴት ነው። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ ኮረብታው ላይ የተሸራውን ቤተልሔም ያውቁታል። ቁልቁሉቱም ሲመላለሱበት የከረሙበት ቁልቁለት ነው። የእረኛ አደባባይ እየተባለ በድሮ ጊዜ የሚጠራው ደግሞ የዕቃ ቤቱ ጠባቂ የሚቀመጡበት የመጠበቂያ ቤት እየተባለ የሚጠራው ነው። ‹በካርታው መሰረት እንግዲህ ከዚህ የመጠበቂያ ቤት ወይም በድሮ ጊዜ የእረኛ አደባባይ ተብሎ ከሚጠራው ቤት በታች የገደል ሸለቆ አለ ማለት ነው። በሸለቆው ውስጥም አዳራሽ። በዚህ አዳራሽ ውስጥ ከሚገኙ መሳህፍት ጋር 0000 አይጠፋም ማለት ነው› ሲሉ አሰቡ። 0000 ምን እንደሆነ ባያውቁትም ።

በደረቀው ሌሊት ከበአታቸው ወጥተው ሽቅብ ወደኮረብታው እየተጣደፉ ወጡ። ከዕቃ ቤቱ የግንብ አጥር በር አጠገብ ቆመው በበሩ ማጮለቂያ ወደ ውስጥ ተመለከቱ። የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ከእረኛ አደባባዩ ቤት ውስጥ አይታዩም።

ከኋላቸው የሰው እጅ ትከሻቸውን ሲነካቸው ተርበተበቱ ዞር አሉ። የዕቃ ቤቱ ጠባቂው ናቸው። እዬተከታተሉአቸው ነበር። የዕቃቤቱን ግቢ በር ከፍተው ወደ ውስጥ ይዘዋቸው ገቡ። «እንኳን ደስ አለህ ዶ/ር ሚራኾ» አሉ የዕቃ ቤት ጠባቂው ወደ መጠበቂያ ቤቱ ይዘዋቸው እየገቡ። «ፈተናውን በብቃት አልፈሀል» ሚራኾ ደነቀው። የዕቃ ቤቱ መጠበቂያ ቤት ውስጥ የሚንቦገቦጉት የመቅረዙ መብራቶች የወለሉን ቀይ ምንጣፍ አመድ አልባ ፍም አስመስለውታል።

የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ቀያዮቹን የወለል ምንጣፎች ገልጠው ወደ ግድግዳው ሊጠቀልሉአቸው አቧራ ከወረሰው ወለል ላይ የተዘጋ የብረት መዝጊያ ብቅ አለ። አቧራውን ጠረግ ጠረግ አድርገው ከትንሽ የብረት ሳጥን ውስጥ ባወጡት ማጭድ የሚመስል ቁልፍ ሊከፍቱት የብረቱ መዝጊያ ተንሸራቶ ወደ ውስጥ ገባ። ከወለሉ ሥር ያለው ዋሻ ጥቅጥቅ ባለ ጥልማሞት ጨለማ ተሞልታል። ከብረት ሳጥኑ ውስጥ ያወጧቸውን አምስት አልቢን ማጭድ የሚመስሉ ቁልፎች ለሚራዥ ከሰጡት በኋላ «ፈተናውን በማለፍህ እንኳን ደስ አለህ»አሉ የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ፈገግ ብለው።

«ዶክተር ሚራዥ» አሉ ዕቃቤት ጠባቂው መነኩሴ ቀይ ቱታ አንጠልጥለው። «እስከ አሁን ቢጫውን የምንኩስና ልብስ ለምን እንዳለበስንህ ሳይገባህ አልቀረም። የልብሱን ክብር ዝቅ ለማድረግ ወይም በአስኬማው ላይ ለመዘባበት አይደለም። አሁን ግን ይህንን ቀይ ቱታ መልበስ ይጠበቅብሃል። በእነዚህ ቁልፎች የሚያጋጥሙህን በሮች እየከፈትክ ቁልቁል ወደ ዋሻው ውረድ» ወፍራም ጣፍ ከመቅረዙ ነበልባል አቀጣጥለው ሰጡት።

ዶ/ር ሚራዥ ያለግብሩ ለብሶ «አባ» ሊባልበት የከረመውን የምንኩስና ልብስ ሊያወልቅ አንዳች ሽክም ከላዩ ላይ ሲወርድ ታወቀው። የደፋውን ቆብ አውልቆ ለመነኩሴው ሲሰጣቸው የነፃነት እስትንፋስ እየተነፈሰ ነበር።

በጣፋ የብርሃን ውጋጋን እየተመራ ጨለማ ወደነገሰበት ጥልቅ ዋሻ በሚያብረቀርቁት የብረት መረማመጃዎች ላይ በቀስታ እየተረማመደ ቁልቁል ወረደ። የዋሻው ውስጣዊ መግቢያ ቱቦ በሚያብረቀርቅ አልሙኒየም መሰል ንጣፍ ታቹም ላዩም የተሰበጠ ነው። በረጅሙ አብረቅራቂ ቱቦ መሰል ዋሻ ውስጥ ጥቂት እንደተጉዋዘ በጥቁር ግዙፍ የብረት በር ቱቦው ተዘጋበት። በሩ ላይም ዲርቶጋዳ የሚል ጽሁፍ በወርቃማና ጥንታዊነትን በተላበሰ ቀለም ተቀርፆበታል።

ወደመጣበት ዞሮ ሊያይ የመጠበቂያው ቤት በር ወደ ላይ ተምዘግዝጎ ሊዘጋ ተመለከተው። ከመጠበቂያው ቤት ሆኖ ይሰማው የነበረው የቤተ ክርስቲያኑ ሰዓታትና የመነኮሳቱ ዜማ በቅጽበት አልም ሲል የዋሻውን ውስጣዊ ክፍል የለበጠው አብረቅራቂ አልሙንየም መሰል ንጣፍ ድምጽ ከውጭ ወደ ውስጥ እንደማያስተላልፍ ተረዳ። ከራሱ እስትንፋስና ፈጣን የልብ ምት በቀር የሚሰማው አንዳች ድምጽ የለም።

በበሩ ሽንቁር ውስጥ ማጭድ የመሰሉትን አራት ቁልፎች እየከተተ ሞክሮ አምስተኛውን ቁልፍ ሽንቁር ውስጥ ሲጠመዝዝ የብረቱ መዝጊያ ከሁለት ተገምሶ ወደ ውስጥ ገባ። በሩን እንዳለፈ መልሶ ራሱ ተከረቸመ።

ወደ ውስጥ እንደገባ ሰፊ በቀያይ ምንጣፎች ያሸበረቀ ሳሎን አገኘ። «የፈጣሪ ያለህ...» አለ በሹክሹክታ። ላዩ በደንና በቁጥቋጦ ውድማ የመሰለ ደሴት ውስጡ ዘመናዊ እጆች ያረፉበት ከተማ ሆኖ ሲያገኘው እጅግ ተደመመ።

ሳሎኑ ውስጥ ቆሞ ሲያማትር መሃል ላይ የቆመ ረጅም መቅረዝ ተመለከተ። የመቅረዙን ሻማዎች ሊለኩሳቸው ሲራመድ ሰፊው ዘመናዊ ሳሎን በብርሃን ተሞላ። ቀና ሲል ትላልቅ አምፑሎችን ተመለከተ። የኤሌክትሪክ መብራታቸው ቡግግ ሲል የዋሻው ውስጥ የጨለማ ግዛት ከመ ቅፅበት በነነ።

«ሰው አለ? .....» ሲል ጮሆ ዋሻውን ጠየቀ። ምላሽ አላገኘም። ሳሎኑ ውስጥ ከታች እስከ ላይ የተደረደሩ ግዙፍ ግዙፍ ጥንታዊ መፃህፍት ተደርድረዋል። «.....በገደል ሽለቆ አዳራሽ እመፃህፍት ጋር ፀፀፀ አያጠፋም።..... » የሚለው ትዝ አለው ። ግን ፀፀፀ ምንድን ነው? ዘመናዊውን ሳሎን በትንግርት መቃኘት ጀመረ።

ቀያዮቹ ሶፋዎች በክቡ ጠረጴዛ ዙሪያ ይታያሉ። ከእሳት መሞቂያው ምድጃ በላይ.....«ማሔር ሻላል ሐሽ ባዝ» የሚለው ቃል በቀይ ነበልባላማ ቀለም ግድግዳው ላይ ተዕፏል። ከሳሎኑ ቀጥሎ ወዳለው በር ሄዶ ማጭድ የሚመስለውን ቁልፍ በሽንቁሩ ውስጥ ከቶ ሲያሽከረክረው ተበረገደ። ሌላ ጨለማ። ጭልጭል የሚለውን የጣፋን መብራት አስቀድሞ ወደ ውስጥ ገባ። ከየት እንደመጣ የማይታወቅ የኤሌክትሪክ ብርሃን ቦግ ሲል ለመቁጠር በሚያታክቱ ዘመናዊ ወንበሮች የተሞላ ሰፊ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ራሱን ቆሞ አገኘው። ወደ አዳራሹ ወንበሮች መሀል ገባ። በአዳራሹ ግድግዳ ዙሪያ የድምፅ ማጉያዎች ተተክለዋል። የአጤ ቴዎድሮስና የአጤ ምኒልክ ትላልቅ ስዕሎች ግድግዳው ላይ ተሰቅለዋል።
ከድምጽ መጉያዎች ውስጥ «ዶ/ር ሚራዥ ወደ ዲርቶጋዳ እንኳን በደህና መጣህ!» የሚል ነጋሪነዳማ ድምፅ ሰማ። ከፍ ብሎ ወደ ተሠራው መድረክ ሲያይ በመድረኩ ላይና በመነጋገሪያው አትሮንስ ጥግ የቆመ ማንም የለም። ወደ መድረኩ ወጥቶ ጥቂቁር መጋረጃዎቹን ሲገልጥ ማንንም ሊያገኝ አልቻለም።

ከመድረኩ ጀርባ ወዳየው በር ሄዶ ሲከፍት ቁልቁል የሚያወርድ አብረቅራቂ መረማመጃ ተመለከተ። የመጀመሪያውን መቃን ሲረግጥ ወደታች እንደአሳንሰር ቁልቁል ይዞት አልም አለ። ጨለማ ወደ ዋጠው ሌላ ክፍል አስገብቶት ሲቆም የጣፋ መብራት ጠፍቶ ነበር። በጨለማ ተውጦ የነበረው ክፍል በብርሃን ሲሞላ ከዘመናዊው የምድር ውስጥ ከተማ ጋር ተፋጠጠ። በህልሙ የሚያየው እንጂ በዛ ድምፅ በማይሰማበት ደሴት ምድር ውስጥ ይህን የመሰለ ዘመናዊ ከተማ በእውኑ የሚያይ አልመሰለውም።

በእውኑ እንዲሆን በልቡ ፀለየ። በእንቅልፍ ልቡ ከሆነም ከእንቅልፉ እንዳይነቃ ፈጣሪውን ተማጠነ።

ተዘጋግተው የነበሩት ሁሉም በሮች ተከፍተው ከየክፍሉ በወጡት ብዙ ሰዎች በመሀል የሚያልፈው ሰፊ የአስፋልት መንገድ ተጥለቀለቀ። ሁሉም በጭብጨባ ዋሻውን አደመቁት። ሁሉም ሰዎች አንድ ዓይነት ቀይ ቀሚስ ለብሰዋል። ሁሉም በአንድ ድምፅ «ዶርቶጋዳ!» አሉ። «ዶ/ር ሚራዥ እንኳን ደህና መጣህ» ድምጻቸው በዋሻው ውስጥ የገደል ማሚቶ ደጋግሞ አስተጋባ። «ዶርቶጋዳ...ዶርቶጋዳ....ዶርቶጋዳ....ዶርቶጋዳ....»

ጭብጨባው ጋብ ሲል አንድ በር ተከፍቶ ረጅም ጢም ያላቸው ሽማግሌ ወጥተው ወደ አደባባዩ አመሩ። «ወንድማችን ዶ/ር ሚራዥን በደስታ ስለተቀበላችሁት እናመሰግናለን.....» ድምፃቸው ይንቀጠቀጣል። ከደስታቸው ብዛት እንደ ህፃን እየተፍለቀለቁ ነበር። ሽማግሌው መነኩሴ አባ ዣንበሩ መሆናቸውን ለመለየት አፍታ አልፈጀበትም። አባ ዣንበሩ ከአደባባዩ ወርደው በቀዩ ቀሚስ ውስጥ ቦርሰስ ቦርሰስ እያሉ ወደ እሱ ሲመጡ ከየክፍሉ ወጥተው የነበሩት ሰዎች ተመልሰው ገቡ። አንድ ሰው ግን ከመግባቱ በፊት እጅን አውለበለበለትና ወደእሱ መጥቶ አቀፈው። ዶ/ር ዣንጊዳ ነበር። ተጠመጠመበት። «ሚራዥ እንደገና በመገናኘታችን ደስ ብሎኛል።» አባ ዣንበሩም አቅፈው ከሳሙት በኋላ ዶ/ር ዣንጊዳ የምድር ውስጡን ምስጢራዊ ከተማ እንዲያስጎበኘው ነግረውት ወደ ቢሮአቸው ገቡ።

ሚራዥ በዣንጊዳ ገለባ እየተመራ የዋሻውን የምድር ውስጥ ከተማ መጎብኘት ጀመረ። «ዶርቶጋዳ የትምህርትና ስልጠና ክፍል» የሚል ጽሑፍ ወደ ተሰቀለበት በር ሲደርሱ በሩን ዶ/ር ዣንጊዳ የከድ ቀጥሮቹን ነካክቶ ከፈተው።

«ይህ ክፍል.....» አለ ዶ/ር ዣንጊዳ ማብራሪያውን ሲጀምር። «ዶርቶጋዳ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥበት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ በምህንድስና በህክምና እና በሌሎች የትምህርት ዘርፎች ስልጠና የሚሰጥበት ነው። በውስጡ ባሉት ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች የሚሰለጥኑ ብዙ አባላት አሉ» እየተዟዟሩ ሲያስጎበኘው ቆይቶ ሰፊውን ክፍል ለቀው ሲወጡ በሩ ተመልሶ በራሱ ተዘጋ።

«ዶርቶጋዳ የጥናትና ምርምር ክፍል» የሚል ጽሑፍ ወደ ተሰቀለበት ክፍል ገብተው ዘመናዊ ኮምፒውተሮችና ረቂቅ የምርምር መሣሪያዎች የታጨቁበትን ማዕከል አስጐበኘው። በልዩ ልዩ ምርምር ላይ የተጠመዱትን ተመራማሪዎችም በየክፍሉ እየወሰደ አስተዋወቀው።

ከዚህ ክፍል ወጥተው የህክምና ማዕከሉን ሲያስጐበኘው ደግሞ የበለጠ ተደመመ። ዓይታቸው በማያውቅ የህክምና መሣሪያዎች የተጨናነቀውን ሆስፒታል ሲመለከት እጅግ ተገረመ። ውስጡ በነጭ ቀለም የተቀባው የህክምና ማዕከል ሁሉም ነገር የተሟላለት ነው። ከቀላል እስከ ከባድ ቀዶ ጥገና የሚሰጥበትን የቀዶ ጥገና ክፍል እየተዘዋወረ ጎብኝቶ የሚቀጥለውን በጉጉት ለማየት ወጣ።

የመረጃና ደህንነት ክፍል መምሪያ ውስጥ ሲገቡ «ኮሎኔል ፍስሐ የዶርቶጋዳ የመረጃና ደህንነት ክፍል መምሪያ ሀላፊ» በማለት ሽበት ጣልጣል ያደረገባቸው ቆፍጣና ሰውዬ እጁን ጠበቅ አድርገው ጨበጡት። «እንኳን ደህና መጣህ ዶ/ር ሚራዥ» .....ሰውዬውን ከዚህ ቀደም አይታቸው ያውቃል።.... አስታወሳቸው። አሜሪካ ውስጥ አያለ በሉሳንጀለስ የፓስፊክ ውቅያኖስ ዳርቻ ጊታሩን የሰጡት ሰውዬ ናቸው። «ኮሎኔል ፍስሐ ይባላሉ። የሚሳየል ሳይንቲስት ሲሆኑ አሜሪካ ውስጥ የጀመሩትን የረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳየል ፎርሙላ ጠረጴዛው ላይ ጥለው የመጡ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ናቸው። ኢትዮጵያ በሚለው ቅጽል ስማቸው ብትጠራቸውም ቅር አይላቸውም። እንዳንተና እንደ ሌሎቹ ብዙ ሳይንቲስቶች በኢንጂነር ሻጊዝ ተመልምለው የተላኩ ናቸው። ይህ ሁሉ የሆነው በሻጊዝ ነው። ገና እዛ የሚሠራ ጉዳይ ስላለ አንጂ በመጨረሻው ሰዓት እሱም ይመጣል» ባድናቆት ራሱን ነቅንቆ እንደገና ጨበጣቸው።

«ይህ ሁሉ ገና ጅማሮ ነው» ብለው ፈገግ አሉ ኮ/ል ፍስሐ። ክፍሉ ግዙፍ በሆኑ ኮምፒውተሮች የተሞላ ነው። ትላልቅ ስክሪኖች ላይ በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምስል ብልጭ ድርግም ይላል። ከወደ ውስጥ አንድ ሴላ ግርማቸው የሚባል ወጣት መጥቶ ተዋወቀው።

ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሲገቡ ሙሉ በሙሉ ሽበት የወረራቸው ፊታቸው ግን ወጣት የሚመስል ሰውዬ ከወንበራቸው ተነስተው «ጀነራል አጥናፉ ታዬ.... የዶርቶጋዳ መከላከያ ጉዳይ ዋና ሐላፊ....» ብለው ራሳቸውን አስተዋወቁት። በእጃቸው ቀጥሎ ወደ ሚታየው በር አመለከቷቸው። በሩ ሳይነኩት ተከፈተ። ዥው ያለው ሰፊ ክፍል አረንጓዴ የስልጠና ልብስ በለበሱ ወታደር መሰል ወጣቶች ተሞልቷል።

«ዶርቶጋዳ የምህንድስና ማዕከል» ወደሚለው ክፍል ሲገቡ ጌራ የሚባል ወጣት ቱታ እንደለበሰ ወጥቶ ሚራዥን ተዋወቀው። ቱታው በግሪስና በሞተር ዘይት ተጨማልቋል። ፊቱ ላይም ጥቋቁር የተፈነጣጠቁ ቀለሞች አርፈዋል። የብሎን መፍቻ በያዘበት እጁ ፊቱን ሞዥቆ ፈገግ ካለ በኋላ «.....ዶ/ር ሚራዥ ስለተቀላቀልከን

ልትደሰት ይገባል። ሁሉን ነገር የምትወደው ይመስለኛል። እርግጠኛ ነኝ ለዚህ ተልዕኮ በመመረጥህ ሳትደሰት አትቀርም»ሚራዥ ይህን ወጣት ለማስታወስ ጊዜ አልወሰደበትም። አባይ ማዶ የሱሬት ፀጋዬ ገብረ መድህንን ግጥም በቃሉ ያነበነበለትና «ገጣሚ» ነኝ ያለው ወጣት ነው። በፈገግታ ተግባቡ።

«ኢንጂነር ጌራ ይባላል። የዴርቶጋዳ የምህንድስና ክፍል አባል ነው።» ሲል ለሚራዥ አስተዋወቀው ዶ/ር ገ/ንጊዳ።« በዚህ የምህንድስና ማዕከል ውስጥ ከብዙ ኢንጂነሮች ጋር በመሆን ዴር33 በመባል የሚጠሩ በራሪ ማሽኖችን የሰራ ባለብሩህ አእምሮ ወጣት ነው። ኢንጂነር ጌራ የአሜሪካ የጦር ኃይል አባል ነበረ።ምርጥ አብራሪም ጭምር። ከልዩ ልዩ የዓለማችን ሀገራት የምርመራ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ሳይንቲስቶችን ዴር33 በምትሰኘውና በዴርቶጋዳ ኢንጂነሮች ጥምረት በተሰራችው በራሪ ማሽን በማምጣት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ ፓይለት ነው።»

«እንግዲያውስ ዴር33ን በቅድሚያ ላስጎብኛችሁ» አለ ኢንጂነር ጌራ። «ዴር33...» ሲል ቀጠለ ገለፃውን። «ደር33.... እንግዲህ ይህች የምታይዋት አውሮፕላን ናት። ይህች ማሽን፣ በኮምፒዩተር የሚታዘዙ ሆነው ወደ ውስጥ ወደ ውጭ የሚወጡና የሚገቡ ክንፎች ያሏት አውሮፕላን ናት። ክንፎቿ ወደ ውስጥ ሲገቡ የመኪና ቅርፅ ስለምትይዝ እንደ ሌሎች መኪናዎች በምድር ላይ ማሽከርከርና በከተሞች አውራ መንገዶች እንደልብ መንዝ ትችላለች። የዚህችው ማሽን የመሽከርከሪያ ጎማዎች ወደውስጥ ሲገቡ መሉ አካሏ በአልሙኒየም ንጣፍ በቅጽበት ስለሚሸፈን ከአየር ወደ ውሃ ገብታ በውሃ ውስጥ መንዝና ሰርጓጅ መርከብ መሆን ትችላለች። ስለዚህ ይህች ማሽን..... አውሮፕላን፣ መኪና እና ሰርጓጅ መርከብ ናት ማለት ነው። ዲዛይኗን ያወጣት የናሳው ኢትዮጵያዊ ሳይንቲስት ኢንጂነር ሽጊዝ እጅጉ ነው። አሁን የያዘችውን ቅርፅ እንድትይዝ ግን የዴርቶጋዳ ኢንጂነሮች ሌት ተቀን ሠርተዋል። ዴር33 አውሮፕላን በየትኛውም ሀገር ራዳር ውስጥ የማያስገባ ቅብ ስለተቀባች ወደየትኛውም ሀገር በመብረር ከዴርቶጋዳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሳይንቲስቶች ለማምጣት ረድታናለች» ብሎ የትልቁን መጋዘን በር ከፍቶ ዴር33ን የሚመስሉ ሌሎች መለስተኛ አውሮፕላኖችን አሳያቸው።

«በዚህ በር...» አለ ኢንጂነር ጌራ። ወደ በሩ እየተራመደ። «በዚህ በር ነው እነዚህ ሰርጓጅ መርከቦች የሚወጡ የሚገቡት። ከባህር ዳር ከተማ በተሰራውና በሌላ ሰው ስም በተከፈተው ጋራዥ በኩል የሚገቡ ብረታ ብረቶች፣ የምግብና ሌሎች የዴርቶጋዳ ቁሳቁሶች የሚመላለሱት በእነዚህ በጣና ውስጥ ለውስጥ በሚንዙ አነስተኛ ሰርጓጅ መርከቦች ነው። በዚህ ዋሻ ውስጥ ላሉ የዴርቶጋዳ

አባላት የሚገቡ ማንኛውም ነገሮች የሚመላለሱትም በእነዚህ ሰርጓጅ መርከብ፣ መኪና እና አውሮፕላን መሆን በሚችሉ መጓጓዣዎች ነው። ማንኛውም ወደዚህ ዋሻ የሚገባና የሚወጣ የዴርቶጋዳ ቁሳቁስም ሆነ ሰው በነዚህ አነስተኛ መርከቦች አማካኝነት ነው» አውሮፕላኖች ከቆሙበት መጋዘን ፊት ለፊት ያለውን ሰፊ አውቶማቲክ በር እያመለከተው አብራራለት።

ድምፅ አልባ ጀነሬተሮች የተተከሉበትንና ሰፊውን ቤተመፃሕፍት ጨምሮ ልዩ ልዩ የዴርቶጋዳ ክፍሎችን ካስጐበኘው በኋላ መልሶ ወደ አባ ገ/ንበሩ ቢሮ ሲወስደው ሚራዥ እጅግ ተገርሞ ነበር።

ከትልቁ ጠረጴዛ ኋላ ትልቅ ወንበር ላይ የተቀመጡት ሽማግሌው አባ ገ/ንበሩ ሐሜ በረዶ የሚመስል ጢማቸውን እያፍተለተሉ ከፊት ለፊት ካለው ምቹ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጋበዙት። «ግራ የተጋባህ ትመስላለህ.... » አሉት ከትንሽ ፀጥታ በኋላ። ዶ/ር ገ/ንጊዳ ወደ ሥራው ተመልሶ ነበር።

«አዎን» አለ ዶ/ር ሚራዥ።

«ግራ ቢገባህ አልደነቅም። ብዙ አዲስ ምልምሎችም ግራ ስለሚጋቡ። .... ይህን የመሰለ ዘመናዊ የምርምር ማዕከል ከዚህ ኋላቀር ሀገር ውስጥ ማን ይጠብቃል? ለዚያውም በዚህ አልባሌ ደሴት ! .....» በረጅሙ ተነፈሱና ቀጠሉ።

«በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1933 ዓመተ ምህረት። በዚህ ወቅት የኢጣሊያ ወራሪ ጦር በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ጥምር ጦር ከኢትዮጵያ ተባረረ።የኢጣሊያ ጦር ወደ አፍሪቃ ሲዘምት ግን አፍሪካን በሙሉ መቆጣጠር እንደሚችል እርግጠኛ ነበር። ለዚህም ከ40 ዓመት ዝግጅት በኋላ ኢትዮጵያን ዋና የቅኝ ግዛቱ ማዕከል ለማድረግ ኃዙን ጠቅሎ መጣ።» ዘመናዊዉ ጠረጴዛ ላይ ያለውን ኮምፒውተር ቁልፎች ሲጫኑ የኢጣሊያ ጦር ሲገባ የሚያሳዩ ፎቶዎች ግድግዳው ላይ ካለው ትልቅ ስክሪን ላይ መታየት ጀመሩ።

«ኢጣሊያ በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ጦርነት ስትጀምር ሶስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ ወታደሮች ነበሯት። ከነዚህ ውስጥ ሁለት መቶ ሺህ ያህል ወታደሮቿ አፍሪካውያን ባንዳዎች ነበሩ» ስክሪኑ ላይ የጣሊያንን ጦር ወታደሮች የሚያሳዩትን ፎቶ ግራፎች ቀና ብሎ ተመለከተ።

ጥቂቁር ወታደሮች ከነጭ ወታደሮች ጋር ነፍጥ ይዘው ሲንዙ የሚያመለክቱ ፎቶ ግራፎችን ትኩረት ሰጥቶ አያቸው። አባ ገ/ንበሩ ቀጠሉ።

«የኢጣሊያ መንግሥት ሀገራችንን ሲወር ከንጉሡ ስደት በኋላ አንዳንዱ በቁጭት ጫካ ገብቶ በአርበኝነት ተዋጋ። አንዳንዱ

ክጣሊያን ጦር ጋር ተቀላቅሎ ሀገሩን በዘበዘ። ባንዳዎች የኢጣሊያን ጦር እየመሩ አርበኞችን እያሳደዱ ሀገራቸውን አጥንቷ እስኪቀር አስጋጧት። ይህን ለማየት ችያለሁ። እኔ በዚያን ወቅት ጫካ አልገባሁም። አካኪ ዘራፍም አላልኩም። ዝም በዬ የጣሊያንን ጦር ተቀላቀልኩ። ተላላኪያቸውም ሆንኩ። ታማኝነትን ለማግኘት ጊዜ አልወሰደብኝም። ወዲያው በሜዲትራኒያን ባህር ላይ የመርከብ ትምህርት ሊያስተምሩኝ ወደጣሊያን ወሰዱኝ። መርከብ መንዳት ተማርኩ። ካፕቴን ሆኜ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ» የካፕቴንነት ማዕረግ ሲሰጡ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ ስክሪኑ ላይ ተመለከተ።

«ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ መሃል አገር በሚያደርገው ግስጋሴ የሰሜን ምዕራብ አካባቢዎችን በተለይም ጉጃምንና ጎንደርን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ያመቸው ዘንድ የማዘዣ ጣቢያውን ጕርጕራ ላይ አደረገ። በጣና ሐይቅ ሰሜናዊ ዳርቻ። መቀመጫውን ጕርጕራ ያደረገበትን ምስጢር ብዙ ሰዎች አያውቁም። ጕርጓራ ሆኖ ጉጃም ውስጥና በባህር ዳር አካባቢዎች ወደ ሚገኙ ጦር ሰፈሮች ስንቅና ትጥቅ ለማጓጓዝ በርካታ ጀልባዎችን በጣና ሐይቅ ላይ አሰማርቶ ይንቀሳቀስ ነበር። እኔንም የአንድ ትልቅ ጀልባ ካፕቴን አድርጉ ሾመኝ። ይህ ጀልባ በጣና ሐይቅ ላይ ይንሳፈፉ ከነበሩበት ጀልባዎች ሁሉ ግዙፉ ነበር። ጀልባ ከማለት ይልቅ መርከብ ብንለው ሳይሻል አይቀርም። በዕርግጥ ይህ መርከብ የመጣው በ1932 ዓመተ ምህረት ነበር። በጣና ሐይቅ ላይ የቆየውም ለጥቂት ጊዜያት ነው። በዛ ወቅት ሳኒኮላ፣ ሳንጆርጅ እና ሳንታማሪያ ከሚባሉት ጀልባዎች ሁሉ ግዙፍ የነበረው መርከብ እኔ እነዳው የነበረው ይህ መርከብ ነበር»

በ1932 ዓ.ም አካባቢ በጣና ሐይቅ ላይ ይታዩ የነበሩት ጀልባዎች ፎቶ ግራፎች ስክሪኑ ላይ ብቅ ብቅ አሉ። አባ ዝንበሩ ይነዱት ከነበረው መርከብ ላይ ከሁለት ሌላ ሐበሾች ጋር ቆመው የተነሱት ፎቶ ግራፍም ስክሪኑን ሞላው።

«እነዚህ ከእኔ ጋር ቆመው የምታያቸው ሰዎች አንዱ አለቃ አያሌው ነው አባ ዲዲሞስ። ሁለተኛውንም ታውቃቸዋለህ። አባ ፊንሐስ ናቸው። በ1933ዓ.ም የኢጣሊያ ጦር ከኢትዮጵያ ተባሮ በሚወጣበት ወቅት ብዙ ጉድ ተከስቷል። የኢጣሊያ ጦር ለወታደራዊ አገልግሎት ሲጠቀምባቸው የነበሩትን ሁሉንም ጀልባዎች ተባሮ ሲወጣ ጕርጕራ ወደብ አጠገብ በሚገኘውና ከፍተኛ ጥልቀት ባለው የሐይቁ ክፍል በአንጋራ ደሴት አስጥሟቸው ሄደ። እንዲያውም ጣሊያን ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የቀረው ጣሊያናዊ ቤተሰብ ዋና አነቀሳቃሽ የነበረ ቡስኪ የሚባል ጣሊያናዊ በ1940 ዓመተ ምህረት ሳንጆርጅ፣ ሳንታ ማሪያና ሳኒኮላ የሚባሉትን ጀልባዎች ከተቀበሩበት የአንጋራ ደሴት አውጥቶ «ናቢጋ

ጣና» የሚባል ድርጅት አቋቁሞ ነበር። በኋላ የጀልባዎቹ ስምም ተቀየረ። ሳንታ ማሪያ- ሊማሊሞ፣ ሳኒኮላ-አንድነት፣ ሳንጆርጅ ደግሞ ታጠቅ በሚል ስም ተቀየሩ። ይህንን ታሪክ ማንኛውም የአካባቢው ሰው ያውቃል። የቡስኪን ማንነት ግን ማንም አያውቅም። ለምን «ናቢጋ ጣና» የሚባል ድርጅት እንደከፈተም ለማንም ግልፅ አልነበረም። በ1967 ወታደራዊው የደርግ አስተዳደር ሥልጣን ሲይዝ ናቢጋ ጣና ከቡስኪ እጅ ወጣ። ቡስኪ መንቀሳቀስ ሲያቅተው ሁሉን ነገር ትቶ ሸሸ። የቡስኪ አላማ ግን በጣና ሐይቅ ላይ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት አልነበረም። ኢትዮጵያ የቀረው የጣሊያን ቤተሰብ ኢትዮጵያ ከጣልያን የተሻለ ለኑሮ የተመቸች ሀገር በመሆንዋ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የቡስኪ ቤተሰብ ለረጅም አመታት ሲገዳደልበት የኖረ ሌላ ከፍተኛ ምስጢር አለ» ከወንበራቸው ተነስተው እስክሪኑን የሞላውንና እርሳቸው ያንቀሳቅሱት የነበረውን መርከብ ፎቶ ግራፍ በብዕራቸው መታመታ አድርገው ተመልሰው ተቀመጡ።

«ጣሊያን በ1933 ዓመተ ምህረት ተባሮ ሲወጣ በጥድፊያ ካሰጠማቸውና በኋላ ቡስኪ የተባለው ጣሊያናዊ በ1940 ዓ.ም ከአንጋራ ደሴት አጠገብ አውጥቷቸው እስከ አሁን በጣና ሐይቅ ላይ አገልግሎት ከሚሰጡት ጀልባዎች ሌላ እኔ እነዳው የነበረው መርከብ እስከ አሁን የት እንደደረሰ አልታወቀም። ይህ መርከብ የት እንደደረሰ ታውቃለህ?» ተነስተው ተንጐራደዱና መልሰው ተቀመጡ።

«ይህ መርከብ የሰጠመው እዚሁ ጣና ሐይቅ ውስጥ ነው። እ....ዚ.....ሁ!.... በአሁኑ ወቅት ብቸኛው በህይወት ያለሁ ምስክር እኔ ብቻ ነኝ። በጣና ሐይቅ ውስጥ ደብዛው ስለጠፋው መርከብ ከእኔ በቀር የሚያውቅ አንድም ኢትዮጵያዊ የለም።» አሁንም ተነስተው ተንቀራጠጡ።

«በከባድ ጥንቃቄና በጥልቀት የሰጠመው ይህ መርከብ ሃምሳ ዘጠኝ በርሜል የጠገራ ብር፣ ሰላሳ ስምንት በርሜል ወርቅ እና በዲያመንድ የተሞሉ የብረት ሳጥኖችን ተሞልቶ ነበር።..... ከዚህም በላይ በሌሎች ምን እንደያዙ ባለወኪቸው የብረት ሳጥኖች ተሞልቶ ነበር የሰጠመው። ይህ ሁሉ ሀብት የተቀረመው በጕንደር ቤተ መንግሥታት ሥር በሚገኙ የገንዘብ ማጠራቀሚያ ገደሎች እና በመላው ኢትዮጵያ ገንዘቦቻውንና ወርቃቸውን በምድር ውስጥ የመቅበር ልማድ ካላቸው ኢትዮጵያውያን የተዘረፈ ነው። የእኛው የራሳችን ውድ ሀብት! ይህ መርከብ በድቅድቅ ጨለማ በጣና ሐይቅ ጠልቆ በተቆፈረ አዘቅት ውስጥ ሲቀበር ከቀባሪዎቹ መካከል እኔ፣ አያሌው እና ፊንሐስ ነበርንበት። በዚህ መርከብ ውስጥ እንሰራ ስለነበር። መርከቡ ከሰጠመ በኋላ የጣሊያን ጀነራሎች ካርታውን

በደንብ አንስተው ዓይኖቻችንን በጥቁር ጨርቅ ተሸፍነን በሌላ አነስተኛ ጀልባተጫንን። መሣሪያ ተወድሮብን ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ካመጡን በኋላ በዚሁ ደሴት በሚገኝ አንድ ትልቅ ዋርካ ሥር ከሌሎች ሃያ አራት ጣሊያናውያን ወታደሮች ጋር የጥይት ናዳ አርከፈክፉብን። ጣሊያናውያን ወታደሮችን ጨምሮ ሌሎች የመርከቡ ዕቃ አውራጅና ጫኚ ኢትዮጵያንም ተረሽነ። እኔ ባቴ ላይ በጥይት ቆስዬ ወደክ። ከስድስት በላይ ሰዎች ከላየ ላይ ተነባብረውብኝ ሲወድቁ እኔ ከአስከሬኖች በታች በደም ተጨማልቄ የሚሆነውን ማዬት ጀመርኩ። እኛን የረሸኑን የኢጣሊያ ጀነራሎች ደግሞ እርስ በእርስ ተፋጠጡ። መርከቡን ያሰጠመብትን ቦታ የሚጠቁመውን ካርታ ሽሚያ እርስ በእርስ መታኮስ ጀመሩ። ካርታውን የያዘው ጀኔራል እኔ ላይ ከወዳደቁት አስከሬኖች በላይ ተመትቶ ወደቀ። እንደምንም እጀን ከኪሱ ሰሰድ ከርታውን አገኘሁት። በደም በተጨማለቀ እጀ ከወደኩበት መሬት ጥግ ካለ ድንጋይ ሥር ተሰቤ ቀበርኩት። ጀኔራሎች ተገዳድለው ሲያልቁ በመጨረሻ የቀረው ጀኔራል የሁሉንም ጀኔራሎች ኪስ መፈተሽ ጀመረ። ካርታውን ሊያገኘው ግን አልቻለም። ዕብድ ሆነ። የወዳደቁትን ወታደሮች ኪስ ሁሉ እየፈተሸ አድሮ ሌሊቱ ሲነጋበት የእኛን ዓይኖች አስረው በመጡበት ሞተር ጀልባ ሄደ።

ይህ ጀኔራል በኋላ ወደ ኢጣሊያ ተጉዞ ከተመለሰ በኋላ ቤተሰቦቹን ይዞ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ጀመረ። ስሙን ቡስኪ ብሎ ቀይሮ በ1940 ዓ.ም ናቢጋ ጣና የሚባል ድርጅት ሲከፍት ማንም የቀድሞ የኢጣሊያ ጀኔራል መሆኑን አላወቀም።»

«እሺ ካርታውስ የት ደረሰ..... » ሚራኾ በተመስጦ ሲያደምጣቸው ከቆየ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥያቄ አነሳ።

«ካርታውን አሸሽሁት። ከእኔ ጋር ተረሽነው የነበሩት አያሌውና ፊንሐስ ቆስለው በህይወት አገኛኋቸው። እኔ ግን ባቴን ጨርፎኝ ካለፈ ጥይት በቀር የጠነከረ ቁስለት አልነበረብኝም። ልብስ እየቀደድኩ ቁስላቸውን ካሰርኩላቸው በኋላ የገዳሙ መነኮሳት ወታደሮችን በመቅበር እንዲተባበሩን ወደገዳሙ ወርጀ ተማፀንኳቸው። በዛ ወቅት በነበሩ መነኮሳት አሁን ደረስ ለታሪክ መዘክርነት ቆሞ ባለው በዛወቅት የጣሊያን ጀልባዎች በጣና ሐይቅ ላይ ሲተላለፉ ምልክት እንዲሆን በተተከለው የመብራት ማማ አቅራቢያ በዚሁ ደሴት ላይ ከሰሩት ወደብ አነባቢ ጥልቅ ጉድጓድ ተቆፍሮ ጣሊያናውያኑ ወታደሮችና የሞቱት ኢትዮጵያን ወዝ አደሮችም ተቀበሩ። እኛም በገዳሙ ውስጥ ከሰነበትን በኋላ ወደ ባህር ዳር ከተማ ሄድን። በዛ ወቅት ንጉሡ ወደ ሃገራቸው ተመልሰው ስለነበር ወደየቤተሰቦቻችን ስንመለስ አያሌው እኔ እና ፊንሐስ በባንዳነት ተከሰን ወደ ወህኒ ተወረወርን። በ1955 ዓ.ም

ሶስታችንም ከእሥር ቤት አመለጥን። ፊንሐስ ወደ ሰሜን ተራራ ሸሸ። ቤተ እስራኤላዊ ስለነበር በሰሜን ተራራ በአንጥረኝነት ከተሰማሩ ዘመዶቹ ጋር ተጉራብቶ ትዳር መሰረተ። አያሌውና እኔ በባህር ዳር ከተማ አቅራቢያ በምትገኝ መንደር ውስጥ መኖር ጀመርን። እኔ በ1959 አንተ ከተወለድክ ሶስት ዓመት ገደማ ሲሆንህ እንደገና የንጉሡ ወታደሮች ስላሳደዱኝ ወደ ዚሁ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አንተን ይዤ ሸሸሁ። በኋላም ፊንሐስ ሲጻራ የምትባል ህፃን ልጁን ይዞ ወደዚሁ ገዳም መጣ። በዚህ ገዳም ሌቶች ስለማይገቡ አንተ እና አሷ ወዳደ[illegible]በት ለእስጦንስ የሌቶች ገዳም አስረከብናችሁ።

«የሥጋ አባትህ ነኝ እያሉኝ ነው?»። ሲል አቋረጣቸው ዶ/ር ሚራኾ።

«አዎ። አባትህ ነኝ። አናትህ እኔ ያለሁበትን እንድትናገር ስትደበደብ አረፈች። ገደሏት።»

«ለምን አስካሁን አባቴ እንደሆኑ አልነገሩኝም?»

«ጊዜውን እየጠበኩ ነበር። በኋላ ከዳጋ ወደ ክብራን ገዳም ልነግርህና ይህንንም ምስጢር ላካፍልህ ስመጣ ከገዳሙ ጠፍተህ መሄድህን ሰማሁ። ፍለጋዬም ከንቱ ሆነ። ይኸው ከስንት አመት በኋላ ታሪክ መልሶ አገናኘን።»

«የሲጻራ አባትስ አባ ፊንሐስ ነበሩ እንዴ?»

«እርሳቸው ነበሩ» አሉና አባ ዝንበሩ ስለ ሰጠመው መርከብ የጀመሩለትን ወግ ቀጠሉለት።

«የእኛን ወደዚህ ገዳም መምጣት ተከትሎ አለቃ አያሌውም መጣ። ካርታው በእኔ እጅ እንደሚገኝ ነገርኒቸውና በአንድ ነገር ተስማማን። የሰጠመውን መርከብ አውጥተን በውስጡ ያለው ሀብት እኩል ለመካፈል። ይህን ለማድረግ ግን አቅማችንም ዘመኑም አይፈቅድም ነበር። የሰጠመውን መርከብ ለማውጣት ኃይል ያስፈልገን ነበር። ምክንያቱም መርከቡ ከሐይቁ ወለል በታች በከፍተኛ ጥልቀት ተቀፍሮ ነበር የተቀበረው። ይህን መርከብ ለማውጣት ምንም አይነት አቅም አልነበረንም ነበር። በኋላ ሶስታችንም ይህንን ዋሻ መቆፈር ጀመርን። ዋሻውን መቆፈር ስንጀምር አላማችን ለራሳችን መደበቂያነት ለመጠቀም ነበር። በኋላ የሀገሪቷን ውድ ሀብቶችና የብራና መፃህፍቶች ከጥፋት መከላከያ ሆኖ አገለገለ። እኔም በዚህ ወቅት በገዳሙ ውስጥ በማነባቸው መፃሕፍት እየተለወጥኩ መጣሁ። ራዕዬን ከግለሰብነት ወደ ሀገራዊነት ቀየርኩት። ራሴን ብቻ ለማበልፀግ ቀን ተሌት የሰጠመውን መርከብ ስመኝ ነበር። በኋላ ሁሉም ነገር አዕምሮዬ ውስጥ ሲቀያየር ታወቀኝ። ወደ ጣሊያን ለመርከብ ነጅነት ሥልጠና ልወስድ በሄድኩበት ወቅት ያየሁት የአውሮፓ ስልጣኔ አስቀናኝ።

የተዘረጉት የባቡር ሐዲዶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች ብልፅግናዎች በሀገሬም እንዲኖሩ ተመኘሁ። እያወክ ስትመጣ በድንቁርና የታወረ አይንህ ሲገለጥልህ የበለጠ መበዝበዝህ ይሰማሀል። መብትህን ካላወክ መጨቆንህ አይገባህም። ስለዚህ ይህንን ዋሻ ወደ ትልቅ ሀቡዕ የምርምርና መንግስታት ሲለዋወጡ የማይለዋወጥ ለሀገሪቷ ፅኑዕ መሰረት የሚሆን ምስጢራዊ ድርጅት የማድረግ ራዕይ በውስጤ ተጠነሰሰ። ሀገሪቷን ከብዝበዛና ከኋላ ቀርነት ማላቀቅ የሚቻለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት በራሷ ልጆች አእምሮ ውስጥ ገብቶ ማዕድኖችዋና ውድ የመሬት ውስጥ ሀብቶቿ በራሷ ልጆች በልፅገ በቅፅበት የምታድግበትን መንገድ ስናፈላለግ መሆኑ ገባኝ። ኢትዮጵያን ለኢትዮጵዮውያን ማድረግ የሚቻለው ትክክለኛው የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ትክክለኛው የቴክኖሎጂ መሣሪያ በራሷ ልጆች እጅ ሲገባ መሆኑን ተረዳሁ። ምክንያቱም እኔ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሃብት ይዞ የሰጠመ መርከብ ካርታ ፍለጋ ስንቀራፈፍ የኖርከበት ምክንያት ትክክለኛው የቴክኖሎጂ መሣሪያና እውቀት ስላልነበረኝ ነው። የኢትዮጵያም ችግር ከዚህ ጋር ተመሣሣይ ነው። ስለዚህ በዚህ ደሴት ውስጥ የኢትዮጵያን የቴክኖሎጂ መሠረት መጣል ተመኘሁ። ይህን ራዕይ የተጋራኝ ሰው አለቃ አያሌው ብቻ ነበር። አያሌው እዚህ ገዳም ውስጥ አባ ዲዲሞስ ይባል ነበር። አባ ዲዲሞስ ብዙ ለውጦችን ለማምጣት ሥልጣን ይፈልግ ነበር። የጣሊያን ባንዳዎች ከጨፈጨፋአቸው ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር ቅርርቦሽ ነበረው። የጠበቀ ጓደኝነትም ነበራቸው። በሀገሪቷ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ቢችሉ ጳጳስ ባይችሉ ኤጲስ ቆጶስ አድርገው ሊሾሙት እንዳቀዱም በገነቱ ልዑል ጉድጓድ ቤት ከመታሰራቸው ቀደም ብለው ነግረውት ነበር። አቡነ ጴጥሮስ ነገሮችን ፊት ለፊት የመጋፈጥ ባህሪያቸውን እንዲተዉ በየቀኑ አባ ዲዲሞስ ይወተውታቸው ነበር ግን አልሆነም። አቡነ ጴጥሮስ በባንዶች የጣሊያን አሽከሮች በጥይት ተደብድበው ሞቱ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አባ ዲዲሞስ ባህሪው ተለዋወጠብኝ። የሰጠመውን መርከብ ካርታ ወደ አንድ ትልቅ የብራና መጽሐፍ ገፅ ላይ ገልብጠነው ነበር። ጣሊያኖች የሠሩት ካርታ የወረቀት ስለነበር በቀላሉ ስለሚበላሽ ያንኑ ካርታ ወደ ብራናው መጽሐፍ ገፅ ላይ እንድንገለብጠው የወተወተኝ ራሱ አባ ዲዲሞስ ነው፤ አለቃ አያሌው። ተከተለኝ» ብለው ከቢሮአቸው ወጥተው የብራና መጻሕፍት ወደ ተከማቹበት አዳራሽ ይዘውት ገቡ። «ይታይሃል?» አሉት። ወደ አንድ ግዙፍ የብራና መፅሐፍ እያመለከቱት። የወደቀ ትልቅ ሳንቃ እንጂ መጽሐፍ አልመስለውም ነበር። በህይወቱ ይህን የሚያህል ግዙፍ መጽሐፍ አይቶ አያውቅም። ዶ/ር ሚራዥ።

«ይህ መጽሐፍ ስድስት ሜትር ቁመትና አራት ሜትር ስፋት ያለው የምድራችን ግዙፍ መጽሐፍ ነው። ካርታውን በቀይ ቀለም የሳልነው በዚህ መፅሐፍ ፬፻፶፩ኛ ገፅ ላይ ነበር።» የመፅሐፉን ሽፋን ሳንቃ መሰሉን ገበታ ለሁለት ጫፍና ጫፍ ይዘው ገለጡት ግዙፉን የብራና መፅሐፍ። በውስጡ የተፃፉት ቃላት የግዕዝ ቃላት ይምሰሉ እንጂ አንዱ ቃል ሊገባው አልቻለም። አባ ዝንበሩ ጥቂት ሲጨነቅ ከተመለከቱት በኋላ «ልጄ ሚራዥ መጽሐፉን ለማንበብ አትጨነቅ.....አይገባህም። መጽሐፉን አልተጠቀምነውም እንጂ በብዙ ሳይንሣዊ ግኝቶች የተሞላ መሆኑን አስጠንቼ ደርሸበታለሁ። በጥንታዊ የሣይንስ ግኝቶች የተሞላ ነው። የተፃፈው በግዕዝ ቋንቋ ቢሆንም ቃላቱ ምልዋጥ በሚባል ስልት የተጻፉ ናቸው» የእጅ መጻፍ የምታህል ሌላ ትንሽ የብራና መጽሐፍ ከተከመሩት መጻህፍት መሃል መዘው አሳዩት።

ይህቺ ትንሽ መጽሐፍ የዚህ ግዙፍ መጽሐፍ መፍቻ ናት። ጠላት ይህንን ግዙፍ መጽሐፍ ሰርቆ ቢሄድ ይህንን መፍቻ ካልያዘ መጽሐፉን አንብቦ ሊረዳ አይችልም። አባቶቻችን ጠንካሮች ነበሩ። እኛ ግን...አየህ ይህ ህልም ወይም ልብ ወለድ አይደለም ...እውነተኛ ታሪክ ነው። ይህ መጽሐፍ የያዘውን ምስጢር ለመፍታት ብዙ ጥናት ይጠይቃል። በራሳችን ሥነ ልቦናዊ እምነት ሰለሰለሰን የእኛን ነገሮች የመመርመር ዝግጅቱ የለንም ። ያም ሆነ ይህ ዋናው አላማችን መጽሐፉን አንብቦ መረዳት አይደለም። እስቲ....፬፻፶፩ኛውን ገጽ ግለጠው» አሉት።

ሚራዥ ለብዙ ደቂቃዎች ትላልቆችን ገጾች እየገለበጠ ፬፻፵፫ኛው ገጽ ላይ ደርሰ። ከ፬፻፵፫ኛው ገጽ ቀጥሎ የመጣው ገጽ ግን ፬፻፵፩ኛው ነው። ፬፻፶፬ኛው ገፅ የለም። ቀና ብሎ ተመለከታቸው። አባ ዝንበሩ ፈገግ አሉ። የውሸት ፈገግታ። አባ ዲዲሞስ 404ኛውን ገጽ ፬፬፬ ብለው አሳስተው እንደፃፉት ያውቃሉ።

«፬፻፵፬ኛው ገጽ የት ገባ?» አለ ዶ/ር ሚራዥ።

«፬፻፵፬ኛው ገፅ ዩት እንደገባ አታውቅም?» አሉት መልሰው አባ ዝንበሩ።

«እኔ?»

«አዎ አንተ። አባ ዲዲሞስ በልጅነትህ ጀርባህ ላይ የነቀሱትን ንቅሣት እስከ አሁን አላየኸውም? ከሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ግጥም ውስጥ ሰቀቃወ ጴጥሮስ የሚለውን በብራና ላይ የፃፉትና ሎሬቱ በግጥሙ ውስጥ እንዲያስገባ የተወሰኑ ምስጢራዊ ቃላት የሰጡት አባ ዲዲሞስ ናቸው። በ1961 ዓ.ም። በግጥሙ ውስጥ ያሰፈሩአቸውን ምስጢራዊ ቃላት ወደ ቁጥር ለውጠው ከአንተ ጀርባ ላይ በንቅሣት አስቀመጡአቸው። በቶ ፊደል ቅርጽ በተሰራው መስቀል የሰጠመውን መርከብ ምስጢር አስቀምጠውበታል። ሰቀቃወ

ጴጥሮስ በሚለው የፀጋዬ ግጥም ውስጥ ብዙ ምስጢራዊ ቃላትን ከማስቀመጣቸው በፊት በዚህ ግዙፍ መጽሐፍ ገጽ ላይ ያስፈርነውን ካርታ ይዘውት ጠፉ። የመጽሐፉን ገጽ ገንጥለው። እንደነገርኩህ በዚህ ወቅት የነካቸውን እንጃ ሁሉን ነገር ከእኔና ከአባ ፊንሐስ መደበቅ ጀምረው ነበር። ምናልባት ተጠራጥረውን ይሆናል። በእርግጥ አባ ፊንሐስን እኔም አላምነውም። ሁልጊዜም ስለ ሀገር ማሰብ አይፈልግም። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ያንገሸግሸው ነበር» በአጻራሹ ውስጥ ተንጐራደዱ አባ ዝንበሩ።

«አባ ፊንሐስ በዚህ ገጻም ውስጥ የተቀመጠበት ምስጢር የሰጠመውን መርከብ ካርታ በእጁ ለማስገባት ብቻ ነበር። አባ ዲዲሞስ ወይም አለቃ አያሌው በዚህ ግዙፍ መፅሐፍ ውስጥ ካርታው የተሳለበትን ፬፻፵፬ኛውን ገጽ ገንጥሎ ይዞ ሲያመልጥ እኔና አባ ፊንሐስ ተከታተልነው ። በዚህ ጊዜ አባ ፊንሐስ የአያሌውን ቤትና ባለቤቱን አቃጥሎ ተስፋ ቆርጦ ፍለጋውን ሲያቆም እኔ ግን እስከ ቦንጋ ተከታትየ አያሌውን ያዝኩት። 404ኛውን ገጽ ግን እጁ ላይ አላገኘሁም ነበር። በቶ ቅርጽ የተሰራውን ባለ ጉጥ መስቀልና ሰቆቃወ ጴጥሮስ የሚለውን የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህንን ግጥም በግብግብ ቀምቼው ተመለስኩ። በኋላ ላይ አያሌው በልጁ መገደሉን ሰማሁ። አባ ፊንሐስም ተመለሰ። ሁሉን ነገር ከፊንሐስ ደብቄ በዚህ ደሴት ውስጥ የዋሻውን ቁፋሮና ሀልሜን ሳስፋፋ ኖርኩ። በኋላ ደግሞ የባለ ጉጡን ግማደ መስቀል ከአንተ ጀርባ ላይ በንቅሣት ተስሎ ሣይ በቶ ቅርጽ የተሰራውን መስቀል ለአንተ አሰርኩልህ» ንግራራቸውን አቋርጠው ጠልቀው ተመለከቱት።ግራተጋባ ሚራዥ።

«አየህ ልጄ ሚራዥ.... ነገሩን ለማሳጠር ያህል። ፊንሐስ ከእኔ ጋር ይሠራ ነበር። 1978 ዓ.ም አካባቢ በሴቶች ገዳም ትኖር የነበረችውን ልጁን ይዞ የደረሰበት ጠፋ። ወደ ጎርጐራ ሂዶበት የነበረው የገዳመ ጀልባ ጎርጐራ ወደብ ከመገኘቱ በቀር ፊንሐስ የት እንደገባ አላውቅም። እኔ ግን ከዛ ጊዜ ጀምሮ በዚህ ዋሻ ውስጥ ደፋ ቀና ማለቱን አላቆምኩም። ከዛ ጊዜ ወዲህ በዚህ ዋሻ ውስጥ ብዙ ለውጦች ታይተዋል። ዋሻውን ተዘዋውረህ እንደጎበኘኸው እጅግ ዘመናዊ የምርምር ማዕከል ለመሆን ችሏል። ይህም የሆነው በውጭ ሀገር ያሉ እንደ ኢንጂነር ሻጊዝ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሳይንቲስቶች በገንዘብም በእውቀትም አብረው መስራት ከጀመሩ ወዲህ ነው። በረቀቀ ዘዴ ዴርቶጋዳ የሚመለምላቸው እነዚህ ሳይንቲስቶች ወደዚህ ዋሻ ጓዛቸውን ጠቅልለው ከመምጣታቸው በፊት ሀብታቸውንና እውቀታቸውን ለዚህ ሀቡእ ድርጅት አውለውታል። ከእነዚህም መሃል የናሳው ሳይንቲስት ኢንጅነር ሻጊዝ እንደ ሆነ አውቀሃል መቼም። እሱ ነው የምንፈልጋቸውን ሳይንቲስቶች አንተ

ከመጣህበት መንገድ በተለዩ መልኩ ወደዚህ ድርጅት መጥተው ሥራቸውን እንዲሰሩ ያደረገልን» በጥልቀት ተመለከቱት።

«ከእኔ የሚጠበቀው ምንድነው?»አለ ዶ/ር ሚራዥ።

«ሁለት ነገር ይጠበቅብሃል። አንዱ ቀሪ ህይወትህን በዚህ ድርጅት ውስጥ በማገልገል ሀገርህን ከጥፋት ማዳን ነው። በዚህ ሰአት አለማቀፍ ማፍያዎች ከማይጠረቁት የመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመሻረክ ሀገርክን እየበዘበዙአት ነው» አንገታቸውን ደፍተው ከተከዙ በኋላ «ማሔር ሻለል ሐሽ ባዝ» ብለው ቀና አሉ። «ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ። ኢትዮጵያ ተስፋ በቆረጡ ወጣቶችና ህዝቦች ተሞልታለች። የብዙ ኢትዮጵያውን መንፈስ ተሰብሯል። የድህነቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ሁላችንም እናውቀው ይሆናል። እሱን ለመድፈን ግን አንድ ልብ የለንም። መንፈሳችን ተሰባብሯል። ስለዚህም በእስቃቂ ሁኔታ እየተበዘበዝን ነው። ራሳችንን ለብዝበዛ ያጋለጥነው እኛው ራሳችን ነን። የጋራ ራዕይ ሊኖረን ይገባል።»

«ለዚህ አላማ ሌላው ከኔ የሚጠበቀው ነገር ምንድን ነው?» አለ ዶ/ር ሚራዥ።

«የሰጠመውን መርከብ የምናወጣበትን ቁልፍ ስጠን።»

«ምን?»

«በቶ ቅርጽ የተሠራውን ግማደ መስቀል መልስልኝ።»

«እሱ መስቀል ቁልፍ ነበር እንዴ?»

«እስከ አሁን ይዘኸው ስትኖር አላወከም ነበር?»

«መስቀሉን እኮ.....» አፉን ከፍቶ ቀረ። የሞቀ ትንፋሹን በረጅሙ ለቀቀው።

«መስቀሉን ስጠኝ። ግማደ መስቀሉን መልስልኝ። የሰጠመው መርከብ ሀብት ለሀገርህ ያስፈልጋታል። ተመልከት...» አሉት ስክሪኑ ላይ የተደነቀረውን የኢትዮጵያን ካርታ ።

«ካርታው ይታሀይል?..... ይህ ካርታ የወደፊቷ ኢትዮጵያን የሚያመለክት ነው። እኔ አሁን እድሜዬ ዘጠና ስምንት ዓመት ደርሷል። የሰጠመው መርከብ ሀብት ወጥቶ ለግሌ የሚፈይድልኝ አንዳች ነገር የለም። ለእኔ አሁን የሚያስፈልገኝ ሶስት ክንድ የከፈን ጨርቅ ብቻ ነው። የምቀበርበትን መቃብር ቆፍሬ ዕለት ሞቴን እየተጠባበኩ ነው። ከሰጠመው መርከብ ሀብት ሳባራ ሳንቲም ለግሌ ለመውሰድ የምመኝበት ወቅት ላይ አይደለሁም..... ያለሁት።.....ካርታውን እየውማ የዚህችን ሀገር ትክክለኛ ብልጽግና የምትመኝ ከሆነ ከሰሜን እስከ ደቡብ...ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የተዘረጉ የባቡር ሀዲዶች ከሁሉም በፊት እንዲኖራት ማለም አለብህ። ከተሞችንና መንደሮችን የሚያገናኙ የባቡር ሀዲዶች ከተዘረጉባት የህብረተሰቡ የንግድና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ይፋጠናል። ትክክለኛ አንድነት ሀገሪቷ የሚኖራትም በነዚህ ሀዲዶች

ላይ እንደጥይት የሚወነጨፉ ባቡሮች ህብረተሰቡን በፍጥነት ሲያቀራርቡት ነው። ባቡሮቹ የሚተነፍሱት የተለያዩ ክልል አየር የአንድነት አስትንፋስ ይሆናል። መንገድብዙዎችን ያገናኛል። ጉንዳኖች ተያይዘው በሚሠሩት መንገድ ታላቅ ወንዝ ይሻገራሉ። ጉንዳኖች ተያይዘው ዓባይን ሲሻገሩ ዓይቻለሁ። እኛም ተያይዘን በምንሠራው መንገድ ወደስልጣኔ እንሸጋገራለን። የኢትዮጵያን እውናዊ አንድነት ከቃል የምናሸጋግረው ህዝቡን በኢኮኖሚና በብዙ ማህበራዊ መስተጋብሮች ስናስተሳስረው ነው። መንገድ የኢትዮጵያ አንድነት ደም ሥር ይሆናል። ኢትዮጵያን አንድ ማድረግና ወደታላቅ ስልጣኔ ማምጠቅ የሚቻለው ከሰሜን እስከ ደቡብ ...ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በተዘረጉ የባቡር ሀዲዶች ላይ እንደጥይት በሚወነጨፉ ባቡሮች ሲኖሩን ነው። ከዛም አንድ ሰው ከደቡብ ጫፍ ተነስቶ ከሰሜኑ ጫፍ ለመድረስ የሚያባክነው ጊዜ እና ብዙ ገንዘብ አይኖርም። ሁሉም ነገር ይፋጠናል። በሀገሪቷ ጠረፋማ አካባቢ ስትሠራ ውለህ ዋና ከተማዋ ውስጥ ካሉ ቤተሰቦችህ ሂደህ ማደር ትችላለህ። የትም ቦታ ለሥራ ብትመደብ አታቅማማም። ምክንያቱም የፈለክውን ጭነህ ቤትህ በቡሌት ባቡር ለመመለስ ጊዜ ስለማይጨርስብህ።

የኢትዮጵያ መሪዎች ራሳቸውን ወንበሩ ላይ ለማቆዬት.... ለፖለቲካ ... ለስብሰባ.... ለፕሮፖጋንዳ መንዣ ....ለካድሬ ኮፍያ እንኳ የሚያወጡት ገንዘብ በሀገሪቷ ሙሉ የባቡር ሀዲዶችን ለመዘርጋት ቢያውሉት እስከ አሁን ሀገሪቷ በድህነት አትማቅቅም ነበር። ይህን ማድረግ ግን አይፈልጉም። ለግል ብልጽግና የሚራኮቱ ቅጥረኞች በመሆናቸው። መንገዶች ከበዙም መንግስትን ለመገልበጥ የሚሞክር ማንኛውም ሀይል በቀላሉ ሊሳካለት ስለሚችል። መሪዎቻችን እነማንም ይሁኑ እነማን እኛ በግላችን በዬትኛውም ጊዜ በዬትኛውም ፈተና ውስጥ ሆነን ሀገራችንን መገንባት አለብን። እስከ መቼ ጥሩ መሪ እንጠብቃለን?.....ለሀገር ብልጽግና የምትቆረቆር ከሆነ ይህን አላማ ትደግፋለህ። የሰጠመው መርከብ ሀብት ደግሞ ከነገርከህ በላይ ማድረግ የሚችል ሀብት ነው። የባቡር ሀዲዱን ለመዘርጋት በቂ ኢንጂነሮች አሉን። የመንገድ ተቋራጭ ድርጅት እናቀርብና.....እንዲያውም አንተን በባለሀብት ሽፋን ከመንግስት ጋር አደራድረን የባቡሩን ሐዲድ በሰጠመው መርከብ ሃብት ለሀገራችን እንዘረጋላታለን። የባቡር ሀዲዱም የሀገራችን አንድነትና ህልውና ደም መዘዋወሪያ የደም ሥር ይሆናል። እስኪ በከተሞች ውስጥ የምድር ውስጥ የኤሌክትሪክ ባቡሮች ሲወነጨፉ.....በምድር ላይ ደግሞ አገር አቋራጭ ተወንጫፊ ባቡሮች በባቡር ሀዲዶች ላይ በተበረቦሩና በተበሱ ተራሮች ውስጥ አያቆራረጡ ሸው እልም ሲሉ የሚመጣውን ብልጽግና አስብ።

ይታይህ ያኔ የሚኖረው አንድነት! ይታይህ ያኔ የሚኖረው መፈቃቀር... ይታይህ ያኔ የሚፈጠረው መቀራረብ ....ይታይህ የተሰባበረው የኢትዮጵያ የአንድነት መንፈስ ሲጠገን... ይሄ ነው እውናዊ አንድነት። አለበለዚያ ዝም ብሎ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ማለት የውሸት ይመስላል። ይህኛው ትውልድ ሠራሁት የሚለውና ለእናት ሀገሩ የፍቅር መግለጫ ስጦታ እንዲሆን የባቡሩን ሀዲድ በዚህ ትውልድ ስም ልንገነባለት ይገባል። ቃል በተግባር ሲታይ የጋራ ህልሙም እውን ሲሆን ያኔ ጉለያይ ብትለው እንኳ የሚለያይ ህዝብ አይኖርም። እንዲያውም ኢትዮጵያዊነት ወደ አፍሪካዊነት እየተለወጠ ኢትዮጵያ ላይ የተለከሰው ችቦ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እየበራ ይመጣል። አፍሪካም ታብባለች። ለዚህ ነው ቁልፉን ስጠኝ የምልህ። ባለጉጉን ግማደ መስቀል.....እድሜ ልኬን ስፋለም የኖርኩለትን ምስጢር መፍቻ.....ስ..ጠ...ኝ...»

«መስቀሉን እኮ..... » ሚራዥ አቀረቀረ። በዓይኑ ዕንባ ሞላ። መጥፋቱን ሊያረዳቸው አልደፈረም። «ዝም ብሎ መስቀል መስሎኝ ለሲጳራ አስሬላት .....ያ...ያ..... ያኔ ...እ...እ...እነ አባ ፊንሐስ ይዘዋት ሲሄዱ..... ይዘውት....ወይኔ.....» ተንተባተበ።

«እ?» በድንጋጤ ቱግ አሉ አባ ገሪንበሩ። ተንደርድረው በጥፊ ድርግም አደረጉት።

አባ ፊንሐስ ሲጳራን ይዘው የሸሹበት ምክንያት ገና ዛሬ ተገለጠላቸው። ከሲጳራ አንገት ላይ በቶ ቅርጽ የተሰራውን ባለጉጥ መስቀል በማየታቸው ይዘዋት እንደከበለሉ ተረዱ። በንዴት ጠፉ። መናገር እንኳ አልቻሉም። ከንፈራቸው ተንቀጠቀጠ።

ሚራዥ ለአንድ ሳምንት ያህል በባዶነት ስሜት ነፍዙ ለነበተ። በኋላ ግን ህይወቱን በሙሉ ከኢትዮያውያን ወገኖቹ ጋር ተባብሮ የባቡሩን ሀዲድ ለመስራት «ዶርቶጋዳ» የሚል ፕሮጀክት ነደፈ። በዚህ ፕሮጀክት መሠረት በጥቂት አመታት ውስጥ ኢትጵያን በባቡር ሀዲድ ለማገናኘት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ዘረዘረ። እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ በገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ በማሳተፍ ይህን ፕሮጀክት የህብረተሰቡ ራዕይ ለማድረግ የሚከተለውን እቅድ ነደፎ ሲጨርስ ከዘቀጠበት ባዶነት ነቃ። ለፕሮጀክቱ መሳካት ቆርጦ ተነሳ። ኩላሊቱን ከመሸጥ ጀምሮ የማይሞክረው ጥረት እንደማያኖርም ወሰኗል። የኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ ጥረት ሀገሩን የሚገነባበት ብቸኛው አድል መቃረቡን አወቀ። «ይዘገይ ይሆናል እንጂ የማይሳካ ህልም የለም» ሲል ህልሙ እውን እንደሚሆን አረጋገጠ። በዓይነ ህሊናው በኢትዮጵያ ተራራዎችና ሸለቆዎች እያቋረጡ እንደ ጥይት የሚምነጨጩ ባቡሮች ታዩት።

በኋላ ደግሞ አባ ዝንበሩ መልሰው አጽናኑት። «የሰው ልጅ ትልቁ ሀብቱ ጭንቀላቱ ነው። የምድራችን ትልቁ ሀብትም ጭንቅላት ነው። ስለዚህ አሁን ወዳለን ነገር ፊታችንን እናዙር። ከሰጠመው መርከብ ሃብት ይልቅ ያንተ ጭንቅላት ለሀገርህና ለወገንህ ይጠቅማል። ስሜታዊ ሆኜ ነገሩን አከረርኩት እንጂ። ስለዚህ ይህችን ሀገር በእውቀትህ አገልግላት» አሉት። «ይልቅ በዚህ ወቅት የምናከናውነው አንድ ታላቅ ተልእኮ ስላለ በዛ ላይ በመሳተፍ እርዳን። ከነገ ወዲያ ወደ አሜሪካ ትጓዛለህ።»

ሚራዥም ኢትዮጵያን ለሚጠቅም ማንኛውም ተልእኮ ራሱን ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይል ገለፀላቸው።

በታህሣሥ ወር መገባደጃ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1998 ዓ.ም አንድ ሌሊት ሚራዥና ዝንጊዳ ኢንጂነር ጌራ በሚያበራት ዴር33 ልዩ ድምጽ አልባ አውሮፕላን ለልዩ ተልዕኮ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ ዋሻ በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ ወጥተው ወደ አሜሪካ በረሩ።

ዴር33 ጣና ውስጥ ሰርጓጅ መርከብ። አየር ላይ ልዩ አውሮፕላን። አሜሪካ ውስጥ የቤት አውቶሞቢል ሆና ለልዩው ተልዕኮ ተሰማራች።

፲፯

ኒውዮርክ፡አሜሪካ
1998 ዓ.ም
ታህሣስ 28.....ከምሽቱ 5:46

የቤቷ በር በሀይል ሲንኳኳ ቀና ብላ ግዳግዳው ላይ ትር...ትር.. ትር....የሚለውን የግድግዳ ሰዓት ተመለከተችው። 5:46። ደግሞ ተንኳ። ትንፋሽዋን ዋጥ አድርጋ ወደ ሽጉጧ እጇን ላከችው። ተሰልሶ በሩ ተሰለቀ።

«ማነው?» አለች ሜሮዳ ጉሮሮዋን ጠራርጋ ።

«እኔ ነኝ» አለ ጎርነን ያለ ደምፅ ከውጭ።

«ማን ልበል ?»

«ይህን ደምፅ አታውቂውም?» አለ ከውጭ የሚመጣው ድምፅ። «ሚራዥ ነኝ»

በሩን ስትበረግደው በማጮለቂያው ለማየት እንኳ ጊዜ አልነበራትም። ሶስት ሰዎች በሩ ከመከፈቱ በችኮላ ተንደርድረው ገቡ። ሌሎችን የሚያይ ዓይን አልነበራትም። ሚራዥን አንቃ ሳመችው። ሰውነቷ ሲንዘፈዘፍባት እየታወቃት ነበር። መርበትበቷን ለማስቆም ግን አቅም አጣች።

«ሚራዥ.....?» ለመናገር ብላ ከንፈሯ ሲንቀጠቀጥባት መልሳ ገጠመችው።

«ሜሮዳ ደህና ነሽ...?»

«አይደለሁም ደህና ነሽ አትበለኝ... ሚራዥ....ጎድተኸኛል። ቢያንስ እንኳን የሄድክበትን ብትነግረኝ ምናለ...?» ወደ ሶፋው በዝግታ ሄዶ ሲቀመጥ በዓይኗ እየተከተለችው።

«ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርኩ.....»

«እናም እኔን ልታየኝ ተመልሰህ መጣህልኝ። ....»

«አይደለም ሜሮዳ ሰው ላድን ነው የመጣሁት ሺዚዝን ላድን ነው የመጣሁት....» አለ ሚራዥ የግንባሩን ላብ እየጠረገ። ሊዋሻት አልፈለገም። «አስቸኳይ ጉዳይ ነው።»

«እሱ! ለእኔማ ምንም ግድ የለህም። አውቃለሁ ። ግን መልሼ ጨቅላ እሆናለሁ። ደደብ ነኝ» አለች ሜሮዳ በሽቃ። «እና ታዲያ ከእኔ ምን ፈለክ? አሁንም ተጠቅመህኝ ጥለኸኝ ልትሄድ.....»

«አንድትረጅን እንፈልጋለን። ህይወቱን እናድነው እባክሽ....»

«እኛ አንታይሽም አይደል.... » ዝንጊዳ እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት።

«ኦው ዶ/ር ዝንጊዳ ተለውጠህብኛል....» አለች። እጁን ጠበቅ አድርጋ ጨብጣ። «...ብዙ ተለውጠሃል።»

በኋላ ደግሞ አባ ገ/ንበሩ መልሰው አጽናኑት። «የሰው ልጅ ትልቁ ሀብቱ ጭንቀላቱ ነው። የምድራችን ትልቁ ሀብትም ጭንቅላት ነው። ስለዚህ አሁን ወዳለን ነገር ፊታችንን እናዙር። ከሰጠመው መርከብ ሃብት ይልቅ ያንተ ጭንቅላት ለሀገርህና ለወገንህ ይጠቅማል። ስሜታዊ ሆኜ ነገሩን አከረርኩት እንጂ። ስለዚህ ይህችን ሀገር በእውቀትህ አገልግላት» አሉት። «ይልቅ በዚህ ወቅት የምናከናውነው አንድ ታላቅ ተልእኮ ስላለ በዛ ላይ በመሳተፍ እርዳን። ከነገ ወዲያ ወደ አሜሪካ ትጓዛለህ።»

ሚራዥም ኢትዮጵያን ለሚጠቅም ማንኛውም ተልእኮ ራሱን ከመስጠት ወደ ኋላ እንደማይል ገለፀላቸው።

በታህሣሥ ወር መገባደጃ በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1998 ዓ.ም አንድ ሌሊት ሚራዥና ገ/ንጊዳ ኢንጂነር ጌራ በሚያበራት ዴር33 ልዩ ድምጽ አልባ አውሮፕላን ለልዩ ተልዕኮ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ ዋሻ በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ ወጥተው ወደ አሜሪካ በረሩ።

ዴር33 ጣና ውስጥ ሰርጓጅ መርከብ። አየር ላይ ልዩ አውሮፕላን። አሜሪካ ውስጥ የቤት አውቶሞቢል ሆና ለልዩው ተልዕኮ ተሰማራች።

፲፯

ኒውዮርክ፡አሜሪካ
1998 ዓ.ም
ታህሣስ 28.....ከምሽቱ 5:46

የቤቷ በር በሀይል ሲንኳኳ ቀና ብላ ግዳግዳው ላይ ትር...ትር.. ትር....የሚለውን የግድግዳ ሰዓት ተመለከተችው። 5:46። ደግሞ ተንኳ። ትንፋሽዋን ዋጥ አድርጋ ወደ ሽጉጧ እጇን ላከችው። ተሰልሶ በሩ ተሰለቀ።

«ማነው?» አለች ሜሮዳ ጉሮሮዋን ጠራርጋ ።

«እኔ ነኝ» አለ ጎርነን ያለ ደምፅ ከውጭ።

«ማን ልበል ?»

«ይህን ደምፅ አታውቂውም?» አለ ከውጭ የሚመጣው ድምፅ። «ሚራዥ ነኝ»

በሩን ስትበረግደው በማጮለቂያው ለማየት እንኳ ጊዜ አልነበራትም። ሶስት ሰዎች በሩ ከመከፈቱ በችኮላ ተንደርድረው ገቡ። ሌሎችን የሚያይ ዓይን አልነበራትም። ሚራዥን እንቃ ላመችው። ሰውነቷ ሲንዘፈዘፍባት እየታወቃት ነበር። መርበትበቷን ለማስቆም ግን አቅም አጣች።

«ሚራዥ.....?» ለመናገር ብላ ከንፈሯ ሲንቀጠቀጥባት መልሳ ገጠመችው።

«ሜሮዳ ደህና ነሽ...?»

«አይደለሁም ደህና ነሽ አትበለኝ... ሚራዥ....ጎድተኸኛል። ቢያንስ እንኳን የሄድክበትን ብትነግረኝ ምናለ...?» ወደ ሶፋው በዝግታ ሄዶ ሊቀመጥ በዓይኗ እየተከተለችው።

«ኢትዮጵያ ውስጥ ነበርኩ.....»

«እናም እኔን ልታየኝ ተመልሰህ መጣህልኝ። ....»

«አይደለም ሜሮዳ ሰው ላድን ነው የመጣሁት ሻጊዝን ላድን ነው የመጣሁት....» አለ ሚራዥ የግንባሩን ላብ እየጠረገ። ሊዋሻት አልፈለገም። «አስቸኳይ ጉዳይ ነው።»

«እኮ! ለእኔማ ምንም ግድ የለህም። አውቃለሁ ። ግን መልሼ ጨቅላ እሆናለሁ። ደደብ ነኝ» አለች ሜሮዳ በሽቃ። «እና ታዲያ ከእኔ ምን ፈለክ? አሁንም ተጠቅመህኝ ጥለኸኝ ልትሄድ.....»

«እንድትረጅን እንፈልጋለን። ህይወቱን እናድነው እባክሽ....»

«እኛ አንታይሽም አይደል.... » ገ/ንጊዳ እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት።

«አው ዶ/ር ገ/ንጊዳ ተለውጠህብኛል....» አለች። እጁን ጠበቅ አድርጋ ጨብጣ። «...ብዙ ተለውጠሃል።»

«ይህ ደግሞ ኢንጂነር ጌራ ይባላል።.....» ሶስተኛውን ሰው አስተዋወቃት። የደስደስ ያለው ወጣት ነው። ቢሆንም ለብዙዎች የምትመፀውተውን ደረት ፈገግታዋን ለገሰችው። የደረት ፈገግታዋን ምንጭ ምንነት ከሷ በቀር ማንም አያውቅም። ከተፈጥሮዋ እንዳልሆነ ግን ሁኔታዋ ያሳብቃል። ጌራ በልጅነት ልብዋ በሀሳብዋ ስላ ታፈቅረው የነበረውን ሰው መሰላት። ልብዋ ድንግጥ ሲል ተሰማት። በድንጋጤ አፍጣ ስትመለከተው ሁሉም ግራ ተጋቡ።

«ሜሮዳ.....?» አለችው እጆቻቸው እንደ ተጨባበጡ እጅዋን ወዝወዝ አድርጋ። «...ስ...ስለ ተዋወቅን ደስተኛ ነኝ።»

«ጌራ.....?» አላት ግራ ተጋብቶ እየተመለከታት።

«ምን ይምጣላችሁ..... ?» አለች ሜሮዳ መጠጦች ወደ ተደረደሩበት ኮሪደር እየተራመደች ።

«ለኔ ውሃ» አለ ሚራዥ።

«ለእኔም ውሃ» አለ ጣጎንጊዳም።

«ኢንጂነር ሻጊዝን ለማዳን ነው የመጣነው ነው የምትሉኝ ?» አለች ውሃ እየቀዳችላቸው። «አልሰማችሁም ማለት ነው !?»

«ምኑን !?» አለ ሚራዥ የብርጭቆውን ውሃ ጨልጦ።

«ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ የኢትዮጵያውያኑን የገና በዓል ከቤተሰቦቹ ጋር ለማክበር ለረጅም ጊዜ ከሚኖርበት የካሊፎርኒያ ግዛት ወደ ቴክሳስ ከተጓዘ በኋላ ቴክሳስ ውስጥ ከልጆቹ ጋር የቅርጫት ኳስ ሲጫወት በድንገት በመውደቁ ወደ ሰሜን አስቲን የህክምና ማእከል ለህክምና መግባቱን አልሰማችሁም!?» ጥያቄ እንዳያበዙባት ያሰበች ይመስላል። ሳታቋርጥ ተናግራ በረጅሙ ተነፈሰች።

«እሱንማ ሰምተናል። ብዙ ሰው የሰማውም ጉዳይ ነው። ከአንድ ሰአት በፊትም ሰሜን አስቲን የህክምን ማእከል ውስጥ ነበርን። ዶ/ር ጣጎንጊዳ በዚህ የህክምና ማዕከል ውስጥ ድሮ ይሠራ ስለነበር እንደገና ሥራውን ለመጀመር አመልክቶ ሊፈቀድለት አልቻለም። ስለዚህ የኢንጅነር ሻጊዝን ህክምና በጣጎንጊዳ እዝ ሥር ለማድረግ አንችልም። በዚህ ላይ የኢንጅነሩን የጭንቅላት ቀዶ ህክምና ለማድረግ የተመደበው ዶክተር ሉስ ካን የተባለ ነፍስ በላው ትውልደ አሰራኤላዊው ዶክተር ነው። ዶ/ር ሉስ ካንን አውቀዋለሁ። ሉሳንጀለስ ውስጥ አብረን ስንሰራ አውቀዋለሁ። እንዲያውም ለሻጊዝ የሚደረግለትን የልብ ቀዶ ጥገና በበላይነት ሲመራ የኖረ ቅጥረኛው ሰው እሱ ነው» ሚራዥ ዓይኖቹን አያኖቿ ላይ እንከባለላቸው።

«እና ከኔ የምትፈልጉት አሁን ምንድን ነው!?» ሜሮዳ የማፈግፈግ ስሜት እየተነበበባት ጮክ ብላ ተናገረች።

«አየሽ ሜሮዳ!?» ዶ/ር ጣጎንጊዳ ተቁነጥንጦ ጣልቃ ገባ። «ከሶስት አመት በፊት ሰሜን አስቲን የህክምና ማእከል ውስጥ ከዶ/ር ሉስ

ካን ጋር አብሮ የመስራት እድል አጋጥሞኝ ነበር። ዶ/ር ሉስ ካንን በደንብ አውቀዋለሁ። እሱ ቀዶ የሰፋው ታካሚ ቆሞ ሊሄድ አይቼ አላውቅም። ይህን የሚያደርገው ታዲያ ችሎታ ሰለሌለው እንዳይመስልሽ። እሱ ቀዶ የሚሰፋቸው ታካሚዎች የተመረጡና የተጠመዱ ሰዎችን ነው። ዶ/ር ሉስ ካን ማለት በእልፍ ቢላዋ የሚበላ ሰው ማለት ነው። ለሲ.አይ.ኤ ይሠራል፤ ከሞሳድ ጋር እንደሚሰራ ግን ሲ.አይ.ኤ እንኳ አያውቅም። ለዚህ በቂ መረጃ ልሰጥሽ እችላለሁ። የድምፅና የምስል ማስረጃ። ስለዚህ የሻጊዝን አንጉል አውጥቶ ሰውሻ ሊወረውረው እንደሚችል አትጠራጠሪ። ኢንጅነር ሻጊዝ ቴክሳስ ውስጥ ይህ ድራማ እንዲሰራበት የተወሰነበት ምክንያት ይህ ነው። ኢንጅነር ሻጊዝ ሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል ውስጥ በዶ/ር ሉስ ካን ታክሞ በህይወት ከወጣ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል።.....አስኪ ማን ይሙት እንዴት ቅርጫት ኳስ ለመዝናናት የሚጫወት ሰው ወድቆ ይህን ያህል ጉዳት ሊደርስበት ይችላል? በየትኛው ሀገር ነው እንዲህ አይነት ተውኔት የተፃፈው!? ምን ያክል ዘሉ ቢወድቅ ነው !?» ዶ/ር ጣጎንጊዳ አፍንጫው ላይ ቁርር ያሰውን ላብ ጠረግ ጠረግ ሲያደርግ ኢንጅነር ጌራ ብዕርና ወረቀት ከደረት ኪሱ አውጥቶ የሆነ ግራፍ ጫር ጫር አደረገ።

«ታያላችሁ?!» አለ ጌራ ግራፉን እያሳያቸው። «የመሬት የስበት ሃይል 9.8 አይደለም እንዴ እዚህ አገር?!.....ወይስ በሲ.አይ.ኤ ስሌት የአሜሪካ መሬት የስበት ኃይል 40 ገባ?! ...እስቲ አስቡት ኢንጂነሩ ምን ያክል ርቀት ወደ ላይ ዘሎ ወድቆ ነው ይህን ያክል ሊጉዳ የሚችለው?! ....ወይስ እንደ ኳሱ በቅርጫቱ ቀዳዳ ሾልኮ በጭንቅላቱ ተፈጥፍጦ ነው?! እሺ ሰምን እግሩ አልተሰበረም?! ዘሎ መሬት ላይ ሲወድቅ ምናልባት በእግሩ ወይም በእጁ መመርኮዙ አይቀርም። ለምን እጁ ተሰብረስ አላሉንም ?! ወይም ወገቡ.... » ራሱን ነቅንቆ ዝም አለ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሰሜን አውስቲን የህክምና ማዕከል የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ዶክተሮችና ነርሶች ይራወጣሉ።. የኢንጅነሩ የቅርብ ሰዎች በጭንቀት ይንቆራጠጣሉ፤ ያምጣሉ። የተዝለፈለፈውን ታካሚ የከበቡት ሐኪሞችና ነርሶች ይተረማመሳሉ። በጭንቀት ሊነጋገሩ አፍንጫቸው ላይ ያደረጉት የሽታ መከላከያ ቡንግ ቡንግ ይላል። ዶ/ር ሉስ ካን እየጮኸ ትዛዝ ያስተላልፋል። ከሁለት ወገን በደረሱት አስፈሪ ትዕዛዛት መሀል አዕምሮው ለምርጫ ተቸግሮ ይዋዥቃል።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

«ያም ሆነ ይህ አሁን ከዚህ በላይ የምናወራበት ጊዜ አይደለም። ፈጥነን ወደ ቴክሳስ መሄድ አለብን። ልንደርስለት

ይገባል። ያስከፍለውን መስዋዕትነት ከፍለን ማዳን አለብን» ዶ/ር ሚራዥ ተፈናጥሮ ተነሣ።

«እኔ ግን.....» አለች ሜሮዳ። «ከአሁን በኋላ ለማንም ለምንም ብዬ የምከፍለው መስዋዕትነት አይኖርም። ሰው ማድረግ የሚችለውንና ማድረግ የማይችለውን ለይቶ ማወቅ አለበት። ወደ ማትችሉት ውስብስብ ነገር ውስጥ እየገባችሁ ነው። ይህ አሜሪካ ነው። በሲ. አይ. ኤ ግዛት ውስጥ ነው ያላችሁት። ኢንጂነር ሻጊዝን ይቅርና ኢንጂነር ሻጊዝ ከተላጨው የፀጉር ዘለላ ላይ አንዲት ቅንጣት እንኳ ይዛችሁ መሄድ አትችሉም። አሜሪካ እንኳንስ ለናሳው እውቅ ሳይንቲስትና ለአለማችን ቁንጮ የህዋ ተመራማሪ ኢንጂነር ሻጊዝ ይቅርና ለአንድ ተራ ዜጋዋ እንኳ የማታነሣው በትር አይኖርም። ትሰሙኛላችሁ? አርፋችሁ ወደመጣችሁበት ተመለሱ። ይህን ነው ልመክራችሁም ልረዳችሁም የምችለው.....አሜሪካ ለዚህ ሰው ስትል ማንኛውንም ጦርነት ለማድረግ ዝግጁ ናት። ሶስተኛው የአለም ጦርነት ቢነሳ እንኳ ይህን ሳይንቲስት ከአሜሪካ እጅ ፈልቅቆ መውሰድ የሚችል አይኖርም። ጃፓን፣ ቻይና፣ በቅርቡ ወደ ህዋ መንኮራኩር ለማምጠቅ ደፋ ቀና የምትለው ህንድ፣ሰሜን ኮርያ፣ እስራኤል፣ ሩሲያ፣ ኢራን፣ ሶርያ.....እነዚህ ሀገራት ሁሉ ሲባዝኑለት ኑረው ያላገኙትን ሰው እናንተ ልትወስዱት? ምናልባት በገዳማዊው ሚራዥ በኩል መለኮት ጣልቃ ካልገባ ወይም ሞት ጠምቷችሁ ካልሆነ በቀር እንዲህ ማሰባችሁ በራሱ የምዕት ዓመቱ ምርጥ ቀልድ ነው። እኔ በበኩሌ በዚህ ሰውዬ ጉዳይ ውስጥ ብሞት አልገባም።እኔ ሜሮዳ ነኝ። የምችለውንና የማልችለውን ለይቼ አውቃለሁ።» አለች ወደ ፊታቸው አንገቷን ከደረታ መዛ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ዶ/ር ሉስ ካን እየተንቀጠቀጠ የመርፌውን ስሪንጅ እስክ ደንደሱ በኢንሱሊን ሞላው። «አ! አምላኬ .....» በጭንቀት ተንፍሶ። «ጲላጦስን እጁን ማነው ያስታጠበው? እኔ ልታጠብ ብል ግን ውሃ የሚጨምርልኝ የለም። እጄን ይቆርጡኛል እንጂ። አ! ያልታደልኩት ጲላጦስ!.....»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ሁሉም አቀርቅረው በሀዋታ ማስላሰል ጀመሩ። አማራጭ እንዳለ።.....

«አንቺ የምታደርጊልን እኮ .....ዶ/ር ሉስ ካንን ማጥመድ ብቻ እኮ ነው» አለ ሚራዥ እስክ ተቀመጡበት ጥግ ተንቀዋቀቆ ተቀምጦ። ለትንሽ ሴኮንዶች እይኖቹን ትኩር ብላ ተመለከተቸው። ናፍቆቱ ሲያርመጠምጣት የኖረችውን ያህል።

«እወድሃለሁ ሚራ!....» አለችው ፈጣሪ ከፅርሃ አርያም ከዋክብት መሀል ነቅሎ የተከለላት የሚመስሉ ዓይኖችዋን አስለምልማ።

«እኔም.....»እወድሻለሁ ሲላት ቃሉ ከከንፈሩ ሲደርስ መልሶ ዋጠው። አንድ ነገር ውስጡ እንዳለ ይሰማዋል። የውስጠኛው ውስጡን ማሸነፍ ግን አልቻለም። ውስተ ውሳጤውን።እንዲያውም እሷን ሲያይ ትዝ የምትለው ሲጻራ ናት። የሜሮዳን አካል አካሏ አድርጋ በሜሮዳ ቃል የምትናገረው ሲጻራ ትመስለዋለች።

«ስለማፈቅርህ ግን ከማትችለው ነገር ውስጥ ስትገባ ይዘኸኝ አትግባ። ላፈቅርህ እንጂ ልታፈቅረኝ የተፈጠርኩ አይመስለኝም በእርግጥ። ውለታ ውዬልህ እንድታፈቅረኝም አልፈልግም። ፍቅር የውለታ ምላሽ አይደለም። እሺ ይህንን ነገር ከሀገርህ አንዛር እንየው ብንል ኢንጂነር ሻጊዝ ለኢትዮጵያ የሚገባት ሰው አይደለም። እንዲያውም አንተን ብዬ እንጂ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ታስጠላኛለች። እንዴት እንዳደኩ እኔ ነኝ የማውቅ። የእናቴ ገላ ሰርካሽ ሽርሙጥና የተሸጠባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። አሁን ኢትዮጵያ ምኗ ይወደዳል ! ቁንጫዋ? ትኃኗ? እከኳ ? መሪዎቿ ? እስኪ ከምኗ ነው ፍቅር የያዛችሁ?.....»

«እከካም ያደረግናት እኛው ራሳችን እንጂ ኢትዮጵያ ለችጋርና ለጉስቁልና አልተፈጠረችም» ኢንጂነር ጌራ ጣልቃ ገባ።

«ያም ሆነ ይህ ያችን ቀፋፊ ሀገር የምወድበት ምክንያት የለኝም። ለኢትዮጵያ ብዬ ደግሞ የማንቆረቁረው ላብ የማፈሰው ደም የለኝም። ሚራዥ..... » አለች እስክ አፉ ተጠግታ።« በዚህ ጉዳይ ልተባበርህ ስላልቻልኩ ይቅርታህን እለምናለሁ። በዛ ላይ ደግሞ ዘግይታችኋል። በዚህ ሰአት በኢንጂነሩ ላይ ያፈጠጡ አንድ ሺህ አንድ ዓይኖች እንደሚኖሩ አትጠራጠሩ። ኬጂቢ፣ ሞሳድ፣ ሲ.አይ.ኤ፣ የኢትዮጵያ የደህንነት ሰዎች ወዘተ ወዘተ። ይህኔ በእነዚህ ኃይሎች የሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል እንደታጠረ መጠራጠር ቂልነት ነው። ኢትዮጵያን ሳይጨምር መላው ዓለም ይህን ሳይንቲስት በእጁ ለማስገባት በሚስገበገብበት ለአት መምጣታችሁ በራሱ ያረፈዳችሁ መሆኑን ሳይሆን የሚያሳየው የቀራችሁ መሆኑን ነው።»

«እንንቀሳቀስ።» አለ ዶ/ር ሚራዥ ቱግ ብሎ ተነስቶ። «ህ!...ኢትዮጵያ ውስጥ ችጋር ያልወቀጠው የለም። ሁላችንም በሰቆቃ ውስጥ ነው ያደግነው። እኔን የሚገርመኝ ....ኢትዮጵያ እንደ የውስጥና የውጭ ጠላቶቿ ብዛት እስክ አሁን ከምድረ ገፅ አለመጥፋቷ ነው። የኢትዮጵያ እስክ አሁን መቆዬት በራሱ ለዚህ ትውልድ ታላቅ ነገር ነው። እስኪ እስቲ ኢትዮጵያ እንደ እስራኤል ጠፍታ ቢሆን ኖሮ መልሰን እንመሠርታት ነበር? አሁን በዚህች

ብቻዋን በቆመች ሀገር ቂም ይያዛል ? ሜሮዳ ...አም እዚህ ...አሜርካ ውስጥ ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ አለ። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ለእያንዳንዱ ችግር ሌላ ችግር አለ። ግን ሁኔታዎች በዚህ አይቀጥሉም። ኢትዮጵያ የምታብበት ጊዜ ሩቅ እንዳይመስልሽ። ትናንት ደሀ ስንላት የነበረችው ህንድ ዛሬ የህዋ ምርምር ተቋም ሳይቀር ገንብታለች። አስቢ..... ሻጊዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ መቶ ሰው ቢያሰለጥን እንኳ የሚመጣውን ለውጥ ማሰብ ቀላል ነው! ኢትዮጵያ የአዕምሮ እንጂ የጥሬ ሀብት ደሀ አይደለችም። እመኝኝ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ሩቅ አይደለም። ከኢትዮጵያ የህዋ ምርምር ተቅዋም መንኮራኩሮች የሚመጥቁበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ይዘገይ ይሆናል እንጂ የማይሳካ ህልም የለም። ጉንዳኖች ማዕበል እንደ ቅቤ እዬናጣቸው ተያይዘው ወንዝ ይሻገራሉ።...ስለ ኢትዮጵያ አናቅማማም አናፈገፍግም። ለስከ መጨረሻዋ የደም ጠብታ.....» በሩን እስኪገነጠል በርግዶት ወጣ። ዶ/ር ጎንጊዳ እና ኢንጂነር ጌራም ተከትለውት ወጡ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ዶ/ር ሉስ ካን ጫን ጫን እየተነፈሰ ታካሚውን በብዥታ ውስጥ ተመለከተው። ጀሮው ላይ በተተከለለት ሬቂቅ ስልክ ውስጥ «ምን ትጠብቃለህ?!» ጎርናና ትዛዛዊ ቃና ያለው ድምፅ ታምቡሩን የቀደደው መሰለው። «አሁኑኑ!» በቀዶ ጥገናው ክፍል ውስጥ የተገጠመውን ስውር ካሜራ ቀና ብሎ ተመለከተው። እንደሚከታተሉት አውቆ በእሽታ ራሱን አወዛወዘ። መርፌውን ከጋወኑ ኪስ አውጥቶ በጭካኔና በቁርጠኝነት አልጋው ላይ ወደተኛው ታካሚ ተመለከተ። በኢንጂነሩ ዙሪያ ይተራመሱ የነበሩትን ነርሶችና የህክምና ቡድኑ አባላት እንዲወጡ ትእዛዝ በመስጠቱ ወጥተዋል። ትክክለኛው ሰአት ላይ መሆኑን ተገንዝቦ መርፌውን የያዘበት እጁ እየተንቀጠቀጠ ወደ ኢንጂነሩ ተራመደ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ከሜሮዳ ቤት ታዛ ወደ ቆመችው መኪና መስላ ደርሳ ልዩ ትንሽ አውሮፕላን ሊገቡ ሲሉ ልብሷን በፍጥነት ለባብሳ ተከተለቻቸው። ሶስቱም ዞረው አዩአት።

ዶ/ር ሚራዥ ፈገግ ሲል ውብ ነጫጭ ጥርሶቹ በመብራቱ ሀዳል ሲፈልቁ ታያት።

«ለአንተ ስል ገሃነምም ቢሆን እገባለሁ» አለችው ልዩ ወደ ሆነችው መኪና ተከትላቸው እየገባች። እጇን ስቦ ፈገግ እንዳለ ከጥጉ አስቀመጣት።ሙሉ ጥቁር ለብሳ እስከ ወኔዋ ወታደር መስላለች ።

ኢንጅነር ጌራ ልዩዋን ዴር33 ዴርቶጋዳ ልዩ ማሽን በፍጥነት እየነዳ የኒው ዮርክን ከተማ ጉዳና ጨርሰው ወደ

ገጠራማው ግዛት እንደገቡ ከመኪናዋ መሪ ጥግ የተገጠሙ ቁልፎችዋን ሲጫን መኪናዋ ከሆድ እቃዋ የወጡ ክንፎችዋን እንደ አሞራ ዘረጋጋች። ቀስ በቀስ ወደላይ ከፍ ከፍ ብላ እንደጀት አውሮፕላን አየሩን እየሰነጠቀች ሰማይ ላይ በከፍተኛ ፍጥነት ስትበር ሜሮዳ አይኗን አፍጥጣ አፏን እንደከፈተች ወደ ሚራዥ ዞረች።

«አሁንስ አታምኝም? ብትሰሚ ኑሮ አም አታምኝም። እያየሽም አለማመን መብትሽ ነው። ማንንም ለማሳመን አይደለም የምንሠራው። ጭንቅላትን ያህል አካል ይዘን የተፈጠርነው ውሃ እንድናሞቅበት አይደለም።»

«እኔ አላምንም ከሰማይ የወረደችላችሁ አውሮፕላን መሆን አለባት» አለች ሜሮዳ ተደንቃ።

«ይልቅ ቀበቶሽን ጠበቅ አድርጊ አውስቲን ልንደርስ ስለሆነ ከገጠራማው መንገድ ላይ ነው የምናርፍ»አለ ኢንጂነር ጌራ በከፍተኛ ፍጥነት እያበረረ። «ሁላችሁም ቀበቷችሁን በደንብ አጥብቁ»

ቀስ በቀስ መኪና መንገዱ ላይ ካሳረፋት በኋላ ሌሎች ቁልፎችን ሲጫን ክንፎቿ ወደ ውስጥ ገብተው ፍፁም መኪና መሰለች። የታርጋ ቁጥሮቿን መሪው ጥግ ባለ ቦርድ ላይ ያሉ ቁጥሮችን ነካክቶ ካስተካከለ በኋላ ወደ ሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል የሚያደርሰውን አውራ መንገድ አሳብሮ ገብቶ በፍጥነት ነዳት።

«በእውነት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የሰራችኋት!?...» አለች ሜሮዳ በአግራሞት አፏን እንደ ከፈተች።

«..ነው እንዳልልሽ ውሸት ይመስልሻል፤ አይደለም እንዳልልሽ እነውት ይመስልሻል» አላት ዶ/ር ሚራዥ እየሳቀ።

ጌራ የሚራዥ መልስ ገርሞት ወደነሱ ዙሮ ሲስቅ ሜሮዳ ካያኖቹ ጋር ተጋጨች። ከውስጡ የፈለቀ አንዳች የማታውቀው ወሳፈን ልብዋን ሲጠብሳት ታወቃት። «አይደረግም!» አለች በውስጥዋ። «ምን አይነት ስስ ልብ ነው ያለኝ በኔ ሞት? ለስንቱ ደንግጬ እዘልቀዋለሁ..... ደሞ እንዴት ያምራል! በርግጥም ይህ ሰው በልጅነት ልቤ ለፍቅር እስለው የነበረው ሰው ነው.....» የልብ ምትዋን ያረግብላት ይመስል የሚራዥን ክንድ ጥብቅ አርጋ ያዘችው። ከጌራ ማጅራት ላይ አይንዋን ሳትነቅል።

፲፮

ቴክሳስ ፣ አሜሪካ
9፡05
ሰሜን አውስቲን የህክምና ማእከል

ታዋቂው የሰሜን አውስቲን የህክምና ማዕከል ግርግር በዝቶበታል። ጆሮአቸውን ቢቆርጧቸው የማይሰሙ የሚመስሉት ነጫጭ ጋወን የለበሱ ዶክተሮች ይራወጣሉ። የተደገመባቸው የሚመስሉት ነርሶችም ይቅበዘበዛሉ። አያሌ የቡድን ረዳቶችና የቴክኒክ ሰራተኞች እንደ ነሐሴ አሸን ብር ብር ሲሉ ርዕደ መሬት የተከሰተ ይመስላል። የቀዶ ጥገና ክፍሎች በዶክተሮችና በነርሶች ተጨናንቀዋል። የድንገተኛ ክፍሎችም በሚያጣጥሩ በሽተኞች የስቃይ ድምጾች ምድራዊ ሲኦል መስለዋል።

ከዶክተሮች መልበሻ ክፍል ነጭ ጋወን ለብሶ ከዋናው መተላለፊያ በስተቀኝ በኩል ያለውን የቀዶ ጥ፣ና ክፍል በርግዶት ሲገባ ዶ/ር ሉስ ካን በቅጽበት ፊቱን በሩን በርግዶ ወደ ገባው ሰው አዙሮ አፈጠጠበት። «አው! ....ዶክተር ጐንጊዳ ....በስንት ጊዜህ ተመልሰህ መጣህ? ከረጅም ጊዜ በኋላ.....» አለ ዶ/ር ሉስ ካን ጆሮ በሚበሳ ቀጭን ድምጽ። ቀጭን ድምጹ ፈጣንም ስለሆነ እንግሊዝኛው ከማሽን የወጣ እንጂ ከሰብአዊ ፍጡር ልሳን የወጣ አይመስልም። አፍንጫው ላይ ያደረገውን የሽታ መከላከያ አረንጓዴ ጓንት ባጠለቀ እጁ ወደ ላይ እያስጠጋ «እንኪን ደህና መጣህ ለማንኛውም፡፡» መርፌውን በግድግዳው በኩል ሸፍኖ ወደ ኪሱ ከተተው።

«እንኪን ደህና ቆየኽኝ ዶክተር ሉስ ካን፡፡» አለ ዶ/ር ጐንጊዳ ጠረጴዛው ላይ ወደተጋደመውና በቀዶ ጥገና መሣሪያዎች ገመድ ጭንቅላቱ ላይ ወደተተበተቡበት ጥቁር ታካሚ እየተጠጋ። «ታካሚህ እንዴት ነው በጣም ተጐድቷል?»

«በጣም እንጂ በጣም ነው የተጐዳው። ከቀዶ ጥገናውም በኋላ ወደ ጭንቅላቱ የሚፈሰውን ደም ማስቆም አልቻልንም። ይህን ቀዶ ጥገና ለማድረግ በአፕሬሽኑ የተሰማራውን የህክምና ቡድን እንደመምራቴና በሪፖርቱም ላይ እንደገለጽኩት ወደ ጭንቅላቱ የሚፈሰውን ደም ማቆም አልቻልንም» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በብሽቀት ተንፍሶ። ጆሮው ላይ የተተከለለትን ረቂቅ ስልክ ለጊዜው ግንኙነቱ እንዲቋረጥ አድርጎ የመከታተያ ካሜራውንም በፍጥነት ዘጋው።

ጐንጊዳ ድምጹን ዝቅ አድርጐ «ይህን አፕሬሽን ለምን እኔ አልጨርሰውም?» አለው።

«ምን!?» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በመጠየፍ እየተመለከተው።

«በደቂቃዎች ውስጥ የታካሚህን ደም ማስቆም እችላለሁ» አሰው የበለጠ ተጠግቶ። «እጅን ላውስህ።»

«....እያልከኝ ያለኸው ከአንተ የበለጠ ችሎታ አለኝ ነው?!» የዶ/ር ሉስ ካን ነጭ ቆዳ በቅፅበት ቀላ።

«.....አይደለም። ላግዝህ ማለት ችሎታ የለህም ማለት ነው? ....አብረን ሰርተን አናውቅም እንዴ ዶ/ር ሉስካን? .....ተጋግዘን አናውቅም እንዴት?.....ይህን ነገር እንዴት በሌላ ትመነዝረዋለህ...? እኔ ያልከህ ሌላ አንተ ያልከኝ ሌላ። ምናልባት ለአንተ ያልታየህ ለእኔ ሊታየኝ ይችላል። እያከምከው ያለኸው ሰው ደግሞ በጣም አስፈላጊ ሰው ነው። የዓለማችን ምርጡ ሳይንቲስት።»

«የማያስፈልግ ሰው አለ እንዴ ዶ/ር ጐንጊዳ?»

«የማያስፈልግ ሰው የለም። አስፈላጊ ሰው ነው ማለት አስፈላጊ ሰው የለም ማለት ነው ዶ/ር ሉስ ካን?»

«አሁን ሥራዬን ልስራበት ያለ ምድብህ መጥተህ አትበጥብጠኝ!» ረጅም አፍንጫው እስኪንቀጠቀጥ ተቆጣ ዶ/ር ሉስ ካን። «አለበለዚያ ለህክምና ማእከሉ ፕሬዝዳንት ለማመልከት እያስገደድከኝ ነው። ውጣልኝ አሁን። ከባድ ጥፋት እያጠፋህ ነው። ውጣልኝ። ለፕሬዝዳንቱ ከማመልከቴ በፊት ውጣልኝ።....ውጣልኝ» አለ ሉስ ካን አመልካች ጣቱን ወደ በሩ ቀስሮ እያንዳንዱን ቃላት አጥብቆ እየጠራ። ‹ዲቃላ!› አለ በውስጡ

«እሺ እወጣለሁ። ግን ስለማደረገው ነገር የማላውቅ እንዳይመስልህ። don't forget what we have done before.... ታስታውሳለህ ሉስ....» አለ ዶ/ር ጐንጊዳ ክፍሉ ውስጥ አቀርቅሮ እየተንጐራደደ። «ከዘጠኝ ታካሚዎች ዘጠኝ ጉበት፣ ከሌላ ሶስት ሌላ ታካሚዎች ደግሞ ሶሶት ኩላሊት፣ እዚሁ የህክምና ማዕከል ውስጥ ከሞተ ከአንድ ታዋቂ ሴናተር ደግሞ ልብ አውጥተህ በመሸጥህ የእነዚህ ሁሉ ሰዎች ደም በእጅህ እንዳለ አታውቅም?»

«ምንድን ነው የምታወራው?» ዶ/ር ሉስ ካን ደመ ሞቀ።

«የእነዚህ ሰዎች ደም በእጅህ እንዳለ ሁሉ ይህንና ሌሎች ዘግናኝ ወንጀሎችን ስትፈጽም በስውር የተቀረጸው ቪዲዮ ካሴት ደግሞ በእኔ እጅ ነው። አሁን ወጥቼ መሄድ እችላለሁ።..... »ዶ/ር ጐንጊዳ ወደ በሩ ሲራመድ የሜርዳ እቅድ እንዳሰራ እየጸለዩ ነበር።

«ቆይ!» አለ ሉስ። «መነጋገር ሳይናገብን አይቀርም።»

«ከዚህ አፕሬሽን ጀርባ ያለውን ሻጥር በሙሉ አውቀዋለሁ። ሞሳድም በለው ሲ.አይ.ኤ የግል ገመናህን ሊሸፍኑልህ አይችሉም። ምናልባት እኔን እዚህ ብታስቀረኝ እንኳ ገመናህን ሊያጋልጥ የሚችል አጋር እውጭ አቁሜ መምጣቴን ልታውቅ ይገባል። መደራደር ካለብን ግን ከዚህም በላይ ጥሩ ወደ ሆነ ነገር

የተበላሸውን ሁሉ ልንቀይረው እንችላለን። ከሞሳድም ሆነ ከሲ.አይ.ኤ ልታገኘው የምትችለው ዋነኛው ነገር ገንዘብ ነው። እኔ እስከ ማውቀው። ገንዘብ ከሆነ ደግሞ መደራደር እንችላለን።» ዶ/ር ጣንጊዳ ትከሻውን ወደላይ ንጦ ዝም አለ።

«እሺ እንደራደር።» አለ ዶ/ር ሉስ ካን የተሸናፊነት እስትንፋስ ተንፍሶ።

«ከእኔ ጋር አይደለም የምትደራደር። ከሴቶች ቁጥር3 ሽንት ቤት ውስጥ ሁለት ሰዎች ይጠብቁሀል በፍጥነት ደርሰህ ተመለስ። እዛ ስትደርስም ‹ዴር› የሚል ድምጽ አሰማ። ይከፍቱልሃል።

ዶ/ር ሉስካን እየተጣደፈ ቁጥር3 የሴቶች ሽንት ቤት በር ላይ እንደደረሰ ‹ዴር› አለ ከማሽን የወጣ በሚመስል ድምፅ በለሆሳስ። የሽንት ቤቱ በር ገርበብ ብሎ ተከፈተ። ነጫጭ ጋዋን የለበሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቆመዋል። የሴቶች ሽንት ቤት ውስጥ። ሜሮዳ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጧን አንገቱ ሥር ስትወሽቅ ሚራዥ ደግሞ የሽንት ቤቱን በር ጠርቅሞ ከውስጥ ዘጋው። ዶ/ር ሉስ ሊናገር አፉን ሲከፍት «እሱሱ.....» አለች ሜሮዳ ጣቷን ከንፈሩ ላይ ጭና። «የመደራደሪያ ሀሳቡ በእኛ ብቻ ይቀርባል። ትስማማለህ? ከሥሩ ሽጉጥ የተደቀነበት አንገቱን በመነቅነቅ ተስማማ። በእጁ የያዘውን ኢንሱሊን እስከሲሪንጁ ደንደስ የማገ መርፌ እንዲጥል አስገደደችው። ረጅም አፍንጫውን ወጥሮ በሳንባው ሙሉ የሳበውን ትንፋሹን ለቆ መርፌውን ጣለው።

«አንደኛ!.....ኢንጂነሩን በህይወት ታስረክበናለህ። ሁለተኛ!....የመሞቱ ዜና ተነግሮ ማንኛውም አካል መሞቱን እስኪያረጋግጥ ይህን መርፌ ትወገዋለህ።» ስሪንጁ ባረገጉዋዴ ፈሳሽ የተሞላ መርፌ እየሰጠችው። «በዚህ መርፌ ውስጥ ያለው ውህድ ከደመ· ጋር ከተቀላቀለ ከሃያ ሴኮንዶች በሁዋላ ሰውነቱ እጅግ በጣም ዝቅተኛ በሆነ ሃይል ውስጥ ሆኖ በህይወት መኖሩን ማንም በማይገነዘበው ሁኔታ በህይወትና በሞት መካከል ይቆያል። ፀሁዋላ በድብቅ በምናስገባው ምስጢራዊ የሬሣ ሣጥን ውስጥ ካስገባኸው በኋላ የሬሣ ሣጥኑ ውስጥ ያለውን የአክስጂን መስጫ መሣሪያ ትገጥምለታለህ።ውስጡ የሚቀመጥልህን ግሉኮስም ትተክልለታለህ። እንደገና ወደ ህይወቱ ሲመለስ ሰውነቱ አስፈላጊውን ሃይል ማግኘት አለበት። ከዛም ሲነቃ እንዳይንቀሳቀስ ሳጥኑ ውስጥ በምታገኛቸው ቀበቶዎች ከሬሣ ሳጥኑ ጋር በደንብ ታስረዋለህ። ሶስተኛ!.... ይህን ምስጢር ማንም ማወቅ የለበትም። አራተኛ!..... የሬሳ ሳጥኑ ረቂቅ ካሜራ የተገጠመለት ስለሆነ ከውስጥም ከውጭም የምታደርገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ቀጥታ እንከታተልሃለን። አምስተኛ!....ከሌላ አካልም ሆነ ከቤተ ሰቦቹ የሚመጣ ማንኛውም የሬሳ ሳጥን ውስጥ አስከራኑን እንዳታስቀምጥ መጠንቀቅ አለብህ። ስድስተኛ!....

ሥርአተ ቀብሩ ተፈጽሞ መካነ መቃብሩ ባዶ ከሆነ በኋላ ከዚህ የህክምና ማዕከል በር ላይ ትጠብቀናለህ። የሰራኸውን የምድራችን ዘግናኝ ወንጀልህን የሚያጋልጠውን ፊልምና አርባ ሚሊዮን ዶላር የያዘ ቦርሣ በእጅህ እናስረክብሃለን። ቤትህ ስር የተጠመደው ፈንጅም ይከሽፋል። ትስማማለህ?»

«ተስማምቻለሁ። ፊልሙ ግን ዋናውም ሆነ ኮፒው በሙሉ በእጄ እንዲገባ አፈልጋለሁ።.....አባካችሁ ቤተሰቦቼን ....ቦንቡ...እ...እንዳይፈነዳ....» ሉስ ትንፋሹ ፈጠነበት።

«እሱን ለእኛ ተወው። ተውኔቱን በደንብ መጫወት አለብህ። ሆሊውድም ቢሆን እጁን ዘርግቶ ይቀበልሀል። አሁን ሥራህን መጀመር ትችላለህ።» በአገጯ የሚወጣበትን በር አመለከተችው። ዶ/ር ሉስ ካን በፍጥነት ወደ ቀዳ ጥገና ክፍሉ ተንቦጀቦጀ።

«በደንብ እየኝ!» አለችው ሜሮዳ ወደ ሚራዥር ዞራ ካን ከሄደ በኋላ። «እኔን የጉደለኝ ፍቅር ነው። ብልጠትና ጥበብ አይደለም። የፈጠርነው ዘዴ እንደሚሰራ አትጠራጠር።»

«እኔ ባንቺ ተጠራጥሬ አላውቅም። የመረጥኪትም ትክክለኛዋን ሰው ነው» አላት ሚራዥ ኮርቶባት።

«ለፍቅር አልመረጥከኝማ። ለዘዴ ብቻ። በልጅነትህ ካደክበት ገዳም በተማርከው ጥበብ ምናምኑን አስነካሃኝ ልበል? ለምን የመስተፋቅር አስደግመህብኝ እንደሁ ቁርጡን አትነግረኝም?»

«ሲሉ ሰምተሻል!» አላት። «ለዛሬ ዘመን ሴት ደግሞ የመስተፋቅር ማስደገም ያስፈልጋል? ህ!....የዛሬ ጊዜ ሴቶች ሳይደገምባቸው የተደገመባቸው ናቸው። የመስተፋቅር ማስደገም አያስፈልግም። መስተፋቅር የሚሉት እውነት ከሆነ እሱን ለማሰራት የዘመኑን ሴቶች የሚቀድማቸው ባልተገኘ። እናንተን ነው መጠርጠርስ። በእውነት ዛሬ የምስተው ሳት ቢኖረኝ ስቁም አይወጣልኝ ነበር»

«እሺ ባይሆን አንድ ጊዜ ጥብቅ አርገህ ሳመኝ» የሜሮዳ ዓይኖች ወደ ሰማዩ ሰማያት ተሸነጠጡ።ተስለምልማ ጥቁሩን የዓይኗን ብሌን ወደሸፋሳ ሳገችው። ሽጉጧን የያዙት እጆቿ አንገቱን ዞሩት። የልቧ ነጋሪት ከልቡ ነጋሪት አኩል ተሳለመ። አፏን ከፈተች። በሩ ከውጭ ተንኳኳ።

«ዴር!» አለ ጣንጊዳ ከውጭ በለሆሳስ። «እንንቀሳቀስ።»

፲፬

ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ የጭንቅላት ቀዶ ጥገና በተደረገለት በአራተኛው ቀን ዓለምን ያነጋገረው ዜና ዕረፍቱ በቅፅበት ተዳረሰ። የኢንጂነሩን ሞት በሰሙ በአሜሪካና በመላው ዓለም ባሉ የቴክኖሎጂ ማህበረሰቦች ላይ ታላቅ የሀዘን ጥላ ወደቀ። ከቤተዘመዶቹ በላይ በእሱ ላይ ተስፋ ጥለው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሀዘናቸውን መቆጣጠር አቃታቸው። በመላው ኢትዮጵያ በታወቀበትና ስሙ ከምንጊዜውም በላይ በተነሣበት ወቅት ‹ሞተ› የሚለው ዜና ሲሰማ ሁሉም በድንጋጤ ተዋጠ።እንደ ጠዋት ጤዛ ወዲያው አይተውት ወዲያው ገና የመጀመሪያው ፀሐይ ሳይወጣ ተነነባቸው።

ከመቼውም ጊዜ በላይ ፊቱን ወደ አፍሪካ በተሰይም የዓለም ጭራ ወደምትባል ሀገሩ ባዞረበት ወቅት በተሰይም ‹‹አፍሪካውያን ተገቢውን ድርሻ እንዲያገኙ ማገዝ የረዥም ጊዜ ህልሜ ነው። ተገቢው ቴክኖሎጂ ያለመኖር የታዳጊ አገሮች በተሰይም የአፍሪካ አገሮች ዋንኛ ችግር ነው። የአገር ሀብትና እምቅ ብሔራዊ ንብረት ዓለም በደረሰበት ሳይንሳዊ ጥበብ አማካኝነት ለህዝባችን ጥቅም ማዋል ይቻላል። እውቀቱ፣ ዝግጅቱና ፍላጐቱ በእኔ በኩል አለ። እስከ አሁን በአሜሪካና በአውሮፓ በግንባር ቀደም የህዋ ሳይንቲስት በመሆን አያሌ ውጤት አምጥቻለሁ። በእኔ እምነት የጠፈር ቴክኖሎጂ ለፈጣን ልማት እድግ እንደሚጠቅም በአሜርካና በአውሮፓ ለማሳየት የቻልኩትን ያህል በኢትዮጵያም ለማሳየት ቆርጬ ተነስቻለሁ። የተጠና...አስፈላጊና የተመረጠ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የምንችልበትን ዝግጅት አጠናቀናል›› በማለት ለኢትዮጵያ ሁሉ ነገሩን አሳልፎ በሰጠበት ወቅት የመሞቱ ዜና መሰማቱ ለአንዳንዶች በለቅሶ እንኳ ሊወጣላቸው የማይችል ስቆቃ ሆኖባቸዋል።

አንዳንዶች ደግሞ ብዙ ኃይሎችን ተጠያቂ እንዲያደርጉ ሁኔታው ጋብዞአቸዋል። ‹‹ለኢንጅነሩ ምስጢራዊ ግድያ ብዙ ሀገሮችና ኃይሎች ተጠያቂ ናቸው›› ከመጠርጠር ባለፈ ግን የተደረገ ነገር አልነበረም። መሞቱን ያላመኑ ብዙዎች ሲኖሩ ‹‹የቅርጫት ኳስ ሲጫወት ወድቆ የጭንቅላት ቀዶ ጥገና ተደርጕለት ደሙን ማስቆም ስላልተቻለ ሞተ›› የሚለውን ዜና ‹‹ኮልካሻና ፈዝ የተሞላበት ምክንያት ነው›› ይላሉ።

በጨረር እንደተገደለ የሚጠረጥሩ እንዳሉ ሁሉ የኢትዮጵያን መንግስት ተጠያቂ ያደረጉም አያሌዎች ናቸው።

አንዳንዶች በድብቅ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰራጨውንና

«እኛን አንድ ነገር ቢያድናቀፈን እንኩዋ እናንተ ሂዳችሁ ሀገራችሁን ለውጡ» የሚል ቃል ያለበትን የኢንጂነሩን ንግግር የያዘውን ቪሲዲ በማጣቀስ ኢንጂነሩ እንደሚሞት አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ወይም አልሞተም ይላሉ።

የኢንጂነሩን የሞት ወሬ ተከትሎ በልዩ ልዩ ቋንቋ የታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ትኩስ ትኩስ ዘገባዎችን ይዘው ወጡ። የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሃንም የኢንጂነሩን ዜና እረፍት በመላው አለም በቅጽበት አዳረሱት። ብዙ ህዝቦችም በአንዳንድ ድህረ ገጾችና የኢንተርኔት ጽሑፎች ዜናውን ለማጣራት ባከኑ። ግን አንዳችም ተጨባጭ ነገር ሊያገኙ አልቻሉም።

«Engineer shagiz, who worked for NASA as chief of spacecraft and satellite systems engineer and scientist, died at 1:00 am on January 13, 2006 four days after he underwent surgery at north Austin medical center in Austin, Texas.

The scientist, a long time resident of California, traveled to Austin to visit with his extended family over the Ethiopian Christmas holiday on January 7, 2006.

He was having fun with his children when he fell and hurt himself. According to family and friends who were by his side when he passed away, a team of neurosurgeons were unable to stop the internal brain hemorrhage.» በማለት ሰፊ ዘገባ ያቀረበው «the African Tribune» ነው።

«Engineer shagiz passed away at the age of 58 on 13 January 2006 in the United States. Apart from his prestigious status as an aerospace scientist, he was also widely known for his efforts to bring about political change in Ethiopia. He publicly denounced the regime in Ethiopia and its atrocious actions and policies. Even though he was ambitious about using his knowledge, experience and high status to help his homeland Ethiopia, he repeatedly said he was not made welcome by the regime. And in 2002, he founded the political party. The Ethiopian National united front to help over throw the unpopular regime and to bring about a stable and democratic political system. He was a passionate believer in Ethiopia who always wanted to utilize his expertise to change things for the better for the average Ethiopia. Despite his sudden and early departure, he

will continue to be a remarkable role model for many generation of Ethiopia As well as for many youths of the world. The tales of his achievements in the field of aerospace will inspire many would be Ethiopia scientists.» ሲል በሳይንቲስቱ ህይወት ዙሪያ ሰፊ ዘገባ ያስነበበው «the scientist» የሚባለውና ሳይንሣዊ ዘገባዎችንና የሳይንቲስቶችን ህይወት በመዳሰስ የሚያቀርበው ታዋቂው ጋዜጣ ነው።

«The former NASA chief of spacecraft and satellite systems engineer and Ethiopian patriot, scientist shagiz died an hour past midnight on January 13, 2006 four days after he under went surgery at north Austin Medical center in Austin, Texas.

In 1978, he invented two a aerospace mechanisms and patented under NASA's new technologies programs while working with other NASA scientists and the Apollo astronaut BUZ Aldrin, second man to walk on the Moon. In several advanced technology application research effort on mars missions, shagiz managed martin Marietta's research team and produced outstanding scientific results.

Shagiz joined Rockwell informational (builder of the space shuttle orbiter), space systems Division in 1986. He becomes a principal investigator and chief research engineer for several advanced space systems projects at Rockwell. He had a long dispute with his former American Jewish wife because of his children. He over saw the development of advanced technologies for kinetic energy weapons systems. He was also a program manager for a lunar mars-rover research and development effort in support of NASA's future exploration missions.

He then turned his attention to Africa and his beloved Ethiopia hoping to introduce and advance technology based development. Ethiopia as well as the whole world has missed one great man on earth. He will be truly missed.» የሚለውን የጠዋቱን ጋዜጣ ሥርአተ ቀብሩ ከሚፈፀምበት መካነ መቃብር ውጭ መኪናው ውስጥ ሆኖ እያነበበ እያለ ፈገግ አለ ዶ/ር ሉስ ካን። የጋዜጦችና የመገናኛ ብዙሃኑ ዘገባ እንኒንስ ለዚህ ምስጢር ባዳ የሆነውን ህገብ እሱን እንኒን መሞቱን ሊያሳምነው ዳር ዳር ብሎ ነበር። ከሀገሩ ከኢትዮጵያ

የመንግስት ብዙሀን መገናኛ ጣቢያዎች በቀር የመላው ዓለም የመገናኛ አውታሮች ዜና ዕረፍቱን በፍጥነት አራገቡት። የሞቱን ዜና በኢንተርኔት የሰሙ ‹ምናለ ሞቱን እንኳ ባይሆን ቢያረዱን....ጠላታችን የሚሉትን ሰው ሞቱን ማርዳት እንዲህ ይከብዳል?.....› ሲሉ በኢትዮጵያ ሚዲያ ላይ ብዙዎች አጉረመረሙ።

ዶ/ር ሉስ ካን ከሞሳድ ማዕከላዊ ቢሮ ጋር ግንኙነት የፈጠረውና ኢንጂነሩ በምስጢራዊው የሬሣ ሣጥን ውስጥ በህይወት የመኖሩን ምስጢር በማቀበል ከሥርዓተ ቀብሩ በኋላ በአስደናቂው የሬሣ ሣጥን ውስጥ ረቂቅ የአክስጅን መስጫ መሣሪያዎችና ሕይወቱን የሚመግብ ግሉኮስ የተተከለለትን ሳይንቲስት አስከ ሳጥኑ ለማስረከብ መደራደር የጀመረው የኢንጂነር ሻጊዝ የቀብር ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ነበር።

ሉስ ካን መኪናው ውስጥ ከመካነ መቃብሩ ፊት ለፊት ተቀምጦ የሚያነበውን ጋዜጣ ካስቀመጠ በኋላ ላፕቶፕ ኮምፒውተሩን ጭኑ ላይ አድርጉ ከሬሣ ሣጥኑ ውስጥ እንዲያስቀምጥ ከሞሳድ የተላከለትን ረቂቅ ካሜራ ከኮምፒውተሩ ጋር ግንኙነት መፍጠሩን ለማረጋገጥ ቁልፎችን ተጫናቸው።

«አዎ።....» አለ ዶ/ር ሉስ ካን በኮምፒውተሩ ስክሪን ላይ የሬሳ ሳጥኑ ያለበትን አካባቢ የሚጠቁመው ቀዩ ጠቋሚ መብራት ሲበራ። ቀጥሎ ደግሞ የውስጥኛው ካሜራ ከውስጥ የተኛውን አስከሬን ቁልጭ አድረጎ አሳየው። ምስጢራዊው የሬሳ ሳጥን በረቀቁ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ተሞልቷል። ከአስከሬኑ አፍንጫ ላይ የአክስጅን መስጫ መሳሪያ ተተክሎለታል።በክንዶቹ ላይም የግሉኮስና የማይክሮ ፍሉድ ምግብ መስጫ መሳሪያዎች ተገጥመውለታል። በድኑም እንዳይንቀሳቀስ ተደርጎ ከሬሳ ሳጥኑ ውስጣዊ ክፍል ጋር በቀያይ ቀበቶዎች ተጠፋፍሯል። ጭንቅላቱ ከብረት የተሠራቆብ ተገጥሞለታል። ድንገታዊ ተኩስ ቢከፈት በህይወት ያለውን አስከሬን ከጥፋት ለማዳንም የሬሳ ሳጥኑ ውስጣዊ ክፍል ጥይት በማይበሳው ብረት ተሸብኗል።

በሬሣ ሳጥኑ ውስጥ በረቀቁ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የታበተውን ህያው አስከሬን ሲመለከት ፈገግ አለ ዶ/ር ሉስ ካን ። «የህይወት ታሪክህን እያዳምጥክ ይሆናል ይዜኔ። ልብ ወለድ በሚመስለው የህይወት ታሪክህ እንደተመሰጥክ ተስፋ አደርጋለሁ። በሬሣ ሣጥንህ ውስጥ ሆነህ ማን በደንብ እንደሚያለቅስልህና ማን እንደማያለቅስልህ ለመለየት የቻልክ ብቸኛው የዓለማችን ሰው ሆይ ለእኔም ኪሴን የሚያወፍር ገንዘብ ባለቤት ስላደረከኝ

አመሰግናለሁ።....እንዴት ነው የቀድሞዋ እስራኤል አሜርካዊት ሚስትህ ስታለቅስ ያምርባታል? ተከራክራ የወለደችብህ ሶስቱ የምትወዳቸው ልጆችህስ?.....ባለቀ ሰዓት ሲላይ ስለሆንክኝ አመሰግናለሁ። ከአንተዎቹ የሐበሻ ሰዎች አርባ ሚሊዮን ዶላር ልቀበል የቀረኝ ሥርዓተ ቀብርህ እስኪፈፀም መታገሥ ብቻ ነው። ከሞላድ ደግሞ ሃምሳ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ዛሬ ማታ ኪሴ ውስጥ ይገባል። ቪቫ!....አመሰግናለሁ አንተ ህያው አስክሬን! ....ነፍስ ይማር። ከአሁን በኋላ ማንንም በሽተኛ ቀዶ መስፋት አከተመ» እያለ ባለሆሳስ ብቻውን ኮምፒውተሩ ላይ እንዳፈጠጠ የመኪናው የመስታወት በር ተንሿሿ። ብንን ብሎ ሲያይ የሞላድ መታወቂያ እያሳየችው አንዲት ጠይም ሴት ጥቁር ሳምሶናይት ከፍ አድርጋ አሳየችው።

ከሞላድ ማዕከላዊ ቢሮ ከእሷ ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ተነግሮታል። እንዲያገኛት የተነገረችው ሴት ፎቶ ግራፍና ስም በግል የኢሜል አድራሻው ስለተላከለት ትክክለኛዋ ሴት ለመሆኗ መታወቂያዋንና ፊቷን የመኪናውን በር ከመክፈቱ በፊት አነጻጸረው። መታወቂያዋ ላይ ያለው ስም ‹‹ሲዳራ ፊንሐስ›› ይላል። መታዋቂያዋ ላይ የሞላድ ኤጀንት መሆኗን አመሳከረ። ‹እሷ ናት› ብሎ በውስጡ የመኪናውን መስኮት ከፈተላት። ምንም ቃል ሳትተነፍስ በገንዘብ የተምላውን ሳምሶናይት ሰጠችው።

ሳምሶናይቱን በፍጥነት ሊከፍት ለመቁጠር የሚያታክት «IN GOD WE TRUST» የሚል ጽሑፍ ያለበት የአሜሪካ ዶላር ታስሮ ታስሮ ተቀምጠለት አየ። «we trust in gold too.» ብሎ ፈገግ አለ። «በእግዚአብሔርም እናምናለን፤ በወርቅም እናምናለን።»

በስምምነቱ መሠረት ከሬሳ ሳጥኑ ጋር የተያያዘውንና የረቂቁ የሬሣ ሳጥን ውስጣዊ ክፍል ካሜራ መቆጣጠሪያ የሆነውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ሰጥታት መኪናውን አስነስቶ በፍጥነት ከአካባቢው ሲለወር ሥርዓተ ቀብሩን የፈፀሙት ሀዘንተኞች ኢንጂነራቸውን ቀብረው እየተመለሱ ነበር።

ዶ/ር ሉስ ካን ከነ ዶ/ር ሚራዥ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ሰሜን አስቲን የህክምና ማዕከል በር ላይ ደርሶ እስከ ምሽት መኪናው ውስጥ ሆኖ ቢጠብቅም ብቅ ያለለት ማንም አልነበረም።

«እነዚህ ከሀዲዎች ተጫወቱብኝ ማለት ነው።...ግዴለም እኔም እጫወትባቸዋለሁ» እያለ ሲያጉረመርም ጥቁር አውቶሞቢል

መኪና እየፈጠነች መጣች። ሜሮዳ ወርዳ ትልቅ ቦርሳ ሰጥታው ተመልሳ በጥቁሯ አቶሞቢል ከአካባቢው አልም አለች።

ቦርሳውን በፍጥነት ከፍቶ ሲያይ በውስጡ ከአንዲት ብጣሽ ወረቀት በቀር ያገኘው ሰባራ ሳንቲም አልነበረም። «ዘግናኙን ወንጀል ስትፈጽምም ሆነ ልብና ኩላሊት እያወጣህ ስትሸጥ በስውር የተቀረፀው ቪደዮ ፊልም የሚሰጥህና የተቀበረው ፈንጂ የሚከሸፈው ሁሉም ነገር በእጃችን ከገባ በኋላ ነው። ገንዘቡም ያኔ ይከፈላል» ይላል ጽሁፉ። ወረቀቱ ላይ ተፍቶበት እንኳ ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ወረቀቱን በጥርሱ ቦጫጭቆ ጥሎት የመኪናውን መሪ በቡጢ ነርቶት በረረ። «የውሻ ልጆች!»

፳

ድቅድቅ ጨለማ በዋጠው መካነ መቃብር ላይ ድምጽ አልባዋ ዴር33 አነስተኛ አውሮፕላን እንዳረፈች ሜሮዳና ሚራዥ ከአውሮፕላኗ በፍጥነት ተከታትለው ወረዱ።

ወደ ትኩሱ የኢንጂነር ሻጊዝ መቃብር ሲደርሱ በጨለማው ውስጥ መቃብሩን የሚቆፍረው ሰውዬ አፈር የሚዝቅበትን አካፋ ጥሎ እጁን እንደ ተማረከ ወታደር ወደ ላይ ሰቀለ።

መቃብሩን እየቆፈረ የነበረው ሰውዬ ዶ/ር ሉስ ካን መሆኑን እንዳረጋገጠች ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጧን ጥይቶች ጭንቅላቱ ላይ አርከፈከፈቻቸው። ሊናገር አፉን እንደከፈተ ከቆፈረው መቃብሩ ውስጥ ያለውን የሬሣ ሣጥን በደመ ረጭቶት ወደቀ። የቆፈረውን ትኩስ አፈርም በደመ አጨቀየው።

ዶ/ር ዣንጊዳ እና ኢንጅነር ጌራ ዴር33ቷን አውሮፕላን ወደ መቃብሩ እንዳስጠጉ የኢንጅነሩን የሬሣ ሣጥን ለአራት ተጋግዘው አውሮፕላኗ ውስጥ ጫኑት። በደመ ተነክሮ መቃብር ውስጥ የወደቀውን የዶ/ር ሉስ ካንን በድን በቆፈረው አፈር አልብሰው የተከፈተውን መቃብር እንደነበረ ከዘጉት በኋላ አራቱም የኢንጅነር ሻጊዝ ምስጢራዊ የሬሣ ሣጥን ወደ ተጫነባት አውሮፕላን እንደገቡ ወዲያው የሚንደቀደቅ የሄሊኮፍተር ድምጽ የመካነ መቃብሩን ጸጥታ አደፈረሰው።

ከሚንደቀደቀው ሄሊኮፍተር በገመድ የወረዱት የታጠቁ የእስራኤል ኮማንዶዎች መቃብሩ ላይ ቆመው መቆፈር ሲጀምሩ ኢንጅነር ጌራ ድምጽ አልባዋን ዴር33 የዴርቶጋዳ አውሮፕላን በፍጥነት ወደ አየር አወጣት።

ወዲያው ከሄሊኮፍተሩ ላይ የተጠመደው መትረዩስ መንደቅደቅ ጀመረ። የኢንጅነሩ የሬሣ ሳጥን በድምጽ አልባዋ አውሮፕላን መወሰዱን የተረዱት ኮማንዶዎች መቆፈር የጀመሩትን ትኩስ መቃብር መልሰው አፈሩን በፍጥነት ከሞሉት በኋላ የሄሊኮፍተሩን ገመድ ይዘው ወጡና ድምጽ አልባዋን አውሮፕላን የጥይት ናዳ እያወረዱባት ተኩተኟት።

ሲጓራ ከሄሊኮፍተሩ የኋላ ወንበር ላይ ተቀምጣ ከሬሳ ሳጥኑ ጋር ግንኙነት ያለውን የዶ/ር ሉስ ካን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ስክሪን ላይ አፍጥጣ ትእዛዝ ታስተላልፋለች።

በኮምፒውተሩ ስክሪን ላይ ብልጭ ብልጭ እያለ ቀይ ምልክት የሚያሳየው ባነቋሚ ካሜራ በረቂቁ የሬሣ ሳጥን ውስጥ ያለውን ህያው በድን እያሳያት ነው።

ለብዙ ርቀት የሄለኮፍተሩ ጥይት ቢተኮስም ዝግዛግ የምትወነጨፈዋን ትንሽዋን ድምጽ አልባ አውሮፕላን ሊያገኛት አልቻለም። መትረየሱ ይንተባተጋል። ፓይለቱ አቅሙን አሟጠ ሄለኮፍተሩን ከተራራዎች አናት በላይ ያበረዋል።

ከብዙ ርቀት በኋላ አስከሬኑን ከጫነችው አውሮፕላን አንድ ሰው ተመታ። ሚራዥ ከሄሊኮፍተሩ የተተኮሰው የመትረይሱ ጥይት ሲቀረቀርበት አቃስቶ ተንሸራትቶ በተከፈተው የአውሮፕላኗ በር ተንሸራተተ። ከሰማይ ወደ ምድር ሊወረወር ሲል እንደምንም ተንጠላጥሎ ቀረ። ከሰማየ ሰማያት ቁልቁል መድረሻ የሌለው ወደ ሚመስለው አዘቅት ሲመለከት አጥወለወለው።

ዣንጊዳ የሚራዥን እጅ ይዞ ቢጮኽ፡ቱውም የተዝለፈለፈ አካሉ ሊሰበሰብለት አልቻለም።

‹‹ልቀቀኝ!›› አለ ሚራዥ ከምትበረው አውሮፕላን ላይ እንደተንጠለጠለ። ‹‹እናንተ አምልጡ ልቀቀኝ›› እጁን ከዣንጊዳ እጅ ሊመነጭቅ ሲታገል ዣንጊዳም ተንሸራትቶ ተከትሎት ተንጠለጠለ። ዣንጊዳ የሚራዥን እጅ ይዞ ሲታገል ሜሮዳ ደግሞ የዣንጊዳን ኮት ጨምድዳ ይዛ ባለ በሌለ ሀይሏ እያቃሰተች መጎተት ጀመረች። ‹‹ሚራዥ! .....ምን እየሆንክ ነው።.....ሚራዥ!.....››

ዣንጊዳ እንደምንም ታግሎ የሚራዥን አንድ እጅ መ፡ሉ በሙሉ እንደያዘ ባለ በሌላ ኃይሉ መጮ፡ት ጀመረ። የሄሊኮፍ፡ሯ ጥይት እየተንተገተገ ነው።

እንደምንም ታግለው ወደ ከአውሮፕላኗ ወለል እንደተመለሱ ሜሮዳ ከሬሳ ሳጥኑ ጀርባ የተቀመጠውን ዘመናዊ አውቶማቲክ መሣሪያ አንስታ በቅርብ ርቀት እየተኮሰ ወደ ሚከተላቸው ሄሊኮፍተር መተኮስ ጀመረች።

ሲጓራ የአስከሬኑን ሳጥንና በውስጡ የጫነውን ህያው አስከሬን እየቀረጸ ከሚያሳየው ልዩ ካሜራ የሚመራውን የኮምፒውተር ስክሪን ሄሊኮፕተሩ ወለል ላይ አድፍጣ እየነካካች

ለፓይለቱ ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፈች፡፡ ‹‹ተመለስ!›› አለች ሲጻራ፡፡ ‹‹የት እንደሚገቡ እስቲ እናያለን፡፡›› የኮምፒውተሩ ሥክሪን ላይ አፍጥጣ አውሮፕላኗ የምትጉዋዝበትን አካባቢ በካርታ ላይ የሚያሳየውን ቀይ ምልክት መከታተል ጀመረች፡፡

ቀዩ ምልክት አስክሬኑን የጫነችው አውሮፕላን በኢትዮጵያ ተራራማ ቦታዎች አልፋ አንድ ሃይቅ ውስጥ ስትገባ አሳያት፡፡ አፏን ከፍታ ቀረች፡፡ አውሮፕላኗ ዓሳ ከውሃ ውስጥ ጠልቆ እንደሚያወጣ አሞራ ሐይቁ ውስጥ ስትጠልም አየች፡፡በቀዩ ምልክት፡፡

ይህንን ሐይቅ ከማወቅ በላይ ታውቀዋለች፡፡ የኢትዮጵያ ካርታ መሃል ላይ የልብ ቅርጽ የሚመስለውን ሐይቅ፤ ጣና ሐይቅን፡፡በደንብ ታውቀዋለች፡፡ ቀዩ ምልክት ሐይቁ መሀል ወዳለው ታላቅ ደሴት ውስጥ ገባ፡፡

ደሴቱንም ታውቀዋለች፤ ባደገችበት ሐይቅ ውስጥ ስመ ገናናውን ደሴት ጠንቅቃ ታውቀዋለች፡፡ ዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት፡፡ ራሷን ነቅንቃ ላፕቶፕ ኮምፒውተሩን ዘጋችው፡፡ በፍጥነት ማሰላሰል ጀመረች፡፡ የጀመረችውን በጅምር መተው ጥሎባት አያውቅም፡፡ ሽንፈትን አሜን ብሎ የሚቀበል ሀሊናም አልፈጠረባትም፡፡

‹‹እንዲህማ አንላቀቅም!›› አለች ሲጻራ፡፡ ‹‹ከገባህበት ገብቼ አንቅሃለሁ፡፡ ጀምሬ የተውኩት ቲያትር አስካሁን የለም፡፡ እንደዚህ የሚፈትን ተውኔት ደግሞ ነፍሴ ነው፡፡ የመድረክ ተውኔት እንጂ እውነተኛው የህይወት ተውኔት ከሞት በቀር መቋጫ የለውም፡፡ እናያለን መጨረሻውን!.....››

ሸዕ

ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፤ ኢትዮጵያ

የኢንጅነሩን ህያው አስክሬንና ምስጢራዊውን የሬሣ ሳጥን የጫነችው ዬር33 ረቂቋ አውሮፕላን ወደ ሰርጓጅ መርከብነት ተቀይራ በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ ዋኝታ ወደ ዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ የምርምር ጣቢያ ስትገባ መምጣቷን ሰፊው የግድግዳ ስክሪን ላይ ይከታተሉ የነበሩ የዬርቶጋዳ ሳይንቲስቶች በፈንጠዝያና ጩኸት ተቀበሏት፡፡

ቁስለኛው ዶ/ር ሚራኻር ወዲያው ወደ ህክምና ክፍል ገባ፡፡ ሜሮዳና ዶ/ር ጐንጊዳ ምስጢራዊውን የሬሣ ሳጥን ከሌሎች የዬርቶጋዳ ሳይንቲስቶች ጋር ተጋግዘው ከአውሮፕላኑ አወረዱት፡፡ ቀያይ ጋዋን የለበሱት የአደጋ ጊዜ ሀራተኞች ወደ ድንገተኛ የህክምና ክፍል የሬሳ ሳጥኑን ይዘውት ገቡ፡፡

‹‹ወንድነህ!›› አለችው ሜሮዳ ጌራ ፓይለቱን፡፡

‹‹አንቺም የምትደነቂ ሰው ነሽ›› አላት ፈገግ ብሎ፡፡ ላታስበው አቀፈችው፡፡

አባ ገቦንበሩ ወደ ሜሮዳ ጠጋ አሉ፡፡ ‹‹ስላደረግሽልን ሁሉ ምስጋና ይገባሻል›› አሏት፡፡ ‹‹ወደ ዚህ ደሴት ሴቶች መግባት ባይፈቀድላቸውም ይህኛው ግን ከደሴቱ በታች በጣና ማህፀን ውስጥ የተሰራ ሀገራዊ ተቋም በመሆኑ ፍራቻ እንዳይሰማሽ፡፡ ወደፊት ሴት ሳይንቲስቶችንም በዬርቶጋዳ ውስጥ ለማካተት እየጣርን ነው፡፡ ስለአንቺም ዶ/ር ሚራኻር ከዚህ በፊት ነግሮኝ ነበር፡፡ ፈቃድሽ ቢሆን አብረሽን ብትሰሪ ፈቃደኞች ነን፡፡ ሀገራችን መንግስታት በተለዋወጡ ቁጥር የማይለዋወጥና የገዢ መደቦችን ብቻ አገልጋይ ያልሆነ ሀገራዊ ህቡእ ድርጅት ያስፈልጋታል፡፡ ሞሳድና ሲ.አይ.ኤ.... ምንም እንኳ በሌሎች ሀገራት ላይ ግፍ ቢፈጽሙም ለሀገሮቻቸው ያደረጉት ነገር ቀላል አይባልም፡፡እንዲያውም ሞሳድ ባይኖር ኖሮ እስራኤል አትኖርም ነበር፡፡ ሲ.አይ.ኤም ባይኖር አሜሪካ እንደዚህ አትሆንም ነበር፡፡ እነዚህ ድርጅቶች አሜሪካና እስራኤል እስካልጠፉ አይጠፉም፡፡ ኢትዮጵያ ግን በየዘመኑ የሚለዋወጡ መንግሥታት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ከሚያቋቁሟት አፋኝ የደህንነት ድርጅት ባሻገር ዘለአለማዊ የሆነና የኢትዮጵያን ደህንነትና ጥቅም የሚያስጠብቅ ተቋም የላትም፡፡ ለዚህም ራዕይ አልባ ሀገር ሆናለች፡፡

ቋሚ ድርጅት ያስፈልጋታል። ለዚህም ነው ዴርቶጋዳ የተቋቋመው። አስፈላጊ ሴት መሆንሽን ዴርቶጋዳ ተረድታለች።››

‹‹ላስብበት›› አለች ሜሮዳ። ‹‹ስለድርጅቱ አላማም በደንብ ማወቅ ይኖርብኛል። ሲ.አይ.ኤ ተጠቅሞብኛል። ሌላ ድርጅት ደግሞ እንዲጠቀምብኝ አልፈልግም። የማሰቢያ ጊዜ ይሰጠኝና አስብበታለሁ።

«ግዴለም አስቢበት። ሁሉን ነገር ልንነግርሽም ዝግጁዎች ነን። እስከአሁን ያደረግሽልን ለዚህ የከበረ አላማ እንድንመርጥሽ አበገድዶናል።»

ሚራዥ ባቱ ላይ የመታችው ጥይት ወጥታ እግሩ በፋሻ ተጠቀለለች። ጠረጴዛው ላይ እንደተንጋለለ ሜሮዳን ትኩር ብሎ ኦያት። «እመሰግናለሁ» አላት።

«ምንም አይደል። ላንተ ስል። .....» አለችው ፈገግ ብላ።

«የሬሣ ሣጥኑ ተከፈተ?» አላት በጉጉት።

«እየተከፈተ ነው።»

«ማየት አለብኝ»አለ ሚራዥ.....እየተነሳ። «ወደዚያው ውሰዱኝ። ኢንጅነር ሻጊዝን ማየት እፈልጋለሁ። እንኪን ደህና መጣህ ብዬ ደስታየን ልግለጽለት ውሰዱኝ።»

ክራንች ተሰጥቶት በላይንቲስቶችና በዴርቶጋዳ አባላት ወደ ተከበበው ምስጢራዊ የሬሣ ሣጥን እያነከሰ ቀረበ ምስጢራዊው የሬሣ ሣጥን ተከፍቷል።

የሬሣ ሳጥኑ ውስጥ በረቂቅ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የተተበተበው አስከሬን ዙሪያውን የከበቡትን ቀያይ ጋዋን የለበሱ ላይንቲስቶችና ባደስታ የተዋጡ የዴርቶጋዳ አባላትን ተመልክቶ ፈገግ አለ። ራሱ ላይ የተገጠመው የብረት ቶብ ወልቆለታል። ጭንቅላቱ በፋሻ ተጠቅልሏል። እንዳይነቃነቅ ከሳጥኑ ጋር በታሰረ አነሱ ዙሪያ የግሉኮስና የአክሰጅን መስጫ መሣሪያዎች ተተክትበዋል። የተገጠሙለት መሣሪያዎች በሙሉ ተፈታተው ተሸከርካሪው የህክምና አልጋ ላይ ተደርጉ ወደ ህክምና ክፍሉ ሲገባ ቀያይ ጋወን የለበሱት የዴርቶጋዳ አባላት በጭብጨባ አጀቡት። እጁን በቀስታ አንስቶ በደስታ አወዛወዘቸው።

፳፪

ቴልአቪቭ ፡ እስራኤል

ሲጻራ ከሞሳድ መስሪያ ቤት በታች በተሰራው የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ፊቷ በአባቷ ፊት ከተቀየረ ከሳምንት በኋላም በቁመ-መስታወት ውስጥ ፊቷ ላይ የተገጠመውን የአባቷን ፊት ማየቷን አላቆመችም። ረጅም ጊዜ ከፈጀው ቀዶ ጥገና በኋላ ፊቷ በፋሻ ታጅሎ ነበር የሰነበተው። ፊቷ በቀዶ ጥገና በአባቷ ፊት ሲተካ አልተቃወመችም። ድምፅዋም የአባቷን የአባ ፊንሐስን ድምጽ እንዲመስል ሆኖ በኮምፒውተር ተስተካክሏል።

ኢንጅነር ሻጊዝን ለእስራኤል ካስረከበች በኋላ የተፈጥሮ ፊቷ እንደሚመለስላት ተነግሯታል።ፊትዋን በመስታወት እየተመለከተች ሞሳድ የኦሷን ፊት የለወጠበት ጥበብና ምስጢር ድንቅ ግርም ብሏታል።

በዘመቻ ሙሴ ወደ እስራኤል ስትመጣ የሱዳን በረሃ ሲሳይ ሆነው የቀሩት አባቷ አባ ፊንሐስ ከመሞታቸው በፊት በሞሳድ የተነሱት ፎቶ ግራፍ በሞሳድ የዶክመንተሪ ክምችት ውስጥ ተገኘ። በፎቶ ግራፍ የነበረው የአባ ፊንሐስ ፊት በልዩ ቀዶ ጥገና ፊቷ እንዲሆን ተደረገ። አባቷ ከመሞታቸው በፊት ስለ ኢትዮጵያ የነሮ ሁኔታና በኢትዮጵያ ፈላሻዎች እንዴት ይኖሩ እንደነበር በረሃ ውስጥ ለሞሳድ ቃለምልልስ ከሰጡት የቴፕ ድምጽ ላይ ድምፃቸው ተጠንቶ የሲጻራ ድምጽ እንደ አባቷ ሆኖ ተስተካክሏል።
በመሆኑም ከአንባቷ በላይ ናቡም አባቷን መስላለች። ድምጿም ከአባቷ ድምጽ አይለይም።

ከቀዶ ጥገናው በኋላ መስታወት ላይ ፊቷን ስታይ አባቷ ድቅን አሉባት። ከሚራዥ ስለለያዩዋትና ትርጉም አልባ ህይወት እንድትመራ ስላደረጓት በውስጧ ሳትረግማቸው አልተረችም። መስተዋቱ ፊት ለፊት ቆማ አዲስ የተገጠመላትን የአባቷን ፊት ስታይ ከቆየች በኋላ አባቷ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ይለብሱት የነበረውን የምንኩስና ልብስ አይነት ስትለብስ ሙሉ በሙሉ እርሳቸውን መሰለች።

እንደ ሞሳድ ውሳኔ ሚራዥ ደረጃንም የወንድ ደረት ለማስመሰል ጡቷም በሰርጀሪ ሊመጠጥ ነበር። እሷ ግን አጥብቃ ተቃወመች። ከአንባቷ በታች የሚፈትሻት እንደሌለ እርግጠኛ ናት። ደረቷ ላይ የተከመሩትን ትላልቅ ጡቶቿን በወፍራም ልብስ አጅላቸዋለች። የመናኒ ደበሎዋም ሴትነቷን ውጦታል። አስፈላጊ

የፀሎት መፃሕፍትንና የመነኩሴ ዝክንትሉችንም አንግታለች። የእሷን አባ ፊንሐስነት የሚጠራጠር ከእሷ በቀር ማንም አይኖርም።

በምስጢራዊው ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት ውስጥ የተሰወረውን ሳይንቲስት ከገባበት ገብታ ለማነቅ ያደረገችው ውሳኔ ትክክለኛ ለመሆኑ እርግጠኛ ናት። ወደ ኢትዮጵያ የምትገባበት አውሮፕላንም ተዘጋጅቶላታል። ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት የምትገባበትና አድርሷት የሚመለስ ጀልባም ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባው የሞሳድ የሰላዮች ቡድን ተመቻችቶላታል። አባ ፊንሐስን ሆና አባቷ ወደ ነበሩበት የወንዶች ገዳም ልትገባ አንድ ቀን ብቻ ነው የቀራት። ወደዛ ገዳም እንኳን የሰው የአራዊትም ሴት እንደማይገባ ታውቃለች።

ያንን ህግ ጥሳ የምትገባበት ቀን ላይ ናት። እንዲያውም በዚህ ህግ ላይ ያደረ ቂም አለባት። ፍቅሯን የከለከላትን የወንዶችን ገዳም ህግም አገረ መንገዷን ለመበቀል ቋምጣለች።

የሬሳ ሳጥኑን የሚያመለክተው ካሜራ የተገጠመለት ኮምፒውተር ሻንጣዋ ውስጥ ከመፅሐፍ ቅዱስና ከሽጉጧ ጋር ተቀምጦላታል። ልዩ ልዩ የመገናኛ መሥሪያዎችም ተሰጥተዋታል። ይህ ሁሉ ጉድ የታጨቀበት ሻንጣዋ ግን የኢትዮጵያ መነኮሳት የሚይዙት አይነት ላዩ ላይ ቡትቶ የተሰፋለት ከረጢት ነው።

«ሲጳራ..... »አሉ የሞሳዱ ዋና ዳይሬክተር ወደስዋ በፍጥነት እየተራመዱ። ከረጢት መሰል ሻንጣዋን እንደተሸከመች ዘወር አለች። «በዶ/ር ሉስ ካን ሪፖርት ላይ እንደተገለፀልን በኢንጅነሩ ጭንቅላት ውስጥ በቀዶ ጥገናው ወቅት ረቂቅ ማይክሮ ፈንጂ ተጠምዷል። ካልያዝነው ይፈነዳል ከያዝነው ደግሞ በሰርጀሪ እናወጣለታለን። ኢንጅነሩን መያዝና ማምጣት ያለብሽ ቦንቡ ከመፈንዳቱ በፊት መሆኑን አትዘንጊ። ቦንቡ መውጣት የሚችለው እዚህ ሲመጣ በምናደርግለት ቀዶ ጥገና ብቻ ነው። መፍጠን አለብሽ። ቦንቡ ሊፈነዳ የቀረው ጊዜ እጅግ በጣም ጥቂት ነው። አሥራ አምስት ቀናት ብቻ። ከአሥራ አምስት ቀናት በፊት ኢንጅነሩ ቴልአቪቭ ካልደረሰ ሁሉም ነገር አከተመለት ማለት ነው። ትሰሚኛለሽ?!.... ከኢንጅነሩ ጭንቅላት ውስጥ የተጠመደው ፈንጂ ሊፈነዳ የቀሩት አሥራ አምስት ቀናት ብቻ ናቸው። ያንቺን ጥሪ የሚጠባበቅ ድጋፍ ሰጪ አካል ከሁዋላ ይከተልሻል።» ይህንን ተናግረው ዳይሬክተሩ ወደ ቢሯቸው ሲገቡ የአውሮፕላኑ ሞተር እያጓራ ነበር።

ወዲያው ዶ/ር አናንያ የሆነ ነገር አንጠልጥሎ እየሮጠ ደረሰባት። «አንተ!.....ም....ምም.... ምን እያደረክ ነው!?» አለች ሲጳራ በድንጋጤ። በእጁ እንደቀላል እቃ እንጠልጥሎ የያዘው የእሷን ፊት ነው። በዝልግልግ ፈሳሽ ወስጥ ህዋሳቱ እንዳይሞቱ

ተደርጎ የተቀመጠበት ባለ መስተወት ጃር ነው። ፊቷ በዝልግልጉ ፈሳሽ ውስጥ ታያት።

«ፊትሽን አየሽው?! ህ!.....ይህ ነው ስትኩራሪበት የነበረው ፊትሽ ያምራል አይደል?....አሁን መሳም እችላለሁ። መልሶ ባይስመኝም እስመዋለሁ። እምጹዋ!» በጃሩ ጠርሙስ ውስጥ በዝልግልጉ ፈሳሽ ላይ የሚንሳፈፈውን የፊትዋን ቆዳ ምጥምጥ አድርጎ ሳመው። ዶ/ር አናንያ ከሽንጡ የመዝረጠውን ሽጉጥ በጃሩ ላይ ደቀነው።

«what the hell are you doing!?» ሲጳራ አፏ ተሳሰረ።

«ከአሁን በኋላ ይህን ስትኩራሪበት የነበረውን ፊትሽን አታይውም። ትዝ ይበልሽ ወንዱን ልጅ እንደ ሴት አስደፍረሽኛል» የሽጉጡን ምላጭ ሳበው። ፊቷ የተቀመጠበትን ጃር በጥይት በሳሳው። ፊቷን ከገደለው በኋላ «ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! »ብሎ በብሽቀት ስቆ የራሱን ሽጉጥ ጠጥቶ ወደቀ። እሷን ያፈቀረበት ራሱንም አስወገደው።

እንደነብር ተወርውራ አስከሬኑን አነቀችው። ሞቷል። የራሷን ሽጉጥ አውጥታ በድኑን ቦተራረፈችው።

«ፊቴን! ፊቴን! ፊቴን!....» ተንሰቅስቃ እያለቀሰች የጥይት ናዳ በድኑ ላይ ብታወርድበትም አልጠቀማትም። ነፍሱን ተከትላ መልሳ ብትገላትም አትረካም።

የሞሳድ ዋና ዳይሬክተርና ሌሎች ኤጀንቶች ቢያጽናኗትም ለቅሶዋ ሊበርድ አልቻለም።

በኋላ ደግሞ እንደምንም ለመሄድ ወሰነች። ፈንጂ ሳይፈነዳ.....።

ሽቦ

ዳጋ እስጢፋኖስ፡ ኢትዮጵያ

አባ ፊንሐስ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎላቸዋል። ሌሊቱን ግን በማያውቁት ጉዳይ ለእስር ተዳረጉ። የሽሪቶች መናሃሪያ በሆነው ቀፋፊ ጎጆ ውስጥ ባለው ሽንቁር ግንድ ታሰሩ። ግንዱ ሊጎተት የማይችል ገንደልላ ነው። በሁለቱ የግንዱ ቀደዳዎች እግራቸውን እንዲከቱ ከተደረጉ በሁዋላ በሁለቱ ሽንቁሮች ያለፉት እግሮቻቸው በእግረ ሙቅ ተጠረነፉና ተቆለፈባቸው። መተኛትም መደገፍም አልቻሉም። ሰውነታችው ተቅመደመደ።

በዛው ሌሊት አባ ዝንበሩ ወደ ታሰሩበት ጎጆ ገቡና " አባ ፊንሐስ!" አሉአቸው። "በአራት ነገሮች ተከሰሃል። ሶስቱን እነግርሃለሁ አራተኛውን ግን ስለምታውቀው አልነግርህም። አንደኛ ከእኔ ጋር አብረህ ጓደኛ መስለህ ዋሻውን ስታቋፍረኝ ኑረህ ወደ ዋሻ ካሸሸናቸው ቅርሶች መኃል የንጉሡን ዘውድ ሰርቀህ በአንጥረኝነት ሙያህ ቀጥቅጠህ ሸጥከው። ሁለተኛ አባ ዲዲሞስን ወይም አለቃ አያሌውን አሳደህ ሚስቱንና ቤቱን በእሣት አቃጠልክ።ካርታውን በጥበብ መውሰድ ስንችል አንተ ግን በጉልበትህ ብዙ ነገር አበላሸህ። ሶስተኛ በእንጦንስ የሴቶች ገዳም ውስጥ የኖረችውን ልጅህን ያሳደግሃት ይመስል የገዳምዋን ልጅ ልክ እንደወንበዴ አፍነህ ከመወሰድህ በላይ የዚህን ገዳም ጀልባ ይዘህ ጠፋህ። የተከሰስከው እንግዴህ በክህደት፣ በስርቆትና በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ነው ማለት ነው። አራተኛውን ወንጀልህን አንተው ታውቀዋለህ። መነኩሴ ነኝ እንጂ የሞት ቅጣት እፈርድብህ ነበር። ለነገሩ....የሚገድልም የሚያድንም እግዚአብሔር ነው። ሙዋች የሆነ ሰው የሞት ፍርድ መፍረድ አይችልም። የሞት ቅጣት እንዳልፈርድብህ የሞት ቅጣትን አቃወማለሁ። ቅጣት ጠባይን ማረሚያ ነው። ብዬ አምናለሁ። ከሞት በሁዋላ የሚታረም ነገር የለም። በገሃነም ወይም በመንግስተ ሰማያት ውስጥ የምትገባን ነፍስ ጠባይ የማያርም ቅጣት ነው የሞት ቅጣት። መልሰን ልንሰራው የማንችለውን ህይወት ማፍረስ ታላቅ ወንጀል ነው ። ያልሰራነውን የማፍረስ መብት የለንም። በዚህ ባላምን ግን የሞት ፍርድ እበይንህ ነበር። አሞ.... አባ ፊንሐስ ወንጀልህ ልክ የለውም" አባ ዝንበሩ ይህን ተናግረው የአባ ፊንሐስን መልስ ሳይሰሙ እየተበሳጨ ተነስተው ሄዱ።

አባ ፊንሐስ በድንጋጤ ተርበተበቱ። ሲጻራ አባቱዋን እስከ ወንጀላቸው ነው ለካ የሰበሰቧቸው....የተሸከመቻቸው። በአባቷ ፊት የአባቷን ቅጣት ተቀበለች። ሲጻራን ፀፀት ሰነጣጠቃት። ይህንን የአባትዋን ወንጀል ብታውቅ ኖሮ በቀዶ ጥገና ፊቷን በአባቷ ፊት ባልቀየረችም ነበር። መቀየር እንዳልነበረባት ተረዳች።

በዚሁ ሌሊት ደሞ አባ ዲዎላ አባ ፊንሐስ ወደ ታሰሩበት ቀፋፊ ጎጆ መጡ። "እንጥረኛው ፊንሐስ?" አሉ አባ ዲዎላ። "እንኳ ቆብ ብረት ብትደፋ እንኳ የምረሣህ እንዳይመስልህ። ልብህ ካልመነኮሰ ራስህ ብቻ ቆብ ቢደፋ ምን ዋጋ አለው?! ከቆብህ በታች የአንተ ገመና ብዙ ነው። .....ትዝ ይልሃል? ትዝ ይለሃል እንጂ! እናቴን ከአልጋዋ ጋር አስረህ አሳት ያነደድክባት ትዝ ይልሃል? እኔ ግን ልረሳው አልችልም። የእናቴ የሰቆቃ ዋይታና ኡኡታ እስከ አሁን ደረስ በጆሮዬ ይሰማኛል። ሲገርፋት የነበረው የአሳት ነበልባል እስከ አሁን ድረስ ሀሊናዬን ይገርፈኛል። ይለበልበኛል። ያቃጥለኛል። አም! ያ..ቃ..ጥ..ለ..ኛ..ል። ያንን ሁሉ ሐጢአት በተሸከምክበት ጭንቅላትህ ላይ ደሞ ቆብ ደፋህበት። አይ አንጥረኛው ፊንሐስ !! አይ ወንጀለኛው ፊንሐስ ! ጉድ ነው! ጉድ እንጂ የጉድ ጉድ። ቂቂቂቂ...ሃ!ሃ!ሃ!...." አባ ዲዎላ በሹፌት ሲንሸፍጡ በጎጆው ቀዳዳ በገባው የጨረቃዋ ወገግታ ባዶ ድዳቸው ግልጥጥ አለ። የጃርት ጉድጓድ የመሰለው አፋቸውን ስታይ ሲጻራ የሲኦል ደጅ ላይ የቆመች መሰላት። አባ ፊንሐስ ወከክ አሉ። ሲጻራ ራደች።

"አባ ፊንሐስ -አንጥረኛው ፊንሐስ! ወንጀለኛው ፊንሐስ!" አሉ አባ ዲዎላ። "ልትፀድቅ ነው መንኩስህ የመጣሃው? እውነት እልሃለሁ ወንጀለኛው ፊንሐስ አንተ ከፀደክ እኔ የመንግስተ ሰማያት መግቢያ ቁልፍ ያዥ እሆናለሁ ማለት ነው። የእናቴን አሰቃቂ አሟሟት እግዚአብሔር ይበቀልልኝ ብዬ የምተውህ እንዳይመስልህ። ገሀነመ እሣትና ሲኦል ሰፈፀምከው በደል ለሠራሃው ኃጢአት በቂ መቀጮዎች አይደሉም። ስለዚህ እኔ በጥሩ ሁኔታ እቀጣሃለሁ። አሞ.....መጀመሪያ በጉጠት ጥፍሮችህን ቀስ በቀስ እነቃቅላቸዋለሁ። ቀጥዬ ጣቶችህን በመጥረቢያ እቀረጥፋቸዋለሁ። ከዛም እጆችህን እጎነድሻቸዋለሁ። ቀጥዬ እግሮችህን አንድ በአንድ እቆራርጣቸዋለሁ። ከዛም ጥርሶችህን አወላልቄ የራስህን ሥጋ በድድህ እያኘክ እንደትበላ አደርግሃለሁ። ይህ ሁሉ ሲሆን እንድታይ ዓይኖችህን ቀድሜ አላጠፋቸውም። አም! ውይ! ረስቼው። ብልትህን ቆርጬ አበላሃለሁ። አም ከዛም እንደ እንቁራሪት ሆድህ እስኪነፋ በእሳት አሰበልብሃለሁ። ይህ ሁሉ እስኪሆን ግን እንድትሞት ስለማፈልግ ነፍስህን ከሥጋህ ጋር የማሥርበት ዘዴ አላጣም። አይዞህ! ቶሎ አልገድልህም።" አባ

ዲዎላ ይህን ብለው እየዛቱ ተነስተው ሄዱ። ሲጸራ ፍርሃትና ጭንቀት ሲወራት ተሰማት። አባ ፊንሐስ ተርበተበቱ። "አባ ፊንሐስ አይደለሁም!" ሊሉ አሰቡ አባ ፊንሐስ። ሲጸራ። ግን ይህን ካሉ የመጡበት አላማ እክል ይገጥመዋል።

ከሰው እስከ እንስሳ ሴት የሆነ ሁሉ ወደዚህ ገዳም እንዲገባ አይፈቀድለትም። ምናልባት ከአዕዋፍ እስከ ትንኝ ያሉ በራሪ ነፍሳትም ሴትና ወንድነታቸው ስለማይለይ እንጂ የእነሱም ሴቶች ተለይተው አይገቡም ነበር። ሲጸራ ይህንን የወንዶች ገዳም ህግ በልጅነትዋ ትቃወም ነበር። በወንዶች ገዳም ውስጥ የነበረውን ፍቅርዋን ሚራኸን ለማየት የከለከላት የማትወደው ህግ ነው። እንዲያውም በዚህ ገዳም ውስጥ የተፈፀመ አንድ አገር ያወቀው ታሪክ መኖሩን ታውቃለች። እቴጌ ምንትዋብ ተገንደር መጥተው እዚሁ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ለመግባት ከጅለው ሲከለከሉ ከወደቡ ኮረብታው ላይ እስካለው ቤተ ክርስቲያን ምንጣፍ አስነጥፈው እኔ ምንጣፌን እንጂ መሬታችሁን አልረገጥኩም ብለው ሲጉዋዙ መሀል ላይ ደም በደም ሆነው ተመልሰዋል ይባላል። በዚህም ምክንያት ደቅ ደሴት ላይ የሚገኘውን ናርጋ ስላሴ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስገነቡ ሲጸራ በልጅነትዋ ያነበበችውን ታስታውሳለች። ለዚህም ነው ፊትዋን በቀዶ ጥገና የወንድ ፊት አልብሳ ወደዚህ ገዳም የመጣችው። ታዲያ ምን ያደርጋል የአባትዋ ፊት የአባትዋን ሐጢአትና ወንጀል አሸከማት። ድምፅዋም ፊትዋም ቁርጥ ጣል እንደ አባትዋ ነው።

ቀኑም እየነጎደ ነው። ከኢንጂነሩ ጭንቅላት ውስጥ በቀዶ ጥገናው ወቅት የተጠመደው ፈንጅ ሲፈነዳ የቀሩት አሥር ቀናት ብቻ ናቸው። ፈንጁ ሳይፈነዳ ኢንጂነሩን መውሰድ አለባት። ግን እንዴት አድርጋ? ይባስ ብሎ ያልጠበቀችው እስራትና ህይወትዋን የምትነጠቅበት አጣ ፋንታ ደረሳት። የአባ ዲዎላ ዛቻና አሰፈሪ ፊት በአእምሮዋ ተመላለሰ። ቅዱስ ሚካኤል የደበደበውን ሰይጣን የሚመስሉት አባ ዲዎላ አርበተበታት።

በሁለተኛው ሌሊት አባ ዝንበሩ አባ ፊንሐስ ወደ ታሰሩበት ደሳሳ ጎጆ ለሁለተኛ ጊዜ ገቡ።

"አባ ፊንሐስ !" አሉ አባ ዝንበሩ። "ልጅህ የት ናት?"

"ልጄ ደግሞ ምን ሠራች?" አሉ አባ ፊንሐስ ።

"ልጅህ አሥራው በነበረው ነገር ምክንያት እንደ ወሰድካት አታውቅምና ነው መልሰህ የምትጠይቀኝ?"

"አይ አባ ....." አሉ አባ ፊንሐስ። "ልጄ የት እንዳለች በምን አውቃለሁ? እኔ እንደሁ ያ ምድራዊ ምኞቴ አሁን ከእኔ ጋር የለም። ሁሉም ነገር ከንቱ መሆኑ ገብቶኛል። ወደ ኢየሩሳሌም ከሄድኩ በሁዋላ በጌታችን መቃብር፣ በጎልጎታ፣ በቀራንዮ፣ በዴርሱልጣን እየዞርኩ ንስሐ ስገባ ስለ ሐጢአቴ ሳለቅስ ኑሬ ነው

የመጣሁት። .....አሁን እዚህ የመጣሁበት ምክንያትም ይህ ቦታ ቅዱስ በመሆኑ እዚሁ እረፍተ ሞቴ እንዲሆን ተመኝቼ ነው። በዚህ ቅዱስ አፈር ላይ ለማረፍ። ቢያስሩኝ ቢገርፉኝ ቢደፉኝ ምንም አይመስለኝም!"

"አትዋሽ! አንተ በፍፁም እንዲህ ዓይነት ሰው አይደለህም። እስከዛሬ የዋሸኽኝ ይበቃሃል" አባ ዝንበሩ በጣም ተጠጉ። ሲጸራ የታሰረችበት እግረ መቅ ቁልፍ ከቢጫው ቀሚሳቸው ኪስ ጫፍ ላይ እየተንዘላዘለ ነው። "አንተን እግዚአብሔር ይቅር አይልህም።"

"ብሎኛል እንጂ! ይቅር ብሎኛል። እግዚአብሔር እንደ ሰዎች አይደለም! ሰዎች በራሳቸው አምሳል መልሰው ፈጥረውት ነው እንጂ። ይቅር ብሎኛል። ይቅር እንዳለኝም ተገልጦ ነግሮኛል። እንባዬን አብሶልኛል። ይልቅስ በመስቀልዎት ይባርኩኝማ። ያሳልሙኝ። መስቀሉን መሣም እፈልጋለሁ።"አባ ፊንሐስ እንቁላል እንደታቀፈች ዶሮ ጎጆ ቤት መስለው እንደታሰሩ ፊታቸውን ለቡራኬ አዘነበሉ። ወደ አባ ዝንበሩ። የእግር ብረቱ ቁልፍ ከኪሳቸው ጫፍ ላይ ተንጠልጥሎ ስላዩ።

አባ ዝንበሩ ካሳለሙአቸው በሁውላ "ለመሆኑ ልጅህ ወዴት ናት?" አሉ።

"እስራኤል ሀገር ውስጥ ናት።"

"የት ቦታ?"

«ስሙን አላውቀውም። ቦታውን ግን በዓይን ባየው አውቀው ይሆናል። በጣም አስፈላጊ ከሆነም ሂደን እናመጣታለን። ግን ልጅ ምንድን ነበር ያሠረችው?»

«አታውቅምና ነው? ለዛ ስትል አይደል እንዴ አንቀህ የወሰድካት»

«ኧረ ወላዲተ አምላክን! እመአምላክን ምን እንደያዘች አላውቅም።»

«በል ወደዚያው ትወስደኝና የያዘችውን አብረን እናያለን» ተነስተው ሄዱ ።

«ይፍቱኝ እንጂ አባ? ይፍቱኝ እንጂ! ተነጋግረን አይደል እንዴ? እግዚአብሔር ይቅር ያለኝን እርስዎ ሊያስሩኝ? ወይ ሰው! ወይ መነኩሴ!» አባ ፊንሐስ ይህን ቢለፈልፉም አባ ዝንበሩ ግን ዞር ብለው እንኳ አላዩአቸውም።

አባ ፊንሐስ በታሰሩ በሁለተኛው ሌሊት ኮረብታው ላይ በሚገኘው የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተንበርክከው ሲፀልዩ ተያዙ። አባ ዝንበሩ "ማን ፈታህ አንተ መናጢ?" አሉ እርሳቸውም እንደ ሚፀልይ ሰው ከጉጋቸው ተንበርክከው በሰሆሳስ።

"አልነገርኩዎትም አባ? እግዚአብሔር ይቅር ብሎኛል ብዬዎት አልነበረም? ይኸው እግዚአብሔር ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ

ከእስራቴ ፈታኝ። እግዚአብሔር የፈታውን ማን ያስረዋል? ይልቅስ ቁልፉን እነሆ። ቅዱስ ሚካኤል ከኪስዎ ወስዶ እኔን ሲፈታኝ ለምን ቁልፉን ሲወስድ አላዩትም? ብዬ አልጠይቅዎትም" አሉ አባ ፊንሐስ። "ቁልፉን መልስላቸው ብሎኖል ይልቅ። ቁልፉን ይውሰዱ"

"ይከተሉኝ" አሉ አባ ዝንበሩ። አባ ፊንሐስ እስከ ገዳሙ ተከተሏቸው።

"ይኸው ቤትዎ። የግል በአትዎ ይኸውና። ከሳምንት በሁዋላ ወደ እስራኤል አብረን እንሄድና ከልጅዎት ጋር ያገናኙኖል" የግል የፀሎት ቤት ሰጥትተዋቸው ሲሄዱ አባ ፊንሐስ እንግዳ ቤት ያስቀመጡት ጓዛቸውን ወደ ግል ቤታቸው አምጥተው አስገቡ።

በኢንጂነሩ አንጎል ውስጥ የተቀበረው ረቂቅ ፊንጅ ሊፈነዳ ስምንት ቀናት ብቻ ቀርታውታል። በዚሁ ሌሊት ከረጢታቸው ውስጥ ያለውን ኮምፒውተር አውጥተው በደሴቱ ምድራዊ ክፍል የሬሣ ሳጥኑን የሚያመለክተውን ቀይ ምልክት ተመለከቱ። በሬሣ ሳጥኑ ውስጥ የነበረው ህያው አስከሬን የለም። የሬሣ ሣጥኑም ተከፍቷል። ኢንጂነሩ በዚህ ዋሻ ውስጥ እንደሆነ ግን ጥርጥር የላቸውም። ኮምፒውተሩን ከፍተው ከመመልከታቸው በፊት ለብሰውት የሰነበቱትን የምንኩስና ልብስ አወላልቀው በመሳናፀፊያው ብቻ ጡቶቻቸውን ሸፍነው ነበር። ሽጉጣቸውንም ከኮምፒውተሩ ጀርባ ካለው መፅሐፍ ቅዱስ ላይ አስቀምጠውት ነበር።

በዚህ ቅፅበት አባ ዲዮላ በሩን በርግደው ገቡ። አባ ፊንሐስ በቅፅበት ሽጉጣቸውን በአባ ዲዮላ አናት ላይ በደመ ነፍስ ሲያነጣጥሩ ራቁታቸውን የተጋለጡ ጡቶቻቸውን ረስተዋቸው ነበር።

አባ ዲዮላ ከሲጻራ ካቦ ካቦ የሚያነክሱ ጡቶች ጋር ሲፋጠጡ "አሃ!" አሉ ጥርስ አልባ አፋቸውን እንደከፈቱ። ከመጥፋት የተረፈችው አንዲት ዓይናቸው የአባ ፊንሐስን እንስታዊ አካል እንደሸኮርት ከታች እስከ ላይ ላጠችው። ግራ ተጋቡ-አባ ዲዮላ። ከአንገት በላይ ዕድሜ ጠገብ ጢማም ሽማግሌ ወንድ! ከአንገት በታች የወሲብ አሳት ጭን ውስጥ የምትለኩስ አማላይ ሴት!

«ወይ ጉ....ድ! » አሉ አባ ዲዮላ። «ሰውን ገልጦ ነው ማየት! ላይ ላዩን እያዩሁ እንስት ነው ተባዕት ስል መኖሬ ከንቱ ነበር ለካ። እግዜር እንስትና ተባዕት አርጎ ፈጥሮዎት ነው ለካ ተንኮለምትን እንዲህ ያበዛው። እንዲህ አይነት ፍጡር አይቼም ሰምቼም አላውቅ» ሽጉጡን ረስተው በሚያዩት ትንግርት ትንፋሻቸው ቆመ። "ሴትና ወንድ ነዎት እንዴ ለካ አንጥረኛው ፊንሐስ?"

"አፍህን ዝጋ!" አለች ሲጻራ። "አባ ፊንሐስ አይደለሁም። ወደ ውስጥ ግባና በሩን የሁዋሊት ዝጋው!" አባ ዲዮላ በሩን

የኋሊት ጠረቀሙት። አንዲቷ ዓይናቸው በአባ ፊንሐስ ትላልቅ ጡቶች መካካል አፍጥጣለች። በሰንሰለት ታስሮ በአባ ፊንሐስ ጡቶች መካካል ወርዶ የተንጠለጠለውን ባለጉጥ ግማደ መስቀል በአንዲት ዓይናቸው ጠቡት።

አባታቸው አለቃ አያሌው አባታቸው አባ ዲዲሞስ የዚህን መስቀል ቅርፅ በመጽሐፍ ቅዱሳቸው መሃል ስለውት አይተው ነበር። ይህን ባለጉጥ ግማደ መስቀል ፍለጋ አይደል እንዴ የቀበሮ ባህታዊ ሆነው ወደዚህ ገዳም የገቡት? ለረጅም ጊዜ መስቀሉ ላይ ሲያፈጡ ሲጻራ ግራ ገባት። አባታ አባ ፊንሐስም ሱዳን በረሃ ውስጥ ከመሞታቸው በፊት እንዲህ ያፈጡበት ነበር። አሁን ደግሞ አባ ዲዮላ።

‹ምንድን ነው ምስጢሩ?› ይህ ባለጉጥ ግማደ መስቀል የምንጊዜም ፍቅሯን ሚራዥን ከማስታወስ ባለፈ ለእሷ ሌላ ምስጢር የለውም። ሚራዥ ካሰረላት ጊዜ ጀምሮ ከእንገቷ ወልቆ የማያውቀው ይህ መስቀል ዘወትር እንደ ጅረት ውሃ ቁልቁል ለሚያፈላት ትዝታዋ የመፈለቂያ ምንጭ ነው። ከዚህ በቀር ሌላ ምስጢር አስራው የኖረችው መስቀል እንደያዘ አታውቅም። ስለዚህ መስቀል ፡ምታውቀው ምስጢር ቢኖር በሀሰቧ ከሚራዥ ጋር የምትገናኝበት የፍቅር ስጦታ መሆኑን ብቻ ነው።

"ወይ አባ ፊንሐስ!" አሉ አባ ዲዮላ እጃቸውን ወደ ላይ እንደተማረከ ወታደር እንዳንጨባረሩ። "ይህን ምስጢረኛ መስቀል ማስረዎትን ባውቅ ኖሮ አሰግድልዎት ነበር እንጂ መች እንደዛ እዝትብዎት ነበር። ይበሉ ይቅር ይበሉኝ አሁን። ይቅር ይበሉኝ" በግንባራቸው ወለሉ ላይ ተደፉ። "ይቅር ይበሉኝ!" በውስጣቸው ቀጥለው ስለሚያደርጉት ነገር እያሰላሰሉ። መስቀሉን የሚቀመሙበትን ዘዴ። ቀስ ብለው እየተሳቡ ከሲጻራ እግር ሊደርሱ ከአባ ፊንሐስ እግር ላይ የተደፉ መስለው ስበው ለመጣል እያሰቡም ነው። ግን ሽጉጡስ? ቀና ብለው አፈ ሙዙን ተመለከቱት።

"ተነሳ!" አሉ አባ ፊንሐስ። "ተነሳ!"

አባ ዲዮላ ተነስተው ቆመ።

"እሱ ዘንድ ተቀመጥ!" ሲጻራ ሽጉጧን በአባ ዲዮላ አናት ላይ እንደነጣጠረች ታናዝዛቸው ጀመር።

"መስቀሉን ለምንድን ነው ይህን ያህል ያፈጠጥክበት?....ስለ መስቀሉ ምን የምታውቀው ነገር አለ?"

"አያውቁም መቼም አልልም። ሳያውቁትማ አያስሩትም መቼም። መስቀሉን! ይህን! ከእኔ የበለጠ እርስዎ ሳውቁት ቀርተው ነው?" በዚህ መስቀል ምስጢር ምክንያት አባታቸውን እንደ ገደሉ ትዝ አላቸው አባ ዲዮላ።

"ይበሉ አባ ፊንሐስ ሽጉጡን ይመልሱትና እንነጋገር።"

"እሺ እንነጋገር" አለች ሲጻራ። ስለዚህ መስቀል ምስጢር የማወቅ ጉጉቷ እየናረ መጣ። ይህን ሰው በመጀመሪያ በኃይል ሳይሆን በጥበብ የመስቀሉን ምስጢር ለማውጣጣት ወሰነች።

"ሴት ነሞት ወንድ ግን ?"

"ሴትም ወንድም አይደለሁም። አሁን ሁለት ምርጫ ልስጥህ። ያየኸውን ነገር ለማንም መናገር አትችልም።የእኔ ሴትነት ወይም ወንድነት እያገባህም። ከተናገርክ ደሞ በህይወትህ ፈርደህ መሆን አለበት።"

"የኖርኩት ሲሲሊ ውስጥ ነው። በአሜርታ ህግ ሰር ነው ዕድሜዬን የገፋሁት"

"ምን ለማለት ነው....."

«አሜርታ አይቶም ሰምቶም ዝም የማለት ህግ ነው። ይህን በልሴ እይዘዋለሁ። የእርስዎ ሴትነት ወይም ወንድነት ለእኔ እያስጨንቀኝም። ይልቅ በአንድ ነገር እንስማማ። የመስቀሉን ምስጢር ለጋራ እናድርግ እኔም የእርስዎን ሴትነት ወይም ወንድነት ለማንም አልናገርም። አንድ ነገር ተረድቻለሁ። ይህን መስቀል ከያዙ ወደዚህ ገዳም የመጡበት ምስጢር ግን አልገባኝም። እኔም እርሰዎም እዚህ ገዳም የመጣነው ፅድቅን ፍለጋ እንደላሆነ ተረድቻለሁ። አሁን እዚህ ገዳም ውስጥ ምን እፈልግ ይመስልዎታል? ፅድቅ? አይደለም። እኔ መፅደቅ አልፈልግም። ልፅደቅ ብል እንኳ የምፀድቅበት ምክንያት የለም። እዚህ ገዳም ውስጥ የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህን መስቀልና የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ብቻ ነው። መስቀሉን በእርስዎ እጅ ገባ በእኔ ምንም ማለት አይደለም። እርሰዎ መስቀሉን ይዘዋል። እኔ ደግሞ በውሃው ውስጥ ጠልቆ የሚቆፍርና በኮምፒውተር ትዕዛዝ ብቻ የሚቆፍር ጠላቂ ኤክስካቫተር-ዶዘር አለኝ። የሰጠመውን መርከብ በዚህ አይነት ትብብር ለሁለታችን ብቻ ማድረግ እንችላለን።" በዚህ ስምምነት የሰጠመውን መርከብ ካወጡ በኃላ ሴትም ትሁን ወንድ በአፍጢሚ እንደሚደፋት እርግጠኛ ነው።

ሲጻራ ምንም ሊገባት የቻለ ነገር የለም። አለማወቋ እንዲንፀባረቅባት ግን አልፈለገችም። "የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ደግሞ ለምንህ ነው?" አለች ገርሟት። ከመስቀሉ ጋር የሚያያዘው ነገር ይኖር ይሆን? መጠየቅ እንደለባት ወሰናለች።

"መጀመሪያ በደንብ እንተዋወቅ። እኔ ዲ.ጆላ እባላለሁ። እርስዎስ አባ ፊንሐስ እይደሉም ግን? አባ ፊንሐስ ቢሆኑም ምንም ማለት አይደለም በእርግጥ። እኔ ቂመኛ ሰው አይደለሁም። ያለፈው አልፎአል። ካለፈ በደል ያሁኑ ይቅር መባባል ይበልጣል። ቂም ያጠቆረው ደም ሲጠራ ብዥታ ያጨለመው የጋራ ራዕያም አብሮ ይጠራል። ሰዎችን በጠላን ቁጥር ራሳችንም በዛው ልክ

እንጠላለን።..... ቂም ቁዋጥረን ከኖርነው መቶ ዓመት በፍቅር የዋልነው አንድ ቀን ይበልጣል። ይቅር ከመባባል የሚገኘውን ትርፍ የሚተካ የለም። አባ ፊንሐስ። ይቅርታ ልብ ላይ እንጂ መሬት ላይ አይወድቅም። ይቅርታ ያድርጉልኝ አባ ፊንሐስ? "

"አባ ፊንሐስ አይደለሁም አልኩህ እኮ።"

"እንግዲያ ማን ነሞት?" ወለሉ ላይ ወደ ወደቀው የሴት መታጠቂያ ተመለከተ። እስከ አሁን ልብ አላለውም ነበር። "ሲጻራ ፊንሐስ" የሚል ስም ተፅፏል። መታወቂያው ላይ የአንጥረኛው ፊንሐስ ልጅ መሆንዋን ተረዳ። ግን በቀሉን ወደ ውስጥ ለጊዜው መዋጥ እንዳለበት ወሰነ። የአባቷን ፊት ገፍፋ ፊትዋ ላይ እንዳጠለቀችው ገብቶታል። እሷም እንደሱ ለዚህ መስቀል ብላ አባቷን እንዳረደች ጠረጠረ። ግዴለም እሱም የሚፈልገውን ከወሰደ በሁዋላ እንደሚያርዳት አረጋገጠ። እስከዚያ ግን ታማኝ ለመምሰል መጣር እንዳለበት አምኗል። ፈገግ አለ አይኑን ከመታወቂያዋ ላይ ነቅሎ።

"አብረን ብዙ ነገር መሥራት አለብን ማለት ነው። አባቶቻችን ለቂም ተፈላልገው ይሆናል እኛ ለፍቅር ብንፈላለግስ?" አለ ዲ.ጆላ። "ሁሉን ነገር በምስጢር ይዘን ወደፊት እንጓዛለን። የኋላውን ወደኋላ ትተን። የአባትሽንና የአባቴን ነገር ወደኋላ ትተን እኔና አንቺ አብረን ለዚህ ነገር መስራት እንችላለን።"

"የጠየኩህን መልስልኝ ። የንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብን አፅም ለምንህ ነው የምትፈልገው?"ዲ.ጆላ ሁሉንም ነገር ተራ በተራ ተረከላት። ስለ ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ አፅም ምስጢርና ስለ ግማደ መስቀሉ ውስጣዊ ካርታ ሁሉን ዘረዘረላት። አንድ ጥያቄ ስትጠይቀው ግን ክው አለ ዲ.ጆላ። ደነገጠ።

"የንጉሡን አፅምስ አገኘህ እንበል። ግን ጥይት እንደ ማያስመታ በምን ላይ ትሞክረዋለህ? ከአፅሙ ቅንጣቢ በእንጥትህ ከአሠርክ በኃላ አፅሙ ጥይት እንደማያስመታ መሞከር አለብህ። አለበለዚያ ..... ማን ነበር ያልከኝ? የማፍያውን ስም?"

"ዶን ሞርሞርዲኖ።"

"የሞርሞርዲኖን ሰዎች ጥይት እንደማያመታህ እርግጠኛ ሆነህ እንዴት ትፋለማቸዋለህ?"

"መጀመሪያ አፅሙን ላግኝ።"

"ከዛስ?"

"በእንጥቱ አስረዋለሁ።"

"ከዛስ?"

"እንቺ በሽጉጥ....."

"እሞክርሃለሁ። ከሞትክ ግን የለሁበትም።"

"ውይ!..... .....ይህማ የማይሆን ነገር ነው። መሞትማ አልፈልግም"

"ታዲያ በምን እናረጋግጣለን?"

"በእንስሳ እንሞክረዋለና!"

"እ..ህ! ለሰው ብቻ የሚሠራ ከሆነስ?"

"ውይ! ልክ ነሽ። ይህ ነገር ቢቀርብኝ ይሻላል።"

"አዎ ይቅርብህ። ይልቅ አብረን ከሠራን ሁሉንም ነገር በእኛ ቁጥጥር ሥር እናደርገዋለን። ጥይት አተኩዋኩስ አለማምድህለሁ። ሞንቅላትህን ካለማመድከው ከአስማትም በላይ ነው።"

"እና እቅዱን ንገሪኛ! አንቺ ለምንድን ነው ወደዚህ ወደ ወንዶች ገዳም የመጣሽው?"

"እየውልህ መጀመሪያ በዚህ ደሴት ውስጥ ወደ ሚገኘው ዋሻ የምንገባበትን መንገድ እንፈልጋለን። ከዛ ዋሻውንና በዋሻው ውስጥ ያለውን በቁጥጥር ሥር ካደረግን በሁዋላ ወደሰጠመው መርከብ ፊታችንን እናዞራለን። ካርታው በእጃችን ነው። ይልቅ መጠንቀቅ ያለብህ ይህ ምስጢር ከአፍህ እንዳይወጣ ነው። ሴት መሆኔን ካወቁ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ከዚህ ገዳም እንደሚያስወጡኝ አስብ። ከዚህ የበለጠ አደጋም አለው!"

"ተያቸው ባክሽ!" አለ ዲዎላ ባዶ ድዱን ግልጡጥ እርጉ። "በወንዶች ገዳም ውስጥ የሚኖሩ መነኩሳት ልባቸው በሴቶች ገዳም ውስጥ ነው። ወሲብን ሽሹት! ዝሙትን ሽሹት! ግን....ወሲብን በመሸሽ ማምለጥ አይቻልም። ወሲብ አብሮን የተጠፈጠረ ነገር ነው። ወሲብን በሸሸነው ቁጥር የበለጠ ይቀርበናል። ወሲብ ሁሌም ከብልታችን ጋር ተጣብቆ በሄድንበት ሁሉ ይከተለናል።"

"እሱ ራስ ምታቴ አይደለም" አለች ሊጻራ። "መፍጠን አለብን። ከሥድስት ቀናት በፊት ሁሉም ኦፐሬሽን መጠናቀቅ አለበት። ሞንቅላቱ ላይፈጸዳ....."

«የምኑ ሞንቅላት?»

«ተወው....ረጅም ታሪክ ነው....»

፳፩

የኢንጅነሩ ህያው አስከሬን ወደ ዴርቶጋዳ ከገባ ከስምንት ቀናት በኋላ የሞቀው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ተዘጋጀለት። በዋናው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የዴርቶጋዳ አባላት በሙሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። ቲያትር ቤት የሚመስለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ የመድረኩ ቀያይ መጋረጃዎች ሲገለጡ በነጩ ስክሪን ላይ ሳይንቲስት ኢንጀነር ሻጊዝ የሰራቸው ሥራዎች በፊልም መታየት ሲጀምሩ አባ ዝንበሩ ወደ መነጋገሪያው ሳጥን እያመሩ ነበር። ከኢንጅነር ሻጊዝ ሥራዎች መካከል በናሳ ውስጥ የፈጠራ ባለቤትነት ያስገኙለት ሁለት መነኩራኩሮች እና በናሳ የማምጠቂያ ማማ ወደ ህዋ የሚመጥቁ መነኩራኩሮችን የሚያሳየው ፊልም ቆሞ አባ ዝንበሩ ንግግራቸውን ቀጠሉ።

«የተከበራችሁ የዴርቶጋዳ አባላት ከ፲መታት በፊት ይህን ዋሻ መቆፈር ስንጀምር ይህን ያህል ዘመናዊ የምርምር ማዕከልና የኢትዮጵያ ምርጥ ምርጥ ሳይንቲስቶች የሚሰባሰቡበት ተቋም ይሆናል የሚል ህልም የለንም ነበር። ግን አንድ ጥሩ ነገር ለማድረግ ለሀገራችን ተመኝተንላት ነበር። ቀስ በቀስ ይህን ለማየት ታደልኩ። ዋሻውን ስቆፍር እየተጋረጡ ያስቸገሩኝ አለቶች ለካ አንድ ነገር እያስተማሩኝ ነበር። የኢትዮጵያ አለት የምትሆንዋትን እናንተን በነዚህ አለቶች ላይ እንደማቆም እየስተማሩኝ ነበር። ተመኘሁ፣ አገኘሁ። ከዚህ በላይ የምመኘው ነገር የለኝም ። በአለም ዙሪያ እውቀታችሁንና ጉልበታችሁን ወዳችሁ ሳይሆን ተገዳችሁ ስትበዘበዙ የነበራችሁ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ! ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን ቴክኖሎጂ ገንብታችሁ እንደምታስረክቧቸው አንዳችም ጥርጥር የለኝም።» ጭብጨባው አስተጋባ።

«ከኢራቅ፣ ከኢራን፣ ከራሺያ፣ ከጃፓን፣ ከእስራኤል፣ ከቻይና፣ ከኩባ፣ ከአሜሪካና ከግብጽ ምስጢራዊ የምርምር ጣቢያዎች የምታገኙትን እንክብካቤና ገንዘብ ትታችሁ ኋላቀር ሀገራችሁን ለመረዳት ከአለም ዙሪያ የተሰበሰባችሁ የዴርቶጋዳ ሳይንቲስቶች ዛሬ ደግሞ እናንተ ከመጣችሁበት አመጣጥ ለየት ባለና በረቀቀ መንገድ ከሥናችሁ ሆኖ ሀገሩን ለመገንባት ለመጣውና እስከ አሁንም በገንዘቡ የዴርቶጋዳን ዘመናዊ መሣሪያዎችና የረቀቁ የቴክኖሎጂ ማሽኖች ሊያስገባልን ለቆየው ለእውቁ የአለማችን የህዋ ሳይንቲስት ለናሳው የእኛ ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ እጅጉ አክብሮታችሁን ትገልጹለት ዘንድ ንግግር እንዲያደርግ ጋብዙልኝ አመሰግናለሁ።»

ጭብጨባው ጋብ ሲል ወደ መነጋገሪያ መድረኩ የወጣው ኢንጅነር ሻጊዝ ንግግሩን ቀጠለ። «.....እስከ አሁን ከሞት ላንቃ

ውጥቼ ከ...ካከላችሁ ለመገኘቴ እርግጠኛ አይደለሁም ነበር። አሁን ግን እርግጠኛ ሆኛለሁ።» አለ በደስታ ተፍለቅልቆ።

«እ....እኔን ለማዳን ያደረጋችሁት ጥረት አንድ ነገር እንድናገር እየገፋፋኝ ነው። ከአሁን በኋላ መዋሸት እንደሌለብኝ ይሰማኛል። እውነቱን ስነግራችሁም የምታደርጉብኝን ሁሉ ለመቋቋም ተዘጋጅቼ ነው።» አቀረቀረ።

በትካዜ የተዋጠ ፊቱን ሲያዩ ሁሉም ቀጥሎ የሚናገረውን ለመስማት ቋመጡ።

«እኔ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለሁም።» መልሶ አቀረቀረ። ከባድ ድንጋጤ በአዳራሹ ላይ ወደቀ። ሁሉም እርስ በእርስ በብዥታና በድንጋጤ ተያዩ።

«እና አንተ ማን ነህ?.....» ዶ/ር ሚራዥ ወደ መድረኩ በክራንቹ እየተመረኮዘ ወጣ።

«እኔ.....» ድምፁ በፅንባ ታነቀ።

«እኔ.....ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ አጦት ስንከራተት ኑሬ በኋላ በብዙ መከራ ወደ አሜሪካ የሄድኩ አንድ ተራ ሰው ነኝ። እንደ ኢንጀነር ሻጊዝ ታዋቂ ሳይንቲስትም አልነበርኩም» ግንባሩ ላይ ጭርር ያለ ላቡን ጠርጎ ንግግሩን ቀጠለ። «አሜሪካ ውስጥ በገባሁ በአምስተኛው አመት ሲ.አይ.ኤ መለመለኝ። ሰፊ ስልጠና ከወሰድኩ በኋላም በሰርጀሪ የኢንጅነር ሻጊዝን ፊትና መልክ እንድመስል ተደረገ። ድምፄም የእሱን እንዲመስል በቀዶ ጥገና ተስተካከለ። ከዛ በኋላ ለስድስት አመታት የኢንጅነሩን ታሪክ፣ ሥነ ልቦና እና ከቤተሰቦቹና ካንዳንድ ከሚያውቃቸው ሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ውይይቶች ሳጠና ኖርኩ። በተሰይ በ1998 ዓመተ ምህረት ኢንጅነሩ ሙሉ በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እና ወደ ፖለቲካዋ መስመጡን ተከትሎ ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገሮች ስላጠመዱት ለመሰወር ሲባል እኔን በመግደል ሞቷል ለማለት ወሰኑ። እኔም በገና ዋዜማ ወደ ቤተሰቦቹ ሄጀ ከልጆቹ ጋር የቅርጫት ኳስ እየተጫዎትኩ እንድወድቅ ተደረኩ። ተዝለፍልፌ ከወደኩም በኋላ ወደ ሰሜን አውስቲን የህክምና ማዕከል ተወሰድኩ። ለቤተሰቦቼ ብዙ ገንዘብ በባንክ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ የተስማማሁት ለመሞት ነበር። ከቀዶ ጥገናው በኋላ እኔን በማያሰቃይ መልኩ እንደምገደል ቃል ተገብቶልኝ ነበር። ቦኋላ ግን መጥታችሁ አዳናችሁኝ። ወይ ፈጣሪ!....እኔን ሊያድን ማን ይመጣ ነበር!? ዳንኩ! አመለጥኩ!....ከሞት መንጋጋ አወጣችሁኝ። ሁሁ!....How can I believe it!?...ዳንኩ!.....አመለጥኩ...» መቀባጠርና መድረኩ ላይ በደስታ መዝለል ጀመረ። እንደ ህፃን አረገው። ፈነጠዘ።

«.....እርግጠኛ ነህ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለህም?!.....» ዶ/ር ሚራዥ በንዴት ጡፎ የለበሰውን ሸሚዝ አወለቀበትና ጀርባውን

ገልጦ ማየት ጀመረ። ከጀርባው «ዴርቶጋዳ» የሚለው ንቅሳት እንደ ሌለ በማስተዋሉ በእርግጥም ኢንጅነር ሻጊዝ እንዳይደለ አመነ። ፊቱና ቁመናው በተሰይም የራሱ ላይ በራ ቁርጥ ጣል ኢንጅነር ሻጊዝን ስለሚመስል ማንም ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለም የማለት ድፍረት አይኖረውም።

«አምን። ይህ ሰው ኢንጅነር ሻጊዝ አለመሆኑን አረጋግጫለሁ።ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለም።»አለ ዶ/ር ሚራዥ ተሰፋው በሰለለ ድምፅ።

«አልነገርኳችሁም እኔ ኢንጅነር ሻጊዝ አይደለሁም። እኔ ማታያስ ማሞ ነኝ። ዘመዶቼን በተሰይም በችጋር ስትጠበስ የኖረችውን እናቴን ከድህነት ለማላቀቅ ራሴን ለሞት አሳልፌ ሰጥቼ ነበር። አሁን ግን ከሞት አዳናችሁኝ። ስለዚህ ባሪያችሁ አድርጋችሁ ልታሰሩኝ ወይም ይህን የሚያህል ሌላ ዋሻ ልታስቆፍሩኝ ትችላላችሁ። መንኮራኩር ዲዛይን የሚያደርግና እንደ ኢንጅነር ሻጊዝ በቴክኖሎጂ የበለፀገ ጭንቅላት ግን የለኝም። ፊቴ እንጂ ጭንቅላቴ የእሱን አይደለም። ቅጂው ሻጊዝ ነኝ። ከሻጊዝ ላይ የተቀዳሁ። ፎርጅዱ ሻጊዝ!.....ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ። ከታሪካችን ጠባሳዎች አንዱን አስታውሱ። ኢትዮጵያ ውስጥ በረሀብ ምክንያት እናት የልጇን ሥጋ በልታለች። ረሀብ ክፉ ነው። ያበላላል።እንኪንስ አንድ ሰው ሀገር ያሸጣል። እኔም እንደናንተ ሀገሬን እወዳታለሁ። ግን ድህነቷ ራሴን ለሞት አሳልፌ እንድሰጥ አደረገኝ። አሁን ግን አዳናችሁኝ። ባትፈርዱብኝ የምለምናችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው። ሀገሬን እንድረዳት እድል ስጡኝ። ከእናንተ ጋር ለለውጥ ሳልደክም አሰራለሁ። ተራራም ቢሆን ለመናድ ዝግጁ ነኝ!»

«ኢንጅነሩ የት ነው ያለው አሁን?» አባ ገ/ንበሩ ወደ መድረኩ እየተንገዳገዱ ወጥተው በቁጭት አንባረቁበት።

«ኢንጅነሩ የት ነው?!....ሻጊዝ የት ነው?!.....» አዳራሹ በሙሉ ተንጫጫ።

«ኢንጅነር ሻጊዝ በናሳ ዋና መስሪያ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ የምድር ውስጥ የምርምር ጣቢያ የሆነ ነገር እንዲሰራ በግዴታ ታግቶ ሳለ እኔ እየሄድኩ ስለቤተሰቦቼ፣ ከቀድሞዋ አስራኤል አሜሪካዊት ሚስቱና ከልጆቹ ጋር የምግባባበትን መንገድ በግዴታ እየተጠየቀ ሳጠና እዛ ውስጥ አይቼው ነበር። ቦኋላ ግን ከዛ አውጥተው የት እንዳደረሱት አላውቅም። » ሁሉም በሃዘን ኩምሽሽ ብለው ተመለከቱት። ታላቅ ሀዘን ወደቀ። ዝምዝምታ። ከዚያ ደግሞ ....ጉምጉምታ.....

ሽሮ

በድቅድቁ የጨለማ ግሣት ውስጥ ወደ ዕቃ ቤቱ ግቢ በግንቡ ላይ ተንጠላጥለው ሲገቡ የዕቃ ቤት ጠባቂው የመጠበቂያ ቤት በር ተከፍቶ ነበር። የመቅረዙ ብርሃን ዕቃ ቤት ጠባቂውን አጋልጧቸዋል። ትልቅ የብራና መፅሐፍ ዘርግተው አፋቸውን ሳያንቀሣቅሱ እያነበቡ ነው።

ጨለማው ውስጥ ተወሽቀው የመነኩሴውን እንቅስቃሴ የሚከታተሉት ዲዮላና ሲጳራ በሹክሹክታ እየተነጋገሩ ነው። "አየሽ አላልኩሽም!?" አላ ዲዮላ።

«አንቺ አትበል አላኩህም? እርሰዎ በል እኮ ብዬህ ነበር። አሁንም ደግሜ አስጠነቅቅሃለሁ አባ ፊንሐስ እንጂ ሲጳራ ብለህ እንዳትጠራኝ። አባ ፊንሐስ ነኝ በቃ።"

"እሺ አባ ፊንሐስ። አላልኩዎትም? መነኩሴው የያዛቸው መዓት ቁልፎች ይታዩዎታል? ብዙ ቁልፎች ናቸው። እዚህ ገዳም ውስጥ የሚከፈቱ በሮች ግን በጣም ጥቂት ናቸው። ስለዚህ እኒህን መነኩሴ....." ንግግሩን አቋረጠ መነኩሴው የሚያደርጉትን ተመለከተ።

መነኩሴው የወለሉን ቀያይ ምንጣፎች ገልጠው ወለሉን ማጭድ በመሰለ ቁልፍ ከፈቱት። ወለሉ ላይ በከፈቱት በር ቁልቁል ገቡ። አባ ፊንሐስ የሩቁን አቅርቦ በሚያሳየው መነፅራቸው የዕቃ ቤቱ ጠባቂ ከወለሉ በታች የገቡበትን በር ሲያዩ በረጅሙ ተንፍሰው አባ ዲዮላን ጎሰሙአቸው። ሁለቱም እንደነብር ተስፈንጥረው ወደ መጠበቂያው ቤት ገቡ። የመቅረዙን መብራቶች አጥፍተው ጠባቧ ቤት ውስጥ ትንፋሻቸውን አጥፍተው ተቀመጡ።

ወለሉ ላይ በተከፈተው በር ቁልቁል የወረዱት መነኩሴ ተመልሰው ወደ መጠበቂያው ቤት ወለል ብቅ ሲሉ የመቅረዙ መብራቶች በመጥፋታው ሊያዩ ያቻሉት ነገር የለም። ወዲያው አንገታቸውን የሆነ ጠንካራ እጅ ፈጠረቃቸው። አፋቸው ውስጥ ደግሞ ወፍራም ጨርቅ ተጎደጎደ። መተንፈስ ያቻሉበት ቅፅበት የለም ነበር። ተዝለፈለፉ።

አባ ዲዮላ የዕቃ ቤት ጠባቂውን ሞት እንዳረጋገጡ የመነኩሴውን አንገት የፈጠረቁበት ጠንካራ ክንደቸውን ከመነኩሴው አንገት ላይ አነሱ። ህያዎታቸው የተጠናቀቀውን መነኩሴ በቀዩ የወለሉ ምንጣፍ ጠቅልለው ወደ ጎን ቧድናቸውን ካስቀመጡት በሁዋላ የመጠበቂያውን ቤት በር ከውስጥ ጠርቅመው ዘግተው የመቅረዙን ሻማዎች ለኮሱላቸው። ከመነኩሴው እጅ በመክራ

ከተፈለቀቀው የቁልፍ መያዣ ማዕተብ ውስጥ ያሉትን ቁልፎች በእጃቸው ካስገቡ በሁዋላ በተከፈተው የወለሉ በር ቁልቁል ወረዱ።

"መመለስ አለብህ።" አለች ሲጳራ ቱቦ በሚመስለው የዋሻው ውስጥ መንገድ ላይ ቆም ብላ። " እንዴት?" አለ ዲዮላ እርምጃውን ገታ አድርጎ።

"የዕቃ ቤት ጠባቂውን እኮ ገድለናቸዋል።"

"እኮ?"

"ማሸሸ አለብህ።"

"ምን? "

"ተመለስና በድናቸውን አሸሽ።"

"አንቺስ?"

"እኔ ወደ ዋሻው እገባለሁ።"

"ወደየት ነው የማሸሸው?"

"ቅበራቸው አለበለዚያ.....?"

"እሺ ቁልፉን አምጭው!"

"የትኛውን ቁልፍ?"

"መስቀሉን... የሰጠመውን መርከብ ቁልፍ።"

"እሱንማ አልሰጥህም። እንደተነጋገርነው ፊታችንን ወደ ሰጠመው መርከብ ለመመለስ መጀመሪያ ሰው አልባዋ ደሴት ላይ ተቅምጦ የላከህን ጣሊያናዊ ልታስወግደው እንደሚገባ ተነጋግረናል። ሁለት ተልእኮዎችን ማጠናቀቅ አለብህ በመጀመሪያ። የመነኩሴውን በድን አጥፋ-- አንድ። ሞርሞርዲኖን ደምስስ-ሁለት። እኔም እዚህ ዋሻ ውስጥ ሥራዬን ልጨርስ። ከዛም ተገናኝተን የሰጠመው መርከብና በውስጡ ያለው የእኛ ይሆናል።"

ዲዮላ ወደ መጣበት ተመለሰ። የወለሉን በር ዘግቶ በቀዩ ምንጣፍ የተጠቀለለውን የመነኩሴውን በድን ተሸክሞ ከወጣ በሁዋላ የመጠበቂያው ቤት በር ቆልፎ የዕቃ ቤቱን ግቢ ለቆ ወጣ።

ሲጳራ ማጭድ በመሣሠሉት ቁልፎች የዋሻ ውስጡን በሮች እየበረገደች ስትገባ ዋሻው በአደጋ ጊዜ ጥሪ ድብልቅልቅ አለ። ወዲያው አውቶማቲክ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች ዙሪያውን ከበቧት ሁሉም ጭንቅላቷ ላይ አነጣጥረዋል። ሁለት እጆችዋን ወደ ላይ አንጨፍርራ እጇን ሰጠች። እጆችዋን በሰንሰለት የፍጥኝ አሰሯትና እያዳፉ ቁልቁል ወደ ሚያወርደው አሳንሰር አስገቧት።

የአሳንሰሩ በር ተከፍቶ ካስወጧት በሁዋላ ወደ አንድ ጨለማ ክፍል አስገብተው ዘጉባት።

ከቆይታ በሁዋላ ሁለት ሰዎች ወደ ጨለማው ክፍል እንደገቡ ጨለማው ክፍል በብርሃን ተሞላ። የሁዋሊት እጆችዋ ታሰረው ወለሉ ላይ እንደተቀመጠች የገቡትን ሁለት ሰዎች አፈራርቃ ተመለከተቻቸው። አንደኛውን ወዲያው አወቀቻቸው። አባ

ዝንበሩ ናቸው። ሁለተኛው ግር አላት። አዲስ ፊት አልሆነባትም። በጣም አፍጣ ተመለከተችው። የምታውቀው ይመስላታል። ‹የት ነበር ያየሁት?› በፍጥነት ማሰብ ጀመረች። አዕምሮዋ ወደሁዋላ ተፍጠነጠነ። እንዴት ሊሆን ይችላል? ለዘመናት ስትፈልገው የኖረችው ሰው እዚህ ዋሻ ውስጥ ምን ሊሰራ መጣ? ሚራዥ ሊሆን ይችል ይሆን እንዴ? በፍፁም ሊሆን አይችልም። ከፊቷ የቆመው ጎልማሳ በውስጧ ለዘላለም የኖረው ሚራዥ ምስላቸው ይቀራረባል። በዚህ ሰው ውስጥ ልቧን በፍቅር ሲያደማ የኖረው ሚራዥን አየችው ።

አባ ዝንበሩ ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደዱ ሲዞሩአት አሷ ግን ዓይኗን ካየችው ጎልማሳ ላይ ለመንቀል ተስኗታል።

"አባ ፊንሐስ!" አሉ አባ ዝንበሩ ለረጂም ዲቂቃዎች እየተንጎራደዱ ከቆዩ በሁዋላ "ወንጀልህ ሁልቆ መሳፍርት ሊኖረው አልቻለም። የተሰወጥክና ንስሐ የገባህ መስሎኝ በዚህ ገዳም እንድትኖር ፈቅጀልህ ነበር። አሁን ግን ሳይፈቀድልህ በጉልበት ወደዚህ ዋሻ ሰብረህ ገባህ!"

«አባ ፊንሐስ ናቸው እንዴ?» ሚራዥ እጁን ወደ ሽንጡ ላከው።

«አዎ ናቸው። አባ ፊንሐስ!» ሽጉጡን ከሽንጡ ልጦ ግንባራቸው ላይ አነጣጠረው። "ሲጳራ የት ናት?" አንባራቀባቸው።አባ ፊንሐስ ግን ምላሽ ሳይሰጡት እስከአሁን አፍጥጠው እየተመለከቱት ነው።

"አባ ፊንሐስ ..... ትዝ አልኩዎት? እኔ ሚራዥ ነኝ። ሲጳራን የት አደረሷት?"

ሚራዥ ከንፈሩ ተንቀጠቀጠበት። "ምላጩን ከመሳቤ በፊት ያለችበትን ይንገሩኝ።"

አባ ፊንሐስ ቡዝዝ ብለው እያዩት በዚያው ከዓይናቸው ዕንባ ፈሰሰ። "ሚ.....ሚ...ሚራዥ በህይዎት አለህ? የኔ ፍቅር አለህልኝ እውነት? ይህን ያህል ዘመን ስፈልግህ ነበር እኮ የኖርከት።"

"የምጠይቅዎትን ብቻ ይናገሩ። ሲጳራ የት ናት?"

"አይ.... እንዲህ ናቸው ድሮም። የተጠየቁትን ሳይሆን.... መናገር የሚፈልጉትን ነበር ድሮም የሚመልሱት። ያ ጠባያቸው ተጠናክሮ ቀጥሏል። አጭበርባሪነታቸውም ንሯል። እንዲህ ናቸው አባ ፊንሐስ" አባ ዝንበሩ በመሰላቸት መንፈስ ተወራጩ።

"እኔ አላምንም! ሚራዥ ብዙ ጊዜ ተስፋ ቆርጬ ነበር። በውስጤ ያረገዝኩትን ምስልህንና ፍቅርህን ተሸክሜ እኖራለሁ ብዬ እንጂ በአካል አንተን የማግኘት ተስፋዬ ተሟጦ ነበር።"

"ምንድን ነው እያወሩ ያሉት?"

"ሲጳራ ነኝ። ሚራዥ.... እኔ ነኝ ሲጳራ። እያየውህ ነው። አንተ ግን ልታየኝ አትችልም። በአባቴ ፊትና በአባቴ ወንጀል ተሸፍኖለሁ" ሲጳራ ይህን ስትናገር አባ ፊንሐስነቷን ዘንግታው ነበር። ድምፅዋ እንደተቀየረ ታውቃለች። ፊቷም ድምፅዋም የአባቷ ነው። በምን ሊለያት ይችላል? እሷነቷን በምን ሊያረጋግጥ ነው? አንድ ሀሳብ መጣለት።

"እመነኝ ሚራዥ። እኔ ሲጳራ ነኝ!..... እኔን ብትረሳኝ ስጦታህን አትረሳውም። የኸውና መስቀሉ በልጅነታችን ደሴት ላይ ያሰርክልኝ ባለጉጥ መስቀል ይኸውና። የእጄን ሰንሰለት ፍታልኝና ላሳይህ።"

የኋሊት የተጠፈነጉ እጆችዋን ከሰንሰለቱ ነፃ ሲያደርግላት የለበሰችውን የምንኩስና ቀሚስና መደረቢያ አወላልቃ ዕርቃኗን ቆመች። በጡቶቿ መሃል በወረደው ሃብል ላይ የተንጠለጠለውን ባለጉጥ መስቀል ሲያይ ቅፅበታዊው ትዝታው እንደ መብረቅ ብልጭ አለለት...መስቀሉን ሲያሰርላት...አባ ፊንሐስ እያስጮሁ ሲወስዷት...

ከላይ ፊቷን አየ። የጢማም መነኩሴ ፊት። የወንድ ፊት። ከአንገቷ በታች ደግሞ የተዋበች እንስት። ዕድሜ ልኩን ሲፈልጋትና ሲያስባት የኖረችው ሲጳራ ልትሆን? ግራ ተጋባ።

ሰኔ

ዲምላ የዕቃ ቤቱን ጠባቂ አስከሬን ተሸክሞ የዳጋን ደሴት ቁልቁለት ከወረደ በሁዋላ ወደቡ ላይ ቆሞ ጥቂት አሰላሰለ። የጣና ሐይቅ ማዕበል ከወደቡ ጋር ወደ ሚያጋጨው አሮጌ ታንኳ በድኑን እንደተሸከመ ገብቶ እየቀዘፈ ወደ ደሴቱ ምዕራባዊ አቅጣጫ አመራ። ከደሴቱ ምዕራባዊ አቅጣጫ አምስት መቶ ሜትር ያህል እንደቀዘፈ ታንኳው ላይ የጫነውን አስከሬን ወደ ሐይቁ ገፈተረው።

በደቅ ደሴትና በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት መካከል በጉረር ወደብ አቅራቢያ ባለችውና የደሀ ሰው መዳፍ ወደምታህለው ሚጢጢ ደሴት አሮጌውን ታንኳ እየቀዘፈ ሲደርስ ትንሽዋ ደሴት ሞቅ ደመቅ ብላ ነበር። ጨረቃዋ በደሴትዋ አናት ላይ ቆማ ቁልቁል ለደሴትዋ ብቻ የምታበራ ይመስላል። ከደሴትዋ ወደብ ጥግ ትልቁ የሞርሞርዲኖ ጀልባ እንደቆመ ነው። ዲምላ በዚህ ጀልባ ያለውን ጠላቂ ኤክስካባተር-ዶዘር ሲያስታውስ ጠላቂውን ኤክስካባተር-ዶዘር ለመንዳት በፓሌርሞ ወደብ አቅራቢያ ሲያደርገው የነበረው ልምምድ ትውስ አለው። ይህንን ጠላቂ ኤክስካባተር-ዶዘር ለማሰራት ሞርሞርዲኖ ያወጡት ወጪ እና የፈጁት ጊዜም ትዝ አለው። ወደቡን አልፎ ወደ ደሴትዋ ሲገባ በድንኳኖች ውስጥ ሳቅ ደምቋል። የሚንደቀደቀው ጀነሬተር ድንኳኖች ውስጥ ብርሃን ለሚፈነጥቁት አምፑሎች የብርሃን ምንጭ ከመሆኑ በቀር በዚህች ደሴት ሌላ የሚሠራ ነገር የለም ።

ሞርሞርዲኖ የሚጠባበቁት ነገር ቢኖር ዲምላንና ካርታውን ብቻ ነው። ካርታውን ብቻ እንጂ። በዘቦች ተፈትሾ ዲምላ መሆኑ ከተረጋገጠ በሁዋላ ሞርሞርዲኖ ወዳሉበት ድንኩዋን ተወሰደ። ጠባቂዎቹ አውቶማቲክ መሣሪያ ታጥቀው በተጠንቀቅ ይጠብቁታል። በሰፊው ጠረጴዛ ላይ በውድ የጣላያን መጠጦች የተሞሉ ብርጭቆዎች ተሸኮትኩተዋል። ከአሥር የሚበልጡ ሰዎች በጠረጴዛው ዙሪያ ተቀምጠው አልኮሉን እየተጎነጩ ይሳሳቃሉ።

ዲምላ ወደዚህ ድንኩዋን እንደገባ ሞርሞርዲኖ ከተቀመጡበት ተነሰተው በደስታ ተቀበሉት ። በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡት ሰዎች መሀል በዚህ ምሽት የመጣውን ባለስልጣን አስተዋወቁት። በጥቁዋቁር መነፅራቸው ውስጥ ሚመለከቱት የሚኒስትሩን የግል ጠባቂዎች በየተራ ገረመማቸው።

"ክቡር ሚኒስትር....." ብለው ሊያስተዋውቁት በውስጡ "ሚኒስትር ወይስ መንጥር?" ሲል አንሾካሾከ። «ይህ ሁሉ ተባይ እዚህች ደሴት ላይ አሰፍስፎ እየጠበቀ ያለው እኔን አይደል?

ለመቀራመት! ህ! አላይህለሁ እያንዳንድህ! ባሪያ ሆኜ መኖር ካልፈለክ በቀር ለዚህ ሁሉ ወፈሰማይ የሰጠመውን መርከብና በውስጡ ያለውን ሀብት ዓይኔ እያዩ አልሰጠውም።» በውስጡ ከራሱ ጋር ተማከረ።

ሞርሞርዲኖ በጠረጴዛው ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ከሚኒስትሩ በቀር በምልክት እንዲወጡ ካደረጉ በሁዋላ "ባሪያው! ስራህን ጨርሰህ መጣህ አይደል?" አሉት የተጎነጩትን ወይን እያጣጣሙ። ምላሳቸውን ከላይኛው ላንቃቸው ላይ ሲያላቅቁት እንደ ጅራፍ አጨኸው።

"አልጨረስኩም" አለ ዲምላ። "አንድ ነገር ይቀረኛል። አውቶማቲክ መሣሪያ።"

"ለምን?" አሉ ሚኒስትሩ ። "ለእሱ አትጨነቅ እሳት የሚተፋ መትረዬስ እሰጥሃለሁ።"

"አሁን ነው የምፈልገው። አሁን!" አለ ዲምላ እየተነሳ። "ጊዜ መፍጀት የለብንም።"

ሚኒስትሩም ተከትለውት ተነሱ። ሚኒስትሩ እየመሩ ደሴቷ ላይ ከመሸ ወዳረፈችው አነስተኛ ሄሊኮፍተር ወሰዱት። ሄሊኮፍተሯ ውስጥ የተቀመጠውን አውቶማቲክ መሣሪያ እያወረዱ "ይሄውልህ።" አሉት። "ምስጢሩን ጠብቀህ ልትጠቀምበት ትችላለህ።"

"የእጅ ቦንቦችም ያስፈልጉኛል።" አለ ዲምላ።

"ለምንህ?" አሉ ሚኒስትሩ። "ሶስተኛውን የዓለም ጦርነት ለመጀመር አስበሃል እንዴ?"

"የተከበሩ ሚኒስትር!?" አለ ዲምላ አውቶማቲኩን ጠመንጃ እያስተካከለ። "ይህ ለእኛ አራተኛው ወይም አንደኛው የዓለም ጦርነት ቢሆን አይደንቀኝም።"

ዶን ሞርሞርዲኖ ቡስኪ የጣና ሐይቁን ብጣቂ ደሴት በኢንቨስትመንት ሥም ሲሰፍሩባት የሰጠመውን መርከብ ምስጢር ለዚህ ሚኒስትር ለመንገርና እገዛ ለማግኘት ለምን እንደፈለገ ዲምላ ያውቃል። ይህ ጉዳይ ወደ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ያልደረሰበት ምክንያት ለዲምላ ግለፅ ነው። በቤተ መንግሥቱ ዙሪያ የተጠመዱ አሳት የሚተፉ ከባድ መሣሪያዎች ይህ ምስጢር እዛ ቢደርስ ኖር ሞርሞርዲኖ ላይ ላለመርከፋከፋቸው ማንም እርግጠኛ አይሆንም። ግን...ሞርሞርዲኖ ሁሌም የሚሀሩትን ያውቃሉ። ከማን ጋር ምን መሥራት እንዳለባቸውም ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰው ናቸው። ይህን ሚኒስትር ለሽፋን የተጠቀሙት እቅመ ቢስ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። እቅመ ቢስ በመሆኑ ብቻም አይደለም ቅንጣት ታህል ሀገራዊ ፍቅር ስላላዩበት ነው። እቅመቢስና ቅንጣት ታህል ሀገራዊ ፍቅር ስላላዩበት ብቻም ሳይሆን በቀላሉ ሊጠመዘዝ የሚችል ሰው በመሆኑም ነው። ይህ ምስጢር

ካራት ኪሎው ሰውየ ዘንድ ደርሶ ቢሆን ኖሮ እንኳንስ እርሳቸው ወፎችና ዓሣ ጠልቀው የሚያወጡ አሞራዎች እንኳ ጣና ሐይቅ ላይ ማረፍ እንደማይችሉ አስቀድመው ያውቃሉ። እሳት የሚተፉት የአራት ኪሎ ከባድ መሳሪያዎች ጣና ሐይቅን ከበው እንደሚጠብቁ በባህርዳር የባህር ትራንዚት ወደብ ጥግ እስከ አሁን ሥራ ላይ ሳትውል የተቀመጠችው የመንግስት ጠላቂ መርከብ የጣናን ሆድ እቃ እንደምታስስ እርግጠኛ ነበሩ። እንዲያውም በባህር ዳር ወደብ አቅራቢያ ያለሥራ የቆመችውን ጠላቂ መርከብ ያዩ ጊዜ ልባቸው በአፋቸው ቱር ብላ እስክትወጣ ደንግጠው ነበር። ምስጢሩ የተደረሰበት መስሏቸው። ሲሲሊ ብዙ ያስተማረቻቸው ሞርሞርዲኖ ግን ይህ ሚኒስትር ለእነሱ ብዙም አስጊ እንዳልሆነ ለዲዎላ ነግረውታል።

ዲዎላ በእጅ ቦንቦች የተሞላውን ዝናር ከታጠቀና ዘመናዊውን አውቶማቲክ መሣሪያ ጥይት ካቃመው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሰማይ አንጋጦ ጨረቃዋን ተመለከተ። ሌሊቱ ከመገባደዱ በፊት ይህንን ለመጀመሪያ ጊዜ የግሉ የሆነውን ተልዕኮ ማጠናቀቅ እንዳለበት ወሰኗል።አውቶማቲክ መሣሪያዎች የታጠቁትን የሞርሞርዲኖን ጠባቂዎችና የሚኒስትሩን አጃቢዎች በየቦታው በዝግታ ቃኖቸው። ሁሉም በተጠንቀቅ ቆመዋል። እንዴት ሊጋፈጣቸው ይችላል? የልብ ምቱ ፈጠነ። የደም ዝውውሩ የቆመ መሰለው። አንዲት ጥይት ሳይተኩስ ጭንቅላቱን እንደሚበሳሱት እርግጠኛ ነው።

ወደ ዶን ሞርሞርዲኖ ቀርቦ "ሰዓቱ እየደረሰ ነው" አላቸው ባዶ ድዱን ግልጢጥ አድርጎ።

"የትኛው ሰዓት?"

"ሁሉምን ነገር በእጃችን የምናስገባበት። ይህ ሚኒስትር ግን....." አለ ዲዎላ በሰሆሳሳ። ሚኒስትሩን ዞሮ ለአፍታ በቆረጣ ተመልክቶ። ጠልያንኛ እንደማይሰማም ያውቃል። እያማጠ ከሚናገረው ሰበርባራ እንግሊዝኛ በቀር። "ባክህ ተወው!" አሉት ሞርሞርዲኖ "ስለዚህ ገርሼ ሚኒስትር አትጨነቅ። ብቻ ካርታውን በእጃችን እናስገባ። ሚኒስትሩ ጠመንጃ እንጂ ጭንቅላት የለውም። እዚህ አገር ጭንቅላት ያለው ሰው አይሾምም አላልከሀም? ያለነው አፍሪካ ውስጥ ነው። ሲያውም ከአፍሪካዊ፡ መናኛ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገዛህ ሕግ ሳይሆን ጠመንጃ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ከጠመንጃ በታች እንጂ ከህግ በታች አይደለም። የሲሲሊ ማፍያዎችና ካፖዲካፒዎች ሲሲሊን የሚገዟት ባልተባፈና በማይገረሰስ ህግ ሲሆን የኢትዮጵያ መሪዎች ደግሞ ኢትዮጵያን የሚመሯት ቡተፃፈና መሪዎችን በማያካትት ህግ ነው። ማንም አረኛ ሚኒስትር ቢሆን ግዴለኝም እኔ

ሞርሞርዲኖ! እንኳንስ ከዚህ ነፈዝ ሚኒስትር ከስንት ጅቦች መንጋጋ ውስጥ ስንት ነገር እንደነጠቅን ሲሲሊ ትመስክር።" ሞርሞርዲኖ በሹክሹክታ ሲናገሩ ቆይተው ሚኒስትሩ ወደነሱ ሲመጣ የዲዎላን ትከሻ ቸብቸብ እደረጉና ፀጥ አሉ። ዲዎላ መሬት ላይ እቃ የጣለ ይመስል አቀርቅሮ ሲያሰላስል ከቆዩ በኋላ ወደ ሞርሞርዲኖ ቀና ብሎ "በዚህች ደሴት ላይ ያለ ሁሉም ሰው ድንኳኑ ውስጥ ለሰብሰባ እንዲጠራ አፈልጋለሁ" አለ።

"ችግር የለም!" አጨበጨቡ ሞርሞርዲኖ። "ሁላችሁም ወደ ድንኳኑ ግቡ!" ሁሉም ድንኳኑ ውስጥ ገቡ። ሚኒስትሩና ሞርሞርዲኖ ብርጭቆአቸውን እንደገና ሞልተው ወይናቸውን መጎንጨት ጀመሩ። በዚህ ስብሰባ ለመካፈል በጠረጴዛው ዙሪያ ከተቀመጡት የቆሙት ብዙ ናቸው። ተሰበሰቡ እንጂ የሚነጋገሩበት ጉዳይ ምን እንደሆነ ማንም አያውቅም። ስብሰባው የተጠራበት ምክንያት ምን እንደሆነ የሚያውቅ ዲዎላ ብቻ ነው። ዲዎላ ጉሮሮውን ጠራረገ። ብቸኛዋ አንዲት ዓይኑ የተጨቀጨቀ በርበሬ መስላ ቀልታለች። አፉን ደም ደም አለው።

"አሁን የተሰበሰብንበት ምክንያት ....."

ጉሮሮውን አሁንም ጠራረገ። "ያልታደለች ትንኝ! ..እእእ!... ያልታደለች ትንኝ በተከፈተ አፍ ትገባለች!..... እእእ!....."

ሞርሞርዲኖ ከት ብለው ሳቁ። ሚኒስትሩም ሳቁን ለመጋራት ተንፈቀፈቁ። ዲዎላም ደሴቱን የሚያናጋ ሳቅ አመለጠው። ቀይ ባዶ ድዱን ሲያዩ ድንኩዋኑ ውስጥ ያሉት ሁሉም ሳቅ በሳቅ ሆኑ። ወዲያው ደግሞ ድርቅ አለ ዲዎላ። ሳቁን ገታው። "ይቅርታ ..... እእእእ! ....." ዲዎላ ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ እየጠራረገ ሲወጣ የሚኒስትሩና የሞርሞርዲኖ ሳቅ እላባራም ነበር። የወይኑ ዱቅዱቅታና የብርጭቆዎች ግጭት "ችርስ!" ከሚለው ቃል ተደባልቀው እየተሰሙት ራቅ ብሎ ወደ ድንኳኑ ዞሮ ቆመ።

ወዲያው ደሴቲ በከፍተኛ ፍንዳታ ተናወጠች። ዲዎላ የታጠቃቸውን ቦንቦች እየፈታ ወደ ድንኳኑ ወረወራቸው ከመሸገበት ቋጥኝ አድፍጦ የተቀባበለውን አውቶማቲክ መሣሪያ በእሳት ከሚጋየው ድንኳን ላይ አርከፈከፈው። ሞርሞርዲኖና ሚኒስትሩ ከጠባቂዎቻቸው ጋር የተሰበሰቡበት ድንኳን በእሳት ሲጋይ በእሳት ተያይዘው የሚወጡትን በጥይት መልቀም ጀመረ።

በዚሁ ቅፅበት ሚኒስትሩና ሶስት ሰዎች በአቅራቢያው ወደ ቆመችው ሄሊ ኮፕተር ሲሮጡ የሚኒስትሩ ኮት በእሳት ነበልባል ተያይዞ ነበር። ዲዎላ ከኋላቸው ከተኮሳቸው ጥይቶች መካከል አንዷ ከሚንስትሩ ኋላ ከሚሮጡት አንዱን አስቀረችው። አቃስቶ ሲወድቅ ሚኒስትሩ በእሳት የተያያዘ ኮታቸውን ላዩ ላይ ወርውረውበት ወደ ሂሊኮፍተሯ ገቡ። ዲዎላ በሚተኩሳቸው ጥይቶች የምትበሳሳው

ሄሊኮፍተር ተነሣችና ከአከባቢው ሸሸች። ካፍታ በኋላ ተመልሳ መጥታ ትንሽዋ ደሴት ላይ ጥይት መዝራት ጀመረት። ዲዎላ ቋጥኞቹ ውስጥ አድፍጦ ኢላማው ውስጥ እስክትገባ ጠበቃት። ኢላማው ውስጥ ግን ልትገባለት አልቻለችም። ወዲያውኑ ከሄሊኮፍተሯ የተተኮሰ ጥይት ግራ እጁን ሲቦተርፈው አቃስቶ ወደ ቋጥኙ ውስጥ ተንሸራቶ ገባ። በቀኝ እጁ ብቻ የያዘው አውቶማቲክ መሳሪያ በደመነፍስ ቋጥኙ ውስጥ ተንጣጣ። ሂሊኮፍተሯ ርቃ ከመሄዷ አንድ ገላው እንደግንድ የተለበለበ ሰው ምድር ለምድር እየተሳበ ዲዎላ ወደ መሸገበት ቋጥኝ መጣ። ዲዎላ አውቶማቲኩን መሣሪያ እየተሳበ ከመጣው ሰው ጭንቅላት ላይ አፈሙዙን ለገተው። በእሳት ተለብልቦና የተጠበሰ ሥጋ መስሎ የመጣው ሰው ዶን ሞርሞርዲኖ መሆኑን የለየው በመጀመሪያው ቃል ነው።

"ከዳህኝ አንተ ጥንብ ባሪያ!" ጥርሱን እንደሚናከስ ውሻ አገጠጠ። የተለበለበ ግንድ የመሰለው ሰውዬ ። "አንተ አህያ .... ከአፌ ቀምቼ እንዳላጎረስኩህ ..... ከ... ከ .. ከዳህኝ!.... ከ.... ከ..ከ ከዳህኝ ! አ.....አ አንተ ጥንብ ባሪያ!" ጥርሶቹን አፋጫቸው።

"ሁልጊዜ ጌትነት ዘለአለምም ባርነት የለም። ለተረኞች መልቀቅ ግዴታ ነው። ሃ! ሃ! ሃ!" ዲዎላ ተሳለቀ።

"እበላህለሁ!.. አንተ ባሪያ! እበላህለሁ!" ዶን ሞርሞርዲኖ ተስበው በጥይት የተመታውን የዲዎላን ግራ እጅ ነከሱት ።

"የጥቁር ሰው ሥጋ ይበላሉ እንዴ እርስዎ? ይቅርብዎት ያስታውከዎታል።" ጥርሳቸው እስከ አጥንቱ ዘልቆ ተሰማው። "አ.....አአአ!"አቃሰተ። አውቶማቲኩን መሣሪያ ጭንቅላታቸው ላይ መልሶ አፈ ሙዝን እበኪያስጠጋ የእጁን ሥጋ ቦተረፉት። የመሣሪያውን አፈሙዝ ከብዙ ትንቅንቅ በኋላ ጭንቅላታቸው ላይ አነጣጥሮ ምላጩን ሲስብ ራስ ቅላቸው ብትንትን አለ። ሄሊኮፍተሯ ርቃ ከተጓዘች በኋላ ተመልሳ መጥታ ደሴቷን እየተሸከረከረች አይናማ ድንጋዮችንና የወደዳቁ አስከሬኖችን ሳይቀር ጥይት አዘነበችባቸው። ሄሊኮፍተሯ ለአፍታ ደሴቷን ተሸክርክራ ዞራ እስክትመጣ ዲዎላ ከተሸጎጠባቸው ቋጥኞች ጠባብቅ ወጥቶ ከደሴቷ ጥግ መልህቁን ወደ ጣለውና ጠላቂው ኤክስካባተር- ዶዘር ወደ ተጫነበት መርከብ ሮጦ ገባ። ወዲያው ዲዎላ የገባበትን መርከብ ሄሊኮፍተሯ ደሴቱዋን ተሸክርክራ መጥታ በቦንብ አጋየቸው።

ሰኗ

ዳጋ እስጢፋኖስ ÷ ምድር ውስጥ

"አወክኝ አይደል ሚራ...አውቀኽኛል አይደል እንዴት ልትረሳኝ ትችላላህ? አወቀኝ የኔ ጌታ..... አወቀኝ አነጂ! ሲጻራ እኮ ነኝ።" እርቃኗን ተንሰፍስፋ አቀፈችው። በአባቷ ፊትና በአባቷ ረጅም ሽበቶ ጢም ፊቷ መሸፈኑን ረስታዋለች። ዕርቃን ገላዋን ከላይ እስከታች ሲያይ ቀፈፈው... ሚራኽ። ፊቷ ዘገነነው። ጢማም ሽማግሌ። ወንድ ያቀፈው መሰለው። ከወደ ደረቱ የሚጎሥሙት ጡቶቿን ሲመለከት ከትላልቅ ጡቶቿና በልጅነቱ ከሰጣት ባለጉጥ መስቀል ጋር ተፋጠጠ።

"ሚራ.... እወቀኝ አነጂ ! እኔ እኮ ነኝ! ...ሲጻራ እኮ ነኝ!.. እሺ እንድታስታውሰኝ .... ትዝ ይልህ እንደሆነ እንዲያውም... አንሶላዬን ቀድጄ ደብዳቤ ፅፌልህ ... አጠበው ብዬህ... እየዋኘህ መጥተህ ... መቃብሩ ቤት ውስጥ ...ስንሳሳም... መቃብር ቆፋሪዎች መጥተውብን...." ጨነቃት። በምን ታስረዳው? "ትዝ አይልህም እንዴ? ሚራ... እወድሀለሁ እኮ! እስከዛሬ ....አንተን ስፈልግ..." ዕንባዋ አነቃት። ባያውቃትስ?

ወዲያው ሲጻራ የታሰረችበት እሥር ቤት ተበርግዶ አንድ ሰው እየተደበደበ ገባ። ሲጻራ ተገፍትሮ ወደ ታሰረችበት የገባውን ሰው ዓይናማ ጀን ከሚራኽ ላይ ነቅላ አየችው ...ዲዎላ ነው።

ዲዎላ ከሁለት ሰዎች ጋር ተፋጣ ርቃኗን ወደ ቆመችው ሲጻራ እጁን ቀስሮ "እዎ! እ...እዎ ከእሷ ጋር ነኝ። አላልኂችሁም.... ከእሷ ጋር ነኝ!" አለ እያቃሰተ። ሰውነቱ በደም ተጨማልቋል። "ወደ ውስጥ ሰብሮ ሲገባ ተይዞ ነው! የእቃ ቤቱን ጠባቂ ገድሎ። በመጠበቂያው ቤት በኩል ወርዶ ሲጋባ ይዘነው ነው!" ዲዎላን እያዳፋ ከመጡት ሰዎች መሀል አንዱ ወደ አባ ገዞንበሩ ዞሮ። የእሥር ቤቱን የኋሊት ዘግተውት ተመለሱ ዲዎላን ያመጡት ሰዎች።

ዲዎላ ወለሉ ላይ እያለከለከ ኺ ብሎ ወደቀ። እነ ሞርሞርዲኖን ትንሽዋ ደሴት ላይ ደምስሶ ወደ መርከቡ ሮጦ ሲገባ ሄሊኮፍተሯ መርከቡን አጋይታው ነበር። ዲዎላ ግን መርከቧ እየተቀጣጣለች ባለችበት ቅፅበት በመርከቧ ሆድ ሥር ወደተቀመጠው ጠላቂ ኤክስካባተር -ዶዘር ገብቶ አስቀድሞ ሲያጠናው የከረመውን ጥበብ መጠቀም ጀመረ። ኤክስካባተር-ዶዘሩ ከመርከቧ ሆድጋር የታሰረባቸውን ወፋፍራም ሰንሰለቶች የሚታዘዙበትን ቁልፍ ሲጫን የመርከቧ ሆድ ተከፍቶ ኤክስካባተር-ዶዘሩ ወደ ሐይቁ ውስጥ ሲገባ

ሞተሩን አስነስቶ በሐይቁ ውስጥ ለውስጥ ሽመጠጠ። ሄሊኮፍተሯ መርከቡን ሙሉ በሙሉ በቦንብ አጋይታ ዲዎላ እንደተቃጠለ አስባ ስትሄድ ዲዎላ ወደ ዳጋ ደሴት ለመድረስ ስምንት መቶ ሜትር ያህል ቀርቶት ነበር። ጠላቂው ኤክስካባተር- ዶዘር ብረት ለበስ ሆኖ የጠላቂ መርከብ ቅርፅ ያለው ሲሆን በመሪው ዙሪያ ያሉት ቁልፎቹ ሲነካኩ መቆፈሪያው እንደ አንቴና ተመዞ ይወጣል። ጠልቆ መቆፈር እንዲችል፣ ቋጥኝ የመፈንቀል አቅም እንዲኖረውና ወደ ውስጥ ውሃ እንዳያስገባ ተደርጎ በብዙ ወጪ የተሰራ ነው።ይህንን ልዩ ኤክስካባተር-ዶዘር በሞርሞርዲኖ ልዩ ትእዛዝ የሠሩት መሐንዲሶች መከራው ከተሳካና ዲዎላ ማሸነፉን ከተለማመደው በኋላ እዛው በፓሌርሞ ወደብ አቅራቢያ ሜዲትራኒያን ባህር ውስጥ ሲገደሉ ከሶስቱ መሐንዲሶች ጭንቅላት ላይ ቃታውን የሳበው ራሱ ዲዎላ ነው።

ዲዎላ ጠላቂውን ኤክስካባተር- ዶዘር በዳጋ ደሴት ሰሜናዊ ዳርቻ ገባ ብሎ ሐይቁ ውስጥ ባሉ ቋጥኞች ጠባብቅ ሰጥሞ እንዲቀመጥ ሠልህቱን ከቋጥኞች ሥር ካያያዘው በኋላ በዋና ወጥቶ ወደ ደሴቱ ኮረብታ አመራ። የአረኖ አደባባይ ተብሎ በሚታወቀው የመጠበቂያ ቤት ገብቶ የወለሉን ቀያይ ምንጣፎች ገላልጦ ወደውስጥ ሲገባ የምድር ውስጡ የአደጋ ጊዜ መጥሪያ ማሽኖች መንጫጫት ጀመሩ። ወዲያው በታጠቁ ጋርዶች ተይዞ አሁን ወዳለበትና ከሲጳራ ጋር ወደ ተገናኘበት የምድር ውስጥ እሥር ቤት እየተደበደበ ተወረወረ። ሲጳራ "እወቀኝ!" እያለች በጥያቄ የምታጣድፈው ሰው ዲዎላ ወደ ገዳሙ ሲገባ በእንግዳ ቤት ውስጥ አብሮት ያደረው ሰው ነው። ዲዎላ እንኪን ከሲጳራ ደረት ላይ ያለውን መስቀል በደህና አገኘው እንጂ የሚጨቃጨቁት ነገር ግድ አይሰጠውም። እንደገና በተኛበት ቀና ብሎ ዕርቃኗን ከሚራዥ ጋር የምትሟገተውን ሲጳራን ትቶ ደረታን ተመለከተ። ደረታ ላይ ያለውን ባለጉጥ መስቀል። ራቅ ብለው ቆመው ሚራዥንና ሲጳራን በትንግርት የሚመለከቱት አባ ገሪንበሩን ትኩረት ሰጥቶ አላያቸውም። ዕረፍት ማድረግ አለበት። ትንሽ ዕረፍት አማረው። በረጅሙ ተነፈሰ- ቡትንጋለለበት።

"አወከኝ አይደል?" ሲጳራ የሚራዥን ዓይኖች በዓይኖቿ እየተማፀነች። ሚራዥ ሳያስበው ዕንባው ተናነቀው።

"ፎቶ ግራፍ ይዘሻል?" አላት።

"ፎ...ፎ...ፎቶ.....ግ..ግ... ግራፍ...ፎቶግራፍ..." አፏ ተሳሰረ፡ "አም ይዣለሁ። እ...እ.. ...እዚህ ግን አይደለም ከበሉቴ ውስጥ ነው። ሽንጣዬ እዛው ነው... ገዳሙ ውስጥ....."

"ሽንጣሽ እኔ ዘንድ ነው" አለ ዲዎላ። እንደተንጋለለ እያዳመጣቸው ነበር። "ከፈለግሽ አብረን ሂደን ማምጣት እንችላለን።"

ሆን ብሎ ነበር ሻንጣዋን የደበቀባት መረጃዋን ሁሉ የያዘውን ሻንጣ ሲደብቅ ለመያዥነት ብሎ ነው።

"እንሂድ!" አለ ሚራዥ። "ፎቶ ግራፍሽን እፈልገዋለሁ"

"ተነስ!" አለች ሲጳራ ወለሉ ላይ ወደ ተንጋለለው ዲዎላ አዘቅዝቃ።

"ሻንጣዬን ስጠኝ።"

"ግዴለም እሰጥሻለሁ።" ቀኝ እጁን ሰጣትና ተውተርትሮ ቆመ።

"የመጀመሪያውን ተልዕኮዬን ፈፅሜአለሁ። ትንሽዋን ደሴት አፅድቻታለሁ። ሞርሞርዲኖን እስከ ሰዎቹ ጨርሼ ወደ ገዛነም ልኬዋለሁ። ሚኒስትሩም ሁሉን ነገር አጥቶ ተመልሷል። አሁን ደሴቷ ብቻዋን ቀርታለች። ትልቁን ጀልባም ሚኒስትሩ አጋይቶታል። እኔን ያገኘ መስሎት። እኔ ግን አልሞትኩም ጠላቂውን ዶዘር በሐይቁ ውስጥ አያበረርኩ ወደዚህ መጣሁ።" አባ ገሪንበሩና ሚራዥ ዲዎላ የሚያወራው ተአምር መሰላቸው። ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቁት ነገር የለም። ከዳጋው የምድር ውስጡ ዬርቶጋዳ ዋሻ እየወጡ የፈፀመውን ጀብዱ ተረከላቸው። በጥይት የቆሰለውን ግራ እጁን በጨርቅ ግጥም አድርጎ ቢያሰረውም ደሙ ጨርቁን ዘልቆ እየተንጠባጠበ ነበር። ሚራዥ ሲጳራ አውልቃ የጣለችውን ልብስ መልሶ አልብሶ እያሰተካከለላትና አባትዋን አባ ፊንሐስን እያስመሰላት ዲዎላ የሚያወራውን ጀብዱ እያዳመጠ ነው።

ባደሴቷ ላይኛው ክፍል እንደወጡ ሲጳራ "ጣላቂውን ዶዘር ታዲያ የት አደረከው?" አለችው።

«ተከተሉኝ»አለ ዲዎላ። በውስጡ የሚፈልገውን አስኪያገኝ ወዳጅነት ፈጥሮ ኋላ አሳይቶ እንደ ሚነሳቸው እያምሰለሰለ።

ከደሴቱ ከረብታ ወርደው በሰሜኑ አቅጣጫ ሐይቁ ዳር እንደደረሱ "እኔ እጄን ውሃው ስለሚቆጠቁጠኝ መዋኘት አልችልም። ከፈለግሽ ውስጥ ለውስጥ ዋኝና እይው። እዛጋ አለለሽ" አላት አገጩን ዶዘሩን ወዳስቀመጠበት አቅጣጫ አሹሎ።

ሲጳራ ውስጥ ለውስጥ ጠልቃ ከዋኘች በኋላ ከቋጥኞች መሃል ተጣብቆ መልህቁ የታሰረውን ዶዘር ስታይ ተገረመች።

"እሺ አሁን ፎቶ ግራፌ ያለበት ሻንጣዬን ስጠኝ" አለችው ሲጳራ ከሐይቁ ውስጥ ጠላቂውን ዶዘር አይታ ከወጣች በኋላ።

"ከዛ በፊት እኔም አንድ ነገር አፈልጋለሁ" አለ ዲዎላ ወደ ገዳሙ በር እያመሩ እያለ።

"ምን?" አለችው ሲጳራ።

"መያዣ እንዲሆነኝ መስቀሉን ስጪኝ።"

"መ... መ... መስቀሉን ነው ያልከኝ?"

"አዎ። መስቀሉን።"

"እሱንማ አልሰጥህም::"

"እንግዲያውስ..... እኔም ሻንጣውን አልሰጥሽም::"

"ወደህ ትሰጠኛለህ!?" ሊጻራ የቆሰለ እጁን ወደ ጎላ ጎተተችው::

"አ.....አአአ!"

"ገና እጅህን እነቅለዋለሁ::"

"እየከዳሽኝ ነው?"

"አይደለም:: ፎቶዬን እፈልገዋለሁ::"

"እሺ ዋሻው ውስጥ ግቡ ሻንጣሽን እዛ አመጣልሻለሁ::"

"እንደምታመጣልኝ በምን አርግጠኛ አሆናለሁ?"

"መስቀሉን ይዘሽ አይደል እንዴ? ያንቺ ፎቶ ለእኔ ምን ይሠራኛል? አመጣልሻለሁ:: ግን እዛው ዋሻው ውስጥ::" ሚራዥና ሊጻራ ተያዩ::

"ተስማምተናል" አለችው ሊጻራ:: "ፍጠን!"

ሸፒ

ዴርቶጋዳ ፣ የቀዶ ጥገና ክፍል

ረጂም ሰዓታት የወሰደው የፊትዋ ቀዶ ጥገና ከተደረገላት በሁዋላ ለቀናት አልነቃችም ነበር:: አሁን ሙሉ በሙሉ አገግማ ተነስታ የምታየውን ማመን አቃታት:: ህልም መሰላት:: "ፊቴን ከየት አገኘሽው?" አለች ሊጻራ በቀዶ ጥገና ወደ ቀድሞው፣ ወደ ራሷ ፊት የተመለሰላት ፊቷን በመስታውት ቆማ እየተመለከተች:: "ወይኔ አምላኬ ፊቴን ወደ ድሮው መልሰህልኛልኮ::"

"ፎቶሽን የፈለኩት ለዚህ ነበር" አለ ዶ/ር ሚራዥ ጋወኑን እንደለበሰ ከጎሰዋ ቆሞ:: ሌሎች የዴርቶጋዳ ዶክተሮችም ረጅም ጊዜ የፈጀው ቀዶ ጥገና በመሣካቱ ተደስተው ሲያይዋት ቆይተው ነበር ወደ መሰብሰቢያ አዳራሽ ወጥተው የሄዱት:: በደስታ ሰክራ ሚራዥን ግጥም አርጋ ሳመችው::

"እሄውልሽ ቃሌን ጠብቄ ፎቶሽን መልሻለሁ:: ፎቶሽን አምጥቼ ሻንጣውን ሰጠኋቸው:: ከዛም የአባትሽን ፊት ከፊትሽ ላይ ገፈው የራስሽን ፊት ፎቶሽን እያዩ ሰሩልሽ:: አየሽ እኔ ፎቶሽን ባላመጣልሽ ኖሮ ጢማም ሆነሽ ትቀሪ ነበር ማለት ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን አንቺ በሰመመመን ውስጥ ስለነበርሽ አታውቂም::" ዲዎላ ውለታ እንደዋለላት ለመናገር ቃል አጠረው::

"በስንት ቀን ነበር ይህ ሁሉ የሆነው?"ሊጻራ በፍጥነት ጭንቀት ወረራት:: "ስ...ስ...ስ.. ስንት....."

"ከስድስት ቀናት በላይ ላይሆን ይቀራል?"

"ከስድስት ቀናት በላይ?! እስቲ ላፕቶፑን አቀብለኝ:: ሻንጣውን አምጣልኝ! ቶሎ በል! የፈጣሪ ያለህ! ዲዎላ ፍጠን!"

"ምንድን ነው?...ም...ምም...ምን ተፈጠረ?!" አለ ሚራዥ በድንጋጤዋ ተደናግጦ:: ዲዎላ ሻንጣዋ ውስጥ ያለውን ላፕቶፕ በፍጥነት አውጥቶ ሰጣት:: ላፕቶፑን ተጣድፋ ከፈተችው:: በቀዩ ምልክት ከኢንጂነሩ ጭንቅላት ውስጥ የተጠመደው ፈንጂ የሚፈነዳበትን ጊዜ የሚጠቁመው ሰዓት አመልካች እየቆጠረ ነው:: ፈንጁ ሊፈነዳ የቀሩት ሃምሳ ዘጠኝ ሴኮንዶች ብቻ መሆናቸውን ያመለክታል:: 00:59.....

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

የዶርቶጋዳን ወርሃዊ ጉባኤ ምክንያት በማድረግ በስብሰባ ላይ ያሉት የዶርቶጋዳ አባላት የኮሎኔል ፍስሐን ስሜት ቆንጥጦ የሚይዝ ንግግር በተመስጦ በማዳመጥ ላይ ናቸው። ማትያስ ማሞ ከስብሰባው አዳራሽ መሀል ጭንቅላቱን ከምሰሶው አስደግፎ ቆዝሞ ተቀምጦ ንግግሩን እያዳመጠ ነው። ኮ/ል ፍስሐ የኢትዮጵያን ሰነደቅ አላማ ባንድጃቸው ከፍ አድርገው ይዘው ያንገታቸው ጡንቻ እየተግተረተረ ይናገራሉ።«.....ይህች ሀገር.....እናት ሀገር ኢትዮጵያ የምንላት ለጥቂቶች አንጉዋች ለብዙዎቻችን ደግሞ የእንጀራ እናት ሆናለች። ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን መመለስ የሚቻለው በዶርቶጋዳ ነው። ዶርቶጋዳ ለጥቂቶች ብቻ የሚያደገድግ ድርጅት አይደለም። ለየትኛውም.....ሃይማኖት፣ ዘር፣ ጎሳ፣ የፖለቲካ ድርጅት...ጥበቃ ለማድረግ የተቋዋቁዋመ ድርጅት አይደለም። ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በአመለካከቱ ምክንያት በጠላትነት አይፈርጅም። የኢትዮጵያን ችግር ሳይንስ እንጂ ፕሮፖጋንዳ አይፈታውም። ዶርቶጋዳ ኢትዮጵያን በሳይንስ ወደ ቀደመ ክብሯ ይመልሳታል።» ጭብጨባው አስተጋባ። ማትያስ ማሞ ቆሞ አጨብጭቦ መልሶ ተቀመጠ። ጭንቅላቱን ለጉባኤው ሽብረቃ ብዙ ጌጣጌጦች ከተንጠለጠሉበት ምሰሶ አስደግፎ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"ኢንጂነሩ የት ነው!?" ሲጮራ አንባረቀች። 00:44....ከንፈሯ ተንቀጠቀጠባት። "ኢ.....ኢንጂነሩ የት ነው? ሳ...ሳሳ...ሳይንቲስቱ! ሻ...ሻ.... ሻጊዝ" ሁሉም ተደናግጠው ዝም አሏት።

"ሚራዥ! ኢንጂነሩ ዬት ነው? ለምን አትነግረኝም!....."

"የቱ ኢንጂነር?" አለ ሚራዥ ድምፁን ከፍ አርጎ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

«የኢትዮጵያን ችግር መፍታት የሚችሉት ኢትዮጵያውን ሳይንቲስቶች ናቸው። ነዳጅዋን ማውጣት፣ ዩራኒዬሟን ማበልፀግ፣ የህዋ ምርምር ቱቅዋሟን መመሥረት ያለባቸው የራስዋ ታማኝ ልጆች እንጂ ቅጥረኞችና ወሮበሎች አይደሉም። ዶርቶጋዳ ይሄን ማድረግ የሚያስችለው ደረጃ ላይ ደርሷል። ዶርቶጋዳ አያወራም ይሠራል እንጂ። ለዚህም ነው እስከዛሬ ድምጡን አጥፍቶ የሚሠራው.....» ድምጻቸው በጭብጨባው ተዋጠ።

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"ኢንጂነር ሻጊዝ። እዚህ ዋሻ ውስጥ .... የትኛው ክፍል ውስጥ ነው ያለው?" አለች ሲጮራ ከህክምና ክፍሉ እየወጣች ላፕቶፑ ላይ ያለው ሰዓት ይቆጥራል።..... 00:23

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ጭብጨባው ጋብ ሲል ንግግራቸውን ቀጠሉ። «አሰክ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ የገዢ መደቦች ጥቅም አስከባሪ ሰላዮች እንጂ መንግስታት በተቀያዬሩ ቁጥር የማይቀያዬር ቋሚ የደህንነት ተቅዋም የላትም። ለዚህም ነው ቋሚ ራዕይና ዘላቂ ሕልም አልባ ሀገር ሆና የመጣው ሁሉ ወደፈለገው የሚያሽከረክራት። ዶርቶጋዳ ከምስጢራዊ የሳይንስ ምርምር ተቋምነቱ በተጓዳኝ የኢትዮጵያ ጠበቃ በመሆንም ያገለግላል። ዶርቶጋዳ መንግስታት በተቀያዬሩ ቁጥር የማይቀያዬር ቋሚ የኢትዮጵያ የደህንነት ተቋም ነው። የኢትዮጵያ ዳግም ትንሣኤና ህዳሴ ምልክትም በ«ቶ» ቅርፅ የተሠራው ይህ ልዩ መስቀል ነው።.....»

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"የትነው እኮ ነው የምልህ? ምን ሆነሃል! "..... 00:05። "ኢንጂነር ሻጊዝ አይደለም" አለ ሚራዥ ቆዝሞ ቆይቶ። "እሱን የሚመስል ሰው በሰርጀሪ ስርተው ....."

"ምን?" ...

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

ማንንም የሚነሽጠውን የድርጅቱን መዝሙር አዝማች ለንግግራቸው ማጣፈጫ ድምጻቸውን ቀስ አርገው ሲጀምሩት ሁሉም ተቀበሉአቸው።.....

ማንም ሰው ላይመጣ እኛን ለመለወጥ
አናፈገፍግም አናቅማማም ለለውጥ።
ዶርቶጋዳ .... ዶርቶጋዳ.... ዶርቶጋዳ
እንነጠቃለን ከተጫነን ፍዳ።
ያቀረቀርክበት አንገት ያስደፋህ ቀን
ነግቷል ብለህ ተነስ ፍዳና ሰቀቀን።
.....

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

"...ሻጊዝ አሁንም እዛው ነው» አለ ሚራዥ ከወደላይ በኩል ከጆሮው ጥልቅ ያለውን ዝማሬ ላፍታ አዳምጦ። «በአንድ ምስጢራዊ የቴክኖሎጂ ምርምር ጣቢያ ውስጥ ታግቶ እየሰራ ነው።".....00:01.....

"ጭንቅላቱ ውስጥ..." ተናግራ ሳትጨርስ ዋሻው ውስጥ ከፍተኛ ፍንዳታ ተሰማ።

ዋሻውን ያናወጠውን ፍንዳታ ተከትሎ የእሳት ነበልባል በዋሻው ውስጥ መጥመልመል ጀመረ። በደርቶጋዳ ዋሻ ውስጥ የተተካከሱት ድምጽ አልባ ጀኔሬተሮች በእሳት ተያያዙ። የነዳጅ ጀሪካኖችና በርሜሎች የእሳቱን ላንቃ አስፋፉት።

ዋይታ.....ጩኸት። የላብራቶሪ ዕቃዎችና የኤሌክትሪክ ገመዶች ተንጣጡ። በዋሻው ውስጥ ያሉ ክፍሎች በሙሉ ወደ ነበልባልነት ተቀየሩ።

የማትያስ ጭንቅላት እንደ ፈነዳ ወዲያውኑ ተደግፎት የነበረው ምሰሶ ተደርምሶ ከጥጉ ያለው ነገር ሁሉ እሳት መትፋት ጀመረ። አንዱ አንዱን ሊያድን ሲተረማመስ ከ/ል ፍስሐ የተያያዘባቸውን ሰንደቅ አላማ እሳት እያጠፉ አባ ዝጉበሩን ለማዳን ሲጣደፉ የርሳቸው ልብስ በሙሉ በእሳት ተያይዞ ነበር። ወዲያው ከላይ የወደቀ መርግ ሲአዳፍናቸው መተንፈስ አቅቶአቸው ወደቁ። ሁሉም ተጣደፈ። እሳቱን የቀደመ ግን ማንም አልነበረም። ማንም ማንንም ማዳንም አልቻለም።

አባ ዝጉበሩ የሚይዙትን አጥተው ሲንቦጀቦጁ ዶ/ር ዣንጊዳ ከእሳቱ ውስጥ ነጥቆ ተሸክሟቸው ቁልቁል መሮጥ ጀመረ። በአደጋ ጊዜ መውጫው በር ሊደርስ አስር ሜትር ያህል ሲቀረው አባ ዝጉበሩን እንደተሸከመ በእሳቱ ተዋጠ። ፀጉሩ፣ ልብሱ ገላው ፣ሁሉ ተለበለበ። "ጣለኝና አምልጥ!" አሉት አባ ዝጉበሩ እያጣጣሩ። "አ....አምልጥ እባክህ ሌሎቹ እንዲድኑ ንገራቸው አምልጥ። ወደ .....እኔን ጣለኝ።"

ኢንጂነር ጌራ እና ሜሮዳ ወደ ህክምና ክፍሉ እየሮጡ ሊሄዱ እሳቱ ከኋላቸው በክፍተኛ ፍጥነት እየተከተላቸው ነበር። ኢንጂነር ጌራ የሜሮዳን እጅ ይዞ እየጎተተ ወደ ዲር 33 አስገባት። ከዛም ወደ ሐይቁ የሚያስገባውን ትልቅ በር ከፍቶ የዲር33ን ሞተር አስነሳ። ሜሮዳ እንደገና ተመልሳ የህክምና ክፍሉን በርግዳ ገብታ "ተከተሉኝ! ፍጠኑ!" አለቻቸው እነ ሚራዥን በጭንቀት። "ውጡ! ራሳቸውን አድኑ.....ሩጡ ! ሚራዥ !"

"ዣንጊዳ ወዴት ነው?" አለ ሚራዥ በሩጫ ሜሮዳን እየተከተለ "አባ ዝጉበሩስ?!"

"እሳቱ ደርሶባቸዋል። ዝም ብለህ ና ! ራስህን አድን።..."

"አልመጣም ጥያቸው አላመልጥም።" ሚራዥ እየተጥመለመለ ወደ ሚከተላቸው እሳት ሮጠ። ሲጓራ ተከትላው እጁን እየጎተተች ጌራ ሞተሯን ወደስነሳት ሰርጓጅ መርከብ ይዛው ለመግባት ተጣደፈች። "እኔ ደግሞ አንተን ጥየህ አልሄድም።"

"ነይ ነው ምልሽ!" አላት ዲምላ ሲጓራን። ከሚራዥ ላይ መንጭቆ ተሸክሞ ወደ ሰርጓጇ መርከብ አስገባት። "በአንገትሽ ያሰርሽውን መስቀል የዘነጋሽው ይመስላል። ወይ ስጭኝና እኔ ልያዝው ....."

ሚራዥ በእሳቱ ውስጥ ሰው ተሸክሞ የሚመጣ ሰው ሲያይ ተመልሶ ወደ እሳቱ ሮጠ። "ዣንጊዳ!" ዣንጊዳ ወደ ሚራዥ አባ ዝጉበሩን እንደተሸከመ ሲደርስ ሁሉ ነገሩ በእሳት ተያይዞ ነበር። "በሩን ዝጉት!" አለ ጌራ ። "ዝጉት!" ከኋላቸው ትልቁን በር ዘግተው ወደ ሰርጓጇ መርከብ ሲቃረቡ ዣንጊዳ አባ ዣንሩን እንደተሸከመ ወደቀ።

"እሳቱን አጥፉት። እሳቱን.... ኩቱን አውልቅለት።" ጌራ መርከቧን እያንቀሳቀሰ አንባረቀ። ዣንጊዳ እንደ ግንድ ተለብልቧል። ሰውነቱ በሙሉ በእሳት ተንጨቅጭቋል አባ ዝጉበሩ ለዘለአለሙ አሸልበዋል። ሁሉም በሃዘን ተኮራመቱ። ሚራዥ አባ ዝጉበሩን እያገላበጠ ተንሰቅስቆ አለቀሰ።

"እሳቱ በሩን ሳያልፍ ኑ ቶሎ ግቡ!" አለ ጌራ። "ቶሎ በሉ በሩ ተያይዟል ፍጠኑ።" ሚራዥ ዣንጊዳን ወደ ዲር33 ተሸክሞት ገባ።.....

ዲር33 እንደ ጠላቂ መርከብ ሆና የጣና ሐይቅን ውስጥ ለውስጥ እየሰነጠቀች ወደ ባህር ዳር አቅጣጫ ገሠገሠች። በዳጋ እስጢፋኖስ ደሴት ውስጥ ለዘመናት ሲገነባ የኖረው የምድር ውስጥ ሃምርምር ተቋም በቅጽበት እንደልነበረ ከሆነ በሁዋላ። ትልልቅ አለቶች እየተሰነጣጠቁ የጣናን ውሃ ወደ ዋሻው አስገቡት። እሳቱን ተከትሎ ውሃው የቀረውን ክፍተት ሞላው። ዋሻው በሁሉም አቅጣጫ ተዘጋጋ።.....

፳፬

ባህር ዳር፥ ግዮን ሆቴል

በዴር33ታ ልዩ ሰርጓጅ መርከብ ከዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ እሳት በጣና ሐይቅ ውስጥ ለውስጥ አምልጠው ሲወጡ መሸቶ ነበር። ትንሿን ጠላቂ መርከብ ከጣና ሐይቅ ትራንስፖርት ድርጅት ወደብ ዝቅ አርገው ሐይቁ ውስጥ መልህቋን ጥለው እንደ ወጡ ቀጥታ ወደ ግዮን ሆቴል ገቡ።

ዶ/ር ሚራዥ ከእንደ መድኃኒት ቤት ማስታገሻ ነገሮችን ገዝቶ የዶ/ር ዣንጊዳን ቁስል ካከመለት በኋላ ህመሙ ታግሶለታል።

በጣና ሐይቅ ዳርቻ ባለው ግዮን ሆቴል ሽር ብትን በሚሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ተሞልቷል። የሚበዙት ቻይናዎች ሲሆኑ በቻይንኛ ቋንቋ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይነጋገራሉ። ከሆቴሉ ፊት ለፊት ከተገተረው ዋርካ ሥርቻ ጋር የሐይቁን ማዕበል የሚያጋጨው ቀዝቃዛ ነፋስ የሆቴሉ አበባዎችን ያወዛውዛቸዋል። የማዕበሉንና የቀዝቃዛውን አየር ተፈጥሮአዊ ሙዚቃ እያዳመጡ በካምፋየሩ ዙሪያ የተሰበሰቡት ቱሪስቶች የተመቻቸው ይመስላሉ።ይሳሳቃሉ፤ ካምፋየሩን እየዞሩ ይጨፍራሉ። ባህር ዳር እንደዚህ የሚያመርባት ምሽት ላይ ነው።በጥቁሩ አስፋልት ላይ ብርሃናቸውን የሚረጩት የመንገድ ዳር አምፑሎች ጎዳናውን ሞልተው የሚጓዙትን የውባውብ ልጃገረዶችንና ጎረምሶችን ውበት ለማሳየት የተተከሉ ይመስል በስራቸው የሚተላለፉትን ሁሉ ወርቃማ ብርሃናቸውን ያፈሱባቸዋል። በዘምባባዎች ላይ እያፏጨ የሚነፍሰው ለስለስ ያለ አየር የዘምባባዎችን ቅርንጫፎች ሙዚቃ ያጫውታቸዋል፤ ያውረገርጋቸዋል፤ ያዘምራቸዋል፤ ያስደንሳቸዋል።

ባህር ዳር በምሽት ለአፍታ ሞቅ ትልና ምሽቱ ገፋ ሲል ወዲያው ታንቀላፋለች። ሁሉም ነገር ይዘጋጋል። ከባህል ሞፈራ ቤቶች የማሲንቆ ድምጾችና የባለገር ዘፈኖች ብቻ መስማት ይጀምራሉ። ምሽቱ ሲገፋ ባህር ዳር ውስጥ የማይተኙት ዘምባባዎች ብቻ ናቸው። የከተማዋ ጠባቂ መላእክት መስለው ቅርንጫፎቻቸውን እንደ ክንፍ ዘርግተው ያሸበሽባሉ።

እነ ሚራዥ ግን ይህን ሁሉ የባህር ዳር ውበት የሚያዩ ዓይኖች አልነበሩዋቸውም። ግዮን ሆቴል ውስጥ በተለከሰው ካምፋዩር አቅራቢያ ተቀምጠው ቆዝመዋል። የሚንቦገቦገው እሳት አልሞቃቸውም። የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየርም አልቀዘቀዛቸውም ። ሀዘን ረሻጅም ጥላውን ጥሎባቸዋል። ቃላት አይለዋወጡም።

ሚራዥ አንገቱን ደፍቶ መራቱን በዓይኑ ይቆረቁራል። ሲጓራ ጭንቅላቷን ከሚራዥ ትካሻ ላይ ጥላ ከጥጉ ተቀምጣለች። ሜሮዳና ኢንጂነር ጌራ ጥግ ለጥግ ቢቀመጡም የሜሮዳ አይን ግን የተተከለው ተደጋግፈው ከተቀመጡት ከሚራዥና ከሲጓራ ላይ ነው። ዶ/ር ዣንጊዳ የሚለበልበው ቁስሉ ትንሽ ቢታገስለትም ቡተፈጠረው ነገር የውስጡ ቁስል ብሶበታል። ዲዎላ ደግሞ ሲጓራ ካሰረችው ባለጉጥ መስቀል ላይ ዓይኖቹን እንደተከለ ነው። በጥይት የተመታውና በሞርሞርዲኖ ንክሻ የተተለተለው የእጁ ቁስል ይቆጠቁጠዋል።

ያዘዙት ራት መጥቶ ባንድነት ከተመገቡ በኋላ ሚራዥ ሲጓራ ያሰረችውን ባለጉጥ ግማደ መስቀል ሲያገላብጥ ቆይቶ በ«ቶ»ቀለበት ላይ ከሰፈሩት ቁጥሮች መካከል ባለፈው ያልፈታቸውን ቁጥሮች ተመለከታቸው። "$98_{123}9_{6}10_{67}40_{567}88_{123456}$" ቁጥሮቹ የ«ሰቆቃወ ኤጥሮስ» ግጥም ሚስጥሮች መሆናቸውን ቢያውቅም ግጥሙ የተፃፈበትና ባለፈው ምስጢሩን መፍታት የጀመረበት ብራና እስከጊታሩ በዳጋ ደሴት የምድር ውስጥ እሳት ጋይቷል።

"ጌራ?" አለ ዶ/ር ሚራዥ ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ። አባይ ማደ ገጣሚ ነኝ ብሎ ሰቆቃወ ኤጥሮስን በቃሉ እንዳነበነበለት ትውስ አለው ። "ያንን ግጥም እስኪ በልልኝ?" አለው።

"የቱን?" አለ ጌራ ከሰመጠበት የሀዘን እንቅልፍ ባኖ።

"ሰቆቃወ ኤጥሮስን።"

"አስታውሰዋለሁ ብለህ ነው? ያኔም እኮ በስንት ትግል ነበር የያዝኩት። አባ ዝጎንበሩ በመካራ ነበር ያስጠኑኝ።"

"እስቲ ግድ የለም ሞክር... "

" እስቲ ልሞክር. " ጉሮሮውን ጠራርጎ ሁለት ስንኞችን እንዳነበነበ ቀጥ አለ። ጠፋበት።

"አዩ፣ ምነው እመብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?

ምነው ቀኝሽን ረሳሻት? ውይ! መልጭ ብሎ ጠፍቶብኛል . . እ. . ."

"አይዞህ አስታውስ . . .. ሶስተኛውን ስንኝ እኔ ላግዝህ እሺ....."

"እስቲ እስቲ. . ."

"እስክ መቼ ድረስ እንዲህ መቀነትሽን ታጠብቂባት?"

"አዎ !.. እስክመቼ ድረስ እንዲህ መቀነትሽን ታጠብቂባት?"

ልቦናሽን ታዞሪባት?

ፊተናዋን ሰቀቀንዋን ጣርዋን ይበቃል ሳትያት?

አላንቺ እኮ ማንም የላት . . . " እያማጠ ስንኞቹን መደርደር ጀመረ። ከዛም ሚራዥ ስንኞቹንና ቃላቱን ከቁጥሮቹ ጋር ማዛመድ ጀመረ።

ዲዎላ ሁሉን ነገር ለመከታተል እየተንፋዋቀቀ ቀረበ።

«98_{123} . . . 98ኛዉ ስንኝ 1ኛው፣ 2ውኛና 3ኛው ቃላት። 98ኛው ስንኝ *'የግማደ መስቀሌ'* ጉጥ እታገስበት አላጣም' ይላል። ተፈላጊዎቹ ቃላትም የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ሲሆኑ እነሱም *'የግማደ መስቀሌን ጉጥ'* የሚሉት ናቸው።» ለብቻ ያዛቸው።

«9_6 . . . 9ኛው ስንኝ *'ሂትለራዊ እባጭ ጫንቃዋን እንደ ኮረብታ ተጭኗት'* የሚለው ሲሆን 6ኛው ቃልም 'ተጭኗት' የሚለው ነው። አይደል? ያዝልኝ።»

«10_{67} . . . .10ኛው ስንኝ *'ቀና ብላ እውነት እንዳታይ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት'* የሚለው ነው። 6ኛው ና 7ኛው ቃልም 'ቁልቁል ጠምዝዟት' በሚለው ሐረግ ውስጥ ያሉት ናቸው። አዎ ! 'ቁልቁል ጠምዝዟት' የሚለውንም ያዝልኝ።»

"40ኛው ስንኝ ምንድነው ነበር ያልከኝ? እስቲ . . ."

"40ኛው ስንኝ *' ውሉ የጋብ ቀፎ ማሰስ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ'* የሚለው ነው"

"እሺ! 40_{567} . .. 40ኛው ስንኝ ውሉ የንብ ቀፎ ማሰስ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ ' የሚለው ከሆነ ፣5ኛው ፣6ኛውና 7ኛው ቃላት" ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ በሚለው ሐረግ ውስጥ ያሉት ናቸው ማለት ነው። መልካም ! " አለ ሚራሻር። " ... ' ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ' የሚለውን ያዝልኝ ።"

"88_{123456} . . . 88ኛው ስንኝ ከ1 እስከ 6 ያሉት ቃላት ..ያ ማለት ሙሉ ስንኙ ማለት ነው። እስቲ 88ኛውን ስንኝ አስታውስ? " ቀና አለ ሚራሻር ወደ ጌራ ። በባለ ጉጡ መስቀል በ «ቶ» ቀለበት ውስጥ ከተፃፉት ቁጥሮች የመጨረሻው ቁጥር ላይ ሲደርስ የበለጠ ጓጉ። "ምንድን ነበር.. 88ኛው ስንኝ . . . እ... እ. . . "ጌራ ከንፈሮቹን ነክሶ 88ኛውን ስንኝ አማጠ።

"አይዞህ!" አለ ዲዎላ አብሮ እያማጠ። ሁሉን ነገር በንቃት ሲከታተል አይታ ሲጓራ ከት ብላ ሳቀች።

"ምን ያስቅሻል ? ...ያስቃል?" አለ ዲዎላ ወደ ሲጓራ ዞሮ። በብቸኛዋ አንዲት ዓይኑ ተኩሶ ቢገላት በወደደ። ልታጋልጠው አንዳይሆን። ልፋቱን አና እንዳትከትበት ሰጋ። በልብሶቹ ውስጥ አጁን ሰዶ ጭኑ ላይ በምላጭ ቁጥሮቹን እየፃፈ ነው። ዲዎላ ቁጥሮቹን ጭኑ ላይ ሲጽፍ የሚደማው የደመ ንጣቢ በልብሱ ላይ እንዳይዘልቅና እንዳያጋልጠው ፊርከክ ብሎ ተቀምጧል። የታቀፈች ዶሮ መስሎ።

"አዎ አስታወስኩት! ።" አለ ጌራ አይኖቹን ጨፍኖ ከንፈሮቹን ሲያንቀሳቅስ ከቆየ በኋላ ። "88ኛው ስንኝ... *' መራራ ክንፏን ገንጥለሽ ቀጠሮ ቃሏን ግደፊያት'* ነው የሚለው አዎ ።" ዶ/ር ሚራሻር እንባቱን አሰግጎ የጌራን ግንባር ግንባሩ አድርጎ ሳመው።

"ልክ ነህ! የኔ ባለ ብሩህ አእምሮ ! እምፂ" በስሜት ዲዎላም የጌራን ጆሮ ግንድ ግጥም አድርጎ ሳመው። ዶ/ር ሻንጊዳ ሀመሙን ረስቶ በዲዎላ ፈገግ አለ።

«በዚህ መሠረት የእነዚህ ቁጥሮች ትርጉም እንግዴህ ይህ መሆኑ ነው። 98_{123} 9_6 10_{67} 40_{567} 88_{123456} » የቁጥሮቹን ትክክለኛነት መስቀሉ ላይ መላልሶ ተመለከታቸው።

"የግማደ መስቀሌን ጉጥ ተጭኗት ቁልቁል ጠምዝዟት ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ መራራ ክንፏን ገንጥለሽ ቀጠሮ ቃሏን ግደፊያት ።" በቁሮቹ የተቀመጡትን ቃላት ገጣጥሞ ሲያነባቸው ሁሉም ተደነቀ። "አ...ሃ!" አለ ዲዎላ ተገርሞ።

ይህንን የመጨረሻ የተሰካካ ቃል ሲያገኙ ሌሊቱ ነግቶ ባህር ዳርም ከእንቅልፍዋ ነቅታ ነበር። ከሆቴሉ የሚወጡና የሚገቡ ሰዎችም እየበረከቱ መጡ።

በደራ ተራራዎች አናት በዓባይ ማዶ ምስራቃዊ የሰማይ ጥግ የወጣችው ወርቃማ ፀሐይ የጣናን ሐይቅ የቀለጠ አለት አስመስላዋለች።

እነ ሚራሻር ግን እስከ አሁን ከምስጢራዊውና በ«ቶ» ቅርጽ በተሠራው ባለ ጉጥ መስቀል ላይ እንዳፈጠጡ ናቸው።

"እነዚህ ቁጥሮች የያዟቸው ቃላት እንግዲህ መስቀሉን የምንከፍትበትን ቅደም ተከተል የሚገልጹ ናቸው ማለት ነው። አዎ። *'የግማደ መስቀሌን ጉጥ ተጭኗት ቁልቁል ጠምዝዟት ያበባ እንቡጥ ሲፈነዳ መራራ ክንፏን ገንጥለሽ ቀጠሮ ቃሏን ግደፊያት'* ነው የሚለው።" የመስቀሉን መስቀልያ ተመለከተው። ሁሉቱ ጫፎች ያበባ እንቡጥ ነው የሚመስሉት እውነትም። በስተቀኝ ያለው ጫፍ *'ቀጠሮ ቃል'* የሚል ሐረግ ተቀርፆበታል። በስተግራ ያለው ጫፍ ደግሞ *«መራራ ክንፍ»* የሚል ፅሑፍ አለበት። የመስቀሉን መገጣጠሚያዎች ሲመለከታቸውም ተከፋች መሆናቸውን አረጋገጠ። ምናልባት ውስጡ የሚሰበር ነገር ተቀምጦ እንዳይሆን በመስጋት በጥንቃቄ መስቀሉን ለመክፈት ትዕዛዙን ደጋግሞ አነበበው **"የግማደ መስቀሌን ጉጥ ተጭኗት ቁልቁል ጠምዝዟት ያበባ እንቡጥ ሲፈነዳ መራራ ክንፏን ገንጥለሽ ቀጠሮ ቃሏን ግደፊያት"** ትዕዛዙ በወንድና በሴት አንቀጽ የተፃፈ ለማሳሳቻነት እንጂ ቅደምተከተሉን እንደማያዛባው ትዕዛዙንም ጎደሎ እንደማያደርገው እምኖ መስቀሉን በጥንቃቄ ለመክፈት አራቱን ጉጦች ተጫናቸው። በትዕዛዙ መሠረት ጉጦቹን ከተጫነ በኋላ ቁልቁል ሲጠመዝዛቸው የአበባ እምቡጥ የመሰለውና በመስቀሉ ጫፍና ጫፍ ላይ ያለው ጉጥ እንደ እምቡጥ አበባ በቅጽበት ፈነዳ። ከዛም መራራ ክንፍ የሚለው ጽሁፍ የሰፈረበት ጫፍ ተገንጥሎ ወደቀ። ቀጥሎም ቀጠሮ ቃል የሚል

ጽሁፍ፡ የተቀረጸበትን ጫፍ አሽከርክሮ ሲፈታው መስቀሉ ብትንትን ብሎ ከውስጡ የተጠቀለለ ብራና ወረቀት ወጣ።

ሁሉም ከመስቀሉ ውስጥ የወጣውን ጥቅል ብራና እና በላዩ ላይ የሰፈሩትን ቁጥሮች በመደመም ተመለከቷቸው።

32_{12} 20_{4} 32_{3} 101_{3} 101_{5} 30_{23} 32_{6} 21_{3} 68_{8} 63_{6} 102_{2} 17_{2} 63_{1} 95_{3} 60_{7} 71_{45} 82_{2} [illegible] 98_{8}!

ዲዎላ ቁጥሮቹን በሙሉ ጭኑ ላይ በምላጩ ጥርሱን ነክሶ ፃፋቸው። ደሙ ልብሱን እያበሰበሰው ነው።

ቁጥሮቹን ወደቃል ለውጦ ምስጢሩን የግሉ ለማድረግ አንድ ነገር እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ያንን ነገር የት እንደሚያገኘውም አላጣውም። እስከ አሁን መጻሕፍት ቤቶች እንደሚከፈቱ እርግጠኛ ነው፤ ረፍዷል። ከመጻሐፍት ቤቶች ባንዱም «እሳት ወይ አበባ»ን እንደማያጣው እርግጠኛ ነው። ቁጥሮቹን በሙሉ መጻፉን ካረጋገጠ በኋላ ከተቀመጠበት አመድረፍ ብሎ ተነሳ። ከጭኑ የፈሰሰው ደም ከቆመበት መሬት ላይ ሲንጠባጠብ ሁሉም ደሙ ያረፈበት መሬት ላይ ሲያፈጡ ዲዎላ ወደ ሆቴሉ በር ተፈተለከ።

ደሙን እያዘራ በሩጫ ከአካባቢያቸው ሲርቅ "እንዴ ! ለውዬው የወር አበባ ማየት ጀመረ እንዴት?"ብሎ ጌራ ሲናገር ሁሉም ከት ብለው ሳቁ።

ዲዎላ አስፋልቱን ይዞ ወደ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አቅጣጫ ሲሮጥ ቆይቶ አንድ መንገድ ዳር አሮጌ መጻህፍት ዘርግቶ የሚሸጥ ወጣት ሲያይ ቆመ።

መጻሕፍቱ ላይ ዓይኑን ቢያንከባልልም "እሳት ወይ አበባ" የሚለውን መጽሐፍ ሊያየው አልቻለም።

"እሳት ወይ አበባ የሚለው መጽሐፍ አለህ?" ዲዎላ እያለከለከ ነበር።

"የለኝም" አለው ወጣቱ መጽሐፍ ሻጭ ።

"እንዴት አይኖርህም?"

"አሃ?"

"እሺ የት ነው ማግኘት የምችለው?"

"የትም አታገኘውም።"

"ሰውዬ! ....ደም እኮ እየፈሰሰህ ነው !" አለ መጽሐፍ ሻጩ የዲዎላን የሚንጠባጠብ ደም አስፋልቱ ላይ እየተመለከተ።

"ዝም ብለህ መጽሐፉን ስለማገኝበት መንገድ ንገረኝ"

"አየህ . . . መጽሐፉ የታተመው በ1966 ዓ.ም ነው። ከ1966 እስከ 1998 ስንት አመት ነው? 32። 32 አመታት። አዎ ከታተመ 32 አመቱ ነው። . . . የመጽሐፉ ደራሲ ዘንድሮ መሞቱን አልሰማህም? ያ . . . ማነው ? ማን ነበር? አዎ የናሳው ሳይንቲስት

ከሞተ ጥቂት ቆየት ብሎ ደግሞ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ሞተ። ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህቺ ሀገር ሁለት ታላላቅ ሰዎች አጣች።"

"እባክህ!" አለ ዲዎላ። "ዝም ብለህ መጽሐፉን የማገኝበትን መንገድ ንገረኝ።"

"ነገርኩህ እኮ! ሎሬቱ ሙቷል። መጽሐፉም ከታተመ 32 አመታት አልፎታል! የት ታገኘዋለህ?"

"በቃ አላገኘውም?"

"ማግኘትማ ታገኘዋለህ ግን በጣም በውድ ዋጋ!"

"ዋት?"

"ስንት ትገዛለህ?"

"መጽሐፉ አለህ እንዴ?"

"መጀመሪያ የጠየኩህን ንገረኝ ስንት ትገዛለህ?"

"በፈለከው ዋጋ!"

"መቶ ብር ትከፍላለህ?"

"ሁለት መቶ ብር አደርግልሃለሁ።"

"አይበቃም።"

"እሺ ሶስት መቶ!"

"እንካ!" አለ መጽሐፍ ሻጩ በድሮ ጋዜጣ የተለበደ አሮር መጽሐፍ ካስቀመጣቸው አሮጌ መፃሕፍት መሃል ጎርጉሮ አውጥቶ።

ዲዎላ መጽሐፉን ቶሎ ገልጦ "ሰቆቃወ ኤጥሮስ" የሚለውን ግጥም ፍለጋ ገፆቹን ማተረማመስ ጀመረ።

"ሰቆቃወ ኤጥሮስ የሚለው ግጥም አለበት?"

"አዎ! ምን ሰቆቃወ ኤጥሮስ ብቻ! የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ፣ እሳት አመድ ወለደ፣ አብረን ዝም እንበል፣ ደህና ዋይ እማማ፣ ቃል ቃተተ . . ."

"በቃ !በቃ! በቃ! አገኘሁት . . . "

"በል .... ሶስት መቶ ብሩን ወዲህ በል! እንግዲያውስ ፡፡ ."

"ያ መጽሐፍ ስለ ምንድን ነበር የሚያወራዉ?" አለ ዲዎላ ወደ አንድ አሮጌ መጽሐፍ ጣቶቹን ቀስሮ ።

መጽሐፍ ሻጩ ጎንበስ ብሎ መጽሐፉን አንስቶ ቀና ሲል ዲዎላ እሳት ወይ አበባ የሚለውን መጽሐፍ ይዞ ዋጋውን ሳይከፍል ሲፈተለክ ተመለከተው።

መጽሐፍ ሻጩ ዲዎላን በሩጫ እየተከተለ "መጽሐፌን! መጽሐፌን! ...መጽሐፌን! አስቁመው.... ሌባ ነው!..... ሌባ !ሌባ!ሌባ! .....ሶስት መቶ ብሬ! ....ያዘው ! ያዘው!.... ያዥው!... ሌባ!ሌባ!..." ቢልም ዲዎላን ማንም ሮጦ ሊይዘው የቻለ የለም። ከኋላው የሚከተሉት ሰዎች እየበረከቱ "ሌባ !ሌባ!"የሚለው ድምጽም እየበዛ መጣ። ከፊቱ ቆሞ ዲዎላን ለመያዝ ግን ማንም አልደፈረም።

አስፈሪ ገጽታውንና ግዙፍ አካሉን አይቶ ከፊቱ ዞር ማለት እንጂ ክንዱን ለመጨበጥ የከጀለ አንድም የለም።

መንገዶችን በየጉራንጉሩ እያሳበረ ከተሰወረ በኋላ ገበያ ውስጥ ገባ። ገበያው ውስጥ ልብስ ለመግዛት ተስማምቶ ልብሱን ከቀየረ በኋላ ደሞ ሾክክ ብሎ ገበያ ውስጥ ገብቶ አልም አለ። ልብሱን የሸጠለት ሰው "ተዘረፍኩ!" እያለ አሪታውን ሲያቀልጥ ገበያው ተተረማመሰ። ዲዎላ ግን ተረጋግቶ ከገበያው ወጣ።

ቨጎዳናው ላይ"ሌባ !ሌባ. . ." እያለ ሲከተለው የነበረው ህዝብ ገና "ሌባ !ሌባ!.." እያለ ጎዳናውን ሞልቶ ነበር። እሱም አብሮ ተቀላቅሎ ከሁዋላ "ሌባ! ሌባ! ሌባ! . . ." እያለ ከህዝቡ ጋር ጎዳናውን ካገባደደ በኋላ ከመናሃሪያ ጀርባ ባለ አንድ አሮጌ ሆቴል ውስጥ ኮራ ብሎ ገብቶ ተቀመጠ።

ዲዎላ "ስቆቃወ ጴጥሮስ" የሚለውን ግጥም ከመጽሐፉ ውስጥ ፈልጎ ካወጣ በኋላ ጭኑ ላይ በምላጭ የፃፋቸውን ቁጥሮች መፍታት ጀመረ። 'መፍጠን አለብኝ ሲል ራሱን መከረ። 'ለእኔስ ያለ እኔ ማን አለኝ !? 32_{12} $20_4$4 32_3 10_{13} 101_5 30_{23} 32_6 21_3 68_6 63_6 102_2 17_2 63_1 95_3 60_7 71_{45} 82_2 ۝۝۝ 98_5! "ለእኔስ ያለ እኔ ማን አለው!?" ቁጥሮቹን ከመጽሐፉ ጋር እያመሳከረ ፈገግ አለ ዲዎላ። ጥርስ አልባ ድዱን አሰጣው።

ዲዎላ ለብቻው የሚሆነውን አይታ ከጭኗ ላይ ትንሽ ልብስ ጣል ያደረገችው አስተናጋጅ ባግራሞት ስትመለከተው ከዲዎላ አንዲት አይን ጋር ተጋጨች።

በብቸኛ አንዲት አይኑ ጥብስ አድርጓት ፈገግ ሲል ከት ብላ ሳቀች። "በአንድ አይን ጠበሳ? ወይኔ ! ሰውዬው ያለጥርስ ነው እንዴ የተፈጠረው ?" ከጥጓ ላለችው አንሾካሾከች።

ዲዎላ ግን ዝም ብሎ ስራውን ቀጠለ። በቀላል ዘዴ ለመጨረስ ሲል ብቻ ከጭኑ ላይ እየደማ አዲስ የገዛውን ሱሪ እያወረዛበት ያለውን ደም እየጠነቆለ በግጥሙ ውስጥ ተፈላጊዎቹን ቃላት ቀባቸው ::

«32_{12}... 32ኛ ስንኝ አንደኛውና ሁለተኛው ቃላት»አለ ለራሱ።

"በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ " ከነዚህ ስንኞች ውስጥ "በወንዝ አፋፍ" የሚለውን ሐረግ ከሥሩ በደመ ቀባው።

20_4 ... 20ኛው ስንኝ 4ኛው ቃል . . .

"አዋጅ የምስራች ብዬ የትብት ምግቤን ገድፌ" ከዚህ ውስጥ *"የትብት"* የሚለውን ቀባው ::

32_3... ከ32ኛው ስንኝ *"ሐረግ "* የሚለውን 3ኛውን ቃል።

101_3 . . . 101ኛው ስንኝ 3ኛው ቃል።

"አስርጭብኝ የአምነት ቀንጃ፣ ለስጋቴ አጣማጅ አታ" ከዚህ ውስጥ *"ቀንጃ "* የሚለውን 3ኛውን ቃል።

101_5. . . ከ101ኛው ስንኝ *"አጣማጅ"* የሚለውን 5ኛውን ቃል እንደገና።

30_{23}. . . 30ኛው ስንኝ 2ኛውና 3ኛው ቃል። *"በገጠር የደመና ዳስ፣ በገደል ሸለቆ አዳራሽ"* ከዚህ ስንኝ *"የደመና ዳስ"* የሚለውን።

32_6 . . . ከ32ኛው ስንኝ *"ጢሎሽ "* የሚለውን 6ኛ ቃል።

21_3 . . . 21ኛው ስንኝ 3ኛው ቃል።

"ከናቴ ማህፀን *አልፌ*" ከሚለው ስንኝ "አልፌ" የሚለውን 3ኛ ቃል።

68_6 . . . 68ኛው ስንኝ 6ኛው ቃል።

"ምነው በረኝነት ዕድሜየ፣ ዓይኔን በንጎጣት የሎስ" ከሚለው ስንኝ "የሎስ" የሚለውን ቃል።

63_6. . .63ኛው ስንኝ 6ኛው ቃል።

'ለህንፃሽ መዲና ቆሞ፣ ለክብርሽ ድባብ ምሰሶ" ከዚህ ውስጥ "ምሰሶ " የሚለውን 6ኛውን ቃል።

102_2.... 102ኛው ስንኝ 2ኛው ቃል።

"ለጭንቀቴ -መቀነቻ" ከሚለው ስንኝ "መቀነቻ"

17_2. . . 17ኛው ስንኝ 2ኛው ቃል።

"እሸሸግበት *ጥግ* አጣሁ " ከሚለው *"ጥግ "* የሚለውን።

63_1. . . ከ63ኛው ስንኝ *"ለህንፃሽ "* የሚለውን 1ኛውን ቃል።

95_3. . . 95ኛው ስንኝ 3ኛው ቃል።

"ቃልሽ በህሊናዬ ዲብ፣ ኃይልሽ በህዋሴ ይረፃ።"

ከሚለው ስንኝ ላይ "ዲብ" የሚለውን 3ኛ ቃል።

"የመናኒው የአባ ተድላ ረድ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ " ከሚለው ስንኝ ላይ "ታድሞ" የሚለውን 7ኛ ቃል።

71_{45}. . 71 ኛው ስንኝ 4ኛውና 5ኛው ቃል።

"ፅናት ስጪኝ አንድካፊል የእናቴን የኢትዮጵያን ናፍቆ፣" ከሚለው ስንኝ *"የእናቴን የኢትዮጵያን "* የሚለውን።

82_2. . . 82ኛው ስንኝ 2ኛው ቃል።

"ሸር- ብር- ጉር እያለች።" ከዚህ ስንኝ ውስጥ *"ብር"* የሚለውን ቃል ሲያይ የልብ ምቱ ፈጠነ። ۝۝۝ . . . ይህን ቁጥር አልፎ የሚቀጥለውን ቁጥር ተመለከተ።

98_5...98ኛው ስንኝ 5ኛው ቃል።

"የግማደ መስቀሌን ጉጥ አታገሥበት አሳጣም" ከዚህ ስንኝ ውስጥ *"አሳጣም፣"* የሚለውን።

በየስንኞቹ ውስጥ በኮድ ቁጥር የተቀመጡትን ቃላት በደመ ቀብቶ ከጨረሰ በኋላ ሁሉንም በአንድ ትንፋሽ አነበባቸው። የተቀቡትን ብቻ።

"በወንዝ አፋፍ የትብት ሐረግ ቀንጃ አጣማጅ የደመና ዳስ ጢሎሽ መንጠልጠል አልፌ የሎስ ምሰሶ መቀነቻ ጥግ ለህንፃሽ ዲብ ታድሞ የእናቴን የኢትዮጵያን ብር ፀፀፀ አላጣም።" የሚል ካርታዊ ዐረፍተ ነገር መሠረተለት። ፎክሮ ተነሳ። ከዚህ ውስጥ የሚያውቀው አንድ ቦታ ብዙ ነገሮችን ገለጠለት። "የሎስ ምሰሶ" ተብሎ በድሮ ጊዜ የሚጠራውን ቦታ በልጅነቱ ያውቀዋል። ያኔ በባህር ዳር ከተማ ዳርቻ ባለ ቆሻሻ ቦታ ቆሻሻ ለቅሞ ሲያድግ።

ወደዛው ለመሔድ ወደ ሆቴሉ በር ሲራመድ አንድ ጥቁር መነጽር ያደረገ ሰው ወደ እሱ በፍጥነት እየተራመደ ሲመጣ አዬ። ሰውዬውን ያውቀዋል። በትንሿ ደሴት ላይ እነ ዶን ሞርሞርዲኖን ሲደመስስ ይህ ሰው ከሚኒስትሩ ጋር አምልጦ ወደ ሄሌኮፕተሯ የገባው ሰው ለመሆኑ እርግጠኛ ነው። የሚኒስትሩ ልዩ ጠባቂ መሆኑን ሲያረጋግጥ የልቡ ምት ሲፈጥን ተሰማው። ከሆቴሉ ወጥቶ ርምጃውን ወደ ሩጫ ቀይሮ ሲፈተለክ የሚኒስትሩ ልዩ ጠባቂም በሩጫ እየተምዘገዘገ ተከተለው። ሆቴሉን ለቆ ከዋናው አውራ ጎዳና እስኪደርስ ድረስ እየተከተለው ነበር።

ወደኋላ እየዞረ እያየ ዋናውን የአስፋልት መንገድ ይዞ እየሮጠ እያለ አንድ ሽምግል ያሉ ሰውዬ የታጨደ ርጥብ ሣር ጭነው ወደ ሚነዷት መኪና አፈጠጠ። ወደ መኪናዋ መስታወት ተጠግቶ ከጎን ከጎን ሲሮጥ ወደ ውስጥ እየተመለከተ ነበር። ውስጥ የግብርና መሣሪያዎች ተሸኮትኩተዋል። ማጭድ፣ መጥረቢያ፣ ደማ፣ አካፋ።

"እርዳታ እፈልጋለሁ! . . . እርዳታ!" አለ ዲዎላ እያለከለከ ጎታታዋን መኪና ከጎን እየተከተለ።

ሽማግሌው በሀዘኔታ ምንም ሳያንገራግሩ የጋቢናውን በር ከፈቱለት። በሩጫ ተንጠላጥሎ ጋቢናው ውስጥ እንደገባ "ምነው ? በደህና?" አሉት ሽማግሌው።

"ደህና ነኝ።..... ምን ደህንነት አለ?. . ." ወደ ኋላ ገልመጥ ብሎ አይቶ የመኪናውን መሪ ከእጃቸው መንጭቆ ያዘው። በቅጽበት የጋቢናውን በር ከፍቶ ሽማግሌውን ወደ ውጭ ገፍትሮ ሲወረውራቸው አስፋልቱ ላይ ተዘርረው መጮህ ጀመሩ።

ዲዎላ አሮጌዋን መኪና ከመጠን በላይ እያበረረ የባህር ዳርን ከተማ አቆራርጦ ከጨረሰ በኋላ ምሥራቃዊውን አቅጣጫ ይዞ ወደ ጢስ አባይ በረረ።

ሚራኾ ቁጥሩን ካወጣ በኋላ ባለ ጉጡን መስቀል እንደነበረ ገጣጥሞ መልሶ ለሲጳራ አስሮላታል።

32_{12} 20_{4} 32_{3} 101_{3} 101_{5} 30_{23} 32_{8} 21_{3} 68_{8} 63_{8} 102_{2} 17_{2} 63_{1} 95_{3} 60_{7} 71_{45} 82_{2} ፀፀፀ 98_{5} የሚለውንና ከባለ ጉጡ መስቀል ውስጥ የወጣውን ቁጥር ጌራ የሰቆቃው ጴጥሮስን ግጥም ስንኞች በቃሉ እያለለት ወደ ካርታ ለውጧቸዋል።

"በወንዝ አፋፍ የትብት ሐረግ ቀንጃ አጣማጅ የደመና ዳስ ጢሎሽ መንጠልጠል አልፌ የሎስ ምሰሶ መቀነቻ ጥግ ለህንፃሽ ዲብ ታድሞ የእናቴን የኢትዮጵያን ብር ፀፀፀ አላጣም" ወደ ሚል ካርታ ለውጦታል። ይህ መልእክት በብዙ ቢሊዮን ገንዘብ ተሞልቶ የሰጠመውን መርከብ ካርታ ለማግኘት የመጨረሻው ምዕራፍ ቢሆንም እነዚህ ቃላት የትኛውን ቦታ እንደሚገልጹ ሰለማያውቁ ሁሉም ግራ ገብቷቸው ተፋጠዋል።

"እነዚህ ቃላት ምናልባት ጎባራ ድልድይን የሚገልጹ ሳይሆን አይቀርም" አለ ጌራ።

«በዚህ ድልድይ ላይ ይመስለኛል ሰዎች በገመድ እየተንጠላጠሉ የሚሸጋገሩት»ሚራዠ የቃላዊ ካርታውን ፊደሎች ቦታውን ይጠቁሙት ይመስል በዓይኑ ተማፀናቸው።

"በወንዝ አፋፍ የትብት ሐረግ ቀንጃ አጣማጅ የደመና ዳስ ጢሎሽ መንጠልጣል አልፌ የሎስ ምሰሶ መቀነቻ ጥግ ለህንፃሽ ዲብ ታደሞ የእናቴን የኢትዮጵያን ብር ፀፀፀ አላጣም።" ጮክ ብሎ መላልሶ አነበባቸው።

"ሰባራ ድልድይ . . . የሎስ ምሰሶ... ይህን ነገር ሰምቸው አውቃለሁ ልበል?" ሲጳራ ጣቷን ከንፈሯ ላይ ጥላ አሰላሰለች።

"ሰባራ ድልድይን ታውቂያለሽ?"

"ሰባራ ድልድይ . . . ሰባራ ድልድይ . . . ሰባራ ድል . ." ሲጳራ በፍጥነት እያሰበች ወደ ሆቴሉ የመረጃ ክፍል ገሰገሰች።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ በራሪ ወረቀት ይዛ ተመለሰች። በራሪ ወረቀቱ ለባህር ዳር ዙሪያ ጎብኚዎች የተዛፈ መሆኑን ይገልፃል።ስለ ሰባራ ድልድይም አጠር ያለ ጽሑፍ ይዟል። ከሰባራው ድልድይ ፎቶ ግራፍ ጋር።

"ይኸውና ድልድዩ" አለች ወረቀቱን ይዛ እንደተመለሰች። ወረቀቱ ላይ ያለውን ጽሑፍ ድምጿን ከፍ አድርጋ አነበበችላቸው።

"ስለ ሰባራ ድልድይ በአባይ ወንዝ ላይ በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት የተሠራ ጥንታዊ ድልድይ ነው። ከባህር ዳር ከተማ ምስራቃዊ አቅጣጫን ይዞ በመጓዝ ይገኛል። በአምስቱ አመት የአርበኝነት ዘመን ጠላት በመሸጋገሪያነት እንዳይጠቀምበት አርበኞች ድልድዩን እንዳፈረሱትና ስያሜውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይነገራል። በአሁኑ ጊዜ ከወንዙ ግራና ቀኝ የሚኖረው ህዝብ ከነጓዙ በገመድ ላይ በመንጠላጠል ከድልድዩ አንድ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ ሲሸጋገር

ማየት የዘወትር አስገራሚ ትዕይነት ነው..." የሚለውን ጽሑፍ አንብባላቸው ስትጨርስ ቀና አለች።

"ታዲያ..... እንዴት ነው መሄድ የምንችለው?"ሚራኾ የኢንጂነር ጌራን አይኖች እየተመለከተ ጠየቀው።

"ዬር33ን መጠቀም እንችላለን" አለ ጌራ። "ጢስ አባይ ፏፏቴ ከባህር ዳር በስተምስራቅ 30 ኪሎ ሜትር ላይ ከጢስ አባይ ከተማ አጠገብ ነው የሚገኘው። ከባህር ዳር ጢስ አባይ ከተማ ለመድረስ የመኪና መንገድ አለ። ከከተማዋ ወደ ፏፏቴው ለመሄድ ከጢስ አባይ ከተማ 1.5 ኪሎ ሜትር ያህል በመኪና መንዝ ይቻላል። ....ከዚህ በታች ባለው የአባይ ሸለቆ ውስጥ ቁልቁል በመንዝ ነው ሰባራ ድልድይን የምናገኘው።.....ዬር33ን ባየር ላይ ስለምንጠቀም የአባይን ወንዝ ቁልቁል ስንከተል እናገኘዋለን ግዴለም።"

"እሞ..... አሁን ስለ ድልድዩ ያነበብኩት ትዝ አለኝ"አለች ሜሮዳ።

"እንዲያውም ሰባራ ድልድይ በአባይ ወንዝ ላይ የተሰራው የመጀሪያው ድልድይ እንደሆነ አንብቤያለሁ። በጥንተ ስሙ የሎስ ድልድይ በመባልም ይታወቃል።"

"በቃ እንንቀሳቀስ።"

ዬር33 መልህቋን ጥላ ወደተደበቀችበት ሲደርሱ የጣና ሐይቅ ፀጥ ረጭ ብሎ ነበር። ማዕበሉ ሰክኖ።

ኢንጂነር ጌራ ሞተሯን ካስነሳ በኋላ በሐይቁ ውስጥ ለውስጥ ነድቶ ወደ ላይኛው የሐይቁ ክፍል አወጣት። ከዛም ሁሌም እንደሚያደርገው መሪዋ ጥግ ያሉትን ቁልፎች ሲጫን ከሆዷ ውስጥ ሁለት ክንፎች ወጡ። በጣና ሐይቅ ላይ ክንፏን እንደዘረጋች ካክበኮባት በኋላ ወደ አየር አወጣት።

በአባይ ሸለቆ ውስጥ ዓባይን ቁልቁል እየተመለከቱ ወደ ጢስ አባይ ከተማ ጥምዝምዙን የአባይን ውሃ ጉዞ ተያያዙት።

ሰባራ ድልድይ፡ አባይ

ዲዎላ ከሰባራ ድልድይ ለመደረስ ብዙ ኪሎ ሜትሮች ሲቀሩት መኪና መንገድ ስላጣ በብስጭት ከርካሳዋን መኪና ከቋጥኝ ጋር አጋጭቷት ወርዶ ሽጥ ለሽጥ በሩጫ ይፈተለክ ጀመር- አቀበት ቁልቁለቱን። ምናልባት የሚቆፈር ነገር ይኖራል ብሎ በመገመቱ የሸማግሌውን ዶማና ማጭድ ይዞአል።

ሰባራ ድልድይ ላይ ሲደርስ ልቡ በአፉ ቱር ብላ እስክትወጣ ከመጠን በላይ በመሮጡ እያለከለከ ነበር። ከሰባራው ድልድይ ወዲህ ማዶ ቆሞ ወዲያኛው ማዶ ያለውን የድልድዩን ምሰሶ ተመለከተ። ይህ ምሰሶ ጥንት «የሎስ ምሰሶ»ተብሎ የሚታወቀው መሆኑን አልረሳውም።ድልድዩ የተያያዘው በቀጭን ገመድ ነው።ይህቺ ቀጭን ገመድ ነበረች ኢትዮጵያን አያይዛት የኖረች። በዚህች ገመድ ላይ ነበር ህይወት ስትውተረተር የኖረችው። በዚህች ቀጭን ገመድ ላይ እንዴት ተንጠላጥሎ ከወዲያኛው ማዶ እንደሚደርስ ግራ ገባው።

ሰባራው ድልድይ ጫፍ ላይ ቁሞ ቁልቁል ሲመለከት አዞረው። በሰፊው ሸለቆ ውስጥ የሚጥመለመለው የአባይ ወንዝ ጭንቅላቱን ይዞበት የሄደ ይመስል ተንገዳግዶ ወደ ኋላ ተመለሰ። ተንፏቆ ተቀመጠ - ስላዞረው።

ከማዶ ካለው የድልድዩ ምሰሶ ወገብ አካባቢ የ«ቶ» ቅርፁ መስቀልና ፬፬፬ የተቀረፀበትን ድንጋይ ከህንፃው ላይ ሲያይ ቅጭም ብሎ ተመለከተው። ገመዱን በጥርሱ ነክሶ ቢሆንም መሻገር እንዳለበት ወሰነ። በገመዱ ላይ መንጠላጠል ጀመረ።

በገመዱ እየተንጠላጠለ ቁልቁል የሚጥመለመለውን የአባይን ውሃ አዘቅዝቆ ሲያይ ሰውነቱ ተንዘፈዘፈበት። ገመዱ አምልጦት ቢወድቅ ከሥር ያገጠጡት ሹል ሹል የአባይ ቋጥኞች አናቱን ሲበጠርቁት በሀሳቡ ታየው። ትንፋሹን ዋጠ። ላብ ክብብቱና ከግንባሩ ጭርር ሲል በአባይ ሸለቆ አናት ካለችው ፀሐይ ይልቅ የውስጡ ትኩሳት ብሶ ነበር። ከወንዙ መሃል ላይ ወደ ቆመው የሎስ ምሰሶ በመከራ እየተንፏቀቀ ደረሰ። የመስቀሉን ምልክትና ፬፬፬ን እስካየበት ድንጋይ በምሶሰው ላይ እየተንሸራተተ ወረደ። ከድልድዩ ምሰሶ ህንፃ ድንጋዮች ላይ በዶማ መቆፈር ጀመረ። ጥብቁን የህንፃ ድንጋይ ለመቦርቦር ብዙ ደቂቃ ፈጀበት። ጠንካራ ክንዱ ከጥንታዊው ጠንካራ ህንፃ ጋር ሲፋለም ቆይቶ መስቀልና ፬፬፬ የተሳሰበት ድንጋይ ከሕንፃው ላይ ተፈንቅሎ ወደ ውሃ ተምዘግዝጎ ድንቡቅ አለ።

ድንጋዩ ወደተፈነቀለበት ሽንቁር እጁን ሲከት ትንሽ ቀይ የብረት ሳጥን ይዞ ወጣ ። ሳጥኗ ላይ "ዴርቶጋዳ" የሚል ጽሑፍ ተቀርጾበታል። "ዋው! ይሄ ነው ዲዎላ!" ብሎ በፉከራ ሲጮህ የአባይ ሽለቆ የባደል ማሚቶ መልሶ ፉከራውን አስተጋባለት። "ዘጠና አምስት በመቶ የምድራችን ሀብት አምስት በመቶ በሚሆኑ ሰዎች እጅ ብቻ ነው ያለው" አለ ዲዎላ ለራሱ። ከሰባራው ድልድይ ምሰሶ ላይ ሽቅብ ለመውጣት ትንሿን ሳጥን ይዞ እየተንፏቀቀ።

«እኔ ዲዎላ ደግሞ የበይ ተመልካች ሆኜ መሞት አልፈልግም። ሕይወት ትግል ናት። በትግሉ የሚሸነፉ ይበዘበዛሉ። እኔ ዲዎላ እስካሁን ተበዝባዥ ነበርኩ። አሁን ግን የብዝበዛ ዘመኔ አክትሟል። .....የሰጠመው መርከብ ካርታ በእጄ ነው። የሰጠመውን መርከብ ካወጣሁት በሁዋላ በመጀመሪያ...ጣሊያን ውስጥ ከዛም ፈረንሳይ...አሜሪካ...እንግሊዝ...ታላላቅ ኩባንያዎችን እገዛለሁ...ከዛም...ፈልሰስ ብየ" እየተንፏቀቀ ድልድዩ ላይ እንደወጣ ጭኑ ላይ በምላጭ የሸነሸነውን የመስቀሉን ካርታ ቁጥሮች ቁስል ተመለከተ። ጭኑ ላይ የፈሰሰው ደም ገግሯል።

«ብዙ ጊዜ!» አለ ትንሿን ሳጥን በእጁ ጠበቅ አደርጎ ይዞ እየተመለከተ። "አዎ..... ብዙ ጊዜ ፈጀሽብኝ። ይገባኛል አይደል?" ሳጥኗ ታናግረው ይመስል ይበልጥ ወደ አንዲት ዓይኑ አስጠግቶ ጠየቃት። «ይገባኛል። የሰጠመው መርከብና በውስጡ ያለው የትየለሌ ሀብት ለእኔ ይገባል። ለእኔ! ምንም ነገር በምደር ላይ ለሌለኝ።" ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ቀና ሲል ሚራዥ በገመዱ ላይ እየተንጠላጠለ ወደ እሱ እየገሠገሠ ተመለከተው።

"አታገኘውም!" አለ ዲዎላ በሹፈት እየሳቀ። "ይልቅ እንዳትከሰክስ። ተመለስ።" ድልድዩ ላይ ድንጋይ አንስቶ በገመዱ ላይ እየተንጠላጠለ ወደ እርሱ የሚገሰግሰው ሚራዥን ጭንቅላቱን ፈጠፈጠው። የሚራዥ ፊት በደም ተሸፈነ።ዲዎላ ሳጥኗን ከድልድዩ ጫፍ ላይ አስቀምጦ ሚራዥ የሚንጠላጠልበትን ገመድ በማጭዱ ቆረጠው። ሚራዥ ዲዎላ ከቆመበት የድልድዩ ጫፍ ሊደርስ ሲንጠራራ ገመዱ ተቆረጠ። «አአአአ.....» ብሎ እየተምዘገዘገ በተቆረጠው ገመድ ጫፍ ላይ ተንጠልጥሎ ውሃው ውስጥ ተደነቀ። የገመዱ ጫፍ ትንሿን ሳጥን ጠርጎ ከድልድዩ ላይ ሲያንሸራትታት ቁልቁል ወደ አባይ ወንዝ ተምዘግዝጋ ወደቀች። በውሃው ላይ እየተንሳፈፈች ቁልቁል ከውሃው ሞገድ ጋር ስትጓዝ በተቆረጠው ገመድ ላይ ተንጠልጥሎ ውሃው ውስጥ የተዘፈቀው ሚራዥ ገመዱን ለቆ በዋና ሳጥኗን መከተል ጀመረ። ዲዎላ በሰባራው ድልድይ ላይ ዘሎ ወደ ውሃው ተወርውሮ ገባ። ሚራዥንና ሳጥኗን በዋና ተከተላቸው። ሚራዥ እንደምንም በፍጥነት ዋኝቶ ሳጥኗን እንደ ጨበጠ የዲዎላ ፈርጣማ ክንድ

ከኋላው ጭንቅላቱን የሚያናጋ ምት አሳረፈበት። ዲዎላ ሚራዥን ውሃው ውስጥ ትንፋሹ እስኪቆም ደፈቀው። ውሃው በደም ቀላ። ሚራዥ የዲዎላን ጠንካራ ምቶች መቋቋም አልቻለም። ትንፋሽ አጥሮት እያቃሰተ ሳጥኗን ለቀቃት። ዲዎላ ሳጥኗን በእጁ እንዳስገባ ሚራዥን ውሃው ውስጥ ደፍቆ ያዘው።

ወዲያው ዲዎላ ከኋላው ከባድ ነጎድጓዳማ ድምፅ ያለው አቅል የሚያስት ምት ጭንቅላቱ ላይ ሲያርፍበት እንደምንም ተንገታግቶ ወደኋላ ዞሮ አየ። ሲጓራ ደጋግማ የሸጉጧን ምላጭ ሳበችው። ግምባሩ በጥይት ሲበረቃቀስ ደም በአፉና በአፍንጫው እኩል ቡልቅ አለ። የዛለ እጁ ሳጥኗን ሊይዝለት አልቻለም። ሳጥኗን ለቆ ውሃው ውስጥ ወደቀ። መናገር አልቻለም። አፉን እንደከፈተ ከአባይ ውሃ ጋር ቁልቁል ወረደ።

ሚራዥ ተንገዳግዶ ሳጥኗን እንደያዘ ከሚፈሰው ውሃ በተቃራኒ ሽቅብ እየዋኘ ወደ ሲጓራ ገሠገሠ። እሱዋም እየዋኘች ወደ ሚራዥ ፈጠነች። በውሃው የተኛው ፀጉሯን ከፊቷ ላይ ገልጦ ቡዝዝ ቅዝዝ ብሎ ተመለከታት። ፊቱ በደም እንደቀላ። አስዋም ፍዝዝ ብላ ተመለከተችው።ከንፈሮቿ እንደድሮውናቸው። የጎመራ የሮማን ፍሬ እንደመሰሉ ናቸው። ጎረሳቸው።

ሜሮዳ ከወንዙ ገንብ ዳር ከጌራ ጋር ቆማ ቁልቁል ሲጓራንና ሚራዥን ስታይ ውስጧ ተፈረካከሰ። ቅናትና ፍቅር። ሚራዥን የግሉዋ እንደምታደርገው አርግጠኛ ሆና ስትኖር ሲጓራ የምትባል መንፈስ በህይወት ትኖራለች ብላ አልገመተችም ነበር።

ጌራ ትክሻዋን መታ መታ አደረጋትና "ሚራዥ ለአንቺ አልተፈጠረም"አላት።

"እኔ ግን የተፈጠርኩት ለእሱ ነበር!" አለች ሜሮዳ።

"ትወጅዋለሽ አይደል ?" አላት ጌራ መልሶ።

"ምን ጥያቄ አለው!"

"እንግዲያውስ እሱ የሚወደውን እንዲያደርግ ተይው። ምናልባት ለአንቺ የተፈጠረ ሌላ ይኖራል። አየሽ ... የሰው ልጅ ትልቁ ፍላጎቱ መፈለጉን ማወቁ ነው። እንደምትፈልጊው ያውቃል። እንደምታስፈልጊውም እንዲሁ። እሱን ሆነሽ አስቢው እሰቲ...ዕድሜ ልኩን ሲፈልጋት ኑሮአል ሲጓራም ስትፈልገው ኖራለች።..."

"የምትለው ይገባኛል ጌራ። ..... እንዳልከው ውስጤን መመርመር ሳይኖርብኝ አይቀርም። ከዚህ በኋላ ግን ያለ ፍቅር መኖር አልችልም። ፍቅር አልባ ሰው እና ክንፍ የሌለው አሞራ አንድ ናቸው። ሁለቱም መብረሪያቸውን አጥተዋል። ታውቃለህ? እኔ ፍቅር እፈልጋለሁ። አበባ ቀጥፎ የሚሰጠኝ አበባ ቀጥፌ የምሰጠው ያስፈልገኛል። ፍቅርን ከቀንቀን ከዘመን ዘመን

ስጠብቅ....ጊዜየን ዕድሜየን ጨረስኩት። ግን....ግን ደሞ ....ፍቅር ጊዜ አይሰጥም። ያለ ፍቅር ከዚህ በኋላ አንድ ቀን እንኩዋ መዋል አልችልም። አበባ ቀጥፎ የሚሰጠኝ አበባ ቀጥፌ የምሰጠው ያስፈልገኛል" ዓይኗ ዕንባ አቀረረ።

ጌራ እየሮጠ ሂዶ ዓባይ ዳር ፈንድታ አሻግሮ ያያትን አበባ ቀጥፎ ተመለሰ።

"አበባ ቀጥፎ የሚሰጥሽ ተገኘ ማለት ነው" አለ ጌራ።

"ይኸው አበባሽን ተቀበይኝ።"

«እየቀለድክብኝ እንዳይሆን!» ፈገግ ብላ ተቀበለችው።

"አየህ . . . እኔ በቀላሉ የሚያዝን ልብና በቀላሉ የሚደሰት መንፈስ ያለኝ ሴት ነኝ። በቀላሉ መደሰት እችላለሁ።" እንባዋን ወደ ውስጧ አመቀችው። ፊቷ ላይ የወረዱትን የእንባ ዘለላዎቿን ሲያብስላት እቅፍ አደረገችው። «ምናልባት ለእኔ የተፈጠርከው አንተ እንደሆንክ ማን ያውቃል?» አለች በውስጧ።

"አመሰግናለሁ። ጌራ . . . እኔ ያለፍቅር መኖር አልችለም። ደግሞም በቀላሉ ማፍቀር የምችል ሴት ስለሆንኩኝ ፍቅሬን ወደ ዚህች ምስኪን ሀገሬ ማዞር እችላለሁ። ይህች ሀገር እንደኔ ሁሉም ተጠቅሞ የሚጥላት ናት። እሷን ማፍቀርና ቀሪ ህይወቴን ለእሷ መስጠት እችላለሁ። እንዲያውም ሀገር ሆኖ ስላላገኘኋት እሷን ሀገር ለማድረግ ፍቅሬን ወደእሰዋ ማዞር እችላለሁ። . . . አንተም . . ."

"እኔም ከጎንሽ ነኝ ሜሮዳ።" ጌራ ሳያስበው ጥብቅ አድርጎ አቀፋት።

ሚራዥና ሲጳራ ተያይዘው ከውሃው ሲውጡ ዶ/ር ጐንጊዳ ከቅርብ ከቆመችው ዩር33 ልዩ አውሮፕላን እያዘገመ ወጥቶ ተቃቅፈው የቆሙትን ጌራንና ሜሮዳን በፈገግታ ተመለከታቸው።

ሚራዥ የባለጉጡን መስቀል የታችኛውን ጫፍና የቀይዋን ሳጥን ቁልፍ ሲያነሳጽር ከቆየ በኋላ የመስቀሉን ጫፍ በቀይዋ ሳጥን ቀዳዳ ከትቶ ሲያሽከረክረው ሳጥኗ በቅጽበት ከተፈተች። ቀይዋ ሳጥን ውስጥ ፬፬፬ የሚል የገጽ ቁጥር የተፃፈበት ከታሳቁ መጽሐፍ ላይ የተገነጠለው ሰፊ የብራና ገጽ ተጣጥፎ ተቀምጧል። ስድስት ሜትር በአራት ሜትር የሆነውን የብራና ገጽ ታጋግዘዘው ሲዘርጉት በቀይ ቀለም የተሳለውንና የሰጠመው መርከብ ያለበትን ትክክለኛ የጣና ሐይቅ ከርሰ ምድር የሚያሳየውን ካርታ ሲያዩ ሁሉም በደስታ ፈነጠዙ ። የሰጠመው መርከብ ካርታ። ኢትዮጵያን የሚገነቡበት ካርታ።

ቀና ብሉ ሁሉንም ተመለከታቸው ።

"ዛሬ ሌሊት!" አለ ሚራዥ። "የሰጠመውን መርከብ እናወጣዋለን። በውስጡ ያለው ሀብትም . . ."

ጌራ ሀሳቡን ቀጠለለት። "የኢትዮጵያ ባቡር ሀዲዶች እንዲዘረጉ እናደርግበታለን። ሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቶች በባቡር ሀዲድ ይገናኛሉ። የኢትዮጵያ ተራሮች እየተቦረቦሩ በውስጣቸው እንደጥይት የሚወነጨፉ ባቡሮች ያልፉባቸዋል። ከተሞች ከከተሞች በባቡር መስመር ይገናኛሉ። በኢትዮጵያ ገጠሮችም ባቡሮች እየተወነጨፉ ያልፋሉ። .....ያኔ የኢትዮጵያ የሕዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ወንድማማችነት ወደ አንድነት ያመራል። ንግድ፣ ትምህርት፣ ነፃነት፣ ኢኮኖሚ፣ ሳይንስ፣..... ስልጣኔ ያብባል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉም ነገር ወደ መልካምነት ይቀየራል። ሳምንትና ከዚያ በላይ የሚጨርስው ጉዞ በደቂቃዎች ውስጥ ይጠናቀቃል። ባቡሮችና የባቡር ሀዲዶች ብዙ ነገሮቻችንን ያስተሳስሩታል። ኢትዮጵያን ከአዝጋሚነት ወደ ተራማጅነት በፍጥነት እንለውጣታለን።"

ሜሮዳ ፈገግ ብላ ወደ መሀላቸው ገባችና "ላፕቶፕሽን አንዴ ልታውሺኝ ትችያለሽ?" አለቻት ሲጳራን እጅዋን ይዛ። ሲጳራ ወደ አውሮፕላኗ እየሮጠች ሂዳ ላፕቶፕዋን ይዛ መጣችና ሰጠቻት።

ሜሮዳ አንደኛውን የፊት ጥርሷን ይዛ ስትጎትት ከጥርሷ በላይ የተደረበ ሌላ ጥርስ የሚመስል ነገር ወለቀ። ሁሉም ባግራሞት ተመለከቷት። ያወለቀችው ጥርሷን ከላፕቶፑ ጋር አገናኝችውና ቁልፎቹን ስትጫን የኢንጂነር ሻጊዝ ፎቶ ግራፍ ስክሪኑ ላይ ወጣ። ቀጥሎ የትልቅ ሀንፃ ፎቶ ተተካ። ከዛም በዘመናዊ መሳሪያዎች የተሞላ ሰፊ የምርምር ጣቢያ....በስራ የተጠመዱ ቢጫ መለዮ የለበሱ ሰዎች በቢጫ በርሜሎች የተሞሉ መተላለፊያዎች...አውቶማቲክ መሳሪያ የወደሩ ብረት ለበስ ሰዎች.....ሳይንቲስት ኢንጂነር ሻጊዝ እጅ። ስክሪኑ ላይ ሻጊዝን ሲያዩ ሁሉም አፋቸውን ከፍቶው ቀሩ።

"ይህ ...ጥርስ አያደለም ስውር ካሜራ ነው" አለች ሜሮዳ።

«እስከዛሬ ደረቅ ፈገግታ የምታሳይን ለዛ ነበር ለካ።» ሚራዥ ራሱን እየነቀነቀ ተመለከታት።

"ይህ የጥርስ ካሜራ ከኢንጂነር ሻጊዝ ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ ሶፍት ዌር የተገጠመለት ነው። እንደምታዩት በየደቂቃው ኢንጂነሩ የት እንዳለ የሚጠቁመ መረጃዎችን እየቀረጸ ይሰበስባል። ፍቅሬን ወደ ሀገሬ በማዞሬ ብቻ አሁን እነግራችኋለሁ። እስከ አሁን ተዋናይ ነበርኩ። ተውኔቱን በደንብ እንደተጫወትኩ ተስፋ አደርጋለሁ። ኢንጂነሩን ከሚከታተሉት የሲአይኤ ኤጀንቶች መካከል አንዷ ነበርኩ። ይህ ካሜራ ተተክሎልኝ አሁን ሳጠምድ ኑሬአለሁ። አሁን ግን ለሀገሬ አጠምደዋለሁ። በዚህ የጥርስ ካሜራ እየተመራን ኢንጂነር ሻጊዝን ማምጣት እንችላለን።" ጥርሷን ከላፕቶፑ ላይ ነቅላ መልሳ ከጥርሷ ላይ ሰካችው። ሁሉም እርስ በእርስ በትንግርት

ተያዩ። "አሁን ሙሉ ለሙሉ አብሬአችሁ ልሰራ ዝግጁ ነኝ። ምክንያቱም....." ጌራን ተመለከተችው። እሱም ፈገግ ብሎ በፍቅር ተመለከታት።

"እኔ ደግሞ አንድ የምስራች ልነገራችሁ" አለ ጌራ ሁሉንም በፈካ ፊት እየቃኘ። "ከወደቀብን የሀዘን ጥላ ጀርባ ሌላ ብርሃን እንዳለ ልነገራችሁ ተዘጋጅቻለሁ። ከኢትዮጵያ ተራራዎች በአንዱ ውስጥ ቁጥር ሁለት ዴርቶጋዳ አለ። ቁጥር ሁለት ዴርቶጋዳ እየጠበቀን ነው። በዚያም በእሳት ከወደመብን ከቁጥር አንዱ ዴርቶጋዳ ውስጥ ይሰሩ ከነበሩ ሳይንቲስቶች በቁጥር የሚልቁ ሳይንቲስቶች ሥራቸውን እየሰሩ ነው። ወደዚያው በዴር 33 እንሄዳለን።"

"አትቀልድ!" ሚራዥ ሀዘኑ እንደ ልብስ ወልቆ ሲወድቅ ተሰማው። ተስፋው መልሶ ሲያቆጠቁጥ ታወቀው።

"ወደ ቁጥር ሁለት ዴርቶጋዳ ምናልባትም በዚህ ምሽት ስትገቡ የምታረጋግጡት ስለሆነ ያኔ ታምኑኛላችሁ። ምናልባት ዛሬ ማታ። አያችሁ....ዴርቶጋዳ ማለት ‹አናቅማማም አናፈገፍግም› ማለት ነው። ‹We never hesitate› ማለት ነው። ‹አናፈገፍግም› ማለት ነው። እንዲያውም የመዝሙሩ ሁለት ስንኞች ትርጉሙን የያዙ ናቸው.....ልዘምርላችሁ....» አብረውት ባንድ ላይ እየዘመሩ ወደ ዴር33 ተከታትለው ገቡ።.....

ዴርቶጋዳ
ዴርቶጋዳ.....
ማንም ሰው ላይመጣ እኛን ለመለወጥ
አናፈገፍግም አናቅማማም ለለውጥ።
ዴርቶጋዳ
ዴርቶጋዳ.....
ያቀረቀርክበት አንገት ያስደፋህ ቀን
ነግቷል ብለህ ተነስ ፍዳና ሰቀቀን።.....

ዴር33 አውሮፕላን ወደ ጣና ሐይቅ ስትበር የዓባይ ዳር ባለ ረጃጅም ክንፍ አሞራዎችም በህብረት መስመር ሠርተው ወደ ጣና እየተምዘገዘጉ ተከተሉአቸው።

ወ...በነሱ ውስጥ የሞቱት በኛ ውስጥ ሀያዋን ናቸው።.....ወ

ነፃ አይታ

እነሆ አንድ ምትሀታዊ ብዕር ከዚህ ትውልድ ሲመዘዝ ካላየ ላይ አንቀላፍታ የቆየችው የስነ ፅሁፍ አድባር ከዱካኪ ነቃች። ይህን ስል ከዚህ በላይ የምልበት ቃል አጥቼ እንጂ ዴርቶጋዳ ከዚህም በላይ የሚባልለት ጉሩም ልብወለድ ነው። ስለዚህም ምትሀታዊ ብዕሩን ከመዘዘው ከይስማዕከ ይልቅ የፈራሁት አንባቢውን ነው። ምክንያቱም አንባቢው ይን ልብወለድ አንብቦ ሲጨርስ ለመጽሀፉ የማይመጥን የወረደ አስተያየት ሰጥተህል ብሎ እንዳያኮርፈኝ ሰግቼ ነው።

ቢሆንም ስለ ዴርቶጋዳ ዝም አልልም። ጤነኛ አንባቢ ይህን ረዥም ልብወለድ አንብቦ ሲጨርስ ዝም አይልም። ወይ ተነስቶ ይሸልላል ወይም ለኢትዮጵያ የስነ ጽሁፍ አማልክት የምሥጋና መስዋዕት ያቀርባል። በዚህ ዘመን ይህን የመሰለ ጥምን ቆራጭ ልብወለድ ያነበበ ልበ ንጹህ ሰው በሀሴት መፍነክነክ እመኑን ነው። ለምን ቢባል ዴርቶጋዳ ለዚህ ዘመን ትውልድ ለሚቀጥለውም የተበረከተ እፁብ ድንቅ ገጸ በረከት ነው።

ይህን ለማለት አፌን ያሞጠሞጥኩበትን ምክንያት መጽሀፉን አንብቦ አጣጥሞ የዘለቀ ሁሉ ይረዳልኛል። ስለ እውነት ተገድጀ እንጂ ለውዳሴ የሚፈጥን ልብ ኖሮኝም አይደለም። ይህን ልብወለድ ልዩ የሚያደርጉትን ብዙ ወርቃማ ባህርያት ለሰሉና እውነተኛ ለሆኑ ሃያስያን ትቼ አንዳንዶቹን ልጠቅስ። መሠረታዊዉ የዚህ ልብወለድ ስኬት እስካሁን ካነበብኳቸው የኢትዮጵያ ልብወለዶች በጭብጥ ልዩ ሆኖ መቅረቡ ነው። ከተነሳበት አቢይ ጭብጥ እስከ ንዑሳን ጭብጦቹ ስንወርድ እስካሁን ያልተነካን ድንግል ሃሣብ የያዘ ረቂቅ ሥራ ሆኖ እናገኘዋለን። ይዞት የተነሳውን ዓላማ በድል ተወጥቷል። ከገጸ ባህርያት ቀረፃ አንፃር ስናየው ደግሞ ፍንትው ብለው የሚታዩ፣ ነጥረው የተሳሉ፣ ከአእምሮ የማይጠፉ ሆነው እናገኛቸዋለን። እንኪንስ አበይት ገጸ ባህርያት ሆነው የተሳሉት(ያን ሁላችንም የምናውቀውን ሰውዬ ጨምሮ) ታይተው የሚጠፉት አስተኔ ገጸ ባህርያቱ እንኪ ተቀርጸውብን የሚቀሩ ናቸው። ሚራዥ፣ሻጊዝ፣ጌራ፣ጣንጊዳ፣ሲጳራ፣ሜሮዳ፣አባ ዣንበሩ፣አናንያ...አባ ዲዲሞስ... ሞርሞርዲኖ፣ዲዎላ.....ሁሉም ልዩ ሆነው ለምክንያት የተቀረጹ ናቸው። አንድም በዘኔ(ሥራ አጥ) ገፀ ባህርይ አታገኙም። ከዚህ ጋር ተያይዞ የዚህ ልብወለድ ግሩም ጥንካሬው የገፀ ባህርያቱ ዲያሎግ ነው። ወመሸመጥ የሚቆርጡና ታሪኩን ወደፊት የሚያስወነጭፉ ንግግሮችን ከእያንዳንዱ ገፀ ባህርይ አፍ እናዳምጣለን። በትምህርተ ጥቅስ እየጨለፍን ማስታወሻችን ላይ

የምናስቀምጣቸው ልባችን ላይ የምንጽፋቸው ፍልስፍናዎች ከአያንዳንዱ ገጽ ላይ አናጣም። ከምንጠላቸው እኩይ ገፀ ባህርያት እንኳ የምንለቅመው ብዙ ቃል ይገኛል።

ሌላው ይስማዕከን ልዩ የሚያደርገው ፈጣን የአፃፃፍ ቴክኒኩ ነው። ገጸ ባህርያቱ ጎርደን እየተጎነጩ ቁጭ ብለው ነገር የሚጎነጉኑ ሳይሆኑ በዚህ የአፃፃፍ ፍጥነቱ እንደ አለላ ስፌት እያሰባጠረ የሚሰድራቸው ጠንካራ ሴራሥቹ አንባቢን የሚያቁነጠንጡ ናቸው። በልዩ የሴራ አወቃቀር ጥበቡ የወዲያውን ከወዲህ እንደ ሽረሪት ድር ሸርቦ የአንባቢን አእምሮ ይፈትናል። ቆይቶ ደግሞ አራሱን አንባቢውን ሴራውን ይፈታ ዘንድ መረቡ ውስጥ ይዶለዋል። በእያንዳንዷ ሴራ ውስጥ የገባችው እያንዳንዷ ሰበዝ ያለ አንዳች ምክንያት አልተሰበዘችም።

ስለዚህም ይህን ልብወለድ የሚያነብ ሰው ወደሁዋላም ወደ ፊትም እየተንደረደረ ቋጠሮዎችን ሁሉ ለመፍታት ከገጸ ባህርያቱ ጋር ይወጣል ይወርዳል። ፈጠራ ይሏል ይሄ ነው! ምን ያህል እድለኞች ነን እናንተዬ!..... እነዚህ ሁሉ የጠቃቀስኳቸው መልካም ጎኖች የደራሲውንና የብዕሩን ምትሀተኛነት ብቻ አይደለም የሚያሳዩን። ይልቁንስ ዶርቶጋዳ ለነገም የሚሆን አንጥት የሚያርስ የፈጠራ ሥራ መሆኑን ነው።

ከነዚህ መሠረታዊ የልብወለዱ ባህርያት አለፍ ስንል የምናገኘው የደራሲውን ሳይንሳዊ የፈጠራ ክህሎት ነው። በዚህ ልብወለድ ውስጥ ከደራሲው ብሩህ አእምሮ የፈለቁት ሳይንሳዊ ግኝቶች በተጨባጭ ሊፈበረኩ፣ ሊደረጉ ሊከወኑ የሚችሉ ናቸው። በልዩ የአፃፃፍ ጥበቡ የፈጠረውን ሳይንሳዊ ጽንሰ ሀሳብ አንባቢን አስገድዶ ያሳምናል። ነገሬን ለመቋጨት ስጥር ሴላ ያላልኩት ሀሳብ እየተሰነቀረ እያስቸገረኝ ሳጠቃልለው.....ዶርቶጋዳ የሸፈተውን አንባቢ ልብ አማሎ ወደ ኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ የሚዶል ድንቅ ሥራ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ዶ/ር ዮፍታሄ ስዩም

ስለ መጽሐፉ ያለምትን አስተያየት ከዚህ በታች
በተጠቀሰው አድራሻ ቢልኩት ለደራሲው ይደርስልዎታል።

ይስማዕከ ወርቁ
ፖ.ሣ.ቁ 17486
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ